የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን
ተሐድሶ
ቅጽ አንድ

ሳታድግ ያረጀች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

ፀጋአብ በቀለ

Million Belete
Private Library
Please Read
and RETURN

ሚያዝያ ፳፻፮ ዓ.ም
ሐዋሳ

Copyright© 2014 Tsega-Ab Bekele
All right reserved

መጀመሪያ እትም ሚያዝያ ፪ሺ ዓ.ም

አዘጋጅና አሳታሚ
ፀጋአብ በቀለ

የአሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር መጽሐፉን በከፊልም ሆነ በሙሉ ማባዛትና ማሠራጨት በሕግ የተከለከለ ነው::

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከመጀመሪያው እትም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: የዘመን አቆጣጠርን በተመለከተ የእውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር (እ.ኤ.አ) በማለት እንዲሁም የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣር ደግሞ (ዓ.ም) በማለት ተለይተዋል::

ጥያቄ፣ አስተያየትም ሆነ ሒስ ካለዎት ጸሐፊውን በሚከተለው አድራሻ ሊያገኙ ይችላሉ

ፀጋአብ በቀለ
የመ.ሣ. ቁ 1077፣ሐዋሳ፣ ኢትዮጵያ
email; tehadeso2006@gmail.com

የሽፋን ጸዳዩን - ዘካርያስ ገርማ
ኦሽን ዲጂታል ስቱዲዮ - ሐዋሳ
0911945840/0916116674
email;dcawassa@gmail.com

የቀዳሚ ስንባቢያን ስሰተያየት

ብስለት ባለው ሁኔታ በተዘጋጀው በዚህ መጽሐፍ ወንድማችን ፀጋአብ በቀለ የእግዚአብሔርን ቃል፥ የታሪክን እውነታ፥ የሌሎች ሰዎችን ጥናቶችና ልምዶች፥ እንዲሁም ነባራዊ የሆኑ ዓለም አቀፋዊና አገራዊ ሁኔታዎችን በመዳሰስ እውነተኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊና መንፈሳዊ ተሐድሶ ምን እንደሚመስልና ለዚህም ተሐድሶ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለምንና እንዴት መነሣት እንዳለባት ያስተምራል። ይህም የተሐድሶ ደወል ከታሪክ እንድንማር፥ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን አንድነት ለመገንባትና ለመጠበቅ ሊያስከፍል የሚችለውን ዋጋ ሁሉ እንድንከፍል፥ የግል ሕይወታችንንና የቤተ ክርስቲያን አሠራሮቻችንን ንጹህና ቅዱስ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል እንድንፈትሽና እንድናጠራ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ላይ በመታነጽ ለአገራችን ሁለንተናዊ ዕድገት ተግተን እንድንሠራ፥ እንዲሁም በዓለም አቀፋዊው የወንጌል ተልእኮ ላይ ያለን ድርሻ የጎላ እንዲሆን ከፍተኛ የሆነ ድምጽ ያሰማል። እንግዲህ በዚህ መጽሐፍ ደራሲው እውነትን በድፍረት ይናገራል፤ በእግዚአብሔር ቃል የበላይነት፣ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ላይ የተመሠረተ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶን ይናፍቃል፤ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አንዲት እንደሆነችና በአገራችን የክርስቶስን ስም የሚጠሩ ሁሉ በአንድነት መኖርና ማገልገል እንዳለባቸው ያምናል፤ እንዲሁም ከራሳችን አልፈን ሌሎች አገሮችን አንድንጠቅም ራእይ ይሰጣል። መጽሐፉን የሚያነቡ ሁሉ የአመለካከትና የሕይወት ለውጥ እንደሚያገኙ፥ ራእያቸው እንደሚሰፋ፥ ስንዴውን ከእንክርዳድ መለየት የሚያስችል ዕውቀት እንደሚቀስሙ" በሕይወታቸው ክርስቶስን ለመምሰል እንደሚያድጉ እርግጠኛ ነኝ፤ ጸሎቴም ነው።

በቀለ ሻንቆ *(ፒ.ኤች.ዲ)*
የካምፓስ ክሩሰድ ፎር ክራይስት ዓለም አቀፍ ምክትል ፕሬዚዳንት - ዩ.ኤስ.ኤ

በብርቱ የተሐድሶ ናፍቆት የጋለ፤ በጠቃሚ ንባባት የደለበ፤ በአገራችን ስላሉት ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እንድናስብ የሚጎተጉተን፤ የተሐድሶ ጉዳና የሚጠቁም ወቅታዊ ጥሪ ነው። ስለ አገርና ስለ ቤተ ክርስቲያን ይገደኛል የሚል ሁሉ ሊያነበው ይጠበቅበታል። ለወንድማችን ፀጋአብ አሁንም ጸጋውን ይጨምርልን እያልሁ አመርቃለሁ።

ንጉሤ ቡልቻ

የኢትዮጵያ ቃለ እግዚአብሔር አንባቢያን ማኅበር ዋና ጸሐፊ

ይህ መጽሐፍ ያለፈውን ታሪክ ብቻ ሳይሆን በ21ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፊት የተደቀኑ እንቅፋቶችንና ዕድሎችን ለታሪክ አጥኚዎች፣ ለነገረ መለኮታውያን፣ ለፖለቲከኞች፣ ለአስተማሪዎች፣ ለተማሪዎች፣ ለሰባኪዎችና ለሕዝበ ክርስቲያኑ በቃሉ የተፈተነና በጠንካራ ጥናት የተረጋገጠ እውነት በገሃድ ያሳያል፤ ለለውጥና ለተሐድሶ በምክንያታዊነት በድፍረት ይሞግታል፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከክበባት መንፈሳዊ እርጅናና ሞት የመውጫው መንገድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶ ብቻ እንደሆነ አበክሮ ያስረዳል። በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሊነበብ የሚገባ ታላቅ የዘመኑ መጽሐፍ!

ተክለአብ ሽብሩ (ፒ.ኤች.ዲ)

አሜሪካ ተኔስኢ ስቴት ዩኒቨርሲቲ - ረ/ፕሮፌሰር

ወንጌላዊ ፀጋአብ በቀለ *"የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ"* በሚል ያዘጋጀው ይህ መጽሐፍ የተሐድሶን መጽሐፍ ቅዱሳዊነት ታሪካዊነት መሠረት በያዘ መልኩ የአገራችን ቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ ተሐድሶ በጉጉት በሚናፍቅ ልብ አቅርቦልናል። የተሐድሶ ያለህ! ብሎ ለሚጮህ ትውልድ በጊዜው የተወለደ ወቅታዊ መጽሐፍ ነው፤ ፀግሽን ጌታ ይባርከው።በዚህ ትውልድ ሊነበብ የተገባው መጽሐፍ ሆኖ አግኝቸዋለሁ።

ጎሣ እሼቱ

በኢትዮጵያ ወንጌላውያን ተማሪዎችና ምሩቃን ማህበር (ኢቫሱ)

የደቡብ ቢሮ አስተባባሪ

ይህ መጽሐፍ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ያለችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከታሪክ ስህተት እንድትማርና ያለችበትን ዘመንና ትውልድ ተረድታ ወደፊት መንቀሳቀስ ትችል ዘንድ የተጻፈ ነው። ድህረ ዘመናዊ በሆነ ትውልድ መካከል እግዚአብሔር ለቤቱ አገልግሎት እንዳስነሣቸው የሚያምኑ አገልጋዮች በሙሉ ይህን መጽሐፍ ቢያነቡ ብዙ ጥቅሞችን እንደሚያገኙ እምነቴ የጸና ነው።

ኢንጅነር ሉሉ ጫንዴ
የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ መምህር

ከ18 እስከ 25 ዕድሜ ያለው ቤተ ክርስቲያንንም ጨምሮ ማንኛውም ድርጅት ራሱን ካላደሰ ዘለቀታ እንደማይኖረው ምሁራኖች በአጽንኦት ይገልጻሉ። ወንድማችን መጽሐፉን ለንባብ ሲያበቃ የማንቂያ ደወልን በእጃችን ማስገባቱ ነው። የተሐድሶን ምንነት፣ ለምንነት፣ እንዴትነትና መቼነት በትክክል ያነበበ አስነባቢ መሆኑን በግሌ ተረድቼዋለሁ። *"አገር ሲያረጅ ጃርት ያፈራል"* እንዲሉት ያለጊዜው እርጅና ተጫጭኖን የተላበስነውን ማንነትና ያፈራነውን አላስፈላጊ መራራ ፍሬዎች አስወግደን እንድንታደስ ጥሪ አቅርቦልናል። እናንብበው፣ እናስነብበው፣ ያነጋግረን እንነጋገርበት።

መጋቢ ተስፋዬ ነንቆ
በደቡብ አፍሪካ ፍሪ ስቴት ዩኒቨርሲቲ
የነገረ መለኮት ፒኤችዲ ተማሪ

ጸሐፊው በእግዚአብሔር ቃል ላይ መሠረት በማድረግ በብዛታቸውም ሆነ በጥራታቸው እጅግ የላቁ መጻሕፍትን መዳሰሱና ማጣቀሱ፣ በስሜታዊነት ላይሆን በምክንያታዊነት ላይ ማውጠንጠኑ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ እንቅፋቶችን ፈልፍሎ በማውጣት ከቃሉ መፍትሔን ማመልከቱ፣ አስደናቂ ታሪካዊ ፍሰቱና እንዲሁም ሚዛናዊነቱ ይኼን መጽሐፍ ልዩ አድርጎታል።

ሰለሞን በርሔ ተድላ
የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ
የታሪክና የቅርስ አስተዳደር ትምህርት ክፍል መምህር

ማንም ለውጥ ናፋቂና ተሐድሶ ጩኸት በውስጡ የሚያስተጋባ ሁሉ ሊያነበው የሚገባ በብዙ ድካምና ጥንቃቄ የተዘጋጀ ድንቅ መጽሐፍ መሆኑን ባገኘሁት የማንበብ ዕድል ለመገንዘብ ችያለሁ። ያለምንም ማጋነን ሳይሰለች እስከ መጨረሻው ገጽ በታላቅ ጉጉት ሊነበብ የሚችል መሳጭና እያንዳንዱ ሰው ቆም ብሎ ርዕሰ ጉዳዩ የራሱ እንደሆነ እንዲገነዘብ የሚያግዝ ሞጋችና በጥናት የተደገፈ መጽሐፍ ነው። አንብቦ ለተጠቀመበት ሁሉ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያንና ብሎም ለአገሩ መሳኢ ዕጣ ፈንታ የራሱን በጎ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት የሚግዝ ነው።

ቄስ መሠረት መሻገሪያ
ሐዋሳ ታቦር መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን

የእግዚአብሔርን ቃል እኛ በፈለግነው መስቀያ ላይ ለማንጠልጠል የእውነት ማድበስበሻ እና ጭብጥ አሳቡን ማሳቻ መንገዶችን ስንፈልግ የመንፈስ ቅዱስን አሳብ ስንቃወም ተገኝተናል፤ ዕድሜ ጠገብ ውሸቶችን እንደ እውነት በመቁጠር የጽድቅ መንገድ አድርገናቸው እግዚአብሔር በልጁ ካዘጋጀልን ጽድቅ ክብር እንደጎደልን ይህ መጽሐፍ የማይካድ እውነት በገሃድ ይናገራል። የአገሬ ሕዝብ ጽድቅ እንደራበው ዘመኑን እንዳይጨርስ የተጻፈውን ይህን መጽሐፍ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ያንብብ።

ወንድም መኮንን ደጉ በላይ
የሻሸመኔ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ

ይህ መጽሐፍ ቤተ ክርስቲያን በታሪክና በዕድሜ ብዛት ሳይሆን በቅዱስ መንፈስና በቃሉ ምሪት፣ በፍቅርና በእምነት በሚታደርገው እርምጃ ለራሷ ታድሳ ሁለንተናዊ ተሐድሶ የምታመጣበትን መንገድ ያሳያል። በዕድሜያቸው ትንሽ ቢሆኑም እንኳ ለአገራቸው ሁለንተናዊ ለውጥና ለዓለም መልካም ተጽዕኖ ምክንያት እየሆኑ ያሉትን የድቡብ ኮሪያና የቻይና ቤተ ክርስቲያንን ሕያው ምሳሌነት በመጥቀስ ያስቀናናል።

ታደለ ጥላሁን
የሕግ አማካሪ

ኢትዮጵያ በርካታ አዳዲስ አስተሳሰቦችን በየወቅቱ ከተጋፈጡ አገራት አንዷ ነች። ከዚህ አንጻርም የዘርፉ ምሁራን ዘመን የተጠቀመባቸው ዕሳቤዎች ለማስተዋወቅ በአንድ በኩል ባሕል ወለዱን ኃይል በመፍራት አዝጋሚ የሆነ ተሰምዶአዊ የለውጥ ዘዴ አማራጭን በሌላ በኩል ደግሞ በየቦታው ፈጣን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች የሚፈነጥቁ ተምሳሌታዊ የለውጥ አብዮትን ሲሸሓት ይታያሉ። የኢትዮጵያ ታሪክ ግን ሁለቱም አማራጮች ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ ያልተሳኩ መሆናቸውን ፍንትው በማድረግ ያስረዳል። አዝጋሚነቱ ባሕላዊ ያለመለወጥን፤ አብዮታዊነቱ ደግሞ አሳስፈላጊ ውድ ዋጋዎችን አስከፍሎአታል። ኢትዮጵያ ያልተፈተሸ አገረ-ወለድ ባሕልም ሆነ ደም አፍሳሽ መዳረሻ የለሌው አሳተገሞራዊ ለውጥ አያስፈልጋትም፤ አያሻትም። ነገር ግን ከራስ ከውስጥ የሆነ ሁለንተናዊ ለውጥና ሽግግር በብዙ ያሻታል። የፀጋአብ በቀለ "ተሐድሶ"ም ለእንዲህ ዓይነቱ ለውጥና ሽግግር ግልጽ ደፋርና ተገቢ አቅጣጫ አመልካች ነው። ለዚህ ስኬቱም *"እንኳን ደስ አለህ"* ልለው እወዳለሁ።

ግርማ መሐመድ (ፒ.ኤች.ዲ)
በቤልጅየም የባሕል ፍልስፍና ረ/ፕሮፌሰርና የ*"Understanding Religion and Social Change in Ethiopia"* መጽሐፍ ደራሲ

መጽሐፉ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የትናንትና የዛሬ ገጽታዎችን በጥናትና በመረጃ አስቃኝቶን የክርስትና ልክት በሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት በመፈተሽ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ሕይወትና የሞት ጉዳይ መሆኑን ይተነትናል። ወንድማችን ችግሮቻችንን አክኮ ከማለፍ ይልቅ በድፍረት በማፍረጥ የተሐድሶን ምንነትና እንዴትነት በመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር በማመልከት ለተሐድሶ ናፋቂ ትውልድ አቅጣጫን አመልካች፣ ወሳኝና ወቅታዊ መማሪያ አቀብሎናል። አሮጌ ነገር የሰለቸውና ተሐድሶ የናፈቀው ሁሉ ሊያነበው የሚገባው ድንቅ መጽሐፍ።

ወቼ ቦሩ
በመካነ ኢየሱስ ሴሚናሪዮም የ2ኛ ዲግሪ የነገረ መለኮት ተማሪ

በአገራችን ለቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ የተከፈለ የደም ዋጋና ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ተሐድሶ መሠረቱ የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መሆኑን በመገንዘብ በመንፈሱ ታድሼ ለቤቱ ተሐድሶ ይበልጥ ራሴን መስጠት እንዳለብኝ በቃሉ የተፈተነ፣ በጥልቅ ጥናት የተከሸነና የማያወላዳ ገገር እውነት በርቶልኛል። የግድ መነበብ ያለበት መጽሐፍ!

መጋቢ በለጠ ሃጃሉ
የሀዋሳ ከተማ ዞን ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት ዋና ጸሐፊ

ይህ መጽሐፍ የአገራችንን ቤተ ክርስቲያን ለለውጥ የሚጋብዝና አሁን የሚታየውን የተሐድሶ ዕድል ባትጠቀም በሌሎች ዓለማት እንደተከሰተው ሁሉ አሁን ካለችበት የባሰ ክፉ አደጋ እንደሚጠብቃት ቃሉን መሠረት በማድረግ በግልጽ ያስጠነቅቃል። የተሐድሶ መማሪያ ለመሆን ራሳቸውን የሰጡ ሁሉ ሊያነቡት የሚገባ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የዘመናት ጓዳ ጎድጓዳ የፈተሸና በገሃድ ለሁሉም ያሳየ የዘመኑ ድንቅ መጽሐፍ እንደሆነ ከልብ አምናለሁ።

ያዕቆብ ዙላ
የሐዋሳ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መምህር

ባለራእይነት ክፍል አንድና ሁለት ካነበብኩ በኋላ ከፍተኛ ተጽዕኖ ፈጥሮብኝ ከመጻሕፍቱ ደራሲ ከሆነው ከወንጌላዊ ፀጋአብ በቀለ ጋር በአካል ባንተዋወቅም ልጽፍለት ተገደድኩኝ። ለሀትመት እየበቃ ያለውን *"የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ"* የሚል ቀጣዩን መጽሐፍ ለማንበብ በውስጤ የተፈጠረውን ብርቱ ረሃቤን ገለጽኩለት። ይህን መጽሐፍ መጀመሪያ ለማንበብ ከበቁት ጥቂት ሰዎች አንዱ በመሆኔ ትልቅ ደስታ ተሰምቶኛል። ይህ መጽሐፍ ክፍለ ዘመኑን የሚመጥን፣ በወሳኝ ጊዜ፣ ለወሳኝ ትውልድ የተደረሰ በዓይነቱ ልዩና አስደናቂ መጽሐፍ ነው። በግምት፣ በመላምትና በግላዊ ቁንጽል አመለካከት ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል፣ በጥልቅ ታሪካዊ ጥናትና ትንተና ላይ ተመርኩዞ እውነትን ሳያመቻምች ለአንባቢያን በድፍረት ይናገራል። ስታነቡት የለውጥና የተሐድሶ ራእይን ይዛችሁ ለተግባር እንዲትነሡ የግድ ይላል። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ይህን መጽሐፍ ማንበብ አለበት።

ቦሻ ቦንቤ
በአርባ ምንጭ መምህራን ትምህርት ኮሌጂ
የታሪክ መምህርና ተመራማሪ

እንደዚህ ዓይነት ድንቅ የሆነና በመረጃ የፋፋ መጽሐፍ ማግኘት ብዙ መጻሕፍትን እንደማገላበጥ ያህል ስለሚጠቅመን የማይታለፍ ድንቅ መጽሐፍ አግኝተናልና ሁላችን እንድናነበው ብቻ ሳይሆን እንድናጠናው እጋብዛለሁ።

ደረጀ ኃይሌ
የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሥነ ጽሑፍ (ፒ.ኤች.ዲ) 4ኛ ዓመት ተማሪ

ይህን መጽሐፍ በጥንቃቄ አንብብያለሁ። ቃሉንና ታሪካዊ መረጃን መሠረት በማድረግ በቀረበው ግልጽ የለውጥ ጥሪ ለልቤ ደርሷል፤ እንዲሁም ብዙ ተምረበታለሁ። እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ በቃሉ ታጥቀን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እርምጃን እንድንወስድ እጠራን እንደሆነ ተሰምቶኛል። መጽሐፉ በቃሉ ላይ እውነተኛ እምነት ላላቸው ድፍረትና ኃይል የሚሰጥ፣ የተሐድሶና የለውጥ ጠንካራ መሠረት ጣይና የቤተ ክርስቲያን ባለንጣን ምሽግ የሚያሳይ የመንፈሳዊ የጦርነት ካርታ ነው። በዘመኑ የለውጥና የተሐድሶ መሣሪያ እንዲሁም ለአገርና ለቤተ ክርስቲያን የበረከት ምክንያት ለመሆን ራሳቸውን ያዘጋጁ የዚህ ዘመን ታሪክ ሠሪዎች ሁሉ እንዲያነቡ እጋብዛለሁ።

ዘርሁን ገብረ
የመካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን
የክርስቲያን ትምህርትና የነገረ መለኮት ክፍል ተጠሪ

ዘታሰቢያነቱ

የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ጥያቄን እንደ እግዚአብሔር ቃል አንግበው በመነሣታቸው ሰማዕት ለሆኑት ለአባ እስጢፋኖስ፣ ለደቂቀ እስጢፋኖስ፣ ለአለቃ ታዬ እንዲሁም የእነርሱን ዱካ በመከተል ዛሬም እየተወገዙ፣ እየተሰደቡ፣ እየተሰደዱና የባሕርይ ገደላ እየተካሄደባቸውም እንደ አበው ቃሉ ላይ ቆመው ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መልካሙን የእምነት ገድል በመጋደል ላይ ላሉት የእምነት አርበኞች ሁሉ ይሁንልኝ።

ማውጫ

ምስጋና xiii
መቅድም (በአጩ ዶ/ር ደረጀ ኃይሉ) xiv
መግቢያ xvi

ክፍል አንድ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ታሪክ

፩ የቤተ ክርስቲያንና የተሐድሶ ምንነት 20

የቤተ ክርስቲያን ምንነት 20
የተሐድሶ ምንነት 22
የተሐድሶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት 24
ተሐድሶ የሚለውን ቃል በትክክል እንረዳ 25
ሦስቱ የተሐድሶ የእንግሊዝኛ ቃላት ፍቺዎች 26
የመነቃቃት ምንነት 29
የመነቃቃትና የተሐድሶ ልዩነት በንፅፅር 33
ተሐድሶ ጠሪ የኢትዮጵያ የቤተ ክርስቲያን ነባራዊ ሁኔታ 34
የተቀየጠ ክርስትናችን 36
አስማት በክርስትና ጥላ ሥር 38
የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን 43
ኢመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች 46
የተለጠጠ ነገረ ማርያም 46
"ያለ እመቤታችን ዓለም አይድንም" 48
"ያለ እመቤታችን ሥላሴ አይታወቅም" 48
"ሁሉም በእርሷ (በድንግል) ሆነ" 49
"የእመቤታችን ስም የሚጠራ አያፍርም" 49
"ቤዛዊት ዓለም ቤዛዊት ኩሉ" 49
ተአምረ-ማርያም የተዛባ የነገረ ማርያም መሠረት ነው 52
የመጽሐፍ ቅዱስ ምንነት 56
የአማርኛና የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ አጭር ታሪክ 56
ስደት የጠገበ መጽሐፍ 57
"ስማንያ አሐዱ- በቃሉ ሲመዘን" 59
"ገመና ዘቸ፟ይዱ" 59
የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት 64
አደጋዎች 64
ብሔርተኝነት የተስፋፋበት ካምፕ መምሰሉ 66
የነቀዘ የአሠራር ዋሻ 70

፪ ከሱተር የቀደሙ የተሐድሶ ጥያቄዎች በኢትዮጵያ 85

የዐፄ ያግበ ጽዮን ዘመን (1278 - 1286) 85
የደቂቀ እስጢፋኖስ ዘመን 87
የአባ እስጢፋኖስ በዐፄ ይስሐቅ ተቀባይነት ማግኘት 87
የአባ እስጢፋኖስ በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ችሎት ስለመወገዛቸው 88
የአባ እስጢፋኖስ ሰማዕት መሆን 93
የደቂቀ እስጢፋኖስ በጳጳስ ፊት 95
የደቂቀ እስጢፋኖስ የማሰቃያ/መግደያ/ መንገዶች 98
ከሰማዕት ደም የተወለዱ ሰማዕታት 101
ዘግናኙን ግድያ ያነበቡ ምን አሉ? 102

፫ የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ማንነት 104

የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ መልካም ሥራዎች 104
የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎች 105
በእርሱ ዘመን የተፈጠሩ የኑፋቄ ትምህርቶቹ? 106
ኢሰብዓዊ ድርጊቶቹ 108
ሚስቶቹና ቁባቶቹ 111
ለአባቶች ምክር ቦታ አልነበረውም 114
ዘርዓ ያዕቆብና ቤተ ክርስቲያን 115
ዘርዓ ያዕቆብና ማርያም 118
ሌሎች ስለ እርሱ ምን አሉ? 120
ሰይፍ ወደ ሰገባው ይመለስ 125

፬ "የቀዳሚ ምሁር" የተሐድሶ ሐሳብ 127

አለቃ ታዬ ገብረማርያም /1853 - 1916 ዓ.ም/ 127
"እኔ ለእምላክ እንጂ ለሥዕል አልሰግድም!" 131
የአለቃ ታዬ ሥራዎች 132
አለቃ ታዬ ለአገር የነበራቸው ታላቅ ራእይ 133
የአለቃ ታዬ ተቀባይነት ማጣት 134
የአለቃ ታዬ ዜና ዕረፍት 134
የአለቃ ታዬ እህት ሙሾ 137
የአለቃ ታዬ አጽም ለውግዘት? 139

፭ የዘመናችን የተሐድሶ እንቅስቃሴ 142

"የፕሮቴስታንት ቅጥረኞች" 142
"የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ልጆች ነን" 144
የአብያተ ክርስቲያናት አንድነትና ልዩነት 148

፮ ያልታደሰው ክርስትናችን የሐዲግታች ሞጋች 152

ክርስትናችን ራስ ተኮር መሆኑ 153
ክርስትና በስብከት ወይስ በኃይል? 154
የኦርቶዶክስ ክርስትና በካፋ 157

የኦርቶዶክስ ክርስትና በሲጳማ 158
ሐዋርያት መንፈልን ያሰራጩት በጡንቻ ይሆን? 162
የዐሜሞቹ ክርስትና 163
የቤተ ክርስቲያን ገዘምታ 170
ከክርስቶስ ምን እንማራለን 171
ከሰይፍ የተወለደ ሰይፍ 173
ነጻነት የተራበ ነጻ ሕዝብ 174
የመስቀል ጦረኞችና ኢየሩሳሌም 178
ሐዋርያት ስለ ክርስትና ገደሉ ወይስ ተገደሉ? 182
በእዋጅ "ቤተ ክርስቲያንን" ማሠራት? 183
ዛሬን በቅጡ ለማወቅ ትላንትን የመረዳት ግዴታ 186
የኢትዮጵያና የኤርትራ ጦርነት የልብ ጥንካሬ ያመጣብን ይሆን? 187
የጦርነቱ አስደንጋጪ ውጤት 188
ዛሬ በምድራችን እየዘራን ያለው እኩይ ዘር 189
በንስሐ ያልተወገደ የትናንቱ የበደል ስንኩፍ 194
መፍትሔ 196
ልባዊና እውነተኛ አገራዊ ንስሐ መግባት ይገባናል 195

ክፍል ሁለት
ዓለምን የሰመጠው የፕሮቴስታንት ተሐድሶ

፮ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ 200

የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ለምን አስፈለገ? 201
በጨለማው ዘመን የተፈለፈሉ የኑፋቄ ትምህርቶች 202
የተሐድሶ ንጋት ኮከቦች 202
ጆን ዊክልፍ (1328 – 1384) 202
ጆን ሑስ /1369 – 1415/ 205
የተሐድሶ መሪ ማርቲን ሉተር (1483 – 1546) 207
አባ ተድሮ ፖፒስኮ "የሩማኒያው ሉተር" 211
ተሐድሶ ከላይ ወደ ታች ወይም ከታች ወደ ላይ 224

፯ የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ሰምስቱ ምሰሶዎች 230

መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ "Sola Scriptura," or Scripture Alone 231
ድነት በጸጋ ብቻ"Sola Gratia," Salvation by Grace Alone 241
ድነት በእምነት ብቻ "Sola Fide," Salvation by Faith Alone 243
ድነት በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ "Solus Christus," In Christ Alone 246
ለእግዚአብሔር ክብር ብቻ"Soli Deo Gloria," For the Glory of God Alone. 248

፰ የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ትሩፋቶች 249

ተሐድሶ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ቃሉ ብርሃን መልሷታል 250
ተሐድሶ የጸጋ መንገድ ከፍቷል 253
ተሐድሶ ለዳኑት ሁሉ የአገልግሎት በር ከፍቶላቸዋል 254
ተሐድሶ መንግሥትንና ቤተ ክርስቲያንን አፋቷል 254
ተሐድሶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የቅድስናን ምንነትን ገልጧዋል 256
ተሐድሶ የላይንስና የምርምር በር ከፍቷል 256

ተሐድሶ ለዓለም ለውጥ ምክንያት ሆኗል 258
ተሐድሶ ሃይማኖትና እምነትን ለያይቷል 260
ተሐድሶ በዓለማችን የሥራን ባሕል ለውጧል 261

፲ ክርስትና የዓለም የሕዳሴና የዕድገት መሠረት ነው 265

ደቡብ ኮሪያ 265
የኢትዮጵያ አርበኞች የደም ዋጋ ለደቡብ ኮሪያ ነፃነት 265
የክርስትና ሚና ለደቡብ ኮሪያ ዕድገት 266
የደቡብ ኮሪያ ዲያስፖራና የሚሲዮናዊነት ራእይ 268
ክርስትና ለደቡብ ኮሪያ ማኅበረሰብ ለውጥ 269
ክርስትና ለደቡብ ኮሪያ ኢኮኖሚ ዕድገት 269
ደቡብ ኮሪያውያን ዛሬ በዓለም በምን ይታወቃሉ? 271
ለደቡብ ኮሪያ የጠቀመው ክርስትና ለኢትዮጵያ ለምን? 272
ክርስትና ለቻይና ኢኮኖሚ ምጥቀት 274
የቻይናውያን ዓለምን በወንጌል የመድረስ ራእይ 276
የቻይና ሁለንተናዊ ለውጥ በመስቀል 277
ከቻይና ክርስትና ምን እንማራለን? 278
ክርስትና ለምዕራቡ ዓለም ሁለንተናዊ ዕድገት 280

፲፩ የተሐድሶ ሞቴ በኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያናት 283

ጥንት ቤተ እምነት አልነበረም 285
ቤተ እምነት ምንድነው? 287
ቤተ እምነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም 288
ቤተ እምነትና ማዕከላዊነት 289
የእግዚአብሔር ሰዎች ስለ ቤተ እምነት ምን ብለዋል? 290
የኢትዮጵያ ቤተ እምነቶች ሁኔታ 292
የተሐድሶ አስፈላጊነት ለፕሮቴስታንቶች 293
ተሐድሶ የሚፈልጉ ዐበይት ጉዳዮች 295

፲፪ የቤተ ክርስቲያን ትርጅና፣ ሞትና ተሐድሶ 300

የደከሙ ኃያላን 303
በሞት ሂደት ላይ ያለች ቤተ ክርስቲያን ምልክቶች 303
ቤተ ክርስቲያን ከልደት እስከ ሞት 8 ደረጃዎች 305
የቤተ ክርስቲያን ሞት? 308
የቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ 310
በብዙ ዕድሎችና አደጋዎች ተከበናል 312
የዓለም ዓይን በአፍሪካ ላይ ነው 315

ማጠቃለያ 317
ዋቢ መጻሕፍት 322
የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች 333
መጠቀሚያ 337

ምስጋና

ከሁሉ በማስቀደም በልጅ ሞትና ትንሣኤ አድኖኝ የኪዳኑ ልጅ ያደረገኝን፣ ወንጌልን እንድሰብክ ጥሪው ስገርመኝ ብዕሬን ለስሙ ክብር እንዳነሣ የመጻፍ ሸክም ጊዜ፣ ትጋትና ትዕግሥት የሰጠኝ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

ወንጌልን ከመስበክና ከማስተማር የመኖር ዓላማዬ ጋር በልቤ እየተቀጣጠለ የመጣው የጽሑፍ ሥራ ሰፊ ጊዜን፣ ብርቱ ትጋትንና ጥንቃቄ እንደሚፈልግ የታወቀ ሲሆን ሁለቱን አብረ ማስኬድ እንድችል በጎኔ ብዙዎች ተሰልፈዋል። በተለይ ውድ ባለቤቴ ቲያ ዳቃና ከልብ የሚንወዳቸው ልጆቻችን ትሁት፣ ሩት፣ ሚናሴና ልዕልት ብዙ ጊዜዬን በተለያዩ ቦታዎች በአገልግሎት አሳልፌ ቤት ስመለስ እንኳ ትንሹን የእነርሱን ጊዜ በመቀማት ቀንና ሌሊት በኮምፕዩተር ላይ ተጥጄ ይህን መጽሐፍ ስጽፍ ፍቅርና ጥንቃቄያቸው ትልቅ ጉልበት ሆኖኛል። ከልብ አመሰግናቸዋለሁ። በዚህ መጽሐፍ ሥራ የተሳተፉ ለምችን ብዛት ሳስብ የሁሉንም ስም መጥቀስ አልችልም። በጸሎታችሁ፣ በምክራችሁና በገንዘባችሁ ለዚህ ዘመን ተሻጋሪ ሥራ ከእኔ ጋር የቆማችሁ፣ እንዲሁም ቀዳሚ መጽሐፎቼን በማንበብ በጽሑፍ እንድበረታ የሞራል ስንቅ ያቀበላችሁኝን ሁላችሁንም ከልብ አመሰግናለሁ።

የዚህን መጽሐፍ ረቂቅ በማንበብ፣ በማረምና ገንቢ አስተያየት በመስጠት ብዙ ያስተማሩኝን የታሪክ ፕሮፌሰር ላጵሶ ጌድሌቦ፣ አባቴ ዳቃ ጅሎ፣ እጩ ዶ/ር ደረጀ ኃይሌ፣ ኢንጅነር ሎሎ ጨንዴ፣ መምህር ሰሎሞን ቤርሔ፣ መምህር ኤፍሬም ጉሉፎ፣ መምህር አባይነህ ተናሽ፣ ቄስ መሠረት መሸሻ፣ ወንድም ዘርሁን ገብረ፣ መጋቢ በለጠ ሃይጃሎ፣ ወንጌላዊ ወቼ ቦሩ፣ ወንድም መኮንን ደጉ፣ የሕግ ባለሙያ ታደለ ጥላሁን፣ መምህር ቦሻ ቤንብ፣ መምህር ያዕቆብ ዘላ እንዲሁም ከባሕር ማዶ ጠቃሚ ምክር የለገሱኝ አብሮ አደግ ጓደኛዬ ረዳት ፕሮፌሰር ተክለአብ ሽብሩ፣ ረዳት ፕሮፌሰር ግርማ መሐመድና የሕይወት እርምጃዎቹ ለእኔ ትልቅ ትምህርት ቤት ለሆነኝ ዶክተር በቀለ ሻንቆ ከልብ አመሰግናችኋለሁ። በአገልግሎቴ የሁልጊዜ አጋገሮቼ የሆኑ መምህር ፍቅረሥላሴ ኃይሉና እህት ሹና አብዲን ከልብ አመሰግናለሁ። የመጽሐፎቼን ሽፋን ዲዛይን በማደረግ *"ባምሰል የግድ ልስበክ"* የሚለውና የሚከራበት የአዋሳ ኦሽን ዲጂታል ስቱዲዮ ባለቤት ዘካርያስ ግርማን አመሰግናለሁ። በመስተግዶአቸውና በሥራቸው ጥራት የሚያስመኩ የርኖቦት አታሚዎች ይህ መጽሐፍ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ለንባብ እንዲበቃ ትልቅ ሥራ ሠርተዋል፤ ልባዊ ምስጋናዬ ለሁሉም ሠራተኞች ይድረሳቸው።

መቅድም

ወንጌላዊ ፀጋአብ በቀለ በእግዚአብሔር ጸጋ የተሞላ፣ በመንፈስ የተቃጠለ፣ ለቤተ ክርስቲያንና ለአገር ዕድገትና ለውጥ ግብዓት ልሆን የሚችል እምቅ አቅም ያለው፣ በሚያስፈልገው ዕውቀትና ክህሎት የታጠቀ ዘመኑን የሚመጥን አገልጋይ ነው። እንደዚህ ዘመኑን የሚያውቁና ለመጪው ጊዜ ቤተ ክርስቲያንንና አገርን አቅጣጫ የሚያሳዩ አገልጋዮች እንደሚያስፈልጉን ሳይታለም የተፈታ ነው። ከሰው በላይ ትልቅ ስጦታ የለምና፣ እግዚአብሔር እያስነሣልን ስላለው ባለራእይ አገልጋዮች ልናመሰግነው ይገባል።

ወንድማችን በጻፋቸው *"ባለራእይነት ቁጥር 1 እና 2"* ምርጥ በአገራችን በብዙሃን እየተነበቡ ባሉ ድንቅ መጽሐፎቹ እጅግ በጣም እንደተባረክን ብዙዎች ይስማሙበታል ብዬ አስባለው። መጽሐፎቹ ልጆቹ እንደሆኑ ሁሉ ቁርጥ አባታቸውን ይመስላሉ። ለትምህርታችን ይሆን ዘንድ የሕይወቱን አቅጣጫ አመልካች ራእዩን በመጽሐፎቹ ላይ አስፍሮልናል። ይህም ስለራእይ ቀመራዊ ዕውቀት አቀባይ ብቻ ሳይሆን የተግባር ሰውነቱን ያመለክታል። ቀደምት ሥራዎቹ ከራእይና ከባለራእይነት ጋር በተያያዘ ውስብስብ የአገራችንን ታሪካዊ ዳራ በሚዛናዊነትና በድፍረት ፈልፍሎ፣ ገለባውን ከፍሬው በመለየት ለዛሬው ችግሮቻችን መፍተኼ ጠቋምና ለነገ የላቀ ራእይ እንዲኖረን አጋዥ መሣሪያዎች ናቸው። ሥራዎቹ የበለሉና ብዙ አመት የተደከመባቸው እንደሆኑ በሚገባ ያስታውቃሉ። በአጠቃላይ ድንቅ የሕይወት ጭማቂዎች፣ ተግባራዊ የራእይና የባለራእነት ትምህርት ቤቶች፣ አንዱ አንበበን የሚናስቀምጣቸው ሳይሆኑ ሁሌም የሚንጠቀምባቸው መመሪያዎች ስለሆኑ ደግመን ደጋግመን እናጥናቸው፤ የቀጣዩም ትውልድ ሀብት ናቸው።

ወንድማችን ፀጋአብ *"የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ቅጽ-1"* በሚለው በዚህ በሦስተኛው ድንቅ መጽሐፉም ርዕሰ ጉዳዩ አገራዊም አለም አቀፋዊም ነው። በዚህ ሥራው የቤተ ክርስቲያን፣ የተሐድሶና የመነቃቃት ምንነት፣ ባለፉት ስምንት ምዕተ ዓመታት የተሐድሶ ጥያቄና የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ምላሽ፣ በአገራችን የተስፋፋው ጫፍ የነካ የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ፍርሃት ሁኔታ፣ ለቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ አሉታዊ ምላሻችን በአገር ዕድገት ላይ ያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶን የፈቀዱ አብያተ ክርስቲያናት ለአገራቸው ዕድገት የተጫወቱት አንጸባራቂ ሚናና የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ጥቅም የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት በማድረግ በመረጃና ጥልቅ ጥናት በማያወላዳ ሁኔታ አቅርቦልናል።

ተሐድሶ ልንፈራው ሳይሆን፣ ልንጠማውና ልንራበው የሚገባ ጉዳይ እንደሆነ በምክንያታዊነት እየሞገተ ያስተምራል። ከሞተ ነገር በቀር ፍጥረት ሁሉ ለውጥ ወይም ተሐድሶ ያስፈልገዋል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶን በመግፋቷ ምን ያህል እራሷንና አገርን ወደኋላ እንዳስቀረች በዚህ መጽሐፍ ላይ በሚገባ በመረጃ ተደግፎ ተተንትኖዋል። ጆሮ ያለው ይስማ!

ይህ መጽሐፍ ከጠባብነትና ከኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘመን ዘለቅ መረዳቶቻችንና ልምምዶቻችን ጋር አጋጭቶን ያፋታናል፤ ሁላችን ለቃሉ ተገቢውን ሥፍራ በመስጠት ለአገር አቀፍ ሕዳሴ መሠረት ለሆነው የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ እንድንነሣ የግድ ይለናል። ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ይሟገታል። ከሁሉም በላይ የአገራችን ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ እንደቀረበ፣ ማንም እንደማያስቀረው የቤቱ አዳሽ እግዚአብሔር እራሱ እንደሆነና የእኛ ድርሻ ከእርሱ ጋር በእምነት ለመሥራት መነሣት እንደሆነ በመዘርዘር መለከታዊ ጥሪ ለአንባቢያን ያቀርባል። ለዚህ ትልቅ አላማ በምድራችን አበ እምነቶች ታላቅ የደም ዋጋ እንደ ከፍሉና እኛም የተሐድሶን መከር ለመሰብሰብ ማንኛውንም ዋጋ ለመክፈል በቃሉና በመንፈሱ ታጥቀን እንድንነሣ ይመክረናል፣ እንቅፋት ለመሆን እንደ ለመድነው ከተነሣን ሳናወቅ ከእግዚአብሔር ጋር እንዳንታገል ያስጠነቅቀናል።

ጸሐፊው *"የቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ያለህ!"* እያለ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ይጮሃል፣ አብራችሁ ከኔም ጋር ትጮሁና ለተሐድሶ በሁሉም አቅጣጫ ትሰለፉ ዘንድ ይችን ድንቅ መጽሐፍ እንድታጠኑና ለምድራችንም ሁለንተናዊና እውነተኛ ለውጥ በትጋት እንድትጸልዩ፣ እንድትሠሩና ካስፈለገም እንድትሞቱላት በታላቅ ትህትና እጠይቃለው። እግዚአብሔር ምድራችንን ይባርክ።

ደረጀ ኃይሌ
የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ መምህር
የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሥነ ጽሑፍ ተመራማሪና
የአራተኛ ዓመት (Ph.D) ተማሪ

ስንደ መግቢያ

የሰውን የአካል አፈጣጠር ስናጠን ከማሕፀን እስከ መቃብር ያለው ሂደት በለውጥ(ተሐድሶ) የታጀበ ሆኖ እናገኘዋለን። ለምሳሌ፦ *የሰው የሆድ ግርግዳ በየሳምንቱ ይታደሳል፤ በአያንዳንዱ ደቂቃ ከ200 እስከ 300 ግራም ገደማ አክሰጅን ያስፈልገዋል፤ አንዲሁም የተቃጠለ ለየር(ካርቦን አክሳይድ) ከሰውነቱ ይወገዳል፤ በየደቂቃው ከ160 ሚሊዮን በላይ ቀይ የደም ሰሎች በሰውነታችን ውስጥ ይፈጠራሉ፤ የዚያሀኑ ያህልም ይሞታሉ፤ አንደ ብረት ጠንካራ የሆነ የሰው ልጅ አጥንት የራሱ ደም ሥርና ነርቭ ያለው ሲሆን ራሱን በራሱ አንዲያድስ ተደርጎ ነው የተፈጠረው፤ የአዋቂ ሰው አጥንት በየዓመቱ ከ10 በመቶ ያህል ራሱን ይተካል።*[86] ይህ ታላቅና ድንቅ አሠራር የክርስቶስ የእጁ ሥራ ውጤት ነው። ለለውነታችን ይህን ድንቅ የተሐድሶ መንገድ የፈጠረው ጌታ አካሉ የሆነች ቤተ ክርስቲያንን እንደሚያድሳት ቃሉን መሠረት ያደረገ እውነት በዚህ መጽሐፍ ቀርቧል። ብሔር፤ ሃይማኖት፤ የትምህርት ደረጃ፤ የፖለቲካ ርዕዮተዓለምና የዕድሜ ልዩነት ሳይገድባቸው ኢትዮጵያውያን ሁሉ ይህን መጽሐፍ ቢያነቡ በብዙ እንደሚጠቀሙ እርግጠኛ ነኝ።

- በአገራችን በተለይ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ እንደ ጦር የሚፈራውንና በአፍራሽነት የተፈረጀውን "ተሐድሶ" የሚለውን ቃል፤ ጽንሰ ሐሳቡን ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር በትክክል ለመረዳት፤ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ዘንድ አቅጣጫ አመልካች የጊዜው መልዕክት ስለያዘች፤ ቤተ ክርስቲያን በዚህች አገር ታሪክ የተጫወተችውን አዎንታዊና አሉታዊ ሚና ለይቶ ለመረዳት፤

- በአውሮፓ ከተነሣው የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ጥያቄ ቀድሞ በኢትዮጵያ የተነሣው ተመሳሳይ የተሐድሶ ጥያቄ በአሰቃቂ ግድያ ለጊዜው ቢዳፈንም፤ ዛሬም የተሐድሶ ጥያቄው ክጫፍ እስከ ጫፍ መቀጣጠሉን ለመረዳት፤

- የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ለዓለማችን ሁለንተናዊ ዕድገት መሠረት ስለመሆኑ በመረጃ የተደገፈ በታሪክ የተረጋገጠ እውነት ስለሚያቀብለን፤

- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ የኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ሕዳሴ መሠረት ስለሆነ፤ ተሐድሶ የግድ መሆኑን ስለሚናገር፤

- ትውልድ ዘለቅ አሉታዊ ንዝረቶችንና ዛሬም እያሰቃዩን ያሉ ታሪካዊ የበደል እርሾን በአንድነት በንስሐ ለማስወገድ፤

የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ባለቤትና የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ እርሱ ቤቱን የሚያድሰው በቃሉ፤ በመንፈሱና በሚታዘዙለት ልጆቹ ነው። ማርቲን ሉተር ኪንግ *"ሰውጥ አይቀሬ በሆነው ሽክርክር ላይ ሳይሆን ቀጣይነት ባለው ትግል የሚገኝ ነው"* እንዳሉት የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆንም ብርቱ መሰጠትና በቃሉ

[86] *Dr Carl Stork (Dr), Reader Digest- September 2013*

ቆሞ እውነት መሳይ ሐሰትን በብርቱ መጋፈጥን ይጠይቃል። የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ጥያቄ በአገራችን ላለፉት ስምንት ምዕተ ዓመታት የቀደሙ የእምነት አባቶቻችን ብዙ የእንባና የደም ዋጋ አስከፍሏል። ዛሬም የአባቶችን ፈለግ በመከተል በእግዚአብሔር ቃል ላይ ቆመው ቤተ ክርስቲያናችን መታደስ አለባት እያሉ ያሉትንም ውድ ዋጋ እየጠየቀ ነው። ታሪክ ስላለፈው ጊዜ መረጃ ላይ ተደግፎ መረጃውን እርስ በርሱ በማረጋገጥ የሚጸፍ ሐተታ እንደመሆኑ መጠን ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ ሰፊው ታሪካዊ መረጃዎችን በማሰባሰብ በቃሉ ብርሃን ይተነትናል። መጽሐፉ ነባሩን መረጃዎች በማሰባሰብ ስለ ተሐድሶ አዲስ አመለካከት፣ አዲስ ራእይና እርምጃ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነቱን ያመለክታል። ይህ መጽሐፍ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቃል እውነት ላይ ታንጻ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ተጽዕኖ በማምጣት ከፍ ብላ እንዲትገለጥ የግድ ይላል፤ ካረጀው አሠራር፣ ከአገራዊ ኢመጽሐፍ ቅዱሰዊ የትውፊት ሰንሰለት፣ ከሰዋዊ አስተምህሮ፣ ከምድር ተኮር ወንጌልና የብዙ አገልጋዮች መለያ እየሆነ ከመጣው "ገበያ መር" የአገልግሎት ፍልስፍና ጋር አጣልቶን ለተሻለው ግጭት ውስጥ ያስገባናል። ሪክ ዋረን *"ዓለማ መር ሕይወት"* በሚለው መጽሐፋቸው እንዳሉት:- *ማለታረቅ ግጭትን መሸሽ አይደለም። ከችግር መሸሽ፣ የሌለ ማስመሰል፣ ወይም ስለ ችግሩ ለመናገር አለመድፈር ፈሪነት ነው። የሰላም ልዑል ኢየሱስ ግጭትን ፈጽሞ አልፈራም። አንዳንድ ጊዜ ለሁሉም ይበጅ ዘንድ አለመግባባትን ቀስቅሷል። አንዳንዴ ግጭትን መፍጠር፣ አንዳንዴ ደግሞ ማስታረቅ ያስፈልገናል።...ሰላምን መፍጠር ላልተግባባነው ሰው የፈለገውን ማድረግ አይደለም።* ማለት ነው።

ይህ መጽሐፍ ስለ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ሙሉ መልስ ባይኖረውም የመንደርደሪያ አሳብ እንደሚያቀብል እርግጠኛ ነኝ። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ላይ የተዘጋጀው መጽሐፍ በሁለት ቅጽ የተከፈለ ሲሆን ይህ የመጀመሪያው መጽሐፍ ነው። ሁለተኛውም መጽሐፍ *"የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ - ቅጽ ሁለት"* በሚል ከዚህ መጽሐፍ ይከተላል። ቅጽ አንድ መጽሐፍ በዓይነቱ ልዩ የሚያደርገው፣ በቤተ ክርስቲያን መታደስ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች በቃሉና በጠንካራ መረጃ አስደግፎ በነቅስ በማመልከት፣ ለኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ ግልጽ የተሐድሶ ጥሪ ማቅረቡ ነው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለተሐድሶ ካልተዘጋጀች ለሁለንተናዊ ዕድገትና በረከት ፋና ወጊ አትሆንም፤ እንደሚገባ የሰማይ መንግሥት ወኪልም መሆን አትችልም፤ የእስታትስቲካዊ ግዘፈት፣ የድርጅታዊ ጥንካሬና የቁሳቁስ ሀብታም ሆና መንፈሳዊ ሙት ትሆናለች።

ቅጽ 1 መጽሐፍ በሁለት ክፍሎች የተከፈሉ አሥራ ሁለት ምዕራፎችን ይዟል። የመጀመሪያው ክፍል *"የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ታሪክ"* በሚል ዋና አሳብ ሥር ስድስት ምዕራፎች ተካተዋል። ምዕራፍ አንድ:- የቤተ ክርስቲያንና የተሐድሶን ምንነት በሰፊው ይተነትናል፤ በተለይ የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስና የፐሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ተጨባጭ ገጽታዎችን አሳይቶ ካልታደሱ ምርጫቸው ሞት እንደሆነ መራራ

እውነት ይናገራል። *ምዕራፍ ሁለት*፦ ከማርቲን ሉተር አስቀድሞ ተመሳሳይ የተሐድሶ ጥያቄ በአገራችን በነማንና የት እንደተነሣ በማመልከት የከፈሉትን የደም ዋጋ በመረጃ አስደግፎ ያስቃኛል። *ምዕራፍ ሦስት*፦ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ ያመከነና የተሐድሶ ጥያቄ ያነሡ ቀደምት አባቶችን በጭካኔ ያስጨፈጨፈ የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን ማንነት በሰፊው ይዳስሳል። *ምዕራፍ አራት*፦ ከኢትዮጵያ ቀዳሚ ምሁራን አንዱ የተባሉ አለቃ ታዬ እምነታቸውን፣ ለአገር የነበራቸው ግልጽ ራእይ፣ አስደናቂ ሥራዎቹን በማሳየት የተሐድሶን ጥያቄ በማንሣታቸውና ስለ እምነታቸው፦ ለእንግልት፣ ለእሥራት፣ ለስደት፣ ለውግዘትና ለሞት የበቁበትን አሳዛኝ ታሪክ ይዟል። *ምዕራፍ አምስት*፦ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ የጥያቄ *"የምትና ሕይወት"* ጉዳይ ሆኖ ብዙዎች መስዋዕት እንደሆኑና የተሐድሶ ጥላቻ በዘመናችንም የባሰበት ቢሆንም ዛሬም የተሐድሶ ጥያቄ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ዳብሮና ሰፍቶ የትውልዱን ልብ እንደያዘ ያስቃኛል። *ምዕራፍ ስድስት*፦ አገራችን ክርስትናን በመቀበል በዓለማችን ቀዳሚ ከሆኑት አገሮች አንዷ መሆኗን፣ ያልታደሰው ክርስትናችን የኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምምዶች ተጠቂ እንዱት እንደሆነ ያሳያል።

የቅጽ አንድ መጽሐፍ ሁለተኛው ክፍል ***"ዓለምን የለወጠው የፕሮቴስታንት ተሐድሶ"*** በሚለው አሳብ ሥር ስድስት ምዕራፎች አሉ፦ *ምዕራፍ ሰባት*፦ የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ፋና ወጊዎችን ራእይ፣ በታላቅ ተጋድሎና በደም የታተመ የተሐድሶ ሰኬት ይዘረዝራል። *ምዕራፍ ስምንት*፦ የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መሠረቱ ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ አምስት የፕሮቴስታንት ተሐድሶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትና ምሶሶዎችን ይተነትናል። *ምዕራፍ ዘጠኝ*፦ የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ በዓለም አቀፍ ደረጃ ምን ለውጥና ውጤት አመጣ? ለሚለው ጥያቄ በጠንካራ ጥናት የተደገፈና በታሪክ የተረጋገጠ ሙሉ መልስ ይዟል። ከዚያም በ*ምዕራፍ አሥር*፦ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ክርስትና በደቡብ ኮሪያ፣ በ*ምዕራቡ* ዓለምና በቻይና ሁለንተናዊ ዕድገት የተጫወተውን ዐቢይ ሚና በምሳሌነት ይጠቅሳል። በዚሁ ክፍል ከሁሉም ቀድመን የተቀበልነው ክርስትና በጐላ መልኩም ባይሆን በተቃራራብ ሁኔታ ለምን እንደ ሌሎች እንዳልጠቀመን ጥያቄ አንሥቶ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያንን ለተሐድሶ ይጣራል። *ምዕራፍ አሥራ አንድ*፦ ቤተ እምነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባይሆንም እስከ ዛሬ እግዚአብሔር ለራሱ ክብር ተጠቅሞበታል፣ ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያናት በብዙ ማርጀታቸውን በማሳየት ለተሐድሶ ግልጽ አገራዊ ጥሪ ያቀርባል። *ምዕራፍ አሥራ ሁለት*፦ የቤተ ክርስቲያንን እርጅና፣ ሞትና ተሐድሶ በዝርዝር ያስቃኛል። በማጠቃለያም የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መሣሪያ ለመሆን ከእኛ ምን ይጠበቃል ለሚለው ጥያቄ አምስት ቁልፍ ነጥቦችን በማስቀመጥ መጽሐፉ ሐሳቡን ይቋጫል።

መልካም ንባብ
ፀጋአብ በቀለ
2006 ዓ.ም

ክፍለ ትንሽ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ታሪክ

፩

የቤተ ክርስቲያንና የተሐድሶ ምንነት

የቤተ ክርስቲያን ምንነት

ቤተ ክርስቲያን 15 እና 50 ሰዎች በስምምነት የሚመሠርቷት የንግድ ማህበር አይደለችም። ቤተ ክርስቲያን በፓስተርም ሆነ በሊቀ ጳጳስ ወይም በንጉሥ የምትሠራ ምድራዊ ድርጅት አይደለችም። ቤተ ክርስቲያንን የሚመሠርታት ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ቅዱሳን ከእርሱ ጋር ለመሥራት በጸጋው የታደሉ ልጆቹ ናቸው። የቤተ ክርስቲያን ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ሞት እና ትንሣኤ የተጠራች የቅዱሳን ጉባኤ እንጂ ግዑዝ ሕንፃ አይደለችም። ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ቦታ ሳትሆን የሚጸልዩ ቅዱሳን ናት። ቤተ ክርስቲያን ቦታ ሳትሆን በቦታ ላይ የሚኖሩ የክርስቶስ ልጆች አንድነት ናት። ቤተ ክርስቲያን የሚሰገድላት ግኡዝ ሕንፃ ሳትሆን በእውነትና በመንፈስ ለእግዚአብሔር የሚሰግዱ ቅዱሳን ሕብረት ናት። ቤተ ክርስቲያን በድንጋይ፣ በሲሚንቶ፣ በእንጨት፣ በብረት ሳይሆን በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ፣ በቃሉና በጸጋው የተገነባች መለኮታዊ አካል ናት።

ዶክተር መልሳቸው መስፍን "ቤተ ክርስቲያን" በሚል መጽሐፋቸው፡- "ቤተ ክርስቲያን" የሚለው ቃል(ሐረግ) በአማርኛ የሚሰጠው ቀጥተኛ ፍቺ *"የክርስቲያን ቤት"* የሚል ሲሆን ቤተ መንግሥት፣ ቤተ ክህነት፣ ቤተ መዘክር እንደሚሉት ሐረጎች ሁሉ ትርጉም የሚያሳላው ቦታውንና ያም ቦታ ወይም ቤት ለምን አገልግሎት እንደሚውል ነው።[86] የእንግሊዘኛው ቃል "ቸርች" የሚለው ደግሞ *"ኩሪያኮስ"* ከሚል የግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም የጌታ የሆነ ማለት ነው። ሆኖም ቤተ ክርስቲያን ለሚለው መጠሪያ የግሪክ ስርወ-ቃሉ "ኤክለሽያ"[87] ሆኖ ከግሪክ ቃል በመመሥረት የእንግሊዝኛ ቀጥተኛ ትርጉም *"ኤክሌሲያስቲካል"* ነው፤ ብለዋል። ይህም ማለት ስብስብ ማኅበር ወይም ጉባኤ ማለት ነው። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን ማለት መሠረታዊ ትርጉሙ የቅዱሳን ጉባኤ ወይም ማኅበር ማለት ነው።[88]

አባ መልከጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ *"የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት"* በሚለው መጽሐፋቸው ቤተ ክርስቲያን ቦታና ሕንፃ ሳትሆን የቅዱሳን አንድነት እንደሆነች ሲገልጹ፡- *...ሕንፃውን ግንቡን ቤተ ክርስቲያን እንላለን እንጂ ቤተ ክርስቲያን ማለት ክርስቶስ በደሙ የዋጃት የመሠረታት እንዲሁም እርሱ ራስ የሆነላት የምዕመናን አንድነት ማለት ነው። ...ቤተ ክርስቲያን የተባልን እኛ ስንሆን የቤተ ክርስቲያንም ራስ ክርስቶስ ነውና*[89] በማለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት አስቀምጠዋል። ሮጀር ካውሲ ቤተ ክርስቲያን *"ትርጉሙ እምብዛም ወደ ሰው እንጂ ወደ ሕንፃ አይደለም።"*[90] ሲሉ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን መባሉ በልማድና በዘይቤ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት እንደሌለው አሳታውቀዋል።

በኒቅያ ጉባኤ (325 ዓ.ም)፣ (የሃይማኖት አንቀጽ) በቁስጥንጥንያ ጉባኤ (381 ዓ.ም) አንቀጽ ሃይማኖት ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከት የተጻፈው አንቀጽ እንዲህ ይላል፡- *"በሁሉ ባለች በሐዋርያዊት ጉባኤ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን"* የሚለው ፍሬ አሳብ አማኞችን እንጂ ሕንፃን አያመለክትም። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ስም በማገልገል ላይ የሚገኘው ለቅዱሳን አንድነት ወይንስ ለግዑዝ ሕንፃ? ከሁሉ በፊት አንዱ በቃሉ መታደስ መለወጥ ያለበት ይህ ዘመን ዘለቅ ስህተት ነው። የቅዱሳን ሕብረት ቤተ ክርስቲያን ናቸው እንጂ ቤተ ክርስቲያን አይሄዱም።

---

[86] መልሳቸው መስፍን (ዶ/ር)(1979 ዓ.ም) *፣ቤተ ክርስቲያን*፣ ሮኖቡት ማተሚያ ቤት፣ ገጽ 17

[87] ekklesia (ek-klay-see-ah) Strong Exhaustive Concordance of the Bile defines as follows:- ekklesia: a calling out i e a popular meeting, especially a religious congregation; assembly. ለምሳሌ፡- በሐዋ 7:38 ይህ ሰው በሲና ተራራ ከተናገረው መልአክና ከአባቶቻችን ጋር በምድረ በዳ በማህበሩ ውስጥ የነበረ ነው በሚለው ማህበር ለሚለው ቃል የተሰጠው የግሪክ ekklesia ነው። ይህ ቃል King James and Standard Versions Church ሲሉት New International Version Congergation ይለዋል።

[88] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 18

[89] አባ መልከጼዴቅ (ሊቀ ጳጳስ)(1994 ዓ.ም.)፣*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት*፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ ገጽ 242-243

[90] ሮጀር ካውሲ(*1963 ዓ.ም*) ጸድቀ ሃይማኖት፣ የቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ውሳኔዎች፣ብ.ሲ.ቀ.ኃ.ሥ.ማ. ቤት፣ ገጽ 66

የተሐድሶ ምንነት

የተሐድሶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት

መጽሐፍ ቅዱስ የተሐድሶ/ *Reformation* /[91] መጽሐፍ ነው። ብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር የተፈጠረው ፍጹም ሰው፣ ከመውደቁ የተነሣ፣ ፍጥረተ ዓለሙ በኃጢአትና በሰይጣን ግዞት ውስጥ ያሳሰፉትን መራራ፣ ጨለማና ያረጀ የቀድሞ ሕይወት ይወክላል። አዲስ ኪዳን ደግሞ በሰይጣን መታሰል ወድቆ የኃጢአት ግዞተኛ የሆነውን የሰው ልጅና ፍጥረተ ዓለሙን ሊያድስ ትልቅ የሕይወት ዋጋ ስለከፈለው ስለ ኢየሱስ ይተርካል።

በኖኅ ዘመን የሰው ልጅ በኃጢአትና በክፋት ዓለምን በሞላ ጊዜ እግዚአብሔር *"ክፋት በምድር ላይ እንደ በዛ የልቡ አሳብና ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደሆነ አየ፤ ...እግዚአብሔርም፦ የፈጠርሁትን ሰው ከምድር ላይ አጠፋለሁ፦...አለ"* (ዘፍ.6:5-7)። በዚህ ክፍል እግዚአብሔር በኖኅ መርክብ ካሉት በቀር በኃጢአት የተበከለውን ፍጥረተ ዓለም በማጥፋት ተሐድሶን በምድር ላይ ሲያመጣ እንመለከታለን። እግዚአብሔር የኪዳን የሆኑ የእስራኤል ነገሥታትና ሕዝቡ ቃሉን በመተላለፍ የክረብታ መስገጃዎችን ሲተክሉና የማምለኪያ አፀዶችን ሲገነቡ አዳሾችን ያስነሣ ነበር። ተሐድሶው የእግዚአብሔር ያልሆነውን በማፍረስ ይገለጥ ነበር። ተሐድሶን ከመሩ ነገሥታት መካከል ሕዝቅያስ አንዱ ነበር። *(2ነገ.10: 27፤ 11: 18፤ 23: 7)*። በስም የእግዚአብሔር በግብር ግን ጣዖት ሲያመልክ የተገኘው ሕዝብ እግዚአብሔር በተሐድሶ ቃል ባመጣ ጊዜ ባይመቸውም የክረብታ መስገጃዎችን ሲያፈርስ፣ የሐሰተኛ አማልክቱን ሲጥል፣ የማምለኪያ አጸዶቹን ሁሉ ሲቈራርጥ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቦታ ይናገራል። *(መሳ.6:28-30፤ 1ነገ.13:1-2፤ 22:43፤ 23:67)*። ይህ የእግዚአብሔር የሆነውን በማደስ የእግዚአብሔር ያልሆነውን ሁሉ በማፍረስ የተገለጠ ተሐድሶ ነበር።

ከተሐድሶ መሪዎች አንዱ የነበረው ሕዝቅያስ ለቤተ መቅደስ አገልጋዮች ባደረገው ንግግር፦ *"ሌዋውያን ሆይ ስሙኝ ተቀደሱ፤ የአባቶቻችሁንም አምላክ የእግዚአብሔርን ቤት ቀድሱ፤ ርኵሰትን ነገር ሁሉ ከመቅደስ አስወግዱ"* *(2ዜና 29:5)*። በዚህ ክፍል ተሐድሶ ከራስ መጀመር

---

[91] ተሐድሶ በሚባለው ቃል ፍቺ የእንግሊዝኛ ሐሳብ እንዳለ ይዞ ቀርቧል፦*The Reformation sought to "reform" Christianity by returning it to original beliefs based solely on reference to the Bible, eliminating later additions which accumulated in tradition. Word origin - "improvement, alteration for the better," early 15c., በተጨማሪ የማያስተላለውን ድረ ገጽ ይመልከቱ፦ http://atheism.about.com/library/glossary/western/bldef_reformation.htm*

እንዳለበት አመልክቷል። መጽሐፍ ቅዱስ የሌዋውያንን አስደናቂ አርምጃ እንዲህ ገልጾታል፦ *"ያነጹት ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ቤት ወደ ውስጡ ገቡ፤ በእግዚአብሔርም መቅደስ ያገኙትን ርኩስ ነገር ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ቤት አደባባይ አወጡት። ሌዋውያንም ወስደው ወደ ሜዳ ወደ ቄድሮን ወንዝ ጣሉት"* *(2ዜና.29:16)*። በሙሴ ዘመን በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ለአንድ ጊዜ ከእባብ ንክሻ ሕዝቡን እንዲያድን ከነሐስ የተሠራ የእባብ ምልክት ተሰጣቸው። ከዚያም በኋላ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ዓይኑን በማንሣት ከነሐስ የተሠራ የእባብ ምልክት ያመልክ ነበር። ይህን የተጣመመና አገርን ሁሉ አስቶ የነበረውን፤ የተሐድሶ ሰው የነበረው ንጉሥ ሕዝቅያስ፦ *"የእስራኤልም ልጆች እስከዚህ ዘመን ድረስ ያጥኑለት ነበርና ሙሴ የሠራውን የናሱን እባብ ሰባበረ፤ስሙንም ነሑሽታን ብሎ ጠራው"(2ነገ. 18: 4)* ይላል።

ዛሬ ዘመን ዘለቅ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሻገሩ የመጡ እንደ ነሐሱ የእባብ ምልክት መወገድ ያለባቸው የብዙሃኑን እይታና ልቦና የያዙ አስትምህሮዎችና ልምምዶች በቤተ ክርስቲያን የሉም ወይ? ካሉ በቃሉና በመንፈሱ ላይ ቆመን እንደ ሕዝቅያስ ማስወገድ ይገባናል። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለሕዝቡ የተሐድሶ ዓላማ እንደነበረው በነብዩ ኢሳይያስ በኩል ሲናገር፦ *"እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን <u>ያድሳሉ</u>"* (ኢሳ.40:31) ይላል።

ወንጌል የተሐድሶ መልዕክት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ዒላማውን ስቶ በኃጢአት ውስጥ ለወደቀው ሰው፣ እንደገና ወደ ተፈጠረበት መለኮታዊ ዓላማ አድሶ በክብር ለመመለስ፣ የሰው ሥጋ ለብሶ ተወልዶ፣ በፍጡር እጅ ሞቶ፣ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣ የተሐድሶ ፋና ወጊ ነው። *"ባዘፋኑ የተቀመጠው ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ"* (ራእ. 21: 5)። ከዚህም የተነሣ መጽሐፍ ቅዱስ በእርሱ አሮጌ ነገር ሁሉ አልፎ ሁሉም አዲስ እንደሆነ መስክሯል፦ *"ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፣ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል"* *(2ቆሮ.5:17)*። ሐዋርያት በነፍሳቸው ተወራርደው በመውጣት፣ እየሰበኩ የሞቱት ይህን የተሐድሶ ዜና ነው።

ተሐድሶ ባያስፈልግ ኖሮ በሮሜ ላሉት ቅዱሳን ታላቁ ሐዋርያ ሲጽፍ *"በልባችሁ <u>መታደስ</u> ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ"* *(ሮሜ.12:2)* የሚለውን ቁልፍ ትዕዛዝ ባልሰጣቸው፤ እንዲሁም ሐዋርያው ጴጥሮስ ቀናዒ ለነበሩ አይሁዶች *"እንግዲህ ንስሐ ግቡ፣ ከመንገዳችሁም ተመለሱ ከጌታም ዘንድ <u>የመታደስ</u> ዘመን ይመጣላችኋል"* (ሐዋ.3:19)። *(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)* ብለው አይናገሩም ነበር። ዛሬም በኪዳናቸው ላይ ቆመው የሕይወትን መታደስ የሚጠባበቁትን ጌታ ያድላቸዋል።

- ተሐድሶ የሕያውነት ምልክት ነው፣
- ተሐድሶ የልጅነት ኪዳን ነው፣
- ተሐድሶ በሰው ድካም የእግዚአብሔር ኃይል የሚገለጥበት መንገድ ነው፣
- ተሐድሶ የዶግማ (የእግዚአብሔር ቃል) መለወጥ ሳይሆን ሰዋዊና እንደ ቃሉ ያልሆኑ አደናቃፊ ቀኖና (ሰዋዊ ሥርዓት) መለወጥ ነው። ተሐድሶ ሰው ያለመቻሉን ለፈጣሪው በማሳወቅ ትዕቢቱን የሚሸርበት መንገድ ነው፣
- ተሐድሶ አሮጌ ነገራችን በአዲስ የሚተካበት ድንቅ ሂደት ነው፣
- ተሐድሶ የመክበር እንጂ የመዋረድ ምልክት አይደለም፣
- ተሐድሶ የእግዚአብሔርን ትክክለኝነት የሰውን ስህተተኝነት የሚያመለክት ሚዛን ነው።
- በዓለማችን ላይ ተሐድሶ የማያስፈልጋት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የለችም።
- ተሐድሶ የብሉይና የአዲስ ኪዳን ቁልፍ ትምህርት ነው። እንደገና ካልተሠራን እንደገና መሥራት አንችልም።

እውነተኛ ተሐድሶ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይመጣ የምንከላከለው አደጋ ሳይሆን እግዚአብሔር ሊያነቃን ሲፈልግ የሚያመጣልን ታላቅ ጸጋ ነው። ተሐድሶ ለሕያው እንጂ ለሙት "ቤተ ክርስቲያን" አያስፈልግም። የሞተ ነገር የሕይወትን ዐዲት ጨርሶ ወደሌላ ስለተለወጠ ትንሣኤ እንጂ ተሐድሶን አይፈልግም። ከዛሬ 41 ዓመት በፊት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ሆነው ሲሾሙ ተሐድሶ እንደሚያመጡ በብዙዎች እንደሚጠበቁ የዛሬዪቷ ኢትዮጵያ የተሰኘው አንጋፋው ጋዜጣ እንዲህ ብሎ ነበር፦

> *የሌሎች አገሮች አብያተ ክርስቲያናት እንደ ታደሱ ሁሉ የእኛም እንደ ዘመኑ መራመድ ይኖርባታል። የአሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን ሰዎች አስተሳሰብና የሃያኛው ክፍለ ዘመን ፍልስፍና በጣም የተራቀቀና የተለየ ስለሆነ ሊያሳምን በሚችለው በአዲስ ዘዴ መቅረቡ የተሻለ ውጤት ያስገኛል። ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ይህን ሁሉ በማመዛዘን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ፣ በአሠራር፣ በአስተሳሰብና በአፈጻጸም የታደሰችና የዘመኑን ሥርዓት የተከተለች እንደሚያደርጉት ከፍተኛ ኃላፊነት ይጠብቃቸዋል።*[92] በማለት ለተሐድሶ ያላቸውን ረዛብ ገልጸው ነበር።

[92] *የዛሬዪቷ ኢትዮጵያ፣ ሚያዝያ 2፣ 1963 ዓ.ም*

ተሐድሶ ራሳችንን፣ አገልግሎታችንንና ቤተ ክርስቲያንን በእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ የምንመዝንበት ዕድል እንጂ እርስ በርስ የምንካሰስበት ችሎት አይደለም። በአገራችን ሰዎች በተሐድሶ ስም የሚካሰሱበትና የሚወገዝበት አንዱ ምክንያት የተሐድሶን አጀንዳ የሰዎች አጀንዳ አድርገው ስለቆጠሩ ነው። የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ስንመለከት የተሐድሶን አጀንዳ እግዚአብሔር በልጆቹ በኩል ለቤቱ ያቀብላል እንጂ ልጆቹ የተሐድሶን አጀንዳ አያመነጩም። ቅዱሳን የተሐድሶ መንገዶች እንጂ ምክንያቶች አይደሉም። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶን ስንታወም የእግዚአብሔርን እንጂ የሰውን ሐሳብ አልተታወስንም። ተሐድሶ ስለ ትክክለኝነታችን የምንመጻደቅበት መድረክ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈሱ ውስጣችን የሚፈተሽበት መንገድ ነው። ትሁታን እንጂ ስለ ትክክለኝነታቸው የሚመጻደቁና የሚሰብኩ በፍጹም አይታደሱም።

ተሐድሶ አዲስ ሀሳብ ማፍለቅ ሳይሆን የቀደመውንና የቆየውን መለኮታዊ ሐሳብ ከኋላ መጥቶ የጋረደና የተካ የሰውን አዲስ ሃሳብ አስወግዶ ወደ ቀደመው የእግዚአብሔር ሃሳብ ለመመለስ አዲስ እርምጃ መውሰድ ነው። ፕሮፌሰር ሮበርት ሲናገር፡- *የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መሪዎች የሰበኩት በራሳቸው የፈጠሩት "አዲስ" ወንጌል ሳይሆን በብሉይና በአዲስ ኪዳናት ያገኙትና የተቀበሉት "አሮጌ" ወንጌል ነው*[93] ብሏል። ተሐድሶ አዲስ ወንጌል ሳይሆን የቀደመውንና የጥንቱን የክርስቶስ ወንጌል የጋረዱና የተቀላቀሉ የሰዎችን ትምህርትና ቀኖና በቃሉ አበጥሮ ሐዋርያት ወደ ሰበኩት የጠራና የጠለለ የወንጌል እውነት መመለስ ነው።

ተሐድሶ የሚለውን ቃል በትክክል እንረዳ

ተሐድሶ የሚባለው ቃል፣ በተለይ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ እጅግ የተለመደና የታወቀ ቃል ነው። ተሐድሶ የሚባለው ቃል ከቤተ ክርስቲያን ጋር ተያይዞ ሲነሣ፣ ምን ጊዜም አፍራሽ ሳይሆን፣ ለተሻለውና ለሚበልጠው ነገር ነው።[94] *"ተሐድሶ"* የሚል ቃል ጽንሰ ሐሳብ ትርጉሙ ምድንነው? ለሚለው ጥያቄ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረን፣ ሰፋ አድርገን ብንመለከት መልካም ነው። ተሐድሶ የሚለው ቃል የግእዝ ቃል ሲሆን፣ የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ተሐድሶን በገቢር ግስ (ሐደሰ) ሲፈታው፡- *ማደሰ፣ መለወጥ፣ ሐዲስ ማድረግ፣ ማጥናት፣ ማበረታታት፣ መሥራት፣ መጠገን*፣ በተጨማሪም "አዲስ ነገር ማውጣት፣ መፍጠር ነው።" ይላል (ገጽ 435)

---

[93] Robert Mcafee Berwon, (1961)', *The Spirit of Protestantism*, New York Oxford University Press p16

[94] *ተሐድሶ የተሰኘው መንፈሳዊ አንቅስቃሴ ግን ምንጊዜም አፍራሽ ሳይሆን ገንቢ፣ አጥፊ ሳይሆን አልሚ ተግባር የሚገለጸበት በመሆኑ፣ ከመንፈሳዊው ዓለም ባሻገር በሥጋዊው ዓለምም በጥቅም ላይ ውሏል። በአገራችን እንኳ ቃሉ በደርግ፣ በኢሕአዴግም መንግሥታት፣ አርሜንና የተበላሸን ነገር ከማሻሻል፣ ከማስተካከልና ከማሰወገድ ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ እንደ ዋለ ይታወቃል። ከመቼውም ጊዜ ይልቅ አገራችን በሁሉም መስክ የተሐድሶ (ሕዳሴን) ድምፅ እያስተጋባች ትገኛለች። መምህር በቃሉ ታመነ (2004 ዓ.ም)፣ ማህበረ ቅዱሳን የቤተ ክህነት ዕዳ፣ ገጽ 33*

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ *"ደቂቀ አስጢፋኖስ በሕግ አምላክ"* በሚለው መጽሐፋቸው፣ ተሐድሶ የሚለውን ቃል ሲተርጉሙ፡- *ተደላድሎና ተመቻችቶ በተቀመጠው ሥርዓት (Establishment) ውስጥ የዛገና የሚራገፍ ነገር የሚያይ፣ የአእምሮ ችሎታና የተፈጥሮ ተሰጥኦ ካላቸው ታላላቅ ሰዎች ዘንድ የሚመጡ አሳቦች ናቸው*[95] ይላሉ። ዶክተር ኢያሱ ፈርንጅ *"ዘመነ ተሐድሶ"* በሚለው መጽሐፋቸው *"ተሐድሶ ማለት ምን ማለት ነው?"* ለሚለው ጥያቄ መልስ ሲያስቀምጡ፡- *ተሐድሶ የሚባለውን የአማርኛ ቃል፣ ጥሬ ትርጉም ስንመለከት፣ እዲስ ከሚለው ቃላት የመጣ ሲሆን፣ ላንድ ያረጀን፣ የተበላሸን፣ የቀድሞ ይዙቱን የለቀቀን ነገር ወደ ቦታው፣ ቀድሞ ወደ ነበረበት ይዘት መመለስ፤ አዲስ ማድረግ ማለት ነው*[96] ብለዋል። በቢ ግሊያም በአሜሪካ ከሚገኙት ጥቂት ዕውቅ የቤተ ክርስቲያን አማካሪዎች መካከል አንዱ የሆኑና የቲ-ኔት ኢንተርናሽናል የፓስተራል ሊደርሽፕ ኮሌጅ ፕሬዝዳንት *"ታላቁ ተልዕኮን መፈጸም"* በሚል ርዕስ ባዘጋጁት የኮርስ መጽሐፍ፡-

> *ተሐድሶ ማለት <u>የነገረ መለኮታዊ የአስተሳሰብ፣ የድርጅታዊ እና የፕሮግራም አወቃቀሮችን ዳግም ማደስ</u> ማለት ሲሆን ይህም ቤተ ክርስቲያን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንድትኖርና በመነቃቃት የተገኙትን ውጤቶች እንዲታበዛ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ለተከታታይና ረዘም ላለ ጊዜ በተሳካ ሁኔታ እንዲትፈጽም የሚያስችላት ለውጥ ነው*[97] ብለዋል።

ሦስቱ የተሐድሶ የእንግሊዝኛ ቃላት ፍቺዎች፡-

ተሐድሶ የሚለውን የአማርኛ ቃል፣ እንግሊዘኛው በሦስት ቃል *(Reformation, Renewal, Restoration)* በማለት ያብራራል። ሦስቱም ቃላት እያንዳንዳቸው ከሁለት ቃላት የተፈጠሩ ናቸው። ሦስቱንም ቃላት ቀድመው የተጠቀሱ ቃላት ተመሳሳይ ሲሆኑ የሚከተለውን ቃል ትርጉም የመለወጥ አቅም ያላቸው በእንግሊዘኛ *"prefix"* ይባላሉ። እነርሱም *"Re"* የሚሉ ቃላት ሲሆን ትርጉሙም */Prefix: Re- Meaning 'Again, back/* በአማርኛ *"እንደገና ወይም ዳግመኛ"* የሚል ጽንሰ አሳብን ይሰጠናል። በእንግሊዘኛው የተሐድሶ ፍቺን ለመስጠት አገልግሎት ላይ የዋሉትን ሦስቱን ቃላት እያንዳንዱን ነጣጥለን ስንፈታው እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1. *Re-formation*፡- *እንደገና መሥራት፣ እንደገና መለወጥ፣ የሚል እንደምታ ሲኖረው፣ በግሪክ ደግሞ ዳዮርቶሲስ (Diorthosis) የሚል ቃል ነው።*

---

[95] *ደቂቀ አስጢፋኖስ፣ ገጽ 23*

[96] ኢያሱ ፈርንጅ *(ዶ/ር) (2004 ዓ.ም)፣ ፣ ዘመነ ታሐድሶ፣ ርኖበት አታሚዎች አዲስ አበባ፣ ገጽ 1*

[97] መንግሥቱ ማሞ(መጋቢ) (2011) እና ታዮች አርጊቾ (ተርጓሚዎች)፣ *ታላቁን ተልዕኮ መፈጸም*፣ ቲ-ኔት ኢንተርናሽናል፣ ገጽ 64

ትርጉሙም የተበላሸውንና የተመሰቃቀለውን ነገር በትክክለኛ ቦታ ሥርዓት አስይዞ ማስቀመጥን፣ ወደ ቀድሞ ይዞቱ መመለስን፣ የቀድሞውን ፈር የለቀቀውን፣ አዲስ ሥርዓት ማስያዝን ያመለክታል።[98]

2. *Re-newal:- ማደስ፣ የቀድሞ መልክና ውበትን መመለስ፣ የዚህ ቃል መሠረት አናካይኖ (Anakaino) የሚል የግሪክ ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም አዲስ ማድረግ ማለት ነው። ያረጀውን ነገር ወደ ቀድሞ ሁኔታ መመለስ፣ የደከመውን የሰውነት ክፍሳችንን እንደገና ኃይል ማግኘትን ያመለክታል። በዚህ አውድ መሠረት የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት ተሐድሶ እንደሚያስፈልገው እንገነዘባለን።*[99]

3. *Re-storation:-ወደ ቀድሞ ሥፍራ ወይም ባለቤት መመለስ። ይህ ቃል አካታስታቶስ (Akatastatos) ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን፣ ስፍራውን የለቀቀውን፣ የተሰረቀውን፣ የተወሰደውን ወደ ሥፍራው መመለሱን ያመለክታል። ዶክተር ሊያሁ ተሐድሶ የሚለውን ሲያብራሩ፣ ተሐድሶ ማለት የተበላሸውንና የተመሰቃቀለውን ማስተካከል፣ ማሻሻል፣ መለወጥ፣ ያረጀውንና የፈረሰውን እንደገና በማደስ፣ እንደነበረው ማድረግ፣ የጠፋውንና ሥፍራ የለቀቀውን ወደ ቀድሞ ሥፍራው መመለስ ነው።*[100] በማለት አብራርተዋል።

በ16ኛው ክፍለ ዘመን፣ እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መንገድ አድርጎ የተጠቀመበት ማርቲን ሉተር በሰው ሥርዓትና ወግ ወንጌልን የለወጠችና ከመንግሥት ጋር ጋብቻ ፈጽማ የሰማይ ሙሽራ በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ላይ የተጫነባትን ሸክም በቃሉና በመንፈሱ አራግፎ ወደ ቀድሞ ከመመለስ ያለፈ ለቃሉ ባዕድና አዲስ የሆነ ነገር ያደረገው አንዳችም አልነበረም። የሉተር ድርጊት ከቃሉ ለወጣች ቤተ ክርስቲያን እንጂ ለቃሉ ባዕድና አዲስ አልነበረም። ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ከቃሉ ጋር የሚቃረኑና የሚጣረሱ ዘመን ዘለቅ ልምምዶችንና አስተምህሮዎችን እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚቆጥሩ ሰዎች ለተሐድሶ አመንታዊ አመለካከት የላቸውም። የሮም ቤተ ክርስቲያን፣ ማርቲን ሉተርን የእግዚአብሔርን ቃል ይዞ ሊነሣ እስከ ሞት እንዳሳደደችው፣ ዛሬም የተሐድሶን ዓላማ አንግበው የሚነሡትን በብርቱ የሚያሳድዱና ለቤተ ክርስቲያን እንደቀኑ የሚናገሩ ሰዎች እጅግ ብዙ ናቸው። ስለዚህም የተሐድሶ መንገድ አልጋ በአልጋ ሳይሆን፣ ብርቱ ትግል፣ ተቃውሞ፣ ስም የማጥፋት ዘመቻ፣ የማጠልሸት አካሄዶች የተሞላ እንደሆነ ታሪክ ያስተምረናል።

ሰይጣን በቃሉና በመንፈሱ ታድሳ የክርስቶስን ውበት በገሃድ የምታሳይ ቤተ ክርስቲያን በዓለም በፍጹም እንድትገለጥ አይፈልግም። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ለማደስ በእርሱ በሚያምኑ ልጆቹ ሲጠቀም ሰይጣንም ቤተ ክርስቲያን እንዳትታደስ የእርሱን አጀንዳ በሚያስፈጽሙ

[98] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 1*
[99] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 3*
[100] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 4*

አማኞች ነን በሚሉ ይጠቀማል። በቃሉና በመንፈሱ የታደሰች ቤተ ክርስቲያንም ከሰይጣን ህቡዕ አሠራር፣ የክርስቶስን ወንጌል ከምጋርዱ አስተምህሮዎች፣ ከዓለም ክፋትና ከሥጋ ምኞት ጋር በፍጹም አትደራደርም፤ አትወግንም። ብርሃን ከጨለማ ጋር ምንም አጋሪነት የለውምና። ለጌታ ክብር ይበልጥ ራስዋን የሰጠች ቤተ ክርስቲያን(ቅዱሳን) ከሌላው የበለጠ መንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ትገባለች፤ ሁልጊዜ ድሉ የጌታና የቅዱሳን ነው። ጂም ቫን ይፐርን *"እርቀ ሰላም ለቤተ ክርስቲያን"* በሚለው መጽሐፉ ስለ ተሐድሶ በምሳሌ እንዲህ አስቀምጠዋል፦

> *በኢጣሊያን ፊሎረንስ ከተማ-ምንስን የተላበሰ ባለ 25 ሜማ የዳዊት ሐውልት ቆሞ ይታያል። ለማይክል አንጀሎ የቅርጻ ቅርጽ ሥራ ፈጠራ ሳይሆን ግኝት ነበር። አንድ የፈጠራ ባለሙያ አንድን ድንጋይ የሚጠርበው ስዘሀ ምን ላወጣ እችላለሁ? በሚል ሐሳብ ነው። ማይክል አንጀሎ ግን ድንጋዩን ከመጥረቡ በፊት ዳዊት አዚያ ውስጥ እንዳለ በማሰብ ነበር ሥራውን የጀመረው። የእርሱ ሥራ በስፍራው የነበረውን ምስል ቆፍሮ ማውጣት ነበር። ይህንም ያደረገው ዳዊት ያልሆነውን ነገር ሁሉ በማስወገድ ነበር። **ተሐድሶ ማለት የክርስቶስ ያልሆነውን ነገር ሁሉ ማስወገድ ነው**"[101]*

ዛሬ ክርስቶስን የማይገልጡ፣ ስብከቶች፣ መዝሙሮች፣ ትንቢቶች፣ ልምዶችና ሥርዓቶች ቤተ ክርስቲያንን አጨናንቀው የሉም ወይ? የክርስቶስን ብቸኛ ቤዛነት በገሃድ የሚቃወሙ፣ የወንጌልን ቃል የጋረዱና የሕዝባችንን ልቦና ያደነዘዙ ባዕድ ትምህርቶች የተጫነባቸው ድርሳናትና ገድላት ቁጥራቸው ይታወቃል ወይ? ለክርስቶስ መስቀልና እውነት ሳንገኝ በክርስቶስ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ኢወንጌል የሆነ ቀመር በወንጌል ሽፋን እያስፋፋን አይደለንም ወይ? ኮንፈራንሶቻችንና ጉባኤያችን ወንጌል የሚሰበክባቸው መድረኮች መሆናቸው ቀርቶ አንዳንድ "ነቢያት" "ሐዋርያት" "ፓስተር" "ወንጌላውያን" ተብዬዎች አባል እንጂ ደቀ መዝሙር ያልሆኑና ቃሉ በውስጣቸው ያላደረውን ምስኪን ሕዝብ እያራቆቱበት አይደለም ወይ? የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ማለት ከላይ የተጠቀሱትን ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችና ልምምዶች ማስወገድ ማለት ነው። አገርና ዓለም ያወቃቸው እነዚህን ኢወንጌል የሆኑ ግሳንግሶች ተሸክመን ተሐድሶን የምንቃወም ከሆነ የእግዚአብሔር መንግሥት እንቅፋት ሆነናል ማለት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል የሚወድና የሚሰብክ ሰው ቃሉ የሚጸረሩ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶችን አይፈቅድም፤ አያሰራጭም።

የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ማለት ኢወንጌል የሆኑ ዕድሜ ጠገብ ትምህርቶችን፣ ሥርዓቶችን፣ ልምዶችን፣ ስብከቶችንና ትንቢቶችን ከቤተ ክርስቲያን ማስወገድ ነው። የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መሪ የነበረው ማርቲን ሉተር እ.ኤ.አ በ1417 በዊተንበርግ ቤተ ክርስቲያን በር ላይ በመደሻ

---

[101] ግርማዊ ቡሽ ተተርጉሞ፣ እርቀ ሰላም ለቤተ ክርስቲያን፣ ሕትመት አልፋ አታሚዎች፣ 2000 ዓ.ም፣ ገጽ 237

ከጠረቀው 95 ነጥቦች መካከል አንዱ፡- *"ለክርስቶስ ሕዝብ ሰላም ሳይሆን 'ሰላም ሰላም (ኤር.6፡14) የሚሉ ነቢያት ሁሉ ይወገዱ"*[102] ብሎ እንደተነሣው መነቀል ያለበትን ከቤቱ የሚነቅሉና መተከል ያለበትን የሚተክሉ የተሐድሶ ነቢያት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በኃይል ይገለጣሉ። ከእንግዲህ በወንጌል ስም የሚነግዱ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቦታ የላቸውም። ከላይ በተለያዩ ምሁራንና የእግዚአብሔር ቤት አገልጋዮች የተጠቀሱት የተሐድሶ ትርጉሞች እንዳሉ ሆነው፤ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ የተሐድሶን ትርጉም እንዲህ ያስቀምጣል፡- **የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ አዲስ ሃይማኖት ሳይሆን፣ ሁሌ አዲስ በሆነው የእግዚአብሔር ቃል መነጽር በማየት በቤተ ክርስቲያን ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ ሰርጎ የገባውን ሥጋዊ፣ አጋንንታዊና ዓለማዊ አሠራሮችን፣ ትውፊቶችን፣ አስተምህሮዎችንና ልምምዶችን በቃሉ ነቅሶ በማስወገድ፣ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ቀድሞ ክብሯ ለመመለስ እግዚአብሔር በልጆቹ የሚሠራው ታላቅ ሥራ ነው።**

የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መሣሪያ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ቃሉ ዒላማ አድርጎ የሚነሣው የቀደመውንና ነባር የሆነውን የቃሉ እውነት ከኋላ መጥቶ ለመሸፈን ወይም ለመናድ በሚታገሉት ልምምድ፣ ትውፊት፣ ሥርዓት፣ ድርሳናትና አስተምህሮ ላይ ነው። የእግዚአብሔር ቃል በቤተ ክርስቲያን የሚካሄደውን እያንዳንዱን ጉዳይ ይዳኛል፣ ይፈትሻል፣ ይሞርዳል፣ ይቀርጻል፣ እውነትን ያፀድቃል፣ ውሸትን ይጥላል፣ መፍረስ ያለበትን ያፈርሳል፣ ያረጀውን ያድሳል፣ መተከል ያለበትን ይተክላል፣ እንዲሁም መነቀል ያለበትን ይነቅላል።

የትኛውም የቤተ ክርስቲያን ትውፊት፣ ድርሳናት፣ ገድላት፣ ልምምዶች፣ አስተምህሮዎችና ቀኖና በመጽሐፍ ቅዱስ ይፈተሻሉ እንጂ ሁላቸውም አንድ ላይ ተጨፍልቀው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰውን አንድ ቃል መፈተሽ አይችሉም። *"በመጀመሪያ ቃል ነበረ"* (ዮሐ.1፡1) የሚለው እውነት፣ የእግዚአብሔር ቃል የሁሉ ቀዳሚ፣ የሁሉ መገኛ፣ የሁሉ ምንጭ፣ የሁሉ ፈጣሪ፣ የሁሉ መሠረትና ሚዛን መሆኑን ያሳያል። ቃሉም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

የመነቃቃት ምንነት

መነቃቃት ተሐድሶ አይደለም፤ ተሐድሶም መነቃቃት አይደለም። በተለምዶ ብዙውን ጊዜ እነዚህ ሁለት የተለያዩ ጽንሰ አሳቦች እንደ አንድ አሳብ ሲቀርቡ ይታያሉ። ሁለቱ አሳቦች ተደጋጋፊና ለቤተ ክርስቲያን እጅግ በጣም አስፈላጊ ሲሆኑ ልዩነታቸውን ማወቅ ግን የግድ ይላል። መነቃቃት

[102] Harold G. Grimm(ed) (1957), *The Ninety-Five Theses ot the Disputation Concering the value of Indulgences: Luther's Works*, Fortress Press Vol.31 USA

ምንድነው? ጂ. አይ ፓከር የተባለ የነገረ መለኮት ሊቅ መነቃቃት የሚለውን ጽንሰ ሳባብ እንዲህ አስቀምጧል፡- *መነቃቃት ማለት እግዚአብሔር በመንፈሱና በቃሉ አማካይነት በመንፈስ ሙት የሆኑትን ሰዎች በክርስቶስ ወደሚገኝ ሕያው እምነት የማምጣትና በእምነት ደክመው የተገኙትን ክርስቲያኖች ውስጣዊ ሕይወት የማደስ ተግባር ነው*[103] ብሏል። ጂ. አይ ፓከር በመቀጠልም የመነቃቃትን አውነተኛ ምልክቶች እንዲህ ሲል ይገልጻል፡-

> *የእግዚአብሔር ሀልዎትና የወንጌል በተሰየና በአስደናቂ መንገድ መገኘት፣ ወደ ንስሐ ሰዎችን የሚመራ መንፈስ በተሰየ ሁኔታ መገኘት፣ የክበረውንና ይቅር ባዩን ክርስቶስ ክልብ በመነጨ ስሜት ብዙዎች መቀበል፣ የጸጋው ሥራ መጠንከርና መፋጠን፣ ብዙ የሚሰወጡ ሰዎች መኖር በማኅበራዊ አንቅስቃሴ አውድ ውስጥ የግለሰባዊ መነቃቃት መኖር*[104] ብሏል።

ኢያን ሙሬይ ደግሞ የመነቃቃትን ምንነት ሲገልጽ፡-

> *በመነቃቃት ውስጥ የሚፈጸሙ ነገሮች በተአምራዊነታቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተለምዶ ከሚፈጸሙት ልምምዶች የተለዩ አይደለም፣ ልዩነቱ መጠኑ እንጂ ዓይነቱ ላይ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ ግን መንፈሳዊው በጎ ተጽዕኖ ሰፊ ነው። የኃጢአተኝነቱ ስሜት ጥልቅ ነው። ሌሎችም ስሜቶች እንዲሁ። ነገር ግን ይህ ሁሉ የተለመደው የክርስትና ሕይወት ማጠናከሪዎች ናቸው*[105] ብሏል።

በአገራችን ኢትዮጵያ በተለይ በፐሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የመንፈሳዊ መነቃቃትና እንቅስቃሴን እንደ ተሐድሶ የመቁጠር አካሄዶች ጎልተው ይታያሉ። ስለዚህ ለጥቂት ጊዜና ለተወሰኑ ወቅቶች ብቻ መጥቶ የሚሄድ መነቃቃት ካልመጣ ምንም ማድረግ እንደማይችሉ የሚያስቡ አብያተ ክርስቲያናትን ለመቁጠር ያዳግታል። ከዚህም የተነሣ ብዙ አገልጋዮች መነቃቃት እንዲመጣ ብዙ ድንጋይ ሲፈነቅሉና ከወንጌል ይልቅ መነቃቃትን ሲሰብኩ ይስተዋላሉ። መነቃቃት ወንጌል እንዲሮጥ መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል እንጂ በራሱ ወንጌል አይደለም። መነቃቃት ወሳኝና አስፈላጊ ነው። መነቃቃት እንዲሆን በትጋት መፀለይ፣ ማስተማርና የሰዎችን መንፈስና ልብ በቃሉ ማዘጋጀት ምንም ስህተት ባይኖረውም ያለ መነቃቃት ወንጌልን መስበክ፣ ነፍሳትን መማረክ፣ ደቀመዝሙር ማድረግ፣ ዓለምን በወንጌል መድረስ እንደማይቻል ማሰብ ገና የሚመጣው መነቃቃት እንጂ በልባችን ያለው የቃሉና የመንፈሱ ኃይል፣ የጸጋውና የወንጌል ኃይል፣ ከታላቁ ንጉሥ የተሰጠን ታላቁ ተልዕኮና የተሰጠንን የልጅነት ሥልጣን ዋጋ ቢስ አድርጎ እንደ መቁጠር ነው።

---

[103] መንግሥቱ ማሞ(መጋቢ)(2011)፣ እና ታየች አርጊቾ (ተርጓሚዎች)፣ *ታላቁን ተልዕኮ መፈጸም*፣ ቲ-ኔት ኢንተርናሽናል፣ ገጽ 62

[104] ዝኒ ከማሁ ገጽ 62

[105] ዝኒ ከማሁ ገጽ 63

የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ዞር ብለን ስንመለት የቤተ ክርስቲያን ዕድገትና የወንጌል ስርጭት በዓለም ላይ እኛ መነቃቃት ብለን በምናስበው መንገድ ብቻ አልተካሄደም፤ አይካሄድምም። ለምሳሌ፦ በዓለማችን በወንጌል ታላቅ ተጽዕኖ በማምጣት ተጠቃሾች የሆኑ እንደ ማርቲን ሉተር፣ ጆን ዊክሊፍ፣ ጆን ሑስ፣ ዊሊያም ኬር፣ ዴቭድ ሊቪንግስተን፣ ወደ አፍሪካና ወደ ኢትዮጵያ ወንጌልን ይዘው የመጡ ታላላቅ የወንጌል ሚሲዮናውያን ዛሬ እኛ ያለ መንፈሳዊ መነቃቃት (ልዩ ትንቢት፣ መገለጥ፣ ድንቅና ተምራት፣ መፋት፣ በልሳን መናገር ወዘተ...) ምንም መሆን አንችልም፤ ብለን በምናስበው መንገድ የተገለጡ አልነበሩም።

እንዲሁም በአገራችንም ቀደሚት የወንጌል አርበኞች መካከል አባ አስጢፋኖስ፣ አለቃ ታዬ፣ በ1880ዎቹ ዓ.ም ከኤርትራ ወደ ወለጋ በመዝለቅ በቦጂ የመጀመሪያ የመካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ከጣሉት አንዱ የሆኑ ቄስ ገብረስታፖስ፣ በዚያው ወቅት ወንጌልን አንግበው ከምጽዋ ጅማ ለመድረስ ሰባት ዓመት የፈጀባቸው የአባጂፋር ጸሐፊ በመሆን ወንጌልን በትልቅ ጫናና ተጽዕኖ ሥር ሆነው የሰበኩ ንጉሤ ታሹ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ተነሥተው ትልቅ የወንጌልን ሥራ ሲሠሩ እየታሰሩ፣ እየተደበደቡ፣ እየተወገዙ በብዙ መቶ ሺዎች የሚገመቱ ነፍሳትን የማረኩና የዛሬ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንን መሠረት ከጣሉት አበው መካከል ዳና መጃ መዳሮ፣ አቶ ሹጉጤ ዳዳ፣ አባ ጎሌ ነነሞ ተጠቃሾች ሲሆኑ እነዚህ ሁሉ ሕይወታቸውን የለወጠውን የወንጌል ቃል በመታዘዝ በወለዱት የእምነት እርምጃ አሁን ላለንበት ታላቅ መንፈሳዊ መነቃቃት ምክንያት ሆነዋል። እኛ ዛሬ የምናጣጥመው መነቃቃት ዓይነት ለእነርሱ ባዕድ ነበር። ቢሆንም አንፀባራቂና ታላላቅ ሥራዎችን ለቃሉና ለመንፈሱ በመታዘዝ ሠርተዋል። የፈጠሩት የጽድቅ ተጽዕኖ ከጫካ እስከ ቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት በኃይል ተሰምቶ ነበር። ለእኛም የበረከት መንገድ ሆነዋል። ከእነርሱ ጋር የነበረውና ከእኛ ጋር ዛሬ ያለው ጌታ ያው ቢሆንም አሠራሩ ልዩ ልዩ ነው። በብዙ መነቃቃት የታጀበው፣ የድምፁን ያህል ተጽዕኖ ፈጣሪ መሆን ያቃተው፣ ለራሱ ድሎት እንጂ ስለሌላው ደንታ ቢስነት ጎልቶ የሚታይበት፣ ቃል ሳይሆን ገበያ ተኮር የአገልግሎት ዘይቤ ግራ ያጋባው የዘመናችን ክርስትና የመንፈሳዊ ጉልበትና የሕይወት ጥንካሬ በዚህ ምድር እንደ ተነሡ ቀደምት አበው እንዳልሆነ ብዙዎች ይስማማሉ።

በእግዚአብሔር ሀልዎት ውስጥ የሚኖር፣ የእግዚአብሔር የቃሉ እውነትና የመንፈሱ እሳት በልቡ ላይ የሚቀጣጠል አማኝ የመነቃቃት ምክንያት ለመሆን ይገለጣል እንጂ መነቃቃትን አይጠብቅም። ትናንት ውሃን በማናወጥ ይፈውስ የነበረው ጌታ ዛሬ ቃል ብቻ በመላክ የውሃውን መናወጥ ለዘመናት ይጠብቁ የነበሩ ብዙዎችን እየፈወሰ ነው። ዛሬ በዓለማችን ታላቅ መነቃቃት እየተካሄደባቸው ካሉት አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ እንደሆነች ብዙዎች ይስማማሉ። ከዚህም የተነሣ ታላላቅ የአምልኮ አዳራሾች ጠበውን የመንግሥት ትልልቅ የስብሰባ ማዕከላት፣ አደባባዮችና ስታዲየሞች በመነቃቂያ ኮንፍራንሶችና በመዝሙር ፌስቲቫል ተሳታፊዎች ተጨናንቀዋል። የድሮ ጸሎት ቤት ሕንፃዎች ስለጠበቡን በዓይነቱ ልዩና

ታላላቅ ዘመናዊ ሕንፃዎች በውድ ዋጋ በአገራችን በከተማና ገጠር በመገንባት ላይ ተጠምደናል። እንደሚገባው ወንጌልን ማሮጥ ቢያቅተንም ሕንፃዎችን በመገንባት ትልቅ ወድድር ላይ ያለን እንመስላለን። ሕንፃን መገንባት ምንም ስህተት ባይኖረውም የዳኑትን ደቀመዝሙር ከማድረግና ወንጌልን ይዘን የምንወጣበት አቅማችንን ከገታ አደገኛ ነው።

በእግዚአብሔር ቃል እንደሚገባ ያልተሠሩ ሰዎች *"ለእግዚአብሔር ቤት"* በመሥራት ሥራ ላይ የተጠመዱ ይመስላሉ። አሳዛኙ ነገር ጌታ በሞት በትንሣኤው የተሠራው የቅዱሳን አንድነት ፈርሶ በእኛ እጅ የተሠራውን ቤት የማይቀበል መሆኑ ነው። መቅደም ለሚገባው ቅድሚያ አንሰጥ። አሁን በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የሚያስፈልገው ሌላ መነቃቃትን ቁጭ ብሎ መጠበቅ ሳይሆን ባለፉት ሃያ ዓመታት መነቃቃት ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተው በአባልነት ላይ ብቻ የተገቱ አባላትን ደቀ መዝሙር የማድረግ ተሐድሶ ነው። በገጠርና በከተማ በቤተ ክርስቲያን ያለው አብዛኛው ሕዝብ ለዛሬ ምኞቱ ፈጣንና አቋራጭ መፍትሔ ሰፈ መሳይ "መገለጥ"ና "ትንቢት" ካልሆነ በስተቀር የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚገባው መማርና ማስተማር *"የመንፈሳዊ ኋላ ቀሮች"* የዱሮ ሥራ መስሏል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በተለይ ወንጌላውያኑ በአፋጣኝ በቃሉ ወደ እውነተኛና ሥር ነቀል ተሐድሶ ካልተመለሱ ሕልውናቸው በአደጋ ላይ ነው። አሁን የሚያስፈልገንን ተሐድሶ የሚያመጣ ቃሉ እንጂ ከቃሉ አፈንጋጮች የሚያደርገን "መነቃቃት" አይደለም። ያረጁና ያፈጁ አሠራሮችን ለማስወገድ ተሐድሶ ብቸኛ መልስ ነው። በቃሉ የታነፁ ለትውልዱ ደራሽና ተደራሽ አሠራሮችን ለመቀመር በመንፈሳዊ ዕውቀት የተገሩ፣ ባሕሪያቸውና ስጦታቸው ያልተፋታ፣ ደባል ስብዕና የማይታይባቸው፣ በቃሉና በመንፈሱ ታደሰው ተሐድሶን የመምራት እምነትና ድፍረት ያላቸው መሪዎች መቅደም አለባቸው። *"ባጥሪ ሳይሆን በጥረት"* የአገልግሎት ቢሮዎችን የመውረር አካሄዶችን በተጠሩ፣ በታጠቁ፣ በተቀቡና በተማሩ ሰዎች የመተካት ተሐድሶ ይጠይቃል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሳቸውን ኪስ ለማደለብ፣ በጸጋ ስጦታ ስም ሆዳቸውን ለመሙላትና ዝናቸውን ለማስራጨት የሚራኮቱትን ወደ ቃሉ መንገድ የመመለስ ተሐድሶ ያስፈልጋታል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከብዙዎች ቀድማ የተቀበለችውን የወንጌል መልዕክት ለአፍሪካና ለዓለም ለማቀበል መንፈሳዊ አቅም አላት።

ሁለንተናዊ ተጽዕኖ የምታመጣ ቤተ ክርስቲያን ሆና ለመገለጥ የአመለካከት፣ የአቋምና የተግባራዊነት ተሐድሶ ይጠይቃል። እውነተኛ ተሐድሶ ወደ እውነተኛ መነቃቃት ይመራናል። የነገረ መለኮት ምሁራን መነቃቃት በፈለግነው ጊዜ የምናመጣው ጉዳይ ሳይሆን የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ሥራ ውጤት እንደሆነ ይስማማሉ። የወንጌል አደራ እግዚአብሔር በፈለገው ጊዜ በሉአላዊ አሠራር በሚያደርገው መነቃቃት ብቻ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በተሰጠን የልጅነት ሥልጣን፣ በጸጋው፣ በኃይሉ፣

በቃሉና በመንፈሱ ጉልበት ሁሌም እንድንፈጽመው የተሰጠን አንገብጋቢና ጊዜ የማይሰጥ ተልዕኮ እንደሆነ መዘንጋት የለበትም። ከእኛ የሚጠበቀው መታዘዝ ነው። ክርስቶስ ባለበት ሕይወት ውስጥ ሁሌም መነቃቃት አለ። በተገለጠላቸው የቃሉ እውነት ላይ ቆመው ተሐድሶን ለማምጣት በራሳቸው ጨክነው የሚወጡ ቅዱሳን ለዘመናት እየጠበቅነው ወዳለነው ታላቅ መነቃቃት ያስገቡናል ብዬ አምናለሁ።

የመነቃቃትና የተሐድሶ ልዩነት በንፅፅር

ባቢ. ግልያም እንዲህ አስቀምጠዋል፦

ቤተ ክርስቲያን አካል እንደሆነች አስቡ፣ በዚህም መሠረት መነቃቃት ለልብና ለአዕምሮ ሕይወትና መታደስን እንደሚያመጣ ነው። ተሐድሶ ደግሞ የአካል አጥንቶችን የሚገጣጥም ነው። መነቃቃት የእምነትን፣ እሴቶችንና ውሳኔዎችን ለውጥ ያስገኛል። ተሐድሶ ደግሞ የባሕሪ፣ የአመቃቀርና የትጥቅ ለውጥ ያመጣል። መነቃቃት ንጹህ ውኃ ወደ ውኃ ጉድጓድ መጨመር ነው። ተሐድሶ ደግሞ በውኃው ጉድጓድ ላይ ያሉትን ቀዳዳዎች መድፈን ነው። ይሁን እንጂ በመነቃቃትና በተሐድሶ መካከል ያሉትን ሁለት ዋነኛ ልዩነቶች ማብራራት ሰፊ ጊዜ ይወስዳል። በመነቃቃትና በተሐድሶ መካከል ያለው የመጀመሪያ ልዩነት መነቃቃት በግለሰብ ደረጃ ሊጀምር የሚችል ሲሆን ውጤታማ ተሐድሶ ግን ከላይኛው የሥልጣን መዋቅር፣ ከቤተ ክርስቲያን አመራር ወይም ከአንድ ቤተ እምነት ይጀምራል።[106]

መነቃቃት	ተሐድሶ
በልብ፣ በአዕምሮና ሕይወት ላይ ያተኩራል	በሰውነት አጥንት ላይ ያተኩራል
በእምነት እሴቶች ላይ መወሰን	ባሕርይንና መዋቅርን ይመለከታል።
በውኃ ጉድጓድ ንፁህ ውኃ መጨመር	በውኃ ጉድጓድ ውስጥ ያሉ ቀዳዳዎችን መድፈን
በግለሰብ ደረጃ ይጀምራል	ከሥልጣን መዋቅር አናት ላይ ቢጀምር ውጤታማ ይሆናል

ምንጭ፦ ቲ-ኔት ኢንተርናሽናል ኮርስ 1 መጽሐፍ[107]

[106] ዝኒ ከማሁ ገጽ 64
[107] ዝኒ ከማሁ ገጽ 64

ተሐድሶ ወይም ሞት!

ተሐድሶ ወይም ሞት! አንዲት ቤተ ክርስቲያን የቃሉንና የመንፈሱን ተሐድሶ እንቢ ካለች ሞትን መርጣለች። የሞተች ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የሕያው አምላክ ወኪል መሆን አትችልም ማለት ነው። እርሱ በኃይሉ እንደገና በቃሉና በመንፈሱ ትንሣኤን ካልሰጣት በስተቀር። በቃሉና በመንፈሱ የማትታደስ ቤተ ክርስቲያን ሕያው ብትመስልም ሙት ናት። የቤተ ክርስቲያን አዳሽ የቤቱ ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን፣ ቅዱሳን ከእርሱ ጋር አብረው ይሠራሉ። ያለመታደስም ሆነ ተሐድሶ ለቤተ ክርስቲያን ባዕድ አይደለም። ሁለቱም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይታወቃሉ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልሳን የሆነው ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ፣ ከ1960ዎቹ መጨረሻ አንሥቶ እስከ መስከረም 1982 ዓ.ም ድረስ ግለሰቦች አስተያየታቸውን የሚያንጸባርቁበት *"የተሐድሶ ዐምድ ለውይይት"* እና *"የተሐድሶ ዐምድ ለውይይትና ለትምህርት"* በሚሉ ተለዋዋጭ ስያሜዎች የሚጠራ የተሐድሶ ዐምድ ነበረው።[108]

ተሐድሶ ጠሪ የኢትዮጵያ የቤተ ክርስቲያን ነባራዊ ሁኔታ

በዚህ መጽሐፍ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ስያሜ በኢትዮጵያ ያሉ አብያተ ክርስቲያናትን ሁሉ ያጠቃልላል። ከዚህ በታች በአገራችን በብዛት የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ያሉበትን ተሐድሶ ጠሪ ገጽታዎችን ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር እያስተያየን ዛሬ ያሉበትን ሁኔታ እንመለከታለን።

"መጽሐፍ ቅዱሳችንን ክፍተን ባነበብን
ቁጥር፣ ተሐድሶ በልባችን ይካሄዳል።" ጆርጅ ጆን

ክርስትና ለአውሮፓ የመንፈሳዊ ሕይወት ለውጥ ምክንያት ከመሆን ባሻገር ለእንዲስትሪው አብዮት፣ ለሥራ ፈጣሪዎች የአዕምሮ ልማትና *"የዲሞክራሲ መመንደግ"*[109] ዐቢይ ምክንያት እንደሆነ በተጨባጭ ጥናት ከተረጋገጠ ምዕተ ዓመታት ተቆጥረዋል። ኮች የተባለው ምሁር ስለዚህ

[108] *ዝኒ ከማሁ 64*

[109] ዊሊያም ተምፒል የተባለ የእግሊአብሔር ሰው በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ለዲሞክራሲ ማበብ መሠረት እንደነበረች ሲናገሩ፦ *"church meetings of the dissenting groups were a fruitfull training ground for democratic procedures"* Temple. Christianity and Social Order. S.C.M. Press, p 67 *በአሜሪካም* የዲሞክራሲ ማበብ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ነበረች፦ *"town church meetings and thus a chif source of democratic practice in America"* Paul K. The Heritage of the Reformation, p 213

ሲናገር፦ *"ክርስትና የምዕራባውያን ሥልጣኔ አቅጣጫ አመልካች የሆኑ የፍልስፍና፣ የሳይንስና የጥበብ መሠረት ነው."*[110] በማለት እማኝነቱን ሰጥቷል። 6ኛው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ጆን ኩዊንስ አዳምስ /1825 – 1829/ የአሜሪካ መንግሥት መሠረት ከክርስትና ጋር ያለውን ቁርኝት ሲገልጽ፦ *"የአሜሪካ መንግሥትና የክርስትና መሠረተ-ሐሳቦች በማይፈታ ቋጠሮ ተሳስረዋል። በፍጹም አይለያዩም። እኛ ያገኘነውም ትልቁ ድል ይህ ነው"* ብሏል። በታሪክ የተረጋገጠው ሁለንተናዊው የአውሮፓ የለውጥና የዕድገት ምክንያቶች አንዱ የ16ኛው ክፍለ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ እንደ ሆነ የታሪክ ምሁራን ይናገራሉ። ይህም የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ለአንድ አገር ሁለንተናዊ ዕድገትና ለውጥ ወሳኝ መሆኑን ያመልክታል። በአገራችን በተቃራኒው በተለይ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ "ተሐድሶ" የሚለው ቃል በአሉታዊነት መፈረጁ ለለውጥ ያለንን ጥላቻና ጫፍ የነካ ፍርሃት ተጠቂ እንደሆንን ያመለክታል። ይህም በታሪክ ፊተኞች የነበርነውን የኋለኞች ሁሉ ኋላ አድርጎናል።

ደቡብ ኮሪያ ከዛሬ መቶ ዓመት በፊት ከድህነቷ የተነሣ *"የአይጥ ጉድጓድ"* የሚል አሉታዊ ስም ዛሬ *"የነብር ኢኮኖሚ"* በሚለው ተለውጧል። ክርስትና አዕምሮአቸውን ብሩህ ከማድረግ አልፎ ባለራእይ እንዲሆኑ፣ በኅብረተሰባቸው ሁለንተናዊ ለውጥ በማምጣት ረገድ የአንበሳውን ድርሻ እንደ ያዘ ኮሪያውያን በገሃድ መስክረዋል። ኤ.ኤ በ2003 ሮበርት ባሮ እና ራሄል ማክክሊሪ የተባሉ የታወቁ የሀርቨርድ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚ ሊቆች የደቡብ ኮሪያ ዓለምን ያነጋገረ ሕልም መሳይ የኢኮኖሚ ፍንዳታ ለማጥናት ሰፊ ጊዜ ከወሰዱ በኋላ በመጨረሻው፦ *"ክርስትና በደቡብ ኮሪያ የኢኮኖሚ ዕድገት ቀዳሚ ሚና ተጫውታል"* *"Christianity has played a major role in South Korea's economic success."*[111] በማለት በአንዳንድ ኢኮኖሚስቶች ዘንድ ያስተቻቸውን ምስክርነት ለመስጠት ተገደዋል።

የቻይና ኮሚኒስት መንግሥት የኢኮኖሚ አማካሪና የኢኮኖሚክስ ፕሮፌሰር ዞህ ቺአ የምዕራባውያንን የኢኮኖሚ ምጥቀት ምስጢር እንዲያጠና በቻይና መንግሥት በታዘዘው መሠረት ጥናቱን ሲቋጭ፦ *"2000 ዓመታት በዓለማችን ላይ የተገኘው ዐቢይ ለውጥና ዕድገት ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው"*[112] በማለት ጥናቱን ይፋ አድርጓል። በዚህም በኢአምላካዊ ፍልስፍና ተወልዶ ያደገው፣ ከዛሬ 60 ዓመታት በፊት የወንጌል ሚሲዮናውያንን ከአገር ያባረረ፣ ቅዱሳንን ወደ ወህኒ በማውረድ አብያተ ክርስቲያናትን በገሃድ የዘጋው ኮሚንስት የቻይና መንግሥት ከራሱ ያራቀው ኢየሱስ ለምዕራባውያን የዕድገታቸው መሠረት እንደሆነ በጥናት የተደገፈ እውነት በራሱ ምሁር ሲነገረው ዱብ ዕዳ እንደሆነበት ይነገራል።

[110] *Koch, Carl(1994), The Catholic Church: Journey, Wisdom, and Mission. Early Middle Ages: St. Mary's Press*

[111] *http://www economics harvard edu/faculty/barro*

[112] *Beyond Economy China's Transformation with the Cross Dr. Peter Zhao Xiao _ TimSchraeder.com htm*

የኮሚኒዝም ርዕዮተ ዓለም መናኸሪያና መሪ የነበረች ሶቪዬት ኅበረት እንደ ቅርጫ ከ15 አገሮች በላይ የተበጣጠሰችው እና ለ70 ዓመታት የሕልም እንጀራ ዓለምን ሲያበላ የቆየው የኮሚኒዝም ርዕዮተዓለም የወደቀው በዓይናችን ፊት ነበር። ኮሚኒዝም በዓለማችን ከሁለት ቢሊዮን *(ከመቶ 40%)* በላይ የሰዎች ልብ ከመማረክም አልፎ መመሪያቸው ቢሆንም የተከታዮች ብዛት ከሞት አልታደገውም። ኮሚኒዝም ወድቆዋል ዓለም ከኮሚኒዝም የአመለካከት ተጽዕኖ ገና ነፃ አልወጣችም። የሶቪዬት ኅበረት ባለሥልጣናት በኮሚኒዝም ውድቀት ማግስት በአምላክ የለሽ ፍልስፍና የተጠመቀው የሶቪዬት ሕዝብ የሞራል እሴት በማጣት እንደጠፋ በገሃድ ተናግረው ነበር።[113] ይህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ለአገርና ለአገር መሪዎች አስፈላጊነቱን ያመለክታል።

የተቀየጠ ክርስትናችን

ወደ አገራችን ስንመጣ *"ክርስትናችን"* ሃይማኖተኞች አደረገን እንጂ ሕይወታችንን አልለወጠም። ክርስትናችን አሉታዊ የረሃብና እርስ በርስ የጦርነት ታሪካችንን፣ ለዘመናት ሲዋዥቅ የኖረውን ፖለቲካችንን፣ ዝንተ ዓለም ታማሚ ሆኖ የዘለቀ ኢኮኖሚያችንንና ለእርስ በርሳችን ያለንን የተንሻፈፈ አመለካከቶቻችንን አልሞረደም። ምክንያቱም በአብዛኛው የክርስትናን ስም እንጂ ወደ ልባችን ክርስቶስ እንዲገባ አልፈቀድንለትምና። ከመጽሐፍ ቅዱሳዊነት ይልቅ እንደ አገራዊ ባሕል የሚወሰድ "ክርስትናችን" የዕድሜውን ያህል ለምድሩም ሆነ ለሰማዩ እንደሚገባው አልጠቀመንም። ወደ ቃሉ ክርስትና ለመመለስ ካልፈቀድን ከእንግዲህም አይጠቅመንም። ክርስትና በኢትዮጵያ ያረጀ ቢሆንም አላደገም። ሌሎች በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ ብቻ ክርስትናቸውን መሥርተው ተለውጠው ዓለምን ሲለውጡ የኛ *"ክርስትና"* በአዋልድ፣ በገድላት፣ በድርሳናትና በአሪታዊ መልኩ በዓለም አቀፋዊ ደረጃ አነጋጋሪ መሆኑ ጥያቄን በውስጣችን ማጫር ሲገባው መጽሐፍ ቅዱስ በማይደግፈን ልዩ መሆን የሃይማኖት ትምክህተኞች ያደረገን ይመስላል።

ክርስትናችን ከአገር በቀል ባሕላዊ የአምልኮ ሥርዓትና ፍልስፍና ጋር ተቀይጦብናል። እስራኤላውያን ቅይጥ አምልኮ በማካሄድ እግዚአብሔርን ያሳዝኑ እንደነበር ማለት ነው። *"እግዚአብሔርንም ይፈሩ ነበር ከመካከላቸውም ለኮረብታ መስገጃዎች ካህናት አደረጉ። በኮረብታውም መስገጃዎች ይሠው ነበር። እግዚአብሔርንም ሲፈሩ ከመካከላቸው እንደፈለሱት እንደ አሕዛብ ልማድ አምላካቸውን ያመልኩ ነበር"* *(2ነገ.17:32-33)* ይላል። በዚህም እግዚአብሔርም በሕዝቡ ድርጊት አዝኖ ሲመክር፦ *"ከእናንተም ጋር ያደርግሁትን ቃል ኪዳን አትርሱ፤ሌሎችንም*

[112] Pat Robertson (1990) The New Millennium, USA, p.5

ለማልክት አትፍሩ። ለምላካችሁን እግዚአብሔርን ፍሩ፤ እርሱም ከጠላቶቻችሁ ሁሉ እጅ ያድናችኋል" (2ነገ.17:38-39) ሲል እንመለከታለን። ሕዝቡ እግዚአብሔርን አልሰሙትም ቅይጥ ሃይማኖታቸውንም አላቆሙም (2ነገ.17:40)። እግዚአብሔርም ለዚህም ይቀጣቸው ዘንድ ለ70 ዓመት ምርኮ አሳልፎ ሰጣቸው። ሕዝቡ በዙሪያቸው የነበሩ የአረማውያን የአምልኮ ባሕል ይከተሉ እንደነበር ቃሉ ይናገራል (ኤር.25:5-11)። ቅይጥነት በእስራኤላውያን ላይ የእግዚአብሔርን ቁጣ እንዳመጣ እኛም ዛሬ ከተለያየ አገራዊ፣ ሙንደራዊና ባሕላዊ አመለካከቶችና ሥርዓቶች ጋር ክርስትናን በመቀየጣችን በሃምድራችን ትልቅ መንፈሳዊ ግራ መጋባት ለምዕተ ዓመታት ተንሰራፍቶ የጨለማና የጥፋት መሠረቱን አጠንክሯል።

ዊልበር አዶኖቫን የአፍሪካ ክርስትና ትልቁ ችግር ቅይጥነት እንደሆነ አመልክቶ ይህም የሆነበት ምክንያት ሲገልጹ፦ በአፍሪካ ባሕልና ሃይማኖት ስለ ተቆራኙ የአፍሪካ ክርስትናን ከነባሩ ባሕላዊ እሴት ጋር የመቀየጥ ባሕርይ ጎልቶ እንደሚታይበት በጥናታቸው አመልክተዋል። በመጨረሻም፦ *"ቅይጥነት (syncretism) ኃጢአት ነው"*[114] ብለዋል። ለመሆኑ የአገራችን ክርስትና ከስንት ነገር ጋር ተቀይጦ ይሆን? የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ከአዋልድ፣ ከአገራዊ ትውፊት፣ ከድርሳናትና ከገድላት ጋር ተቀይጦብናል። በተአምርና በተረቶች ላይ ተመሥርቶ ነገሥታቶችን ለማወደስ በግብዣውያን አርቃቅነት በደብተራዎቻችን የተዘጋጀው የኢትዮጵያ ዐዜዎች ታሪክ ከእሥራኤላዊነት ታሪክ ጋር ተቀይጦብናል። ይህም ትክክለኛ ማንነታችንን በመረዳት ላይ ትልቅ ግራ መጋባትን ፈጥሮብን ኢትዮጵያውያን የነበሩ ነገሥታቶቻችን የእስራኤላውያን እንደሆኑ በታሪካዊ ጥናት ያልተረጋገጠውን "የንግሥተ ሳባን"[115],[116] ተረት ፈጥረው ሲያውጁ እኛም የእነርሱን ውሸት እንደ ገደል ማሚቶ ሲናስተጋባ ኖረናል። ይህም በራሱ ማንነት የማከራ ሕዝብ አድርጎናል። ከዚህም የተነሣ እውነት መሳይ መላምታዊ አገራዊ

[114] ግርማዊ ቡሽ(ተርጓሚ) (1996)፤ *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና በአፍሪካውያን ዕይታ*፤ ኤስ. አይ ኤም ማተሚያ ድርጅት፤ ገጽ 364

[115] ማማን ሙሳ አዳሙ ከመቀሌ ዩኒቨርሲቲ *ያቀረቡት ጥናት በከፍል እንዲህ ይነበባል*፦ "The claims of the legend of Queen Sheba do not help us to concretely understand the foundation of the Ethiopian ruling house because it cannot beproven historically. The legend seemed to have been used to legitimize theclaims by the ruling house to be descendants of Abraham, the chosen people,in order to remain in power in perpetuity. This has affected the identity of theruling house and the entire people of Ethiopia, their heritage, politicalstanding in Africa as well as their being the probable evolutionary home ofthe whole of mankind." Mamman Musa Adamu *(2009)*, Africa Research Review, The Legend of Queen Sheba, the Solomonic, *Dynasty and Ethiopian History: An Analysis An International Multi-Disciplinary Journal Vol. 3 (1), p.480*

[116] *የፐሮፌሰር ታደሰ ታምራት በእንግሊዝኛ ስለ ንግሥተ ሳባ ተረት እንዳለ ቀርቧል*፦"Like all legends they serve the question of establishing an identity, very strong identity. I myself believe this is a post Christian legend…it developed only after the Ethiopians started to have direct contact with the books of the Bible, from about the middle of the 6th Century… And then it became a very important constitutional device and an act of faith. I cannot publicly speak against it in front of the patriarch of the orthodox church, for example, because then he would say, you are no longer an Orthodox Christian. In the days of Emperor Haile Selassie you couldn't speak against the tradition because it would be treasonable to talk against it." *http://www.bbc.co.uk/worldservice/africa/features/storyofafrica/8chapter2.shtml*

ውሸት ፈጥረን ማውራት መለያችን ሆኖ የቀረ ይመስላል። ዛሬም የንግሥተ ሳባ ተረት በታሪካዊ ጥናት መሠረት የለሽ መሆኑን የአገራችን ታሪክ ምሁራን ሳይቀሩ ደጋግመው ጥናታቸውን እየነገሩን የተቀየጠውና የተሳሳተው ታሪክ ዛሬም በብዙዎች እንደ እውነት ይቆጠራል። ወንጌልና ጥቅም፣ ክርስትናና ሃይማኖት፣ ባሕልና ክርስትና፣ ሆድና ወንጌል፣ የወንጌል ሰባኪና በወንጌል የሚነግድ ተቀይጦብናል። መጽሐፍ ቅዱስ ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ብቸኛ ቤዛና አዳኝ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ በግልጽ እየተናገረ በአገራችን ተቀይጦብን ቤዛና አዳኝ *"ማርያም"*[117]፣ *"ሚካኤልም"*[118] ወይም ሌሎችም ሊሆኑ እንደሚችሉ አገራዊ መጽሐፎቻችን ያለ አንዳች እፍረት ይሰብኩናል። በእጃችን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ እውነቱን በግልጽ ቢናገርም ቃሉ ላይ ቆመን የተቀየጠውን ለማጥራት አቅም ያለን አይመስልም። ለምሳሌ፦

አስማት በክርስትና ጥላ ሥር

በአገራችን በእግዚአብሔር ቃል ፈጽሞ የተወገዙ አስማት፣ ድግምትና ጥንቆላን የሚያስፋፉ ድርሳናት "አገልጋዮች" በቤተ ክርስቲያን አካባቢ እንዳሉ የአደባባይ ምስጢር ነው። ከብዙዎቹ መካከል ድርሳነ ጊዮርጊስ የቅዱሱ የእግዚአብሔር መልአክ ጊዮርጊስ በአስማት ኃይል ስለ ሠራው ሥራ ሲናገር፦

> *አንተ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ በእነዚህ <u>አስማት</u> ኃይል ሰባ ነገሥታትን በዳድያኖስ ፊት እንደ ደመሰስካቸው የእኔንም ጠላቶች እንደ እነርሱ ደምስሳቸው (ቱላዳን ዘቅዳሜ ገጽ 183)* ለመሆኑ ጊዮርጊስ በአስማት ኃይል ሰባ ነገሥታትን እንደገደለ መጽሐፍ ቅዱስ ጽፎታል እንደ? የቅዱሱ እግዚአብሔር መላእክና አስማትን ምን አገናኘ? የእግዚአብሔርን መልአክ ሰዎች ጠላቶቻችንን ደምስሳቸው ብለው መላክ ይችላሉ እንደ? ይህ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አሳብ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በአስማት ስለመሥራቱ፦
>
> *እነዚህን <u>አስማቶች</u> ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚካኤል ክንፍ ላይ ጻፋቸው፣ በእነዚህም አስማቶች ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ ጨለማን ተጎናጽፎ ወደቀ* (ድርሳነ ሚካኤል ገጽ 62)፣

መጽሐፍ ቅዱስ ዲያብሎስ በልቡ ትዕቢት እንደወደቀና ከሚካኤል ጋር ጦርነት ገጥሞ ተሸንፎ ከሰማይ ወደ ምድር እንደ ተጣለ እንጂ በአስማት እንደወደቀ አይናገርም (ራእ.12:7-10)። ኢየሱስንና አስማትን ምን አገናኘ?

[117] ማርያም አዳኝ እንደሆነች በመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ቃል የሌለ ሲሆን በተአምረ ማርያም ለመቁጠር የሚያዳግቱ ጥቅሶች የማርያምን አዳኝነት በግዛድ ይናገራሉ። ወንጌልና ተአምረ ማርያም ተቀይጦብናል።

[118] የመስከረም ሚካኤል ዜ.ቅ፦ "መላዕክት፣ ጻድቃንና ሰማዕታት ካላከበርናቸው ዋስ ጠበቃና ቤዛ ሊኖረን እንማይችል ይናገራል" ማክበር የተገባ ሆኖ ሳለ በደሙ የገዛንና የዋጀን የሞተልን ቤዛችን ኢየሱስ የት ሄዶ ነው እነርሱ ቤዛ የሚሆኑልን?

መልአኩ ገብርኤል ወደ ማርያም በተላከ ጊዜ ማርያም እንዳትደነግጥ የሚያደርግ አስማት ተጠቅሞ እንደነበር ድርሳን ይናገራል፦

ግዕዝ፦ *"መድንኤል፣ ሕያውታኤል፣ አውካኤል፣ ተርቡታኤል፣ ግኤል፣ ዝኤል፣ ቡኤል እሉንተ ቃላት ዘነገሮ እግዚአብሔር ለቅዱስ ገብርኤል ሊቀ መላዕክት ለመ ተጸብኦ ለዲያቢሎስ ወለመ አብሰራ ለቅድስት ድንግል ማርያም ከመ ኢትደንግጽ..."* *(መጽሐፈ ቱላዳን ገጽ 196)።*

ትርጉም፦ *"ገብርኤል ዲያብሎስን በተጣላ ጊዜና (ዳን.10:10-21) ማርያምን ባበሰረ ሰዓት(ሉቃ.1:26-36) እግዚአብሔር እነዚህን አስማቶች ለቅዱስ ገብርኤል ነገረው"*[119]

ግዕዝ፦ *"ኦ ኢዮብ ሀበኒ ሀብተ ወሚመተ ወከሥት ንግደትየ ወአርትዕ ፍናትየ" (መል.ኢዮብ ገጽ 29)*

ትርጉም፦ *"ኢዮብ ሆይ ሀብት ስጠኝ ንግዴን ግለጥ መንገዴንም አቅና"*

> *"አቤቱ በዚህ ስምህ በዚህ አስማት ኃይል ፍጥረት ሁሉ የኔን ፈቃድ ብቻ ይፈጽሙ ዘንድ ልቦናቸውን ምታው፣ አቅልጠው፣ ግደለው"(መጽሐፈ ቱላዳን ገጽ 3-8)* ይህ ሰይጣናዊ እንጂ የክርስትና ትምህርት እንዳይደለ ልቡ የበራ የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል የተረዳ ሰው ሁሉ ያውቀዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአስማት፣ በድግምት፣ በጥንቆላ በፍጹም እንደማታምን የታወቀ ነው። ይህን የምንለው መሠረቷ የእግዚአብሔር ቃል ስለ ሆነ ነው። ከላይ እንደተመለከትነው በዘመን ብዛትና ቆይታ በውስጧ ያሉ አንዳንድ ድርሳናት፣ ካህናት፣ ደብተራዎች፣ መሪጌቶች በእግዚአብሔር ቃል የተወገዙና በቤተ ክርስቲያኒቷም ተቀባይነት የሌላቸውን አስማት፣ ድግምት፣ ጥንቆላና መስተፋቅር በስፋት እንደሚያራምዱ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ቀሲስ ደረጀ ገዙ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተወለዶ እንዳደገ፣ በገዳም እንዳሳለፈ፣ የዲቁናንና የቅስና ማዕረግ እንደተቀበለ፣ በቤተ ክርስቲያኒቷ ሥርዓት ጋብቻውን እንደፈጸመ፣ በአንድ ትልቅ ገዳም የስብከተ ወንጌል ዋና ኃላፊና አስተማሪ ሆኖ እንዳገለገለ፣ በዘመናዊ ትምህርትም ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተመርቆ በወሎ ዩኒቨርሲቲ መምህር ሆኖ እንደነበር ግለ ታሪኩ ያወሳል። ቀሲስ ደረጀ ገዙ በኦርቶዶክስ በአገልጋዮች ዘንድ ስለተንሰራፋው ጥንቆላ ሲናገር፦

> *የተንኮል ትምህርት ማለት ጥንቆላ ወይም መጻሐፍ ገለጣ፣ ኮከብ ቆጠራ፣ ሥር መማስና ቅጠል መበጠስ በዚያ አጠራር ጥበብ ...አንደ ግዴታም ነው፤ ምክንያቱም እርስ በርስ ጠብ ይኖራል ያን ጊዜ እራስህን ለመከላከልም ሆነ ያለፈ ነገር ለማደረግ ለመርታት ትንሽም እንኳ እንዳልተማርክ ከተሰማ መጫወቻ ያደርጉሀል፤ በተቃራኒው ከታወቀ ትከብራለህ። ለድርድርና በቀላሉ ወደ እርቅ ትገባለህ ስለዚህ ሁኔታው አስገዳጅ ነው ለመማር፤*[120] ብለዋል።

[119] ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 96

[120] ቪዥን ቅጽ 1 ቁጥር 2 ጥር-የካቲት 2004 ገጽ 5

መሪጌታ ሙሴ መንበሩ በጎጃም ምድር እነብሴ ሣር ምድር በሚባል ወረዳ እንደተወለደ ይናገራል። በቅዳሴ በሰባት ደብሮች እንዳገለገለ[121] በአብነት ትምህርት ቤትና በገዳም ለቤተ ክርስቲያንቷ አገልግሎት የሚያበቃ መንፈሳዊ ትምህርት እንደቀሰመ ግለ ታሪኩ ያወሳል። ወደ ወንጌል ብርሃን ከመምጣቱ በፊት እንዴት ወደ ጥንቆላ ሥራ እንደገባ ሲናገር፦

> *የጥንቆላን ሥራ ከብዙ ካህናት ካሰባሰብኩ በኋላ ወደ ተግባሩ ተሰማራሁ፤[122]...ከስድስት ዓይነት አጋንንት ጋር ቃል ኪዳን የፈጸምኩት እኔና ወደ እኔ የሚመጡትን አስጠንቋዮች በሰይጣን ሥራ የተሳካልን ሰዎች እንድንሆን በማሰብ ነበር።[123]...ሁሉንም የጥንቆላ እንቅስቃሴዬን በዚህ መጽሐፍ ገልጬ አልጨርሰውም[124]* ብሏል። መሪጌታ ሙሴ ጥንቆላ፣ ድግምትና አስማት ከየት እንዳገኘ ሲናገር፦ *...ንጹሃን ልጆችን በማግባባትና በማሳመን የአጋንንት ሕብረት እንዲኖራቸው የሚያደርጉ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያናችን መምህራን፣ ቁላውሰት፣ ዲያቆናት አገልጋዮች ናቸው ...ይህ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የታቀፈቻቸው የመናፍቃን መሪጌቶች አስተምህሮ ነው*[125] ብሏል።

ነገሩ ከላይ የተመለከትናቸው የኦርቶዶክስ "ቄስ"ና "መሪጌታ" እንደሆኑ እንደሚናገሩት ከሆነ ቤተ ክርስቲያኒቱ እነዚህን የሳቱና ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮን በማስፋፋት ምድሪቷን ከእርግማን በታች የጣሉ ጠቋሮች፣ አስማተኞችና ደጋሚዎች ወደ እውነተኛ ቃል የመመለስና በእነርሱ የተደረሰ ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር የሚጣረሱ አደገኛ ድርሳናትን ለይታ በገሃድ በማውገዝ የማቃጠል ትልቅ ሥራ ይጠብቃታል። ተሐድሶ ማለት ይህ ነው። እግዚአብሔር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በዚህ ነገር ከቃሉና ከመንፈሱ የሆነ መለኮታዊ አቅም፣ ራስን የማየት፣ እግዚአብሔር በሚለው አቅጣጫ እርምጃ እንድትወስድና በወንጌል ለዓለም በረከት እንድትሆን ለተሐድሶዋ እንጸልይላት እንደቃሉም የምገባንን በትጋት እናድርግ። እግዚአብሔር መተተኛና አስማተኛ በሕዝቡ መካከል እንዳይኖሩ ከልክሏል፦ *"በያዕቆብ ላይ አስማት አይሠራም፣ በእስራኤል ላይ ምዋርት የለም"(ዘኁ.23:23)።"መተተኛይቷ በሕይወት እንድትኖር አትፍቀድላት" (ዘጸ.22:18)* በማለት በዚህ ክፉ ሥራ ላይ በተሰማሩ ሰዎች ላይ የሞት ብያኔ ሰጥቷል። በብሉይ ኪዳን አስተማተኞች የአሕዛብ ነገሥታት አማካሪዎች

[121] ዝኒ ከማሁ፣ 21

[122] *ዝኒ ከማሁ ገጽ 37፤* መሪጌታ ሙሴ የጥንቆላውን ሥራ ከየትና እንዴት እንዳገኘ ሲናገር፦ "እኔ በዚያ መጥፎ ዘመን ከስንት አጋንንት ጋር እንደተዋረስኩ (ቃል ኪዳን እንዳደረኩ) ልንገራችሁ። ወይም እንደ ፈጸምኩ ልግለጽላችሁ። (1) የዛር መንፈስ ተዋርሶ(ቃልኪዳን) (2) ምስሀበ ቅዱሳን አጋንንት ተዋርሶ (ቃል ኪዳን) (3) ያየር ጴጥሮስ (ኩማኤል) ተዋርሶ (ቃል ኪዳን) (4) ሕልመ ዮሴፍ የጋኔን ተዋርሶ (ቃል ኪዳን) (5) አፈ ህዳን የጋኔን ተዋርሶ (ቃል ኪዳን) (6) ሕልመ አንደርቢ የጋኔን ተዋርሶ። እነዚህ ሁሉ የተለያዩ መናፍስቶች ቢሆኑ ሁሉም የክፋት ሠራዊቶች ናቸው። ከእነዚህ መካከል ሦስቱን በገዳም ውስጥ በመነኮሳት በኩል ስዋረስ ቀሪዎቹን ሦስቱን ደግሞ ከገዳም ውጭ በመሪጌቶች (ደብተራዎች) በኩል ነበር የተዋረስኩ። በገዳም አንዳንድ ጠንቋይ በሆኑ መነኮሳት በኩል የተዋረስኳቸው አጋንንቶች፦ ምስሀበ ቅዱሳን፣ ሕልመ ዮሴፍ፣ የዛር መንፈስ ናቸው።" *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 34,35*

[123] ዝኒ ከማሁ ገጽ፣ 36

[124] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 39

[125] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 179

ነበሩ *(ዘፍ.41:8፣ዳን.2:2፣ዘጸ.7:11-22)*። እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ኖኹም ቦታ እንዲኖራቸው አልፈቀደም። በአዲስ ኪዳን አስማተኞች ወንጌልን ሰምተው ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ ስለሆነው ነገር ሉቃስ እንዲህ ብሎ መስክሯል፦*"ከአስማተኞችም ብዙዎች መጽሐፋቸውን ሰብስበው በሰው ሁሉ ፊት አቃጠሉት"(የሐዋ.19:19)*። በእግዚአብሔር ቃል አስማተኞች በሰማያዊ መንግሥት ዕድል ፈንታ እንደሌላቸው በግልጽ ተናግሯል (ራእ.9:21፣22:15)። መሪጌታ ሙሴ መንበሩ *"ከመጋረጃው በስተጀርባ"* በሚለው መጽሐፉ አስማትና ጥንቆላ በቤተ ክርስቲያናቸው አካባቢ ምን ያህል እንደተንሰራፋ ሲገልጽ፦

> *በገዳሙ ውስጥ አንዳንድ የአጋንንት ማህበርተኞች አግኝቻለሁ። የአጋንንት ማህበርተኞች የሚባሉት አስማተኛ ዲያቆናት፣ ቁላውሰትና መምህራን ናቸው።[126]...ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስሜ አጋንንትን ታወጣላችሁ ብሎ ያዘዘውን ቃል በመተላለፍ ይህንኑ አስማታቸውን ከውዳሴ ማርያምና ከድርሳነ ሚካኤል፣ ከመልክዓ ማርያምና ከመዝሙረ ዳዊት ወዘተ...ጋር በቃል በማጥናት አንዳንድ ጠንቋይ ካህናት መነኮሳት በየጸበሉ የሚደግሙት ይህንን ነው። ሕዝባችንም የተያዘው በዚሁ አስማት ነው። ሰያዘው በሽታ መፍትሔ ለማግኘት በየጸበሉ ሲንከራተት የማያውቀውን ቃላትና ቋንቋ በሚሰገድለት ታቦትና ለቤተ ክርስቲያን ስጦታ አድርጎ በሚያቀርበው ዕጣን የእግዚአብሔር ሰዎች በሚባሉ ነገር ግን የሰይጣን ግበረ አበር በሆኑ ጠንቋይ ካህናት እየተደገመበት ሕዝባችን በበሽታው ላይ ሴላ በሽታ እየጨመረ ይመለሳል[127]...እኛ የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች እንደ መሆናችን መጠን መልዕክት አለን። መልዕክታችንም በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ በአገልግሎት ላይ የሚገኙ ጠንቋይ ካሕናት ላይ እርምጃ መወሰድ አለበት ቤተ ክርስቲያኒቱ ይህንን እርምጃ የማታደርግ ከሆነ ስሟ እንደ ጎደፈ ይቀራል። እውነቱ በተገለጠ ቁጥርም ልጆቿ ሳይቀሩ ያቀልሏታል* የሚል ነው።[128] ብሏል።

ነገሩ መሪጌታ ሙሴ እንደተናገረው ከሆነ የጥንቆላና የአስማት ሥራዎች የቤተ ክርስቲያኒቱ ስም ከማጎደፍና በልጆቿም ከመቅለል ባለፈ የቤተ ክርስቲያን ራስ በሆነው በክርስቶስ ፊት ተጠያቂነት እንዳለም መዘንጋት የለበትም። እንደ ተባለው አስማት፣ ድግምትና ጥንቆላ በቤተ ክርስቲያን ባሉት አገልጋዮች በኩል ከተሰራጨ ለዚህች አገር ትልቅ አደጋ ነው። የኋላ ቀሪነታችን፣ የድህነታችን፣ የረሃብተኝነታችን፣ የስደተኝነታችን፣ የመጎደርተኝነታችንና የተገለጠ የቃሉን እውነት በመግፋት የራሳችንን አገራዊ እውነት ለማቆም የመጣሪ አደገኛ አካሄዶቻችን መሠረትና ምንጩ በክርስትና ስም ድግምት፣ አስማትና ጥንቆላ በማስፋፋታች ነው፤ የሚሉ ብዙዎች ናቸው። ለዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶ ብቸኛ መፍትሔ ነው። ኢትዮጵያ ሆይ! ከራስሽ እውነት ወደ ቃሉ እውነትና ብርሃን ተመለሺ! ሁላችንም ወደ እግዚአብሔር ቃል እንመለስ!

[126] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 30-31

[127] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 58

[128] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 86-87

ክርስትና ሌሎችን ማኅበረሰባቸውንና አገራቸውን እንዲለውጡ የሥራ ፈጣሪ ሲያደርጋቸው "ክርስትናችን" በአብዛኛው ሥራን እንደ እርግማን አስቆጥሮን ረሃብ እየጠበሰን በዓል አክባሪዎች ብቻ አድርጎናል። ይህም ዕድገታችን እረፍት የሚነሣቸው ግብዣውያን ለራሳቸው የማይመሩበትን ዘመን ዘለቅ የሃይማኖት መሪነታቸውን ተጠቅመው እውነትን በተረት ቀይጠው ያቀበሉንና እስከዛሬም እንደ ልዩ መገለጥ የሚታሰቡ ድርሳናት ውጤት እንደሆነ የተረጋገጠ ቢሆንም ከዚህ ቅይጥነት ለመውጣት ዛሬም አልነቃንም። *"ድርሳነ ሚካኤል የተባለ መጽሐፍ ባለበት አገር ረሃብ፣ ቸነፈርና በሽታ ሊይኖርም"*[129] የሚል አደገኛና ገዳይ መርዝ ስላመንን የድርሳናት ጎተራ ቢንሆንም ችግራችንን አወሳስበው ግራ ከማጋባት ያለፈ አንዳች አልፈየዱልንም። በዓለም ላይ የሰልጣኔ ማዕከልና ቀዳሚ በሆነች አገር እየኖርን ዛሬም መታወቂያችን ረሃብ፣ ድህነት፣ በሽታ፣ ስደት፣ ጥላቻና መንደርተኝነት ነው። ይህ ሁሉ ሆኖ ልብ ሰባሪው ጉዳይ ዛሬም በኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ድርሳናትና ገድላት የተማረከው ልባችን ጠያቂ ለመሆን ያለመፍቀዱ ነው።

ዶክተር በቀለ ሻንቆ ለትራንስፎርሜሽናል መሪነት በቤከ ዩኒቨርሲቲ የፒ.ኤች.ዲ ማሚያ ባቀረቡት ጥናታቸው፡-

> *የኢትዮጵያ ክርስትና ከፍተኛና ለስደናቂ የቁጥር ብዛት ቢያስመዘግብም እንደሌሎቹ በአገሪቷ ማህበረሰብና ኢኮኖሚ ላይ ተጠቃሽ ውጤት ለሳስመዘገበም*[130] ብለዋል።

"ሰው ምራቁንና ሃይማኖቱን ይወዳል" አንድ የአገረ አዋቂ እንዳሉት ስሙን እንጂ ውስጡን በትክክል ለማናውቀው አገር በቀል *"የክርስትና"* ሃይማኖታችን ጥብቅና ለመቆም መቁረጣችን መልካም ሆኖ ሳለ አስደንጋጭ የሚሆነው ክርስትናችን በመጽሐፍ ቅዱስ ከተገለጠው የክርስቶስ ትምህርት ጋር በብዙ መጣረሱ ነው። ያልታደሰውና በብዙ አስተምህሮዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር ፊት ለፊት የሚላተመው አገር በቀል ክርስትናችን፣ የዚህች ታላቅ ጥንታዊ አገር ውድቀት እንዱ ምክንያት ነው። ይህን የምለው ላለፈው ታሪካችን እንደንቆጭ ወይም ሌላ ሰጥ-አገባ ለመጫር ሳይሆን የክርስትናችን ማዕከል የክርስቶስን ቃል በማድረግ ለተሐድሶ እጅ ለእጅ ተያይዘን በመቆም ለአገራችን ሁለንተናዊ ለውጥ የበኩላችንን እንፀባራቂ ሚና በአንድነት ለመጫወት እንደገና እንድንነሣ ነው። ለዚህ ግራ መጋባትና ዘመን ዘለቅ ቀውስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶ መልስ ነው። በኢትዮጵያ ያሉት ቤተ እምነቶች በሙሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶ የግድ ያስፈልጋቸዋል። ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ታድሳ የሁለንተናዊ ተሐድሶ ፋና ወጊ ካልሆነች እንቅፋት መሆኗ ይቀጥላል።

[129] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 89

[130] Bekele Shanko Mamiru,*(2012), Emerging Leader Initiative (ELI), A Manual for Developing Transformational Leaders in the Ethiopia Context A Final Project Submitted to The Faculty in Candidacy For The Degree of Doctor of Transformational Leadership p viii*

የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ላይ በጥንታዊነት ከሚታወቁት አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዷ ናት፤ በቀዳሚነቷም በአገር ውስጥ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንደ እናት የምትጠቀስና የኢትዮጵያ ታሪክ አካል የሆነች ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ናት። ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ለማጥናት የሚነሣ የትኛውም አካል ከመንግሥት ጋር በጥምረት ለብዙ ምዕተ ዓመታት አገርን ትገዛ ስለነበረችው ስለዚህች ቤተ ክርስቲያን ለመጥቀስ ብቻ ሳይሆን ለማጥናት ግዴታ ውስጥ ይገባል።

ያለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የኢትዮጵያ ታሪክ ብቻውን ሙሉዕና ትርጉም ያለው አይሆንም። የቀደምት ሥልጣኔ ባለቤት የሆነችው አገራችን የራስዋ ፊደል፣ ቁጥርና የዘመን ቀመር ባለቤት ያደረጓት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቀደምት አበው እንደሆኑ ታሪክ ምስክር ነው። ለዚህ ድንቅ ሥራ አድናቆትና ክብር ልንቸራት ይገባል። ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ስላሉ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ለመናገር ስንፈልግ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መጀመር የግድ ይለናል። እንደ አክሱም ሐውልት፣ እንደ ላሊበላና የዐፄ ፋሲል ግንቦች የጸና ታሪክ ባለቤትና የአገር ኩራት ስለሆነችው ስለዚህች ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። **እግዚአብሔር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ይባርካት፤** በማለት ለእርሷ ያለኝን ትልቅ ፍቅርና አክብሮት ስገልጽ ራሴን እንደ ዕድለኛ በመቁጠር ነው።

በዚህ መጽሐፍ ከ4ኛው እስከ 21ኛው ክፍለ ዘመን የዘለቀና የአስደናቂ ታሪክ ባለቤት የሆነችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና ከእርሷም በኋላ በዚህ ምድር የተገለጡ አብያተ ክርስቲያናትን በስሜት ላይ በመንተራስ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል፣ በምክንያታዊነትና በጥናት የተደገፈ መረጃን በማቅረብ በቃሉና በመንፈሱ እንዲታደሱ መለኮታዊ ጥሪ ቀርቧል። ተሐድሶ ለምን? ለሚለው ጥያቄ መልሱ በምድራችን ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በተሐድሶ ጠሪ ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ መገኘታቸው ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተሐድሶ ጠሪ ሁኔታ ውስጥ እንዳለች መነገር ከተጀመረ ምዕተ ዓመታት እንደተቆጠሩ ድርሳናት ያወሳሉ። በቤተ ክርስቲያን የእውነት ሚዛኑ የሰዎች ድጋፍና ተቃውሞ እንዳልሆነ ሁሉ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ተሐድሶ እንደሚያስፈልጋት ወይም እንደማያስፈልጋት ወሳኙ የቤቱ ባለቤት የሆነ ቃሉና ቤተ ክርስቲያኒቷ ያለችበት ተጨባጭ ሁኔታ እንጂ የችሎት ውሳኔ፣ የክርክርና የእጅ ብልጫ ነው ብዬ አላምንም። ቤተ ክርስቲያን በሰዎች ክርክርና በችሎት ውሳኔ አልተመሠረተችም፣ አትመራም፣ አትታደስምም።

ቤተ ክርስቲያኒቷ ተሐድሶ እንደሚያስፈልጋት ለማረጋገጥ የትናንት ታሪኳና ዛሬ ያለችበት ተጨባጭ ሁኔታ ምን ይመስላል? በብዙ ተጋድሎ ከአንድ ሚሊኒየም ተኩል በላይ ሃይማኖቷን ጠብቃ ረዥም ዕድሜን ባስቆጠረች ቤተ ክርስቲያን በውስጧ ምን እየተካሄደ ነው? ለሚሉ ጥያቄዎች በቤተ ክርስቲያኒቷ ተወልደው፣ አድገው፣ ተምረውና ለአገልግሎት የበቁ አገልጋዮች ከጻፉት የመንደርደሪያ ሐሳቦች እዚህ ጋ ብጠቅስ መልካም ነው። ቀሲስ መዘምር ወልደ ሩፋኤል የአቃቂ መንበረ ሕይወት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን የስብከት ወንጌል ክፍል ኃላፊ[131] *"ፈውስ ለቤተ ክርስቲያን"* በሚል መጽሐፋቸው፦

> *በጣም የሚገርመው ነገር፣ በዓለማችን ለሠራሮች ሁሉ በፍጥነት እየተቀየሩና እየተለወጡ ባለበት ዘመን ላይ ሆነን፣ የእኛ ቤተ ሰዎች ግን በአረጀ አስተሳሰብ ተጠፍረው፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከዘመን ጋር እንዳትራመድ አድርገዋታል[132] እኛ ትናንት በቁጥር ብዙ ነበርን፣ ዛሬ ብዙ ወገኖቻችን አንድ አንድ እያሉ ፊታቸውን ወደ ሌሎች የእምነት ተቋማት አዙረዋል። በቅርቡ ይፋ በሆነ መረጃ እንኳ፣ የምዕመናኖቻችንን ቁጥር 7,000.000 (ሰባት ሚሊዮን) ቀንሷል።[133] ሥልጣንን በሞኖፖል አንቆ በመያዝና የእክክኝ ልክክልህ አሠራር በቤተ ክርስቲያናችን የቆየና የተለመደ ነው። እንዲህ ዓይነቱ የአረጀ አሠራር ካልተቀየረ ደግሞ፣ ለውጥና ዕድገት በተለምር አይመጡም[134] ከዲቁና እስከ ጵጵስና ያሉት መንፈሳዊ ክንውኖች ሁሉ፣ ያለ ሙስና የማይታሰቡ እየሆኑ መምጣታቸውን በዚህ መንገድ ያለፉ ሁሉ አንደበታቸውን ሞልተው እየተናገሩ ነው[135] ,በዘረኝነት መንፈስ የሚናጡ አብያተ ክርስቲያናት ቁጥር ቀላል አይደለም። ...ከአለቃው (አስተዳዳሪው) ይጀምርና ቀስ እያለ ወደታች (ወደ ካህኑ) ይሠርፃል። 'ሸዋ፣ ወሎ፣ ጎጃም፣ ጎንደር፣ ትግራይ...' ተብሎ በስምና በአካባቢ ያልተፈረጀ አይኖርም። እንደተባለውም ዘረኝነትን የሚያራግቡ መንደርተኞች ጥቂት አይደሉም። በየተዛወሩበት ደብር ሁሉ የአገር ለው ብቻ የሚጎትቱ፣ ሌላውን አገልጋይ በጥርጣሬና በሥጋት የሚያዩ፣ የቤተ ክርስቲያን ዕዳዎች ሞልተዋል።[136]* በማለት ቤተ ክርስቲያናቸውን የገጠማትን ውስጣዊ ተግዳሮቶች ይፋ አድርገዋል።

አባላት ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ወደ ፕሮቴስታንት ለምን ይፈልሳሉ? ለሚለው ጥያቄ የሁለት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች መልሳቸውን ብጠቅስ መልካም ይመስለኛል፦ ሊቅ ማእምራን ዲበ ኩሉ *"የቃሉን እውነት ካለማስተማራችን የተነሣ ሕዝባችን ወደ ፕሮቴስታንቱ እየፈለሰ ነው."*[137] ብሎ ምክንያቱን ካቀረበ በኋላ ቤተ ክርስቲያኒቷ ተሐድሶን የማትፈቅድ ከሆነ ሕልውና የማጣት አደጋ ከፊት ለፊቷ

[131] *መዘምር ወ/ሩፋኤል (ቀሲስ) (2005 ዓ.ም) ፣ ፈውስ ለቤተ ክርስቲያን፣ ገጽ 29*
[132] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 29*
[133] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 72*
[134] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 31*
[135] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 35*
[136] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 55*
[137] *ሉፈ 2005 ዓ.ም ገጽ 84*

እንደተጋረጠባት፦ *"አሁን ባለው ፍጥነት ከቀጠለና ተሐድሶን አንቀበልም የሚል ግትር አቋም ከያዝን በጥቂት ዓመታት ውስጥ ቤተ ክርስቲያናችን ሕልውናዋን ማጣቷ አይቀሬ ነው."*[138] በማለት ከመቶ ዘጠና አምስቱ ሕገወጥው ክርስቲያኖች የነበሩና የታላላቅ ዓለም አቀፍ ተጽዕኖ ፈጣሪ ቀደምት የነገረ መለኮት ምሁራን ያፈለቁ ግብዕና ሊቢያ የመሳለሉ አገራት ከለላ ሃይማኖት እንደተወረሱ ካልነቃን ለእኛም አይቀርልንም በማለት ሳናቋርጡን ይፋ አድርጓል።

መምህር ብሩክ ገበረ ሊባኖስ ተስፋዬ ከሕፃንነቱ ጀምሮ ዕድገቱ በቆሎ /አብነት/ ትምህርት ቤት እንደሆነ፣ የቅዱስ ያሬድን ጸዋትው-ዜማዎች፣ አቋቋምና ቅኔን እንዳጠናቀቀ፣ በመጨረሻም በቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሚሰጠውን የትርጓሜ መጻሕፍትና ባሕረ ሐሳብ አጠናቆ በ1991 እንደተመረቀ በመጽሐፉ ተጠቅሷል። በአገልግሎትም በአዲስ አበባ ውስጥ በተለያዩ አድባራትና ገዳማት የስብከተ ወንጌል ኃላፊ ሆኖ ዘጠኝ ዓመት እንዳገለገለና አሁንም በአውስትራሊያ ቤተ ክርስቲያኒቷን በማገልገል ላይ እንዳለ ይገልጻል። መምህሩ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ወደ ሌላ እምነት ለምን ይሄዳሉ? ለሚለው ጥያቄ መልሱን ጥያቄያዊ አድርጎ መልሶአል፦

> *አሁንም ሐቁን እናውጣና ሰዎች ኦርቶዶክስን ጥለው ወደ ሌላ በረት የሚሄዱት ምክንያት ወደድንም ጠላንም ችግሩ ከላይ እስከ ታች ባለን የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮችና ሠራተኞች ችግር ምክንያት ነው። ምክንያቱ ምንድነው? ቢባል*

- *ሰባኪዎች የተባልነው የሕይወት ምግብ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል በስፋትና በጥራት እንዲመገቡ ባለማድረጋችን አይደለም?*
- *የማያጠግብና ሕይወትን የማይለውጥ ተረታ-ተረት እንዲመገቡ በማድረጋችንስ አይደለም?*
- *ብዙዎቻችን በቃላችን እንጂ በሕይወታችን ማስተማር ስላልቻልን አይደለምን?*
- *የንስሐ አባቶች የተባሉት ብዙዎቹ ዕውቀታቸው በቂ ባለመሆኑ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ሲጠየቁ ተገቢ መልስ መስጠት አለመቻላቸው እውነት አይደለምን?*
- *ዘረኝነትን በወንጌል ማጥፋት ሲገባን የዘረኝነቱ ዋና፣ መሪና ተዋናይ ሆነን ሕዝቡን በጉሙና በብሔር መለያየታችን እውነት አይደለምን?*
- *ምዕመናን በተለያዩ ድግሳ-ድግሶች ሆዳችንን ስለሚሞሉን ሲያጠፉና ሲሳሳቱ ከማረምና ከመገሠጽ ይልቅ 'እንደ እናንተ ያለ ክርስቲያን የለም!' እያልን የምንሸነግላቸው አይደለምን?*
- *ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የሚገኘውን ዘላለማዊ ደኅንነትና ዕረፍት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ገልጠን ባለማስተማራችን አይደለምን?*

[138] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 84*

- *የሰላምና የፍቅር ሰዎች መሆን ሰገባን ሰላምን፣ ፍቅርን፣ አንድነትን የምናደፈርስ ሰውን የምናስበረግግ አይደለምን? በእነዚህና በመሳሰሉት ችግሮቻችን ምክንያት ሕዝባችን ለፍልሰት ተዳርጓል፣ ስለሆነም ተጠያቂዎቹ እኛው ራሳችን የቤተ ክህነት ሰዎች ነን፣*[139] ብለዋል::

ከላይ የተዘረዘሩ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባላት የፍልሰት ምክንያቶች ከሆኑ ተሐድሶ ለዚህች የአገር ኩራትና እናት ለሆነች ቤተ ክርስቲያን አያስፈልግም ማለት እንዴት ይቻላል? ተሐድሶ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሞትና ሕይወት ጉዳይ እንደሆነ ከላይ ያሉ ተጨባጭ ሁኔታዎች ያመለክታሉ :: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያለመታደስ ለቀለመ ብዙ አገራዊ ችግሮች መሠረት መሆኑን አንዘንጋ::

ኢመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በዓለማችን በዕድሜ ጠገብነቷ ብቻ ሳይሆን ለአሥራ ስድስት ምዕተ ዓመታት የራሷንና የዚህችን አገር ታሪክ ከነገሥታት ጋር እጅና ጓንት ሆና እንዳቆየች ይታወቃል:: ይህ ትልቅ ነገር ነው:: በተቃራኒው ደግሞ ግልጽነት የሚጎድላቸውና ከመጽሐፍ ቅዱስ በተለይ ከአዲስ ኪዳን አስተምህሮ ጋር በፍጹም የማይሄዱ፣ ባዕድ ልምምዶችንና አስተምህሮዎችን እንደ ተሸከመች በእርሷ ውስጥ ተወልደው ያደጉና ለአገልግሎት የበቁ "ቤተክርስቲያናችን ወደ ቃሉ ተመልሳ መታደስ አለባት" ብለው ድምፃቸውን ማሰማት ከጀመሩ ምዕተ ዓመታት ተቆጥረዋል:: ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር በቀጥታ የሚጋጩና መታደስ እንዳለባቸው ከተነሡ አሳቦች መካከል ሁለቱን እዚህ ላንሳ:-

የተለጠጠ የነገረ ማርያም

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ቅዳሴ ስለ ማርያም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ያዘለ ሐሳብ እንዲህ ይነበባል:- *"...ከሌቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ የማህፀንሽ ፍሬ የተባረከ ነው:: ጸጋን የተሞላሽ ሆይ! ደስ ይበልሽ፤ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነውና..."*[140] እንደሚለው ብፅዕት የሆነችው ማርያም በታዋን ያወቀችና ጌታን በታማኝነት አገልግላ ያለፈች ታላቅ ሴት ናት:: እርሷ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት፣ ከሐዋርያቱም ጋር የነበረች፣

[139] መምህር ብሩክ ገበረ ሊባኖስ ተስፋዬ *(2005 ዓ.ም)* ፣ *የሰው ያለህ፣* ገጽ 435-336

[140] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ፊደል አሳታሚ፣(ዓ.ም) የለውም፣ ገጽ 104

በእምነቷ፣ በቅድስናዋ፣ በብዕዕናዋና በመታዘዝዋ ለቅዱሳን ሁሉ ታላቅ ምሳሌ ናት:: ከዚህም የተነሳ ልትወደድ፣ ልትደነቅ፣ ልትመሰገን የሚገባት ከሌቶች መካከል ሞገስ ያገኘች ልዩ ሴት በመሆኗ ክብር ይገባታል:: *"ክብር ለሚገባው ክብር ስጡ" (ሮሜ.13:7)* ያለው ቃሉ ነውና:: ማርያም እግዚአብሔርን በመታዘዝ ለሁላችንም ትልቅ ምሳሌነትና በመሥዋዕትነት ጌታን ካገለገሉት ቅዱሳን መካከል ቀዳሚ ተጠቃሽ ናት:: እንወዳታለን፤ እናከብራታለን ማለቱ የተገባ ሲሆን ያለቦታዋ በግድ እንዳናስገባት ግን እንጠንቀቅ:: *"ከተጻፈው አትለፍ"* (1ቆሮ.4:6) የሚለውን ቃል እናስተውል::[141]

ቀደሰ ዓለማየሁ ሞገስ ደረሶ ስለማርያም በአገራችን ጫፍ የነካ የማርያም አስትምህሮ የተናገሩትን ከመጥቀሴ በፊት ስለማንነታቸው ያሉትን ልጥቀስ:- *"እኔ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በዘራቸው በሃይማኖታቸው፣ በብቃታቸው፣ በትንቢታቸው፣ ከታወቁ ቤተሰቦች ተወልጄ ያደግሁ"* ካሉ በኋላ ስለ አገልግሎታቸውና የሕይወት ልምዳቸው:- *"የቅኔ መምህር ሆነው መጻሕፍት ሐዲስን አንዳጠኑ፣ ዘጠኝ የተለያዩ ቋንቋዎችን አቀላጥፈው ይናገሩ እንደነበር፤ ወደ ዩኒቨርሲቲም ዘልቀው ታሪክና ቋንቋን ለጎንተው እዚያው መምህር ለመሆን የበቁ ሊቅ እንደነበሩ"*[142] ገልጸዋል:: ይህ ታላቅ ሰው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ቆመው ቤተ ክርስቲያናቸው ወደ ቃሉ እንድትመለስ እና በሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም ላይ የሚታዩ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አካሄዶችን በመሞገት ይታወቃሉ:: ቀደሰ ዓለማየሁ *"ሁሉም ሁሉን ይወቅ"* በሚለው መጽሐፋቸው ማርያም በትውልድ ሁሉ ምስጋና እንደሚገባት ከገለጹ በኋላ በቤተ ክርስቲያናቸው ስለ ማርያም የተለጠጠና ወንጌልን ስለ ጋረደው አስትምህሮ ሲናገሩ:-

> *ለማርያም የታዘዘው ምስጋና ከአምላት አንድ ነው:: በእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን በጣም በዛና ወንጌል እንዳትሰብክ ከለከለ:: በሰዓታቱ፣ በማሕሌቱ፣ በኪዳኑ በቅዳሴው ሁሉ እሷ ናት፤ ወንጌል እናንብ የተባለ እንደሆነ ታምራ ሳለች ይባልና የወንጌሉ ነገር ይረሳል:: ስለዚህ የእኛ ቄሶች ከተአምረ ማርያም ውጭ በማሕሌት ኪዳን በሰዓታት ተወጥረው ስለተያዙ ይህን የጠቀስነውን ሊያዙ ስለሃይማኖት ባያውቁ አይፈረድባቸውም:: መልሳቸውም ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋራ የማይስማማው ገድላንድልና ተአምረ ማርያም ነው:: የእኛ ማርያም ወዳጆች ማርያም በሥላሴ ላይ መፈንቅለ መንግሥት ያደረገች አስመሰለው ሥላሴን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን ትተው ቅዱሳት መጻሕፍት እንዳይሰበኩ ማድረጋቸው ነው እንጂ*[143] ብለዋል::

ኢየሱስ አገልግሎቱን አሀዱ ብሎ ሲጀምር *"የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ"(ማቴ. 4:17)* በሚል ግልጽ ስብከት እንጂ የእናቱ ስም በማወጅ አልነበረም፤ ሐዋርያትም ስሟን በየቀኑ መስበክ እንዳለባቸው አላዘዟቸውም:: ሐዋርያት በስብከታቸው፣ በትምህርታቸውና

[141] ፀጋአብ በቀለ (2005 ዓ.ም) *ባለራእይነት ኢትዮጵያ ግን ለምን? ርኖቡት አታሚዎች*

[142] ዓለማየሁ ሞገስ ደረሶ(ቀደሲ) (1987 ዓ.ም)፣ *ሁሉም ሁሉን ይወቅ*፣ ገጽ 10

[143] ዝኒ ከማሁ ገጽ 155

በመጽሐፋቸው ትኩረታቸው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እንጂ በማርያም ላይ በፍጹም አልነበረም። ኢየሱስ ሐዋርያትን ሲልካቸው፦ *"ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ለፍጥረት ሁሉ ወንጌልን ስበኩ" (ማር.16:15)* በማለት ወንጌል መስበክ/ማወጅ እንዳለባቸው በግልጽ ተናግሯል። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ሲናገር፦ *"እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን"* (1ቆሮ.1:23) ካለ በኋላ ከዚህ ውጭ የሰማይ መላዕክት እንኳ ቢሆኑ *"ሌላ ወንጌል የሚሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን" (ገላ.1:8-9)* በማለት ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ትታ ሌላ ነገር የምትሰብክ ከሆነ የሚጠብቃት እርግማን እንጂ በረከት እንዳልሆነ በግልጽ አስቀምጧል። በአገራችን በግልጽ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚጋጩ፣ ለማርያም የሥላሴን ቦታ የሰጡና በቅርብ ጊዜ እንደ ወንጌል በአንዳንድ ቡድኖች ያለ ክልካይ እየተሰበኩ ያሉ አሳዛኝና አስደንጋጭ አሳቦች መካከል፦

ሀ. "ያለ እመቤታችን ዓለም አይድንም"

ይህ የእግዚአብሔርን ቃል ካለመረዳት አንዳንዶች የሚያውጁት የተሳሳተ አሳብ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ የተረዳ ማንም ሰው ያውቀዋል። ማርያም የዓለም መድኃኒት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም የመጣበት መንገድ እንጂ መድኃኒት እንደሆነች፣ እርሷም አልተናገረችም፣ ኢየሱስም ስለ እርሷ እናትነት እንጂ መድኃኒትነት በፍጹም አልገለጸም፤ ሐዋርያትና የቤተ ክርስቲያን አበው ይህን በፍጹም አልሰበኩም፤ አልጻፉም። የማርያም እጮኛ ለነበረው ዮሴፍ መልአክ በሕልም ተገልጦለት ከማርያም የሚወለደው ልጇ እንጂ እርሷ መድኃኒት እንደሆነች አልተናገረም፦ *"ልጅ ትወልዳለች አርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ"(ማቴ.1:21)*። ሳምራውያን ኢየሱስን ካዩት በኋላ፦ *"በእውነት ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት እንደሆነ እናውቃለን"* (ዮሐ.4:42) በማለት መስክረዋል። የዓለም አዳኝ በማርያም በኩል ወደ ዓለም የመጣው እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ ማርያም እንደሆነች መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም።

ለ. "ያለ እመቤታችን ሥላሴ አይታወቅም"

ልዑሉ እግዚአብሔር (አሐዱ-ሥላሴ) በፈለገው መንገድ ራሱን ካልገለጠ በስተቀር ማንም ሊያውቀው አይችልም። ያለ እግዚአብሔርና እርሱ ከፈቀደው መንገድ በስተቀር እግዚአብሔርን በትክክልና በሙላት የሚገልጥ አካልም ሆነ መንገድ በምድር አልነበረም፣ የለም ወደፊትም አይኖርም። ኢየሱስ ሲናገር *"...ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ የለም፤ ከወልድም በቀር፡ ወልድም ሊገለጥለት ከሚፈቅድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም"(ማቴ.11:27)* በማለት የአብ ገላጭ ወልድ እንደሆነ የወልድም ገላጭ አብ እንደሆነ በግልጽ ተናግሯል። ስለ ሥላሴ ስንነጋገር መዘንጋት የሌለብን ወልድ ባለበት አብና መንፈስ ቅዱስም መኖሩ ነው። ያለ ማርያም ሥላሴ

እንደማይታወቅ የእኛ እንጂ የሥላሴ ቃል አይናገርም። ዋናው መንገዱ ሳይሆን መገለጡ ነው። መንገዱን የሚመርጠው ደግሞ የመገለጡ ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔር ሉዓላዊና ውስን ያልሆነ አምላክ ስለሆነ ውስንና ደካማ ለሆነ ለሰው ልጅ በፈለገው መንገድ የመገለጥ ሙሉዕ ብቃትና ምርጫ ያለው አምላክ ነው። ስለሆነም *"ያለ እመቤታችን ሥላሴ አይታወቅም"* ማለት ቃሉን በትክክል ያለመረዳታችንንና አምላክን እንደራሳችን የመገደብ ደካማ ሙከራችንን ያሳያል። እግዚአብሔር ራሱን የሚገልጥ አምላክ ነው። ራሱን በሰው ሕሊና፣ በተፈጥሮና በቃሉ ገልጧል። በመጨረሻም ከድንግል ማርያም በተወለደው ልጁ ራሱን ገልጧል። ማርያም ወልደ ሥጋን ለብሶ ወደ ዓለም የገባበት መንገድ እንጂ የሥላሴ ማሳወቂያ ብቸኛ መንገድ እንደሆነች መጽሐፍ ቅዱስ በፍጹም አይናገርም። ማርያም እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም ያመጣበት መንገድ እንጂ የሥላሴ ማሳወቂያ መንገድ አልነበረችም፣ አይደለችም እንዲሁም መሆን አትችልም። ማርያምን የምናከብራት በእግዚአብሔር ቃል ያልተባለላትን በማለት መሆን የለበትም።

ሐ. "ሁሉ በእርሷ (በድንግል) ሆነ"

ቃሉ ያለው፦ *"ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳችም ሳንኳ ያለ እርሱ ለልሆነም" (ዮሐ.1:2)* የተባለለት የሥላሴ አንዱ አካል ለሆነውና በዚህ ክፍል *"ቃል"* ለተባለው ለእግዚአብሔር ወልድ ነው። ይህን ቃል በመግፋት ሁሉ "በእርሷ"(በማርያም) ሆነ በማለት "በእርሱ" (ክርስቶስ) የተደረገውንና በቃሉ የተጻፈውን እውነት እንዳለ ከማመን ተደናገሮ ማደናገር ለምን አስፈለገ? የተባለውን ማመን እንጂ ለእኛ እንደሚመቸን አድርገን አስተካክለን መጻፍ፣ መናገርና ማመን ከእግዚአብሔር በላይ አዋቂነታችንን ለመግለጥ ብርቱ መሻት እንዳለን ቢያመለክትም ገዛድ የሚታየው ግን ያላዋቂነታችን ነው።

መ. "የእመቤታችንን ስም የሚጠራ አያፍርም"

መጽሐፍ ቅዱስ፦ *"እነሆ የተመረጠና የከበረን የማዕዘን ራስ በጽዮን አኖራለሁ <u>በእርሱ የሚያምን አያፍርም</u>"* (1ጴጥ.2:6) ያለውን *"በእርሷ የሚያምን አያፍርም"* ብሎ መለወጥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተደረገ የድፍረት ኃጢአት ነው።

ሠ. *"ቤዛዊት ዓለም፤ ቤዛዊት ኩሉ"*

ይህ ለማርያም የተሰጣት ስም ኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛ የዓለም ቤዛ መሆኑን ለመተካት የወጣ ስም እንደሆነ ለማንም ግልጽ ነው። ኢየሱስ ብቸኛ የዓለም ቤዛ ነው(ማቴ.20:28)። ማርያም የዓለም ቤዛ ከሆነች ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ቤዛ ሆኖ መምጣት ለምን አስፈለገው? ዓለም አንድ እንጂ

ሁለት ቤዛ የላትም፤ አያስፈልጋትምም። መጽሐፉም ያለው፡- *"ባእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና"* *(ዮሐ.3፡16)*። በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛ አንድ ብቻ እንደሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲናገር፡- *"አንድ እግዚአብሔር አለና በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፡* ***እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፡ <u>ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ</u>"*** በማለት ያለውን ዘላለማዊ እውነት ከገለጸ በኋላ ሐዋርያ ጳውሎስ ስለ ራሱ አገልግሎት ሲናገር፡- *"እኔም ለዚህ ነገር አዋጅ ነጋሪና ሐዋርያ በእምነትና በእውነትም የአሕዛብ አስተማሪ ለመሆን ተሾምሁ እውነትን እናገራለሁ፤ አልዋሽም"(1ጢሞ.2፡5-7)*። በማለት የክርስቶስ ብቸኛ ቤዛነት አዋጅ ነጋሪ እንደሆነ ተናግሯል።

ሳሙኤል ፈቃዱ *"ነገረ ሃይማኖት" (ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ)* በሚለው መጽሐፋቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስለማርያም ያላትን አስተምህሮ ሲገልጹ፡- *"እመቤታችንን እናመልካትም፤ አዳነችንም እንልም"*[144] በማለት የቤተ ክርስቲያናቸውን አቋም የገለጹ ሲሆን ሊቀ ጳጳስ ኤጲፋንዮስም ሲናገሩ፣ *"ማርያምን አክብሩ፤ መመለክ ያለባቸው ግን አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ናቸው"* ያሉት ቃል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። እውነቱ ይህ ከሆነ ከላይ የተመለከትናቸውን ስለማርያም የተጋነኑና ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚጋጩ አስተምህሮዎች ምንጫቸው ከየት ይሆን? ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ እንደደረሰው በሚነገረው በመስተብቁዕ ዘመስቀል ላይ፡-

> *ኑ ለንግሢ እንሰገድ እናመሰግናትም/እንገዛለትም...ለሷ ክብርና ስብሐት ይገባታል፤ ከልጇም ጋር አምልኮና ስግደት... ለእነዚህ ሁለቱ ፍጡሮች የፈጣሪ ስብሐት ይገባቸዋል በክብራቸው ተካክለዋልና"*[145] ብለዋል።

ይህ አደገኛ የኑፋቄ ትምህርት ቢሆንም ከአምስት ምዕተ ዓመታት በላይ ዕድሜ ስላስቆጠረ ወደ እውነትነት ያደገ ይመስላል። ቀደስ ዓለማየሁ፡- *"ባቤተ ክርስቲያን አንድ ነገር እንደምንም ብሎ ሁለት ትውልድ ካለፈ ከእምነት ተቆጥሮ ይናራል"*[146] ያሉት በቆየው ብሂላችንም *"ውሸት ተደጋግሞ ሲነገር እውነት ይመስላል"* እንደተባለው በቤተ ክርስቲያን ከቃሉ ጋር በግልጽ የሚጋጩ ብዙ ውሸቶች ከጊዜ ብዛት ወደ እውነትነት ያደጉ ቢመስሉም ውሸት የትም መቼም ቢሆን ውሸት ነው።፡ የኢትዮጵያ ክርስትና አገር በቀል እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንዳልሆነ በብዙዎች አፍ ሲነገር የምንሰማው ከዚህ ዓይነት የእልህና የድፍረት ዘመን ዘለቅ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የውሸት አስተምህሮ በመንሰራፋቱ ነው። እግዚአብሔር በምሕረቱ ልባችንን ወደ ቃሉ ብርሃን ያቅናው።

[144] ሳሙኤል ፈቃዱ *(2003 ዓ.ም) ነገረ ሃይማኖት (ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ)*፤ ገጽ 207
[145] በጌታቸው ኃይሌ(ፕሮፌሰር) (ትርጉም) *ደቂቀ አስጢፋኖስ በሕግ አምላክ*፤ ገጽ 36-41
[146] ዓለማየሁ ሞገስ ደረሶ(ቀደስ) (1987 ዓ.ም) ፤ *ሁሉም ሁሉን ይወቅ*፣ ገጽ 169

ለመሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማርያምን የፈጣሪ ወንበር ላይ ለማስቀመጥ የሚታገል ዘመን ዘለቅ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የነፋቄቄ ትምህርቶችና እነዚህን መጻሕፍት የተቃወመችበትና ያወገዘችበት ሁኔታ ይኖር ይሆን? ትላንት በዘርዓ ያዕቆብ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስትምህሮ ላይ ጠንካራ እርማት ባለመደረጉ ዛሬም *"ማርያም ፈጣሪ እንደሆነች"*ና ኢትዮጵያውያን *"የማርያምን ሰም ብቻ በመጥራት እንደሚድኑ"* የሚናገሩ የነፋቄቄ ትምህርቶች በስፋው መስበክና መጻፍ ቀጥለዋል።

መምህር ኪዳነ ማርያም ጌታሁን *"መጽሐፈ ሰዓታት በመናፍቃን ኣይመዘንም"* በሚለው መጽሐፋቸው፡- *"የኢየሱስ ክርስቶስ የዘላለት(መድኃኒትነት) የተመሠረተው በድንግል ማርያም ላይ ነው"*[147] ብለዋል። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አይደለም። ኢየሱስ ያለ ማርያም ማዳን አይችልም? ማርያም የዓለም መድኃኒት የሆነው ኢየሱስ የመጣበት መንገድ ናት ወይስ የመድኃኒቱ መሠረት? ዚቅ መጽሐፍ ደግሞ ማርያምን ከዘላለት ወደ ፈጣሪነት ወንበር አሸጋግሯታል፡- *"ንዑ ንሰግድ ወንግነይ ላቲ ለመድኃኒትነ ማርያም ድንግል ለዘገብረት ብርሃናት ዓበይተ ባሕቲታ"*[148] ትርጉም *"ብቻዋን ታላላቅ ብርሃናት ለፈጠረች ለመድኃኒታችን ለድንግል ማርያም ኑ እንሰገድላት ለእርሷም እንገሠ"*[149] በዚህ መጽሐፍ አሁንም ***"ከመ ትቤዙ ነቢያተ ወጻድቃነ አማን ተወለደ ...ማርያም"*** (ነቢያትና ጻድቃንን ትቀጅ ዘንድ ማርያም በእውነት ተወለደች) የሚል ንባብ አለ። ይህ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ነው። ማርያም ፈጣሪ እንደሆነች የአገረ ደራሲያን የጻፉት የዚቅ መጽሐፍ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ በአንደኛ መጽሐፍ በአንደኛው ምዕራፍ እግዚአብሔር ማርያም ገና ከመወለዷ ከብዙ ዓመታት በፊት ብቻውን ብርሃናትን እንደፈጠረ በግልጽ ይናገራል፡-*"እግዚአብሔርም አንዲህ አለ፡-...በምድርም ላይ ያበሩ ዘንድ በሰማይ ጠፈር ብርሃናትን ይሁኑ አለ እንዲሁም ሆነ። እግዚአብሔርም ሁለት ታላላቆች ብርሃናትን አደረገ፤ ትልቁ ብርሃን በሌሊት እንዲሠለጥን አዋክብትንም ደግሞ አደረገ"* (ዘፍ.1፡14-19)።

መሪጌታ ተክለሃይማኖት ገብረሥላሴ *"ሰው የለም ወይ?"* በሚለው መጽሐፋ ኢትዮጵያውያን የማርያም ስም በመጥራት ብቻ እንደሚድኑ የጻፉው "ጉድ" እንዲህ ይነበባል። *"የኢትዮጵያ ሕዝብ ከእግዚአብሔር ለማርያም አሥራት ስለ ተሰጣት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የማርያምን ስም በመጥራት ብቻ ይድናል"* ያለው *"የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል" (ሮሜ. 10፡13)* ከሚለው ቃል ጋር በቀጥታ ይቃረናል።

ነገሩ ቀደስ ዓለማየሁ፡- *"ለኢትዮጵያ ካህናት የክርስቶስ ስም ስለማይጣፍጣቸው በመጽሐፉ ይገለጥ እንጂ ርዕሰ መሆኑ ይቅር ተብሎ ተዘሏል"*[150] እንዳሉት አገር በቀል የሆኑ ድርሳናትና ገድላትና የመጽሐፍ

[147] ኪዳነ ማርያም ጌታሁን(መምህር) *(1994 ዓ.ም)*፤ *መጽሐፈ ሰዓታት በመናፍቃን ኣይመዘመንም*፣ ገጽ 36
[148] ዚቅ መጽሐፍ በየካቲት 16 ዝክረ ገጽ 144
[149] መሪጌታ ሠረቀ ብርሃን፤ ዘወንጌል ገጽ 50
[150] ዓለማየሁ ሞገስ ደረሶ(ቀደስ) (1987 ዓ.ም) ፤ *ሁሉም ሁሉን ይወቅ*፣ ገጽ 7

ቅዱስ ዐቢይና ብቸኛ ስለሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ እንዲሁም የቤዛነት ሥራው ላይሆን ስለ ማርያም፣ ስለ መላዕክት፣ ስለ ዝክር፣ ስለ ታቦት፣ ስለ ባሕታዊነት፣ ስለ በዓላት ከድነት ጋር በማያያዝ ያለገደብ ያወራሉ። ይህም በምድራችን የተዛባ ነገረ ድነት ምን ያህል ሥር የሰደደ መሆኑንና ልባችን ያለበትን ቦታ ያመለክታል። ማስተማራችን ባልከፋ አሳዛኙ ነገር ከእግዚአብሔር ጋር እንዳለን በኩራት ታሪክን እያጣቀስን እያወራን በእጃችን ካለው ከቃሉ ርቀን መገኘታችን ነው።

በአገራችን ከወንጌል ይልቅ ማርያምን እንደ ፈጣሪ የመቁጠር፣ የማምለክና የፈጣሪን ስግደት እንደሚገባት የሚናገሩ ኢክርስትናዊ ትምህርቶች የተለመዱ ብቻ ሳይሆን የሕዝባችንን ልብ ሰርቀዋል። ጥንት ግን እንዲህ አልነበረም፦ *"15ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ለድንግል ማርያም መገዛት፣ መሰገድ፣ ስለ እርሷ መዘመርና ልዩ ልዩ በዓላቷ የሚባሉትን ማክበር በሰሚም መለመንና መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ተስፋ ማድረግ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፈጽሞ አልነበረም"*[151]

ተአምረ ማርያም-የተዛባ የነገረ ማርያም መሠረት ነው

ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና ጫፍ የነካ የነገረ ማርያም ትምህርት በምድራችን በከፍተኛ ሁኔታ የተስፋፋው "ተአምረ ማርያም" በሚባለው መጽሐፍ በኩል እንደሆነ መዛግብቶች ያወሳሉ። *ተአምረ ማርያም መጽሐፍ ለለራሱ ሲመሰክር ከአረብኛ ቋንቋ ወደ ግዕዝ በንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ተተረጉሞሁ በማለት ለራሱ ምስክርነቱን ሰጥቷል።*[152] የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት፣ የወንጌልን እውነት በግልጽ የሚቃወሙ፣ በጻጻሳትና በነገሥታት ስምምነት በቤተ ክርስቲያን ቦታ የተሰጠው ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ መጻሕፍት መካከል አንዱ በሆነው ተአምረ ማርያም ውስጥ የተጻፉና ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር በግልጽ የሚጋጩ አሳቦች ጥቂቱን እንመልከት፦

- *ለጋቢአን መድኃኒታችሁ ስለ ሆነች (መቅድም ገጽ 4 ቁጥር 33፣ ገጽ 5 ቁጥር 34)*
- *ክኃጢአት ታነጻዋለች (ተአምር 12 ገጽ 48 ቁጥር 54፣ 56፣ 62)*
- *በርሷ ላመኑት ድኅነታቸው ነች (ተአምረ ማርያም 63 ገጽ 198 ቁጥር 13:37)*
- *ባንቺ ድነት አገኘን (ተአ 12 ገጽ 44 ቁጥር 13*

[151] ክኅቱ ብርሃን መጽሔት፣ ሴኔ 2002 ዓ.ም ገጽ 13
[152] ዝኒ ከማሁ ገጽ 20

- *እመዚታችንን የዓለም መድኃኒት እንዳደረጋት አውቁ (ተአምረ ማርያም 12 ቁጥር 62)*
- *የዓለም ሁሉ መድኃኒት ሆይ (ተአምር ማርያም 83 ቁጥር 25 ተአ. 84 ቁጥር 11)*
- *"እንደ እኔ ያላችሁ ኃጢአን ወንድሞቼ ሆይ ከእንግዲህ ወዲህ 16ቱን ሕግጋት/10ሩ የኦሪት ሕግጋት ዘፀ. 20:1 እና 6ቱን የአዲስ ኪዳን ሀግጋት ማቴ.5:21-48/ ለመፈፀምና የእግዚአብሔር ባሮች መሆንን አንፈልግ/ ይልቁንም የማርያም ባሮች ለመሆን ፈጽመን እንሽቀዳደም ብዬ እነግራችኋለሁ"*[153]

በማለት የእግዚአብሔርን ቃል በመተላለፍና በማርያም ኪዳን ከእግዚአብሔር የዘለለም ቁጣ ማምለጥ እንደሚቻል ተስፋ ይሰጣል። የእግዚአብሔርን ቃል ጥላችሁ እኔን ለመታዘዝ ተሽቀዳደሙ የምትል የኢየሱስ ክርስቶስ እናት የሆነች ማርያም በፍጹም ልትሆን አትችልም። ማርያምን ለመታዘዝ የእግዚአብሔርን ቃል የግድ መጣስ አለብን ወይ? ይህ አደገኛ የኑፋቄ ትምህርት ነው። መጋቤ ጥበቤ ሰሎሞን በመጽሐፉ በዚህ ጥቅስ ላይ ተሞርኩዞ ሲናገሩ፦

> *እንግዲህ ይህ በመቃብር ተገኝ የተባለው ቃል ኪዳን የኃጢአት ተባባሪ ከሆነና ማርያም ይህ ሁኔታ ስለባሕሪዋ ተስማሚ ሆኖላት ከተባበረች እንዲሁም እግዚአብሔር ሕጉንና በኃጢአት ላይ የሚያወርደውን ቁጣ ከተወው መንግሥተ ሰማያትም የአመፀኞችና የብልጣብልጦች መኖሪያ ሆነች ምን ዓይነት ማርያም፣ ምን ዓይነት ቅዱስ እግዚአብሔር፣ ምን ዓይነትስ የምትናፍቅ መንግሥተ ሰማያት ልትሆን ትችላለች?*[154] ብለዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ *"አትሳቱ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳል። በገዛው ሥጋው የሚዘራ በሥጋ መበስበስን ያጭዳል"* (ገላ.6:7-9) ይላል። "እመቤታችንን አናመልካትም፣ አዳነችንም አንልም"[155] የሚለው ነገረ ሃይማኖት(ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ) መጽሐፍና ከላይ በተአምረ ማርያም የተዘረዘሩ አሳቦች እርስ በርሳቸው አይጣረሱም ወይ? ከሁለቱ መጻሕፍት አሳቦች የቤተ ክርስቲያኒቷን የእምነት አቋም የሚገልጠው የትኛው ነው? የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የእምነት አቋሟን የማይገልጡ የእርሷ ያልሆኑ አሳቦችን አስተምህሮዎችን እንደእሷ አስተምህሮ ተደርገው የሚሠራጩትን የእርሷ አስተምህሮ እንዳልሆኑ ካላሳወቀች ስለ አንድ ነገር እርስ በርስ የሚቃረኑ አሳባች ከአንድ አካባቢ እየወጡ ያሉ ይመስላሉ። ይህ ተሐድሶ አያስፈልገውም ወይ? ከላይ ከተአምረ ማርያም የተጠቀሱ ክፍሎች ማርያምን ሙሉ በሙሉ በኢየሱስ ምትክ ያስቀምጣሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን በፍጹም አያስተምርም። ይህ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ሙሉ በሙሉ የሚጋጭ፣ ነቢያት፣ ሐዋርያትና

[153] የኢ.ኦ.ተ ቤ/ክ፣ *ተአምረ ማርያም*፣ 3ኛ እት.ም፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤተ አዲስ አበባ፣ 1989 ዓ.ም ገጽ 47
[154] ጥበቤ ስለሞን (መ.ጋቤ)፣ *በውኑ በማርያም ማመን ይገባሃልን?* አዲስ አበባ 2000 ዓ.ም ገጽ 147
[155] ሳሙኤል ፈቃዱ *(2003 ዓ.ም)፣ነገረ ሃይማኖት (ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ)፣ ገጽ 207*

የቤተ ክርስቲያን አበው ያልሰበኩት ኑፋቄ ነው። ይህ በቃሉ መታደስ የለበትም ወይ? አዳኝ ኢየሱስ እንጂ ማርያም አይደለችም። ይህ የፕሮቴስታንቶች፣ የካቶሊኮች ወይም የኦርቶዶክሶች ትምህርት ሳይሆን ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ የዮሐንስ ራእይ የመጽሐፍ ቅዱስ ገዢና ዐቢይ ትምህርት ነው።

ክብረ ነገሥትም፦ *"ማርያም ለኢትዮጵያ ሕዝቦችም እስከ ዘላለም መድኃኒታቸው ትሆናለች"*[156] የሚል ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐሳብ ይዟል። መሪጌታ ተክለሃይማኖት ገብረሥላሴና ስለ ማርያም የተዛባ አስተምህሮ እያሰራጩ ያሉ የስህተት ትምህርት አስተማሪዎች ማጣቀሻቸው መጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን ተአምረ ማርያምና የግብፃውያን የአዕምሮ ውጤት እንደሆነ የሚነገርለት የ*"ክብረ ነገሥት"*[157] መጽሐፍ ነው። እዚህ ጋ የቀደስ ዓለማየሁን ምክር ቢጠቅስ መልካም መስሎ ታየኝ፦

> *የክርስትና እምነት መሥራች ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከእርሱ ጋር የሚጣላ ትምህርት ሁሉ ምንጩ ያው የእውነት ጠላት ዲያብሎስ መሆኑን አውቃችሁ ተጠንቀቁበት፤ ንቁበት።...የአዋልድ መጻሕፍት በቅዱሳት መጻሕፍት አይጠቀሱም፤ ቅዱሳት መጻሕፍት ደግሞ ለማብራሪያ ካልሆነ በቀር በወንጌል ላይ አይጠቀሱም። የመጻሕፍት ሁሉ ቁንጮ፤ ዘውድ፤ ከራስ ላይ የምትቀመጥ አክሊል ወንጌል ናት*[158] ብለዋል።

መምህር ብሩክ ሐምሌ 18 ቀን 1994 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉዞ አዘጋጅቶ ሙሉ አውቶብስ ሰዎችን ይዞ ወደ ቁልቢ ገብርኤል ተጉዞ እንደነበር ይገልጻል፤ አብረው ከሄዱት ጋር የህብረት ፕሮግራም አድርገው ከምሽቱ 5:00 ሰዓት ላይ ካጠናቀቁ በኋላ በአጠገባቸው ወደ ነበረው ድንኳን በማምራት የሰማውን የአንድ ባሕታዊ ስብከት እንዲህ አቅርቧል፦

[156] ለርገው ገላው(ዶ/ር)(1994)፣ ፣ ትርጉም፣ ክብረ ነገሥት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ገጽ 72

[157] **የታሪክ ሊቅ ዶ/ር ላጵሶ ጌድሶቦ ክብረ ነገሥትና ፍትሐ ነገሥት ግብፃውያ ግራ ሊያጋቡንና ትክክለኛ ማንነታችንን እውቀን እንዳንነቃ በተንኮል ቀምመው የሰጡን መርዝ እንደሆነ የተለያዩ ምሁራንን ጠቅሶ እንዲህ ብለዋል፦** በ12ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አጋማሽ ላይ በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ በዳግማዊ ገብርኤል ዘመን (በ1131-1145) የኢትዮጵያ አገው አመፀኛ ንጉሥ ሀርቤ 69 የአገሪቱን ቤተ ክርስቲያን ከግብፁ ቤተ ክርስቲያን ተገዢነት ነፃ ለማውጣት የወሰደውን የፖሊሲ እርምጃ ለማጥፋት የግብፁ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖችና ምሁራን ሁሉቱንም የክብረ ነገሥትና የፍትሐ ነገሥት መዛግብት አዘጋጅተው ወደ ኢትዮጵያ እንዳስገቡ፤ አሁን በታሪክ መረጃ በጥናት በትክክል ተረጋግጧል። ...ከዚህ ከ13ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ከላይ በቀረቡ በፖለቲካ ምክንያቶችና መንገዶች ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት በገባው ክብረ ነገሥት...በኢትዮጵያ በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ባሕሎችና ሃይማኖቶች፣ ጎብረተሰብ፣ መንግሥትና ታሪክ ታላቅ ግድፈት ፈጥረዋል፤[157ሀ] *የኢትዮጵያ ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች፣ 1999 ዓ.ም፣ ገጽ 123*

[158] *ሁሉም ሁሉን ይወቅ፣ 1987 ዓ.ም ገጽ 232*

*ያለ ርዕስ ብዙ ከሰፈሰፈ በኋላ፦ ምዕመናን፣ ሁላችሁ በእመቤቴ በድንግል ማርያም አመኑ፣ **'ኢየሱስ ጌታ ነው፣ አዳኝ ነው' የሚባለውን እንዳትቀበሉ፣ እኛ ከድንግል ማርያም ሌላ አዳኝ የለንም፣*** ብሎ ሲያስተምር ከፕሮግራሙ በኋላ ባሕታዊውን ሲያነጋግር፦ *"ጴንጤ ከመካከላችን ገብቶ ሲበጠብጠን ዝም ብላችሁ ታዩታላችሁ እንዴ!"* ብሎ ሕዝብ ቀስቅሶ ሊያስደበድበኝ ምክሮ ነበር፣ የሚያውቁኝ ሰዎች ባይገላግሉኝ ኖሮ አልቆልኝ ነበር፣*[159]* ብሏል።

ይህ በምድራችን ዘመን ዘለቅ፣ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በግልጽ የሚጋጭ፣ የክርስቶስን ወንጌል በገሃድ የሚቃወምና ጫፍ የነካ የነገረ ማርያም ትምህርት መስፋፋቱን ያመለክታል። ከዚህም የተነሣ ክርስቲያን የተባሉ አብዛኛው የአገራችን ሕዝብ *"ኢየሱስ ክርስቶስ"* ተብሎ ሲሰበክ መታገስ እያቃተው ነው። ሰባኪያን፣ ዘማሪያንና ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ከሰበኩ "ጴንጤ" ተብለው እንዳይፈረጁ በትልቅ ሥጋት ላይ ወድቀዋል። ለዓለም ድነት ከሰማይ በታች የተሰጠውንና ብቸኛ የሆነውን የኢየሱስን ስም ለመጥራት ትልቅ ፍርሃት በምድራችን ነግሦአል። የአዳኙ የክርስቶስ ስም በገሃድ ካልተጠራ፣ ካልተሰበከ፣ ካልተዘመረ፣ ካልተደነቀ ከዚህ ስም በላይ የሆነውንና የምናከብረው ስም ካለ ክርስትናችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። እግዚአብሔር ከስም ሁሉ በላይ ያለውን ስም የሰጠው ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው (ፊል.2:9-10)። የኢየሱስ ስም በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን በሚመጣውም ዓለም ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ ነው(ኤፌ.1:21)። እርሱ፦ *"በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራል፣ ለእለቅነትና ለሥልጣንም ሁሉ ራስ በሆነ እርሱ ሆናችሁ ተሞልታችኋል"(ቈላ.1:9-10)*። ክርስቶስ በሙላት የማይገለጥበት ክርስትና ከክህደት አይሻልም። በአገራችን ሰዎች በወንጌል ስም የሚነገራቸው ምድር ተኮር መላምት እንጂ እውነተኛ ሙሉ ሰማያዊ ወንጌል መስማት መራራ ኪኒን እንደመዋጥ ከባድ ከሆነ ዘመናት ተቆጥረዋል።

ወገኖቼ፦ ክርስቶስ በሙላት ባልተሰበከበት ምድር እውነተኛ ክርስቲያኖች መኖር እንዴት ይችላሉ? እውነተኛ ክርስቲያን ሳንሆን ክርስቲያን መባሉ ምን ይረባናል? ከቃሉ ጋር በቀጥታ የሚጣረሱ የኑፋቄ ትምህርቶችን በጉያችን አቅፈን ያለ አንዳች ፍርሃት መስበካችን በእኛና በቃሉ መካከል ያለውን ርቀት አመልካች ነው። በክርስትና ስም የኑፋቄ ትምህርት በምድራችን መንሰራፋቱ የብዙዎችን ልብ በኑፋቄ መማለሉን ያሳብቅብናል። *"ሃሰተኛዉ አትለፍ" (1ቆሮ.4:6)* የሚለው የማስጠንቀቂያ ቃል በምድራችን ለምን ሰሚ አጣ? ታዲያ በዚህ ኑፋቄ የተከበበች ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ አያስፈልጋትም ማለት እንዴት ይቻላል? የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይበልጥ ለአገርና ለዓለም በወንጌል በረከት ትሆን ዘንድ በቃሉና በመንፈሱ መታደስ እንዳለባት ይህ አያመለክትም ወይ?

[159] *የሰው ያለህ፣ 2005 ዓ.ም ገጽ 145*

የመጽሐፍ ቅዱስ ምንነት

በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ የተሰኘው ይህ ምትክ የለሽና ድንቅ መጽሐፍ በግሪክኛ "ባይብሉስ" በሚል ይታወቃል። የእንግሊዝኛ ተናጋሪዎችም "ዘ-ባይቢል" የሚል ስያሜ የሰጡት ለዚህ ነው። የነገረ መለኮት ሊቅ የነበሩ ዶክተር ሉውስ ስፔር ቼፈር የመጽሐፍ ቅዱስ ልዩ መሆን ሲናገሩ፡- *ሷሰገራሚ ተያያዥነት ያላቸው 66 መጻሕፍት በአንድ ላይ መያዙና የተጻፈው ቃል ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ለመጻፉ ቋሚ ማስረጃ መኖሩ ነው*[160] ብለዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆች ብቸኛ አዳኝ ሆኖ ቀርቧል(ሐዋ.4፡12)።

መጽሐፍ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን መሠረት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን መመሪያና ውስጠ ደንቧ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የማይለወጥ (ማቴ.5፡17-18)፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሥልጣን የሚያደርግ (ኢሳ.55፡11)፣ ልብን ሁሉ የሚመረምር (ዕብ.4፡12)፣ የሚፈውስ (መዝ.107፡20)፣ የሚቀድስ (ዮሐ.17፡17) ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እስትንፋሰ እግዚአብሔር እንዳለበት በነቢያት፣ በሐዋርያት፣ በቤተ ክርስቲያን አበውና በነገረ መለኮታውያን የተረጋገጠና የካኖን መመዘኛ ያለፉት 66 መጻሕፍትን በአንድነት አቅፎ የያዘ መለኮታዊ ቤተ መጻሕፍት ነው።

የአማርኛና የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ አጭር ታሪክ

በአገራችን ቅዱስ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ በ4ኛው ክፍለ ዘመን በፍሬምናጦስ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ቀጥሎም በ5ኛው ምእተ ዓመት በዘጠኙ ቅዱሳን በግሪክኛ ከተዘጋጀው ከሰባ ሊቃናት ወደ ግዕዝ ተተርጉሞአል። የሕዝብና የቤተ ክርስቲያን መገልገያ በነበረው የግዕዝ ቋንቋ የተዘጋጀው መጽሐፍ ቅዱስ እየተነበበና እየተብራራ እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን ቆይቶአል። እንደ እነ ፒተር ሄይሊንግ አንዳንድ ሚሲዮናውያን በ17ኛው ክፍለ ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ወደ አማርኛ ለመተርጉም ያደረጉት ጥረት በታሪክ አይዘነጋም። ሥራቸው ለአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በር ከፋች ሆኗል።

የፈረንሣይ ኤምባሲ ምክትል ቆንስላ በነበረው አስሊን ዕርዳታ "*አባ አብርሃም*"[161] ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን በግብፅ ለአሥር ዓመት ቁጭ ብለው ወደ አማርኛ የተረጐሙት ኢትዮጵያዊ ሲሆኑ እርሳቸው በመጋቢት በ1811

[160] ተክሉ መንግሻ(ተርጓሚ) *(2003 ዓ.ም)* ፣ *የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ዋና ጭብጦች*፣ አዲስ አበባ የላፕሲሲ ብሩክስ ፋውንዴሽን፣ ገጽ 19

[161] ጉስታቭ ኦሬን፣ *ቀደምት ወንጌላውያን በኢትዮጵያ*፣ *ገጽ 42-44* በሚለው መጽሐፋቸው ስለ አባ አብርሃም ሲናገሩ፡- "አባ አበርሃም የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህን የሆኑ መነኩሴ ነበሩ። ምድረ ሙላጻቸውም ጕጃም ገልጸዋል። አባ አብርሃም በዐረብኛው አጠራር፡- *"አቡሂም፣ አቡሩህ፣ አቢሩሚ"* እየተባሉ ይጠራሉ። ሁሉም አበርሃም ማለት ነው።"

ዓ.ም ከሞቱ በኋላ የተረጐሙት ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛ በ1832 ዓ.ም በለንደን ታተመ። የተሻሻለ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በ1923 ዓ.ም ትዕዛዝ ተሰጥቶ በኢትዮጵያ ሊቃውንት ብቻ ከግዕዝ ወደ አማርኛ የተተረጐመ መጽሐፍ ቅዱስ ከ1928-1934 ዓ.ም ታተመ። እንደገናም በየካቲት 27 ቀን 1939 ዓ.ም ሰባት ኢትዮጵያውያንና ሦስት የውጭ አገር ሊቃውንት ያሉበት ጉባኤ በንጉሡ ትዕዛዝ ተሰይሞ አባ አብርሃም የተረጎሙትን መጽሐፍ ቅዱስ ከዕብራይስጥና ከፅርዕ ጋር በማነጻጸር የተሻሻለ ትርጉም በ1944 ዓ.ም ታተመ።[162] ይኸው ትርጉም በ1953 ዓ.ም በአገራችን በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት 66 መጻሕፍት የያዘው መጽሐፍ ቅዱስ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስን ጨምሮ በኦርቶዶክስ ሊቃውንት ብርቱ ጥንቃቄ ተተርጉሞ እንደተዘጋጀ ይታወቃል። ይህ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ለሁሉም የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት መንፈሳዊ ሃብትና መመሪያ ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል።

ሌላው ታላቁ ባለራእይና የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ የተረጐሙት የተከበሩ ቄስ አናሲሞስ ነሲብ (አባ ጋማቺስ) ሲሆኑ አስቴር ገኖ የቅርብ ረዳታቸው ነበረች። ስዊድናውያን የቅርብ አማካሪዎቻቸው የነበሩ ሲሆን በ1886 ዓ.ም የኦሮምኛ አዲስ ኪዳን ታትሞአል። በ1891 ዓ.ም ሙሉው የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ ታትሞአል። የአባ ጋማቺስ ታላቅና ፋና ወጊ ሥራ የኦሮምኛ ሥነ ጽሑፍ በር ከፋችና መሠረት እንደሆነ በብዙዎች ይጠቀሳል። ይህም በብዙዎቻችን እጅ የሚገኙና በአገራችን ቀድመው የታተሙ የአማርኛና የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች እንድናገኝ ያደረገ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፣ በግብፅ የፈረንሣይ ቆንስላ የነበሩ አስሊን፣ አባ አብርሃም፣ የኦርቶዶክስ ሊቃውንቶች፣ ንጉሥ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ፣ አባ ጋማቺስ፣ አስቴር ገኖና የስዊድን አማካሪዎች ትልቅ ምስጋና ልንቸራቸው የሚገባ የኢትዮጵያ ባለውለታዎች ናቸው። ከላይ በተጠቀሱት ሰዎች የተተረጐመው መጽሐፍ ቅዱስ 66 መጻሕፍት የያዘ እንደነበር መዘንጋት የለበትም። አሁን ግን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱሷን ከ66 መጻሕፍት ወደ 81 አሳድጋለች። *"ለመሆኑ ይህን 1953 ዓ.ም የታተመ መጽሐፍ ቅዱስ መለወጥ ለምን አስፈለገ? ያዘጋጁትስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳውያን አባቶች በቂ መንፈሳዊ ዕውቀትና መልካም ሕይወት አልነበራቸውምን? ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ሲገለገሉበት የኖሩት መጽሐፍ ቅዱስ የተሳሳተ ነበር?"*[163]

ስደት የጠገበ መጽሐፍ

በዓለማችን በነገሥታት፣ በህቡዕ የክህደት ርዕዮተዓለም፣ በ"ክርስቲያኖች" በሰይጣን በ"ቤተ ክርስቲያን" ወዘተ... ትልቅ የተቃውሞ፣ የእገዳ፣ የውግዘት፣ የማጥፋትና የማቃጠል አዋጆችን ሁሉ አልፎ በብዛት

[162] ኖኅተ ብርሃን፣ ጥር 2006 ዓ.ም ገጽ 13-23 *"የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ሐምሌ 18 እና 19 ባዘጋጀው ሲምፖዚየም ላይ በምሥራች አገልግሎት ሥራ መሪ ከቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ የተወሰደ"*

[163] በንስሓ የመታደስ አገልግሎት በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣(2002 ዓ.ም)፣ አዲስ አበባ፣ ገጽ 60

በመታተምና በመሰራጨት ቅድሚያ የያዘ አንድ መጽሐፍ ቢኖር አርሱም መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ለምሳሌ፡- በ305ዓ.ም የተነሣው ዲዮቅልጥያኖስ አብያተ ክርስቲያናት ይዘጉ፣ አብያተ ጣኦታት ይከፈቱ በማለት ሲያውጅ በጊዜው የተገኙ መጽሐፍ ቅዱሶች እንዲቃጠሉ ካደረገ በኋላ በተቃጠለው ቅዱስ መጻሕፍት አመድ ላይ ቆሞ ፎክሮዋል። በአገራችን ኢትዮጵያ ለእግዚአብሔር እንደቀኑ የሚነገርላቸው በዐፄ ዮሐንስ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ተሰብስቦ እንዲቃጠል አዋጅ አውጥተው እንደነበር ድርሳናት ያወሳሉ። አባ ጋማቺስ በኦሮሞኛ የተረጎሙትን መጽሐፍ ቅዱስ ለሕዝብ እንዳይሰራጭ ከአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ትልቅ ተቃውሞና እገዳ እንደደረሰበት ታሪክ ሕያው ምስክር ነው። በደርግ ዘመን የአብዮቱ ካድሬዎች በተለይ የወንጌላውያንን አብያተ ክርስቲያናት የመዝጋትና መዝረፍ፣ መሪዎችን ማሰር፣ ቅዱሳንን ማሳደድና መጽሐፍ ቅዱስን ሰብስቦ ማቃጠል እንደ ትልቅ ጀብዱ ይቆጥሩ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

በርናርድ ራም የተባለ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስለደረሰው ሲናገር፡- *"ሺህ ጊዜ መጽሐፉ እንደሞተ ተለፍፏል፣ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ተካሂዷል፣ መቃብሩ ላይ ማስታወሻ ተጽፏል የሕይወት ታሪኩ ተነቧል ዳሩ ግን ሬሳው ጉድጓድ ውስጥ ቆይቶ አያውቅም"* በማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የደረሰውን ታላቅ ጫናና ብርቱ ድል ለመግለጽ ጥረት አድርጓል። በታሪክ ለመጽሐፍ ቅዱስ ሕልውናና መልዕክት ብርቱ አደጋ ሆና የዘለቀችው በአንደቤቷ ቃሉን በልቧ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሰው ፍልስፍናና ድርሳናትን የምታራምድ "ቤተ ክርስቲያን" እንደ ሆነች ይጠቀሳል።

መጋቤ ሰሎሞን ጥበብ ስለዚህ ሲናገር፡-

> *...መጽሐፍ ቅዱስ በስሙ ተመስርቻለሁ የምትለው ቤተ ክርስቲያን ሳትቀር ገፍታዋለች። በአደባባይ አቃጥላው ታውቃለች። በዛሬ ዘመን እንኳ ሳይቀር መጽሐፍ ቅዱስን በማንበባቸውና የሕይወታቸው መመሪያ ያደረጉትንና በእውነት የሰበኩትን ሰዎች ታሳድዳለች አሳዳለችም። ከማህበራዊ ሕይወታቸው እንዲገለሉ የተፈረደባቸው ታሪክና ቤቱ ይቁጠራቸው።አንዳንዶች መጽሐፍ ቅዱስን ይዘው ኢመጽሐፍ ቅዱስን የሚሰብኩ የተባለውን ትተው ያልተባለውን፣ በልባቸው የቋጠሩትን ሲወርድና ሲዋረድ የመጣላቸውን ሲያሰኛቸው የሚመስለውን ካላስኬደም ትውፊት ከሚል ዋሻ አልያም ደግሞ ከባሕልና ከምድር ከሚያያቸው በዕድሜ የገፉ በሥልጣን የላቁ ጊዜ የገጠማቸውን የሰዎችን ተረትና አባባል እየጠቀሱ መጽሐፍ ቅዱስን ይቃወማሉ።* [164]

"የንስሐ የመታደስ አገልግሎት" መጽሐፍ አዘጋጅ፡-

> *በቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ ቅዱስ ተገቢውን ክብር ያላገኘ እንደሆነ በግልጽ ይታያል። የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት የሚጻረሩ የፍጡራን ድርሰቶች በየዐውዱ ምሕረቱ ይነበባሉ፣ ይሰበካሉ። በአንዳንድ ክብረ በዓሎችም አንዳንድ ሰባኪዎች መጽሐፍ ቅዱስን የሚቃረኑ ተረቶቻቸውን በስብከት ስም ያለ ምንም ከልካይ ይለፍፋሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሆነ የማያውቁ ካህናት ጥቂት አይደሉም*[165] ብሏል።

[164] ጥበብ ስለሞኝ(መጋቤ)፣ 2000 ዓ.ም (መግቢያ) ገጽ 10
[165] የንስሐ የመታደስ አገልግሎት፣ 2003 ዓ.ም

"ሰማንያ አሐዱ- በቃሉ ሲመዘን"

ቴዎድሮስ ደመላሽ *"ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን"* በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፍ መግቢያ ለኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የታተመ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስን መቅድም ዋቢ በማድረግ በቤተ ክርስቲያናቸው ስላለው የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ቁጥር እንዲህ ብሏል፡-

> *የመጽሐፍ ቅዱስን ቁጥር በተመለከተ አብዛኛው ዓለም የእግዚአብሔር ቃል ብሎ 66 መጻሕፍትን ይዞ ሲገኝ የእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን 81 መጻሕፍትን ይዛለች፣ ቅዱሳት መጻሕፍትም 81 እንደሆኑ ታስተምራለች።*[166]

ቴዎድሮስ በ66ቱ መጻሕፍት ላይ የተጨመሩ 15 መጻሕፍት ከቃሉ ጋር ሰፊ ሚዛና ካደረገ በኋላ በመጽሐፉ ማጠቃለያ ሲሰጥ፡-

> *ቅዱሳት የምንላቸው መጻሕፍቶቻችን ሆኑ አስተምህሮዎቻችን እንደ ቅዱስ መጽሐፍ ካልሆኑ የተሰጣቸው የቅድስና ስም ቅዱስ ሊያደርጋቸው አይችልም። ቤተ ክርስቲያናችን "ቅዱሳት" እና የእኔ ብላ የያዘቻቸውና ምእመናንንም የእናንተ ነው ልትላቸው እየሞከረች ያለውን የመጽሐፍ ቅዱሷን ቅዱስነት ብትፈትሸው ከእምነታ ጋር ፈጽሞ የማይጣጣም መሆኑን መመልከት በቻለች ነበር። እምነታችን ወንጌልን ያማከለ ነው፣ አስተምሯችንም ከሐዋርያት የወረሰነው ነው እየተባለ የወንጌልን እውነት የሚፃረርና የሐዋርያትን ትምህርት የሚቃወም ኑፋቄ ትምህርት ይዞ መገኘቱ ለምን ይሆን? እንደ እውነቱ ከሆነ በዚህች መጽሐፍ ለመመርመር እንደ ተሞክረው በተጨማሪዎቹ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ ፀረ ወንጌልና ፀረ ክርስትና ምክሮችን የያዘው መጽሐፍ የእኛ ሊሆን በፍጹም አይገባውም።*[167]... ካሉ በኋላ *"እስካሁን ከተመለከትነው አንጻር "መጽሐፋችን 66 ሳይሆን 81 ነው" ማለቱ ብዙ የሚያዋጣ አይደለም።* በማለት የጥናታቸውን ውጤት ደምድመዋል።

"ግመና ዘቸቸደዱ"

ቀስሲ ደረጀ ገ. *"ግመና ዘቸቸደዱ"* በሚለው መጽሐፉ ስለ ሰማንያ አንዱ የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ፡- *በ1980 ዓ.ም ለኦርቶዶክስ የታተመው 81ዱ መጽሐፍ ከ1954/62/ ዓ.ም ከታተመው 66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ አሳቦችን በመቆራረጥ በሃይማኖታዊ ቃልና ሀረግ ፍቆ በመተካት ከፍተኛ የሆነ የማጭበርበር /foreign/ ሥራ ተሠርቶበታል።* እንዲህም ሆኖ ያልረኩት ደብተሮች *በ2ሺ ዓ.ም ብሉይ ኪዳኑን ከእናት ቋንቋው ከዕብራይስጥ፣ አዲስ ኪዳኑን ከግሪኩ በሚቃረን መልኩ የእግዚአብሔርን ቃል ሰርዘውና ደልዘው*

[166] ቴዎድሮስ ደመላሽ *(2004 ዓ.ም)*፣ *ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን*፣አዲስ አበባ፣ ገጽ 11
[167] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 135

አሳትመዋል::[168] ካለ በኋላ የቸገዱን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ "መጽሐፍ ቅዱስ" ጉልህ ችግሮች እንዲህ ዘርዝረዋል፦

1. *የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ትርጉም ከእናት ቋንቋው የተለየ ቃል፣ ሀረግ፣ የጎላፊና የመጻእያት ጊዜውን ያልጠነቀቀና ያልተጣራ የትርጉም ይዘት ያለው ሆኖ መቅረቡ*

2. *ከእሀት አብያተ ክርስቲያናት /Oriental Church/ በተለየ መልኩ ቀኖናውያን ያልሆኑ መጻሕፍትን እንደ መለኮታዊ ቃል በመቀበል፣ ከቀዳት ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ተበላጥሮ ለመለየት የሚያሻማና ትውልድን በሚያታልል መልኩ ታትሞ መቅረቡ:: በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እናቴ የእስክንድርያዋ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ነች ብትልም የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን የማታውቀውንና የማትቀበለውን የደብተሮች ጥንቆላ መጻሕፍት ሁሉ በአንድነት ተካተው መታተማቸው (ሀሳብ ውስጥ ተካተዋል)*

3. *"ቤተ ክርስቲያኒቱ" የሰባ ሊቃናትን ትርጉም ነው የተጠቀምኩት ብትልም በብዙ አገራት ከሚታወቀው የሰባ ሊቃናት መጽሐፍት ጋር የማይመሳሰል የቁጥር መረጃ /Canon or norm/ አገር በቀል የደብተራ ፈጠራ መሆናቸው በበቂ መረጃ መረጋገጥ በመቻሉ::[169] ብለዋል::*

ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር በቀጥታ የሚጋጨ አንዳንድ ዘለማንያ አሀዱ (81ዱ) ክፍሎች፦ በማጨስና በማጫጫስ አጋንንትን ማስወጣት እንደሚቻል *"ሊቀ መላዕክት ሩፋኤል"*[170] አስተማረ ስለመባሉ፦ *...ያም ልጅ መልኣኩን ይህ ዓሣ ልብና ጉበት ሀሞቱስ ምንድነው? አለው መላኩም ልቡና ጉበቱ የሚያሳምም ክፉ ጋኔን ያደረበት ሰው... በፊቱ ቢያጨሱለት አይታመምም ሐሞቱ ደግሞ ብልዝ ያለበት ሰው ቢከሉትና*

[168] ቀሲሲ ደረጀ ገ. *(2003 ዓ.ም)* ፣ገመና ዘቸገዱ ፣ ገጽ 2

[169] *ገመና ዘቸገዱ ፣2003 ዓ.ም ገጽ 3*

[170] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 127-128 ይመልከቱ) ቀሲስ ደረጀ ገ. "ሩፋኤል" የተባለው መላዕክት ለመጽሐፍ ቅዱስ ስሙ ባዕድ ሲሆን ባሕሪውም ከመላዕክት ባሕሪ ጋር እንደሚጋጭ እንዲህ ብለዋል፦ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ "ቤ/ክ፫ን" ውስጥ መታሰቢያ ዕለት ተሰይሞለት ወር በገባ በየ13ኛው ቀን የሚከበርለትና የሚዘከርለት መልኣክ ሩፋኤል ይባላል:: ይህ መልኣክ በሁሉም አፖክሪፓ መጻሐፍትና ድርሣናት ውስጥ ስሙ የተገለጠ ቢሆንም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን አይታወቅም:: በአፖክሪፓም ሆነ በድርሣናቱ ውስጥ የተገለጠባቸው ማንነቶች ቅዱስ መላእክ መሆኑን እጅግ አጠራጣሪ ገለጻዎች ናቸው:: እንደ መጽሐፉ ጠቢት ገለጣ ከሆነ ሩፋኤል የመላእክት አለቃ ነው:: ባሕርይውን ሲገልጥ ደግሞ እንኳን በእግዚአብሔር ፊት የሚቆም መላዕክ፣ አንድ ዓለማዊ ሥጋዊ ፍጡር ከሞራል አንጻር እንኳ ሊፈጽመው የማይችል ገጸ ሞቆሪን ተሳብሶ ቀርቧል:: መጽሐፈ ጠቢት ምዕራፍ 7 እና 16 የእግዚአብሔር መላእክ የተባለው ሩፋኤል የመተት አሠራርን ለሰዎች ሲያስተምር እናያለን:: በምዕራፍ 12: 9 ደግሞ ምጽዋት ከሞት /ከገሃነም "እሳት/ እንደሚያድን ከጌሊላታም ነዛ እንደሚያወጣ ይናገራል:: በምዕራፍ 12: 20 ደግሞ የሰዎችን ጉዳይ የሰሰት ውሱ እየተከታተለ ታሪክ ሲዘግብ የሚውል ጋዜጠኛ አደርጎ ሩፋኤልን ያቀርባል:: በመጽሐፈ ሔኖክ 19:1 ደግሞ ሩፋኤል ከሚካኤል ጋር ሆኖ በመቅረብ መንፈስ ቅዱስን ሲያመ እናነባለን:: ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስሙ የማይታወቀው ይህ ሩፋኤል የተሰኘ መልኣክ በተጠቀሰባቸው የአፖክሪፓና የድርሣናት ክፍል ውስጥ ሁሉ ለሰዎች ጥንቆላን፣ ሐሰትን፣ ሀሜተኝነትን የሚያስተምር ነው:: ስለዚህ ባሕሪውንና ሥራዎቹን በመንተራስ የመልኣኩን ማንነት ማረጋገጥ ይቻላል:: ከዚህ የተነሣም ደብተሮቹ ሩፋኤል በማለት የሚጠሩት የቅዱሳን መላእክት ወገን ሳይሆን የአጋንንት አለቃ ለመሆኑ ጥርጥር አይኖረንም" ብለዋል::

ሀ ተባሉት ይድናል" (መ.ጦቢያ 6: 6-8:: 16 እና 17 ላይም ከደቀቀ እጣን ጋር ቢያጨሰበት ጋኔኑ እስከ ላይኛው ግብጽ ድረስ ሲሸተው ይሸሻል ይላል:: "የቤተ ክርስቲያናችን" መጽሐፍ ስለመንፈሳዊ ዓለም ምንም ሳይሰጥ ሳይናገረው መናፍስትን በማጫጨስና በማጫስ ለማባረር ማሰቡ፣ ከክንቱ የሃይማኖተኝነት ስሜት ያለፈ ዕውቀት እንደሌለው ያሳያል::[171]

በ1980ዎቹ ባህታዊ እንደ ሆነ ይናገር የነበረው ገ/መስቀል "ከሃይማኖትዎ አይፈሩ" በሚል መጽሐፉ፦ *ወይራና ነጭ ሽንኩርት ሊጋንንት አይወዱም ከቤታችሁ አይጥፉ፣ አጭሰብት ሲል አጋንንት*[172] የሚናባርርበት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ በገሃድ ሰብኩ ነበር:: አጋንንትን በማጫጫስ፣ በወይራና በነጭ ሽንኩርት ሳይሆን በኢየሱስ ስም እንደሚወጡ ኢየሱስ ራሱ ሲናገር፦ *"በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ" (ማር.16:17)* ብሏል:: ሐዋርያት በኢየሱስ ክርስቶስ ተልከው ወንጌል ሰብከው ሲመለሱ አጋንንትን እንዲት እንዳወጡ ሪፖርት ሲያደርጉ፦ *"ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው፦ ጌታ ሆይ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት" (ሉ.ቃ.10:16)::* ታዲያ አጋንንትን በጭስ ስለማባረር ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ትምህርት እንዴት በአገረ ዕድሜ ጠገብ ቤተ ክርስቲያን "መጽሐፍ ቅዱስ" ተገኘ? 81ዱ የአገራችን *"መጽሐፍ ቅዱስ"* የሰውን ልጅ ማንበብና መጻፍን ያስተማረ የአጋንንት አለቃ ነው ይላል፦

> *የመቶ አጋንንት አዝማች...አራተኛው ስም ፔንሙ ለሰው ልጆች የተሰወረ ጥበብን ሁሉ አስተማራቸው ለለምኝም በቁጥር ቀለም በወረቀት ላይ መጻፍን አስተማራቸው ...ሰው እንዲህ ያለ ሥራ አልተፈጠረም ነበር በጥቁር ቀለምና በቀይ ቀለም ጽፈው ሃይማኖታቸውን ሲያጸኑ ሰው ለእንዲህ ያለ ሥራ አልተፈጠረም ነበረና.. ይላል* (መ.ዜናዎክ 19: 15-24 ገጽ 1010)

በመጽሐፍ ቅዱስ (66ቱ መጻሐፍ) ከዘፍጥረት እስከ ራእይ አስተምህሮ አጋንንት የሰው ልጆችን ማጥፋትና አቅጣጫን ማሳት እንጂ በአንድም ቦታ አምንታዊ ነገር እንዳደረገ አልተዘከረለትም:: በኦርቶዶክስ መጽሐፍ ቅዱስ *"የመቶ አጋንንት አዝማች...አራተኛው ስም ፔንሙ ለሰው ልጆች የተሰወረ ጥበብን ሁሉ አስተማራቸው ለለምኝም በጥቁር ቀለም በወረቀት ላይ መጻፍን አስተማራቸው..."* የተባለው አጋንንት የትኛው አጋንንት ይሆን? የጥበብ፣ ማስተዋልና የዕውቀት ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር እንደ ሆነ እንጂ ሰይጣን ጥበብና መጻፍን ለሰው ልጆች እንዳስተማረ መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም:: ይህ ሙሉዕ የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ካለመረዳት የሚመጣ አደገኛ ስህተት ነው:: *መጽሐፈ ሄኖክ ሰለጌጥ ማጌጫ ስለጨረቃ አወጣጥ ስልት ስለ ቅንድብ መኪልና የሰማይ ምስጢራትን ሁሉ አጋንንት ለሰው ልጆች ያስተማሩ ነው ሲል ይናገራል (መ.ሄኖክ 2:19-25)::* ይህ አሳብ ለመጽሐፍ ቅዱስ ባዕድ ነው::

[171] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 98

[172] ገ/መስቀል ኃ/መስቀል (ባህታዊ)፣ *በሃይማኖትሥ አይፈሩ*፣ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ ገጽ 13

ሌላው በሐዋርያት ዘመንና ከዚያም በኋላ እስከ 5ኛው ክፍለ ዘመን ኤጲስ ቆጳሳትና ርዕሳነ ኤጲስ ቆጳሳት አንድ ሚስት አግብተው ቤተሰባቸውን እንደ እግዚአብሔር ቃል እየመሩ ያገለግሉ እንደነበር ታሪክ ይናገራል። ከ5ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ከቃሉ አፈንግጣ ጨለማ ውስጥ መኳተን በጀመረችበት ዘመን ኤጲስቆጳሳት/ጳጳሳት/ የጳጳሳት ስብሳቢ ፓትርያሪክ ሚስት ማግባት እንደሌለባቸው የእግዚአብሔርን ቃል በተላለፉ ሽማግሌዎች ተወስኖ በሥራ ላይ መዋል ጀመረ። ፍትሐ ነገሥትና የአዋልድ መጻሕፍት በመጽሐፍ ቅዱስ የሌለውን ይህን አደገኛ ትምህርት ይደግፋሉ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ይህን ወግ ተቀብላ ኖራለች። ይህን የዘመናት ወግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ በ81ዱ እንደ ጣሰች ቀሲስ ደረጀ ሲናገር፦

> *በቅርቡ ሓዲሱ መጽሐፌ ብላ ባሳተመችው የ2ሺህ አትም 81ዱ ላይ በ1ኛ ጢሞ. ምዕራፍ 3 ቁጥር 1-3 ለፓትርያርኩ ጋብቻ (አንድ ሚስት) ሲፈቅድ፣ ሌሎች ጳጳሳትን መከልከሉ ብዙዎችን ያሳዘነ ጉዳይ ነው። ይህም በየመድረኩ መናፍቃን /በጸድቃን ምልጃ የማያምኑ/ መጽሐፍ ቅዱስን እየቀናነሱ ቃላቶችንም እየለዋወጡ ያሳትማሉ ይባል የነበረው ፉከራ ሁሉ "ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ ጅግራ ናት ይሏታል" እንዲሉ ራሳቸው ለለውጥ ዝግጅት ላይ ስለነበሩ ነበር፣*[173] *ብሏል።*

እንደተባለው ከሆነ ስህተቱ 81ዱ የአገራችን መጽሐፍ ቅዱስ ለፓትሪያርኩ ጋብቻን መፍቀዱ ሳይሆን በጳጳሳት ላይ የተጣለውን የጋብቻ ማዕቀብ ያለማንሣቱ ነው። ጳጳሳት እንዳያገቡ የመከልከል ውጤት ቤተ ክርስቲያንን ትልቅ ዋጋ እያስከፈላት ይገኛል። በተለይ በምዕራቡ ዓለም ጳጳሳት በግብረ ሰዶማዊነት፣ ሕፃናትን በመድፈርና ኢሞራላዊ በሆነና የእግዚአብሔርን ቤት ስም በሚያጎድፍ ምግባር ውስጥ መገኘታቸው ከአገልግሎት መባረር፣ ተከሰው ፍርድ ቤት መቆምና በሚሊዮን ዶላር የሚገመት ገንዘብ ቤተ ክርስቲያንን በማክሰር ላይ እንደሚገኙ በብዙሃን መገናኛ በየጊዜው ሲነገር እንሰማለን። እንደ ሎሳንጀለስ ታይምስ ጥናት *"በአሜሪካ 15% የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳትና ካህናት ሰዶማያውያን እንደሆኑ መስክረዋል"*[174] ስለዚህ ቀውስ ቀሲስ ደረጀ በመጽሐፋቸው ሲገልጹ፦

> *ብዙ ሰዶማውያን ከእንስሳት ጋር የሚገናኙ በየገዳማቱት የፈሉት ይሸው የሰው ሥርዓት ጫና ስለሆነባቸው ነው። እህት መነኮሳትም ቀላጮች የሆኑት በዚሁ ምክንያት ነው፣* ብለዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ *"ጋብቻ ቅዱስ ነው መኝታውም ንጹህ"* ይላል (ዕብ.13:5)። ጋብቻን የሚከለክል ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። *"መንፈስ ግን በግልጥ በኋለኛው ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንት ትምህርት እያደመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል፤ በገዛ ሕሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው እነዚህ ውሸተኞች መጋባትን ይከለክላሉ ...እግዚአብሔር ከፈጠረው መብል እንዲርቁ ያዝዛሉ እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነውና ከምስጋናም ጋር ቢቀበሉት የሚጣል ምንም የለምና" (1ጢሞ.4:1-5)*። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መጻሕፍት በመጨመር

[173] *ገመና ዘቤተ ዳ፣2003 ዓ.ም ገጽ 107-108*

[174] Stammer, Larry B. October 20, 2002 Los Angeles Time Retrived December, 21 2013

ሂደት እጅግ የተማረሩ የሚመስሉ ቀደስ ዓለማየሁ ሞገስ ደረሶ *"ሁሉም ሁሉን ይወቅ"* በሚለው መጽሐፋቸው፦

> *ዛሬ ዓለም ሁሉ በቀድሞ ዘመን ባለመግባባት የተነጣጠሉ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በሃይማኖት ካልሆነ በሥርዓት የተለያዩት ሁሉ ለመገናኘት በሚጥሩበት ጊዜ በሁለት ባሕሪ ምክንያት ያልነበረ እያወራችሁ ልዩነትን በልበ ንጹሓን የምትተክሉ፣ ሰማንያ አሐዱ መጻሕፍትን ገድላገድሉን ሁሉ ፈጽመራችሁ ከ83:93 ያገባችሁ ቃለ እግዚአብሔር ከእናንተ አሳብ ጋራ ካልተስማማ ስትደልዙና ስትሰርዙ የማታፍሩ ሰዎች መሆናችሁ ክርስቲያን ናችሁ ተብሎ ይመሰከርላችኋል?*[175] በማለት ጥያቄያቸውን አቀርበዋል።

ቀደስ ዓለማየሁ በዚሁ መጽሐፋቸው፦

> *ከሦድም ጀምሮ በፍትሐ ነገሥቱ የታዘዘው 81 መጻሕፍት ቁጥር ይህ ሲሆን አሁን ግን በግዕዝ የተጻፉ አዋልድና ሊቃውንት ለምን ይቀራሉ፤ ብለው መሰለኝ በ1980 ዓ.ም በሲናዶሱ ፈቃድ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አሳታሚነት የታተመው መጽሐፍ ቅዱስ 93 ደርሷል። በዚሁ እትም ሌላም አሻሽለን እንጨምራለን፤ ብለው ቃል ስለገቡ፤ እነ ሰይፈ መለኮት፤ እነ ኢ.ጋኖርን፤ እነ ውዳሴ አምላክ ወዘተ...የመሳሰሉትም ቢሆን እንደሚጨመሩ ባለመሉ ተሰፋ ነን። መጽሐፈ ባልቴትስ ቢሆን ከልፋፈ ጽድቅ ጋራ በገዛ አገሩ ቢጨመር ምን አለበት?*[176] ብለዋል።

የ81ዱ መጽሐፍ እንዲታተም ምክንያት የሆነው የፍተሐ ነገሥት ሠላሳምትን ዕውን ለማድረግ እንጂ የተካተቱ መጻሕፍት የካኖን መመዘኛ ስላሟሉ አይደለም። አባ መልከጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ ስለዚህ አንዲህ ብለዋል፦

> *ሰማንያ አንድ መጻሕፍት ቁጥር 81(ሰማንያ አንድ) ይሆናል። ሰማንያ አንድ መጻሕፍት የሚለው ቃል ግን ሊቃውንት ያተቱላቸው ፍትሐ ነገሥቱ በደፈናው ሰማንያ አንድ ስላለ ያንኑ ለመሙላት ብቻ የገቡ ናቸው እንጂ፣ ሕጋውያን አይደሉም። ያም ሆኖ ሊቃውንት በነዚህ መጻሕፍት ቁጥር ላይ አልተወሰኑም፣ እገሌን እንደሆነ፣ እገሌን አስገብቶ፣ እገሌን ያስገቡ እንደሆነ እገሌን አስወጥቶ የሚል ሐተታ መስጠታቸው አሁንም አልቀረም፣ ስለምን ውሰን አይደለምና።*[177]

አባመልከጼዴቅ እንዳሉት 81 መጻሕፍት ለመሙላት ብቻ የገቡ እንጂ ሕጋውያን አይደሉም ከተባለ በእግዚአብሔር ቃል ላይ በመጨመር ሕዝብን ማሳት አይሆንም ወይ? የአዲስ ኪዳንና የብሉይ ኪዳን ካኖን ከተጠናቀቀ ከ1700 ዓመታት በላይ ያለፈ ሲሆን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጉያ እንደ አሸን የፈሉ ድርሳናት ዛሬም ወደ መጽሐፍ ቅዱስነት እያደጉ እንደሆነ ማየት ለእኔ ከእግዚአብሔር የመራቃችን አንዱ ምልክት ነው ብዬ አምናለሁ። *"ያም ሆኖ ሊቃውንት በነዚህ መጻሕፍት ቁጥር ላይ አልተወሰኑም"* የሚለው ሐሳብ መጽሐፍ ቅዱስ ተደርጎ የተሰጣቸውን መቀበል ሳይሆን የፈለጉትን መጽሐፍ ቅዱስ ማድረግ አቅም እንዳላቸው የሚያሰበ ሊቃውንት ተጨማሪ መጻሕፍትን ገና የመጽሐፍ ቅዱስ አካል ለማድረግ በዝግጅት ላይ ያሉ ይመስላሉ። ይህ አደገኛ አካሄድ ነው። ታዲያ

[175] ዓለማየሁ ሞገስ ደረሶ (ቀደስ)*(1987 ዓ.ም)* ፣ *ሁሉም ሁሉን ይወቅ*፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ ገጽ 240

[176] *ዝኒ ሰማሁ፣ ገጽ 214*

[177] አባመልከጼዴቅ ገጽ 59

ለዚህ ተሐድሶ አያስፈልግም ወይ? በአዕምሮዬ የሚያቃጭሉ ጥያቄዎች፦ በዓለማችን ያሉ አብያተ ክርስቲያናት የፈለጉትን ቆርጠው ወይም ቀጥለው የራሳቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ማዘጋጀት ይችላሉ ወይ? በየአገራቱ ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የሚያሳትመው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የተስማሙበትን መጽሐፍ ቅዱስ ነው? ወይስ በየአገራቱ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት የሚያቀርቡለትን?

የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ዛሬ

የኢትዮጵያ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ባለፈው አንድ ምዕተ ዓመት በትልቅ ስደት፣ መከራና ጫና ሥር ሆነው በከፍተኛ ፍጥነት በማደግ ላይ እንዳሉ መረጃዎች ያመለክታሉ። *በ1900 ዓ.ም በኢትዮጵያ ምንም እንደሌሉ የሚነገርላቸው ፕሮቴስታንቶች ዛሬ ከአገሪቷ ሕዝብ 16.8% ሲሆኑ እ.ኤ.አ በ2007 በአጠቃላይ 31000 አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት እንዳሉ ጥናቶች ያመለክታሉ።*[178] እግዚአብሔር በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት እየሠራ ስላለው መልካም ነገር ስሙ የተባረከ ይሁን። እግዚአብሔር ይባርካቸው። ፕሮቴስታንቶች በዚህች ታላቅ አገር ከተመሠረቱ አንድ ምዕተ ዓመት ብቻ ያስቆጠሩ ቢሆኑም ከተመሠረቱበት ጊዜ አንሥቶ የዚህች ታላቅ አገር የታሪክ አካል ሆነዋል። እግዚአብሔርን ስለ እነርሱ እናመሰግናለን።

መጋቢ ተስፋሁን ሐጢያ በአመራር(መሪነት) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ባደረጉት ጥናት፣ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በውስጣዊ አሠራርና በአመራር ዘይቤያቸው 30% ኦርቶዶክሳዊ እንደሆኑ ይፋ አድርገው ነበር። ከላይ ቀሲስ መዘምር ወልደ ሩፋኤል እና የሊቀ ማእመራን ዲበ ኩሉ በቤተ ክርስቲያናቸው አፋጣኝ መፍትሔ የሚሹ አሳሳቢ ጉዳዮች የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆኑ፣ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ያለው ነባራዊ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ይመለከታሉ።

አደጋዎች

በአገራችን ባሉት ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ፊት የተደቀኑ አደጋዎች፦

- ከዘመኑ ጋር የማይሄድ አሠራር እንደ ዶግማ መቆጠሩ፣

[178] *Evangelical Churches Fellowship of Ethiopia in partnership with DAWN Ministries carried out its first basic research in 2005 on the status of the evangelical churches in Ethiopia; it's not yet published.*

- ዛሬ ላይ ቆሞ ነገን በትክክል አይቶና አውቆ፣ በራእይ ኃይል ያለመነሣት፣
- አስተምህሮአቸው በድነት ወንጌል ላይ ብቻ ያተኮረ ስለሆነ ብዙዎች ስለ ንግድ፣ ስለ ትምህርት፣ ስለ ፖለቲካ፣ ስለኢኮኖሚ፣ ስለአገርና ስለ ዕለታዊ ኑሮ ተግባራዊ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕውቀት ማጣት[179]
- የተጠሩ፣ የተሰጡ፣ የተቀቡና ዘመኑን በቃሉና በመንፈሱ በትክክል አውቀው ማሳወቅ የሚችሉ አገልጋዮች እጅግ አናሳ መሆን፣
- ዘመኑንና ትውልዱን የማይመጥኑ፣ ያላደጉ አሳዳጊዎች የቤተ ክርስቲያንን መድረክ መቆጣጠራቸው፣
- ለውጥን እንደ ጦር ከመፍራትም አልፎ፣ የለውጥ ተቃዋሚዎች መብዛት፣
- በፍልሰትና በመከፋፈል መባዛት፣ እንደ ልዩ ራእይ መቆጠሩ፣
- ለመንጋው የሚያስፈልገውን ሳይሆን፣ መንጋው የሚፈልገውን ብቻ መመገብ፣
- ቤቱ በደቀመዝሙር ሳይሆን በቲፎዞዎችና የቃሉ ዕውቀት በሌላቸው አባላት መጨናነቅ
- የከሰረ ነጋዴ፣ "ሞፈር ሰቀል"[180]፣ የሰነፈ ተማሪና ከመንግሥት ሥራ ጡረታ የወጣ፣ የፈለገውን የአገልግሎት ቢሮ ስም (ሐዋርያ፣ ነቢይ፣ፓስተር...) በራሱ ላይ ለጥፎ፣ ለጥቅም አገልጋይ የመባል መንገዱ አልጋ በአልጋ መሆን፣
- ሳይማሩ በማስተማር መንፈስ የሰከሩ "አስተማሪዎች" እንደ አሸን መፍላት፣
- ስጦታቸው/ካሪዝማቸው/ና ባሕሪያቸው/ካራክተራቸው/ የተፋታ "አገልጋዮች" የሕዝቡን ልብ ማማለል፣
- ዘመኑንና ትውልዱን ያልተረዳና መረዳት የማይፈልግ አመራር መንጋውን ማመሰ ፣

[179] Tibebe Eshete, Ethiopian historian, writes *"The Church pursued a one-way track of survival, where social and political agendas were put on the back burner. This position also limited the Church's capacity to develop a broader theology of social concerns and economic development, a handicap that continues to hamper the Church's contribution to Ethiopian society at large."* Tibebe Eshete *(2009), The Evangelical Movement in Ethiopia: Resistance and Resilience (Waco, TX: Baylor University Press), 303.*

[180] *ሞፈር ሰቀል፦ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ የተለመደ ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም የግብርናውን ሥራ ትቶ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ዋሻ የሚጠቀምባት የባላገር ዱርዬ ወይም ትዳሩ ሞቶ ወይም በእርሻው አልጠቀም ብሎ ወይም በሰንፍና ምክንያት ትዳሩን ፈትቶ ገዳም የገባ ሁሉ ሞፈር ሰቀል ይባላል። እንዳንዱም «ዘንዶ እምዓፀባ» ማለትም ከችግር የሸሸ ተብሎ ይጠራል። መምህር ጽጌ ስጦታው(2004 ዓ.ም)፣ ወ,ማን፣ ገጽ 127*

- እንደ ልምድ አዋላጅ በልምዱ ያለ ቅጥ የሚደገፍ፣ የአመራር ዘይቤ በአብዛኛው አብያተ ክርስቲያናት ተቀባይነት ማግኘቱ፣
- መስናና ግልጽነት የጎደላቸው አሠራሮች መንሰራፋት፣ ከቤተ እምነት ዋና ቢሮ እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተዘረጉ *"ጠባብ ብሔርተኝነት/መንደርተኝነት"*[181] ከብዙ ጥቂቶቹ ናቸው።

ብሔርተኝነት የተንሰራፋበት ካምፕ መምሰሉ

ብሔርተኝነት በብሔሮች ምሥረታ ታሪካዊ ሂደት ውስጥ የተወለደና እያደገም የመጣ ክስተት እንደመሆኑ ከብሔር ቋንቋዎች፣ ባሕሎች፣ ሥነ ልቦናዊ አመለካከቶችና እምነቶች በጥብቅ የተሳሰረ[182] እንደሆነ ይገለጻል። ብሔርተኝነት የከረረ አቋም ይዞ በሚገኝበት ጊዜ ብሔር ትምክህተኝነት ይባላል። የብሔር ትምክህተኝነት የአንድን ብሔር ጥቅም ከሁሉ በላይ የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ብሔሮች በጥላቻና በበታችነት የሚያይና አስከፊ ለሆነ ብዝበዛና ጭቆና የሚያዘጋጅ፣ አንዳንዱም ጨርሶ ለመጨፍጨፍ የሚያነሣሣ ነው። የብሔር ትምክህተኝነት አንዱ አዝማሚያ ዘረኝነት ነው።[183] ይትባረክ ግደይ በመጽሐፋቸው ዘረኝነት ከየት እንደሚመነጭ ሲገልጹ፣

> *በአጠቃላይ ዘረኝነት ከበላይነት ስሜትና ከሥልጣን ፍላጎት ከምቀኝነት፣ ከተንኮል ከክፋትና ከራስ ወዳድነት ይመነጫል። እነዚህ ክሌሉ ዘረኝነት ብሎ ነገር ቦታ የለውም*[184] ብለዋል።

እንደ ተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባባል ደግሞ፦ *የአንድ ዘር የበላይነት በላይንስ ውሸት፣ በግብረ ገባዊ ሚዛን የተኮነነ የማኅበረሰብ አደጋና ጠንቅ ነው። የዘር መድሎን በንድፈ ሐሳብና በተግባር የሚያጸድቅ ሕግ በዓለም ላይ ተቀባይነት የለውም*[185]። ዘረኝነት ኃጢአት ነው። ሉዲስ ኪዳን በዘርና በብሔር ስም የሚደረገውን መድልዎ እንድንዋጋ እንጂ እንድናስተጋባ ዕድል አይሰጠንም። ማንኛውም አድልዎ ለክርስቲያኖች ውጉዝ ከመሆኑ ነው። ዘረኝነትና ብሔርተኝነት ኑፋቄ ነው።[186] መጽሐፍ ቅዱስ፦ *በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ፣ ከቋንቋም ሁሉ፣ ከወገንም ሁሉ፣ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ*

[181] "የመንደርተኝነት መነሻውም መድረሻውም መንደሩ ነው፤ ከመንደሩ የሰፋ፣ የላቀና የረቀቀ ነገር አይታየውም፤ መንደርተኝነት የሚጀምረው እዚያው በቅርቡ የሚታየውንና የሚሰማውን መሠረት በማድረግ ነው፤ ይህ የመንደርተኝነት መሠረት ምንድነው? ዘር ነው፤ ቋንቋ ነው፤ ሃይማኖት ነው፤ ባህል ነው፤ መንደርተኝነት ባህል ምንድነው? ብሎ አይጠይቅም፤ መነሻውም መድረሻውም የመንደሩ ቋንቋ፣ የመንደሩ ሃይማኖት፣ የመንደሩ ባህል ከሌላው ሁሉ የተሻለና የበለጠ ነው የሚል ጠባብ አስተያየት ነው፤ መነሻውም ሆነ መድረሻው ልዩነትን ማጉላት ነው" መስፍን ወልደማርያም (2005 ዓ.ም) ፤ መክሸፍ አንደኢትዮጵያ ታሪክ፣ ገጽ 171

[182] ማርክስ ዝም ሌኒንም መገዛበ ቃላት፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1978 ዓ.ም፣ ገጽ 206

[183] ዝኒ ስማሁ፣ ገጽ 213-214

[184] ይትባረክ ግደይ፣ ዘረኖ ማን ነው? ኢትዮጵያውያን ፍረዱ! ገጽ 84

[185] International Convention on the Elimination of All Forms of Racial Discrimination"Office of the United Nations High Commissioner for Human Rights. December 23, 2011.

[186] ምኒልክ አስፋው፣ ገጽ 93

ለለምላሳችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው (ራእ. 5: 9 - 10) ይላል።

ሰብለ ወንጌል ዳንኤል፣ *"ብሔርተኝነት ቤተ ክርስቲያን ያላለፈችው ፈተና"*[187] በሚል ርዕስ በጻፈችው ጽሑፍ፣ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት *"የበታችነት እና የበላይነት ስሜቶች ጎልተው የሚንፀባረቁባቸው ሊጋጣሚዎች በርካታ ናቸው፤ ጊዜው ከታሪካዊ ቁርሾ በመነሣት አንዱ ብሔር ለሌላው ያለው አይታ የከፋ ደረጃ ላይ እንደደረሰ"* አስደንጋጭ የጥናት ድምዳሜ አስነብባናለች።

በአንዳድንድ የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ከላይ እስከ ታች በክርስቶስ ከተሰጠን ማንነት ይልቅ ትልቅ ቦታ እየተሰጠ ያለው የዘር ሐርግ ቆጠራ ነው። የአመራር መዋቅራዊ ሰንሰለት ውቅሩ ዘርና ቋንቋን መሠረት ያደረገና ያን የሚያስፋፋ ይመስላል። የራስን ቋንቋና ባሕል እንዲሁም እሴት አውቆ ማሳደግ ባይከፋም የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ ወንጌል እንጂ ያ አይደለም። ወንጌልን ከሌሎች እንደተቀበልን በተራችን ለሌሎች ለማቀበል የማያደርገን አካሄድ ከቃሉና ከዘመኑ የአመለካከት መርህ ውጭ ነው። ዓለም መንደር በሆነችበት ዘመን መንደራችን ዓለም ከሆነብን ብሰለት ዕድገታችን ጊዜው ከሚጠይቀው ደረጃ በታች እጅግ የወረደ ነው። ወንጌሉንና ዘመኑንም አልተረዳንም ማለት ነው። ሉልአቀፋዊነት ለመንደርተኝነት ቦታ የለውም። አማኝ የተባልን ሁላችንም ስለ መንደራችን፣ ስለቋንቋችን፣ ስለ ባሕላችንና ስለ እሴታችን ማሰቡ ምንም ክፋት ባይኖረውም አደገኛው የሚሆነው በዘራችንና በመንደራችን ፍቅር ልባችን ወድቆ ሌላውን የመቀበል አቅምና ወንጌልን ለሁሉም የማድረስ ራእይ የለሽ ካደረገን ነው።

በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ እንኳ ከመለኮታዊ ጥሪ፣ ከተገለጠ ጸጋ፣ ለአገልግሎት ከተሰጠ ሕይወትና ከአገልግሎት ፍሬ ይልቅ አንድን አገልጋይ ለመሾም "የዘር" ጉዳይ ዋና መመዘኛ ከሆነ ውሎ አድሯል። ነገረ መለኮትን ተምረው ነገ ያለማወቅን ጨለማ ከሕዝቡ ላይ ይገፋሉ ተብለው በተጠበቁ የአንድ ክፍል ተማሪዎች መካከል በተደረገው ጥያቄ አብዛኛዎቹ ከክርስትናቸው ይልቅ "ዘራቸው" ምርጫቸው እንደሆነ ተናግረው ነበር፦

> *አንድ የነገረ መለኮት መምህር በአንድ ወቅት በኢ.ወ.ቤ.መ.ኢ ለሚናገሯቸው ለተማሪዎቹ "በዘራችሁ" ወይም "በክርስትናችሁ" ካላችሁ ማንነት የትኛው ነው በጣም ጠቃሚ? ብለው ሲጠይቁ፣ ሁለት ሦስተኛው "ዘራችን" ብለው መለሱ።*[188]

[187] ማቴዎስ ቁጥር 12 ጥር 2002 ዓ.ም

[188] Bo Eriksson, et al (1999), *The Gospel of Restoration*: Experiences From a Field Study in Ethiopia 1998 (Uppsala Swedish Institute of Missionary Research, p 99

የዚያን ጊዜ የነገረ መለኮት ተማሪዎች የነበሩ ዛሬ ብዙዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደሆኑ አንዘንጋ። ዘራቸውን ከክርስትናቸው በላይ የሚመለከቱ የትላንት ተማሪዎች የዛሬ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሁሉ በላይ የሆነውን ክርስቶስን እንዴት መስበክ ይችላሉ? ክርስትናችን ከቋንቋችንና ከብሔራችን አልፈን እንድናይ ካላደረገን ዋጋ የለውም። ሌላው ይህ አብያተ ክርስቲያናትን በብዙ ያሽመደመደው አደገኛ የጠባብ ብሔርተኝነት መንፈስ ወደ ወንጌላውያን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችም በከፍተኛ ሁኔታ እየተዛመተ መሆኑን ነው። ተማሪዎች ባለራእዮች ሆነው ለቤተ ክርስቲያንና ለአገር ጠቃሚ እንዲሆኑና የጊዜውን የእግዚአብሔርን አሳብ ተረድተው አዲስ የታሪክ ምዕራፍ እንድከፍቱ ሳይሆን ወደ ጎጣዊ የአመለካከት ዋሻ ለማስገባት በመንፈሳዊ አገልግሎት ስም የሚታገሉ ግለሰቦችና የተደራጁ *"መንፈሳዊ ድርጅቶች"* ብዙ ናቸው። እያንዳንዱ ቤተ እምነት የራሱን ተማሪ ተከታትሎ የማገልገል ትጋታቸውን ባደንቅም የብዙዎቹ እርምጃ ከተለያየ ቤተ እምነት፣ ባሕል፣ አካባቢ፣ ቋንቋና ልምድ የመጡና ለቤተ ክርስቲያን፣ ለአገርና ለዓለም የለውጥና የዕድገት ኃይል የሆኑትን በቃሉ ከማስታጠቅና ታላላቅ ባለራእዮች እንዲሆኑ ከማላደግ ይልቅ በቤተ እምነታዊ ብሔርተኝነትና በቋንቋ በመበታተን አንድነትንና ፍቅርን ጥያቄ ውስጥ ማስገባት በየትኛውም ሚዛን መንፈሳዊነት አይደለም። በዚህ አካሄድ ከራሱ ይልቅ የሚኖርለት ትልቅ የመኖር ዓላማ ያለው ትውልድ እንዳይነሳ እንቅፋት መሆናችንን ያመለክታል። ለራሱ ተሰናክሎ ትውልድን ለሚያሰናክል ለዚያ ሰው ወዮለት!!

በየአጥቢያዎችችን ሠርቶ ልዩነትን ያላመጠው የአገልግሎት ዘይቤያችን የራስን ስም ለማስጠበቅና የተማሪዎችን መንፈሳዊ ዕድገት ከማቀጨጭ ውጭ ልዩ ተአምር ያመጣል ብዬ አልጠብቅም። ለዚህ ሁሉ ተሐድሶ ያስፈልጋል። ይህን ክፍል ስጽፍ ወደ አንድ ዩኒቨርሲት ለአገልግሎት ተጋብዤ ሄጀ ነበር። ከ2000 በላይ የዩኒቨርሲቲ ክርስቲያን ተማሪዎች ሕብረት መሪ ሆኖ የሚያገለግል ወጣት ምላ አብረን እየበላን ሳለ በጣም እያዘነ ፍርሃቱን እንዲህ ብሎ ተናገረ፡-

> *የዩኒቨርሲት ክርስቲያን ተማሪዎች ሕብረት የመበታተን ትልቅ አደጋ ተጋርጦበታል። አደጋውን ያመጡት ለእኛ የሚያስቡና የማገለገል ሸክምና ልብ እንዳላቸው የሚናገሩና የአብያተ ክርስቲያን አውቅናም የተሰጣቸው ቢሆኑም ትልቁ ችግራቸው ዘመኑን፣ ትውልዱን፣ የእግዚአብሔርን የጊዜው አጀንዳ ያልተረዱና ጠባብነት ጎልቶ የሚታይባቸው መሆናቸው ነው። እነዚህ አካላት የተለያየ ስም እየሰጡን እኛን በተለያየ ስም በታትነው የባሰቤትነትን ሰሌዳ በእኛ ላይ በመለጠፍ ስማቸውን ከማስጠራት ያለፈ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለተማሪዎች ለአሁኑና መፃኢ ሕይወት አልፎም ለእግዚአብሔር መንግሥት ምንም እዚህ ግባ የሚባል ራእይ እንደሌላቸው የታወቀ ነው። ብሏል።*

ጳውሎስ ፈቃዱ በቤተ ክርስቲያን ስለ ተንሰራፋው የዘር አባዜ ሲናገር፡-

> *ወንዛዊነት ሥር ሰዶ፣ ክልልተኝነት ተንሰራፍቶ፣ ዘረኝነታቸውን በክርስትና ሞንብል የሸፈኑ ሰዎች ስለ በዙ በእግዚአብሔር ቤት ሁሉም የራሱን ሰውና የራሱን ጎጥ ብቻ ለይቶ ለመጥቀም፣ ቋንቋውን ለማግነን ይውተረተራል። ጌታ ኢየሱስ ሲመጣ ምን ይሰን ይሆን?*[189] በማለት ሃሳቡን በጥያቄ ደምድሟል።

በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ዓለም ***"ኢትዮጵያውያን ወንጌልን ይዘው ወደ እኛ ይመጣሉ"*** ብላ እየጠበቀችና እግዚአብሔርም የመጨረሻው ዘመን የመንግሥቱ ዘሮች አድርጎ ሊያስነሣን በፈለገበት በዚህ ወሳኝ ጊዜ ላይ ጎሰኝነትና መንደርተኝነት መንፈሳዊነትን ተላብሰው ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ያንበረከኩ ቢመስልም እግዚአብሔር ለትውልዱ ያለውን ትልቅ ራእይ ለማፍረስ ጠላት የዘራው ዘር እንደሆነ አንስትም። ይህን እኩይ መንፈስ የሚያፈራርሱ የተሐድሶ አገልጋዮች በተለይ በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል ነበሩ አሁንም በብዛት በልዩ ኃይልና ቅባት ይነሣሉ።

ጠባብነትንና ጎሰኝነትን በቃሉ ላይ ቆመን በገሃድ ካልተቃወመን ውጤቱ ለማንም መልካም አይሆንም። ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ወደ አባቱ ሲጸልይ፡- *"እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ"* (ዮሐ. 17:22) ሲል ታላቁ ሐዋርያ ጳውሎስም የቅዱሳን አንድነት ሲገልጽ፡- *"አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፣ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፣ ወንድም ሴትም የለም ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ አንድ ሰው ናችሁና"* (ገላ.3:29) በማለት ዘመን ዘለቅ እውነት ነግሮናል። በጌታ ሙሉ ወንጌል፣ መካነ ኢየሱስ፣ ቃለ ሕይወት፣ ሕይወተ ብርሃን፣ 7000 ምርጦች፣...ፕሮቴስታንት፣ ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክ እንደሌሉ ሁሉ እንዲሁም አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ካንባታ፣ ሃድያ፣ ወላይታ፣ ሱማሌ፣ ሱርማ፣ ቦረና፣ ቡርጂ፣ ጋብራ፣ ጋሪ ...ወዘተ የለም! ሁሉም በእርሱ አንድ ናቸው። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ከሆነች ክርስቶስ አንድ እንጂ ብዙ አካሎች የለውም።

ትልቁ ችግራችን ብሔርና ቋንቋ ላይሆን ብሔርን፣ ቋንቋንና ባሕልን ሽፋን በማድረግ ቅምና በቀልን የተሞላ ልባችን ነው። ልባችን ለወንጌል እውነት ካልተንበረከከ መዝሙር፣ ስብከታችንና የአገልግሎት ግርግር ሰይጣን እየደገሰልን ካለው የጥፋት አጀንዳ ከሌላ ልሆኑን በፍጹም አይችሉም። እግዚአብሔር ልባችንን በቃሉና በመንፈሱ ይለውጥ! የእግዚአብሔር መንግሥት ከጎሳ፣ ከቋንቋ፣ ከባሕል፣ ከተለያየ አካባቢ፣ የነሮ ዘይቤና ንጽሮተ ዓለም ተጠርተን ለጠራን ጌታ የሚንኖርበት ግዛት እንጂ ሁላችንም የቋንቋችንና የባሕላችንን የበላይነትም ሆነ የበታችነት የሚንሰብክበት ቦታ አይደለም። ቋንቋ፣ ብሔር፣ ባሕል፣ መልካም ልምድና

[189] ጳውሎስ ፈ.ቃዱ. (2004 ዓ.ም)፣ *የብርሃን አንጋሥት*፣ ርኖቡት አታሚዎች፣ ገጽ 189

አስቶቻችን ለዚህ ሕይወት አስፈላጊና ጠቃሚ ሲሆኑ ወንጌል ለዚህ ሕይወትና ለዘላለመም የበላይና ብቸኛ ተስፋችን ነው። ይህ እውነት በአማኞች ልብ ሁሉ አሸናፍ ይሆን ዘንድ ተሐድሶ ያስፈልገናል። የኢትዮጵያ ክርስትና በብሔር ጉዳይ እጅግ ግራ እንደተጋባ ፕሮፌሰር መስፍን አስተውሎታቸውን ሲያስቀምጡ፦

> *ክርስትናም በጎሰኝነት እየታመሰ የኢትዮጵያዊነት የክብር ልብሱ እየተቀደደበት ነው፤ አስካሁን ድረስ ጎሰኝነትን ተጋፍጦ በቆራጥነት የተቋቋመው አስልምና ብቻ ነው*[190] ብለዋል። ለዓለም ጨውና ብርሃን መሆን ያለመቻል ብቻ ሳይሆን ጥላቻን ያለመቀባበልንና ጠባብነትን ማስፋፋታችን እጅግ ያሳዝናል። ለዚህ ተሐድሶ አያስፈልግም ወይ?

የነቀዘ አሠራር ዋሻ

ዶክተር ሳምሶን አስጢፋኖስ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አሠራር ላይ ባደረጉት ጥናት ላይ፦ *"የቀድሞው አሠራር የለሁኑን አሠራር ሊሸከመው አልቻለም፤ ሊፈነዳ ደርሷል"*[191] ካሉ በኋላ፤ በጥናታቸው በኢትዮጵያ ባሉት በ60 የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ላይ የታየውን አሳዛኝ ሁኔታ ሲጠቅሱ፦

> *በ60 አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በሚሊዮን የሚቆጠር የገንዘብ ምዝበራ አይቻለሁ፤ እርስ በርስ አስክ መታከስ የደረሱ አሉ፤ ከሽብርተኞች ጋር የተባበሩና የተደበቁ ሁሉ ተገኝተዋል። በእኛ ስም ጋጢአት ብቻ ሳይሆን፤ ወንጀል ሁሉ ተሠርቷል። የወንበዴዎች መደበቂያ ሆነናል*[192] ያሉት ያስደነግጣል።

ዶ/ር ልደቱ ዓለሙ ከፈኔ፤ አንድ የመንግሥትን ባለሥልጣን ንግግር ዋቢ በማድረግ፤ በአንድ አውደ ጥናት ላይ ባቀረቡት ጽሑፍ ፦

> *አናንተ ቤት መጽሐፍ ቅዱሳችሁ የሰላም መጽሐፍ ነው። ነገር ግን ሰላምን ያጠፋው ነገር ምንድነው?*[193] ይህን እንዲሉ ያደረጋቸውን ምክንያት ሲገልጹ፦ *"አስካሁን ድረስ 3 የኦሮቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሆነ አቤቱታ ቀርቦልናል፤ 4 ከሙስሊም ቀርቦልናል፤ 245 ከወንጌላውያን ቀርቦልናል።*[194]

ያሉት ያለንበትን አደገኛ ሁኔታና የቆምንበትን መስቀለኛ መንገድ ያመለክታል። ይህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶ ለኢትዮጵያ ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያናት በእርግጥ አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል። በአጠቃላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ

[190] መስፍን ወልደ ማርያም (2002 ዓ.ም)፤ አገቱኒ ተምረን ወጣን፤ አዲስ አበባ ገጽ 129
[191] *ማቴ፡ሰስ ግንቦት 2003 ዓ.ም*
[192] ዝኒ ከማሁ፤
[193] ልደቱ ዓለሙ ከፈኔ *(ዶ/ር) (መጋቢት 2004 ዓ.ም)* ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአመራር ገጽታ: ከመሪነት ጋር የተያያዙ ችግሮችና ሱሌያዊ አመራር የሚሰጠው መፍትሔ፤ በቤተር ላይፍ ሚኒስትሪ በተዘጋጀ ዓውደ ጥናት ለውይይት የቀረበ፤ አዲስ አበባ ፤ ገጽ 9
[194] *ዝኒ ከማሁ፤9*

የክርስቶስ አካል በሆንችው ቤተ ክርስቲያን እንደ ወረርሽኝ የተንሰራፋው አመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮና ልምምድ የተሐድሶ አስፈላጊነትን ያመለክታሉ። ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስ አካል እንደመሆኗ መጠን የሚያድሳት እርሱ ራሱ ነው። እርሱም ሕያው በሆነው ቃሉና በመንፈሱ አካሉን በማደስ በዚህ መጨረሻ ዘመን ላይ የመንግሥቱን ወንጌል በኃይል እንድትሰብክ ያደርጋታል። ትልቁ ጥያቄ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ያድሳል ወይ? ሳይሆን፤ ቤተ ክርስቲያን ለመታደስ ትፈቅዳለች ወይ? መሆን አለበት።

"ተሐድሶ ለቤተ ክርስቲያን አያስፈልጋትም"

ዲያቆን እሱባለው በየነ (ናትናኤል) *"የሚለወጥ ዓለም የማይለወጥ ለምላክ ተሐድሶ ለማን?"* በሚል ርዕስ ባሳተመው መጽሐፍ፤ ተሐድሶ *የሚለውን ሐሳብ ማርቲን ሉተር እንደ ጀመረና ያነሣቸው ጥያቄዎች በወቅቱ ተገቢና አሳማኝ ሲሆኑ፤ በመጨረሻ ግን የተነሣበት ግብ በመተው ስሕተት ውስጥ መዘፈቁን*[195] እርሱና ተከታዮቹ (ፕሮቴስታንት) መታረምን እንቢ ብለው ለለንዳዱ *በአርቶዶክስ መናፍቅ የሚል ስም እንደተሰጣቸው*[196] ገልጸዋል። መሪራስ አማንም ደግሞ ሉተርና ፈለጉን የተከተሉ ክድነት መንገድ እንደጠፉ ግምቱን ሲናገር፦ *ሉተርና የሉተር መንፈስ የተሰራጨባቸው ቅዱሳንና ጻድቃንን ሲቃወመ. ስማቸውም እንዳይነሣ ይሰብካሉ. ምክንያቱም ለቅዱሳን የተሰጠው ጸጋ በእነርሱ ላይ የለምና ከቅዱሳንና ከጻድቃን ጋር የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ አልታደሉምና*[197] ብሏል።

መሪራስ እንዳሉ ሉተር የተቃወመው ቅዱሳንና ጻድቃንን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል የጋረዱ፤ ትውፊት፤ ድርሳናት የጳጳሳት ገደብ የለሽ ሥልጣንና ልቅ የእኗኗር ዘይቤ እንደ ነበር መዛግብት ያወሳሉ። ዛሬ የሉተርን ፈለግ የሚከተሉ አብያተ ክርስቲያናት ሐዋርያት የሰበኩትን ወንጌል እንጂ የቅዱሳንና ጻድቃን ስሞች አይሰበኩም። በዓላትን በስማቸው አያከብሩም፤ በስማቸውም ድግስ አይደግሱም፤ እንዲያማልዱላቸውም ለመናቸውን ወደ እነርሱ አያቀርቡም። ይህን የማያደርጉበት ምክንያት ቅዱሳንና ጻድቃንን ስለሚጠሉና ስለማያከብሩ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚያ እንዲያደርጉ ስለማያዛቸው ነው። በወንጌል እውነት የዳነ ሁሉ የቅዱሳንን የሕይወት ምሳሌነት መከተል፤ በመልካም ሥራቸው እነርሱን መምሰል፤ እነርሱ ለጌታና ለወንጌል እንደኖሩ መኖር ይገባቸዋል። ይህን ሁሉ የሚያደርጉት በእነርሱ ላይ ያለው ጸጋ እንዲያድናቸው ሳይሆን እነርሱ ባመኑት ጌታ ጸጋ አምነው ከዘላለም ሞትና ኩነኔ ስለዳኑ ነው።

[195] ዲያቆን እሱባለው በየነ(ናትናኤል) ፤*(2004 ዓ.ም)*፤*የማይለወጥ ዓለም የማይለወጥ አምላክ ተሐድሶ ማን?* ገጽ 32
[196] ዝኒ ከማሁ፤ገጽ 35
[197] መሪራስ አማን ፤*(2001 ዓ.ም)* ፤ መጽሐፍ ክብር፤ ገጽ 356

እንዲሁም አበበ ጋሻዬ፡-

የፐሮቴስታንት ሃይማኖት መሥራች የነበረው ሉተር የዚህች ቤተ ክርስቲያን አባል ስለነበረ፣ በራሱ ምክንያት ከቤተ ክርስቲያኒቱ ተለይቶ ከወጣ በኋላ፣ እዚያው ሆኖ የተማረውን ይህን ክፉ ትምህርት እርሱም በተግባር ሲተረጉመው ኖሯል። ለተከታዮቹም አውርሷቸዋል። ...በመሆኑም የዛሬዎቹ ሉተራውያን በክርስትና ሃይማኖት ስም እያካሄዱት ያለውን ጠብ አጫሪ ተግባር ኮርም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የተማሩት ነው ማለት ይቻላል[198] ብለዋል። ይህ ከጥላቻ የመነጭ ባዶ አሳብ ነው።

ሉተር ከካቶሊክ ቤት ክርስቲያን የወጣው ተገፍቶ እንደነበር በሰፊው የተዘገበ እውነት ነው። ቤተ ክርስቲያን በሰዋዊ ትውፊት፣ ለእግዚአብሔር ቃል ዕውቅና በማይሰጥ የሰው ልምድና ሥርዓት መመራት የለባትም በማለቱ የካቶሊክ ጳጳሳት እንዳሳደዱት ታሪክ ምስክር ነው። ሉተርና ተከታዮቹ እንደ ማንኛውም ሰው የራሳቸው ድካም እንዳላቸው የታወቀ ሲሆን ክፉ እንደሆኑ ግን ቃሉ አይናገርም። ከጥንት ዘመን ጀምሮ ባልተረጋገጠ፣ ገሰባውን ከፍሬው ሳይለዩ ጥራዝ ነጥቀ አመለካከት ተጠቂ የሆኑ ግለሰቦችና *"ቤተ ክርስቲያን"* በጅምላ እንደምያወግዙት ቢሆን ኖሮ፣ በእግዚአብሔር መንግሥት ደጅ ማንም ዝር ባላለ ነበር። በእግዚአብሔር ቃል ያልተወገዘን ግለሰቦችም ሆኑ ቤተ ክርስቲያን ብያወግዙ ዋጋ የለውም።

ዲያቆን እሱባለው ስለ ተሐድሶ ሲናገር፣ *በመጀመሪያ በእምነት ውስጥ ተሐድሶ (Reformation) የሚለው ቃል አያስፈልግም*፣[199] ቤተ ክርስቲያን (እምነት) *ተሐድሶ እንደሚያስፈልጋት በቀይ መስመር አስምሬ አልፋለሁ*።[200] ተሐድሶ የሚለው ጽንሰ ሐሳብ *ለሥጋዊ ሕይወታችን እንጂ ለቤተ ክርስቲያን አያስፈልግም*[201] ብሏል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን *ተሐድሶ ለቤተ ክርስቲያን የሞትና የሕይወት ጉዳይ እንደሆነ ያስቀምጣል*። የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሲሆን ቃሉና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይህን እውነት ያረጋግጣሉ። ሰለሞን አበበ ገብረ መድኅን የነገረ መለኮት መምህርና በኢቫንጀሊካል ቴዎሎጂካል ኮሌጅ (ኢቲሲ) ረዳት የአካዳሚክ ዲን ሆነው በመሥራት ላይ የሚገኙ ሲሆኑ *"የትሩፋን ናፍቆት"* በሚል መጽሐፋቸው የተሐድሶን አስፈላጊነት ሲናገሩ፡-

በኑፋቄ ተከብበንና በዐመፃ ተውጠን እያለን 'ካፈርኩ አይመልሰኝ' በሚል ድርቅና 'ሃይማኖት አይታደስም' ብለን ብንፎክር ፈውሳችንን ያዘገየው እንደሆነ እንጂ ሐቁን አይለውጠም። ማንኛውንም ነገር በየባልነቱ ደርበን ለማምለክ ብንሞክር፣ ይህ ብክለት ነውና ሃይማኖት ይታደሳል። ማንኛውም ነገር ከመለኮታዊው አስተምህሮ በተፃሮ ሲቆም፣ ወይም ቅይጥነት ሲዳበለው ተሐድሶ ያስፈልገዋል። የእግዚአብሔር ሰው ነኝ የሚል ሁሉ

[198] አበበ ጋሻዬ *(2005 ዓ.ም)* ፣ትምህርተ ተዋሕዶ፣ ገጽ 229
[199] *ዝኒ ከማሁ*፣ ገጽ *36*
[200] *ዝኒ ከማሁ*፣ገጽ *37*
[201] *ዝኒ ከማሁ*፣ ገጽ *39*

ለምለኩተ ባዕድን፣ ርኩሰትን፣ ጥንቆላን፣ ኑፋቄን፣ በወንጌል ሰም መነገድን፣ ወዘተ. ማፍረስ ግድ ይለዋል።[202]

ቅዱስ ቃሉ ፍጹም ስለሆነ አይታደስም፤ ቅዱሳን በዚህ ምድር ሳለን ኅጹማን ስላይደለን ዕለት ዕለት በመንፈሱና በቃሉ እንታደሳለን። ለዚህ ነው ታላቁ ሐዋርያ ጳውሎስ "የውስጥ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል" (2ቆሮ.5፡ 16)፤ ብሎ የተናገረው። ቅዱሳን በንስሐ ዕለት ዕለት በጸጋው ዙፋን ፊት ቀርበው የሚታደሱ ከሆነ፣ በቅዱሳን ሕብረት የተገነባች ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ አያስፈልጋትም ማለት እንዴት እንችላለን? እግዚአብሔር አይታደስም፤ ነገር ግን የእርሱ የሆኑት ግን ኃይላቸውን እንደሚያድሱ ቃሉ ሞቢ መስጠቱ ለሕዝቡ የተሐድሶ አስፈላጊነትን ያመለክታል። በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ቤተ ክርስቲያን ፍጹም የሆነችው ጌታ የሞተላት ተቋም በመሆኗ እንጂ፣ የፍጹማን ገባኤ ስለ ሆነች አይደለም። ወደ ፍጽምነት በምታደርገው ጉዞ በቃሉና በመንፈሱ መታደስ (መለወጥ) ምርጫ ሳይሆን ግዴታዋ ነው። ተሐድሶ ለውጥ ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያን በቃሉና በመንፈሱ አማካይነት ለውጥ ዕለት ዕለት ያስፈልጋታል።

ያለመለወጥ እንጂ ለውጥ ለቤተ ክርስቲያን አዲስ አይደለም

በ21ኛው ክፍለ ዘመን እንደ ትልቅ አደጋ የሚቆጠረው ለውጥ ሳይሆን ያለመለወጥ ነው። በዓለማችን በእያንዳንዱ ሚሊ ሰከንድ ትልልቅ የለውጥ አብዮቶች ይካሄዳሉ። ለውጥ የተለመደ ክስተት ሆኗል። ዊትን እና ካሜሮን የተባሉ ጸሐፊዎች ስለዚህ ሲናገሩ፡-

በዓለማችን ላይ ለመገመትና ለመተንተን እጅግ በጣም አስቸጋሪና ለመቁጠር የሚያዳግቱ ለውጦች በተደራራቢነት እየተካሄዱ ስለሆነ ከአሥር ዓመታት በኋላ በእርግጠኝነት የዓለማችን ገጽታ ምን እንደምትመስል መገመት በፍጹም አይቻልም[203] ብለዋል።

በዓይነ ቅጽበት እየተለዋወጠች ባለችው ዓለም ላይ ያለች የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አትለወጥም፤ ለውጥም አያስፈልጋትም ማለት ትልቅ ስህተት ነው። ቤተ ክርስቲያን ትለወጣለች፤ ማለትም ለትውልዱ ደራሽና ተደራሽ መሆን እንደሚገባት ለማመልከት እንጂ መልዕክቷን ትለውጣለች ማለት እንዳልሆነ መታወቅ አለበት። ወንጌል አይለወጥም። ከቀደመው እንደተገኘ ማመንና ማወቅ መልካም ነው፤ የቀደመው አሠራር፣ ሥርዓትና ወግ እሥረኛ መሆን ደግሞ ከሞት ጋር ውል እንደመፈራረም ነው። በቀደመው መልካም ነገር ላይ ቆመን ለሚበልጥ ለውጥና ተሐድሶ መነሣት የሕያውነት ምልክት ነው።

[202] ሰለሞን አበበ ገብረ መድኅን *(ሺዩኛ ዓ.ም)*፣ የትሩፋን ናፍቆት፣ ርኖቦት አታሚዎች አዲስ አበባ፣ ገጽ 118
[203] Whetten D.A and Cameron, K.S.(2010), (8th Ed), *Developing Managemenet Skills*, Boston, Prentic Hall, p450

ቤተ ክርስቲያን የተወለደችው በለውጥ ለለውጥም ነው። ገና እንደተወለደች ትልልቅ ለውጦች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተካሂደዋል። በሐዋርያት ሥራ የመጀመሪያዪቷ ቤተ ክርስቲያን በምን ዓይነት የለውጥ ሂደት ውስጥ እንዳለፈች ጥቂቶቹን እንመልከት፦

- ቀዳሚና ዋና መሪዎች ሲደበዝዙ በወንጌላት ውስጥ የምናውቃቸው እነ እንድርያስ፣ ቶማስ፣ በርቴሎምዮስ እና ማቴዎስ (ከሐዋ.1:13) የት እንደደረሱ ምንም ፍንጭ እንኳ አይሰጠንም።

- ከጌታ ሐዋርያት አንዱና በገንዘብ ላይ ተሹሞ የነበረው የይሁዳ ውድቀት፣ (የሐዋ.1:18-19)

- በጰንጠቆስጤው ቀን 3 ሺህ የሃይማኖተኞች የሆኑ አይሁዶች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መቀበልና የመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም መመሥረት (የሐዋ.2)።

- በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ የተፈጠረው አድሎና ወገንተኝነት፣ ሐዋርያት ራሳቸውን ለቃሉና ለጸሎት በመለየት፣ ለሌሎች ኃላፊነት በመስጠት አዲስ አሠራርና የአገልግሎት በር መክፈት (የሐዋ.6)።

- የቀድሞ ቀንደኛ የቅዱሳን አሳዳጅና የሃይማኖት አክራሪ ሳኦል(ጳውሎስ) ክርስቶስን በመቀበል ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ተካይና መሪ መሆን። (ሐዋ. 9)

- ሮማዊ፣ አይሁዳዊ፣ አረባዊና አፍሪካዊ በአንድነት በቤተ ክርስቲያን አብረው ጌታን ማምለክና ማገልገል። ምኩራብ የአይሁዶች የአምልኮ ቦታ እንደሆነ የታወቀ ነበር። በክርስቶስ ኢየሱስ የተመሠረተችው የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ሁሉን አቀፍ ሆና የክርስቶስን መልክ ለዓለም በመግለጧ "ክርስቲያን" የሚል ስም በሌሎች ወጥቶላቸዋል። ጥቁሮች ወደ ቤተ ክርስቲያን ተጨመሩ (ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ሐዋ.8:26-40) ስምዖን ነጌሪ የተባለ (የሐዋ.13:1)። ይህም ቤተ ክርስቲያን ቋንቋን፣ ድንበርን፣ ባሕልንና አካባቢን አልፋ የምትሄድ መሆኗን ያመለክታል። ይህ ትልቅ ጥርመሳ ነው።

- በመንፈስ ቅዱስ እሳት (የሐዋ.2)ና በታላቅ የመከራ (የሐዋ.8) በትር ከኢየሩሳሌም ዋሻ አልወጣ ያለው የሐዋርያት አፈቀላጤ የነበረው ጴጥሮስ *"ጌታ ሆይ አይሆንም"(የሐዋ.10:14)* በማለት ለውጥን እየተቃወመ መለወጥ።

- የጸጋ ወንጌል እየተሰበከ ሾልኮ ሊገባ የነበረውን ጁዳይዘር *(ሰንድ ሰው እውነተኛ ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት የሙሴን ሕግ በሚገባ መጠበቅ አለበት ባይ ናቸው)* የኑፋቄ ትምህርት ነጥሎ የመታ የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ፤ (የሐዋ.15)

- ሐዋርያት ሥራ ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ አሥራ ሁለት ኢየሩሳሌም የሐዋርያት መቀመጫና የዓለም መንፈሳዊ ነገር ማዕከል ሆና በሐዋርያት መሪነት በዓለም አቀፍ ከአይሁድ ለአይሁድ የወንጌል አገልግሎት ተጠምዳው ነበር። በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ አሥራ ሦስት ታሪኩ ተገለበጠ። ጌታ ካረገ 40 ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የክርስትና ማዕከል ወደ አንጾኪያ ተቀየረ። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አይሁድ የሆኑ ሐዋርያት ብቻ ሳይሆኑ በጌታ የተጠሩ ቅዱሳን ወንጌልን ይዘው ወደ ዓለም የመሄድ አዲስ ምዕራፍ ተከፈተ። ይህ ያልተለመደ ታላቅ ለውጥ ነበር። ከምዕራፍ አሥራ ሦስት እስከ ሃያ ስምንት በጴጥሮስ ምትክ ስመ ተደጋግሞ የተነሣው የአዲሱ እንቅስቃሴ መሪ ጳውሎስ ሆኖ እናገኛለን።

በሐዋርያት ሥራ ከምዕራፍ አሥራ ሦስት ቀጥሎ ያሉ ምዕራፎች ቤተ ክርስቲያን በተለያየ ባሕል፣ ቋንቋ፣ አገር፣ ሕዝብና ዓለም ላይ ያመጣቸውን ጫና፣ ያስመዘገበችውን ዕድገትና ለውጥ ያሳየናል። ቤተ ክርስቲያን የመላዕክት ጉባኤ ሳትሆን የአማኞች አንድነትና ኅብረት ናት። አማኞች በለውጥ ጉዳና ላይ እየነጎደች ባለችው ዓለም እየኖሩ ለውጡ ቤተ ክርስቲያንን አይነካትም ማለት ዘበት ነው። እንዲሁም ዓለም በተለዋወጠች መጠን ቤተ ክርስቲያን ትለወጣለች ማለት ሳይሆን ቤተ ክርስቲያን በዓለም ለውጥ እንዳትለወጥ በቃሉና በመንፈሱ ትውልዱን በሚመጥን መልኩ እውነትን መናገር እንድትችል ሁሌ በቃሉና በመንፈሱ መለወጥ እንዳለባት ለማመልከት ነው።

የናቤል ሽልማት ተሸላሚ የሆኑ ስትንባኪ ስለ ለውጥ ሲናገሩ፦ *"የሰው ልጅ ዕድሜው ባረጀ መጠን በተለይ ለተሻለ ሕይወት ያሚያዘጋጀውን ለውጥ በብርቱ ይቃወማል"* እንዳሉት የምድራችን ቤተ ክርስቲያን ለውጥን አጥብቃ የምትቃወመው በጣም ስላረጀች ይሆን? ጆርጅ ባርናርድ ሾው *"አመለካከታቸውን የማይለውጡ ሰዎች አንዳች ነገር መለወጥ አይችሉም"*[204] በማለት የማንለወጥ ከሆነ ለመለወጥ እንደማንችል ይፋ አድርገዋል። ቤተ ክርስቲያን ዕለት ዕለት በቃሉና በመንፈሱ የማትለወጥ ከሆነ በለውጥ ሀዲድ ላይ እየተምዘገዘገች ላለችው ዓለም ደራሽ ልትሆን አትችልም። ተለውጠን ለቤተ ክርስቲያን ለውጥ ራስን ማቅረብ እንዳለብን አንዘንጋ።

ወንጌልን የሰበከ ሁሉ

"ጴንጤ" ወይም *" መናፍቅ"* ተብሎ የሚፈረጅበት አገር

[204] *http://www.goodreads.com/quotes/tag/change*

"የሚለወጥ ዓለም የማይለወጥ አምላክ ተሐድሶ ለማን?" መጽሐፍ ደራሲ እንዳለት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፕሮቴስታንቶችን "መናፍቅ" ትል ይሆን? በአገራችን ብዙዎች መናፍቅ የሚለውን ቃል ጽንሰ ሐሳብ ባለመረዳት ያልተቀበሉትን አገልግሎት ሁሉ መናፍቅ ብሎ መፈረጅ የተለመደ ነው። በአገራችን በተለይ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የተባለውን ሁሉ ከማመን ውጪ ምክንያታዊነትና በእግዚአብሔር ቃል እውነት ላይ መነጋገር አልተለመደም። የአንድ ሃይማኖትም ሆነ ርዕዮተዓለም ደጋፊ ካልሆንክ ወዲያው በተቃዋሚነት ትፈረጃለህ። ውሸት ፣በሰው ልብ ነግሣ እውነት በአደባባይ የተጣለች ትመስላለች። ከዚህም የተነሣ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ በክርስትና ስም በገሃድ የሚያራምዱ እውነትን በተቀመጭ ብዙሃን ሲሞካሹ በቃሉ እውነት እየኖሩ እውነትን በሚሰብኩት የእግዚአብሔር ሰዎች በተቃራኒው የባሕርይ ገደላ ሲካሄድባቸውና በአደባባይ ሲወገዙ ይታያሉ።

ኢየሱስ ሲናገር፦*"...የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል"(ዮሐ.16፡2)* እንዳለው የእውነተኛ ወንጌል አገልጋዮች መልካም ስምና አገልግሎት ገዳዮች የብርሃን መልአክን መልክ ተላብሰው እየታዩ ናቸው። ያም ሆኖ በእውነት ላይ ማንም ምንም ሊያደርግ አልቻለም። እውነት ተናጋሪን መግደል ቢቻልም እውነትን መግደል ግን በፍጹም አይታሰብም። እውነት ከራሱ ውጪ ሌላ ደጋፊ አይፈልግም። እውነት ሁሌ አሸናፊ ስለሆነ ለማሸነፍ ትፎዘ አያስፈልገውም፤ ተቃውሞም ምንም ስለማያደርገው አይሸበርም። ኢየሱስ እውነት ነው። መምህር ብሩክ ገብረ-ሊባኖስ ተስፋዬ መናፍቅ እያሉ የመፈረጅ ወረርሽኝ በቤተ ክህነት እንዴት እንደተዛመተ እንዲህ ይገልጻል፦

> *እንደ ግለሰቦቹ እምነት እነርሱ ከሰበኩት ውጭ ያለው ስብከት 'ክህደትና ኑፋቄ' ነው፤ የእነርሱ አባል ያልሆነ ሰባኪም ' መናፍቅ ተሐድሶ' ነው፤ እነርሱ ያልዘመሩት መዝሙር 'ዘፈን' ነው።... ግለሰቦቹ ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን መናፍቅ ብለው ለማወገዝ ደረጃቸውና ዓቅማቸው ባይፈቀድላቸውም ቤተ ክህነት ውስጥ ደረጃ መዳቢ ባለሥልጣን ስለሌለ እንደ ፈለጉ ስም ያጠፋሉ፤ ይሳደባሉ ይዘልፋሉ፤ ያወግዛሉ፤ ይገዝታሉ።*[205]

የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እንደሆኑ በመጽሐፉ የገለጹት ሊቀ ማእምራን ዲቡ ኩሉ በቤተ ክርስቲያኑ ስለተንሰራፋው የ"ዘመነ-ገዝ ሁኔታ እንዲህ ብሏል፦

> *መሪጌታ እገሌ፣ ቄስ እገሌ፣ አቡነ እገሌ መምህር እገሌ ዘማሪ እገሌ ወ.ዘ.ተ ተሐድሶ ናቸው መወገዝና መባረር አለባቸው እየተባለ ቤተ ክርስቲያኗን ምዕመን ብቻ ለማስቀረት ሰይጣን እየተጠቀመባቸው ያሉ ወገኖች አሉ። እነዚህ ሰዎች ይህንን በማድረጋቸው ንስሐ ሊገቡ ይገባል*[206] *ብለዋል።*

[205] *የሰው ያለህ፣ 2005 ዓ.ም ገጽ 408*

[206] ሊቀ ማእምራን ዲቡ ኩሉ *(2005 ዓ.ም)* ፣ ሉሬ፣ አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ፣ ገጽ 85

አሳዛኙ ነገር የክርስትና ደሴት በተባሉች አገራችን ነቢያቶች የተነበዩለት፣ በሥጋ የተገለጠው የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ የሚሰብኩ *"ጴንጤ፣ ተሐድሶ፣ መናፍቅ"* ተብለው ስለሚወገዙ ወንጌልን በገሃድ እንዳይሰብኩ ብዙዎች በፍርሃት ተጠፍንገዋል። አብዛኛው የስብከትን መድረክ የተቆጣጠሩ ያልተማሩ አስተማሪዎች፣ የወንጌል ስብከት ጥሪም ሆነ ዕውቀቱ ስለሌላቸው መንጋውን በማሳሳት ላይ ይገኛሉ። ስለዚህም መጋቤ አእላፍ መክብብ ትዝብቱን እንዲህ ብሎ አስፍሮዋል፦

> *አንዳንዶቹማ ያለችሎታቸው በየዘሩት የስብከት ወንጌል መድረክ ሰንቱን ሕዝብ በማሳሳት ግራ ሲያጋቡ ይኖራሉ። አብዛኛውን ጊዜ ትምህርታቸውም ሆነ ስብከታቸው እግዚአብሔርን ማአከል አያደርግም። ኢየሱስ ክርስቶስ ብሎ መናገርም በተሐድሶነት ያስጠረጥረናል ብለው በስሙ የሚያፍሩበት ብዙዎች ናቸው።*[207]

ጥቂቶች በነፍሳቸው ተወራርደው ክብራቸውን ጥለው የጌታን ወንጌል በድፍረት ሲሰብኩ ለእውነትና ለቤተ ክርስቲያን ቀኒዓ እንደሆኑ በሚናገሩ ሰዎች *"የተሐድሶ መናፍቅ"* ተብለው የባሕሪይ ገደላ ሲፈጸሚባቸውና እንደ አርዮስ ሲወገዙ ማየት በአገራችን የተለመደ ነው። ዛሬ በሰንደን እንግልዝ መንገድ ላይ ቆሞ ግብረሰዶማዊነትን ትክክለኛ የአኗኗሪ ዘይቤ እንደሆነ ማወጅ የማያስጠይቅና ማንንም የማያስከፋ ሲሆን ኢየሱስ ብቸኛ የዓለም መድኃኒት እንደሆነ በአደባባይ መስበክ ግን ለእሥራትና ለወህኒ ይዳርጋል። እንደዚሁም በኢትዮጵያ በአንዳንዶች ዘንድ ስለ መላዕክት፣ ስለ ማርያም፣ ስለሰንበት፣ ስለቅዱስ እገሌ አዳኝነት መስበክና መጻፍ የተለመደ ሲሆን የዓለም አዳኝ እንደ ሆነ ነቢያት፣ ሐዋርያትና የቤተ ክርስቲያን አበው የሰበኩት የጠራውን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መስበክ ፍርድ ቤት ባያስቆምም መናፍቅ፣ ጴንጤ፣ መጤ፣ የአገር ጠላት፣ ፀረ ማርያም የሚሉ ፍረጃ ተጠቂ ያደርጋል። ከተሳዳጆች ጋር የሚቆም እግዚአብሔር በእውነት ላይ ቆመው ውሸትን እየሞገቱ ባሉ ጥቂቶች ምድራችንን ለዘመናት ከተጠፈረችበት እውነት መሳይ ውሸት ይፈታታል ብዬ አምናለሁ።

የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ፣ የኃጢአት ኑዛዜና ዳግም በመወለድ በአዲስ ሕይወት ከክርስቶስ ጋር መኖር እንዳለብን የማይሰበክበት "ወንጌል" ማንም ይስበክ፣ የትም ይሰበክ መንፈሳዊ ወንጀል ነው። በምድር ሕግ ባንጠየቅም የዘላለም ጌታ እያንዳንዳችንን እንደሚጠይቀን ቃሉ ይናገራል። *"እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሥሳችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንቆም ይገባናል" (2ቆሮ.5:10)።* *"እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክበዋል" (ሮሚ.2:6)።* ወንጌል አጭርና ግለጽ ሲሆን ወንጌል ያልገባቸው *"ሰባቂዎች"* የምድሩንና የሰማዩን ቀይጠው ሲያወሳስቡት ማየት በእኛ ዘመን የተጀመረ ሳይሆን የነበረ ነው። ወንጌል ግን ሁሉንም ያሸንፋል። የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሐዋርያትን ሲልክ የማይለወጠውን ወንጌል ሰጥቷቸው ነበር፦ *"...የማይለወጠውን ቅዱስ*

[207] መክብብ አጥናው (መጋቤ አእላፍ) *(2004 ዓ.ም)*፣ አምስተኛው ንብሌ ዕድሜ ቀጥል፣ ትምህርት ዐዘል ሶአቡዶች ሥዳዮታ፣ ክፍል አንድ፣ አዲስ አበባ ፣ ገጽ 12

ወንጌል ከዐሐይ መውጫ እስከ መጥለቂያው ድረስ በአጃቸው ላከ"(ማር.16:8)። "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" ሐዋርያ ጳውሎስ ማንን ይሰብክ እንደነበር ሲናገር:- "እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን" (1ቆሮ. 1:23) ካለ በኋላ ራሱንና እኛንም ሲያስጠነቅቅ *"ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ" (1ቆሮ.9:16)*። ብሏል።

መናፍቅ ማን ነው?

በተለይ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ኑፋቄ፣ መናፍቅ፣ መናፍቅነት የሚሉት መጠሪያዎች ለጆሮአችን አዲስ አይደሉም። ፍቺው ከሊቃውንቱ መዝገበ ቃላት ሲፈተሽ ደስታ ተክለወልድ (በገጽ 794) ላይ ኑፋቄን (መናፍቅን):- *"ሃይማኖተ ግማሽ"* ሲሉት፣ ከሣቴ ብርሃን ተሰማ የተሰኘው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ደግሞ (ገጽ 110) ላይ *"ከእውነተኛ ሃይማኖት መውጣት፣ በፈጣሪ በእግዚአብሔር የማያምን፣ ይልቁን የኢየሱስ መድኃኒትነት፣ የመንፈስ ቅዱስን ሕይወትነት የማያምን የሚክድ"* ነው፤ ብሎ ይፈታዋል። የሊቃውንቱ ትርጉም ግልጽና ትክክል ነው። የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ሸራርፎ፣ ቆርጦ፣ ገምሶ የሚያስተላልፍና የሚሰብክ ሁሉ በኑፋቄነት ይመደባል።

በተለይ የኢየሱስ ክርስቶስን መድኃኒትነትና የመንፈሱን ሕይወትነት የማይቀበሉ መናፍቃን ሲሆኑ ያፈነገጠና የጉደለ ትምህርት ኑፋቄ ነው። ሐዋርያ ጳውሎስም ስለዚህ ሲናገር:- *"እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፣ የተረገመ ይሁን። አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፣ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን" (ገላ.1:6-8 መ.ይ.ት.)*። በማለት ለሰው ልጆች የተሰጠው የመዳን መንገድ የሚያመለክት የወንጌል ቃል የማይደለዝ፣ማስተካከያ የማይፈልግ፣ የማይቀነስና የማይጨመርበት እንደሆነ በግልጽ አስቀምጧል። ከዚህ የተለየ ሁሉ ኑፋቄ ነው። ተስፋዬ ሮቢሌ በዐቃብያነ ክርስትና *(Apologetics)* ላይ በዛ ያሉ መጻሕፍት ያቀበለን የነገረ መለኮት ሊቅ ሲሆን፣ "ዐበይት መናፍቃን" በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፍ፣ ዕውቅ የነገረ መለኮት ምሁራንን ዋቢ በማድረግ መናፍቅ የሚለውን ቃል ምንነት ሲያስረዱ:-

> *ከክርስትና እምነት የወጡ መናፍቃን ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ፣በመሪዎቻቸው ወይም በድርጅቶቻቸው የተሰጠውን የተወሰነ አስተምህሮአዊ ሥርዓት የሚከተሉ፣ ይህም አስተምህሮአዊ ሥርዓት ከሥልሳ ስድስቱ የመጽሐፍ ቅዱሳን ጽሑፎች የተቀዳውን የክርስትና እምነት መሠረታዊ አስትምህሮ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ትምህርት የሚክዱትን መናፍቃን ብለን እንጠራቸዋለን።[208]* ብለዋል።

[208] ተስፋዬ ሮቢሌ *(2001 ዓ.ም)* ፣ዐበይት መናፍቃን፣ ገጽ 11

በመቀጠልም:-

> *መሠረታዊ በሆኑ ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፣ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንና የፐሮቴስታንቶች (የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት) አንድ ዓይነት አቋም አላቸው። ምናልባት አብያተ ክርስቲያናት ያላቸውን መሠረተ እምነት አማኒያኖቹ ላይረዱት ይችላሉ። እንዲረዱት ማድረግ ተገቢ ቢሆንም፣ ቤተ ክርስቲያናቹን እንደ መናፍቅ መቁጠር ግን ፍጹም ስሕተት ነው[209]* ብለዋል።

በዚህ ላይ ሳልጠቅስ የማላልፈውና በጣም ያስገረመኝ አንድ ጉዳይ፣ በዚህ ጥናት ብዙ የአገራችን መጻሕፍትና መረጃዎችን ሳገላብጥ፣ አብዛኛው የኢትዮጵያ የፐሮቴስታንት የነገረ መለኮት ጸሐፍት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር የመሠረተ እምነት አንድነት እንዳላቸው ሲቀበሉ፣ አብዛኛው የኦርቶዶክስ ጸሐፍት ግን ሌላው ቀርቶ የፐሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናትን *"ቤተ ክርስቲያን"* ብለው ለመጥራት እንኳ እንደማይፈልጉና ከአንድነት ይልቅ፣ ያለውን ልዩነት እጅግ ለማጉላት ሲታገሉ መታየታቸው ነው። አንድነታችን የመጣው ከክርክራችን ሳይሆን ሠመሪያችን ብለን ከያዝነው በአጃችን ካለው ቃልና የምንጠራው አምላክ አንድ መሆኑ ነው። አንዳንድ የኦርቶዶክስ ጸሐፍት እንደሚሉት ፕሮቴስታንቶች መናፍቅ ከሆኑ ቤተ ክርስቲያናቸው በአህጉርና በዓለም አቀፍ ደረጃ የአብያተ ክርስቲያናት ማህበር ላይ የመሠረተ እምነታቸውን ተቀብላ "ከመናፍቅ-ፕሮቴስታንቶች" ጋር ለምን ጎብረት መሠረተች? ምናልባትም ይህ አመለካከት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አቋም ሳይሆን የቃሉን ትርጉም ያልተረዱት አንዳንድ ጸሐፊዎች የሚያካሂዱት መሠረተ የለሽ አሳብ ሊሆን ይችላል። ጥር 30 ቀን 2001 ዓ.ም፤ በአፍሪካ ጎብረት አዳራሽ ዓለማው በኢትዮጵያ የአብያተ ክርስቲያናት ጎብረት ምሥረታ ላይ ለመመካከር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ዙተ ክርስቲያንና የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት መሪዎች አንድ ላይ ተቀምጠው ነበር።[210] በዚህ የምክክር ጉባኤ ላይ ጥናታዊ ጽሑፍ ካቀረቡት መካከል በኦርቶዶክሳውያን በኩል የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት ምክትል ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ንቡረኢድ ኤልያስ አብርሃ ይገኙበታል። እሳቸው ለዚህ ጉባኤ ጥናታዊ ጽሑፋቸውን ሲያቀርቡ:-

> *ጥንትም አሁንም ለወደፊቱም የማይለወጠው የእግዚአብሔር ዓላማ፣ ሁሉንም በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክርስቶስ መጠቅለል ነው። የአሁኑ ትውልድም መሥራት ያለበት፣ ይህንኑ የእግዚአብሔር ዓላማ በመቀበል ነው። ነገር ግን ወደዚህ ውሕደት እንዴት መምጣት ይቻላል? የሚል ጥያቄ ቢኖር፣ በመጀመሪያ በመከባበር፣ በመተጋገዝና በፍቅር ላይ የተመሠረተ ጎብረት መፍጠር...መፍትሔ ሊሆን ይችላል።[211]*

[209] ገዘ ከማሁ፣ ገጽ 15
[210] ማቴቴስ መንፈሳዊ መጽሔት፣ ቁጥር 10 መጋቢት 2001 ዓ.ም
[211] ኤልያስ አብርሃ (ንቡረአድ)፣ የአብያተ ክርስቲያናት ጎብረት ጥቅም እና የልዩነታቸው ጉዳይ (ጥናታዊ ጽሑፍ ያልታተመ)

ብለው የተናገሩት ቤተ ክርስቲያናቸው ለሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ያላትን ትልቅ ልብና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አቋም በግልጽ ያመለክታል።

ተሐድሶ የእግዚአብሔርን ቃል የመስመጥ ሂደት ሳይሆን፣ የሰዎችን ያረጀ ሕይወት፣ ሊመጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምምዶችና ስለተምህሮዎችን በማይስመጠው ቃሉና መንፈሱ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የመስመጥ ሂደት ነው።

የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ያልነበረውንና የሌለውን መፍጠር ማለት አይደለም። የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ በክርስትና ሃይማኖት መሠረተ እምነት ላይ ለውጥ ማድረግም አይደለም። የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ የቤተ እምነት ስም የበላይነት የሚሰበክበት ምስባክም አይደለም። የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ኦርቶዶክስን ፕሮቴስታንት ወይም ካቶሊክን ኦርቶዶክስ አሊያም ፕሮቴስታንትን ኦርቶዶክስ የማድረግ ዘመቻ በፍጹም አይደለም። ሊሆንም በፍጹም አይገባም። የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ በቃሉና በመንፈሱ የልብ ለውጥ እንጂ የድርጅት ስም ወይም የታፔላ ለውጥ አይደለም።

ተሐድሶ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያንን እንደ እግዚአብሔር ቃል የማደስ እንጂ አገራዊ ባሕልና እሴቶቻችንን ምዕራባዊ ለማድረግ የምንዋደቅበት ሜዳም አይደለም። የክርስትና መሠረት ክርስቶስ እንጂ የምዕራቡ፣ የምሥራቁ፣ የሰሜኑ፣ የደቡቡ ዓለም ባሕልና እሴት አይደለም። የኢትዮጵያ ባሕልም የክርስትና መሠረት አይሆንም። ክርስትና ከባሕሎች ሁሉ የበላይ የሆነ መለኮታዊ መልዕክት ነው። የክርስትና መሠረት ክርስቶስ ለማያዊ ሲሆን አካሉ የሆነች ቤተ ክርስቲያንም በምድርና በሰማይ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት የተገለጠች ለማያዊ አካል ናት። ተሐድሶ፦

- ተሐድሶ የበላይነታችንን የምንሰብክበት ሳይሆን የበላይ ለሆነው የእግዚአብሔር ቃል ዕውቅና በመስጠት ዝቅ በማለት ራሳችንን የምናይበት ሚዛን ነው።
- ተሐድሶ ወደ ስማችን ሰዎችን የምንጠራበት ሜዳ ሳይሆን በቃሉ ብርሃን እየተመራን የጌታን ዱካ የምንከተልበት መንገድ ነው።
- ተሐድሶ ለእያንዳንዱ ክርስቲያንና እውነተኛ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ዋና ጉዳይ እንጂ ተጨማሪ የቤት ሥራ አይደለም። ተሐድሶን መጥላት መንፈሳዊ እርጅና እና ሞትን እንደ መውደድ ነው። የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ በክርስትና መሠረተ እምነት ላይ የተገነቡ ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስትምህሮዎችን፣ ትውፊቶችን፣ ልምዶችንና አሠራሮችን የሚያጠራ ነው።

በሌላ አገላለጽ ተሐድሶ ማለት፦ ወደ ቀደመው እውነት ወይም አስተምህሮ መመለስ፣ የተቀበረውን ቆፍሮ ማውጣት፣ እንዲሁም የቀደመውን ጤናማ ትምህርት መጠበቅ፣ መያዝ፣ እንደገና መገንባት፣ ወደ ተሻለ ሁኔታ መቀየር፣ የተሳሳቱ ልምምዶችንና አጠቃቀሞችን በማስወገድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ጉዳዮችን በአገባቡ ማስተካከል ነው።[212]

በአገራችን አንዳንዶች ተሐድሶን የሌለ ነገር እንደመፍጠርና እንደ ሜራቅ አድርገው ስለሚያቀርቡ የተሐድሶ ፍርሃት በቤተ ክርስቲያን እጅግ ከመንገሡም አልፎ የተሐድሶን አሳብ አንግበው የተነሡ ሁሉ እንደ ከሃዲ፣ እንደአጥፊ፣ እንደ አፍራሽና እንደሳተ ተቆጥረው በዚህችው ታላቅ አገር ሲሰደዱ፣ ሲታሠሩ፣ ሲወገዙና በኢ-ሰብዓዊ መንገድ ሲገደሉ ምዕተ ዓመታት ተቆጥረዋል። ከዚህም የተነሣ ምድራችን ነባ የሰዎች አሳብ እንደ ጦር የሚፈራባት፣ የተለየና ብልጫ ያለው አሳብ ያላቸው ዜጐች እንዲኖሩባት በፍጹም የማንፈቅድ ስለሆነ አገራችን በታሪክ ከሁሉም ቀዳሚ ሆና በተግባር የመጨረሻዎቹ መጨረሻ ሆናለች። በየትኛውም ዓለምና ሕብረተሰብ ዘንድ የለውጥ ፍርሃት ያለ ቢሆንም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ያለው ግን የተለየ ነው። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ/የለውጥ/ ፍርሃት እንዲነግሥ አንዱ ዐቢይ ምክንያት የሆነው ለኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትውፊት የተለየ ቦታ መስጠታችን ነው። "ትውፊት"[213] ቅብብሎሽ ነው። ትውፊት የባሕላችን አካል የማንነታችን መገለጫ ነው። ትውፊት ያስፈልገናል። ነገር ግን ከቃሉ እውነት ጋር የሚጋጭና ሁሌ ወደ ኋላ ብቻ እንድንመለከት የሚያደርገንና ለተገለጠው ለእግዚአብሔር ቃል እንዳንታዘዝ እንቅፋት የሚሆነብን ትውፊቶች የግድ መፈተሽ አለባቸው።

አባ መልከጼዴቅ ጳጳስ ስለዚህ ሲናገሩ፦

በስመ ትውፊት ማንኛውንም መቀበል የለብንም፣ በእውነተኛውና በቅዱሱ ትውፊት መካከል ለይክተረናችን፣ ለቅዱሰም መጽሐፍችን ተቃራኒ የሚሆኑ ትውፊቶች መስለው የገቡ ሊገኙ ይችላሉና። ቤተ ክርስቲያን ግን ቅዱስ መጽሐፍን ከሐሰተኛ መጽሐፍ ሁሉ ለይታ አጣርታ እንደተቀበለች ጠብቃ አክብራ እንደያዘችው ሁሉ አሁንም እውነተኛውን ትውፊት ለይታ አክብራ መያዝ አለባት። ሐሰተኛ የሆነውን ሰው ሠራሽ የሆነውን ሥርዓት እንደ ትውፊት አድርገውም ቢይዙት ከእግዚአብሔር ሕግ ውጪ ያደርጋል፣ ለቅዱስ መጽሐፍም ተቃራኒ ይሆናል። እንደዚህ ያለውን ሰው ሠራሽ ሥርዓት ፈሪሳውያን እንደ ትውፊት አድርገው ቢይዙት ጌታ እንደተቃወመ እናገኛለን[214] በማለት ከቃሉ ጋር የማይፋለስና የማይጣረስ ትውፊት አስፈላጊነትንና ሰው ሠራሽ ከሆነ ግን አደገኛ ሊሆን እንደሚችል ገልጸዋል።

[212] Chaillot Christian, *(.2002), The Ethiopian Orthodox Church: A Brife introducation to its life and spirituality,* (Paris: inter Orthodox Dialogue 31-32. see also Taddese Tamrate*(1972) , church and state* Oxford: Clarendon., 114

[213] *"...ልማድ፣ ትምህርት፣ ወግ፣ ታሪክ፣ ሃይማኖት፣ ሥርዓት ከጥንት ከአበው ሲያያዝ ሲወርድ ቃላት በቃል ሲነገር የመጣ"* አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፌሌ *በመዝገበ ቃላት ገጽ 396*

[214] አባ መልከጼዴቅ ጳጳስ (1994 ዓ.ም)፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አምነትና ትምህርት፣ ገጽ 71*

ሪክ ዋረን በትውፊት ስለሚመሩ ቤተ ክርስቲያናት ሲናገር፦

ትውፊት-መር በሆነ ቤተ ክርስቲያን የተወደደው ሐሪግ 'እኛ ሁልጊዜም በዚህ መንገድ ነበር እንሠራ የነበረው' የትውፊት-መር ቤተ ክርስቲያን ግብ ያለፈውን ነገር ማስቀጠል ነው። ለውጥ ሁልጊዜም ቢሆን በአሉታዊ መልኩ የሚታይ ነው፤ ደግሞም ባሉበት ረግቶ 'አለመንቀሳቀስ መሠረት አንደ መያዝ ነው...በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ትውፊት፣ ሁሉም ነገር፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንኳ ሁለተኛ የሚደረግበት፣ አንደዚህ ዓይነት አንቀሳቃሽ ኃይል ነው[215] ብለዋል።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ትውፊት በቤተ ክርስቲያን የቃሉን ቦታ ከወሰደ፣ ዛሬ ላይ የትናንቱ ባሕልና አሠራር አቀንቃኝ ካደረጋት ዕድገትና ለውጥ አይታሰብም። የአገራችን ቤተ ክርስቲያን እንደ ቃሉ የሆኑ መልካም ትውፊት መጠብቅ አለባት፤ ቃሉን ከሚጋርድ ትውፊት ግን በቃሉና በመንፈሱ መታደስ አለባት። የቤቱ ራስ የሆነው ክርስቶስ በቃሉና ለዚህች ቀን በተዘጋጁ ልጆቹ ይህን የዘላለም አጀንዳውን እውን ያደርጋል።

ክርስቶስ አይታደስም፤ መጽሐፍ ቅዱስ አይታደስም *(ለዘመኑ በሚመጥን ቋንቋ አይተረጎምም ማለት ግን አይደለም)*፤ የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊና መሠረታዊ ትምህርት (ዶግማ) አይታደስም። ቤተ ክርስቲያን ማለት የቅዱሳን ጎብረት ስለሆነች ቅዱሳን ደግሞ በሥጋ ስላሉና በወደቀች ዓለም ስለሚመላለሱ ዕለት ዕለት በቃሉና በመንፈሱ መታደስ አለባቸው። የቤተ ክርስቲያን ቀኖና *(በሰው የተፈጠሩ ሥርዓቶች)* ይታደሳሉ። ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ፣ ራስን መመርመር፣ በቃሉና በመንፈሱ ራስን ማየት፣ ወደ ቀደመው መንገድ መመለስ፣ ባያስፈልጋት ኖሮ የቤተ ክርስቲያን ሠሪና ራስ የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ከዛሬ ሁለት ሺ ዓመት በፊት *"እንግዲህ ከወዴት እንደወደቀህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፤ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንስሐ ባትገባም መቅረዝህን ከሥፍራው እወስዳለሁ"(ራእ.2:5)*። በማለት የመነሳት ዕድልና ማስጠንቀቂያ ባልሰጣት ነበር። በሀብቷ፣ በስሟ፣ በሕዝብ ብዛትዋና በዝናዋ ገናና የነበረች፤ በሥርዓትና በወግ ተወጥራ ክርስቶስን ከቤቱ ገፍታ ከውስጧ ላስወጣችና የዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ተምሳሌት ለሆነች የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን *"ከአፌ ልተፋህ ነው"* (ራእ.3:14)። በማለት ባላስጠነቀቃትም ነበር።

መፍትሔው ምን ይሆን?

ድህረ ዘመናይነትና አንጻራዊነት ላንበረከካት ለምዕራባዊቷና ገድል፣ ድርሳናት፣ የትላንትና ልምድና አሠራር ላስረጃት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መፍትሔው አንድ ሲሆን፣ እርሱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶ

[215] *ዓለማ መር ቤተ ክርስቲያን (ተርጓሚ የሌስ ላይ ሌም ሥነ ጽሑፍ) 1995 ገጽ 98*

ነው። መፍትሔው ወደ ቀደመው የቃሉና የመንፈሱ መንገድ መመለስ ነው። ለመመለስ ደግሞ አሁን ያለንበትን አሮጌ ቀለበት ሰብረን መውጣት አማራጭ የለውም። ክርስቶስ በግድና በኃይል አላዳነንም በኃይልም አያድሰንም። ቃሉ ስለ ኤፍሬም ሲናገር፦ *"ሸበት ወጣበት፤ እርሱም አላወቀም፤ የእስራኤልም ትዕቢት በፊቱ መለከረ፤ ወደ አምላካቸው ወደ እግዚአብሔር አልተመለሱም፤ በዚህም ሁሉ አልፈለጉትም"* (ሆሴ 7:8-9)። እንደሚለው ማርጀታችንን ቃሉና ያለንበት ተጨባጭ ሁኔታ እየመሰከሩብን፤ የጎኖቱን መንገድ መርጠን እንዳንጠፋ እርሱ ይርዳን።

ኢየሱስ ክርስቶስ በግድ ቤተ ክርስቲያንን የሚያድስ ቢሆን ኖሮ፤ የሎዶቅያን ቤተ ክርስቲያን *"ደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ"* (ራእ. 3:19)። እያለ በትህትና ውጪ ቆሞ ወደ ውስጥ ገብቶ ለመረዳት ፈቃድዋን ባልጠየቃት ነበር። እንዲሁም ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ሕያው መስለው ባልሞቱ፤ ትውፊት፣ ድርሳናትና ገድላት የወንጌልን ቦታ ባልወሰዱ ነበር። የአምልኮ ሕንፃዎች ግንባታ፣ ልበ ክርስቲያን ያልሆነ ሕዝብ የአምልኮ ቦታ ማጣቡበና የለው ብዛት ብቻውን የአንዲት ቤተ ክርስቲያን የሕያውነት ምልክት ሊሆን በፍጹም አይችልም። ይህማ ቢሆን ኖሮ በሌሎች ዓለማት ያየናቸው ትላንት በቅዱሳን አምልኮና ምስጋና የታወዱ፣ ድንቅና ታምራት የለመዱ መድረኮችና የዘላለም ወንጌል የተሰበከባቸው ታላላቅና ውብ ካቴድራሎች፣ ለምግብና ለሞፈራ ቤትነት ባልተሸጡ ነበር። በሕዝብ ብዛት ተጨናንቀው የኢየሱስ ወንጌል በገሃድ የማይሰበክባቸውና ሕዝብ አጥተው የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉቱም አንድ ናቸው።

የቃሉና የመንፈሱ ተሐድሶ፣ ከእግዚአብሔር የጊዜው አጀንዳ ጋር ለሚሄዱ ሲሆን፣ በደጅ ቆሞ እያንኳኳ ያለውን፣ የቤቱን ባለቤት ድምፅ ሰምተው፣ የልባቸውን በር የሚከፍቱ አብያተ ክርስቲያናት ብፁዓን ናቸው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፣ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትም ሆነ በካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ሥር ለሚገኙ ሁሉም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶ ያስፈልጋቸዋል።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አሸናፊ ሆና ለመገለጥ፦

- በቃሉ ዓለት ላይ መመሥረት፣ የመንፈስ ሰይፍ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል መታጠቅ፣
- ያረጁና የተበላሹ አሠራሮችን ከቤተ ክርስቲያን ማስወገድ፣
- እግዚአብሔርን፣ ዘመኑን፣ ራሳቸውንና ተልዕኮአቸውን በቅጡ አውቀው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለተግባራዊነቱ የሚገለጡ አገልጋዮችን ማፍራት፣

- አገልጋዩና ምዕመኑ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲፈሩ ማድረግ፤ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሚታበዩትን ማቅናት፣ መገሰጽና ተገቢውን እርምጃ መውሰድ። በአባላት ቁጥር በቤተ እምነት ማንነት ከመታበይ ይልቅ የመንፈስ ፍሬ ላይ ትኩረት መስጠት፣

- ከቤተ እምነታዊ ብሔርተኝነት ይልቅ የእግዚአብሔርን መንግሥት አመለካከት ማሳደግ፤ ሲወርድ ሲዋረድ ለመጣው አሮጌው አሠራርና አመለካከት ብቻ ሳይሆን፣ በአዳዲስ አሳቦች ላይ በግልጽ የመነጋገር ባሕልን ማዳበር፣

- የለውጥ አንቀሳቃሽ ሞተር የሆነውን አዲሱን ትውልድ በቃሉና በመንፈሱ ኮትኩቶ ማሳደግ፤በቤተ ክርስቲያን ያደጉና ኑሮአቸውን በቃሉ መርህ የቃኙ በፖለቲካው፣ በንግዱ፣ በግብርና፣ በትምህርት፣ ወዘተ እንዲገለጡ ማስተማር፣

- ቅዱሳንን ተጽዕኖ ፈጣሪዎች እንዲሆኑ ማደፋፈር፣ ተግቶ መሥራት፣ ትልቅ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ራእይ አንግበው መነሣት ይገባቸዋል።

ዛሬም በ21ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት፣ ክርስቶስን ማዕከል ካላደረገው የሃይማኖት ግርግር፣ ወንጌል ከሌለበትና የሰዎች ምኞት እንደ ወንጌል ከሚሰበክባቸው አብዛኛው የኮንፍረንሶች ድግስ፣ የመስቀልንና የጸጋን ሥራ ከጋረዱ ባዶ ኢመጽሐፍ ቅደሳዊ ትውፊቶችና አገራዊ እውነቶች ወደ ጠራውና ወደ ጠለለው ቃል በመመለስ አስተምህሮዎቻቸውን በቃሉ ፈትሸው ለለውጥ ካልተዘጋጁ ጌታ እንዳለው ሕያው መሳይ ሙት ይሆናሉ። ግን ተሐድሶ/መለወጥ፣ መመለስ፣ ንስሐ/እያለ ሞት ለምን? የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በደጅ ያለውን የተሐድሶ ድምፅ ቸል ማለት አይገባትም። ተሐድሶ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያስፈልጋታል። የተሐድሶ ጥያቄ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተነሳው የተሐድሶ ውጤት የሆኑ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በዓለም ላይ ሳይወለዱ ነበር።

በአገራችን የተሐድሶ ጥያቄ ከ800 ዓመታት በላይ የተቆጠረ ቢሆንም ዛሬም ፕሮቴስታንቶችን ተከትሎ ከ100 ዓመት ወዲህ ወደ አገር ውስጥ የገባ "መጤ" ጽንሰ ሐሳብ ተደርጎ ይታሰባል፤ ሲነገርም ይሰማል። ይህ ትልቅ ስህተት ነው። ከብዙ አገሮች ቀድማ የተሐድሶ ጥያቄ የተነሣባት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄውን ማስተናገድ አልቻለችም። ተሐድሶ የሚለው ስም በአገራችን በቤተ ክርስቲያን አካባቢ እንደ ጦር ከመፈራት አልፎ አንድን ሰው ወይም ቡድን ለማግለል፣ ለማራቅና ተቀባይነት እንዳይኖረው ከተፈለገ በስሙ ወይም በስማቸው ላይ የሚለጠፍ የውግዘት ታፔላ(ስሌዳ) መስሏል። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ ዘመን ዘለቅ መሆኑን በታሪክ ገጽ የተቀመጠውን እውነት በመረጃ በማስደገፍ በሚቀጥለው ምዕራፎች በስፋትና በጥልቀት ቀርቧል።

፪

ከሉተር የቀደመ የተሐድሶ ጥያቄ በኢትዮጵያ

የዐፄ ያግብ ጽዮን ዘመን *(1278 - 1286)*

የተሐድሶ(ለውጥ) ጥያቄ ማርቲን ሉተር ከመወለዱ ከ150 ዓመት በፊት እንዲሁም፣ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በኢትዮጵያ ከመታወቃቸው ከ614 ዓመት በፊት በኢትዮጵያ ተወልዶ በደም የታተመ ታሪክ አለው። ይህ እውነት ታሪክን ከግለኝነትና ከጠባብነት ወጥቶ በሐቅ የሚያጠና ሁሉ በቀላሉ የሚረዳው እውነት ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ ሲነሣ ደቂቀ እስጢፋኖስ የመጀመሪያ እንዳልሆነ የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ። አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው ከመነሣታቸው ከመቶ ሃምሳ ዓመት በፊት ትግራይ ውስጥ ለሥዕልና ለመስቀል አንሰግድም *"ምክንያቱም ሥዕል ሠሌዳ ነው፤ መስቀልም የጎልጎታ እንጨት ነው"* ብለው ታላላቅ ሰዎች ተነሥተው እንደነበር ታሪክ ይናገራል። በጊዜው ለተነሣው የተሐድሶ (ወደ ቃሉ የመመለስ) ጥያቄ አፄ ያግብ ጽዮን፦

አመቤታችን ተገልጻልኛ "ለሥዕሌና ለልጀ መስቀል መሰገድ ይገባል" ብለኛ ለጉና ያልታዘዘ "እንገቱ ለገመድ፣ ያከማቸው ንብረት ለሠራዊቴ፣ ቤቱ ለጠመንጃዬ አፎትና እሳት ይጻረጋል" ብሎ ስላወጀ ሕገቡ ከፍርሃት የተነሣ "ንጉሡ ያለንን እናደርጋለን ለመስቀልና ለሥዕል እንሰግዳለን"[116]

[116] ደቂቀ እስጢፋኖስ ገጽ 23፣ የሚከተለው መጽሐፍ በግርጌ ገፅ ጠቅሰዋል። K. Cont Rossini, *(1965)'Vitae Sanctorum Indiginarum I Acta Marqoewos*, CSCO, vol.33/19, ,pp. 12-14

- አገልጋዩና ምዕመኑ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲፈሩ ማድረግ፤ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሚታበዩትን ማቅናት፣ መገሰጽና ተገቢውን እርምጃ መውሰድ። በአባላት ቁጥር በቤተ እምነት ማንነት ከመታበይ ይልቅ የመንፈስ ፍሬ ላይ ትኩረት መስጠት፣

- ከቤተ እምነታዊ ብሔርተኝነት ይልቅ የእግዚአብሔርን መንግሥት አመለካከት ማሳደግ፤ ሲወርድ ሲዋረድ ለመጣው አሮጌው አሠራርና አመለካከት ብቻ ሳይሆን፣ በአዳዲስ አሳቦች ላይ በግልጽ የመነጋገር ባሕልን ማዳበር፣

- የለውጥ አንቀሳቃሽ ሞተር የሆነውን አዲሱን ትውልድ በቃሉና በመንፈሱ ኮትኩቶ ማሳደግ፤በቤተ ክርስቲያን ያደገና ኑሮአቸውን በቃሉ መርህ የቃኙ በፖለቲካው፣ በንግዱ፣ በግብርና፣ በትምህርት፣ ወ.ዘ.ተ እንዲገለጡ ማስተማር፣

- ቅዱሳንን ተጽዕኖ ፈጣሪዎች እንዲሆኑ ማደፋፈር፣ ተግቶ መሥራት፣ ትልቅ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ራእይ አንግበው መነሣት ይገባቸዋል።

ዛሬም በ21ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት፣ ክርስቶስን ማዕከል ካላደረገው የሃይማኖት ግርግር፣ ወንጌል ከሌለበትና የሰዎች ምኞት እንደ ወንጌል ከሚሰበክባቸው አብዛኛው የኮንፍረንሶች ድግስ፣ የመስቀልንና የጸጋን ሥራ ከጋረዱ ባዶ ኢመጽሐፍ ቅደሳዊ ትውፊቶችና አገራዊ እውነቶች ወደ ጠራውና ወደ ጠለለው ቃል በመመለስ አስተምህሮዎቻቸውን በቃሉ ፈትሸው ለለውጥ ካልተዘጋጁ ጌታ እንዳለው ሕያው መሳይ ሙት ይሆናሉ። ግን ተሐድሶ/መለወጥ፣ መመለስ፣ ንስሐ/እያለ ሞት ለምን? የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በደጅ ያለውን የተሐድሶ ድምፅ ችል ማለት አይገባትም። ተሐድሶ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያስፈልጋታል። የተሐድሶ ጥያቄ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተነሳው የተሐድሶ ውጤት የሆኑ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በዓለም ላይ ሳይወለዱ ነበር።

በአገራችን የተሐድሶ ጥያቄ ከ800 ዓመታት በላይ የተቆጠረ ቢሆንም ዛሬም ፕሮቴስታንቶችን ተከትሎ ከ100 ዓመት ወዲህ ወደ አገር ውስጥ የገባ "መጤ" ጽንሰ ሐሳብ ተደርጎ ይታሰባል፤ ሲነገርም ይሰማል። ይህ ትልቅ ስህተት ነው። ከብዙ አገሮች ቀድማ የተሐድሶ ጥያቄ የተነሣባት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄውን ማስተናገድ አልቻለችም። ተሐድሶ የሚለው ስም በአገራችን በቤተ ክርስቲያን አካባቢ እንደ ጦር ከመፈራት አልፎ አንድን ሰው ወይም ቡድን ለማግለል፣ ለማራቅና ተቀባይነት እንዳይኖረው ከተፈለገ በስሙ ወይም በስማቸው ላይ የሚለጠፍ የውግዘት ታፔላ(ሰሌዳ) መስሏል። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ ዘመን ዘለቅ መሆኑን በታሪክ ገጽ የተቀመጠውን እውነት በመረጃ በማስደገፍ በሚቀጥለው ምዕራፎች በስፋትና በጥልቀት ቀርቧል።

፪

ከሉተር የቀደመ የተሐድሶ ጥያቄ በኢትዮጵያ

የዐፄ ያግብ ጽዮን ዘመን *(1278 - 1286)*

የተሐድሶ(ለውጥ) ጥያቄ ማርቲን ሉተር ከመወለዱ ከ150 ዓመት በፊት እንዲሁም፤ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በኢትዮጵያ ከመታወቃቸው ከ614 ዓመት በፊት በኢትዮጵያ ተወልዶ በደም የታተመ ታሪክ አለው። ይህ እውነት ታሪክን ከግለኝነትና ከጠባብነት ወጥቶ በሐቅ የሚያጠና ሁሉ በቀላሉ የሚረዳው እውነት ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ ሲነሣ ደቂቀ እስጢፋኖስ የመጀመሪያ እንዳልሆነ የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ። አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው ከመነሣታቸው ከመቶ ሃምሳ ዓመት በፊት ትግራይ ውስጥ ለሥዕልና ለመስቀል አንሰግድም *"ምክንያቱም ሥዕል ሠሌዳ ነው፤ መስቀልም የጎልጎታ እንጨት ነው"* ብለው ታላላቅ ሰዎች ተነሥተው እንደነበር ታሪክ ይናገራል። በጊዜው ለተነሣው የተሐድሶ (ወደ ቃሉ የመመለስ) ጥያቄ አፄ ያግብ ጽዮን፡-

እመቤታችን ተገልጻልኝ "ለሥዕሌና ለልጀ መስቀል መሰገድ ይገባል" ብላኛ ለኛና ያልታዘዘ "እንገቱ ለገመድ፣ ያከማቸው ንብረት ለሠራዊቴ፣ ቤቱ ለጠመንጃዬ አፎትና እሳት ይዳረጋል" ብሎ ሰላወጀ ሕገ፡ከፍርሃት የተነሣ "ንገሡ ያለንን እናደርጋለን ለመስቀልና ለሥዕል እንሰግዳለን"[116]

[116] ደቂቀ እስጢፋኖስ ገጽ 291 የሚከተለው መጽሐፍ፡ በግርጎ ገጻገ ጠቅሰዋል። K. Cont Rossini, *(1963)'Vitae Sanctorum Indigenarum I Acta Marqoewos*, CSCO, vol.33/19, ,pp. 12-14

ደቂቀ እስጢፋኖስ ዘመን

የሀገራችን ያልሆነ ትምህርት ታስተምራለህ! ሲሉ በጥል ተነሡብኝ። የዚህች አገር ትምህርት ምንድነው? እንዴትስ የሌላ ነው? በክርስቶስና በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ከሆነው ሁሉ በቀር ሌላ አላውቅም።
አባ እስጢፋኖስ

ደቂቀ እስጢፋኖስ የተባሉት በአሥራ አምስተኛው ምእተ ዓመት በኢትዮጵያ በነበረችው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ ላስነሱት ለአባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው የተሰጠ ስም እንደሆነ ይነገራል። ደቂቀ ማለት "ልጆች" ማለት ሆኖ እንደ "ደቀ መዝሙር" የተከታዮች መጠሪያ ነው። አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው *(1406 - 1421)* ይዘውት የተነሡትን የተሐድሶ ጥያቄ ፕሮፌሰር ኃይሌ በመጽሐፋቸው፡-

ለአብ፣ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር (ለወላዲተ አምላክ) ሥዕል፣ ለመስቀልና ለንጉሥ አንሰግድም (አራስን የሚያስጎነበስ እጅ አንነሳም) ከቤተ ክርስቲያን መጽሐፍት ውጪ የሆኑትን አንቀበልም የሚባል እንደነበር ይገልጻሉ።

እንዲሰገድለት በብርቱ ለሚፈልግ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የስግደት ጥያቄ አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቹ እንቢ ይሉ ነበር፡-

እስጢፋኖስና ደቂቀ እስጢፋኖስ ወደ ንጉሡ በቀረቡ ጊዜ ሹሉ እጅ መንሣታቸው አልቀረም፣ ንጉሡ ግን በዚህ አልረካምና ለምን አትሰግድልኝም? ሲል ለፍ አውጥቶ ጠየቀው። እግዚአብሔር ብቻ እንጂ ለፍጡራን ይሰግድ ዘንድ እንዳልታዘዘ ነገረው።[218] ንጉሡም ራስኽን ዝቅ በማድረግ የማትሰግደው ለምድነው? ሲል እስጢፋኖስን ጠየቀው፣ እርሱም ሲመልስ አንተ እንደምትለው እንድንሰግድ በመጽሐፍ አልታዘዘም። ለእግዚአብሔር እንድንሰግድ ታዘናል እንጂ። ስግደት ከእኛ አትፈልግ፣ ጸሎትና ቡራኬ ይበቃኻልና አለው።[219]

አባ እስጢፋኖስ
በዐፄ ይስሐቅ ችሎት(1406-1421) ተቀባይነት ስለማግኘታቸው

አባ እስጢፋኖስ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የንግሥና መንበራቸውን ከመቆናጠጣቸው በፊት በዐፄ ይስሐቅ ዘመን *(1406-1421)* ስለ ትምህርታቸው ተከሰው ንጉሥ ፊት ቀርበው ነበር። አባ እስጢፋኖስ በንጉሥ፣ በጳጳስ፣ በመነኮሳትና በደብተራዎች ፊት ቆመው ትምህርታቸው

[218] ዘአኅተሞ መምህር ወማኅበር ዘጉንዳጉንዶ ደብረ ገረዛን ማርያም ገዳም *(1996 ዓ.ም)፣ ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዶ፣ ገጽ 16*
[219] *ዝኒ ስማሁ፣ ገጽ 139*

ብለው በመታዘዛቸው እንቅስቃሴው እንደተገታ ፕሮፌሰር ጌታቸው በመጽሐፋቸው ዘርዝረዋል። በዓለማችን ላይ በነባ ፈቃድ፣ ምርጫና ስብከተ ወንጌል የታወቀው ክርስትና በኢትዮጵያ ቅዱሳን ያነሱትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥያቄ በገመድ፣ በጠመንጃና በእሳት በማስፈራራት የሰዎችን የማሰብና የመምረጥ ነፃነት በኃይል ሲያኮላሽ እንመለከታለን። ከአራተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ "ክርስትና" በኢትዮጵያ የተስፋፋው በወንጌል ስብከት ብቻ ሳይሆን በነገሥታት ጉልበት እንደሆነ ታሪክ ምስክር ሲሆን ከላይ የተመለከትነው የዐፄ ያግብ ጽዮን የማስፋራራትና የኃይል እርምጃና ዛቻ አንዱ ማስረጃ ነው።

"የኢትዮጵያ ነገሥታት የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር ከመንግሥታቸው ለመራራ ለይተው አይመለከቱም ነበር"[217] በተለይ ዐፄዎቹ ከቤተ ክህነት ጋር በመጣመር ለአገር አንድነት ያላቸው ብርቱ ትጋት ቢደነቅም ክርስትና ሕይወት ለዋጭ መሆኑ ተዘንግቶ የፖለቲካና የግዛት ማስፋፊያ መሣሪያ ማድረጋቸው በመንፈስና በሥጋ ላስንበት ፈርጀ ብዙ ቀውስ ምክንያት ሆነዋል። በአገራችን ክርስቶስ ያልገነነበት አፋዊ ክርስትና መንሰራፋት ብቻ ሳይሆን የለውጥ ጠላቶች አድርጎናል። ዓለም ሁሉ በሁለንተናዊ ለውጥ ባሕር ሲዋኝ እኛ በነገር ሁሉ ከሁሉ ኋላ ቀርተን ዛሬም እንደቀዳሚዎች መፎከራችን ያሳዝናል። ከዚህም የተነሣ አብዛኛው ሕዝባችን በቃሉና በመንፈሱ ልቡ ሳይለወጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር የተፋታና ለክርስቶስ ባዕድ በሆነ አገራዊ የ"ክርስትና" ዱር ተውጧል። ክርስትናችን የቃሉና የመንፈሱ ድሃ፣ የሰይፍ፣ የስደት፣ ሰዎችን የማሰቃየት፣ የመግደል፣ ፀረ ምናምን እያልን የመፈረጅ፣ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ የሰው ልጆች ቁም ስቅል የሚያዩበት የሥጋትና የስቃይ ካምፕ መስሎ እንደዘለቀ ብዙ ምሁራንና የታሪክ ሊቃውንት ዘግበዋል።

ክርስትናን በጠራ የወንጌል ስብከት ሳይሆን በሥጋ ኃይል ማስፋፋት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ሽፋን የተሰጠው ስለሆነ ምድራችንን ከእርግማን በታች ያቆየን ሰንኮፍ ሆኖብናል። በአጠቃላይ በዐፄ ያግብ ጽዮን ዘመን የምንመለከተው በኢትዮጵያ ክርስትና ሥጋዊ የኃይል አጠቃቀም አይሎ መቀጠሉን ነው። በአጭር ቃል በዘመኑ የነበሩ ጥቂት ቅዱሳን እግዚአብሔር በቃሉ የገለጠላቸውን እውነት በመያዝ ነባሩንና የተንሻፈፈን አስተምህሮ ለማቅናት በተነሡ ጊዜ ሞት ሲታወጅባቸው ዝም ለማለት እንደተገደዱ ታሪክ ምስክር ነው። ይህ በኢትዮጵያ ከሚሲዮናውያንና ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ልደት እጅግ የቀደመ የተሐድሶ/ለውጥ ጥያቄ እንደሆነ ልብ ይበሉ። የተሐድሶ ጥያቄ በኃይል አዋጅ ለጊዜው ቢታፈንም ሙሉ በሙሉ አልከሰመም፡ ነበር። ከዚህ የተሐድሶ ጥያቄ በኋላ የተከተለው፡-

[217] *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ (2000 ዓ.ም)* ገጽ 330

ከእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ባመለከቱ ጊዜ መሳሳታቸውን ሊያመለክት ማንም አልቻለም።

ከዚያ በኋላ ንገሡ እንዲህ የሚል ዐዋጅ ይነገር ዘንድ አዘዘ። ይህ መነኩሴ ትምህርቱ ቀና አይደለም፤ ከሕግ ውጪ ያስተምራል በማለት ከሰው ወደዚህ አምጥተው ነበር። አሁን እኔና ካህናተ ደብተራ ዅሉ ነገሩ የታመነና ትምህርቱም ቅዱሳን ሐዋርያት እንደሚያስተምሩት ትምህርት ወንጌል እውነተኛ እንደሆነ ተረድተናል። ስለዚህ እኛ ትምህርቱን ተቀብለነዋልና አናንተም ውደዱት። ከዚህም ሽነ ከሌሎች አውራጃዎች ትምህርቱን መከተል የሚወድ ማንም ሰው አይከልክለ።[220]

በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ችሎት - ስለመወገዛቸው

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ወደ ዙፋን ከመጣ በኋላ ነገሩ ተገለበጠ።

አባ አስጢፋኖስ በክሐዲነት ተከሰው ሰሱ በፊት በነገሠው በዐፄ ይስሐቅ ችሎት ሲቀርቡ ከገለጡት እምነታቸው የተለየ አልነበረም። ሆኖም በዐፄ ይስሐቅ ችሎት የተመሰገኑ መነኩሴ በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ችሎት ተወገዘ።[221]

አባ አስጢፋኖስ በዐፄ ይስሐቅ ችሎት ፊት ተከሰው ቀርበው ካህናትና ደብተራዎች ሁሉ ባሉበት ጉባኤ አቅርበው ትምህርታቸው ከሐዋርያት ትምህርት የሚስማማ መሆኑ ተመስክሮላቸው በነፃነት እንዲያስተምሩ ተፈቅዶላቸው ነበር። አባ አስጢፋኖስ የመጀመሪያ ትምህርታቸውን ሳይለውጡ፣ ከካህናትና ከደብተራዎች መካከል መሳሳታቸውን በግልጽ በቃሉ ያሳየ አንድም ሰው ሳይኖር በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ችሎት ለምን ተወገዙ? አባ አስጢፋኖስ በሐዋርያት ትምህርት ላይ ከቆሙ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ምን ላይ ቆሞ ነው እነርሱን ያወገዘው? መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የላቸውም።

ንጉሥ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ደቂቀ አስጢፋኖስን እጅግ ከመጥላቱና ከመቃወሙ የተነሣ አባ አስጢፋኖስን "እሰጢፋ" ተከታዮቻቸውንም "ደቂቀ እስጢፋ" (የአስጢፋኖስ ልጆች) ይላቸው ነበር። ይህም የሽሙጥ ስም እንደሆነና ደቂቀ አስጢፋኖስ ሽሙጡ እንደገባቸው ከሆነ "እስጢፋ" ማለት በግብጽ ቋንቋ የሰይጣን ስም ስለሆነ እኛን የሰይጣን ልጆች ለማለት ነው፤ ይላሉ።

የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የስደት አዋጅ

የአዋጁ ሙሉ ቃል በግዕዝ

አብለክሙ ኦ ሕዝበ ክርስቲያን ምእመናኒሃ ለማርያም ድንግል በክልኤ። ኩሉ ብእሲ ዘተወክፈ ኪያሆሙ፤ ወዘተሳተፈ ምስሌሆሙ፤ ወዘአንበሮሙ ውስተ ቤቱ ወገብ ቤተክርስቲያን ወውስተ ምድረ ርስቱ እመሂ ሥዩም ይሰዐር። ወይትበርበር ቤቱ ወኩሉ ንዋዩ፡ ወምድረ ርስቱ ይኩን ለባዕድ። ሊቃነ ካህናትኒ ወንኩራን እድ ውኩሎሙ ሥዩማነ ቤተ ክርስቲያን ወመነኰሳትኒ ወኩሉሙ ሕዝብ ለእመ ተረከቡ አንዘ የኀብኡ ኪያሆሙ፡ ፈድፋደ ኩነኔ ላዕሌሆሙ። ሚመቶሙ ወምድረ ርስቶሙ ይኩን ለካልኤ እስመ ኮኑ ሱቱፋነ ምስሌሆሙ። ወእሙንቱሰ ደቂቀ እስጢፋ በአማን አይሁድ እሙንቱ፤ እሰ አብዩ ሰጊደ ለማርያም ድንግል በክልኤ፤ ወሰ መስቀል ወልዳ። ሎሙሰ ኩነኔሆሙ ሞት። ወዘረከቦሙሂ ይኩንኖሙ በጽኑዕ ኩነኔ። ወቀቲልሰ ኢይቅትሉሙ፤ አላ ያብጽሖሙ ውስተ ኩርንኔነ ከመ ንስማዕ ቃሎሙ፤ ወከመ ይኩን ፍትሕ ላዕሌሆሙ። ወዘሂ ተረክበ ብእሲ እንዘ ይብሉ ሰላም ለአስጢፋዊ መክፈልቱ ምስለ እሰ ተወክፍዎሙ ለደቂቀ እስጢፋ።

የአዋጁ ሙሉ ቃል በአማርኛ

በነፍስ በሥጋ ድንግል የምትሽን የማርያም ምዕመናን የሽናችሁ ሕዝበ ክርስቲያን ሆይ! እንዲህ አላችኋለሁ፡- ማናቸውም ሰው ዅሉ ደቂቀ እስጢፋን የተቀበለ ከእነርሱ ጋር የተባበረ በቤቱ ውስጥም ያኖራቸው፤ ወይም በቤተ ክርስቲያኑና በርስቱም ምድር ያኖራቸው ቢገኝ፤ ሹመት ያለው ከሽነም ከሹመቱ ይሻር፤ ቤቱም ይዘርፍ፤ ገንዘቡ ዅሉና ያለው የምድር ርስት ለባዕድ ይኹን።

ሊቃነ ካህናት፣ ንኩራን እድ የቤተ ክርስቲያን ሹማምንትና መነኮሳትም ዅሉ ሕዝቡም ዅሉ እነርሱን ሲደብቁአቸው ከተገኙ በእነርሱ ላይ ከፍ ያለ ቅጣት ይፈጸምባቸዋል። ሹመታቸውና የምድር ርስታቸው ለሌላ ይኹን። ከእነርሱ ጋር ተባብረዋልና ነው። እነዚህ ደቂቀ እስጢፋ ግን ለድንግል ማርያምና ለአንድ ልጅዋ መስቀል መስገድ እምቢ ያሉ ናቸውና፤ በእውነት አይሁድ ናቸው። የእነርሱ ቅጣት ሞት መሆን አለበት። ያገኛቸው ዅሉ በጽኑ መከራ ይቅጣቸው። ቃላቸውን ሰምተን በአደባባያችን ሾንን እንድንፈርድባቸው ወደ አደባባያችን ያምጣቸው እንጂ መግደልን ግን እርሱ ራሱ አይግደላቸው። እንደዚሁም ደቂቀ እስጢፋ የሽነውን ሰው አግኝቶ ሰላምታ የሰጠው ሰው ሁሉ ዕድል ፈንታው ደቀ እስጢፋን ለተቀበሉ እንደሚደረግባቸው ይሽናል።[222]

በማለት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አዋጅ አስነገረ። ለመሆኑ ለማርያምና ለአንድ ልጅዋ መስቀል መስገድ አንቢ ያለ አይሁድ እንደሆነና ሞት እንደሚገባው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል ወይ? ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከዐፄ ያግብ ጽዮን የሚለይበት በሥልጣኑ ተጠቅሞ የማርያምና የመስቀል አምልኮ የኑፋቄ ትምህርት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ በአዋጅ መጫኑና በቃሉ ላይ ቆመው ኑፋቄውን የተቃወሙ አበው ላይ የከፋ ስደትና ጥፋት ማወጁ ነው። አባ አስጢፋኖስ ጀርመናዊው ማርቲን ሉተር ከመነሣቱ በፊት በኢትዮጵያ ምድር የጠራውንና የነጠረውን የወንጌልን እውነት በመረዳት ለተሐድሶ የተነሡ ታላቅ ፋና ወጊ አባት የነበሩ ሲሆን ብዙ ደቀ መዛሙርት (ደቂቀ አስጢፋኖስ የተባሉ) አፍርተው ነበር።

[220] ገደለ አቡነ አስጢፋኖስ፣ (1996 ዓ.ም)፣ ገጽ 109 - 110
[221] ደቂቀ አስጢፋኖስ ገጽ፣ 25
[222] የኢትዮጵያ ዓመታዊ ታሪክ መጽሔት 4ኛ መጽሔት 1954 ዓ.ም ገጽ 79-87



የተሐድሶ መሪ የነበሩ አባ እስጢፋኖስ
ምንጭ፡- (ደቂቀ አለጢፋኖስ በሕግ አምላክ ከሚል መጽሐፍ)

አቡነ ኢስጢፋኖስ የተወለዱት በትግራይ ክልል በምሥራቃዊ ዞን አውራጃ ስቡሐ በምትባል ቀበሌ በሚኖር ብርሃነ መስቀልና በሚስቱ ሣራ የሚመራ ክርስቲያን ቤተሰብ ነበር። የሚመኙለትን መልካም ዕድል ጠቋሚ ስም ሊያወጡለት ዐስበውም "ጎድገ አንበሳ" "የአንበሳ ቅሬታ" "የአንበሳ ደቦል" ብለው ሰየሙት።[223] በዚያም ለጎድገ አንበሳ "እስጢፋኖስ" የሚል ሰመ ምንኩስና አወጡለት።[224]

በአውሮፓ "የተሐድሶ የንጋት ኮከቦች" የሚባሉት፡- ጆን ካልቪን፣ ጆን ሑስ፣ ዋልዴስ ወዘተ.. በዘመኑ ወንጌልን ረግጣ ከሮም ቄሳሮች ጋር ጋብቻ ፈጽማ በኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትውፊትና ወግ ታሥራ በነበረችው ቤተ ክርስቲያን ትዕዛዝ ለእውነት ሰማዕት እንደሆኑ፣ አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቹም ተመሳሳይ የሰማዕትነት ጽዋን በመጎንጨት ከምዕራባውያንም የቀደሙ ናቸው። የተሐድሶን ጥያቄ የቀደሙ የኢትዮጵያ የሃይማኖት አበው ከምዕራባውያን አስቀድመው ያነሡት ሀሳብ እንጂ የከረጅት መጤ ትምህርት እንዳልሆነ ታሪክ ይመሰክራል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ መጤ ሀሳብ ሳይሆን አገር በቀልና ዘመን ዘለቅ ጥያቄ ነው። ልዩነቱ የእነርሱ ከእኛ ኋላ ተነሥተው ዓለምን በሁሉም አቅጣጫ መለወጣቸው ሲሆን የእኛ "ተሐድሶ" የሚል ቃል እስከ ዛሬ እንደ ተዋጊ አውሬ መፈራቱና መፈረጁ ነው።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ ከምዕራባውያን የተሐድሶ ጥያቄ በኩር ቢሆንም ከዘጠኝ ምዕተ ዓመት በኋላም አመርቂ ውጤት አላስገኘ ም። ከዘጠኝ መቶ ዓመታት በኋላም "ተሐድሶ" የሚል ቃል በራሱ

[223] *ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ፣ (መቅድም) ገጽ 12*
[224] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 13*

በአንዳንዶች ዘንድ እንደ ቦር የመፈራቱ ነገር ከድሮ ይልቅ በዘመናችን እንደባሰ ይነገራል። ስለ ተሐድሶ በአምንታዊ መልኩ የሚናገር ወዲያው "የፓሮቴስታንት ጋሻ ጃግሬ" "የመናፍቅ ትምህርት አቀንቃኞች" "የቤተ ክርስቲያን ሰፍራሽ" "የሳተና የተሳሳተ" "የፓሮቴስታንት አፈቀላጤ" ተደርጎ ይፈረጃል፤ ከቤተ ክርስቲያን በውግዘት ይባረራል፣ በየመድረኩም ስሙ ይብጠለጠላል።

አባቶች በዚህ ምድር ለቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ የከፈሉት የደም ዋጋ ተዘንግቶ ስለ ተሐድሶ በተነሣ ቁጥር ተሐድሶን ትላንት ከመጡ የፓሮቴስታንት (ወንጌላውያን) አብያተ ክርስቲያናት ጋር ብቻ ማያያዝ ትልቅ ስህተት ነው። በታሪክ ላይ ለምን እንደሚዋሽ ግልጽ አይደለም። ይህ ያለፈውን ታሪክ ካለማወቅ ወይም እውነትን እንደ ቀድሞ ለመጋረድ ከመጣር የመጣ ሊሆን ይችላል።

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ደቂቀ እስጢፋኖስን ለምን ጠላቸው?

በጣም የሚገርመው ለእግዚአብሔር፣ ለመስቀልና ለማርያም በመቅናት ዘግናኝ ጭካኔ ይፈጽም እንደነበር የሚነገርለት ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ለደቂቀ እስጢፋኖስ ያቅርብላቸው የነበረው ተደጋጋሚ ጥያቄ፣

መምህራችሁን ሰደቡ(አባ እስጢፋኖስን ማለቱ ነው) ለኔ ሰገዱ የሚል ሲሆን እነርሱ በበኩላቸው ደማቸው እንደጉርፍ እየፈሰሰ፣ ገላቸው እንደ ቋንጣ እየተጠበሰ፣ አንገታቸው በስለት እየተቀነጠሰ፣ ደረታቸው በጦር፣ ዓይናቸው በእሾህ እየተወጋ ንጉሥ ፊት በቀረቡ ቁጥር "ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በስተቀር ላንተ አንሰግድም፣ መምህራችን (አባ እስጢፋኖስን) አንሰድብም፣ ይሉ ነበር።[225]

ንጉሡ

...በሰግደት እንዲያከብረው በሽንላ ቃል ይልክበት ነበር፣"[226] *"ቅዱስ እስጢፋኖስም እየወሰዱት ሳለ በመንገድ ላይ ከአሳሾች ወገን አንዱ ተገናኝውና ለተቀባው ንጉሥ የማትሰግደው ለምን ድነው? አለው።ሲመልስም ለሥላሴ ቅዱስ (ለሥላሴ) ራስን አስገዝቻለሹ፣ በሥላሴ ላይ አራተኛ አልጨምርም*[227] *ብሎ መለሰለት። ንጉሡ ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስን፡- ለመንግሥቴ ክብር ካልሰገድክ የት ትሄዳለህ? በማን ምድር ትኖራለህ? ሲለውና ቅዱሱ ይሽንን ከመለዕክተኞቹ ሲሰማ ያበቀልከውን አልበላሁም፣ ያዘነምከውን አልጠጣሁም።መጽሐፉ ሰማዩት የእግዚአብሔር ነው፣ ምድርን ግን ለሰው ልጆች ሰጠ ይላል። እግዚአብሔር ሰማይን ሲፈጥር ረድተኸዋልን? ደግሞ ምድር አትክልት እንድታወጣ ያዘዛት ላንተ ብቻ ነውን? እነሆ በየዘሩ*

[225] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 47*
[226] *ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዶ፣ ገጽ 154*
[227] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 149*

የሚዘራውን አትክልት ሰጥቻትኋለሁ፤ ያለው ለብዙዎች አይደለምን? በሉት፡ አላቸው።[228]

እያንዳንዱንም ለንጉሥ እንዲሰግዱ ያስገድዳቸው ጀመር፤ እነርሱም እንደ አባታቸው እንቢ ባሉት ጊዜ እንደ ትናንቱ ደማቸው እስኪፈስስ ድረስ ደበደባቸውና ኹሉንም በጅንግላ አሰራቸው። ከዚህ በኋላ የቅዱስ እስጢፋኖስን ማደሪያ አቃጠለው፤ ያላቸውንም ኹሉ ወሰደባቸው ልብሳቸውን ገፈፉአቸው።'[229] *ከንጉሡ እንደታዘዙት የሸኾናቸውን ቋንጃ መቁረጥ ጀመሩ። ከነሱ ውስጥ አምጎ ማርያም የሚሏት እጂጂ የታመመ ጉልበቶቿ የተጣበቁ አንዲት መነኩሲት ነበረች። የንጉሡን የቁጣ ደረጃ ለማሳየት ያለምሕረት በእርሷ ጀምረው ሁሉንም ፈጸሙ።*[230] ይላል።

ይህ ምን ዓይነት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና ኢሰብዓዊ ድርጊት ነው? የእግዚአብሔር ቃል፡- *"በላይ በሰማይ ካለው በታችም በምድር ካለው ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ። አትስገድላቸው አታምልካቸውምና፤"* (*ዘዳ.20:4-5*)። ኢየሱስ ሊሰገድለት የሚገባ እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ሲናገር፡- *"ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ" (ማቴ.3:10)* ብሏል። እንዲሁም ሐዋርያው ዮሐንስ ለመልአኩ ልሰግድ በእግሩ ፊት ስደፋ መልአኩ ስግደት ለእግዚአብሔር እንጂ ለእርሱ እንደማይገባ በማስጠንቀቅ የተናገረውን እንመልከት፡- *"እንዳታደርገው ተጠንቀቅ ከአንተ ጋር የኢየሱስ ምስክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ ለእግዚአብሔር ስገድ የኢየሱስ መንፈስ የትንቢት መንፈስ ነውና አለኝ" (ራእ.19:9-10)*። ታዲያ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የእግዚአብሔርን ስግደት ለእኔ ካልሰጣችሁ ብሎ ቅዱሳንን የፈጀው ከየት ተምሮ ይሆን? ሰውን ማክበር የተገባ ሲሆን የግድ ሰዎች እንዲያከብሩን መጠየቅና ማስገደድ በልባችን ያለውን ድብቅ ማንነት ያመለክታል። ለመሆኑ ዘርዓ ያዕቆብ ምድሪቷን በንጹሐን የእምነት አባቶች ደም ሲያጥብ፣ አንዳንድ ካህናትና ደብተራዎችን የህበ፡ዕ አጀንዳው ጋሻ ጃግሬ አድርጎ ሲያሰልፋቸው፣ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ኑፋቄን ያለ አንዳች ከልካይ ወደ ቤተ መቅደስ ሲያስገባ በየትኛው መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ተመርቶ ይሆን? ከእያንዳንዱ ድርጊት ጀርባ የእግዚአብሔር ወይም የሰይጣን አጀንዳ መኖሩ የታወቀ ሲሆን ከዘርዓ ያዕቆብ ጭፍጨፋ ጀርባ ያለው የማን አጀንዳ ነበር? መልሱን ለአንባቢያን።

ይትባረክ ግደይ፡- *"ዘረኛ ማነው? ኢትዮጵያውያን ፍረዱ!"* በሚል መጽሐፋቸው ዘርዓ ያዕቆብ ለምን ይህን ዘግናኝ ጭፍጨፋ እንዳካሄደ ሲናገር፡- *"ዘርዓ ያዕቆብን ያሣሣቱት ግብጻውያን ጳጳሳት በሃይማኖት ሰበብ እንደሆነ አያጠራጥርም። ...በዚያን ወቅት ደግሞ በሃይማኖት የመጣን ነገር*

[228] *ደቂቀ እስጢፋኖስ 1996 ዓ.ም ገጽ 168*
[229] *ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 152*
[230] *ጌታቸው ኃይሌ (ፕሮፌሰር) (1996 ዓ.ም) ፤ ደቂቀ እስጢፋኖስ፤ ገጽ 160*

ወይም ጠላትን መግደል እንደ ጽድቅ ይቆጠር ስለነበር"[231] ብለዋል። ይትባረክ ግደይ እንዳሉት በዚያ ዘመን ለሃይማኖት ብሎ ሰውን መግደል እንደጽድቅ የሚቆጠር ከሆነ የኢትዮጵያ ክርስትና በዚያ ዘመን ዛሬ በእጃችን ካለው መጽሐፍ ቅዱስ የተለየ መመሪያ ያለው አያስመስልም ወይ? ይህም ክርስትናችን በዘመን ሁሉ ግድያን በሚያወግዘው ግልጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ እንዳልተመሠረተና ችግር እንዳለበት ፍንጭ ይሰጣል። በእውነተኛ ቤተ ክርስቲያንና በአዲስ ኪዳን በየትኛውም ዘመን ሌላውን መግደል እንደ ጽድቅ የተቆጠረበት ዘመን የለምና።

የአባ እስጢፋኖስ ሰማዕት መሆን

"ሰማዕት" የሚል ትርጉም የያዘው የእንግሊዝኛ ቃል፣ *(Martyr)* (ማርቲየር) ከላቲን የመጣ ሲሆን፣ ቀጥተኛ ትርጉሙ *"ምስክር"* መሆን ማለት ነው። የቀድሞ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ጌታ መሆኑን ከደው ከመናር ይልቅ *"ለሚያምኑትና ለተቀበሉት ሃይማኖት ምስክር"* ሆነው መሞት የመረጡትን አማኞች ለመግለጽ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሙበት ቃል ነው።[232] ፕሮፌሰር ኃይሌ የተሐድሶው ፋና ወጊ የነበሩ አቡነ እስጢፋኖስ ላይ የደረሰውን የመጨረሻ መከራና ሰማዕትነት በመጽሐፋቸው እንዲህ ዘግበዋል።

> *ቅዱሱንም (አባ እስጢፋኖስ) ፊቱን ወደ ላይ አቅንተው ሁለንተናው ደም በደም እስኪሆን ደበደቡት። የንጉሡ የግራ ወታደሮች ሲያዩ ከራሱ እስከ እግሩ በመደብደብ በቅዱሱ ላይ ተረባረቡበት። ንብ ማርን (እንደሚከብ) ከበቡት። ሰውነቱ አልበቃ ሲላቸው የመልኩ ውበት እስኪ ሰውጥ ድረስ ግማሾቹና ግማሾቹ ተራ በተራ ተፈራረቁበት። በእሳት የጠበሱት እንጨት መሰለ። ከድብደባው እብጠት የተነሣ የጉንጩ ስፋትና የከንፈሮቹ ሥርዓት (በእብጠት) ከአፍንጫው ጫፍ ጋር እኩል ሆኑ። ዓይኑ ማየት አልቻለም። ብቻ ደሙ ከድንኳኑ በር እንደ ውሃ ይወርድ ነበር።*[233] *ቅዱሱንም (አባ እጢፋኖስ) ከወደቀበት ቦታ አመጡት። (ሲያመጡት) አጕንበሶ ነበረ የሚሄደው፣ ምክንያቱም በጢሙ ላይ የወረደው የአፍንጫውና የአፉ ደም ሲረጋ እንደ ገመድ ሆኖ ሳይበጠስ ከቀሚሱ ጋር ተያይዞ ነበር። ሲመቱት ቆቡን ጥለዋት ስለነበረ ራሱ ራቁቱን ነበር፤ ግን በልብሱ መገናኛ ቁልፍ ተይዛ ተንጠልጥላ ነበረ። ልጆቹ አስተካክሉት፤ ቆቡን ራሱ ላይ አደረጉለት፤ የደሙንም ገምድ ከጢሙ አስወገዱለት። ዐይኑ ግን ጠፍቶም እንደሁ ወይም እንዳለ ለመረዳት አልቻሉም።*

ቅዱሱም ልጆቹን እንዲህ አላቸው፡-

አሁን ታዲያ በዚህ ታዝናላችሁን? ይሽ ድብደባ ብቻ ሳይሆን ስለ ክርስቶስ አጥንቴን ሁሉ እንኳን ቢበታተኑም እንደዚሁ እደሰታለሁ።[234]

[231] ይትባረክ ግደይ *(2000 ዓ.ም)* ፤ዘረኛ ማነው? ኢትዮጵያውያን ፍረዱ፤ ገጽ 149
[232] መለሰ ወጉ *(ዶ/ር) (2004 ዓ.ም)*፣ መሰቀል-አልባ ክርስትና፣ ሕትመት ፋር-ኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ.ማህ፤ ገጽ 133
[233] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 103
[234] *ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 104*

አባ እጢፋኖስ እየታሰሩና ለጥቂት ጊዜ እየተፈቱ ከደረሰባቸው ከፍተኛ ድብደባና አሰቃቂ መከራ የተነሣ መራመድ ሣይችሉ በሥጋቸው ሕመምተኛ ና በጣም የተጎዱ ቢሆኑም ለክርስቶስ ያን መከራ በመቀበላቸው እንደ ትልቅ በረከት ይቆጥሩ ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ፦ *"ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል" (የሐዋ.14:22)* እንዳለው ማለት ነው። አባ እስጢፋኖስ የራሳቸውን መከራና ችግር ዘንግተው ሌሎች ፈለጋቸውን ተከትለው ለክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል ነፍሳቸውን መስጠት እንዳለባቸው አበክረው ያስተምሩ እንደነበር ገድላቸው ያስረዳል። በመጨረሻም በሁሉም ስላልተቻሉ ከደቀ መዛሙርቱ ተለይተው በጊዜው በመ.ሲሊም መካከል እንዲታሰሩ አደረገ፣

> *ቅዱሱን ብቻቸውን ወደ ጎተር ለደደው። እዚያ እስር ቤት ውስጥ እንዲዘጉበት አዘዘ።...እጆቹንና እግሮቹን በእግር ብረቶች አሰረው ዋዝርማ በምትባል ከተማ ጨለማ ቤት ውስጥ ዘጉበት።[235]*

ስለ ወንጌል እውነት ብዙ ድብደባና እንግልት ከተቀበሉ በኋላ፣ በመጨረሻም ፕሮፌሰር ጎይሌ በመጽሐፋቸው የአባ እስጢፋኖስ እረፍት እንዲህ ዘግበዋል፦

> *አባታችን እስጢፋኖስ እስር ቤት ተዘግቶበት እነሆ ስድስት ወር ቆየ። ከዚያም በሰባተኛው ወር በታኅሣሥ 18 ቀን ጠባቂዎቹ "ክርስቶስ" ብሎ ሦስት ጊዜ ሲጣራ ሰሙት። ይህን ብሎ ዝም አለ። በዚያን ጊዜ የሀገረው ሰዎች እንዳረፈ አስኪረዱ ድረስ በዚያ ቦታ ትልቅ አስገራሚ ግርማና (የመሬት) መንቀጥቀጥ ሆነ። ከድንጋጤ የተነሣ እዚያ ቅዱሱ ከአለበት ቤት መቅረብ አልቻሉም።[236]*

ይላል።

ከምድራችን ለተነሡት ለእኚህ ታላቅ የእምነት አባት፣ የክርስቶስ አሻራ በእያንዳንዱ እርምጃቸው እስከ ዛሬም በግልጽ ለሚታየው፣ የኖሩለት ብቻ ሳይሆን የሞቱለት የወንጌል እውነት ባለቤት ለሆኑት፣ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ነፍሳቸውን አሳልፈው ለሰጡ፣ የእውነትን ቃል አንግበው ቤተ መንግሥትና ቤተ መቅደስን ለሞገቱ፣ ነፃ አሳብ በዚህ ምድር መከበር እንዳለበት ዛሬም በደማቸው ለሚናገሩ እንደ አባ እስጢፋኖስና ደቂቀ እስጢፋኖስ ዓለም ሁሉ ለማዕትነታቸውን በአድናቆት ይመለከታል። ለቃሉ እውነት ለከፈሉት ታላቅ የደም መሥዋዕትነት በሰማይ ዋጋቸው ትልቅና ዘላለማዊ ነው። ትውልድ በጭፍን ድጋፍና ተቃውሞ እንዲሁም ለሕይወት አልባ ትውፊት ዘበኛ ሆኖ ውድ ዘመኑን በከንቱ ከሚያጠፋ የቀደሙ የእምነት አበው ዱካ በመከተል ውሸትን በእውነት፣ ጨለማን በብርሃን፣ ኃጢአትን በጽድቅ ለመተካት በጨከነ ሕይወት መግጠም አለበት። እውነትን ሽጠው በውሸት ለሆዳቸው ከኖሩት ይልቅ ውሸትን እንቢ ብለው ለእውነት ሕይወታቸውን የሰጡትን ምሳሌነታቸውን ብንከተል በዘመናችን ታላቅ ታሪክ

[235] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 110
[236] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 111

እንሠራለን። የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ሕዳሴንም እውን እናደርጋለን። እግዚአብሔር በእኛ ይከብራል፣ ሕዝባችንንም ይባርካል። የትውልድ ተምሳሌት እንሆናለን። ቃሉም ይህን እንድናደርግ ይመክረናል፦ *"የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፣ የኑሮአቸውንም ፍፃሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው"* (ዕብ.13:7)። ሐዋርያው ጳውሎስ ወጣቱን ጢሞቴዎስ ሲመክር፦ *"አንተ ግን ትምህርቴንና አካሄዴን አሳቤንም እምነቴንም ፍቅሬንም መጽናቴንም፣ ስደቴንም መከራዬንም ተከተል" (2ጢሞ3:10-11)*። እንዳለው የዘላለም ቃሉን በእጃቸው ይዘው ለእውነት የኖሩና የሞቱ አባቶችን ዱካ መከተል ይገባናል። ውሸት እውነት መስሎ በነገሠበት ምድር ለእውነት ሰማዕት መሆን ሽንፈት ቢመስልም በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ታላቅ ክብርና ድል ነው። ቢዘገይም ይህ የጽድቅ ዘር ኢትዮጵያን ሳይወርሳት እንደማይቀር እምነት አለኝ።

የደቂቀ እስጢፋኖስ በአባ ገብርኤል ፊት

አባ እስጢፋኖስ ሰማዕት ሆነው ወደ ቀጣዩ የሕይወት ምዕራፍ በድል ከተሻገሩ በኋላ፦

> *አባታችን እስጢፋኖስ ወንጌል እንዳዘዘው ክርስቶስን ተከትሏል፣ እንደዚሁ እኛ ም አባታችን እርሱ እንዳስተማረን እንከተለዋለን፤ሉላ አንፈልግም[237]*

በማለት የመምህራቸውን ዱካ የተከተሉ ደቂቀ እስጢፋኖስ (የእርሱ ተከታዮች) ተመሳሳይ የመከራና የሞት ጽዋ በመጨለጥ የተሐድሶን ዘር በደማቸው ዘርተው በድል አልፈዋል። ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ለሰው አዕምሮ የሚቀፍ መዓት በደቂቀ እስጢፋኖስ ላይ እንደ ዝናብ ቢያዘንብም የወንጌልን እውነት የተረዱት መከራና ሞት በታላቅ ደስታ ይቀበሉ ነበር። ንጉሡ በወቅቱ የነበሩ ጳጳስ እንዲያወግዟቸው አቡነ ገብርኤል ፊት ባቀረቧቸው ጊዜ እምነታቸውን በግልጽ በማስታወቅ ያልተጠበቀ ምላሽ ከጳጳሱ እንዳገኙ ካሳይ ገ/እግዚአብሔር *"ምንኩሰና በኢትዮጵያ ዛሬና ትናንት"* በሚል መጽሐፋ ተአምረ ማርያምና ደቂቀ እስጢፋኖስ ገድል አበው ወላጎውን ዋቢ በማድረግ ያዘጋጁትን ቃለ መጠይቅ እንዳለ ጠቅሻለሁ፦

ደቂቀ እስጢፋኖስ በጳጳስ ፊት

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ደቂቀ እስጢፋኖስን ወደ ጳጳሱ ሲልክ እንዲህ ከሚል መልዕክት ጋር ነበር፣

> *...ወደ ጳጳሱ እንዲወስዷቸው አዘዘ፤ ለሱም፣ እንዲህ ሲል ላኩበት፣ እነዚህ መነኩሴዎች(ፈለሰኮ) ...ሥራቸው ሁሉ የአይሁድ ሥራ ነው። ለማርያም አይሰግዱም እኔንም አይታዘዙም። ውሰድና ክርስትናቸውን አውግዝ፣ ከሀገረታቸውንና ምንኩሰናቸውን ሻርና ሰዎች በእንጀራም በውሃም፣ በእሳትም(መጫርም) ለሕይወት በሚያስፈልገው ሁሉ እንዳይቀበሏቸው ...እድርግ።*

[237] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 110

መልዕክተኞቹ ቅዱሳንን አያጣደፏቸው ወሰዷቸው። ራቁታቸውን ነበሩ ምግብም አላገኙም። ...በዚህ ሁኔታ አያደከሙ ከጳጳሱ ዘንድ አመጧቸው። አነርሱም ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ከሰላምታ ቃል ጋር ጳጳሱን በሚገባ ቡራኬ ባረኩት።

የጳጳሱ ጥያቄ

"ይህ የሚሏችሁ እውነት ነውን?" ሲል ጠየቃቸው።

ቅዱሳኑ ሲመልሱ፤

"አይደለም አባ" አሉት።

ጳጳሱም፤

"ታዲያ ሃይማኖታችሁ ምንድነው?" አላቸው።

ቅዱሳኑም ሲመልሱ፤

ሃይማኖታችን በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ከሁሉ በላይ በሆነችው በሐዋርያት ገባኤ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፣ ለኃጢአት ማስተሰሪያ በምትሆን በአንዲት ቅድስት ጥምቀት፣ በሁለተኛው ትንሣኤ ጊዜ በሙታን ትንሣኤ ማመን ነው። ከቅዱሳን ሐዋርያትና በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ወደ ጸጥታ ወደብ ከቀዘፉ ከተከታዮቻቸው በኒቅያ ኩተሰበሰቡት ከ318 የአርቶዶክስ ሣኅበር፣ በቁስጥንጥያ ከተሰበሰቡ ከ150፣ በኤፌሶን ከተሰበሰቡ ከ200 የተሰየ ሌላ ትምህርት የለንም። በአካልና በሀሳዌያት ከሥላሴ አንጨምርም፣ ከሥላሴ አናጐድልም። ይህንን ከአባታችን ከቅዱስ አስጢፋኖስ ተምረናል፣ አሉ።

ጳጳሱም፤

...ሃይማኖታችሁ መልካም ነው፤ ታዲያ ለማርያም ለምን አትሰግዱም? አላቸው።

ቅዱሳኑ ሲመልሱ፤

"እኮ ዘረኩብነ ቅድመገ እንዘ ይብል እሰግድ ማርያም ዘእንበል ዘይትብሃል እሰግድ ለአብ፣ ወወልድ ወወመንፈስ ቅዱስ" ትርጉም "ካሁን በፊት ለአብ፣ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ እሰግዳለሁ ሲባል አንጂ ለማርያም እሰግዳለሁ ሲባል አላገኘ ንም።" አሉት።

አባ በርተሎሜዎስ አባ አስጢፋኖስን በሃይማኖቱ እንዳደነቀው ሁሉ አባ ገብርኤልም ደቀ መዛሙርቱን በማድነቅ እንዲህ አላቸው፡-

ዕውቀት የሌላቸው ናቸው እንጂ ዕውቀት ያላቸው አያቃልሏችሁም፤ ስለዚህ ለማርያም ባትሰግዱ ስሕተት አይሆንባችሁም፣ ብትሰግዱም ኃጢአት አይሆንባችሁም። የሞታችሁ ምክንያት ለማርያም ባለመስገድ አይሁን፣ ለንጉሥ ባለመስገድና የመምህራችሁን ስም ባለመስደብ እንጂ። በዚህ ብትሞቱ ጥሩ ይሆንላችኋል። አሁንም ኑ አብረን እንስገድ አላቸው።

ቅዱሳኑ፡-

አንተ አባታችን ነህ፣ በመንፈስ ስትነግረን መልካም ነው፤ አባ ሆይ፣ በፊትም ለማርያም አንሰግድም ያልነው አቃልለን አይደለም። እኛ ክርስቲያንን በማርያም ነው። የትምህርታችን አነሰልል፣ የመድኃኒታችን መጽሐፈ፣

የንጽህናችን መሠረት የተገኘው ስለ ድኅነታችን ሰው የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል በወለደች በድንግል ማርያም ነው አሉት። ከዚያ ከጳጳሱ ጋራ ከቤተ ክርስቲያን ገቡና ለማርያም ሰገዱ።

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ባጻፈው ተአምረ ማርያም ደቂቀ እስጢፋኖስ በአቡነ ገብርኤልና በአቡነ ሚካኤል እንደተወገዙ አደርጎ ቢያቀርብም ደቂቀ እስጢፋኖስ በበኩላቸው እምነታቸውን ምክንያት በማድረግ ያወገዛቸው አንድም ጳጳስ እንዳልነበረ ጽፈዋል። እስከ አሁን ባለው ሁኔታ በደቂቀ እስጢፋኖስ ዙሪያ ጥናት ካደረጉት ሊቃውንት መካከል አንድም የደቂቀ እስጢፋኖስን አባባል ያስተባበለ ጸሐፊ አልተገኝም።[238] እንደ ብዙዎች የታሪክ ምሁራን እምነት በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብና በደቂቀ እስጢፋኖስ መካከል የነበረው አለመግባባት ዋናው ምክንያት "ለምን እንደ ሌላው ተሸቆጥቁጠው፣ አሜን ይሁን ብለው አልተገዙልኝም" የሚል ይዘት ያለው ግላዊ የሥልጣን ጉዳይ ነው። ከዚህ ውጭ ደቂቀ እስጢፋኖስ ፀረ ማርያም ነበሩ ለማለት የሚያስችል ተጨባጭ መረጃ የለም።[239]

መሪጌታ ግርማ ኤልያስ ይህን እውነት እንዲህ ብለው አጠናክረዋል፡-

"በነገሥታቱ ሥልጣን ላይ ተቃውሞ ያስነሣና የአርሰን ስህተት ያጋለጠ፣ እንደ ፈጣሪ ለነገሥታት ያልሰገደ ማንኛውም ሰው ያለምንም ርህራሄና ይቅርታ በሕይወትና በንብረቱ ይፈረድበታል፣ ከሐዲ፣ መናፍቅ፣ እግዚአብሔር ቀብቶ ሳነገሠው የማይሰግድ ተብሎ ይወገዛል"[240]

የደቂቀ-እስጢፋኖስ ጉዳይ ነገሥታቱን እንቅልፍ የነሣበት ዋናው ምክንያት የእግዚአብሔርን ቃል ስለተላለፉ፣ "ፀረ ማርያም"ና "ፀረ መስቀሉ" ስለሆኑ ወይም ጠንካራ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ስለነበሩ እንዳልሆነ በገድላቱ ላይ በግልጽ ተዘግቧል።

ገድለ አኃው 1ኛና 2ኛ ዝርዝር የእስጢፋኖሳውያንን የመገደል ምክንያት ሲያብራራ፡- አንደኛ አጉብዳጆቹ መነኩሳት ወይም ካህናት-ደብተራ ነገሥታቱ ለሆነ ጉዳይ ሲወጡ፣ ሲገቡ፣ በሸንጉ ሲቀመጡ፣ ሁለተኛው ደግሞ በአነርሱ ስብከት በየቀኑ ብዙ ሰው ስለሚሳብና ብዙ ተከታይ ስላፈሩ ለንጉሥ የማይሰግድ ሕዝብ ይበረክታል ብለው ስለሰጉ እንደሆነ ይገልጻል። "ለንጉሥ ስገዱ" የሚል ጥያቄ በገድለ ወአኃት 86 ጊዜ የቀረበ ሲሆን ኢስጢፋኖሳውያኑ አንደም አልተቀበሉም።

[238] ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር፣ ምንኩስና በኢትዮጵያ ዛፊና ቅናንትና፣ ገጽ 52
[239] ዘኒ ኮግሶ ገጽ 52
[240] ደቂቀ እስጢፋኖስ ቦደብረ ብርሃን ስንቀ ገጽ 86

የደቂቀ እስጢፋኖስ የማስቃያ/መግደያ/ መንገዶች

መምህር ብሩክ ገብረ-ሊባኖስ ተስፋዬ "የሰው ያለህ" *(2005ዓ.ም፣ ገጽ 59-60)* በሚል መጽሐፋ ከፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ መጽሐፍ ለብቻ የለቀመውን የእስጢፋኖሳውያንን ዋና ዋናዎቹ የማስቃያና የግድያ ዓይነቶች የሚከተሉ ናቸው፡-

1. *በእጆቻቸውና እግሮቻቸው ያሉትን ጅማቶች በምላጭ እየተሰተሉ ያወጡባቸው ነበር፣ ይህም ብርታት እንዳያገኙ ሽባ ለማድረግ ነው።*
2. *ምላሳቸውን ይቁርጧቸው ነበር፣ ተቀባይነት ያገኘውን ትምህርታቸውን ማስተማር እንዳይችሉ ለማድረግ።*
3. *አፍንጫቸውንና ጆሯቸውን ይቁርጧቸው ነበር፣ ይህም በሰው ዘንድ አስጠሊታዎች እንዲሆኑ ነው።*
4. *ቋንጃቸውን ይቁርጧቸው ነበር፣ ይህም ከቦታ ወደ ቦታ ተዘዋውረው ማስተማር እንዳይችሉ ነው።*
5. *በጋለ ጉጠት/ወስፌ/ ዓይናቸውን ያወጡባቸው ነበር፣ ይህም ሌላውን ለማስደንገጥ ነው።*
6. *በጋለ ብረት ፊታቸውን ይተኩሷቸው ነበር፣ ይህም ሰው በሩቁ አይቶ እንዲርቃቸው ነው።*
7. *ቀኝ ግራ ጉንጫቸውን በምላጭ በመተልተል የተሰያዩ ቅርጾችን ያወጡባቸው ነበር፡- ይህም "የነገሥታቱ ባሮች ናቸው" ለማለት ነው።*
8. *የላይና የታች ከንፈራቸውን በመግፈፍ ጥርሳቸውን ባዶ ያስቀሩት ነበረ፣ ይህም በሰው ዘንድ መሳለቂያ ለማድረግ ነው፣*
9. *ዒላማ በማድረግ በጦርና በአንካሴ ይወጓቸው ነበር፣ ይህም የሚፈራ ካለ ለማስፈራራት ነው።*
10. *አንዳንድ ሴቶችን ጡታቸውን ይቁርጧቸው ነበር፣ ጎፍረተ ሥጋቸው ውስጥም እሳት ይጨምሩባቸው ነበር፣ እናትና እህት የላቸውም ይሆን?*
11. *የእድና የአግር ጣቶቻቸውን አንድ በአንድ እያሉ ይቁርጧቸው ነበር፣ ይህም የሕመም ነርቮች በጣቶች ጫፍ በብዛት ስላሉ "ስቃይ ሲበዛባቸው አቋማቸውን ይቀይሩ ይሆናል" ተብሎ ነው።*
12. *ሲሞቱ መቃብር በመክልከል ለአራዊት ይሰጡ ነበር፣ ሰዎቹ ክርስትና ቀርቶ ሰብዓዊነትም አልነበራቸውም ማለት ነው።*
13. *አጉዳ ያስረግጧቸው ነበር፣ ባልጠፋ ምት!!*
14. *እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን እንዳለ እንዲቆረጡ ይደረግ ነበር፣ ኒሮና ቄሣር ከዚህ የበለጠ ግፍ ምን ሠሩ?*

15. *ልብሳቸው፣ ቀባቸውንም ዒምር በመግፈፍ ኃይለኛ ብርድ ባለበት ራቁታቸውን በማስቀመጥና ምንም ዓይነት ምግብ እንዳያገኙ በማድረግ በረሃብ እንድማቅቁ ይደረግ ነበር። አገራት በተባለው እጅግ ኃይለኛ ብርድ ባለው ተራራ በአንድ ወቅት 98 እስጢፋኖሳውያን በብርድ አልቀዋል።[241]*
16. *ለየብቻ እየተነጠሉ በእስር መልክ ወደ እስላም አገር ይበተኑ ነበር። በእስላም አገር የታወቀ እሥር ቤት አልነበረም፣ ነገር ግን የንጉሡ ወዳጆች ለሆኑት መሲሊሞች አንዳንድ ሰው ይሰጣቸዋል፣ ከዚያም ራሳቸው በፈጠሩት የማሰቃያ ዘዴ ተጠቅመው አሰቃይተው ይገድሏቸው ነበር።ፕሮፌሰር ጌታቸው ይህን ሲገልጹ፡-"እስላሞቹም ደም በማስተፋት ቁጣውን አስተንፍሰውሰታል"[242]*

ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር *"ምንኩስና በኢትዮጵያ ዛሬና ትናንትና"* በሚል ርዕስ በጻፈው መጽሐፍ በዐፄ ዘርዓያዕቆብ ትዕዛዝ በደቂቀ እስጢፋኖስ ላይ የተፈጸመ ኢሰመጽሐፍ ቅዱሳዊ ድርጊቶች እንዲህ ተንትኖአል፡-

> *ጢምና ጠጉራቸው በደረቁ ያለ ውሃ በመሸለት፣አካላቸውን በጦር ወግቶ በተበሳው ቦታ ጠጠር በመወተፍ፣ በእሳት ነበልባል ውስጥ በማሳለፍ ወዘተ የበለጠ ሥቃይ የሚቀበሉበት ቅጣትም ይፈጸምባቸው ነበር። ከፈሉ-ኦችንም ከቤተ መንግሥቱ በሚወጣው የሽንትና ሰገራ ቦይ መውጫ እንዲተኙና የቆሻሻ ጎርፍ በላያቸው ላይ እንዲፈስባቸው በማድረግ ጣራቸውን ሲያበዛባቸው፣ መነኮሳቱንም ደግሞ ምላሳቸውንና አፍንጫቸውን ብቻ ሳይሆን ጡታቸውንም ይቆርጡዋቸው፣ በማሕፀናቸው ውስጥም የእሳት ፍም ይጨምሩባቸው ነበር። አንዳንዶችንም ሬሳቸውን ካቃጠሉ በኋላ አመዱን ወንዝ ውስጥ ይጨምሩታል። በአደባባይ ያላወጡት ምስጢር ሳይታወቃቸው ሊናገሩ ይችላሉ በሚል መድኃኒት (አብሶ) እንዲጠጡና አንዳንዱም ያለ አቅማቸው ኮሶ በማጋት ሆዳቸው ተተርትሮ እንዲሞቱ የሚያደርግበት አጋጣሚም ታይቷል።[243] እነዚህ ቅዱሳን በዘርዓ ያዕቆብ የቁጣና የአምልኮ ባዕድ ፍዳን የተቀበሉት ከሕያው እግዚአብሔር በቀር ለማርያም ስዕልና ለመስቀል ምልክት እንሰግድም በማለታቸው ነው።[244] ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብና አድር ባይ ጋሻ ጃግሬዎቹ በአገዛዝ ዘመኑ የተነሡትን የወንጌል አገልጋይ መነኮሳት፣ ማለትም እነ አባ እስጢፋኖስ (ዐምደ ሃይማኖት ወማንቶት ቤተ ክርስቲያን ዘጉንዳጉንዲ)፣ አባ አበ ከረዙል፣ አባ ዕዝራንና ሌሎች የክርስቶስ ደቀ መዛሙርትን ለመፍጀት የተጠቀሙበት ዋነኛ ክስ «ፀረ-ማርያምና ፀረ መስቀል፣ የሚል ነበር።[245]*

መጽሐፍ ቅዱስ፡-

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በመጽሐፋቸው፡- "አረማዊን የገደለ ምንም ወንጀል አልሠራም"[246] ብለዋል። ይህ የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን ክርስትና ትልቅ ጥያቄ ውስጥ

---

[242] ደቂቀ-እስጢፋኖስ፣ በሕማ አምላክ ገጽ 35
[243] ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር *(2000 ዓ.ም)*፣ ምንኩስና በኢትዮጵያ ዛሬና ትናንትና፣ገጽ 44-44
[244] ኢኡተቤክ *(1985 ዓ.ም)*፣ ተአምረ ማርያም፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት ገጽ 133
[245] ገብረ መሲሕ*(2002 ዓ.ም)* ፣ የመምሩ ምርቅ እና መረቅ፣ ገጽ 35
[246] ዘርዓ ያዕቆብ፣ መጽሐፈ ብርሃን፣ *1 26-27*

አሰምሮ ለማሰብ እጅግ የሚከብድ ጭካኔ በእግዚአብሔር ስም፣ *"አገረ እግዚአብሔር" "መሐሏ ገነት" "የክርስቲያን ደሴት"*...ወዘተ በማለት ስናቆላምጣት በፍጹም በማንሰለቸው አገራችን የተፈጸመ ህቡዕ ዘመን ዘለቅ አንነት የሚያስደፋ ታሪክ ነው። ለዚህ ንስሐ መግባት የሰብንም ወይ? *"አለባብሰው ቢያርሱ ለአረም ይመለሱ"* በቆየ ብሂላችን እንደምንለው ይህን ለዓለም አሮጌ ለእኛ ለባለታሪኮቹ አዲስ የሆነ የጭፍጨፋ ታሪክ ሌላ ስም ሳንሰጠው በእግዚአብሔር ፊት በመናዘዝ ለምድራችን ፈውስ በእውነት ንስሐ ልንገባ ይገባል። *"ምክንያት ሰነፎች ቤት ሲሠሩ የሚጠቀመብት ሚስማር ነው"* እንደሚባለው ከንስሐ ውጭ ምክንያተ ብዙነት ይህን ዘመን ዘለቅ ቁስል አይፈውስም፣ ምድራችንም እንድትባረክ አያደርግም። ከላይ የተመለከትነው አሰቃቂና ዘግናኝ የመዓት ውርጅብኝ የጠራ እምነት በያዙት በአባ አስጢፋኖስ፣ በደቂቀ አስጢፋኖስና በሌሎች ሰማዕታት ላይ ቀርቶ እንደተባሉትም "መናፍቅ" ቢሆኑ እንኳ አይገባቸውም። አሳዳጆች መንፈሳውያን ቢሆኑ *"ባእምነት የደከመውንም ተቀበሉት በአሳቡም ላይ አትፍረዱ" (ሮሜ.14:1)* ቃሉ እንደሚለው ባደረጉ ነበር።

ከሰማዕታት ደም የተወለዱ ሰማዕታት

አባ አስጢፋኖስና የእርሱ ተማሪዎች የነበሩ ደቂቀ አስጢፋኖስ ከላይ እንደተመለከትነው ለሰው አንሰግድም፣ ለማርያምና ለመስቀል የአምላክ ስግደት ይገባቸዋል የተባለውን ኑፋቄ በቃሉ ላይ ቆመው በመቃወማቸው ሰማዕት ሆነው እንዳሸነፉ ታሪክ ይመሰክራል። ብዙዎች ይህን ታላቅ የእምነት ተጋድሎ በዓይናቸው ስላዩት ለሰማዕትነት ራሳቸውን በእምነት ሰጥተዋል፦

"ገድለ" እማሆ መክብዬ

ደብረ ሰላም በሚባል ቦታ የምትኖር መክብዬ የሚሏት አንዲት መበለት ነበረች። እንግዳ ተቀባይ፣ በምግባሯም ጥሩ ነበረች። ወንድና ሴት ልጆች አሏት። ይኸንን ዓለም ለመተው ስትወስን ንብረቷን ከሦስት ከፈለችና ዘመዶቿን አንብረቷ፦ " ሁለቱ እጅ ለልጆቹ ይሁን አንዱ እጅ የኔ ነው ዕዳ ቢመጣብኝ በልጆቼና በዘመዶቼ ላይ ሐዘን እንዳይመጣ ከሱ እሰጣለሁ" አለቻቸው። እሷ ግድ እንደሚመጣባት እያወቀች ቅዱሳኑን ከቤቷ ታስገባቸው አብራቸውም ለመሆን ትፈልግ ነበር። (ንብረቷን) እንደዚህ (የከፋፈለችው) ስለዚህ ነው። በዚህ ሥራ ዘመዶቿ ብዕዕት አደረጓት አደነቋትም። "ጥሩ ነው እንዳልሸው ይሁን" አሏት። ከዚህ በኋላ ቅዱሳኑን "መነኩሲት እንድሆን አፈልጋለሁ" አለቻቸው። "ታገሺ የምንኩስና ሥራ አሰጨናቂና ጽኑ ነው ብዙ ሥቃይና ስደት አለበት፦ እስከ መሞትም ያደርሳል" አሏት። "እግዚአብሔር ዐቅሙን ይሰጠኛል" አለቻቸው። ሁለቴም ሦስቴም ነገሯት፦ እሷም ያንኑ መለሰች። ወደነሱ ለሚመጣ ሁሉ ሥርዓታቸው እንደዚህ ነው። ከዚያ መንኩሳ በንጽሕ ሥርዓት ኖረች። ከዚያ በኋላ እንደነገሯት ደረሰባት። ቅዱሳን እና እሷንም ከቤቷ ያዟቸው። እሷም እንዳለችው አደረገች (ቅጣቷን) ሰተላኩት ከገንዘቧ ሰጠች፣ ልጆቿን አላሳዘነችም። ወስደው ለብቻዋ አቆሟት።

ያስገባ አደገኛ ፍልስፍና ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ሰውን እንዲገድል አይፈቅድም። ከአሥርቱ ትዕዛዛት አንዱ *"አትግደል"(ዘፀ.20:13)* ይላል። ኢየሱስ በአዲስ ኪዳን፦ *"ለቀደሙት አትግደል እንደተባለ ሰምታችኋል፣ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል። እኔ ግን አላችኋለሁ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል" (ማቴ.5:21)* በማለት ለነፍሰ ገዳይ ሳይሆን ወንድሙን ለሚቆጣ ሁሉ ፍርድ እንደሚገባው ገልጾአል። እንዲሁም ነፍሰ ገዳዮች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ ቃሉ ይናገራል*(ራእ.22:15)*። *"ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ። እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል፣ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን ልንሰጥ ይገባናል" (1ዮሐ.4:16-17)*። በክርስቶስ ሞት በእውነት የዳነ ሰው ማንኛውንም ሰብዓዊ የሆነ ፍጡር ለመግደል አይነሣም። ታዲያ መንፈሳዊነታቸው በአንዳንዶች የሚመሰከርላቸው ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከላይ በተመለከትነው አሰቃቂ ሁኔታ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ቆመው ውሸትን ያወገዙ የኦርቶዶክስ አባቶችን ለእግዚአብሔር እውነትና ለቤተ ክርስቲያን በመቅናት እንደገደሏቸው በኩራት ቢወሳላቸውም በእግዚአብሔር ቃል ግን ድርጊታቸው የተወገዘ ነው።

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ እንደዚህ የከፋና መራራ የመከራ መዓት ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ ሌላ ነገር በእጃቸው በሌላቸው የአምነት አበው ላይ ሲያደርስ ማን መርቷቸው ነው? ይህን ኢሰብዓዊና ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አኩይ ድርጊት ሲያደርስ ቤተ ክርስቲያን ዝምታን ለምን መረጠች? ያለፈ ይቅር ካልን አሁን ባለንበት ዘመን ስለ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብና ስለዚያ ክፉ ዘመን የሚጽፉ ብዙዎች የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን እንከን አልባ መሪና ታላቅ መንፈሳዊ ሰው ብቻ አድርገው በማቅረብ በእውነት ላይ መዋሸትን ለምን መረጡ? ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ለአገር ያደረገው መልካም ነገሮቹ ሲጠቅሱ በኢትዮጵያ የነፋቄን ትምህርት እንዳስፋፋና የእምነት አባቶችን በጭካኔ እንደ ጨፈጨፈም መገለጽ አለበት። ገዳይና ተገዳዮች በዚህ ዘመን ባይኖሩም ለተሳሳተ ድርጊት የመንፈሳዊነት ሽፋን ዛሬም እየተሰጠ ስላለ በቃሉ ገለባውን ከፍሬው ለይተን የራሳችንን እምነትና አቋም በቃሉ እንድንፈትሽና ካለፈ ታሪክ ዞር ብለን በማየት መማር እንድምንችል ይህ ታሪክ በሰፊው ተጽፎአል።

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ በአፈታሪክ ላይ የተመሠረተ ክርስትናችን ወደ ቃሉ እንድመለስ፣ ያለፈውን አሉታዊ ታሪክ በትክክል በመረዳት አዎንታዊ ታሪክ ለመሥራት እንድንነሳ፣ የጠራ ወንጌል ትውልዱ ዳግም እንዲያነሣ፣ የለማይን ምሕረትና ፍቅር በምድራችን ተያይዘን ለማወጅና ምድራችንን ከእርግማን በንስሐ ለማጽዳት ነው። ስለዚህ የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ አድናቂዎች ከእርግማን በንስሐ ለማጽዳት ነው። ስለዚህ የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ አድናቂዎች ነን የሚሉ ሰዎች ለትምህርታችን ይሆን ዘንድ የእርሱን ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ነን የሚሉ ሰዎች ለትምህርታችን ይሆን ዘንድ የእርሱን ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ሳይጠቅሱልን ማለፍ አልነበረባቸውም። ግማሽ እውነት ከውሸት ብላጫ የለውምና። ይህ በቀደምት አባቶቻችን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ የተከፈለ የደም ዋጋ ነው። ይህ ኢሰብዓዊ፣ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና በሰው

ንጉሡ:- "በእነሱ ዘንድ ምን አየሽ? ለምን ከነሱ ጋራ ተባበርሽ?" ብሎ ላከባት:: ሮ"እግዚአብሔርን መንገድ ስላገኘሁ ከነሱ ጋራ ተባበርኩ" አለችው:: ደግሞ (እንድትመለስ) በብዙ ሸነገሏት: እምቢ አለቻቸው:: ከቅዱሳኑ ጋራ ወደ አሳቱ ወሰዷትና አዚያ ብዙ አስቃዩዋት:: የንጉሡ ወታደሮች በብዙው ሰደቧት:: በትር እያነሡ ደበደቧት:: እጇን ይዘው ወዲያና ወዲህ እየጎተቱ ከአሳቱ አጠገብ ጣሏት:: ትንታጉን እያነሡ እላይዋ ላይ በመበተን አቃጠሏት:: ደግሞ ፍም አንስተው አልብሷ ላይ ጣሉት::

ወታደሮቹ የመራሮች ውጤት ስለሆኑ እሷን ማስቃየቱን ጋብ አላደረጉም:: (ሲወለዱ) የወጠብተን በር ሳያፍሩ እግሮቿን (በርግደው) ይዘው እሥጋዋ ላይ እሳት ትንታግ እየተከታተሉ ጨመሩበት:: ሥጋዋ እስኪነፍር ድረስ እየተፈራረቁ እንደዚህ አደረጉ:: ቅዱሳኑ ያበረቷት ነበረ:: እሷም በዚያ የቃጠሉ በሽታ (ለማዕትነቷን) እስክትፈጸም ይሽንን ሁሉን ታገሠች[247]

"አንዱ እግሬ ተረስቷችሁ ቋንጃውን አላወጣችሁምና ተመለሱ"

የቅዱሳኑን የሸኾናቸውን ቋንጃዎች ሲያወጡ የአንዱን ወንድም አንድ እግር ረስተውት ናሮ በልቡ አሰበና: "ሐዋርያ ጳውሎስ የክርስቶስን ፍቅር ማን ያስተወናል? ሥቃይ ወይስ ችግር?" አለ:: ይሽንን ብሎ የንጉሡን ወታደሮች ጠራቸውና: "አንዱ እግሬ ተረስቷችሁ ቋንጃውን አላወጣችሁምና ተመለሱ" አላቸው:: ይሽንን ሲሰሙ ገረማቸው:: ተመልሰው ቋንጃውን አወጡለት:: አንዱ ወንድም ምላሱን: ለፍንጫውን: የሸኾናውን ቋንጃ ሲቆርጡት ደሙ ስላላቆመ እዚያው ለማዕትነቱን በጌታ ሰላም ፈፀመ:: ጸሎቱ ከኛ ጋራ ትሁን አሜን::[248]

ዘግናኙን ግድያ ያነበቡ ምን አሉ?

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በበኩላቸው እንዲህ ሲሉ በቁጭት ተስፋቸውን ያዘለች አሳብ ጽፈዋል:-

በየትም አገር ቢሆን በተደላደለው ሥርዓት ላይ ተመቻችተው የተቀመጡ ኃላፊዎች የሚነካቸውን ለውጥ ስለሚጠሉ እንዲህ ያለውን የለውጥ መሪ ይቃወሙታል:: እንዲያውም ተጠሪዎቹን ባላቸው ሥጋዊና መንፈሳዊ ኃይል ሁሉ ሊያጠፏቸው ይሞክራሉ:: በአባ እስጢፋኖስ ላይ የደረሰው ይህ ነው:: አበባቸውን አረገፉት፤ የእንቅስቃሴያቸው ክልባል ውኃ ቸልሰውበታል ሳይቀጣጠል ቀረ:: የመንግሥቱን ኃይል የሚጋፉት አልነበረም፤ ሆኖም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውግዝ ታደርጋቸው እንጂ ተልዕኳቸውን ውስጥ ውስጡን በጽሞና እየተቀበለችው በመሄድ ላይ እንዳለች ሥነ ጽሑፎቿ ይመለክራሉ::[249]

[247] ጌታቸው ኃይሌ (ፕሮፌሰር)(*2003 ዓ.ም*)፣ ደቂቀ እስጢፋኖስ፣ ገጽ 142

[248] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 173

[249] ከማቱ ዘርሃነ፣ ቁጥር 3 *2004 ዓ.ም* ገጽ 30

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም "ደቂቀ እስጢፋኖስ" በተባለው ፕሮፌሰር ጌታቸው በጻፉት መጽሐፍ የውጭ ሽፋን ላይ:- "*የደቂቀ እስጢፋኖስ ሰቆቃ ያስደነግጣል፣ ያሳዝናል፣ ያስቆጣል፣ የማናውቀውን ራሳችንን እና እርቃናችንን ያሳየናል*"[250] ብለዋል::

ሌላ ጸሐፊ ደግሞ:-

የክርስቲያን ደሴት፣ ሀገረ እግዚአብሔር እየተባለ ቢፎክርም፣ የክርስቲያን አባቶች ደም እንደ እንሰሳ ደም ሲፈስ ግን ጆሀድ የምታካሂድ ሀገር ያላት ማንም አልነበረውም:: በፍቅርና ራስን ለሞት አሳልፎ መስጠት ከወንጀለኝነትና ከኃጢአት አረንቋ ሕዝብን ለመታደግ የተመሠረተው ክርስትና ጀሀዳውያን እስኪመስል ድረስ ቅዱሳኑ ሲታረዱና ሲመነጠሩ ይህ ድርጊት ፀረ ወንጌል አካሄድ ነው ብሎ የተቃወመ አንድም የሃይማኖት መሪ አንድም ደብተራ አልነበረም:: እንዲያውም አብረው አሳዳጆችና ገዳዮች ነበሩ[251] ይላል:: መናፍቃንም ከመጽሐፍ ይልቅ ለይፍ ከጥቅስ ይልቅ ዱላ ይቀናቸው ነበርና ወንድሞቻቸው በወንጌል አስረጂነት ሲከራከሯቸው አንገታቸውን በሰይፍ ይቆርጡ ምላሳቸውንም ይፈንኗቸው ጀመር:: ከዚህም የተነሣ ጥንታዊዋ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን አስተምህሮ ቅርፅና መልክም ሆነ አጠቃላይ የእምነት አቋም ተበራረዘ::[252] ብለዋል::

በዓለም ላይ "*ለወንጌልና ለእውነተኛ ክርስትና በመቅናት*" በክርስቲያኖች ላይ እንደዚህ የከፋ ኢሰብአዊ ድርጊት በክርስቲያን ነን ባዮች በእውነተኛ ክርስቲያኖች ላይ የተፈፀመባት ከኢትዮጵያ ውጭ ሌላ ሀገር ትኖር ይሆን? መጽሐፍ ቅዱስ በእውነት የዳኑ የክርስቶስ ልጆች ለክርስቶስ ብለው እንዲሞቱ እንጂ ስለ ክርስቶስ ብለው ሰዎችን እንዲገድሉ ያስተምራል ወይ? ይህ የክርስቶስ ትምህርት አይደለም:: ድርጊታችን በመጽሐፍ ቅዱስ የማይመራ ክርስትና እንደምንከተል ያሳብቅብናል:: ትውልድ ከዚህ አሉታዊ ታሪክ አዎንታዊ ታሪክ መሥራትን መማር አለበት:: የአንድነታችን ጠላት ልዩነታችንን ያለመቀበል እንደሆነ አንዘንጋ:: የተነሣው ተሐድሶ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቦታ ቢያገኝ ናሮ ምን ይሆን ነበር? ለሚለው ጥያቄ ወንድዬ ዓለ በመጽሐፉ ሲገልጽ:-

በዚህች ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዓይነቱ መነቃቃት ሳይቋረጥ በመላት ተካሂዶና የሥነ መለኮታዊ ይዘቱ በሚገባ ተቀርጾ እንዲሁም በሕይወት መታደስ ላይ አትኩሮ ቢሆን ናሮ በነፍስም በሥጋም አገራችንና ሕዝባችን ከአሁን በተሻለ አቋም ላይ ይገኝ ነበር የሚለውን ግምት ብዙዎች ይጋሩታል::[253] ይላል::

በመካከለኛ ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ የተነሣው የተሐድሶ ጥያቄ ሲወሳ ጥያቄውን ያመከነው ዘርዓ ያዕቆብ አብሮ ስሙ ይነሳል:: ዘርዓ ያዕቆብ ማን ነው? ሰፊና ጥልቅ መረጃ በሚከተለው ምዕራፍ ላይ ቀርቧል::

[250] ጌታቸው ኃይሌ (*2003 ዓ.ም*)፣ ደቂቀ እስጢፋኖስ፣ በሕጎ አምላክ፣ የመጽሐፉ ውጭ ሽፋን ላይ ከተጻፈው

[251] የኢትዮጵያ ለመታዊ ታሪክ መጽሔት አራተኛ መጽሔት *1954*፣ ግርማ ዘውዱ *(1985 ዓ.ም)*: ኢትዮጲስ: ካሉ ማ/ቤት ገጽ 78 - 79

[252] ቀሲስ ደረጀና ጄቶ-መዝሙር በዛ፣ «መጽሔደስ የገቡ መናፍቃን»፣ ገጽ 148

[253] ወንድዬ ዓለ፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዘሃጥኦ፣ ገጽ 4::

፫

የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ማንነት

የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ መልካም ሥራዎች

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ለዚህች አገር አንድነት በተጫወተው አዎንታዊና አንፀባራቂ ሚና፣ በመሪነቱና በጸሐፊነቱ ሊደነቅ ይገባል። በኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት ላይ የታወቁ ኢንግሊዛዊው ምሁር ኤድዋርድ አሉንድሩፍ የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን ታላቅነት ሲገልጹ፦ *"ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከአክሱም ገናና ንጉሥ ከኢዛና ጀምሮ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ንጉሥ ሲሆን ከአርሱ ጊላ ከተነሡት ነገሥታት መካከል ከዐፄ ሚኒልክና ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ጋር ይመሳሰላል"*[254] ብለዋል። የተለያዩ መጻሕፍት ታላቅ አስተማሪና የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እንደ ነበር መስክረዋል። ዶክተር ምክረ ሥላሴ ገ/አማኑኤል "የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ" በሚል መጽሐፍ፦ *ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ እንደነገሡ ታላቅ ሥራዬ ብለው የያዙት አንደኛ በኢትዮጵያ ስብከተ ወንጌል እንዲሰራጭና የክርስትና ሃይማኖት በሰፊው ተሰብክ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በመላ ኢትዮጵያ እንድትስፋፋ ማድረግ ነበር*[255] ብለዋል።

[254] Edward Ullendorff, (1960) ,*The Ethiopians: An Introduction to the Country and People*, second edition London: Oxford University Press, p. 69

[255] ቀ/ዶ/ር ምክረ ሥላሴ ገ/አማኑኤል *(2002 ዓ.ም)* ፣ *የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ (ሁለተኛ መጽሐፍ)*፣ አዲስ አበባ፣ ገጽ 128

እንዲሁም "*የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*" በሚል መጽሐፍ ገጽ (49)

> *የቤተ ክርስቲያናችንን ሥነ-ጽሑፍና ሊኑ-ጥበብ ያስፋፉት የአምልኮ ጣኦትን ከምድረ ኢትዮጵያ ጨርሶ ለማጥፋት የታገሉት ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ናቸው።* በማለት በቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ቦታ ጸሐፊው አመልክተዋል። መልካም ምስክርነት የተገባ ነው።

ዘርዓ ያዕቆብ እንደተባለው በወንጌል ስብከት የበረታና ቤተ ክርስቲያንን ያስፋፋ መንፈሳዊ ሰው ከሆነ በእምነት ስም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አቋም የያዙትን አበ እምነቶች የማሰቃየትና የመግደል ፍልስፍናን ከየት አመጣው? ስብከትና ሰይፍን አንድ ላይ ማስኬድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና አስተምህሮ አይደለም። ከአንድ ምንጭ ደግሞ ጣፋጭና መራራ ውሃ መቅዳት እንደማይቻል የታወቀ ነው። ታሪክን በጥንቃቄ ያጠኑ አንዳንድ ሰዎች ዘርዓ ያዕቆብ የአምልኮ ጣኦትን ከምድራችን እንዳስወገደ የሚነገርለትን ተረት በፍጹም አይቀበሉም። በተቃራኒው ዘርዓ ያዕቆብ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን በምድራችን በማስፋፋት፣ እንደ አምላክ በግልጽ እንዲሰገድለት በማስገደድ፣ እንቢ ባሉት የእምነት አበው ላይ ኢሰብዓዊ ድርጊት በመፈጸሙና በዘግናኝ ሁኔታ በማስገደል፣ ነፃ ሐሳብ በምድራችን እስከ ዛሬ እንደ ጦር እንዲፈራ በማድረግ ረገድ አሁን ላለንበት መንፈሳዊ ቀውስ የዳረገን መሪ እንደነበር ይናገራሉ።

የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎች

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሉ ከግዕዝ ወደ አማርኛ *"ደቂቀ አስጢፋኖስ በሕግ አምላክ"* በሚል ርዕስ በተርጉመት መጽሐፍ የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ትምህርታቸው ምን ይመስል እንደነበር ፍንጭ ይሰጠናል፦

> *ለየገዳማቱ በላካቸው መጽሐፍ መግቢያ ውስጥ ፍጥረት ሁሉ ለእመቤታችን ተፈጠረ። አዳምና ሔዋን ስለ እመቤታችን ተፈጠሩ ...በቅድስት ማርያም ስም ለአንድ ለተጠማ ሰው ውሃ ስለሰጠ ብቻ መንግሥተ ሰማያት ገባ* የሚል ስላለበት አበምኔቶቹ ስለ ንጉሡ ትዕዛዝ ምን እንደሚያደርጉ ተቸገሩ፣ አንዳንዶች ደፍረው ተቃውሞ ጀመሩ[256] ብለዋል።

ይህ አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። በአዲስም ሆነ በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ አይናገርም። ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ እናት የሚሰጠው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክብር አንዳለ ሆኖ ፍጥረት ሁሉ አዳምና ሔዋን ለእርሷ ክብር ተፈጠሩ ካልን የእግዚአብሔርን ቦታ የሰጠናት አይመስልም ወይ? ሌላው *"በቅድስት ማርያም ስም ለአንድ ለተጠማ ሰው ውሃ ስለሰጠ ብቻ መንግሥተ ሰማያት ገባ"* የሚል የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የፌዝ ትምህርት የኢየሱስ ክርስቶስን የቤዛነትን ሥራ በግልጽ የሚቃወም ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የተገለጸች የጌታ እናት ማርያም የእግዚአብሔርን ክብር የመሻማት ዝንባሌ እንደነበራት መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም። ስለ እርሷ በቃሉ የተጻፈው

[256] ጌታቸው ኃይሉ (ፕሮፌሰር) *(1996 ዓ.ም)*፣ *ደቂቀ አስጢፋኖስ*፣ ገጽ 25-26

በአገራችን ባለት አንዳንድ ድርሳናትና ገድላት ከተጻፈው ጋር በብዙ ይጋጫል። ሐዋርያው ዓለም ሳይፈጠር በክርስቶስ እንደተመረጥንና እግዚአብሔር ይህን ያደረገበት ትልቁ ዓላማ የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ እንደሆነ ገልጾአል፦

ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን። በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን። በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ። (ኤፌ 1: 3-6)

ሐዋርያው ጴጥሮስ በነገር ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር ይከብር ዘንድ ይላል፦ *ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ በሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከበር ዘንድ አሜን። (1ጴጥ.4:11) ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት (1ቆሮ.10:31)።* ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር እንጂ ለማርያም መሰጠት እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ በፍጹም አይናገርም። የጌታችን እናት ማርያም የአገራችን ድርሳናት የቀደመውን ቃሉን ቸል በማለት የሚሰጧትን ከንቱ ውዳሴ እንደማትቀበል የታወቀ ነው። ከሁሉ በላይ በእግዚአብሔር የከበረችና የተባረከች የጌታ እናት የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በሚጋፋው በእኛ ተረት ቦታ ለማግኘት የምትታገል ሴት አይደለችም።

በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የተፈጠሩ የኑፋቄ ትምህርቶች?

መምህር ጽጌ ስጦታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ጳውሎስ የከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ምሩቅ፣ በጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል የስብከተ ወንጌል ኃላፊ፣ የወንጌል ሰባኪ፣ አስተማሪ ሆነው ያገለገሉና በቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ አስፈላጊነት ላይ ዳጎስ ያሉ ጥራዞች ያሏቸውን መጻሕፍት የጻፉ አገልጋይ እንደሆኑ ግለ ታሪካቸው ያወሳል። ወጋገን (ገጽ 215 -216/ 2004 ዓ.ም) በሚለው መጽሐፋቸው የዘርዓ ያዕቆብ ጉባዔ የወሰነው ውሳኔና የፈጸመው ስህተት በሚል አሳብ ሥር የሚከተሉትን ዘርዝረዋል።

1. *መስቀል ያማልዳል።*
2. *ለመስቀልና ለማርያም የፈጣሪ ስግደት ይገባቸዋል።*
3. *በክብራቸው ከፈጣሪ ጋር ተስተካክለዋል።*
4. *ዓለም የተፈጠረው እመቤታችንን ለማመስገን ነው።*
5. *አዳምና ሔዋንም እመቤታችንን ለማመስገን ተፈጠሩ።*
6. *ለሥዕል ስግደት፣ ውዳሴና ምስጋና ይገባል።*

7. *ለእመቤታችን ሥዕል የሚሰግድ ከቆመበት ሥፍራ ይጥፋ፣ ስም አጠራሩም አይታወቅ መላዕክትም አሜን ይበሉ።*
8. *16ቱን ትዕዛዛት በመፈጸም የእግዚአብሔር ባሪያዎች ለመሆን አንሻ ይልቅስ የማሪያም ባሪያዎች ለመሆን እንሽቀዳደም።*
9. *የእመቤታችንን የ33ቱን በዓላት እንደ እሑድ ሰንበት አድርጎ የማያከብር ወልድ በጌትነቱ እስኪመጣ ድረስ የተረገመ ይሁን።*
10. *ለሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ስግደት ይገባል።*
11. *መስቀል በአንገት ማሠር ይገባል።*
12. *በመስቀል ምልክት ማማተብ ሰይጣንን ያርቃል መንፈስ ቅዱስንም ያቀርባል።*
13. *ድርሳናትና ገድላትን ማንበብና መጻሰይ ይገባል።*
14. *ከተነበቡ በኋላ መሳሳምና መተሻሸት ያስፈልጋል።*
15. *በቅጽረ ቤተ-ክርስቲያን የሚገኝ ማንኛውም አፈር አመድ /እምነት/ ቅጠላቅል ውኃ ሁሉ ከማንኛውም ደዌ ይፈውሳል።*
16. *የእመቤታችንን ተአምር የሰማ ሥጋ ወደሙን እንደተቀበለ ይቆጠርለታል። የሚሉትና የመሳሰሉት ሕገ ልቡናዎች የተሠሩበት ጉባዔ ነበር።*

ዘርዓ ያዕቆብ ካስተማረው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች መካከል የ*"መስቀል"* ምልክት የእግዚአብሔር ስልጣንና ኃይል እንዳለው ብቻ ሳይሆን ስግደት እንደሚገባውና እንደሚያማልድ በገሃድ ማስተማሩና ዛሬም በብዙዎቹ መታመኑ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ለማን መሰገድ እንዳለበት በግልጽ ተናገሯል፦ *"በላይ በሰማይ ካለው በታችም በምድር ካለው ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውም ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ። አትሰገድላቸው አታምልካቸውምም" (ዘዳ.20:4-5)። "እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል"(ዮሐ.4:24)።* የሚለውን ግልጽ አስተምህሮ ዘርዓ ያዕቆብ መተላለፍን ለምን ወደደ?

ለእንጨት መለኮታዊ ኃይል ማላበስና ልዩ ሃይማኖታዊ ጉልበት መጨመር የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ አይደለም። መስቀል በራሱ የኃይል ምንጭ ሳይሆን የኃይል ሁሉ መሠረት የሆነ ጌታ የተሰቀለበት ነው። መስቀል ኢየሱስ ክርስቶስ ስለተሰቀለበት ብቻ የኢየሱስ መለኮታዊነት ወይንም ልዩ ኃይል ተካፋይ አልሆነም። የመስቀል እንጨት ቢሆንም የዓለም መድኃኒት በእርሱ ላይ በመሰቀሉ ልዩ ያደርገዋል። ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ *"ባዚህ የመስቀል ዘንግ ሐዋርያቱ ተዓምር ሠሩ፣ አጋንንት አባረሩ፣ ጣዖታትን ሰባበሩ"* በማለት በሐዋርያት ትምህርትና አገልግሎት ያልተጻፈውን አስነብቦናል። በሐዋርያት አገልግሎት ተዓምር የተሠራው፣ አጋንንትን ከሰው ያስወጡት በመስቀል ዘንግ ሳይሆን በመስቀል ላይ በተሰቀለው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስ ወደ መቅደስ ከሚገቡት ምጽዋት

ይለምን ዘንድ መልካም በሚሉአት በመቅደስ ደጅ በየቀኑ ያስቀምጡት ከእናቱ ሆድ ጀምሮ አንካሳ ለነበረው ሰው ፈውስን ያመጣለት *"በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ"(የሐዋ.3:6)* በማለት ነበር። በአጋንንት አሠራርና በጥንቆላ ተይዛ ወደ ነበረችው የሰማርያ ከተማ ፊልጶስ ወርዶ ክርስቶስን ሲሰብክ፡- *"ርኩሳን መናፍስት በታላቅ ድምፅ እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ይወጡ ነበርና ብዙም ሽባዎችና አንካሶች ተፈወሱ በዚያችም ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ"* (የሐዋ.8:4-7)። ሐዋርያው ጳውሎስ አገር ገዢውን ከማመን ሊያጣምም የፈለገውን ጠንቋይ ሥራውን ያፈረሰው *"...እነሆ የጌታ እጅ በአንተ ላይ ናት"(የሐዋ.13:10)* ብሎ የጌታን ስም በእምነት በመጥራት ነበር። ኢየሱስም ሐዋርያቶችን ሲያዝ በስሙ እንጂ በመስቀል ስም አጋንንት እንዲያወጡ አልነበረም። *"በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ"*(ማር.16:17)።

ኢሰብዓዊ ድርጊቶቹ

ዐፄ ዘርዓ ያቆዕብ የአገር መሪ፣ የወንጌል አማኝና ሰባኪ እንደነበር ተመስክሮለት ሳለ በተረዱት የቃሉ እውነት ላይ የቆሙትን አማኞች እጅግ ዘግናኝ፣ ኢሰብአዊና ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ እርምጃ ወስዶባቸው እንዳሰቃያቸውና እንደገደላቸው ብዙዎች አይጠቅሱትም። ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በሃይማኖት ሰበብ ስለወሰዳቸው ዘግናኝ እርምጃዎች ለመናገር ፍርሃት ለምን ነገሠ? የጸሐፊው ስም ያልተጻፈበት *"የአቡነ አስጢፋኖስ የደም ድምፅ!!"* በሚል ርዕስ በተጻፈው መጽሐፍ (ገጽ 28)

> *እስከ ዛሬ በአገር ውስጥ ያሉ ምሁራን ወይም ሊቃውንት ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በዘመኑ የሠራውን ግፍ ለመጻፍ ላልደፈሩም* ካለው በኋላ *"ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የነገሠባቸው ሠላሳ አራት ዓመታት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የልቅሶና የዋይታ ጊዜ ነበር ማለት ይቻላል።* ብሏል። ወንድዬ አሊ በመጽሐፉ ስለ ዐፄ ዘርዓያዕቆብ ሲናገር፡- *ከመጠን ያለፈው ቅንዓቱ በተቃዋሚዎቹ ላይ ኢሰብዓዊን ቅጣት እንዲፈጽም ጎሊና ሚዛኑ እስኪዛባ አድርሶታል፣ በማለት ጽፏል።*[257]

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በደቂቀ አስጢፋኖስ ላይ ስላወጀው ዘግናኝ አዋጅ በገድለ አቡነ አስጢፋኖስ የቀረበው በ1956 ከታተመው ተአምረ ማርያም የተወሰደው - ተአምር እንዲህ ይነበባል፡-

> *ንጉሡ አፍንጫቻቸውና ምላሶቻቸው እንዲቆረጡ አዘዙ። ሌሎችም እንዲፈሩ ተብሎ አፍንጫቻቸውና ምላሶቻቸውን ቁረጡአቸው። ...እነዚያ ወንጀለኞች አፍንጫቻቸውን፣ ምላሶቻቸውን በመቁረጥ ብቻ ለምን ተዋችኋቸው? በነፍስ በሥጋ ድንግል ለሸነኸ ለእግዝአትነ ማርያምና ለልጅዋ መስቀል አንሰግድም ስላሉ በድንጋይ ሊወገሩ ይገባል አሉ። በየካቲት ወር በ2ኛው ቀን ዓርብ ዕለት በድንጋዮች ወግረው ገደሏቸው*[258] ይላል።

[257] ወንድዬ አሊ፣ ገጽ 55

[258] *ገድለ አቡነ አስጢፋኖስ፣ ገጽ ገጽ 31-32*

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን በሃይማኖት ስም የተፈጸመውን ኢሰብአዊ ድርጊት በፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሉ "ደቂቀ አስጢፋኖስ" "በሕግ አምላክ" በሚል ርዕስ በተተረጐመ አስደንጋጭ መጽሐፍ ቀዳሚው ቃል በሚል ርዕስ ሥር፡-

> *የደቂቀ አስጢፋኖስ ሰቆቃ ያስደነግጣል፣ ያሳዝናል፣ ያስቆጣል፣ የማናውቀውን ራሳችንን እርቃናችንን ያሳየናል። ከስድስት መቶ ዓመታት በኋላም ፍንክች አለማለታችን ውስጣችንን እንድንመረምር ያስገድደናል። ይህን መጽሐፍ ሳነብብ የምዕራባውያን (በእንግሊዝኛ) "ቶርቸር" (የግዕዝ ጸሐፊዎች "ኩነኔ") የሚሉትን ሰውን የማሰቃየት ዘዴ እኛ የፈጠርነው መሰለኝ*[259] ብለዋል።

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ *"ደቂቀ አስጢፋኖስ"* የሚለውን የፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌን መጽሐፍ በዚህ አጋጣሚ እንዲያነብ እየለመንኩ ለተርጓሚው ያለኝን ልባዊ አድናቆትና ክብር መግለጽ እወዳለሁ። ይህን አካሄድ የመጽሐፍ ቅዱሱ ክርስትና የእውነተኛ ቤተ ክርስቲያን አካል አድርገን እንዴት እንቆጥራለን? ይህ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና የጭፍጨፋ ታሪክ በየትኛውም ሚዛን ተቀባይነት የለውም። ስለ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የሚጽፉ የታሪክ ጸሐፊዎች ይህን እውነት መዝለል የለባቸውም። መጽሐፍ ቅዱሳችን እግዚአብሔር እንደ ልበ ያለውን ንጉሥ ዳዊት ቅንነቱን፣ መልካምነቱንና ፊርሃ እግዚአብሔር እንደነበረው ብቻ ሳይሆን በክፋትና በተንኮል እንዴት ኦሪዮንን አስገድሎ ሚስቱን እንደቀማ ሳያስባብስ መናገሩ ሚዛናዊነቱንና አስተማሪነቱን ያመለክታል። ኢትዮጵያ ሚዛናዊ ታሪክ ጸሐፊ ያስፈልጋታል።

የውዳሴ ታሪክ አጻጻፍ ስልት የሚከተሉ አብዛኛው ቆየት ያሉ የአገራችን የታሪክ ጸሐፊዎች ገለባውን ከፍሬው ለይተው ስላላቀረቡልን የረሻም ዘመን የአገራችንንም የሆነ የክርስትናችን ትክክለኛ ታሪክ ለማወቅ አስቸጋሪ ሆኗል። ከዚህም የተነሳ ከአምስት ምዕተ ዓመታት በፊት በአበ እምነቶች ላይ በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የተፈጸመው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና ኢሰብዓዊ ታሪክ ምዕራባውያን ለዘመናት ሲያነቡ ፕሮፌሰር ጌታቸው በቅርበት እርምጃ እስከወሰዱ ድረስ የእኛ ታሪክ ለእኛ ባዕድ ነበር። ይህ መጽሐፍ ወደ አማርኛ በመተርጉሙ እጅግ የተበሳጨ እንዳለ ይታወቃሉ። ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ *"ዐጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ" (ገጽ1)* በሚል መጽሐፋቸው ስለ አገራችን የታሪክ ጸሐፊዎች ችግር ሲናገሩ፡- *"ለእውነት መፍረድም ትተው በአድሎአ ልባቸውን ያጠባሉ፤ አጻጻፋቸውም ድብልቅልቅ እየሆነ ለአንባቢው ለይገባም"* ብለዋል። በጣም የሚያሳዝነው የውዳሴ የታሪክ አጻጻፍ ስልት የደብተራዎች ብቻ ሳይሆን በከፍተኛ የትምህርት ደረጃ በደረሱት አንዳንድ ምሁራን ላይ በዘመናችንም መንጸባረቁ ነው። ታቦር ዋሚ *"የውገና ድርሰቶችና የታሪክ እውነቶች"* በሚለው መጽሐፍ፡-

> *በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ሁለት በጣም የሚያሳዝኑ እንቆቅልሾችን እንመለከታለን። አንደኛው በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች እስከ ፕሮፌሰርነት ደረጃ ደርሰው በአሁኑ ጊዜ ግን ወደ ታሪክ ጥናት ያዘነበሉና ከጥንቱ ተረታ ተረት ሰንዝር እንኳ ፈቀቅ ያለ አስተሳሰብ*

[259] *ጌታቸው ኃይሌ (ፕሮፌሰር፣ተርጓሚ) (1996)፣ ደቂቀ አስጢፋኖስ 13*

የማያቀርቡ፣ ሁለተኛው ደግሞ የታሪክ ምሁራን ሆነው ስለ አገራችን ሕዝቦች ታሪክ በራሳቸው ዕውቀት በተማሩት ሳይንሳዊ የታሪክ አጻጻፍ ዘዴ ጥናት አካሂደው በመረጃ የተደገፈ የሕዝብ ታሪክ እንደማቅረብ ፈንታ የጥንቱን የደብተራዎችን በተሰምራት የተሞላ ተረታ ተረት እንደ ማስረጃ እየወሰዱ ከዱሮ በባሰ ሁኔታ የአገራችንን ሕዝብ ማወናበድ ላይ የሚገኙ ናቸው።[260] ብሏል።

በአገራችን ባሉት ዩኒቨርሲቲዎች የኢትዮጵያ ታሪክ መማርና ማስተማርም በጣም አስቸጋሪ እየሆነ እንደመጣና *"ይህ ሚዛናዊ ታሪክ አይደለም" "የሚያወራው ስለ አንድ ዓይነት ሕዝብና ባሕል ነው"* የሚል አከራካሪ ጉዳይ ከመፈጠሩ አልፎ የታሪክ ክፍል እንደሚገባው ተማሪዎች እንደሌሉት ይነገራል። በገጠሮች መገሳና ፈቃድ ላይ ተመስርቶ የተጻፈ አብዛኛው የአገራችን ታሪክ በጠያቂ ትውልድ ፊት ቅቡልነት ያገኘ አይመስልም። የተሠራው ሥራ በራሱ ጠቃሚነቱ ባያጠያይቅም በምክንያታዊነትና ሁሉንም ባካተተ መልኩ ሚዛናዊ ሆኖ ባለመዘጋጀቱ የተሻለና ሁሉንም ያካተተ፣ በመረጃ የዳበረ፣ የታሪክን ሳይንስ የተከተለ፣ ከተረት ተረት የጸዳና የደብተራዎች ወሬ ያልገባበት በተሻለ ዘመን ያሉ የታሪክ ሊቃውንቶች ይህን የተፈጠረውን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም አዲስ የኢትዮጵያን ታሪክ ያቀብሉናል ብዬ ተስፋ አደረጋለሁ። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ክፍል ምሥረታ 50ኛ ዓመቱን ምክንያት በማድረግ የካቲት 21 እና 25 ቀን 2006 ዓ.ም ባሰናዳው ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ 25 የጥናት ወረቀቶች የቀረቡ ሲሆን የታሪክ ክፍል የመዘጋት ስጋት እያንገበገበበት እንደሆነ ተገልጸዋል። በወይይት ከቀረቡት አሳቦች መካከል፦

ባለሙያ ባልሆኑት ብቻ ሳይሆን በታሪክ ባለሙያዎች ተጽፈው በቀረቡ መጻሕፍትም መረጃን የማጣረስ፣ የሚጋነንና የአንዱን ታሪክ ለሌላው የመስጠት ሁኔታ በአገራችን የታሪክ ጥናት ላይ ትልቅ አደጋ እንዳመጣ ተገልጸዋል።[261]

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከዚህ በፊት የዚህችን ታላቅ አገር ታሪክ ለመጻፍ የጣሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዝናን ያተረፉ የታሪክ ሊቃውንት እንዳፈራ የሚታወቅ ነው። ለእነዚያ ታላቅ የአገራችን የታሪክ ምሁራን ሥራዎች ትልቅ አክብሮትና አድናቆት ይገባቸዋል። ከእንግዲህም በመላምት፣ በተረት ተረት፣ በደብተራዎች ወሬ ግራ ያልተጋቡ፣ የተለየ ሕዝብና ባሕል ወገንተኝነት የማይንፀባረቅባቸው፣ ገለባውን ከፍሬው የመለየት አቅም ያላቸው፣ በመረጃ የተደገፈ፣ ሳይንሳዊና ዘመናዊ የታሪክ አጻጻፍን ስልትን የተከተለ ሚዛናዊ የአገራችንን ታሪክ እንደገና የሚጽፉ የታሪክ ምሁራን እግዚአብሔር ጉልበታቸውን እንዲያጠነክር ጸሎቴ ነው። ታሪክ የሌለው ሕዝብ በዘመኑ የሚበልጥ ታሪክ መሥራት አይችልም። እውነተኛ ታሪክ የአንድ አገር ትልቅ ሀብት ነው።

[260] ታቦር ዋሚ (2006 ዓ.ም)፣ *የውገና ድርሰቶችና የታሪክ አውነቶች* ገጽ 619
[261] አዲስ አድማስ፣ መጋቢት 6 ቀን 2006 ዓ.ም ገጽ 20

ታሪክ እውነትነት ከሌለው ደግሞ ታሪክ ሳይሆን ተራ ተረት ነው። ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት በዚህች ምድር ለዘመናት አብረው ስለገዙ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አካባቢም ያለው የታሪክ ተአምነት የሚገድለው፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር የምጣረሱ፣ ከቃሉ ይልቅ ገድላትና ትውፊት የገነነበት ተረት ይበዛል። ይህም እንደገና መጻፍ ሳያስፈልግ ይቀራል?

ሚስቶቹና ቁባቶቹ[262]

አንዳንድ ምሁራን ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በክርስትና ስም ይህን ዘግናኝ ጭፍጨፋ በገዛ ሕዝቡ ላይ ይፈጽም እንጂ ለራሱም በእግዚአብሔር ቃል በፍጹም የማይኖር ሰው እንደነበር ይናገራሉ። የሚገርመው እስከ ዛሬ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን አንዳንዶች ከእግዚአብሔር የተላከ ታላቅ "የእምነት ሐዋርያ" አድርገው መቁጠራቸው ነው። መቁጠሩ ባልከፋ፤ ለመሆኑ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በየትኛው የእግዚአብሔር ቃል ሚዛን ነው "የእምነት ሐዋርያነት" ቦታ የተሰጣቸው? ምሁራኑ የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ክርስትናን ጥያቄ ውስጥ ከሚያስገቡበት ነጥቦች መካከል የሚስቱን የኢቴጌጉን ዜላ አባት (አማቹን) ገራድ ምሕማድንና ቤተሰቦቹን ክርስቲያን ማድረግ ያለመቻሉን፤ በብዙ ሚስቶችና ቁባቶች መከበቡን፡ እንደ ማስረጃ ይጠቅሳሉ።

1. *ዣን ኃይላ ፍሬማርያም (ግራ ባልቲሐት)*
2. *እሌኒ (ቀኝ ባልቲሐት)*
3. *ጽዮን ምገላ የተባሉ "ሕጋዊ" ሚስቶችና ሌሎች ስማቸውና ቁጥራቸው ያልታወቀ ቁባቶች እንደነበሩት ተክለ ጻድቅ መኩሪያ በመጽሐፋቸው ጠቅሰዋል።[263]*

ጋብቻ በመጽሐፍ ቅዱስ በብሉይና በአዲስ ኪዳን ግልጽ አስተምህሮ ያለው ትልቅ መለኮታዊ ተቋም ነው። አዳምና ሔዋን የመጀመሪያ ባልና ሚስት ሆነው አብረው እንዲኖሩ እግዚአብሔር ሲያጣምራቸው፡- *"ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ"(ዘፍ.2:34)* በማለት የባልና የሚስት አንድነት አውጇል። በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያንም ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሚፈፀም ሥርዓት እንደሆነ ቃሉ ይናገራል። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ኤጲስ ቆጶስነት መመዘኛ ሲያስቀምጥ *"የአንዲት ሚስት ባል ሊሆን ይገባል"(1ጢሞ.3:2)*፣ ስለ ዲያቆንም *"እያንዳንዳቸው የአንዲት ሴት ባሎች ይሁኑ"(1ጢሞ3:12)* እንዲሁም ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌነት የሚበቃ ሰው *"...የማይነቀፍና ያንዲት ሚስት ባል የሚሆን..."(ቲቶ.1:6)*

[262] *የሚስቶቻቸው ስምና የማዕረግ ስምም የአንዷ ንግሥት እሌኒ ቀኝ ባዓልቲት የሁለተኛይቱ ንግሥት ፋሪ ማር ግራ ባዓልቲት የሚል ሲሆን፤ በውስጥ ጦርነት ፖለቲካዊ ግጭቱን ለማብረድና ጦርነቱን ለማቆም ሲሉም ማንም ያልሄደበትን መንገድ ተጉዘው በአዲስ ስልት በመጠቀም ከመሲሊም /ከይፋት ወላስማ/ ሴት ልጅ ጋር ጋብቻ ፈጽመው ነበር። ንግሥት እሌኒ ወገን /ቅንዓ ባልቲት/ የወላስማ ዘር ስትሆን ክርስትና አስነስተው ነበር ያባቷ። ፍስሐ ያዜ ካሣ (2003 ዓ.ም)፣ የኢትዮጵያ 5ሺ ዓመታት ታሪክ ከኖኅ እስከ አ.ሀለዴግ፣ መጽሐፍ 1፣ አልፋ አታሚዎች፣ ገጽ 255)*
[263] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ይሱና አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል* ገጽ 168

ብሎ ግልጽ መመሪያ አስቀምጧል። ለኤጲስ ቆጶስነት፣ ለዲያቆንነትና ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌነት ብቻ ሳይሆን የአዲስ ኪዳን ጋብቻ በአንድ ባልና በአንዲት ሚስት መካከል ብቻ እንደሚፈፀም ቃሉ ይደነግጋል፦ *"...ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት"(1ቆሮ.7:2)።* ለእያንዳንዱ ለራሱ *"ሚስቶች"* ለእያንዳንዲቱ ለራስዋ ደግሞ *"ባሎች"* እንዳላለ ልብ እንበል።

ወንድም ሆነ ሴት አንድ ሆነው ከብዙ የተቃራኒ ጾታ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም መጽሐፍ ቅዱስ *"ዝሙት"* እንደሆነ ይናገራል። "ከዝሙት ሽሹ" (1ቆሮ.6:18) ተብለናል። ሐዋርያው ጳውሎስ በገላትያ 5: 19-21 ላይ የሥጋ ሥራ የተገለጠ ነው ብሎ ከዘረዘራቸው 17 የኃጢአት ዓይነቶች መጀመሪያ የጠቀሰው "ዝሙት"ን ነው። በመጨረሻም *"...እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም"(ገላ.5:21)* ብሏል። በኢትዮጵያ የአብያተ ክርስቲያናት እናት የሆነች የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም የአንድ ወንድና የአንዲት ሴት ጋብቻ ለዘመናት ሲታስተምር ቆይታለች። በደንቢም ቁባት ማኖር የተከለከለ መሆኑን በግልጽ ደንግጋለች፦ *"ዕቁባት ማኖርስ በተቀደሰች ሕጋችን ውስጥ የተከለከለ ነው" (አን.25/964)* እንዲሁም *"አንድ ሰውስ እንኳ በቤቱ ከዕቁባቱ ጋራ ይኖር ዘንድ ሥልጣን አይኑረው፣ በእርሱና በዘማውያን መካከል ልዩነት የለም" (አን.25/966)* የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የደነገገችው ግልጽ ውስጠ ደንብ ዘርዓ ያዕቆብን መያዝ አልቻለም።

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ለሃይማኖቱ ቀናኢ፣ ለእግዚአብሔር ቃልና ለቤተ ክርስቲያን ታዛዥ እንደነበር የሚመሰክርለት በጋብቻ ጉዳይ የእግዚአብሔርን ቃልና የኦርቶዶክስን ሥርዓት በገሃድ በመተላለፍ በሦስት ሚስቶችና በብዙ ቁባቶች ተከቦ የኖረና በታሪክ ስለዚህ መተላለፉ ንስሐ እንደገባ ምንም ያልተነገረት ሰው መንፈሳዊ እንደሆነ መቁጠር የአንድን ሰው መንፈሳዊነት ለመመዘን ከቃሉ ውጪ አገራዊ ሚዛን እንዳለን ያመለክታል። ክርስትና ለነገሥታት፣ ለጳጳሳት፣ ለምሁራን፣ ወዘተ...ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የተለየ ስውር መመሪያ የለውም። መጽሐፍ ቅዱስ ባል ለሚስት ሊኖረው ስለሚገባው ሲናገር፦

> *"ባሎች ሆይ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ...እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደ ገዛ ሥጋቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዱአቸው ይገባቸዋል። የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል፣...እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት፣" (ኤፌ.5:21-33) "ባሎች ሆይ ሚስቶቻችሁን ውደዱ መራራም አትሁኑባቸው" (ቈላ.3:19)።*

ለሚሉ ቃሎች ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ቦታ እንዳልነበረው የሚያመለክተው ከሚስቶቹ መካከል ጽዮን ሞግሳን ለዙፋኑ ስለሠጋ አስደብድቦ እንዳስገደላት በታሪክ መዘገቡ ነው። ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ቃልና ከሃይማኖቱ ይልቅ ለሥልጣኑ ቀናኢ መሆኑን የምናውቀው ሚስቱን ጽዮን ሞግሳን ***"አንቺ እኔ በመንግሥቴ ሳለሁ ልጅሽን እንዲነግሥልሽ በየአድባራቱ ከአሉት ቅዱሳን ጋር ተላልከሻል"*** በማለት በጅራፍ አስገርፎ በዱላ አስደብድቦ በማስገደሉ ነው። ***"ንጉሡ ተናደው እንዲገረፉና እንዲደበደቡ አዘዙና ከዚህ ግርፋትና ከድብደባው የተነሣ ታመው ሲኖሩ ከብዙ ቀን በኋላ ሞቱ"***[264] ይላል። ለሥልጣኑ ብሎ ሚስቱን አስደብድቦ[265] ያስገደለ "ጀግና" በሃይማኖት ሽፋን አበ እምነቶችን ቢገድል አያስደንቅም።

ዘርዓ ያዕቆብ ለሥልጣን ብሎ ሚስቱን ብቻ ሳይሆን ወደ ዙፋን ሲወጣ ነገ ይቀናቀኑኛል ብሎ የፈራቸውን የገዛ ወንድሞቹን ፈጅቷል።[266] ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የምንኩስናን ቆቡን ጥሎ በመንገዱ ላይ የቆሙትን ገድሎ በማስወገድ ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ ቃሉንና ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍልስፍናን አንድ ላይ በመቀየጥ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያንን አንድ ላይ አቆራኝቶ ለመንዳት ጥረት ያደረገ ሲሆን በአብዛኛው ያፈራው መራራ ፍሬዎችን ነው። *"ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ"* (ማቴ.7:16)። በክርስቶስ ቤዛነትና በእውነተኛ አምላክ ላይ ባለው እምነቱ ሳይሆን እንደ አምላክ ስግደት ለሚፈልገው፣ የእግዚአብሔርን ቃል ለጣለና ያለቅጥ በሃይማኖቱ ለሚመካ ሃይማኖተኛ ከዚህ በላይ አይጠበቅምና። ከዛሬ 134 ዓመት በፊት በዐፄ ዮሐንስ 4ኛ ዘመን በቦሩ ሜዳ በ1870 ዓ.ም *"ማርያም ከልጇ ጋር መመሰክ አለባት"* የሚለውን የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ *"ስህተት ነው፤ ክሂደት ነው ተብሎ ተወግዞ እንደ ነበር"* ድርሳናት *ዘግበዋል።*[267]

---

[264] *ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ ግራኝ አህመድ ወረራ ገጽ 120*

[265] ስለ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በእንግሊዝኛ የተጻፈ እንዳለ ቀርቧል፦ Zara Yaqob "Seed of Jacob," modern *zer'a yā'iqōb*) (1399–1468) In his later years, became more despotic. When Takla Hawariat, abbot of Dabra Libanos, criticized Yaqob's beatings and murder of men, the emperor had the abbot himself beaten and imprisoned, where he died after few months. Zara Yaqob was convinced of a plot against him in 1453, which led to more brutal actions. He increasingly became convinced that his wife and children were plotting against him, and had several of them beaten. Seyon Morgasa, the mother of the future emperor Baeda Maryam I, died from this mistreatment in 1462, which led to a complete break between son and father. Eventually relations between the two were repaired, and Zara Yaqob publicly designated Baeda Maryam as his successor. *http://en.wikipedia.org/wiki/Zara_Yaqob "He encouraged translations of religious works, and even of occult literature, which was introduced into Ethiopia during his reign."Tsehai Berhane Selassie* http ://www.dacb.org/stories/ethiopia/zarea_yaeqob.html

[266] *ሮራ ቁ. 18 ገጽ፣ 25-25*

[267] *ጸሐፌ ትዕዛዝ ገ/ሥላሴ:: ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ሚኒሊክ ንኒዘኢትዮጵያ/አ ገጽ 92*

ለአባቶች ምክር ቦታ አልነበረውም

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ አባቶችን የሚያከብረውና የሚሰማው እርሱን ሲሰሙት ብቻ እንደ ሆነ ይነገራል። ለምሳሌ፦ አንዱ ንጉሡ ይመለከት በነበረው የፈረስ ጉግስ አንድ ደሃ ገበሬ ተረግጦ ሲገደል ዝም ብለው በደስታ መመልከታቸውን ያስተዋሉ በቦታው የነበሩ አቡነ ተክለ ሐዋርያት ስላላስቻላቸው ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን ስለ ዝምታቸው በድፍረት ገሠጹ። ንጉሡም *"የተቀባውን እንዴት ትደፍራለህ?"* በማለት ዓለም በቃኝ ገድንድ ውስጥ እንዳሠራቸውና በመጨረሻም ወደ ሲዳሞ እንዳጋዛቸው ታሪክ ያወሳል።[268] መጽሐፉ *"ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላቸሁ" (ማቴ 7:16)* እንዳለው የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ፍሬዎች ስለማንነቱ ምን ያሳውቁን ይሆን? ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ሰዎችን ያስገደለው ለራሱ ስምና ሥልጣን ወይስ ለእግዚአብሔር ክብር? ፍርዱን ለአንባቢያን።

> *አንድ ሰው ለሰይጣን መስዋዕት ሲያቀርብ ስታየው በጦር ወይም በዘንግ (በምርኩዝ) አልያም በድንጋይ ግደለው*[269] ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ

መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አያስተምርም። በነቢያት፣ በኢየሱስ፣ በሐዋርያት፣ በጥንት የቤተ ክርስቲያን አበውና በእኛም ዘመን ሰይጣንን የሚያመልኩ ነበሩ ዛሬም አሉ። የፍቅርን ወንጌል ለእነሱ በመስበክ እንጂ በጦር፣ በዘንግና በድንጋይ እንድንገድላቸው መጽሐፍ ቅዱስ በፍጹም አያስተምርም። ይህ የኢየሱስ ሳይሆን የዘርዓ ያዕቆብ "ወንጌል" ነው። ኢየሱስ ለሐዋርያት ሲናገር፦ *"ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙአችሁንም መርቁ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፣ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፣ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናብን ያዘንባልና"(ማቴ.5:43-48)*። ኢየሱስ ሰዎችን ለማዳን ከሰማይ ወደ ምድር ወርዶ ሞቶ እኛ ሰዎችን እንዲንገድል አልላከንም። ማዳን የኢየሱስ አጀንዳ ሲሆን መግደልና ማጥፋት የሰይጣን አጀንዳ ነው። (ዮሐ.10፡10)። ማንም በክርስትና ስም ሰውን የመግደል ሀቡዕ አጀንዳ የሚያራምድ ከሆነ ምናልባት ስሙ ቅብዓ ቅዱስ ሊሆን ቢችልም በምግባሩ የኢየሱስ ሳይሆን የሰይጣን ደቀ መዝሙር ነው።

ገዳዮቹን በዘንግና በድንጋይ ሳይሆን በአፉ ቃል ማጥፋት እየቻለ እንዲህ ብሎ ማለደላቸው፦ *"አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ"(ሉቃ.23:34)* እንጂ የዛቻ ቃል እንኳ አልተናገረም። ታዲያ ዘርዓ

[268] ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ደቂቀ አስጢፋኖስ ገጽ 245
[269] Church and State in Ethiopia , p.240

ያዕቆብ ሰው ለሰይጣን መስዋዕት ሲያቀርብ ስታየው በጦር ወይም በዘንግ (በምርኩዝ) አልያም በድንጋይ ግደለው የሚለውን ከየት አመጣው?

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብና ቤተ ክርስቲያን

የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን እውነተኛና ሙሉ ታሪክ ለመጻፍ አንዳንድ ጸሐፊዎች ዝምታን ወይም በእውነተኛ ታሪክ ላይ መዋሸትን ለምን እንደመረጡ ግልጽ አይደለም። *"ስግደት ለፈጣሪ እንጂ ለፍጡር አይደለም"* የሚል ቁልፍና መሠረታዊ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት የአባ እስጢፋኖስ ጥያቄ ዛሬም በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያን አፋጣኝ መልስ የሚሻ አንዱ የተሐድሶ ጥያቄ ነው። በወቅቱ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ንጉሡ በአገልጋዮቿ ላይ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና ኢሰብዓዊ የጭካኔ ግድያ በሃይማኖት ስም ሲፈፀምባቸው የት ነበረች? በእግዚአብሔር ቃል ፍጹም የተወገዘ ሰውን የመግደል ኃጢአት በእግዚአብሔር ስም ሲፈጸም ቤተ ክርስቲያን ድርጊቱን ለምን አላወገዘችም? እንደ ግርማ ዘውዱ "ኢትዮጵያ" መጽሐፍ ከሆነ በአባ እስጢፋኖስና በተከታዮቻቸው ግድያ የቤተ ክርስቲያን እጅ እንደ ነበር እንዲህ ብሏል፦

> *ከእኛ እምነትና አስተሳሰብ ጋር አይሄዱም። ለንጉሡ፣ ለማርያም፣ ለሥዕልና ለመስቀል አይሰግዱምና ይጥፉ። በማለት ከነገሥታት ጋር እጅና ጓንት በመሆን ውሳኔውን ታፀድቅ ነበር።*[270]

ለነገሩ በመካከለኛ ክፍለ ዘመን በተለይ በዐፄዎቹ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የቤተ መንግሥት የፖለቲካ መሣሪያ እንደሆነች የታወቀ ሲሆን ቄሶች ዘውድ ያልደፉ ነገሥታት ነበሩ። ስለዚህም የታሪክ ሊቅ ዶክተር ላጵሶ ጌድሌቦ ፦

> *የዘመኑ የታሪክ መረጃና ትምህርት በስፋት እንደሚያመለክተው፣ ከትምህርትና ከተግባር አኳያ፣ ሃይማኖቶቹ በአንድ በኩል ለተጠቀሱት መንግሥትና ነገሥታት ፍጹም የፖለቲካ መሣሪያዎች እና አገልጋዮች ነበሩ*[271] ብለዋል።

ታሪካዊ እውነቱ ይህ ከሆነ በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብና በአባ እስጢፋኖስ ጉዳይ የቤተ ክርስቲያንን አቋም መጠየቅ *"አንበሳው ይሻው! ዱካው የት ነው?"* ብሎ እንደመጠየቅ ይቆጠራል። የተለያዩ መዛግብት ሳገላብጥ ያገኘሁት ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በአባ እስጢፋኖስና በተከታዮቹ ላይ ባደረገው ግድያ የቤተ ክርስቲያን እጅ እንዳለበት የሚያመለክቱ ተጨማሪ መረጃዎችን እንመልከት፦

> *ንጉሡ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የእግዚአብሔርን ሥራ የሚሠራ በማስመሰል የራሱን ሥርዓት ሲያቆም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጉዳዩን ሳያውቁት ቀርተው ሳይሆን በሥልጣን ፍለጋና በአድርባይነት እንዲሁም በቅናት በአስጢፋኖስ ትምህርት ተከታዮች ላይ "ፀረ ማርያም፣ ፀረ መንግሥት...ናቸው" በማለት ለፖለቲካ ሥልጣኑ ሲል ንጉሡ ሲፈጃቸው ተባባሪዎች ሆኑ። ...ይሻውም ንጉሡ ማንኛውም ዓይነት ቅጣት ሲበይን አነርሱ እንዲያውቁትና እንዲስማሙበት ያደርግ ነበር። ከቤተ ክርስቲያን*

[270] ኢትዮጵያ 1985 ዓ.ም ገጽ 177
[271] ላጵሶ ጌድሌቦ (ረዳት የታሪክ ፕሮፌሰር)(1999 ዓ.ም)፣ የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች፣ (አራተኛ መጽሐፍ)፣ ገጽ 45

መሪዎች ውስጥ አንድም ሰው ሁኔታው እንዲገታና በመንፈሳዊ ጉባዔ፣ በፀሎት ወይም በውይይት መፍትሔ እንዲያገኝ ያደረገ የለም።[272] አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህን ሁሉ ግፍና ግድያ በክርስቲያን ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ላይ ሲፈጸም ንጉሡ የጽድቅ ሥራ እንደሠሩ በመቁጠር ስለእርሱ የውዳሴ ድርሰት መጻፍና ማደፋፈር ጀምሩ። ንጉሡም ጊዜና ሁኔታው አመቺ ሆኖ ስላገኘው በሚያደርገው የግፍ ሥራ የልብ ልብ ተሰማው እንጂ ፈጽሞ አልተጸጸተም።[273]

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የራሱን ውሳኔ በቤተ ክርስቲያን እጅ ያስፈጽም እንደነበር "ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ" በሚል ርዕስ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፈቃድ ለሕትመት እንደበቃ በሚናገረው መጽሐፍ እንዲህ ይላል፣

የዚያን ጊዜ አባ ማቲዎስ ከሚባል ከአስከንድርያ ሊቀ ጳጳስ ዘንድ የተላኩ መልዕክተኞች በኢትዮጵያ ነበሩ። እነርሱም ሦስት ናቸው።... ንጉሡም (ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ) ከአስከንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ከግብጽ ተልከው ለመጡት መልዕክተኞች ለእግዝአትን ማርያምና ለልጅዋ መስቀል አንሰግድም ያሉ ወንጀለኞች ናቸው ብሰው እንዲፈርዱባቸው አዘዛቸው። እነርሱም በነፍስ በሥጋ ድንግል ለሾነችው ማርያምና ለልጅዋ መስቀል አንሰግድም ያሉት በድንጋይ እንዲወግሩ ፈረዱባቸው። የአፍርንጊና (ፈረንጆች ለማለት ነው) የቁስጥንጥንያ ሰዎችም ከንባኤው ጋር ተባብረው በድንጋዮች ሊወገሩ ይገባል ብለው ፈረዱባቸው። ፍርዱም ባለቀ ጊዜ ንጉሡ በድንጋዮች ወግረው እንዲደበድቡ አዘዘና በየካቲት ወር በ2ኛው ቀን ዓርብ ዕለት በድንጋዮች ወግረው ገድሏቸው።[274]

ምንም እንኳን ይህ ስህተት ከተፈፀመ ከአምስት ምዕተ ዓመት በላይ ቢያልፍም በዚህች ምድር የፈሰሰው የንፁሃን አባቶች ደም ወደ እግዚአብሔር ዛሬም ይጮኻል። ሚጆቹና የግድያው ዋና ደራሲ የነበረው ዘርዓ ያዕቆብና ግብረ አበሮቹ ሞተዋል። ታሪክ ግን ዛሬም ሕያው ነው። ቤተ ክርስቲያን ከዘርዓ ያዕቆብ ጋር በማበር በቀደምት የእምነት አባቶች ላይ ለተፈመፀው ዘግናኝ ግድያ ግልጽ ይቅርታ መጠየቅ አለባት። ይቅርታን መጠየቅ የትንሽነት ሳይሆን የትልቅነት ምልክት ነው። እኛም እንደዚህች አገር ዜጋ ስለ ምድራችን በእግዚአብሔር ፊት በንስሐ በመውደቅ ይቅርታ መጠየቅ ይገባናል። እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይፈውሳት።

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጻድቅ አባት መባል

በታሪክ በብዙ ሚሊዮን ለሚገመቱ ራሽያውያን እልቂት ምክንያት እንደሆኑ የሚነገርላቸው ጆሴፍ ስታሊን በዘመኑ የሰላም ኖቤል እጩ ተደርገው እንደቀረቡ ያነበብኩት ታሪክ ትዝ ይለኛል። ግን በምን መስፈርት? መልካም ሥራዎቹ እንዳሉ ሆነው ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በሃይማኖት ስም የተሐድሶ ጥያቄ

[272] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 88
[273] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 89
[274] ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዶ፣ 1996 ዓ.ም ገጽ 32

ይዘው የተነሡትን የኦርቶዶክስ አባቶችን በዘግናኝ ሁኔታ ቢያስጨፈጭፍም ልዩ ቦታ ተሰጥቶት እንደሚዘከርለት የታወቀ ነው። ግን በምን መስፈርት? የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ምሩቃን የሆኑ ቀሲስ ደረጀና ደቀ-መዝሙር በላ "ቤተ መቅደስ የገቡ መናፍቃን" በሚል ርዕስ በጥምረት ባሳተሙት መጽሐፍ፡-

እኒሁን ጻድቅ አባት ቆዳቸውን ገፍፎ በሰቃይ የገደለና የአርሳቸው ደቀ-መዛሙርት የነበሩትን ከ300 በላይ የገዳሙን መነኮሳት በሰይፍና በገደል ውስጥ ከብት በመንዳት የገደሰውን ንጉሥ፣ ጻድቅ በምልጃቸው የሚረዱን ብላ ታቦት ቀርባ ምስል ስላ ታስተምራለች። እኒሁ ጻድቅ የተባሉት ንጉሥ መነኮሳትንና የመጽሐፍ ቅዱስ መምህራንን ከማስጨፍጨፋቸውም በላይ የምንኩስና ቆባቸውን ጥለው ሲነግሡ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት /በተክሊል/ ሁለት ሚስቶችን እንዳገቡ ዜና ገድላቸውም የሆነ የኢትዮጵያ የታሪክ ድርሳናት ያትታሉ። በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያኗ ከወንጌል ጋር የሚስማማ የጋብቻ መመሪያ ከጥንት ጀምሮ የነበራት ሲሆን፣ እኒህ ሰው ግን ይህን ሕግ አፍርሰው/ሚስጢረ-ተክሊል/ ሁለት ሚስት ሲያገቡ ሥርዓቱን መፈጸም አልነበረባትም። ይሁን እንጂ በመቃወም ፋንታ "አንድ ወንድ ለአንድ ሴት" የሚለውን መለኮታዊ ትዕዛዝ ንጉሡ ሊጥሱ ለታጢአታቸው ተባባሪነቷ ሳያንስ "ጻድቅ አባት፣ የኃይማኖታችን ሐዋርያ፣ የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ደንጋጊ ወሳኝ" በማለት ነፍሰ ገዳይን ሰው ቅዱስና ጻድቅ ብላ እስካለንበት ዘመን ድረስ ታቦት ቀርጻ መልክዕ ደርሳ ስታወድስ የመታሰቢያም በዓል ስታከብር ትገኛለች።[275] ብለዋል።

ነገሩ ከላይ እንደተገለጸው ከሆነ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በኢትጵዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንደ ጻድቅ አባትና፣ እንደ ሃይማኖቱ ሐዋርያ እንዲታይ ያደረገው ምን ይሆን? በ1996 ዓ.ም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የትግራይ ምሥራቃዊ ሀገ ስብከት ጽ/ቤት መሉ ፈቃድ፣ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የትግራይ ማስታወቂያና ባሕል ቢሮ እና በትግራይ ባሕል ማኅበር ድጋፍ "ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ" በግዕዝ ትርጉመም ጎን ለጎን በአማርኛ መታተሙ በጣም የዘገየ ቢሆንም ታላቅ እርምጃ ነው። "መምህር ወማኅበር ዘጉንዳጉንዶ ደብረ ገሪዛን ማርያም" ለዚህ ታላቅ ሥራ እግዚአብሔር ይባርካቸው። አሳታሚዎቹ የአባ እስጢፋኖስን ገድል በማድነቅ "ለቅዱሳኑ እስከ ሞት ድረስ የጸኑበትን ረድኤት የሰጠ ቸሩና ለጋስ የሾነው አምላክ ቅዱሳን ለእኛም የማያልቀውን ረድኤቱን እንደሚቸረን እናምናለን።"[276] በማለት ተመሳሳይ የጸጋና ጽናት ዕርዳታ ለአንባቢያን ሁሉ በመመኘት የገዳመ ማስታወሻ የሚለውን አሳብ ይደመድማሉ።

አንድ ጥያቄ በአዕምሮዬ ውስጥ ተፈጠረ፡- ቤተ ክርስቲያን ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና ኢሰብዓዊ ድርጊት በቀደምት የእምነት አበው ላይ የፈጸመውን ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን እንደተባለው "ጻድቅ አባት" ብላ በዓላትን በስሙ ሰይማ እያከበረች ከሆነ በእርሱ ለተገደሉ አባቶች ገድል ዕውቅና በመስጠት እንዴት

[275] ቀሲስ ደረጃና ደቀ-መዝሙር በላ (2000 ዓ.ም.)፣ መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ (መቅድም) ባሕር ዳር፣ በተጨማሪ ተዓምረ ማርያም ምዕራፍ 24 በትንሣኤ ዘጉባኤ የታተመውን ይመልከቱ።
[276] ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዶ፣ 1996ኛ ዓ.ም ገጽ 11

ለሕትመት እንዲበቃ ፈቀደች? ዘርዓ ያዕቆብን እንደ ጻድቅ አባት በእርሱ የጭካኔ ፍርድ የተጨፈጨፉትን ደግሞ እንደ የቀደሙ የቤተ ክርስቲያኒቷ ሰማዕታት ተቀብሎ አንድ ላይ መዘከር ይቻላል ወይ? ቤተ ክርስቲያን የሁለቱን አስተምህሮ በቃሉ በመፈተሽ ያገኘችው ውጤት አለ ወይ? ሁለቱን አንድ ላይ ትክክል ነው ብሎ መያዝ እርስ በርስ የሚጋጭ ሐሳብ አይሆንም ወይ? የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እንደተባለው ከዛሬ ስድስት መቶ ዓመታት ገደማ በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጠንሳሽነት በአባ እስጢፋኖስና በተከታዮቹ ላይ ለተፈፀመው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና ኢሰብዓዊ ጭፍጨፋ እጇን ካስገባችበት ግልጽ ይቅርታ መጠየቅ የለባትም ወይ? ዓለም ካወቀው ከ400 ዓመታት በላይ ለተቆጠረው እኛም በቅርቡ ለማወቅ ለበቃነው አስደንጋጭና ሰቅጣጭ ታሪክ ሁሳችንም በእግዚአብሔር ፊት በወንጌል እውነት ላይ በቆሙት አባቶች ላይ በዚህ ምድር ስለተደረገው ግፍ ንስሐ ልንገባ ይገባል። ኢትዮጵያ እንደ ዕድሜዋ አቅም እንዳይኖራት ውስጧን በልቶ የጨረሰ አንዱ እርግማን በእግዚአብሔር ለዕድገታችንና ለበረከታችን የተሰጠንን፣ ታላቅ የተሐድሶ ራእይ ይዘው የተነሡ አባቶችን *"ለእግዚአብሔርና ለቤተ ክርስቲያን እንቀናለን"* በማለት በጅምላ መጨረሳችን ነው። ምሕረት ለምድራችን! ኢትዮጵያ ታላላቅ ልጆቿን በልታ ተጽዕኖ ፈጣሪ ልጅ አልባ ሆናለች።

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብና ማርያም

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የማርያምን ስም ከኢየሱስ ስም በላይ ለምን አገነነ? በቅዳሴ ጊዜ ካህናት ቆመው ተአምረ ማሪያምን እንደ ወንጌል እንዲያነቡት ለየገዳሙ ልከ፣ *ልጆን ወለተ ማርያም፣ ገብረ ማርያም ብሎ የሠየመ መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳል።(ተአምረ ማርያም፣ 12:41)* በማለት የማርያምን ልጅ ሞትና ትንሣኤ ዋጋ ቢስ አድርጓል።

ከላይ ያለው በዘርዓ ያዕቆብ የተገለጠው ክሂደት በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ የተደረገ አደገኛ የኑፋቄ ትምህርት እንደሆነ ለማመልከት የጠለቀ የነገረ መለኮት ዕውቀት አይጠይቅም። ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ማርያም በፍጹም የማይለውንና ለቃሉ ባዕድ የሆነውን አሳብ በድፍረት ማስተማር ምን አነሳሳው? ከአዳኙ በላይ ለእናቱ ልዩ ትኩረት ለምን ሰጠ? እርሱ ማርያም እያለ በሚጠራትና በጌታችን እናት መካከል ልዩነት ይኖር ይሆን? ዘርዓ ያዕቆብ ለማርያም ልዩ ትኩረት የሰጠበት አንዱ ምክንያት ሊሆን የሚችለው በፕሮፌሰር ጌታቸው መጽሐፍ የተገለጠው አሳብ ይሆን?

> *ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የስለት ልጅ ነበረ። እናቱ የፊተኛው ልጇ ስለሞተባት ያሁኑ ፅንሱ ተወልዶ በጤና ካደገ ለቅድስት ድንግል አመቤታችን አሰጠዋለሁ ብላ ተሰላ እንደነበር ተጽፏል። በአመቤታችን ዕርዳታ በሰላምና በጤና ስለተወለደ ለሷ ሰፍ ያለ ክብር መስጠት ግዴታ የተሰማው ይመስላል።*[277] *ብለዋል።*

[277] *ደቂቀ አስጢፋኖስ፣ ገጽ*

መምህር ጌታቸው በመጽሐፉ ብዙ የአገራችን የኑፋቄ መጻሕፍት ጸሐፊዎች ማርያም ብለው የሰየሟት ከመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናት ጋር የስም መመሳሰል እንጂ አንድ እንዳይደለች ሲገልጽ፣

> *ጸሐፊዎች ማርያም እያሉ የሚጠሯት መጽሐፍ ቅዱስ ስለትህትናዋ ስለቅድስናዋ፣ ስለታማኝነቷ፣ እግዚአብሔርን ስለመፍራቷ የጸሏትን የጌታችንን እናት ማርያም ነች ለማለት አያስደፍርም።*[278] *ዘርዓ ያዕቆብ ወደ ሩቅ ምሥራቅ ሄዶ እንደነበር የታወቀ ነው። አንዳንድ ምሁራን በምድራችን ዛሬ እንደ አሸን የፈሉ የአምልኮ ሰዓላትና ቅርጻቅርጾች ንጉሡ ከዚያ እንዳመጣ ይገልጻሉ። በሩቅ ምሥራቅ ያሉ ኢአማንያን የሚያመልኳትና የሚያጥኑላትን "የሰማይ ንግሥት" የምትባለው ሴት ምሥል ዛሬ በአገራችን በጌታችን እናት ስም አስመስለው ድንግል ማርያም እያሉ የሚሰግዱላትን የሚያጠኑላትን ምስል በመልክና በቅርጽ ተመሳስለው መገኘትን ነው። የሚገርመው የእኖዎችም ሰዎች ይኽን ስዕል "ንግሥት ሰማይ ወምድር" በማለት መጥራታቸው ነው።*[279] *ብሏል።*

አባ እሰጢፋኖስና ተከታዮቹ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ቆመው የተጋፈጡ ሲሆን በደስታ ለወንጌል እውነት ሰማዕት ሆነዋል። ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ክፉ ክሂደቱን በምድራችን ሲዘራ፣ የኑፋቄ ትምህርት ያለ አንዳች ከልካይ ሲያስፋፋ፣ የቀደመ የኦርቶዶክስ የእምነት አባቶችን ደም በከንቱ ያለ ርህራሔ ሲያፈስ፣ አፍቅሮተ ንዋይ ልባቸውን የጋረደና አድርባይ ሥልጣን ፈላጊ ደብተራዎች አጀብ እንደነበረው መዛግብቶች ያወሳሉ። በተቃራኒው፦

> *ዘርዓ ያዕቆብ በገንዘብና በሹመት አባብሎም ኽነ በሥቃይ አስፈራርቶ ከደቂቀ አስጢፋኖስ አንዱን እንኳ ሐሳቡን ለማስለወጥ ባለመቻሉ ተደንቋል!*[280] ይላል።

የኢትዮጵያ አንዱ ያለመባረክ ምክንያት በእግዚአብሔር ስም እንዲህ ያለ ዘግናኝ ጥፋት በዚህ ምድር መደረጉ ብቻ ሳይሆን በዚህ ጉዳይ ላይ በእውነት ንስሐ ያለመግባታችንና አንዳንዶቻችን ለዚህ ለፈጠጠው ኢሰብዓዊና ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ድርጊት ዛሬም ጥብቅና ለመቆም መዳዳታችን ነው። እግዚአብሔር ምሕረትን እንዲያወርድልን ንስሐ እንግባ። የሚገርመው ነገር የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን ዘግናኝ የጭፍጨፋ ድርጊት ዛሬም በደፈናው የሚደግፉና ሥራው ፍጹም እንደነበር የሚሟገቱ ሰዎች መኖራቸው ነው። መምህረ ኪዳነ ማርያም ጌታሁን በመጽሐፉ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን *"ጻድቅና ታላቅ ንጉሥ"*[281] *"ደግ ንጉሥ"*[282] ብሎ ስለጽድቁ ከመሰከረለት በኋላ አንዳች ነውርና የሚያስነቅፍ ነገር በእጁ እንዳልተገኘ ሲመሰክር፦

[278] *መምህር ጌታቸው(ስመ ጥምቀቱ ገብረ ኢየሱስ) (1995 ዓ.ም)፣ገድል ወይስ ገደል? ገጽ 32*
[279] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 47*
[280] *ገድለ አቡነ አስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዲ፣ 1996 ዓ.ም ገጽ 25*
[281] *ኪዳነ ማርያም ጌታሁን (1993 ዓ.ም)፣ ፣ አመቻ ፊልጶስ ምልምል ቅጥረኞች ዐረ ማርያሞች አታወናብዱን፣ ክፍል አንድ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ ገጽ 9*
[282] *ጌታቸው ዓለሙ (ሻምበል)(2001 ዓ.ም) ገጽ 193*

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በዘመነ መንግሥታቸው አስገደዱ፣ አሳደዱ፣ አስገደሉ የሚል ታሪክ አልተጻፈባቸውም፣ እንኳን ዓለም የሚያውቀው ይቅርና አካባቢ የሚያውቀው ነውር ነቀፋ የላቸውም[283] *ብሏል።*

መምህሩ ከአገር ቤት አልፎ ላለፉት 400 ዓመታት ለምዕራቡ ዓለም በቋንቋው ተተርጉሞለት ያነበቡትንና በቅርቡም ፕሮፌሰር ጌታቸው ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ የታተመውን *"ደቂቀ አስጢፋኖስ"* የሚለውን መጽሐፍ አንብቦ ይሆን? ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ስለሠራው መልካም ሥራ መገለሳ የተገባ ሲሆን የእግዚአብሔርን ቃል በመያዝ የእርሱን የኑፋቄ ትምህርት የሞገቱትን አበ እምነቶችን እጅግ ዘግናኝና ኢሰብዓዊ በሆነ ሁኔታ አሰቃይቶ እንደገደላቸው መዘለል የለበትም። ይህን በብዙ መረጃ የተረጋገጠውን እውነት ዓይኔን ግንባር ያድረገው ብሶን ከካድን ለዚህች አገር ዘመን ዘለቅ ችግር ባለመፍትሔዎች አንሆንም። ለመሆኑ የተሐድሶ ባለ ራእዮችን በመግደል የተሐድሶን ሃሳብ መግደል ይቻል ይሆን? የደቂቀ እስጢፋኖስ ጥያቄ ከአራት መቶ ዓመት በኋላ በ21ኛክፍለ ዘመን በምድራችን ላለችው ቤተ ክርስቲያን ዛሬም አውራ ጥያቄ አይደለም ወይ?

ሌሎች ስለ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ምን አሉ?

በኢትዮጵያ የነገሥታት ታሪክ ውስጥ ዘርዓ ያዕቆብ የገዛበት ዘመን (1426-1460 ዓ.ም) አሳፋሪና ዘግናኝ ከሚባሉት ዘመናት አንዱ እንደነበረ አንዳንድ ምሁራን ይገልጻሉ። *ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የነገሠባቸው ሠላሳ አራት ዓመታት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የልቅሶና የዋይታ ጊዜያት ነበሩ ማለት ይቻላል።*[284]

ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ፦

ለምባገነን ነበረ...ወጥ የሆነን ሃይማኖት ለመፍጠር ካለው መነሣሣት የተነሣ ጠማር የሆኑ ሕጎችን በሕዝቡ ላይ ተጠቅሞአል፣[285] *የሃይማኖት ብሔርተኝነትና ፈላጭ ቆራጭ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም በአንድ ላይ በመቀየጥ በሥሩ ያሉትን በማስፈራራት የገዛ*[286]

በማለት ዘርዓ ያዕቆብ የሃይማኖት አሀዳዊነት በአገሪቷ ለማስፈን ጠማር ሕግ በሕዝቡ ላይ የተጠቀመ ፈላጭ ቆራጭ መሪ እንደነበር አስቀምጠዋል። መጽሐፍ ቅዱስ በወንጌል ስብከት እንጂ ማንም በልዩ ሕግና በጉልበት የሰዎችን አቋም እንዲያስለውጥ አያዝም። የክርስትና መሠረት የሆነው ክርስቶስ፣ ከእርሱ የተማሩ ሐዋርያትና የቤተ ክርስቲያን አባቶች ወንጌልን በኃይል አላስፋፉም፣ የሰዎችን ውሳኔ በኃይል አላስቀየሩም።

[283] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 12*
[284] *የአቡነ አስጢፋኖስ፣ የደም ድምፅ!!! ገጽ 29*
[285] Tddesse Tamrat, *Church and State in Ethiopia 1270-1527*(Oxford, 1972), p.240
[286] *Ibid,pp 238-42, 284-85*

እንደዚህም በፋጹም አላስተማሩም። ክርስትናን በሚመለከት ዋና አስተማሪ፣ መካሪ፣ መንገድ አመልካች፣ ሰባኪ የሆነች ቤተ ክርስቲያን በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጉዳይ ለምን ዝምታን መረጠች? መጥምቁ ዮሐንስ ንጉሥ ሄሮድስ የወንድሙን ሚስት ሲቀማ "አይገባህም" የሚል የግሳጼ ድምፁ ከምድረ በዳ በቤተ መንግሥት እንደተሰማ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የፈለገውን ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ሲያስተምርና ቃሉን ይዘው የቆሙትን የእምነት አባቶችን ለክርስትና በመቅናት ሲገድል ይህ አግባብ አይደለም፤ ብላ ለምን አልሞገተችውም? ዲያቆን ጽጌ ስጦታ "ይነጋል" በሚል መጽሐፉ ስለ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ሲገልጽ፦

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ፀረ ወንጌል አቋም በመውሰድ ቤተ ክርስቲያን በሞንቅ አምጣ የወለደቻቸውን እንቁ ልጆቿን ላይቀጡ ቅጣት ቀጣቸው። ቤተ ክርስቲያንንም ልጅ አልባ በማድረግ በምትኩ እርሱን ጨምሮ የአጋንንትን ትምህርት እየደመጡ፣ ከመናፍስት ጋር የሚያቆራኘውን ክፉ ትምህርት ያለ ከልካይ አስገባ። [287]

እንደ ዲያቆን ጽጌ ከሆነ፦

ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ ከሐዋርያት ያልተገኘ ትምህርት በአቀንቃኝ ደብተራዎች ታግዞ ወደ ቤተ ክርስቲያን ያለ ከልካይ በገፍ አስገብቶታል። ይህም በሆነበት ወራት ዳግማዊ እስጢፋኖስ በትግራይ ክፍለ ሀገር ነጥር ያለውን ያልተበረዘውን የሐዋርያትን ትምህርት በማስተማር ጥቂት ከማይባሉ ደቀ መዛሙርት ጋር ወደ መሐል ለማራ ገስገሱ። ከሐዲው ዘርዓ ያዕቆብ ያስተላለፈውንም እንግዳ ትምህርት አወገዙ። ብዙ ምዕመናን ተከተሉ።[288] *ብሏል።*

አንዳንድ የአገራችን ጸሐፊዎች ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ፣ በፖለቲካው ስለተጫወተው አዎንታዊ ሚና፣ ለሥነ ጽሑፍ ዕድገት ያበረከተው አስተዋጽኦና ቤተ ክርስቲያን ማስፋፋቱ ገንቢ እንደነበር በሰፊው ጽፈውለታል። ይህን ማድረጋቸው መልካም ነው። ለዚህም ሊመሰገኑና አክብሮት ሁሉ ሊቸራቸው የተገባ ነው። ነገር ግን በሃይማኖት ስም ምድሪቷን በሰው ደም እንዳጨቀየና የኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ዘር በምድሪቷ እንደዘራ ለትምህርታችን መግለጽ ነበረባቸው።

ስለቤተሰባዊ ሕይወቱና አንዳንድ ድርጊቱ ማጤን ስለ ክርስቶስ፣ ስለ ክርስትና ትምህርትና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የነበረውን መረዳት እንድናውቅ አንዳንድ ፍንጭ ይሰጠናል። የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ታሪክና በክርስትና ስም በምድራችን የፈጸመውን ዘግናኝ ድርጊት እኛን ብቻ ሳይሆን ዓለምን ካነጋገረ ውሎ ሰንብቷል። *"ጀሮ ለራሱ ባዳ ነው"* እንደሚባለው በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የተፈፀመው የሰማዕታት ታሪክ *"ደቂቀ እስጢፋኖስ"* በመባል የሚታወቅ ሲሆን ይህ ታሪክ ከግማሽ ሚሊኒየም በላይ ያስቆጠረ የቆየ ታሪክ

[287] ጽጌ ስጦታ (ዲ.ዮቆን) *(1997 ዓ.ም)፣ይነጋል፣* ገጽ 63
[288] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 59*

ቢሆንም ለብዙ ኢትዮጵያውያን አዲስ ነው። መረጃ መደበቅ በማይቻልበት ባሁኑ ዘመን በመወለዳችን ይህን ለማመን የሚያስቸግር ጉድ ለማወቅ ዕድለኞች አድርጎናል። ይህ በአገራችን ኢትዮጵያ የተደረገው ግፍ የእኛ ታሪክ ለእኛው አዲስ ይሁን እንጂ ከግእዝ መጻሕፍት ወደ ፈረንሳይኛ፣ ወደ ጣሊያንኛ፣ ወደ እንግሊዘኛና ወደ ሌሎቹ የአውሮፓ ቋንቋዎች ተተርጉሞ በምዕራቡ ዓለም መነበብ ከጀመረ ከ400 ዓመታት በላይ እንደሆነ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ጠቅሰዋል። በሃይማኖት ስም በምድራችን የተደረገውን ኢሰብዓዊና ዘግናኝ ድርጊት አውቀን እንድንጠነቀቅ ይህን መጽሐፍ ስላቀበሉን ዳግም ሊመሰገኑ ይገባል።

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ የጅሃድ ባሕሪይ እንዲላበስ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ምንም መሳይ የማይገኝላቸው አስተምህሮዎች በምድሪቷ እንዲንሰራፉ፣ የክርስቶስ ወንጌል በባዶ ሥርዓትና ወግ እንዲጋረድና አገር በእውነት መሳይ ተረት እንድትዋጥ ካደረጉት መሪዎች ቀዳሚ ነው። ዛሬም የወንጌል አገልጋይነት ስም ያላቸው፣ ያለ ዕውቀት እንደ አይሁዶች ለሃይማኖታቸው የሚቀኑ፣ እግዚአብሔርና የአገሩ ሕግ አደብ እንዲገዙ ባያደርጋቸው በወንጌል እውነት የሰውን ልብ ከመማረክ እንደ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በሌላው ላይ ሰይፍ ከማንሣት የማይመለሱ ጥቂቶች አይደሉም። ይህ በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የተዘራ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘር እንደሆነ ከላይ የተመለከትናቸው ጥቅሶቹ በቂ ምስክሮች ናቸው። *"የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ"* የሚለው መጽሐፍ ስለ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ እንዲህ ብሎ ያጠቃልላል፦ *"በአጠቃላይ ዘርዓ ያዕቆብ የፈፀማቸው ተግባራት በክርስቲያኑ ሕዝብ ዘንድ ታላቅ አመኔታንና ተወዳጅነትን ስለፈጠሩ በፖለቲካውም ሆነ በሃይማኖቱ ወገን የአገሪቱን አንድነት ጠብቆ ለመግዛት እንዲችል ስፍ ያለ አሰተዋጽኦ አድርገውለታል"*[289] ዘርዓ ያዕቆብ ለዚህች አገር ዕድገት ምንም አላደርገም የሚል አቋም ባይኖረኝም "አጠቃላይ ተግባሩ በሕዝበ ክርስቲያኑ ዘንድ አመኔታና ተወዳጅነትን ማትረፉ" የተባለው ሐሳብ ከላይ ያለውን ዘግናኝ ታሪክ ለሚያነብ ሚዛናዊ ሰው ሁሉ ጥያቄ ሳይፈጥርበት አይቀርም ብዬ አምናለሁ። ይህ የታሪክ አንዱ ገጽታ ብቻ ሲሆን ሌላው ጸሐፊ ደግሞ፣

> *የጻድቃን የሰማዕታት ምልጃ፣ የሰዕልና የእንጨት ስግደት ጣዖት አምልኮ ነው። ከሌያት ከቅደመ አያቶቻችን ያልተረከብነው ክሂደት ነው ሲሉ ብዙ አባቶቻችን በንጉሥ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ እጅ በሰይፍ የተቀሉ፣ ትዳር ልጆቻቸውን ያጡ፣ ጥረው ግረው ያፈሩትንም ንብረት ለእሳት የገበሩ ከ13ኛው - 15ኛው ክፍለ ዘመን ነበሩ።*[290] ሲሉ

[289] ሱሌ መልእኩ *(1997 ዓ.ም)*፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ ገጽ 96

[290] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ *ከዐፄ ይኩኖ አምላክ - ዐፄ ልብነ ድንግል*፣ *2ኛ መጽሐፍ*፣ ትንሣኤ ማተሚያ ቤት፣ ገጽ 191

ተሲስ ደረጀም በመጽሐፉ፦

> *ዐፄው ከምሥራቃውያን ጉብኝታቸው በኋላ በየቦታው ባመጡት የጣዖት አምልኮ ልማድ የኦርቶዶክሰን "ቤተ ክርስቲያን" ሲያምሷት ከደብተሮቹ በስተቀር ሕዝቡ አምርሮ ተቃውሞ ነበር። ይህ ታሪክ በንጉሡ ዜና ገድል በደቂቀ እስጢፋኖስ፣ በገድለ አንወና በነአባ አበከረዙን ገድላት ተጸፎ ይገኛል*[291] ብሏል።

እንዲሁም ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር በመጽሐፉ፦

> *ገበሬዎች ሳይቀሩ ከደቂቀ እስጢፋኖስ ጋር ለመሞት ራሳቸውን ይሰጡ እንደነበር እንዲህ በማለት ይተርካሉ፣ ንጉሡ የአካባቢው ገዢዎች ደቂቀ እስጢፋኖስን እየያዙ ሲገርፋቸው፣ እድና እግራቸውን ሲቆርጡዋቸው፣ እኛም ከበረከቱ አይለፈን እያሉ በገዛ ፈቃዳቸው ራሳቸውን ለማርፋትና ለሞት እየሰጡ መሥዋዕትነትን የከፈሉ ወንድና ሴት ገበሬዎች ነበሩ*[292] ብሏል።

ንጉሥ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ለአገር አንድነት በተጫወቱት ጉልህ ሚና ሊመሰገን ይገባል። በክርስትና ሃይማኖት ስም ለፈፀመው ዘግናኝ ግድያ በብዙ ጸሐፊዎች ምንም ያለመባሉ የጽሑፋቸውን ተአሚኒነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል። *"የሰማዕታት ደም የቤተ ክርስቲያን ዘር ነው"* ተርቱሊያን እንዳሉት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለተሐድሶ የፈሰሰው የቅዱሳን ደምና የምልጃ እንባ በዘመናችን ማንም ምንም መቋቋም በማይችል ሁኔታ በኢትዮጵያ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ መብቀሉ አይቀሬ ነው።

እግዚአብሔር የዘመናትን የቅዱሳን ምልጃ፣ የፀሎት እንባና ለአያሌ ዘመናት ለተሐድሶ የታሰሩ፣ የተገረፉ፣ የተሰደዱ፣ የተወገዙና የተገደሉ የአባቶችን ደም ዘር የ21ኛ ክፍለ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ በማድረግ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በወንጌል ለዓለም እንድትተርፍ ያደርጋል። የተሐድሶ ብርቱ ተቃዋሚዎች በምድራችን እያሉ ብርቱ ጌታ አልፎ ቤቱን በዘመናችን በቃሉና በመንፈሱ ያድሳል።

አመለካከት በተሻለ አመለካከት እንጂ በሰይፍ አይሸነፍም

በሰይፍ የሚደረግ አመለካከትን የማስለወጥ ዘመቻ ብዙ የአመለካከቱን ጽንፈኞች ይወልዳል። ይህ ትውልድ ያልተበረዘውንና ያልተሸቃቀጠውን የእግዚአብሔርን ቃል በመያዝ፣ ለሌላው ሰው እምነት ቦታ በመስጠት፣ የመቻቻልን ባሕል በማዳበር፣ በልበ ሰፊነት በመደማመጥና በመነጋገር፣ በተሻለና እውነትን መሠረት ባደረገ ብልጫ ባለው አመለካከት እንጂ በሰይፍና በጎራዴ የአመለካከት ልዩነት ለማጥፋት ሊነሣ አይገባም። ይህ አስተሳሰብ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ቦታ የለውም።

[291] ቀሲስ ደረጀ (2003 ዓ.ም)፣ *ገሙና ዘ ፀረ-ዱ*፣ ገጽ 94

[292] ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር፣ *ገጽ 64*

ዶክተር ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ በመጽሐፉ የዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ምን መምሰል እንዳለባት ሲገልጽ፡- *"የ21ኛው ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚሆን መልዕክት ለማኅበረሰቡ ማዘጋጀት ይኖርባታል"*[293] ብሏል። ይህ ማለት ቤተ ክርስቲያን የማይለወጠውን የወንጌል ቃል በተለወጠ መንገድ በፈጣን ለውጥ ውስጥ ለሚገኝ ለዚህ ትውልድ ለማቅረብ የአመለካከት ለውጥ እንደሚያስፈልጋት ያመለክታል። ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ትውልድ በወንጌል ቃል ደራሽ መሆን ብቻ ሳትሆን ተደራሽም መሆን አለባት። ተደራሽና ደራሽ መሆን የምትችለው በተሐድሶ ብቻ ነው።

በሰይፍ የሰዎችን አመለካከት ለመለወጥ መነሣት የተሸናፊነት ምልክት ነው። በእግዚአብሔር ቃል፣ በኢትዮጵያና በዓለም አቀፍ ሕጎችም የተወገዘና የሚያስጠይቅ አካሄድ ነው። የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ኢየሱስ ስለ እምነት በሰይፍ በሰው ላይ ካልዘመተ አንተም በኢየሱስ/ቤተ ክርስቲያን ስም በሌላው ላይ በሰይፍ የመዝመት መብት የለህም። ቃሉም አይደግፍህም። ባለመስማማት ተስማምቶና ተቀባብሎ አብሮ መኖር፣ በአንድ አሳብ መለያየት በሁሉ መለያየት እንዳልሆነ መረዳት፣ የራሳችንን አሳብ ሌላው በኃይል እንዲያስለውጠን እንደማንፈቅድ ሁሉ በሌሎችም ማሰብ የለብንም። የሌሎችን የአሳብ ልዩነት በኃይል ለማስለወጥ መታገል ዛሬ ላይ ሆነን እንደ ዱሮ እያሰብን እንደሆነ ያመለክታል።

> በኢትዮጵያ የምንኖረው አንድ አገር ስላለን እንጂ አንድ ዓይነት አስተሳሰብና አንድ ዓይነት ሃይማኖት ስላለን አይደለም።

አንዲት እናት ለልጆቿ እናት የምትሆነው ስለወለደቻቸው እንጂ እንደ እናታቸው ስለሚያስቡ አይደለም። እንደ እናታቸው እንዲያስቡ አይጠበቅባቸውም። እግዚአብሔር እንኳ የእርሱን ሕግጋት ስንጥስና ከፈቃዱ ውጭ ስንሆን የመንገዱን ፍሬ እንድንበላ ይተወናል፤ እንጂ ፈቃዳችንን ረግጦ በኃይል አይገዛንም። ከክርስቶስም የተማሩና ወንጌልን የሰበኩ ሐዋርያት በተለያየ አሚሚት ስለ ጌታ እንደሞቱ እንጂ የተለየ አስተምህሮና አመለካከት ስላላቸው ብቻ የሌላውን ሰው ምላስ፣ ክንፈር፣ አፍንጫ እንደቆረጡና አንድንም ሰው እንደ ገደሉ አዲስ ኪዳን አያስተምረንም።

•

[293] ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ *(ዶ/ር) (2001 ዓ.ም)፣ ኢትዮጵያውያን በአሜሪካ ማንነታቸውና ሥነ ልቦናዊ ትንተና፣* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ፕሬስ፣ ገጽ 265

ሰይፍ ወደ ሰገባው ይመለስ

የእምነታችን ራስና ፈጻሚ የሆነውን የናዝሬቱን ኢየሱስ የአይሁድ ካህናት፣ አለቆችና የሕዝቡ ሽማግሌዎች ሰይፍና ጉመድ ታጥቀው ሊይዙት በመጡ ጊዜ ጴጥሮስ ሰይፉን መዞ ማልኮስ የተባለ የሊቀ ካህናቱ ባሪያ ቀኝ ጆሮውን እንደቆረጠ ቃሉ ይናገራል(ዮሐ 18፡ 9-11)። ጴጥሮስ ሰይፍና ጉመድ ታጥቀው ክርስቶስን ለመያዝ የመጡትን እንደ አመጣጣቸው ሊመልሳቸው፣ ጌታውን ከገዳዮቹ እጅ በሰይፍ ሊያስጥልና፣ ለጌታ ያለውን ፍቅርና ቅንአት ለመግለጽ በስሜታዊነት ተነድቶ የወሰደው እርምጃ ከኢየሱስ ዘንድ ግሣጼና ብርቱ ተቃውሞ አስከትሎበታል። ኢየሱስም *"ሰይፍን የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ሰገባው መልስ"* ብሎት ጴጥሮስ የቆረጠውን የማልኮስን ጆሮ ፈውሶአል። እግዚአብሔር ሁሉንም በአንዴ ማጥፋት ሲችል ባልንጀራ ባልንጀራውን እንዲያጠፋ ሰይፍና ጎራዴ አስታጥቆ እንደሚልክ አዲስ ኪዳንና እውነተኛ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አያስተምረንም። የአዲስ ኪዳን ዐቢይ መልዕክት ፍቅር ነው። ቃሉ "የሚያሳድዱአችሁን መርቁ" *(ሮሜ12፡14)*። አለ እንጂ ግደሉ አላለም። በሰይፍ ወንድምን ግደሉ ብሎ የሚያስተምር ሳይሆን *"ወንድምን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው፣ ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ ዘንድ እንዳይኖር ታውቃላችሁ"* (1ዮሐ 4፡ 15) ይላል።

> እውነተኛ ክርስቲያናችን ሞቶ ያዳናቸውን ጌታ በመስበክ እንጂ ሌሳውን አጥፍተው እነርሱም እየጠፉ የሚያራምዱት ሃይማኖት የላቸውም። በሃይማኖት ስም ወንድምን መግደል እጅግ የተሳሳተ የባዶ ሃይማኖት ምልክት እንጂ በእግዚአብሔር ላይ እምነቱን ያደረገ ሰው ድርጊት ሊሆን አይችልም።

ዛሬ የአገር መሪዎችንና የተባበሩት መንግሥታትን እንቅልፍ የነሳቸው የሁልጊዜ አጀንዳቸውም በሃይማኖት ስም ያለ እኛ ሌላው ሃይማኖት የተወገዘና በፍጹም መኖር የለበትም የሚሉ አንዳንድ ግለሰቦችና ቡድኖች ለጥፋት መነሳታቸው ነው። በእምነት ጉዳይ ሰይፍ በመጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ጊዜና ሁኔታ የተወገዘ ነው። በሃይማኖት ስም ሰይፍን አማራጭ የሚያደርጉ ሰዎች ዐቢይ ምክንያት በልባቸው ውስጥ የተደበቀ የፍርሃት፣ የተሸናፊነትና የበታችነት መንፈስ መኖሩ ነው። እነዚህ ወገኖች የሰውን ልጆች ሞት በሞቱ ሽሮ በሰይፍ ሳይሆን በወንጌል ስብከት ዓለምን ወደ ራሱ እየጠራ ወዳለው ጌታ መምጣት አለባቸው። በዓለም ላይ ላለው ፈርጀ ብዙ ችግር ሰይፍ ሳይሆን ወንጌል ብቸኛ መልስ ነው።

ማጠቃለያ

ተሐድሶ የቀደምትና የአሁኗ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዐቢይ ርዕሰ ጉዳይ ነው። በብዙዎች ልብ ስለ ተሐድሶ ያለው አመለካከት አሉታዊ ከመሆኑ የተነሣ ብዙ አሳዛኝ ተውሶች በዚህች ምድር እንደተካሄዱ ተመልክተናል። አበው *"ላለፈው ዘረምት ቤት አይሠራም"* እንዳሉት

ስላለፉት ዘመናት ብዙ ያወሳነው ስላለፈው አሳዛኝ ታሪክ ማንንም ለመክሰን ወይም ለመሸለም ሳይሆን ያለፈውን መጥፎ ታሪክ እንዳንደግምና ለአሁኑና ለመጭው ትውልድ እንደ ቤተ ክርስቲያን የእውነተኛ ብርሃንነትና ጨውነት ሚናችንን ለመግለጥ አዲስ ራእይ ይዘን እንድንነሣ ነው። የቤተ ክርስቲያን መሠረት፣ ስብከት፣ መመሪያና መሣሪያ የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል። እውነተኛ ጥያቄዎች እውነተኛ መልስ ማግኘት አለባቸው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የቤሎች አብያተ ክርስቲያናት ቀዳሚ እናት እንደ መሆኗ፣ የረዥም ዕድሜና ሰምንታዊ አሴቶች ባለቤት፣ በዓለማችን በቀዳሚነት ከሚታወቁት አብያተ ክርስቲያናት አንዷ፣ በዚህች ምድር ካሳት የዳበረ ልምድና አቅም የተነሣ አባሎቿ ብቻ ሳይሆኑ ኢትዮጵያውያንና የዓለም ሕዝብ ሁሉ ከእርሷ ብዙ ይጠብቃሉ።

ወንጌልን ማዕከል ያደረገ፣ የእግዚአብሔርን ቃል የበላይነት ያጎላ፣ በነፍሳት ድነት ላይ ያተኮረ፣ አገራዊ አውድን የተላበሰ፣ ከስሜታዊነት የጸዳ እርምጃ፣ ዓለም አቀፋዊ የወንጌል ራእይ የሰነቀ፣ በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላለው ትውልድ የለውጥ፣ የዕድገትና የተሐደሶ አቅጣጫ አመልካች እንድትሆን ስለዚህች የአገር ኩራትና የኢትዮጵያ ታሪክ ማዕከል ለሆነች ቤተ ክርስቲያን ከሚጸልዩላት አንዱ በመሆኔ ራሴን እንደ ዕድለኛ አቆጥራለሁ። እግዚአብሔር ኦርቶዶክስና ኦርቶዶክሳውያንን ይባርክ። በኢትዮጵያ ያሉ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትም በጎያቸው የአየተፈለፈሉ ያሉ አለማዊነት፣ ምድር ተኮር ወንጌል፣ ከአፍቅሮተ ንዋይና አፍቅሮተ ሚመት፣ ከራስ ተኮርነት ወደ ዓለም አቀፍ ሚሲዮናዊነት ለመሻገር የቃሉና የመንፈስ ተሐድሶ ያስፈልጋቸዋል። በቃሉና በመንፈሱ ተሐድሶን ከቤተ ክርስርቲያናችን (የቅዱሳን ጉባኤ) ሳይሆን ከግል ሕይወታችን እንጀምር። ያልተለወጠ ለዋጭ፣ መልዕክት የሌለው መልዕክተኛ፣ ያላየ መስካሪ፣ እግዚአብሔርን በግሉ የማያውቅ ስለ እግዚአብሔር ተከራካሪና የእግዚአብሔር ቃል ደንታ ቢስ ሆነን የአባቶች ወግ ጠባቂ እንዳንሆን እንጠንቀቅ። በቃሉ እንታደስ!

በሚቀጥለው ምዕራፍ በአገራችን ቀዳሚ የአገራችን ምሁር፣ የታሪክ ሊቅ፣ የወንጌል ሰባኪና ደራሲ የነበሩ አለቃ ታዬ የተሐድሶን አሳብ በማንገባቸው የደረሰባቸውን መራር መከራ፣ ስደትና ሰማዕትነት እንመለከታለን። ከአባ እስጢፋኖስና ከተከታዮቹም ሰማዕትነት በኋላ በምድራችን የለውጥ ፍርሃትና አሉታዊ እርምጃ በአለቃ ታዬም ዘመን ያለመለወጡን ያመለክታል። ዝርዝሩን በቀጣይ ምዕራፍ ይመልከቱ።

፬

"የቀደሚ ምሁር" የተሐድሶ ሐሳብ

አለቃ ታዬ ገብረማርያም

/1853 - 1916 ዓ.ም/

አለቃ ታዬ ገብረማርያም በዐፄ ቴዎድሮስ ዘመነ-መንግሥት በበጌምድርና ሰሜን ጠቅላይ ግዛት ከምከም ወረዳ፣ ልዩ ስሙ ግምጃር ሚካኤል በተባለ ሥፍራ ህዳር 21 ቀን 1853 ዓ.ም ተወለዱ። አለቃ ታዬ ገና በሕፃንነታቸው በቤተ ክህነት ትምህርት ሥርዓት ንባብንና ጽሕፈትን ተማሩ። ምጽዋ በሚገኘው በምንኩሉ የሲዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤትም ከአሥር ዓመት በላይ የወንጌልን ቃል እንደተመራመሩ ግለ ታሪካቸው ያወሳል። በትምህርት ቤት በነበራቸው ቆይታ ትጉህ ተማሪ ነበሩ። በወቅቱ የነበሩ ዊንክቨስት እና ኤሚሊ ሉንደል የተባሉ መምህራን እንዳጠኑ፦

ታዬ በባሕላዊ ትውፊቶች በመመሰጣቸው፣ ከምዕራባውያን ትምህርት ይልቅ ለምሥራቁ ቅድሚያ ሲሰጡ ታይተዋል። ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ልዩ ዝንባሌ ነበራቸው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥናት ሰፊ ጊዜ ይሰጣሉ፣ አብዛኛውን ጊዜም እስከ ሌሊቱ ሊጋማሽ ድረስ ከግእዝ መጻሕፍት እያጣቀሱ ይመራመራሉ። በማለት እማኝነታቸውን ሰጥተዋል።[86]

[86] ስለሞን ጥላሁንና ሥምረት ገብረማርያም(*2000 ዓ.ም*)፣ ደማቀቹ፣ ርኖቡት አታሚያች፣ ገጽ 60

ሃይማኖት ሰባኪ፣ የሚራቀቁ ደራሲ፣ የሚመራመሩ ታሪክ ጸሐፊ፣ ስለ ጎሊና ነጻነት ተከራካሪ፣ ከውጭ አገር ተበትነው የነበሩትን የኢትዮጵያ መጻሕፍት ሰብሳቢ ነበሩ። በቤተ መንግሥት የተከበሩትን ያህል በወጎኒ ቤት ማቀዋል። የተወደዱትን ያህል ብዙ ጠላቶችም ተነሥተውባቸዋል።



አለቃ ታዬ ገብረማርያም/1853 - 1916 ዓ.ም/

ምንጭ፡- ጮራ መጽሔት ቁ.40. 2003 ዓ.ም

ተሐድሶ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልስ ያላገኘ ዘመን ተሻጋሪ ጥያቄ እንጂ ሚሲዮናውያንን ተከትሎ የመጣ "መጤ" ጥያቄ አይደለም። ይህ ትውልድ የተሐድሶ ጥያቄ በቃሉ ላይ ቆሞና ከቀደምት አባቶች ተቀብሎ እንጂ በራሱ ፈጥሮ እያስታጋባ አይደለም። የወንጌል መልዕክተኞች ወደ ሀገራችን ሳይመጡና ወንጌላውያን የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት በተለምዶ ፕሮቴስታንት የሚባሉ ሳይመሠረቱ የተሐድሶ ጥያቄ በአገራችን ነበር። ከዛሬ መቶ ዓመት በፊት በቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ/የለውጥ ሀሳብን በገሃድ ካነሡት ፋና ወጊ የአገራችን ምሁራን መካከል አለቃ ታዬ አንዱ ነበሩ። በአርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተምረው ያደጉና በእውነት ላይ ቆመው እውነትን በራስ በመወራረድ አንዳች ሳይፈሩ በገሃድ የገለጡ የእምነት ሐዋርያ እንደነበሩ ቅን ልቦና፣ ሚዛናዊ አዕምሮና የማርን ጣፋጭነት እያወቁ እሬት ነው ለማለት ሕሊናቸው ፈቃድ ለማይሰጣቸው ኢትዮጵያውያን ሁሉ የአደባባይ ምስጢር ነው። በኢትዮጵያ ባለፉት ዘመናት በእውነት ላይ በመቆማቸው ያለ ፍትሕ የሥርዓቱ ሰለባ የሆኑ ኢትዮጵያውያንን ለመቁጠር የሚቻል አይመስለኝም። አንዳንዶች ለዚህች አገር አንድነት፣ ዕድገትና ለውጥ ላበረከቱት መልካም ሥራ ትልቅ አድናቆት የተቸራቸው አሉ ሌሎች ደግሞ ተረስተዋል።

በተከታዩ ዓመት ማለትም በኖቬምበር 1882 ዓ.ም ታዬ ቅኔ ለመቀኘት ፊታቸውን ወደ በጌምድር መለሱ። ምርምራቸውንም ዕውቅና ባላቸው በተለያዩ አድባራትና ገዳማት ካጠናቀቁ በኋላ "አለቃ" የተሰኘውን ከፍተኛ ማዕረግ አገኙ።[87]

> *አለቃ ታዬ ከፊል ትምህርታቸውን ከውጪ አገር መምህራን ዘንድ በመቅሰማቸው፣ አንዳንድ የቤተ ክህነት ሰዎች ተቃውሞ ያነሱባቸውና ያስነሱባቸው ነበር።[88] ፀሐፊ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ እና አቡነ ማቲዎስ ከፍተኛ በደል እንደፈፀሙባቸው የሰሙ ዐፄ ሚኒልክ ባለሟላቸውን (ፀሐፊ ትዕዛዝ) ገብረሥላሴ በእጅጉ ገሰጸዋቸዋል። ለአቡኑም ቢሆን አለቃ ታዬን በማይረባ በማንገላታታቸው ቅሬታቸውን በይፋ ገለጹላቸው።[89]*

ያም ቢሆን ንጉሡ አለቃ ታዬን ከወህኒ፣ ከመከራና ከገዳዮች እጅ ማስጣል አልቻሉም። ይህም በአገራችን የአሳብ ነፃነት በፍጹም እንዳልነበረና እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠውን የአሳብ ልዕልና ቤተ ክርስቲያን በመደፍጠጥ ቀዳሚ እንደነበረች የአለቃ ታዬ መከራና ሞት ተጨባጭ ማስረጃ ነው። ለአለቃ ታዬ ንጉሥ ሊራራላቸው አንዳንድ የቤተክህነት ሰዎችና አቡኑ ለምን ጨከነባቸው? አለቃ ታዬ ይደርስባቸው የነበረውን ተቃውሞና በደል ለንጉሡ በማመልከታቸው ዐፄ ሚኒልክ እንዲህ የሚል ደብዳቤ ጽፈውላቸው ነበር፡-

> *ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ሚኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ አለቃ ታዬ ገብረማርያም የሚባል ሰው ምጽዋ የነበረ ሃይማኖቱን እኛ መርምረነዋልና ማንም አንዳች አይበለው በሃይማኖቱ ነገር።* [90]

ስለ አለቃ ታዬ ካህናት፣ አቡን፣ የንጉሥ ጸሐፊ የነበሩ ወንጌልን በመናገራቸው ቢቃወሟቸውም አንዱም የሚያስተምረው ትምህርት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ በማጣቀስ የረታቸው አንድም ሰው በሕይወት ዘመናቸው እንዳልተገኘ ታሪካቸው ይናገራል። የእግዚአብሔርን ቃል እውነት በመኖር የወንጌልንም ቃል በገሃድ ቢናገሩም ከመከራና ከእስራት ማምለጥ አልቻሉም። የካቲት 25 ቀን 1961 ዓ.ም የአዲስ ዘመን ጋዜጣ *"ምን ሠርተው ታወቁ"* በተሰኘው አምዱ የመረጣቸው ከቀዳሚ የአገራችን ምሁራን መካከል አንዱ አለቃ ታዬ ነበሩ። ስለ እርሳቸው ሲናገር፡-

> *አንደ ዛሬው ኤ.ቢ.ሲ.ዲ. የቆጠረው በመቶ ሺህ ሳይቆጠር፣ ኢትዮጵያዊ ፕሮፌሰርና ዶክተር ሳይገኝ፣ አለቃ ታዬ የዐሥራ ዘጠነኛው ዘመን ኢትዮጵያዊ ምሁር ነበሩ። ሙያቸውና ችሎታቸው በአንድ መሥመር ብቻ የተወሰነ አልነበረም። በአንደበታቸው የሚመስጡና ልብን የሚማርኩ የክርስቲያን*

[87] *ገዢ ከማሁ፣ ገጽ 61*
[88] ፋጹም ወ/ማርያም *(2005 ዓ.ም)፣ ያልተዘመረላቸው፣* ህትመት ፋርኢስት ትሬዲንግ፣ ኃላ. የተ. የግ. ማህበር፣ ገጽ 46
[89] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 67*
[90] *ህዳር 6 ቀን 1891 ዓ.ም በወረኢሉ ከተማ ተጻፈ (ኃይሉ ከበደ (1963 ዓ.ም) ገጽ 3*

ለስዕልና ለመስቀል አይሰግድም፤ በሞቱ ቅዱሳን አማላጅነት ሊያምንም፤ ዝክርና ምዕዋት፣ የሞተ ሰውን ሊያጸድቅ እንደማይችል ይናገራል፤ የልማድ ጸም ዋጋ እንደሌለው ይሰብካል፤ ቀናትን አያከብርም” ስሉ የክሱን ጭብጥ አብራሩ። ገባኤው በክሱ በጭብጥ ላይ በብርቱ ከተወያየ በኋላ አለቃ ታዬን ለወደፊቱ ይህን ትምህርት እንዳያስተምሩ አስጠንቅቀው ቢያሰናብቱም በአለቃ ታዬ መለቀቅ የተበሳጨ ካህናት በወቅቱ ለዐፄ ምኒልክ ባለ ሙሉ ስልጣን እንደ ራሴ ለነበሩ ለራስ ተሰማ በማመልከት ያለ ሕግ ከታላቁ ወጎኒ ቤት እንዲገቡ አደረጉ። ለመሆኑ አለቃ ታዬ ለግዙት የዳረጋቸው *ለሥዕልና ለመስቀል እንድንሰግድ፣ የሞቱ ቅዱሳን እንደምያማልዱ፣ ዝክርና ምጽዋት የሞተን ሰው እንደሚያጸድቁና የልማድ ጸም ዋጋ እንዳለው* በየትኛው መጽሐፍ ቅዱስ ነው የተጻፈው? ከዚህ የሚረዳው አለቃ ታዬ ፍዳን ያዩት በእግዚአብሔር ቃል ላይ ቆመው ነባሩን ልምድ ስለ ሞገቱ ነው።

እኚህ ታላቅ ምሁር በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በቃሉ ብርሃን ጨለማን መግለጥ ሲጀምሩ *“አለቃ ታዬ የሃይማኖት ፀረ ማርያም ነውና አገር መግዛት አይገባውም፤ ፀረ ማርያም አይደለሁም ካለ ሥዕለ ማርያም ይምጣለትና ይስገድ”* ሲባል (ዘጸ.20፡1-6) በመጥቀስ ለሥዕል አልሰግድም ሲሉ ወደ ወህኒ ቢያወርዷቸውም አቋማቸውን እንዲህ ብለው በስንኞች ቋጥረዋል ፡-

“እኔ ለአምላክ እንጂ ለሥዕል አልሰግድም!”

ይከራከሩኛል እየተጋገዙ፣
በከንቱ ላይረቱኝ አምላክን ሳይዙ።
ወህኒ በመግባቴ በጣም ደስ ብሎኛል፣
አምላኬ በእኔ ስም ተመስግኖልኛል፣
ለወንጌሉ ስብከት ጊዜው ሊጋጥሞኛል።
መናፍቅ ነው ቢሉኝ እኔ ምን ዕዳዬ፣
ውዳሴ ከንቱ ነው ከሰው ምስጋናዬ
አንተ ሁነኝ እንጂ በነፍሰ በሥጋዬ
ታምጄብሃለሁ አትጣለኝ ጌታዬ።
አንኳን በእግር ብረት ቢያገቡኝ በግንድ፣
ከቶ ምንም ቢሆን እውነትን አልክድ፣
መጨመር ነው እንጂ ክሳት ላይ ባሩድ፣
የተሰወረውም እንዲሆን ገሃድ፣
እኔ ለአምላክ እንጂ ለሥዕል አልሰግድ።

እንዲሁም ከሁሉ በላይ አንፀባራቂ ሥራ የሠሩትን ጥቂቶች ሲያሞግሷቸው በአንዳንዶች ዘንድ እንደ ከሃዲ የሚቆጠሩና ሞተው እንኳ የሚወገዙ ታላላቅ ሰዎችም አልታጡም። ከእነዚያ መካከል አለቃ ታዬ አንዱ ናቸው። የብዙዎች ዓይን ገና ባልበራበት ዘመን *“የአሥራ ዘጠነኛው ዘመን ኢትየጵያዊ ምሁር”* የሚል ቅጽል ስም ወጥቶላቸው ነበር። የዘመኑን የግብፅ ጳጳሳት የበላይነት፣ በቤተ መቅደስ የተንሰራፋውን ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ እንደ አባ እስጢፋኖስና ተካታዮቹ በእግዚአብሔር ቃል ላይ በመቆም በግልጽ የሞገቱና ለእውነት ራሳቸውን የሰጡ ታላቅ ሰው ነበሩ፡-

> *አለቃ ታዬ የተቃውሞ ትምህርት ያስተምራሉ በሚል በጳጳሱ ፊት ቀረቡ። ስለተከሰሱበት ነገር ራሳቸውን መከላከል ሲጀመሩ ጳጳሱ በቁጣ አቋርጠዋቸው አንተ አህያ ሃይማኖትህ ምንድነው? ሲሉ ዘለፏቸው። እርሳቸውም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተሾሙትን ግብጻዊ ጳጳስ በክርስቲያናዊ እምነታቸው ላይ እንዲቀልዱ ባለመፍቀድ፡- **በርግጥ እኛን የማይረቡ አህዮች ያሰኘን እስ በቤተ ክህነታችን ላይ እንደ እርስዎ ያሉትን ባዕዳን መሾማችን ነው**[91] ብለዋል።*

አለቃ ታዬ ከጀርመን መልስ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ኒሻን ከዐፄ ምኒሊክ ተሸልመው በትውልድ ቀያቸው ጉልት ተቀብለው ሥራቸውን ቀጠሉ። ደጃዝማች መሸሻ ወርቁ በቅናት ተነሣስተው የአለቃ ታዬን ጉልት ገሚሱን በኃይል ከነጠቁ በኋላ ቀሪውን ደግሞ ለመጠቅለል አስበው በጊዜው የበጌምድር ገዢ ለነበሩት ለንጉሥ ወ/ጊዮርጊስ እንዲህ ብለው ጻፉ፡- *“አለቃ ታዬ ሃይማኖቱ ንስጥሮስ ነው፤ ይህን ሃይማኖት ለሕዝብ ያስተምራል።”* ንጉሥ ወ/ጊዮርጊስ ቁጣና ብስጭት በተሞላበት መንፈስ እንዲህ ብለው ለአለቃ ታዬ ላኩ፡-

> *የተላክ ከራስ ወ/ጊዮርጊስ ይድረስ ለአለቃ ታዬ እንዴት ሰንብተሃል? እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። ዝም ብለህ ተቀመጥ ስንልህ እንደዚህ ያለ ትምህርት ከየት ያመጣኸው ነው? በምን ተጣላኸኝ እንዳትል። በ1903 ዓ.ም ጎንደር 24 ቀን ተጻፈ።*

ደብዳቤው እንደ ደረሳቸው ሃይማኖታቸው ተዋሕዶ መሆኑንና የተፈጸመባቸው ግፍ ተገቢ እንዳይደለ ለንጉሥ ወ/ጊዮርጊስ በመግለጽ የተወሰደባቸውን መሬት እንዲያስመልሱላቸው ጠየቁ፤ ንጉሡም ደጃዝማች መሸሻ ወርቁን አስጠርተው የወሰዱባቸውን ጉልት ለአለቃ ታዬ እንዲመልሱላቸው ፊረዱ። ሁኔታው ያልተዋጠላቸው ደጃዝማች መሸሻም፣ ታዬ *“ሃይማኖቱ ፀረ ማርያም”* ነውና አገር መግዛት አይገባውም በማለት ሌላ ክስ ከፈቱበት።[92] ንጉሥ ወ/ጊዮርጊስ ጉዳዩ ሃይማኖት ነክ በመሆኑ ታኅሣሥ 24 1903 ዓ.ም ክሱን ወደ አቡነ ማቲያስ መሩት። ጥር 28 1903 ዓ.ም በዋለው ገባኤ አለቃ ፊለቀ ከሳሽ ሆነው በመቅረብ *“አለቃ ታዬ*

[91] *ጮራ መጽሔት ቁጥር 40 ታህሣሥ 2003 ዓ.ም ገጽ 13-14*
[92] *ደማቁቹ ገጽ 67*

ለፍቼ አልቀረሁ አንዳገልግሎቴ
ግምጃ ሱሪ አግረ መቅ ወህኒ ቤት ግዛቴ፣
ለፍቼም አልቀረሁ የኔ ጌጥ ይሽዋ፣
ግምጃ ሱሪ አግረ መቅ ሰንሰለት ቢተዋ::[93]

ይህ ግጥም አለቃ ታዬ ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ የሆነውን አሳብ እንቢ በማለቱ መታሠሩን፣ እሥራቱን ደግሞ የወንጌል አገልግሎት በር አድርጎ መቁጠሩን፣ መናፍቅ ብለው አምላክን ሳይዙ በብርቱ እንደሚከራከሩት፣ እርሱ በአምላክ እጅ በእርግጠኝነት እንዳለ በመታመን እየተናገረና የአምላክን ዕርዳታ መጠየቁንና ለአምላክ እንጂ ለሥዕል ስግደት እንደሌለው በግሄድ ይናገራል:: በአጠቃላይ ግጥሙ እምነት፣ ጽናት፣ ቆራጥነት፣ መረዳት፣ የጠራ አስተምህሮው ብቻ ሳይሆን የተቃዋሚዎቹ እምነትና መረዳት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ፍንትው አድርጎ ያመለከተ ነው::

የአለቃ ታዬ ሥራዎች

በ1897 ዓ.ም የጀርመን ንጉሥ ነገሥት ግዕዝና አማርኛ የሚያስተምር አንድ ሊቅ እንዲላክለት ጠየቀ:: ዐፄ ሚኒልክም፤ *"ለዚህ ተግባር የሚመጥን አለቃ ታዬ ነው!"* ብለው መረጧቸው::

ምኒ አንበሳ ዘእምነገድ ይሁዳ ጻግሜዊ ሚኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ይድረስ ለአለቃ ታዬ እንዴት ሰንብተሃል:: እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ:: ከጀርመን መንግሥት ተልከው የመጡ ሰዎች በምጽዋ በኩል ወደ አገራቸው ለመሄድ በጎጃም በኩል መጥተዋል:: ነገር ግን ከኢትዮጵያ የሄደ በአገራችን ብዙ የጥናት መጽሐፍ አለ:: ያንን የሚያውቅ ብልህ ሰው ይሂድና እንዲያይ ይሁን ብለናል:: አንተ የዚያን አገር ባሕል ለምደኸዋልና እናንተ ዘንድ በደረሱ ጊዜ አንተም ከነርሱ ጋር አብረህ እንድትሄድ ይሁን::[94]

አለቃ ታዬ በአውሮፓ ቆይታቸው ከጀርመን በተጨማሪ ሲዊድንን፣ ቱርክን፣ ኢጣሊያንንና ግሪክን ጎብኝተዋል:: በመንገዳቸውም ላይ አስክንድርያና ኢየሩሳሌም ላይ ቆይታ አድርገዋል:: ብልህነቱንና አቅሙን ያስተዋሉ የጀርመን፣ የግሪክና የኢጣሊያንም መንግሥታት ልዩ ልዩ የክብር ኒሻኖች

[93] ዮሐንስ አድማሱ *(2004 ዓ.ም)*፤ *ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ*፤ ገጽ 41 *(ይህ ግጥም አለቃ ታዬ፣ በለውጥ ፈላጊነታቸው ረገድ ምን ዓይነት ሰው እንደነበሩ ጥሩ ምስል ያተርባል፣ የጊዜውን ማህበራዊ - ፖለቲካዊ አየር ቃና ይናኘል:: አለቃ ታዬ በዚህ ረገድ ስለደረሰባቸው መከራና ለቀረበባቸውም ሃይማኖት የመከረ ክሰ ስለሰጡት መልስ ባሕሩ ዘውዴን Pioneers of change in Ethiopia: The Reformist Intellectuals of the Ethiopia of the Early Twentieth Century* (James Currey,(2002), *Ohio* University Press, Addis Ababa University press,

[94] መጋቢት 9 ቀን 1997 ዓ.ም

ሸልመዋቸዋል:: ከንጉሥ የተሰጣቸውን ተልዕኮ በስኬት እንደተወጡ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴም "የሕይወት ታሪክ" በተሰኘ መጽሐፋቸው እንዲህ ዘግበዋል:-

የጀርመን መንግሥት የግዕዝ ቋንቋ የሚያስተምር አንድ ሊቅ ይስጠኝ ብሎ ዐፄ ሚኒልክን በለመነ ጊዜ፣ አለቃ ታዬን መርጠው ሰደዷቸው:: በጀርመንም መንግሥት ሦስት ዓመት ሙሉ ግዕዝ ቋንቋ አስተምረው፣ ኒሻን ተሸልመው ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ ዐፄ ሚኒልክም ኒሻን ሸልመው ያባታቸውን አገር ሰጥተው ወደ በጌምድር ሰደዱዋቸው::[95]

አለቃ ታዬ ስለ ዘመናዊ ኢትዮጵያ ታሪክ አባዓፍ በር ከፋች ናቸው ሊባሉ ይችላሉ::[96] ታላቅ ደራሲ ነበሩ:: ከጻፉአቸውም መጻሕፍት መካከል:-

- *መጽሐፈ ሰዋሰው*
- *መጽሐፈ መነፅር*
- *የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ*
- *የኢትዮጵያ ታሪክ*
- *መዝገበ ቃላት*
- *የመንግሥት ሕይወት*
- *መዝሙረ ክርስቶስ*
- *ትርጓሜ ዳዊት ከእነታሪኩ እና*
- *አምስቱ አእማድ የተባሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው::*

አለቃ ታዬ ለአገር የነበራቸው ታላቅ ራእይ

ጌታቸው በለጠ (*በኢምፓክት መጽሔት 2000 ዓ.ም*) አለቃ ታዬ በውጭ አገር ሲማሩ ለአገራቸው ዕድገትና ለውጥ ትልቅ ራእይ እንደነበራቸው ለንጉሡ የጻፉትን ደብዳቤ በጽሑፋቸው የጠቀሱት እንዲህ ይነበባል:-

አውሮፓውያን ለጥበባቸው ፍጻሜ የለውም:: በየዕለቱ አዲስ ነገር እሰማለሁ:: ጃንሆይ ከአገርዎ ልጆች ወደ አውሮፓ ሰደው ብልሃት ቢያስተምሩ መልካም በሆነ... የጃንሆይ ብር እንዲለሰጥን የፊተኛውን ብርና አሞሌ ያጥፉ... በአገራችን ጥቂት ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች በማከበር ፈንታ ስለሚሰደቡ፣ ስለሚዋረዱና ስለሚጠቁ ጠቃሚ ጥበብ ሥራ ትተው መባዘን መረጡ:: ያውሮፓና አሲያ ሰዎች ከአፍሪካ ሰዎች ከፍልም ጥቂቶቹ ብልሃተኞች ሲሆኑ እኛ ሀበሾች ... መጽሐፍ ቢማሩ እንጨት ቆርቋሪ ... ቆዳ ቢፍቅ ጥንበ በላተኛ ፋቂ እየተባለ ለየሥራው ሁሉ ሰም እየሰጠን ስለሚሰደብ የጥበብ ሥራ ከረዜ ወደ ረዜ

[95] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴም(*1915 ዓ.ም*) ፤ የሕይወት ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ራስ ተፈሪ ማተሚያ ቤት *ገጽ 37-38*

[96] *አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ 1961 ዓ.ም ገጽ 2*

ተብሎ የተገጠመላቸው ለአለቃ ታዬ ነበር። የታሪክ ምሁሩና ጸሐፊ አለቃ ታዬ በ1916 ዓ.ም ሲሞቱ በአዲስ አበባ ሥላሴ ቅበሩኝ ብለው ከመሞታቸው በፊት እንደተናገሩ ይነገራል። መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ "ዋሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ" በሚለው መጽሐፋቸው በአለቃ ታዬ ቀብራቸው ላይ ተገኝተው የታዘቡትን እንዲህ ዘግበዋል፦

ቤተሰቦቻቸውና ወዳጆቻቸው ወደ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ካህናቱን ፍትሐት ፍቱልን ቢሏቸው አንፈታም አሉአቸው። ቀባሪዎችም መቃብር ለመቆፈር ቢጀምሩ ካህናቱ በደወል ተሰበሰቡና "ይህ ጸረ ማርያም፣ በቤተ ክርስቲያናችን አይቀበርም" ሲሉ አምባጓሮ አንሥተው ከለከሉ። ...በአምቢታቸው ስለ ጠነከሩ የአለቃ ታዬ ሬሣ ወደ ጉለሌ ተወሰዶ በፕሮቴስታንቶች የመቃብር ሥፍራ ተቀበረ።... የዚህ ታሪክ ጸሐፊ የአለቃ ታዮን ሞት ሰምቶ ለማስቀበር ወደ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ነበርና አምባጓሮው ላይ ደርሶ የነገሩን ሁኔታ ተመልክቷል። ካህናቱ ክፉኛ ተቆጥተው መቋሚያ ይዘው ለጥል ተሰልፈው ነበር[99] ብለዋል።

ካህናቶቹ መቋሚያ ይዘው ለጥል የተሰለፉት ከማን ጋር ለመግጠም ይሆን? ከአፈር የተሠራው የሰው ሥጋ ሲሞት ወደ አፈር መመለሱ እንጂ በኦርቶዶክሶችና በፕሮቴስታንቶች የቀብር ቦታ መቀበር በሚቹ ላይ አንዳች ለውጥ እንደሚያመጣ መጽሐፍ ቅዱስ ምንም ፍንጭ አይሰጥም። የአንድ ሰው አስክሬን በልዩ አጀብ በክብር ወይም በውርደትም ቢቀበር፣ ሳይቀበር በስብሶ ወደ አፈርነት ቢለወጥ ወይም በእሳትም ቢቃጠል፤ በሕይወት እያሉ በጌታ ያመኑ ለዘላለም ከጌታ ጋር ለመኖር ያላመኑ ደግሞ ለዘላለም ፍርድ አንድ ቀን ሁሉም እንደሚነሡ ቃሉ ይናገራል። አለቃ ታዬ በሕይወት እያሉ ብቻ ሳይሆን በሞታቸውም ብዙ ወሬ ተነዝቶባቸው ነበር። አንዱ ወሬ፣ ከእምነታቸው የተነሣ ከቁላውስቱ ጋር አይስማሙም ነበር። በዚህም የተነሣ መሬት አስክሬናቸውን እየተፋች አስቸገረች የሚል ነው። በዚህ የተደነቀ አንድ ሰው "ትልቅ ሰው በመሆናቸው መሬት አልችላቸውም ብላ ነው" ሲል መለሰ ይባላል።

ቃሉ ለሕያው ሰው እንጂ ለአስክሬን ሥርዓት የለውም

አንድ የሚስዮሎጂስት ፕሮፌሰር ሲያስተምረን ወደ ህንድ የወንጌል መልዕክተኛ ሆኖ ባገለገለበት ዘመን የአንድ አማኝ የቀብር ሥርዓት ትልቅ የወንጌል በር እንደከፈተለት የተረከልን ታሪክ ትዝ አለኝ፣ እንዲህም ብሎ ምስክርነቱን አካፈለን፦

እግዚአብሔር በወንጌል ያልተዳረሰውን የመድረስ ትልቅ ሸክምና ጥሪ ስለሰጠኝ ከአስራሳቢ ትምህርት በኋላ ኤ.ኤ 1976 ከአሜሪካ ወደ ህንድ አቀናሁ። ወንጌልን መስበክ በጀመርኩበት አካባቢ 99.9% የነበረው ሕዝብ የህንዱይዝም ሃይማኖት የሚከተሉና የተለያየ ጣኦት አምላኪዎች ነበሩ። ከሁለት ዓመት

[99] መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ(1896-1922 ዓ.ም) ፤ *የሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ፤ የዘመን ታሪክ ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት (ሁለተኛ እትም)*፣ አዲስ አበባ የኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ ገጽ 272-273

እየቀዘቀዘ ጠፋ። ስለዚህ ጉዳይ ጃንሆይ ለስበውበት እንዲህ ያለው ሲድብ ሁሉ ባዋጅ እንዲከለክል ... ሰዎች እንዲከበሩ ቢያደርጉ ... በሌላ መንግሥት ሰምና መልክ የተቀረፀ ገንዘብ ከመገበያየት በጃንሆይ መልክና ስም የተቀረፀበት ገንዘብ እንዲወጣ ቢያደርጉ ነፃ መንግሥትም ራሱን የቻለ የተሟላ ይሆናል...

ኃይሉ ከበደም በመመረቂያ ጽሑፋቸው አለቃ ታዬ ጀርመን ሆነው ለንጉሥ ስለጻፉት ደብዳቤ እንደሚከተለው ገልጸዋል፦ *በየዕለቱ አዲስ ነገር አያለሁ፤ አዲስ ነገር እሰማለሁ። ...ይህን አይቼ ለአገሬ መንግሥት ቅንዓት እንደአሳት በላኝ። ምንስ አደረጋለሁ? አዝኜ ወደ መቃብር እወርዳለሁ[97]* በማለት ከአውሮፓ ወደ አገር ቤት የሰደዱት ደብዳቤ አለቃ ታዬ ለአገራቸው ክብር፣ የኢኮኖሚ ብልጽግና የሥራ ባሕል ለውጥ የነበራቸውን ተቆርቋሪነት አመልካች ነው።

የአለቃ ታዬ ተቀባይነት ማጣት

ለአገሩ ዕድገትና ብልጽግና ተቆርቋሪና በእግዚአብሔር ቃል ላይ በመቆም በዘመኑ የነበረውን ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮና ልምምድ በገሃድ የሞገቱት አለቃ ታዬ በትልቅ መከራና መገፋት ውስጥ እንዳለፉ ታሪካቸው ያወሳል። ታዋቂ የኢትዮጵያ ምሁር ነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ ስለ አለቃ ታዬ ሲናገሩ፦

አስክ ዛሬ ድረስ አሩቅ አገር ተሰደው ወይም ወደ ለበሾኝ ከመጡት ፈረንጆች ጥቂት ጥበብ ተምረው ያገራቸውን መንግሥት ሊጠቅሙ የሚፈልጉ ወንድሞቻችንን መናፍቃን፣ የሌላም መንግሥት ሰላዮች እየተባሉ ሲራቡ፣ ሲከሰሱም እናይ የለምን? እነዚያን መከረኞች ስም ሰንት ብለን እንቁጠረው? የሚከተሉት የሁለት ሰዎች ስም እንዲወሰ የግድ ነው። እነርሱም ከንቲባ ገብሩና አለቃ ታዬ ናቸው። ሦስት ዓመት ሙሉ አዲስ አበባ ላይ ስቀመጥ እንደእነዚህ ሁለት ሰዎች አድርጉ መንግሥቱን የሚወድ ሰው አላየሁም። ይህ ደግነታቸው ግን እስከ ዛሬ ድረስ አልታወቀላቸውም ይመስለኛል። እጅግ ያሳዝናል። የእነርሱን ዕድል ያየ ሰው የኢትዮጵያ መንግሥት ለወዳጅ አይጠቅምም ብሎ ይቆርጣል።[98]

የአለቃ ታዬ ዜና ዕረፍት

"ቢከፋ ቢደሰት ሁሉም በሞት ያልፋል

የመልካም ሰው ዝና ታሪኩ ይተርፋል።"

[97] ኃይሉ ከበደ *(1963 ዓ.ም)*፣ የአለቃ ታዬ ጉዘሪማርያም የሕይወት ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ኢ.ኤ.ዩ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ፣ ክፍል ለእርት ባችለር ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጽሑፍ፣ (ያልታተመ)

[98] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 26*

ጸሎትና አገልግሎት በኋላ በአንድ ሀብታም ቤተሰብ የተወለደ ሽባና በብዙ በሽታዎች የተጠቃ ሰው ወንጌልን ስምቶ በጌታ ኢየሱስ አምኖ ተጠመቀ። ቤተሰቦቹም አዲሱን ሃይማኖት በመቀበሉ አልተቃወሙትም። ወዲያውም ታሞ ሆስፒታል ሲገባ እንዲዐልይለት ተጠርቼ ወደ ሆስፒታሉ መጥቼ በመዐለይ ሙሉ ቀን ከእርሱ ጋር ዋልኩ። በመጨረሻ የጌታ ፈቃድ ሆኖ ቀዳሚውና ብቸኛው የቤተ ክርስቲያናችን አባል የነበረው ሰው በሞት ተለየን። ከቤተሰቡ ጋር አለቀስን፤ አዘንን። ቤተሰቡም ወደ እኔ መጥተው አስክሬኑን በሃይማኖትህ መሠረት የሚታደረገውን አድርግ አሉኝ። እኔም፡- በክርስትና ለሞተ ሰው የሚደረግ የተለየ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥርዓት የለም። ሲላቸው፡- ፈቃድ ጠይቀውኝ በሥርዓታቸው መሠረት ፈጸሙን አቃጠሉ። ከዚያ በኋላ ያልተጠበቀ ነገር ሆነ። በነጋታው ቤተሰብ ሁሉ በአንድነት አንተ መልካም ሰው ስለሆንክና አኛን እንዳለን ስለተቀበልከን ከዛሬ ጀምሮ ሁላችንም ካንተ ጋር ክርስቶስን አንክተላለን አሉኝ። አውነት አልመሰለኝም። ግን አውነት ነበር። ጌታን ተቀበሉ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ተምረው በአንድ ጊዜ ከአርባ ሰዎች ከአንድ ቤተሰብ ተጠመቁ። ዛሬ ያች ቤተ ክርስቲያን ከ4000 አባላት በላይ አላት፤ በአካባቢው ከ100 የሚበልጡ አብያተ ክርስቲያናት በዚህች ቤተ ክርስርስቲያን አማካይነት ተተክለዋል ብለዋል።

በአገራችን ክርስትና ትልቁ ሰው በሕይወት እያለ ማቅናትና ከኃጢአት መንገድ እንዲመለስ መምከርና መገሰጽ ሳይሆን ሲሞት አስክሬኑን ማንከራተት ወይም ለሞተ ሰው ምንም የማይፈይድ ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥርዓቶችን መፈጸም የተለመደ ነው። አለቃ ታዬ ብቻ ሳይሆኑ በተለይ የወንጌል አማኞች እንደ ተፈረደባቸው "ፀረ ማርያም" ተብለው የቀብር ቦታ ሲከለከሉ፣ የተቀበረውን አስክረን ከመቃብር አውጥቶ ለጅብ መስጠትና በአንጨት ላይ መስቀልና ማቃጠል "በዚህች የክርስቲያን ደሴት" "ኢትዮጵያ አገረ አማዚአብሔር" "ገነት ናት" በአንዳንዶች በተባለላት ኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ነን በሚሉት የሚፈፀም የተለመደ አንዱ ኢሰብዓዊ ድርጊት ነበር። ለምሳሌ በዘመናችን የሆኑትን ሁለት ሁኔታዎችን ልጥቀስ

በጉራጌ ዞን በዳሎቻ ወረዳ በውልባረግ ቀበሌ ውስጥ ሐምሌ 4/1987 ዓ.ም የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አባል የነበረ የአንድ ሰው አስክሬን እንዳይቀበር በካህናቱ በመወሰኑ ያ አስክሬን 40 ኪሎ ሜትር ተጉዞ ሆሳዕና ከተማ እንዲቀበር ተደርጓል። በዚሁ በጉራጌ ክልል ውስጥ መቀበሪያ በማጣት ተወርውሮ በአውሬዎች የተባላ ቅሪተ አጽም ተሰብስቦ አዲስ አበባ ድረስ ተጓጉዞ በመምጣት የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች እንዲመለከቱትና የማፉን ክብደት እንዲረዱት የተደረገው በዚያው ዘመን ነው። ድርጊቱ እንኳን ሰተመልካች ቀርቶ ይህንን ግፍ ያደመጠውን ሁሉ አስለቅሷል።[100] ከደብረ ዘይት ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኘው በጨፌ ዶንሳ ቀበሌ ውስጥ ነሐሴ 1/1984 ዓ.ም አዲሱ ተሰፋዬ የተባለው የ18 ዓመት ወጣት አማኝ በአካባቢው በሚገኘው የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ካህናት አቀነባባሪነትና በቤተ ክርስቲያኒቱ የሰንበት ት/ቤት መምህር የቡድን መሪነት "ዴንጤ ነው" ተብሎ መገደሉና አስክሬኑ በትልቅ ዛፍ ላይ መሰቀሉ፤ በስድስተኛው ቀንም አስክሬኑን ከመቃብር አውጥተው በርብራብ እንጨት ላይ

[100] ጌታቸው በለጠ፣ ገጽ 320

ሊጋድመው ቤንዚን በማርከፍከፍ የማይታገላቸውን በድን ማቃጠላቸው በወቅቱ በታተመ በፐሬስ ውጤቶች ላይ ተደጋግሞ ተጠቅሷል።[101]

አስደንጋጩና አንገት የሚያስደፋው ጉዳይ የዚህ ኢሰብዓዊ ድርጊት ፈጻሚዎች የክርስትናንና የቤተ ክርስቲያንን ስም መጠቀማቸው ነው። ከአራተኛ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በኢትዮጵያ በወንጌል ስም ሰው ማሳደድ፣ ማሰር፣ ማሰቃየት፣ አልባሌ ስም መለጠፍና መግደል በእኛም ዘመን መዝለቁን ነው። ይህ ድርጊት በፍፁም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። የዚህ ኢሰብዓዊ ድርጊት ምንጩ የኦርቶዶክስ አስተምህሮ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል እጦት ነው። የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተቀበረውን የሌላ ሃይማኖት ሰው ከተቀበረበት ወጥቶ እንድጣልና በእንጨት ላይ እንድሰቀል አላስተማረችም፤ አታስተምርምም። በወንጌል ልቡ ያልተለወጠ በኦርቶዶክስ ብቻ ላይሆን በፕሮቴስታንትና በካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ቢሆን ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም። ሰው የትም ይሁን የት ልቡ በወንጌል እንጂ በቤተ ክርስቲያን አባልነት አይለወጥም። ልቡ ያልተለወጠ ሰው የቤተ ክርስቲያንን አባልነት እንደ ክሌላ በመጠቀም የጨለማ አሠራር ሠራተኛ ይሆናል። ተሐድሶ ያስፈልጋል ሲባል ይህ ከክርስትና ጋር የተጣበቀ አሉታዊ አመለካከትና ድርጊት ጭምር እንደሆነ መዘንጋት የለብንም። ወደ እግዚአብሔር ቃል መመለስ አለብን። ከእሳት እንኳ ነጥቀን እንድናድን (ይሁዳ.23) እንጂ ገድለን በአስክሬን እንድንጫወት መጽሐፍ ቅዱስ አያስተምረንም። ይህ የሚያመለክተን ሰዎች አሉታዊ ድርጊት እንዲፈጽሙ ያደረጋቸው አሉታዊ የክርስትና መረዳት እንዳላቸው ነው።

የአለቃ ታዬ እኅት ሙሽ

አለቃ ታዬ ሲሞቱ እኅታቸው ወይዘሮ ላቀች አምነህ በሚከተለውን ሙሽ አለቀሱላቸው፤ የአለቃ ታዬን መከራ ዕፁብነት፣ በጌታ ላይ የነበራቸውን እምነት፣ ለተረዳው አውነት ሰማዕት መሆናቸውንና የገዳዩቹን ማንነት በብዙ ያስረዳናልና እነሆ፡

ሲናገር አዳምጡ ዘመዶቼ ቁሙ፣
ሌላ ያስለቅሳል እንኳን ለወንድሙ።
ጠላው ተዘንብሎ ወርዶ በማቶት፣
እንጀራው ተሠርቶ ቀርቦ በሌማት፣
አጠፉት መብራቱን እንዳንበላበት።
ተነሡ እንተኛ በሉ ሁሉም ቀረ፣
መብራቱ በታየ እንበላ ነበረ።
አለቅሰልሃለሁ ቁሜ ብዙ በቁሜ፣

[101] ግርማ ዘውዱ፣ ገጽ 65-67

አላፍርም ስናገር ይህን ደጋግሜ፣
እውነት ሲመሰክር አይፈራም ወንድሜ።
ይሠሩህ ያግዙህ ይስደዱህ የትም፣
አንተ ብትሰቃይ ታሪክህ አይሞትም።
ቢከፋ ቢደሰት ሁሉም በሞት ያልፋል፣
የመልካም ሰው ዝና ታሪኩ ይተርፋል።
ቅባትና ጸጋ ተሸሽጎ ቆየ፣
የተዋህዶማ መሠረቱ ታየ።
አንተ ቢቆረጥ በሰይፍ በካራ፣
አልሰግድም ለሥዕል ለሰው እጅ ሥራ።
ይህንን ቢናገር በቆራጥነት
አቡንና እጨጌ ብዙ ካህናት፣
በዚህ ምክንያት ነው የፈረዱበት፣
ይዘው የከተቱት ከጨለማው ቤት፣
አትብሉ ስላለ የሙታን ንብረት።
ከመሀኒ ቤት አስረው የዘገቡት ሳንቃ፣
ብሎ ተናገሮ ነው የወንጌል ቃል ይብቃ።
የወንጌልን ሥርዓት ተማሩ ቢላቸው፣
ትልቁም ትንሹም ሁሉም ደደብ ናቸው፣
አሉት ፀረ ማርያም መልስ ቢሳናቸው።
መጽሐፍም ሲሰበር በንባብ በትር፣
ምስጢር መድኃኒቱን ቀበቶ ለማሰር፣
ይህ ሐኪምነቱ ዕውቀቱ ነበር።
ዕውቀትና ምግባር ጉድጓድ ተከተተ፣
አራት ነው እንጂ መች አንድ ሰው ሞተ።
ወዝውዘው ነዝንዘው ጣሉት እንደ ዝሆን፣
ያው ወደቀላቸው ይበሉት እንደሆን።
ከጨለማ መኻል በወጣ ብርሃን፣
አጥፉት አጥፉት አሉ እንዳይታየን።

መቅረዙ ተሰብሮ መብራቱ ቢጠፋ፣
ብርሃን የማይወዱ ፈገግን ሊሰፋ
መልሶ እንዲጨልም አደረጉ ተስፋ።[102]

የአለቃ ታዬ አጽም ለውግዘት?

ኢትዮጵያ በየዘመናቱ አዲስ አሳብ የሚያመነጩና እንዲያስቀድሟት በእግዚአብሔር የተሰጧት ልጆቿን አሳዳ በመግደሏ ቀዳሚ ተብላ በሁሉም የሁሉ ጭራ እንደሆነች ዓለም የሚያውቀው እውነት ነው። ለዚህ ነበር ባለቅኔውና ፀሐፊ ተውኔቱ አፈወርቅ አዳፍሬ፣ "ላገረ መሞት" በተሸኘው ቲያትሩ ላይ እንዲህ ሲል ጎምዛዛ ምፀቱን ያስቀመጠት፦

ኢትዮጵያ ሆይ ሞኝ ነሽ ተላላ
የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ፣

ይህ ግጥም ደራሲውን ከሥልጣኑ አስወርዶ እስከ ሞት እንዳደረሰው ፍጹም ወ/ማርያም "*ያልተዘመረላቸው*" በሚል መጽሐፉ የአቶ በለጠ ገብሬ "የጉዞ ትዝታ"ን ዋቢ በማድረግ ጽፈዋል።[103] "*ከማይታወቅ መልአክ የሚታወቅ ሰይጣን ይሻላል*" የሚል የቆየ ብሂላችን ለተለመደው ነገር ያለንን ፍቅርና ለአዲስ ነገር ዝግ መሆናችንን ፍንጭ ይሰጠን ይሆን? ከዚህም የተነሣ በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ላይ ቃሉን ይዘው የተሐድሶ ጥያቄ ያነሡ በዚህች ምድር በግፍ እንደተሰቃዩና እንደተገደሉ የአባ እስጢፋኖስ፣ የደቂቀ እስጢፋኖስና የአለቃ ታዬ ታሪክ ሕያው ምስክሮች ናቸው። ዛሬም ልባችን ብዙ አልተለወጠም። በቅርቡም በአዲስ አበባ አገረ ስብከት በሚገኙ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ስም በጥቅምት 2 ቀን 2004 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጽሕፈት ቤት ቀረበ የተባለው በታላላቅ ሰዎች የስም ዝርዝር አለቃ ታዬ፣ ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፣ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴና ሌሎች የተሐድሶ ጥያቄ ያነሡ አባቶችን የጸጋ ቅባት "*የኑፋቄ ትምህርት ሠራተኞች*" በማለት በይፋ እንዲወገዙ ጥያቄ እንደቀረበ ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት ይፋ አድርጓል።[104] የአለቃ ታዬ አስክሬን በሰላም እንዳያርፍ ካህናቶች መቋሚያ ይዘው ከተዋጉ ከ89 ዓመት በኋላ የዚያ ሀሳብ አቀንቃኞች አጽሙን ለውግዘት ማዘጋጀታቸው ከታሪክ ለመማር እንቢተኝነታችንንና የልባችንን ጥንካሬ ያመለክታል። እግዚአብሔር ይቅር ይበለን። የእኛ ያለመባረክ አንዱና ዋና ምክንያት ይቅርታን የማያውቅ የደነደነና ጠንካራ ልባችን ነው።

---

[102] ዮሐንስ አድማሱ *(2004 ዓ.ም)*፣ ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ ገጽ 41-42
[103] *ያልተዘመረላቸው 2005 ዓ.ም፣ ገጽ 156*
[104] *ጮራ መጽሔት፣ቁጥር 44፣ 2005 ዓ.ም ገጽ 13*

መጽሐፍ ቅዱስ የት፣ በማን፣ እንዴት እና መቼ መቀበር እንዳለብን አንድም ቃል ያለመናገረ የትም መቀበር በአንድ ሰው የዘላለም ዕጣ ፈንታው ላይ ምንም ስውጥ ስለማያመጣ ነው።

አስተውሎት

ቤተ ክርስቲያን መታደስ እንዳለባት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከሞገቱት ከኢትዮጵያ ፋና ወጊ ምሁራን መካከል ነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ፣ ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ ዘብሔረ ዓድዋ፣ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ይገኙባቸዋል። አለቃ ታዬን ነጥለን ያየንበት ምክንያት ከቀደሙት ምሁራን እንደ ምሳሌ ለመውሰድ ነው። በተጨማሪ በእነርሱ የተጻፉ መጻሕፍትን ስናነብ የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ አንገብጋቢ ጥያቄያቸው እንደነበር ማየት እንችላለን። ይህም የተሐድሶ ጥያቄ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአሁኖቹ ትውልድ ብቻ ሳይሆን የቀድሞዎቹ፣ ያልተማሩቱ ብቻም ሳይሆን የቀለም ፋና ወጊ የተባሉና ከቤተ ክርስቲያን የተገኙ የቀድሞና የአሁኑ ትውልድ ጥያቄ እንደሆነ ያሳየናል። እግዚአብሔር ያለፈውን የዘመናት የደም ዋጋ፣ የቅዱሳንን ዕንባ፣ ያልተቋረጠ ብርቱ ምልጃና መሥዋዕትነት ተቀብሎ በምህረቱና በጸጋው ራርቶልን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በቃሉና በመንፈሱ በማደስ ለዓለም በረከት በወንጌል በዘመናችን ያደርጋታል ብዬ አምናለሁ።

በዘመናችን አባቶች ለተሐድሶ የከፈሉትን ዋጋና የእምነት ተጋድሎ ማንበብ ብቻ ሳይሆን የእነርሱን ዱካ ለመከተል መልካሙን የእምነት ገድል በመጋደል ላይ ያላችሁ፣ ትልቅ የስም መጥፋት የደረሰባችሁ የተዛተባችሁና እውነትን በመያዛችሁ የተወገዛችሁ የሐዋርያትን፣ የነቢያትንና የዚህች ምድር የቀደሙ አባቶችን ታላቅ ዕድል አግኝታችኋልና እንኳን ደስ አላችሁ። ጌታ ይመጣልና በርቱ። ቀጣዩ ምዕራፍ ቀደሚት አባቶች ሰማዕት የሆኑለት የተሐድሶ ጥያቄ በዚህም ትውልድ መቀጠሉን ያስቃኘናል።

አጽሙ ከመቃበር ወጥቶ የተቃጠለ የተሐድሶ ሰው!

በአውሮፓ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ የንጋት ኮከብ የተባለው ጆን ዊክሊፍ መጽሐፍ ቅዱስን ከላቲን የብዙሃኑ ቋንቋ ወደ ሆነው እንግሊዝኛ በመተርጎማቸው እርሱ ከሞተ ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ የሮማ ጳጳስ አሩንዴል *"ውግዝ ከመሰረዮስ"* በማለት በገሃድ አውግዞት ነበር። የሮማ ጳጳስ ማርቲን አምስተኛ ደግሞ ጆን ዊክልፍ ከሞተ ከ44 ዓመት በኋላ በ1428 ዓ.ም የጆን ዊክለፍ አጥንት ኮተቀበረበት ወጥቶ እንዲቃጠልና አመዱ በወንዝ ላይ እንዲበተን አዞዋል። ቤተ ክርስቲያን ይህን አስነዋሪ ድርጊት እንድታከናውን ሥልጣን አልተሰጣትም።

ቤተ ክርስቲያን የሰማያዊ ቃል ድሃ ስትሆን ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና ኢሰብዓዊ ድርጊት በአምላክ ስም ሽፋን መፈጸሟ አይቀሬ ነው፤ ልዓም እንደበጠሰ ፈረስ በመሆን በውሸት ሜዳ ያለ ከልካይ ለጊዜውም ቢሆን ባለድል ትመስላለች፤ ሰውን በማዳን ምትክ በሰዎች ደም ጣቶቿን ነክራ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዳገለገለች ማሰብ ብቻ ሳይሆን በድፍረት መናገሯ ሙት መሆኗን ያሳብቅባታል። መታወቅ ያለበት እውነት ቤተ ክርስቲያን ለኢሰብዓዊ ድርጊቷ አንድ ቀን በታላቁ ጌታ የፍርድ ወንበር ፊት ቆማ መልስ ትሰጥበታለች። ቤተ ክርስቲያን ከዘላለም የሞት ፍርድ ብታመልጥም የሥራ ፍርድ እየጠበቃት እንዳለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ነው። *"መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናል"* (2ቆሮ.5፡10)። በቤተ እምነት፣ በቡድንና በቤተሰብ ስም ሳይሆን እያንዳንዳችን የምድር አገልግሎትና ሥራችን በእሳት ገና እንደሚፈተን ቃሉ ይናገራል፦ *"...የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋልና"*(2ቆሮ.3፡13)።

ቤተ ክርስቲያን ከተጠያቂነት በላይ አይደለችም። ከላይ እንደተመለከትነው በጆን ዊክልፍ ላይ ቤተ ክርስቲያን ያደረገችው አሰቃቂና ኢሰብዓዊ ድርጊት ዋና ዓላማ የፕሮቴስታንትን ተሐድሶ ለማምከን ቢሆንም አልተሳካም። የእግዚአብሔር ቃል ሁሉንም አሸንፎአል። እንዲሁም በኢትዮጵያም ምን ያህል የተቀነባበረ ሤራ፣ የማሳደድ፣ የመግደልና የሙትን አጽም እስከ ማውገዝ የተሐድሶ ጥያቄ ይዘው በተነሡት ላይ ቢበዛም ኢየሱስ ክርስቶስ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በዘመናችን በመንፈሱና በቃሉ ያድሳታል። መልዕክተኛውን እንጂ መልዕክቱንና የመልዕክቱን ባለቤት ምንም ማድረግ እንደማንችል እንወቅ። ማንም ሊቋቋምመው የማይችል የቤቱ ራስ የሆነው ኢየሱስ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶን በዘመናችን እውን ያደርጋል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ቀጠሮ ላይ ደርሰናል።

፫

የዘመናችን የተሐድሶ እንቅስቃሴ

"የፐሮቴስታንት ቅጥረኞች"

የዚህ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ እንቅስቃሴ መቀጣጠል የተጀመረው በ1950 ዓ.ም ገደማ እንደሆነ ይነገራል። በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ ሥርዓት ለማደስ ከተነሡት ሊቃውንት መካከል መምህር መሠረተ ስብሐት ከዋነኞቹ አንዱ ነበር።[105] በሀገራችን አንዳንድ ታሪክን አዛብተው የተረዱና የሚያስረዱ ሰዎች *"የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ"* የሚል ስም በተነሣ ቁጥር ቶሎ ብለው ተሐድሶ ከጀርመናዊው ማርቲን ሉተርና የእንቅስቃሴው ውጤት ሆነው በዓለማችን ላይ ከተገለጡት ፕሮተስታንት አብያተ ክርስቲያናት ጋር ብቻ አያይዘው ለመተንተን ይጣደፋሉ። በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች መምሪያ "የተሐድሶ መናፍቃን ዘመቻ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ" በሚል ርዕስ *"በማህበረ ቅዱሳን ዶክመንቴሽን ክፍል"* የተዘጋጀው መጽሐፍ፡-

[105] *ከሣቴ ብርሃን፣ ቁጥር 3፣ 2004 ዓ.ም ገጽ 23*

ከማርቲን ሉተር በፊት በአገራችን በቀደመችው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተነሣውን ተመሳሳይ የተሐድሶ ጥያቄ በመዝለል *"ተሐድሶን በሀሳብ ፀንሶ በነቢብ ወልዶ በገቢር ያሳደገው መነኩሴ የነበረውና ቆቡን የጣለው ጀርመናዊው ማርቲን ሉተር ነው"*[106] በማለት ታሪክን ያላገናዘበ ውሸት በድፍረት ከነገረን በኋላ በአገራችን የተነሣው ዘመን ጠገብ የተሐድሶ ጥያቄ ትናንት ፕሮቴስታንትን ተከትሎ የመጣ አድርገው ሌላ ውሸት እንዲህ አቅርበዋል፡-

> *ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን 'ቤተ ክርስቲያናችን ያረጀች ያፈጀች ስለ ሆነች ተሐድሶ ያስፈልጋታል፣ ተሐድሶውንም የምንፈጽመው እኛው ልጆቿ ነን' በማለት <u>የፐሮቴስታንቱ ቅጥረኞች በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ተመሳስለው ገብተው የፐሮቴስታንቱን ዓላማ ለማሳካት በመሯሯጥ ላይ ይገኛሉ።</u>*[107]

እንዲሁም ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌም ከፐሮቴስታንት በፊት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተነሣውን የተሐድሶ ጥያቄ ዱካውን በማጥፋት አሁን ስላለው የተሐድሶ ጥያቄ ከእውነት የራቀ ተረት እንዲህ አስቀምጠዋል፡-

> *የመጨረሻው ግብ ደግሞ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን በ"ተሐድሶ" <u>ሰም የፐሮቴስታንቲዝም ገባር ማድረግና ማጥፋት ነው</u>*[108] ብለዋል።

በኢትዮጵያ ያሉ አብዛኛው የፐሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ለማደስ እንጂ ለማጥፋት በመጡት ሚሲዮናውያን አልተመሠረቱም። በአብዛኛው የፐሮቴስታንት (የወንጌል አማኞች) የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን የማጥፋት ዓላማ ሳይኖራቸው የተሐድሶ ጥያቄ በተነሣ ቁጥር በተለይ በአንዳንድ የኦርቶዶክስ ጸሐፊዎች ዘንድ ፕሮቴስታንት የተባሉ ሁሉ ስማቸው በአሉታዊ መነሣቱ የፐሮቴስታንት ፍርሃት (ፕሮቴስታንት-ፎቢያ) ይመስላል። በታሪክ፣ በዕድሜ፣ በሀብት፣ በሰው ብዛት፣ በዓለማችን ገናና ከሆኑት አብያተ ክርስቲያናት አንዷ የሆነች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የመቶ ዓመት ሕፃን የሆኑ ፕሮቴስታንቶችን ትፈራለች ተብሎ ባይታሰብም አንዳንዶች ግን በኦርቶዶክስ ስም ያልበሰለና የወረደ አሳብ መወርወራቸው መልካም አይደለም። ሊዘነጋ የማይገባው ጉዳይ ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ የፐሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ሳትወለድ ቢያንስ ከስድስት ምዕተ ዓመት የቀደመ መሆኑ ነው። እውነተኛ ተሐድሶ የቃሉ ጥያቄ እንጂ ለሰዎች የመሠረታቸው የቤተ እምነቶችና ዶግማ የበላይነት የሚሰበክበት እንዳልሆነ መታወቅ አለበት። እውነተኛ ተሐድሶ ከእግዚአብሔር፣ ለእግዚአብሔር ሕዝብ፣ ለእግዚአብሔር ክብርና ለዓለም በረከት የሚሰጥ ስጦታ ነው።

[106] *የተሐድሶ መናፍቃን ዘመቻ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ፣* 2003 ዓ.ም ገጽ 13
[107] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 13*
[108] *ሐመር ተዋሕዶ (ልዩ እትም)፣ ነሐሴ* 2002 ዓ.ም ገጽ 85

የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ የእግዚአብሔር ጉዳይ እንጂ የኦርቶዶክስ፣ የካቶሊክና የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ጉዳይ ብቻ አይደለም። ከእርስ በርሳችን ይልቅ ወደ ችግሮቻችን ዒላማችንን ብናነጣጥር ያዋጣናል። ካልሆነ ግን ለራሳችንም፣ ለዓለምና ለእግዚአብሔርም ሳንሆን ዘመናችን በከንቱ ማለቁ ነው።

የፕሮቴስታንት ተሐደሶ እንቅስቃሴ በዓለም ከመገለጡና ሉተር ከመወለዱ በፊት በዐፄ ያግብ ጽዮን *(1278 – 1286)* እና በደቂቀ እስጢፋኖስ*(1406 - 1421) ዘመን* በኢትዮጵያ ተነሥቶ የነበረውን ተመሳሳይ የተሐድሶ ጥያቄ በኢትዮጵያ በወቅቱ ያልነበሩ የፕሮቴስታንት "ቅጥረኞች" ጥያቄ ነው እንበልን? በዚያ ዘመን በኢትዮጵያ ቀርቶ በዓለም ላይ ያልተወለደ ፕሮቴስታንቲዝም "ቅጥረኞችን" እንዴት ወለደ? እንዲሁም በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተወልደው ያደጉ አለቃ ኪዳነ ወልደ ክፍሌ፣ አለቃ መሠረት ስብሐት ለአብ፣ አለቃ ታዬ፣ ብላቴን ጌታ ኀሩይ ወልደ ሥላሴ፣ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ... ወዘተ ያሉ ቀደምት ደራሲያን በጽሑፎቻቸው የተሐድሶ አስተሳሰብ አራማጆች እንደነበሩ የእነርሱን ጽሑፎች ማንበብ በቂ ነው። እነርሱንስ ምን እንበላቸው? እንዲሁም በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ከነበሩ ስመጥር አስተማሪዎች እንደ የኔታ በየነ ዘውቁጣ እና አለቃ በየነ ዳምጤው እንዲሁም አባ ሀብተ ጊዮርጊስ ያሉ ለተማሪዎቻቸው ትክክለኛውንና የተሳሳተውን አስተምህሮ በመለየት በማስተማር የተሐድሶ ጥያቄ ለቀጣዩ ትውልድም ጥያቄው እንዲሆን የበኩላቸውን ሚና መጫወታቸው መዘንጋት የለበትም።

"የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ልጆች ነን"

የዛሬ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ ከዘመን ወደ ዘመን እየተሸገረ የመጣ ውስጣዊ እንጂ እንደ ባሕር ዛፍ ከውጭ የእንዳልመጣ፣ ትናንት ከመጡ ፕሮቴስታንቶች የተኮረጀ ሳይሆን ትውልድ ከአባቶቹ እንደተቀበለ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በቤተ ክርስቲያኒቷ ተወልደውና አድገው ለአገልግሎት የበቁት ቅዱሳን ከአባቶቻቸው ተላልፎላቸው አንግበው ስለተነሡት የተሐድሶ ጥያቄ የሚሉትን ከራሳቸው እንስማ።
ዲያቆን ያሬድ ወልደ ማርያም ሲናገሩ፦

አሁንም እነዚህ ቤተ ክርስቲያናችንን በመውረር በንጹሕ ሐዋርያዊ መሠረቷ ላይ እንደ ኩይሳ የተከመሩባት የኑፋቄ ትምህርቶች መስተካከል እና መታረም አለባቸው እንላለን። ይህንን ደግሞ የምንለው ከሉተር ቀድተነው ሳይሆን ከአባ እስጢፋኖስ ተምረነው ነው። ...ስለዚህ እንዳንዶች እንደሚሉት የሃይማኖት ነፃነት ስለተገኘ ወይም ኢሕአዴግ ከመጣ ድንገት የተወለደ አለበለዚያም ከሉተር የተቀዳ ሳይሆን ከአባ እስጢፋኖስ የተወረሰ በልባችንም የተነሣና የኖረ (የደረጀ) ጥያቄ ነው። እንደምትሉትም መጤና የነጮች ተጽዕኖ ያረፈበት አይደለም[109] ብለዋል።

[109] *የማኅበረ ቅዱሳን የወቅቱ ዘመቻና የፈጠራ ሠነዱ፣ 2004 ዓ.ም ገጽ 15*

አባ ተስፋ ማርያም ስለዚህ ሲናገሩ፦

በመጀመሪያ እኛ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ልጆች ነን፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ የክህነት አገልግሎት ውስጥ ተሳታፊ የሆንን የቅኔ፣ የዜማ፣ የቅዳሴ የአቋቋምና የመጽሐፍት ፍቺ በመማር ያሳለፍን ቤተሮች ነን እንጂ ከሌላ ሥፍራ የመጣን አይደለንም። በቤተ ክርስቲያኗ በቅስና፣ በዲቁና በመሪጌታነት በተለያየ የአገልግሎት ዘርፍ ያለን፣ በአርባ ቀንና በሰማኒያ ቀን የተጠመቅን ክርስቲያኖች እንጂ "ማህበረ ቅዱሳን" እንደሚያስወሩት የፕሮቴስታንቶች ቅጥረኞች አይደለንም፣[110] በማለት በማህበረ ቅዱሳን የደረሰባቸውን ውንጀላ በገሃድ ተቃውመዋል።

በዘመናችን በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ አንግበው የተነሡ የኦርቶዶክስ አገልጋዮች እንጂ ፕሮቴስታንቶች እንዳይደሉ ምስክርነታቸውን በገሃድ በመናገር ላይ ይገኛሉ። ዛሬም ትውልዱ ይዞት የተነሣውን የቆየውን የተሐድሶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ ከመመለስ አቅጣጫን ለማሳት የፕሮቴስታንት "ቅጥረኞች" ናቸው ማለት ብቻ በቂና ሚዛናዊ መልስ አይደለም። መላውን አፍሪካ ሲያምስ የነበረው ፈላጭ ቆራጩ የሊቢያ መሪ ጋዳፊ ሕዝብ ፈንቀሎ ወደ አደባባይ ወጥቶ ሥልጣኑን እንዲለቅ ሲጮህ የቢቢሲ ጋዜጠኛ ለጋዳፊ፦ *"ሕዝቡ አንተን እየተቃወመ ስለሆነ ሥልጣን ለምን አትለቅም"* ሲለው ጋዳፊም፦ *"ሕዝቡ እኔን እየደገፈ የእናንተን የምዕራባውያን ጣልቃ ገብነት እየተቃወመ ነው"* በማለት ለትክክለኛ ጥያቄ ያልተገባ መልስ በመስጠት ለመሸወድ ብሞክርም ከአሳዛኝ ሞት ራሱንና ቤተሰቡን ማስመለጥ አልቻለም። ይህም የሕዝቡን ጥያቄ አቅጣጫ የማሳት አደገኛ አካሄድ በአፍሪካ ቤተ ክርስቲያንና ቤተ መንግሥት የተለመደ መሆኑን ያመለክታል። በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ዘለቅ የሆነ የተሐድሶ ጥያቄ በተነሣ ቁጥር ፕሮቴስታንታዊ አድርጎ ዱካውን የማጥፊት አካሄድ ከእንግዲህ አይቻልም። ማንም ሊክድ የማይችለው እውነት *"የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ያስፈልጋታል"* የሚል ድምፅ በግልና በተደራጀ መልኩ በምድራችን ከመቼውም ጊዜ ይልቅ በማስተጋባት ላይ እንዳለ የአደባባይ ምስጢር ነው። በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአገልግሎት ላይ እንዳሉ የሚናገሩ አገልጋዮች ቤተ ክርስቲያናቸው በምን ላይ ተሐድሶ ማድረግ እንዳለባት ለሕትመት በበቁት ቱባ መጻሕፍት በግልጽ ጥያቄያቸውን ከማቅረብ አልፈው በተለያየ መንፈሳዊ አገልግሎቶች ተዋቅረው ለቤተ ክርስቲያናቸው ተሐድሶ የበኩላቸውን አዎንታዊ ሚና በመጫወት ላይ እንደሚገኙ የታወቀ ነው።

በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዲቁናን፣ ቅስናንና መምህርነትን ተቀብለው በአገልግሎት እንደተሰማሩ በሚናገሩት አገልጋዮች በተሐድሶ ላይ ከተጻፉ ከብዙ መጻሕፍት መካከል *"ኦርቶዶክሳዊነት እንዲህ ነው"*፣ *"በውኑ በማርያም ማመን ይገባልን?"*፣ *"ገድል ወይስ ገደል"*፣ *"ከመጋረጃው ጀርባ"*፣ *"መጽሐፍተ ኑፋቄ"*፣ *"አካልና ጥላ"*፣ *"ሰፊ"*፣ *"ክርስቶስ ታቦታችን"*፣ *"የተቀበረ መክሊት"*፣ *"የለውጥ ያለህ"*፣ *"የዘመናት እንቆቅልሽ ሲፈታ"*፣ *"መስተበቁዕ ዘመታን"*፣ *"ማሣቀል"* ወዘተ የሚሉት ይገኙበታል።

[110] *ስማቱ ብርሃን፣ ቁጥር 3, 2004 ዓ.ም ገጽ 23*

በተቃራኒው ደግሞ ተሐድሶ የሚለውን ቃል እንደ ጦር የሚፈሩ፣ ስለተሐድሶ የሚያነሣውን ሰው ሁሉ በማብጠልጠልና በአሉታዊ መልኩ አሳቡን አጣመው ማቅረብን እንደ ትልቅ አገልግሎት የቆጠሩ ቡድኖች በአገራችን ነበሩ፤ ለጊዜውም ቢሆን ይኖራሉ። አንድ ማወቅ የሚገባን እውነት ተሐድሶ የሰው ጉዳይ ሳይሆን የቤቱ ራስ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤቱ ያለው የዘመኑ አጀንዳ መሆኑን ነው። ስለዚህ የሮማው ማኅበተምና የወታደሮች ጥብቅ ጥበቃ የክርስቶስን መነሣትና የድንጋዩን መፈንቀል መግታት እንዳልቻሉ ሁሉ በ21ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እየተቀጣጠለ ያለውን የተሐድሶ እሳት ማንም ሊያጸፍን አይችልም።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ካልታደሰች የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የመሠረተ ልማት፣ የትምህርት፣ የአገር ገጽታ ሕዳሴ መልዕ አይሆንም የሚል እምነት አለኝ። ለኢትዮጵያ ሕዳሴ ሕዝቡ ከመንግሥት ጋር በመያያዝ በትጋት በመሥራት ላይ እንዳሉ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው የናዝሬቱ ኢየሱስ አካሉ የሆነቸውን የምድራችንን ቤተ ክርስቲያን በቃሉና በመንፈሱ ሊያድስ እየሠራ እንደሆነ መንፈሳዊ ዓይኑ ለተከፈተ ሰው ሁሉ ገሃድ የወጣ እውነት ነው። የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ አጀንዳ የግለሰቦች፣ የቡድኖችና የመንግሥት አጀንዳ ሳይሆን የክርስቶስ አጀንዳ ነው።

ቤተ ክርስቲያን የሰዎች የጠረጴዛ ዙሪያ ክርክር ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ ውጤት ካልሆነች ተሐድሶዋም በዚያ መንገድ አይሆንም። የክርስቶስ የዘላለም አጀንዳው ወንጌል ሲሆን በወንጌል ፊት የተደቀኑ የሰው ሥርዓትና ወጎች እንዲሁም እውነትን የጋረዱ ትውፊቶችን ለማስወገድ በእኛ ይጠቀማል እንጂ እኛን አያማክረንም። ለጌታ እጃችንን ብንሰጥ መሣሪያዎቹ ያደርገናል፤ መንገዱ ላይ ብንቆም ግን ጉዳታችን አስደንጋጭ ይሆናል። ከሁሉ የከፋው ጉዳት እኛን ለእኛው አሳልፎ ትቶን መሄድ ነው። በራሷ ሃይማኖታዊ ሥርዓትና ቅደም ተከተል ተጣብቃ ጌታን ቸል ስትለው ትቶዋት እንደ ሄደ እንደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ትቶን እዳይሄድ (ማቴ.24:1) መጠንቀቅ ነው። ከራሳችን በላይ ቃሉንና መንፈሱን እንስማ። በቤተ ክርስቲያን ለሚነሣው ፈርጀ ብዙ የተሐድሶ ጥያቄዎች መልሱ ወደ እግዚአብሔር ቃል መመለስ እንጂ ምክንያተ ብዙ መሆን አይደለም። የራሳችንን ችግር በወጉ በማጤን፣ ከስሜታዊነት ነጽተን፣ ቃሉን መሠረት በማድረግ፣ ጸጋውን ተደግፈን የመፍትሔ እርምጃ በእምነት መውሰድ እንጂ ለራስ ችግር ሌላውን ተጠያቂ ማድረግ ችግሩን ቢያባብስብን እንጂ ከችግሩ የመውጫ መንገድ ሊሆነን አይችልም። *"የጠቢብ ዓይኖች ወደ ራሱ ነው"* የተባለው ለዚህ ነውና።

በዐሜ ያግብ ጽዮን ዘመን ከተነሣው የታሐድሶ ጥያቄ ከ718 ዓመት በኋላ፣ በደቂቀ እስጢፋኖስ ዘመን በአሰቃቂ ግድያ ከተጠናቀቀው የተሐድሶ ጥያቄ ከተነሣ ከ583 ዓመት በኋላ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዛሬም የተሐድሶ ጥያቄ ቀዳሚ ጥያቄ እንደሆነ መጻሕፍት፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦችና የተለያዩ ድህረ ገጾች ያስተጋባሉ። መጋቢ ጥበቡ ሰሎሞን *"ኦርቶዶክሳዊነት እንዲህ ነው!"* በሚል መጽሐፋቸው፦

ቤተ ክርስቲያኗ የለበው አስተምህሮ ልትይዝ ይገባል። በኋላ የመጣላትን ስህተት የተቀበለችውን ቤተ ክርስቲያናችን በንስሐ እንድትመለስ ወንጌል በአውደ ምሕረታችን በሥልጣን ገብቶ ሥፍራ ይያዝ ምዕመናን በቃለ እግዚአብሔር ይታጠቁ! ቤተ ክርስቲያናችን ትጠናከር የሚሉ ቅንአተቤተ ክርስቲያን የበላቸው በርካታ የቤተ ክርስቲያን መነኮሳት፣ ቄሳውብት፣ ዲያቆናት ምዕመናን ሁሉ ተነሡ። ነገር ግን ክፉዎች ነግሠው ብዙዎችን አሳደዱ፣ ገደሉ፣ መጽሐፍ ቅዱስን አቃጠሉ፣ የስም ማጥፋት ዘመቻውንም አጧጧፉ። ይሁን እንጂ ጥያቄው እየሰፋ እንቅስቃሴውም እየጎለበተ ከመንበረ ፓትሪያርክ እስከ አዲስ አጥቢያ ድረስ ተዳርሷል።[111] በማለት የተሐድሶ ጥያቄ የሁሉን ደጅ በማንኳኳት ላይ እንደሚገኝ ለማመልከት ጥረዋል።

ጥያቄው ምን እንደሆነ ከዚህችው የዕድሜ ባለጠጋና የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እናት ከሆነችው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተወልደው፣ አድገው፣ ተምረው ለአገልግሎት የበቁና ዛሬም የእርሷ ልጆች እንደሆኑ ከሚናገሩ መካከል "ከሣቴ ብርሃን ስብከት ወንጌል ዘኢትዮጵያ" አገልጋዮች በጽሑፎቻቸው በገሃድ ይናገራሉ። "ብሔራዊ ተሐድሶ" በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጽሔት ባሉበት ቤተ ክርስቲያን ትልቁ የተሐድሶ ጥያቄያቸው ምን እንደሆነ ሲገልጹ፦

ተሐድሶአውያን የሚጠይቁት ዋና ጥያቄ ቤተ ክርስቲያናችን ክርስቶስን አጉልታና አብዝታ በመስበክ ሰው ሁሉ ድነትን ያግኝ የሚል አንጂ ከዚህ የተለየ ነገር የለም[112] ይላሉ።

እነርሱ እንዳሉት ጥያቄው ኢየሱስን መስበክ ከሆነ ክርክሩ ከየት መጣ? የቤተ ክርስቲያን መሥራችና ራስ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን ሲልክ *"ወደ ዓለም ሂዱ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" (ማር.16:15)* ሲል ሐዋርያው ጳውሎስም *"እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስ እንሰብካለን" (1ቆሮ. 1:23)* በማለት የቤተ ክርስቲያን ቀዳሚ አጀንዳ የወንጌል ስብከት እንደሆነ አስታውቋል። ከወንጌል ስብከት የሚበልጥ ቤተ ክርስቲያንን በምድር የሚያኖራት አጀንዳ ምንም የለም። ታዲያ ቤተ ክርስቲያኒቷ ወንጌልን እየሰበከች ከሆነ የተሐድሶ ጥያቄ አንግበው እንደተነሡ የሚናገሩ ልጆቿም ጥያቄያቸው የወንጌል ይሰበክ ከሆነ ጥል፣ ውግዘትና ስም የማጥፋት ዘመቻውን ምን አመጣው? ዓለም እየጠበቀቻችሁ አለና ጠብ፣ ክርክርና ጥላችን አስወግዳችሁ በሰላም ወንጌል ሰላም በመመሥረት በክብርና በኃይል የመጨረሻውን መከር ለመሰብሰብ ይህ ዘመናችሁ ነውና እባካችሁን ንቁ! የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን በዚህ ዘመን እግዚአብሔር በትልቅ ክብር በወንጌል ለወንጌል እንደሚያስነሣት አምናለሁ።

ዛሬ ተሐድሶን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ወይም በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በወንጌላውያን አማኞችም ዘንድ ዐቢይ ርዕሰ ጉዳይ ያደረገው መንፈሳዊነትን ተላብሶ ዓለማዊነትና ሥጋዊነት በቤተ ክርስቲያን እየተዛመተና እውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል በሰዎች ልምምድና ቤተ ክርስቲያናዊ ባሕል እየተቀየረ በመምጣቱ ነው። የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ

[111] ጥበቡ ሰሎሞን (መጋቢ)(*1999 ዓ.ም*)፣ *ኦርቶዶክሳዊነት እንዲህ ነው!* ገጽ 172
[112] ብሔራዊ ተሐድሶ፣ 1ኛ ዓመት ቁጥር 1፡ ጎንደር 2004 ዓ.ም ገጽ 7

እንደ ቃሉ ያልሆኑ ብዙ ተሐድሶ የሚያስፈልጋቸው ነገሮች በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እንዳሉ ያምናል። ይህን ዘመን ጠገብ ጥያቄ እንዳይመለስ ቤተ ክርስቲያን አሉታዊ እርምጃ በመውሰድ ታሪካዊ ስህተት እንዳትፈጽም፣ በባለራእይነት ዓይን አሻግራ ማየት እንድትችልና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ በመስጠት ወንጌልን ለዓለም በማድረስ ዋና ተልዕኮዋ ላይ እንድታተኩር የሁላችንም ጸሎት ይሁን።

የአብያተ ክርስቲያኒት አንድነትና ልዩነት

ዳንኤል ተሾመ *"የቅርብ ዘመኑ (1979-1999) የተሐድሶ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን"* በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ባደረጉት ጥናት ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር አንድ ስለሚያደርጋት መሠረተ እምነት ሲገልጹ፡-

> *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን አዳኝነትም ሆነ መድኃኒትነት የምትቀበል፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነው የአሐዱ አምላክ በሦስት አካል መገለጥ (ሥላሴ) አስተምህሮ የምታምን መሆንዋን እንዲሁም በብሉይና በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት (መጽሐፍ ቅዱስ) የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ የምታምን፣ ደግሞም ሦስቱን ዓለም አቀፍ የሆኑ የሃይማኖት መግለጫዎች (አመክንዮታት) (የሐዋርያት፣ የኒቂያና የአትናቴዎስ) የተቀበለች መሆኗ የመሠረት ችግር እንደሌለባት ያመለክታል*[113] ብለዋል።

ዳኅስ ያሉ መጻሕፍት ደራሲ (ቀደሰ) ዓለማየሁ ሞገስ ደረሶ *"አንድ እረኛ አንድ መንጋ"* በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፋቸው ስለ እነዚህ የሃይማኖት መግለጫ (አመክንዮታት) ሲናገሩ፡-

> *እነዚህን አመክንዮታት የሚቀበል ሁሉ ክርስቲያን ነው፣ ስለሆነ የቀረው ችግር ሁሉ በክብ ጠረጴዛ ውይይት፣ መሪዎች ሰላም፣ ከፈለጉ ሊፈታ ይችላል፣*[114] ካሉ በኋላ በዚሁ መጽሐፋቸው *"ክርስቲያን የሚባሉ(ና) ያለመለያየት አብረው መኖር የሚገባቸው"* የግሪክ ኦርቶዶክስ፣ የአሪንታል ኦርቶዶክስ፣ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንና ከሉተር ጀምሮ ያሉት ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ናቸው[115] ብለዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የራስዋ የሆኑ ብዙ ትውፊቶችና ሥርዓቶች ቢኖሯትም እ.ኤ.አ በ1948 በተቋቋመው *"የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር"*[116] አባል፣ እንዲሁም እ.ኤ.አ በ1963 የመላ

[113] ዳንኤል ተሾመ፣ 2004 ዓ.ም ገጽ 50-51
[114] ዓለማየሁ ሞገስ ደረሶ (ቀደሰ) (1989 ዓ.ም)፣ "አንድ እረኛ አንድ መንጋ"፣ ገጽ 106
[115] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 179-180
[116] የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የአንድነታቸው ዋና ዓላማ It arose out of the ecumenical movement and has as its basis the following statement *he World Council of Churches is a fellowship of churches which confess the Lord Jesus Christ as God and Saviour according to the*

አኅጉሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ሲመሠረት የድርጅቱ መሥራች አባል መሆኗ በክርስቶስ ኢየሱስ ከሌሎች ጋር ያላትን አንድነት ለማመልከትና ወንጌልን ለዓለም አብሮ ለማድረስ እንደሆነ ለማንም ግልጽ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የ2000 ዓመታት ታሪክ የተዘከረበት መጽሐፍ ስለ ዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ዓላማ እንዲህ ይገልጻዋል፡

> *ዓለማና ተግባሩም ምስጢረ ቁርባንን በአንድነት ለመፈጸም እስከሚቻል ድረስ አባል <u>አብያተ ክርስቲያናት ስለ እምነት አንድነት የሚያደርጉትን ጥረት ማበረታታትና የክርስትናው ዓለም አንድነቱን በተግባር እንዲያሳይ ማብቃት ነው</u>።(መስመሩ በኔ)... የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዚህ ድርጅት መሥራች አባል ስትሆን አሁንም በአባልነቷ እንደጸናች ትገኛለች።*[117] *በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የታቀፉት አብዛኛው የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት፣ ከፕሮቴስታንቶች አንግሊካን፣ ሉተራን፣ መቶዲስት፣ መዋመቃውያን፣ ፕራስበተሪያን፣ የፔንተኮስታል፣ አንዳንድ የቆዩ የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ወዘተ..ናቸው።*[118]

ከሮማ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በቀር የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር በ150 አገራት ከሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የተሰባሰቡ ሲሆን በአጠቃላይ ከ500 ሚሊዮን በላይ አባላትን ይዟል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአህጉርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ባሉት የአብያተ ክርስቲያናት ማኅበራት ከፕሮቴስታንቶች ጋር እጅ ለእጅ ተያይዛ መቆሟ ትልቅነቷንና ለአንድነት ያላትን ልብ ያሳያል። አንዳንድ የአገሬ የኦርቶዶክስ ጸሐፊዎች ቤተ ክርስቲያናቸው ከፕሮቴስታንት ጋር አንድ የሚያደርጋት ቀርቶ ፕሮቴስታንቶችን እንደ ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን *"ፀረ ማርያም"* የሚል ዘመን ዘለቅ የውግዘት ስሌዳ ማሸከማቸው የተለመደ ነው። አንዳንድ ያላዋቂ ደፋር ጸሐፊዎች ደግሞ ፕሮቴስታንቶችን *"ሰይጣን"* እስከማለት ደርሰዋል። ትልቁ ችግራቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የመረዳት ድሃ መሆናቸው ነው። እግዚአብሔር ዓይናቸውን ያብራ። በፕሮቴስታንትም ወገን አንዳንድ ጽንፈኞች የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምንም እውነት እንደሌላትና የጠፋች እንደሆነች የሚናገሩና የሚጽፉ አይታጡም።

ይህ ትልቅ ስህተት ብቻ ሳይሆን አንድ እምላክ እየጠራንና አንድ ወንጌል እንሰብካለን እያልን የጐሪጥ የምንተያይ ምስኪኖች አድርጎናል። ዋናው ኦርቶዶክሳዊነትና ፕሮቴስታንታዊነት ሳይሆን ለዓለም ኃጢአት በሞተልን ጌታ መገኘታችን ለዘላለም አንድ ያደርገናል። እግዚአብሔር የልጁ መንግሥት እንጂ የካቶሊክ፣ የፕሮቴስታንትና የኦርቶዶክስ መንግሥት የለውም። በምድር ወንጌልን በማሮጥ ሊጠቀምባቸው ግን ይችላል። እውነቱ ግን ከልዩነታቸው ይልቅ አንድነታቸው የአደባባይ ምስጢር መሆኑ ነው። በአንድነት ውስጥ ያለውን ልዩነታችንን አውቀን ብንቀባበል፣ መማማርና

scriptures, and there fore seek to fulfil together their common calling to the glory of the one God, Father, Son and Holy Spirit. ይበልጥ ለመረዳት ቀጣዩን ድረ ገጽ ይመልከቱ። *http://en.wikipedia.org/wiki/World_Council_of_Churches*
[117] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከሐዲት እርስቶስ እስከ 2000 ዓ.ም፣ ገጽ 299
[118] http://en.wikipedia.org/wiki/World_Council_of_Churches

መደማመጥ ቢኖር ለዓለም በወንጌል በረከት በሆንን ነበር። እዚሁ ስንናቆር ለዓለም መድረስ ቀርቶ የጠራ ወንጌል ለሕዝባችን ሳናቀብል ቀዳሚ የሆንን እየመሰለን ኋለኞች ሆነናል። በዓለም አቀፍ መድረክ የኦርቶዶክስና፣ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የመያያዛቸው ምስጢር *ዮ"ቀኖና"*[119] ልዩነት ቢኖራቸውም *"ዮዶግማ"*[120] (መሠረተ እምነት) አንድነት እንዳላቸው ስላመኑ ነው። የአንድነታቸው መሠረት በዓለም አቀፍ ደረጃ በአብዛኛው አብያተ ክርስቲያናት ዕውቅና ባገኘው የሃይማኖት መግለጫዎች ላይ ስለቆሙ እንጂ በሁሉም አንድ ስለሆኑና የአንዱን አስተምህሮ ሌላው ሙሉ በሙሉ ስለሚቀበልና ስለተቀበል አይደለም።

በኢትዮጵያ የሚገኙ ፕሮቴስታንቶች እንኳ በቀኖና እጅግ መለያየታቸው ብቻ ሳይሆን ከዛሬ 30 ዓመት በፊት አንዱ የአንዱን ድነት ለመቀበል የሚቸገርና አንዱ የአንዱን እንክን ለመግለጥ ይተጉ እንደነበር የሚታወስ ነው። አሁን እጅ ለእጅ የተያያዙት ከችግራቸው በላይ ያደገ አመለካከትና የወንጌል እውነት ምስጢር ከትናትናው ይልቅ ዛሬ መረዳት ስለበዛላቸው ልዩነታቸው እያለ አንድነታቸውን ለማጉላት የወንጌል እውነት አስገድዷቸው ነው። በዚህ 21ኛ ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፣ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንና በኢትዮጵያ በሚገኙ ፕሮቴስታንቶችም መካከል ያለው አሉታዊ ውጥረትና ትችት ረግቦ በክርስቶስ ኢየሱስ እውነት ተያይዘው ለዓለም በወንጌል መጥለቅለቅ ምክንያት ይሆናሉ። ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ የወንጌል መልዕክተኞችም የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን በመቀበል አብሮ ለመሥራት የፈቀዱበት ዋና ምክንያት ቤተ ክርስቲያኒቷ የመሠረተ እምነት ችግር የለባትም ብለው ስላመኑ ነበር። የክርስትናን መሠረተ እምነት የሚጎዱ የሉልዓቀፋዊነት አሉታዊ ጫና፣ የድህረ ዘመናዊነትና የአንጻራዊነት ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍልስፍና ለመቋቋም አንድ መሠረተ እምነት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ከልዩነታቸው ይልቅ አንድነታቸውን በማጉላት በሕልውናቸው ላይ የመጡ የዘመኑን ተግዳሮቶች አሸንፈው ወንጌልን ለቀጣይ ትውልድ የማቀበል አደጋ ተጋርጦባቸዋል። እየመጡ ያሉት ፈርጀ ብዙ ተግዳሮቶች አንድነትን ውዴታ ብቻ ሳይሆን ግዴታ የማድረግ አቅም አላቸው።

ከላይ የተገለጡትን ሦስቱ ዓለም አቀፋዊ የሆነ የክርስትና ሃይማኖት መግለጫዎችን የሚቀበሉ አብያተ ክርስቲያናት በአንዳንድ የአስተምህሮ ልዩነታቸው ላይ መነጋገር መቻል አንድ ነገር ሆኖ አንዱ ለአንዱ *"መናፍቅ"* ማለት እንደማይችሉ ምሁራን ይናገራሉ። አንዲት ቤተ ክርስቲያን የመሠረተ እምነት ችግር የላትም ማለት አስተምህሮዋ ስህተት አልባ ስለ መሆኑ

[119] *ቀኖና፡- አምልኮተ እግዚአብሔርን ለማካሄድ ወንጌልን ለማሰራጨትና የመሳሰሉትን መንፈሳዊ ተግባራት ለማዘናወን ሲባል የሚወጣ ሥርዓት ነው። ቀኖና ሥርዓት በመሆኑም እንደጊዜው ሁኔታ ታይቶ መሻሻል የሚደረግበት ነው። ዝኒ ከማሁ፣ 17*

[120] *መሠረተ እምነት (ዶግማ)፡- በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የቆመ፣ የሚጨመርበት የሚቀነስለት ወይም እንደ ሁኔታው ታይቶ የሚሻሻል የሌለበት ዘላለማዊ ነው። ዲያቆን አማዛቸው ተፈራ፣ የተቀበረ መክሊት፣ አፍሪካ ማተሚያ ቤት፣ ገጽ 17*

ሞስትና ሊሆናት በፍጹም አይችልም። አብዛኛው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ የመናፍቅ ትምህርት ጥንትም ሆነ ዛሬ በአገራችንና በዓለም ላይ እንደ አሸን በመፍላት ላይ የሚገኘው የመሠረተ እምነት ችግር በሌላቸው አብያተ ክርስቲያን እንደሆነ አንዘነጋ። ዋናው መሠረተ እምነት ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው መሠረተ እምነት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስትምህሮ መመራት የግድ ነው። የአንዲት ቤተ ክርስቲያን መልካም ጅማሬ መልካም ፍጻሜዋን አያመላክትም። በፍቅር የታወቀችና ዝናዋን ሰምቶ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ፍቅሯ የመሰከረላት የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን *(ኤፌ.1:16)* ከ45 ዓመት በኋላ ኢየሱስ ፍቅርን ጥላ እንደወደቀች ሲመሰክርባት፡-

> *"ዳሩ ግን የምንቅፍብህ ነገር አለኝ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና። እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውን ሥራህን አድርግ አለዚያ አመጣብሃለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከሥፍራው አወሰዳለሁ" (ራእ.2:5)።*

እንዲሁም ክርስቶስ በዓይናቸው ፊት እንደ ተሰቀለ ተሥሎ የነበረው የገላትያ ቅዱሳን 30 ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ክርስትናቸው አዚም *(የሚያፈዝ ወይም የሚያደነግዝ መተት አስማት)*[121] እንደሆነባቸው (ገላ.3:1) እና ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቀደመው መንገድ ሊመልሳቸው *"ልጆቼ ሆይ ክርስቶስ በእናንተ እስኪሣል ድረስ ዳግመኛ ስለ እናንተ ምጥ ይዘኛል" (ገላ.4:19)* በማለት ይናገራል። ቤተ ክርስቲያን እንደተቀበለችው ቃል ዕለት ዕለት መራመድና ፍሬ ማፍራት በመቻሏ፣ የቃሉን እውነት በማስተማር ደቀ መዝሙር በማድረግ አቅሟ፣ ወንጌል ያልሰማውን ዓለም በወንጌል ለመድረስ ባላት የሚሊዮናዊነት ራእይ፣ ስለ ክርስቶስ መከራን ለመቀበል ባላት ዝግጁነትና በክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል በመኖር ባላት ምሳሌነትና ፍሬ ትመዘናለች። ከወንጌል ማህፀን የተወለዱ፣ ትናንት በዓለም አቀፍ ደረጃ ድንበር ዘለል የወንጌል ሚሲዮናውያንን በመላክ ለሚሊዮኖች የመዳን ምክንያት የነበሩ፣ ዛሬ በደርጅታዊ መዋቅራቸው ጥንካሬና በትናንትና ስም ያለ ቅጥ የሚደገፉና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሙት ሆነው ክርስቶስ ሳይሆን በክርስቶስ ስም ክሂደት የሚሰበክባቸው አብያተ ክርስቲያናት እጅግ ብዙ ናቸው። ወደ ቀድሞው ክብራቸው ለመመለስ ተሐድሶ ብቸኛ መንገድ ነው። አገራችን ኢትዮጵያ አሁን ለቆመችበት መልካም የዕድገት መሠረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአንበሳ ድርሻ ብትወስድም ተሐድሶን እንቢ በማለቷ ለቀጣዩ ዕድገትና ብልጽግና ሳታውቅ እንቅፋት ሆናለች።

ዕድሜ ጠገብ ሆኖ ያልታደሰው ክርስትናችን እንደ አገር ላለንበት ኋላ መቅረት፣ ድህነት፣ ጥላቻና ጠባብነት ዋና ምክንያት ነው። በቃሉና በመንፈሱ ላለመታደስ በኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያቶች ዋሻ የተደበቀውና በአብዛኛው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምምድና ትውፊት የተተበተበው ክርስትናችን ከእግዚአብሔር እውነት ያራቀንና ለአገራዊ ዕድገትም ብርቱ ሞጋች እንደሆነብን በቀጣዩ ምዕራፍ እንመልከት።

[121] *የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ (1993 ዓ.ም)፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ገጽ 333*

፭

ያልታደሰው "ክርስትናችን" የዕድገታችን ሞጋች

"ለእነዚያ ደግሞ እንደ ተነገረ ለእኛ የምሥራች ተሰብኮልናል፣ ዳሩ ግን የሰሙት ቃል ከሰሚዎቹ ጋር በእምነት ስላልተዋሐደ አልጠቀማቸውም።" (ዕብ. 4:2)

እ.ኤ.አ 2007 በኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን ይፋ በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ ውጤት የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሕዝብ፡- *"73,750,932 ሲሆን ከዚህም፡ 62.8% ያህሉ ክርስቲያኖች፣ ከዚህም ኦርቶዶክሳዊያን 43.5% ወንጌላዊያን (ፕሮቴስታንቶች) ደግሞ 18.6% እንዲሁም ካቶሊካዊያን 0.7% የሚሆነውን ድርሻ ይይዛሉ"*[122] በማለት ገልጾአል። ምንም እንኳን የፕሮቴስታንቶች ዕድገት ከ10 ዓመት በፊት 11% ከነበረው አሁን ትልቅ ዕድገት ላይ እንዳለ ቢያመለክትም የኢትዮጵያን ክርስትና የሕዝብ ብዛት ዕድገት ወንጌል ወደዚህች ሀገር ከገባበት ከአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንጂ በወንጌላውያን የ100 ዓመት ዕድሜ ፍጹም መለካት የለበትም የሚሉ ምሁራን ጥቂት አይደሉም። ከአፍሪካ፣ ከአውሮፓ፣ ከሩቅ ምሥራቅ አገሮች፣ ከአሜሪካና ከላቲን አሜሪካ ቀድማ ወንጌልን ከተቀበለች 2000 ዓመታት ባስቆጠረች ሀገር ዛሬም ወንጌል በእርሷ ውስጥ ላሉት ብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ባዕድ መሆኑ ያስገርማል።

[122] *2007 Ethiopian census, first draft, Ethiopian Central Statistical Agency*

አገራችን ከሁሉ ቀድማ ወንጌል ብትቀበልም ዘግይታም ቢሆን ያቆየችውን የወንጌል መልዕክት ለሌላው ዓለም ማቀበል ለምን አልቻለችም? ብዙ አገራት ክርስትና ለሕይወት ለውጥ፣ ብርቱ ሠራተኛ እንዲሆኑና ለአገራቸው ሁለንተናዊና ፈጣን ዕድገት ጉልህ ድርሻ እንዳበረከተ ሲመሰክሩ ለእኛ እንደ ዕድሜው ለምን አልጠቀመንም? ለሚለው ጥያቄ የሚከተሉትን ምክንያቶች ማስቀመጥ ይቻላል።

ታሪክ በትክክል የሚጻፈው ነፃነት በለፈነበት አገር ብቻ ነው።
የፈረንሳይ ፈላስፋ ቮሊቴር 1737

ክርስትናችን ራስ ተኮር መሆኑ

የኢትዮጵያ ወንጌላውያንን የመቶ ዓመት ዕድገት ከደቡብ ኮሪያ የመቶ ዓመት ቤተ ክርስቲያን ዕድገት ጋር ብናነጻጽረው ዕድገታችንን እንዴት እንገመግማለን? በተለይ ያለፉት 21 ዓመታት ኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ምቹና አንጸባራቂ የዕድገት ዘመን ነበር። እኛ ኢትዮጵያውያን ራስ ተኮር ባንሆን፣ በመከፋፈል መባዛት ሥራ ላይ ባንጠመድና ውስጣዊና ውጫዊ ዕይታዎቻችን ሚዛናዊ ቢሆኑ ዓለምን በወንጌል ለመድረስ የጌታ መሣሪያዎች በሆንን ነበር። በእርስ በርስ መወነጃጀልና በፍርድ ቤት ሙግት የባከነ የሰው፣ የገንዘብና የጊዜ ኃይል ለወንጌል ስርጭት ቢውል ኖሮ ከዚህ እጥፍ ዕድገት ሊገኝ እንደሚችል ብዙዎች በቁጭት ይናገራሉ። አሁንም ሌላ ጊዜ ተሰጥቶናል። ቁጭታችንን በሚበልጥ ሥራ እንወጣ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የባህር ዘለል ሚሲዮናዊ ራእይን ያላሳደገች፣ ከ23 ሚሊዮን በላይ ሕዝቦቿ ገና ወንጌልን በጭራሽ ያልሰሙባት፣ 18.6% የወንጌል አማኞች ብቻ ያሉባት፣

ከ5 ያነሰ ነገረ - መለኮትን በዲግሪ የሚያስመርቁ ኮሌጆችና አንድ የነገረ መለኮት ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ያለባት፣ በአጠቃላይ በዕድሜ ቀድማ በተግባር ከሁሉ ኋላ የቀረች ትመስላለች። በወንጌል የተለወጡ ደቡብ ኮሪያውያን ለመንፈሳዊ ለውጥ፣ አልፎም ለኢኮኖሚያቸው ምጥቀት፣ ለማኅበራዊ ሕይወት መቃናትና ሁለንተናዊ ለውጥ ክርስትና ትልቅ ሚና እንደተጫወተ ሲመሰክሩ የተለያዩ ጥያቄዎች በውስጤ ይፈጠራሉ፡- በኢትዮጵያ ለ2000 ዓመታት፣ በደቡብ ኮሪያ ላለፉት 100 ዓመታት የተሰበከው ወንጌል ልዩነት አለው ወይ? ልዩነት ከሌለው አንድ ዓይነት ባይሆንም ተቀራራቢ ውጤት እንኳ ለምን አላስገኘም?

በቀለ ሻንቆ *"የክርስቲያን ኃላፊነት ሁለንተናዊ ዕድገትን ለማፋጠን"* በሚለው መጽሐፋቸው የምድራችን ክርስትና የተፈለገውን ውጤት እንዳላመጣ ሲገልጹ፡-

ሳታደን ደረጀች ... ...

የጠቀሱት ታቦር ዋሚ "የውገና ድርሰቶችና የታሪክ እውነቶች" በሚለው መጽሐፍ:-

> ያገር ጉልበት አንድነት ነው:: አንድነትም የሚወለደው የጋራ ከሆነው ከቋንቋ፣ ከልማድና ከሃይማኖት ነው:: ስለዚህ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ሉዓላዊነት ለመጠበቅና አንድነቷም ተጠብቆ እንዲቀጥል ለማድረግ ቋንቋችንና ሃይማኖታችን በመሳው በኢትዮጵያ ግዛት በአዋጅ መዘርጋት አለበት:: ይህ ካልሆነ እስከ መቼም ድረስ አንድነት አይገኝም:: በመላው በኢትዮጵያ ግዛት ለሥጋዊና ለመንፈሳዊ ሥራዎች ያማርኛና የግዕዝ ቋንቋዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋዎች ሆነው መታወቅ አለባቸው:: ሌላው ማናቸውም የአረማውያን ቋንቋ ሁሉ እንዲደመሰሰ ማድረግ ያስፈልጋል::[130] እንደ ዶክተር ዓለሜ አሸቴ አስተሳሰብ ኢትዮጵያዊነት በኦርቶዶክስ ክርስቲያንነትና በአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪነት ብቻ የሚወሰን እንደነበር፣ ከዚህ ውጭ ያሉት ሁሉ ኢትዮጵያውያን ሳይሆኑ ተገዢዎች እንደሆኑ፣ ይህንኑ አስተሳሰባቸውን በ1975 ዓ.ም Whose History is Ethiopian History? በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ታሪክ መካነ ጥናት ለተደረገ ስብሰባ እንዳቀረቡ አስረድተዋል:: ታቦር ዋሚ በዚህ ላይ አሳባቸውን ሲያጠቃልሉ:- ዶክተር ዓለሜ በኢትዮጵያ ታሪክ ስም እስከ ዛሬ ድረስ ተጽፈው የሚገኙት ኢትዮጵያዊነት በኦርቶዶክስ ክርስቲያንነትና በአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪነት ብቻ የተወሰነ ነበረ የተባለው ብዙ የሚያከራክር አይሆንም፣ ምክንያቱም ሲጽፉ የቆዩትን ሁሉ ማየት ይቻላልና ነው[131] ብለዋል::

ዐሚዎች አገራችንን ይገዙ በነበረበት ዘመን መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ተጣምረው በወንጌል ኃይል ሳይሆን በአዋጅና በግዴታ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትናንና አማርኛን ያስፋፉት የአገርን አንድነት ለማስጠበቅ እንደነበር ከላይ የተቀመጠው አሳብ ያስረዳል:: የአገርን አንድነት ማስጠበቅ መልካምና የሚደነቅ አሳብ ቢሆንም አንድነቱን ለማስጠበቅ የተጠቀሙበት መንገድ ትልቅ ስህተት ከመሆኑም አልፎ አሁን ላለንበት ፈርጀ ብዙ ችግሮችና የመንደርተኝነት መንፈስ መንሰራፋት ዳርጎናል:: አንድ ቋንቋና አንድ ሃይማኖት አንድነትን በአንድ አገር ማምጣት እንደማይችልና ልዩ ልዩ ቋንቋ እና ሃይማኖት ብቻውን በአንድ አገር የመለያየት ምክንያት ሊሆኑ እንደማይችሉ ብዙ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል:: አንድ ቋንቋና አንድ ሃይማኖት የአንድነት ምክንያት ቢሆን ኖሮ አንድ ነገድ፣አንድ አገር፣ አንድ ባሕል፣ አንድ ሃይማኖት፣ አንድ ቋንቋ፣ አንድ እሴት ያላቸው ሉማሊያውያን፣ ኢራቃውያን፣ ሶሪያውያንና ሩዋንዳውያን በዓይናችን ፊት የእርስበርስ ደም ባልተቃቡና በዓለም ላይ ስደተኞች ሆነው ባልተበተኑ ነበር:: የአንድነት ጠላት ከቋንቋና ከሃይማኖት ጀርባ የተጠመደ አደገኛ ሀቡዕ በትዕቢት፣ በጥላቻ፣ ራስን የተሻለ አድርጎ የመቁጠር፣ ሌላውን ወደ ታች የመመልከትና ክፋት፣ ቅምና በቀል የተሞላ የሰው ልብ እንጂ የትኛውም ሃይማኖትና ቋንቋ የአንድ አገር አንድነት አደጋዎች አይደሉም::

[130] ታቦር ዋማ (2004 ዓ.ም)፣ የውገና ድርሰቶችና የታሪክ እውነቶች፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 2 ገጽ 576 (Bahru Zewde prof (2005)...: Pioneers of Change in Ethiopia, Finfinnee p. 140)

[131] ዝኒ ከማሁ ገጽ 258

በአብዛኛው ክርስትና በኢትዮጵያ ተሸናፊዎች አሸናፊዎችን ለማስደሰት የሚቀበሉት የግዴታ ሃይማኖትና የገዢዎች የፖለቲካ መሣሪያ ሆኖ እንዳገለገለ እንጂ በእውነተኛ የወንጌል ስብከት ላይ የተመሠረተ ሕይወት ለዋጭ አልነበረም:: ተጨማሪ ተግባራዊ ምሳሌ ካስፈለገ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስም በካፋና በሲዳማ ሕዝቦች መካከል ክርስትናን በወረራ ለማስፋፋት የተደረገውን አደገኛ አካሄድ እንመልከት:-

የኦርቶዶክስ ክርስትና በካፋ

በቀለ ወ/ማርያም አዱሎ "የካፋ ሕዝቦች እና መንግሥታት ሓጭር ታሪክ" በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፍ የካፋ ሕዝቦች ከክርስትናና ከእስልምና ሃይማኖቶች በፊት "ኤቆ" በሚባል መንፈስ ያምኑ እንደነበር ይተርካሉ::[132] ከዛሬ 400 ዓመታት በፊት የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ወደ ካፋ እንደገባም ጽፈዋል::[133] የኦርቶዶክስ ክርስትና እንዴት እንደተስፋፋ ሲናገሩ:-

> ...የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖትም የሰሜን ኢትዮጵያ የገዢ መደቦች ሃይማኖት በመሆኑ አዲስ ወረራ በተደረገባቸው አካባቢዎች ሁሉ በተጽዕኖ ጭምር እንዲስፋፋ መደረጉ ይታወቃል:: በሌላ በኩል ግን ከጥንት ጀምሮ በለሜኑ ክልል የሚገኙና የሥጋት ምንጭ ያልሆኑት ደግም የራሳቸው አምነት ያላቸው የወይጦና የፈላሻ ሕዝቦች የዚህ ሃይማኖት ተከታይ እንዲሆኑ አልተደረገም:: ይህም የሚያመለክተው ገዢው መደብ አባላቱን ያሳሰባቸው የሃይማኖቱ መስፋፋት ሳይሆን ተወራሪውን ሕዝብ በሃይማኖት ተጽዕኖ ጭምር በመጠቀም ለመግዛት እንዲያመቻቸው ማድረግ መሆኑ ነው፣[134] ብለዋል::

በዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ዐቢይ ጉዳይ በኢትዮጵያና መካከለኛው የአውሮፓ ክርስትና ታሪክ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ዘመንና አገር እውነተኛ ክርስትና በወረራ መሰራጨቱን ዕውቅና የሰጠበት ታሪክ የለም:: ኢየሱስ፣ ሐዋርያትና የእምነት አበው ክርስትናን በዓለም ላይ ያሰራጩት አንድን ማኅበረሰብና መንግሥት በመውረር ላይሆን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወንጌልን በመስበክ እንደ ነበር ቃሉ ምስክር ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ማንም በወረራ ክርስትናን እንዲያሰራጭ አያዝም፤ አይፈቅድም:: ማንም በወረራ መልክ ክርስትናን ለማሰራጨት ጥረት ቢያደርግ አድራጊው ክፍል እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና አይጠየቅም:: የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ብትሆን በወረራ ሃይማኖቱን አስፋፋለሁ የሚል ደንብም የሆነ ሕግ እንደሌላት የታወቀ ነው:: የክርስቶስ መንገድ የመስቀል እንጂ የሰይፍ አይደለም:: ክርስትና በዓለም የታወቀው በወንጌል ስብከት እንጂ ለገዢ አካል የፖለቲካ መሣሪያ በመሆን አይደለም:: ክርስትናን በወረራ ማሰራጨትም ሆነ ማስጠበቅ በመጽሐፍ ቅዱስ የተወገዘ ነው::

[132] በቀለ ወ/ማሪያም አዱሎ(1996 ዓ.ም)፣ የካፋ ሕዝቦች እና መንግሥታት ሓጭር ታሪክ፣ገጽ 218

[133] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 222

[134] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 223

የኦርቶዶክስ ክርስትና በሲዳማ

የኦርቶዶክስ ክርስትና በሲዳማ መቼና እንዴት እንደተሠራጨ *"የሲዳማ ብሔር ታሪክና ባሕል"* መጽሐፍ ፀሐይ የተባለን ጸሐፊን ዋቢ በማድረግ፡- *የኦርቶዶክስ ክርስትና ወደ ሲዳማ የደረሰው ወራሪውን የሚኒልክ ሠራዊት ተከትሎ እንደነበርና በሲዳማ ምድር በመጀመሪያ የተሠራው ቤተ ክርስቲያን የሺሻ ማርያም ሆኖ ዘመኑም በ1884 እንደነበር ይናገራል።*[135] ካለ በኋላ የኦርቶዶክስ ክርስትና እንዴት እንደተስፋፋ ደግሞ ሲናገር፡-

> *የሃይማኖቱ አመጣጥም ከነፍጠኛውና ከመልከኛው ሥርዓት ጋር ስለነበርና ሥርዓቱም የሕዝቡን መሬት ወስዶ ጭሰኛና ገባር ባደረገበት ሂደት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አጋር ስለነበረች በሕብረተሰቡ ዘንድ የነበራት ተቀባይነት እምብዛም ነበር። በሌላ መልኩ የኦርቶዶክስ እምነት ሳይለወጥ ሕዝቡ በግድ በአዋጅ እንዲጠመቅ ስላደረገ በወቅቱ ቤተ ክርስቲያኒዋ በነበራት የፖለቲካ ወገንተኝነት ሕዝቡ በተደጋጋሚ አልቀበልም ማለቱ ይነገራል።*[136]

"የሲዳማ ብሔር ታሪክና ባሕል" መጽሐፍ የአንድን አዛውንት ምሬት እንዲህ አቅርቧል፡-

> *ሕዝቡ ልብሶቻቸውን ገፍፈው ወንድና ሴቱን ራቁታቸውን አጥምቀዋቸዋል። ክርስትና ያሰነሡዋቸው ለወንድማዊ አኩልነት ሳይሆን በክርስትና ሰም ሕዝቡን ተከፋፍለው ለማላረስና አገልጋዮች ለማድረግ ነበር። ይህን የተገነዘበው የሲዳማ ሕዝብ ከጣሊያን በፊት የነበረውን የገባሪነት ሥርዓት በክርስትና ስም ሊጭኑብን ነው በማለት ሸሽቶዋቸዋል። ሚሽኖች ግን መጥተው ወንጌልን ሲሰብኩ ሕዝቡም ተቀብሎዋቸው ወደ እነሱ ተመልሷል። የኦርቶዶክስ እምነት መሪዎች ግን የሲዳማ ሕዝብ የሚሸን እምነት በመከተሉ 'እኛ ክርስትና አስነስተናችሁ ሕዝቡን አከፋፍለው የሚያጠፉትን የሚሸኖች እምነት ለምን ትቀበላላችሁ? ሲሉ እኔ በወቅቱ የሰጠኋቸው ምላሽ፣ እናንተ ለእኛ ክርስትና ስታስተምሩ ወደ ቤተ ክርስቲያን አስጠግታችሁ የክርስትናውን ምስጢር መቼ አስተማራችሁን? ክርስትና ማንሣት የሃይማኖት ምስጢር ማስተማር ሆኖ እያለ እናንተ ግን እያንዳንዳችሁ አቅማችሁ የፈቀደውን ያህል 200 ወይም 300 ሰው ተከፋፍላችሁ። ልጆች መጡ እያላችሁ ወደ ጓሮዎችሁ አሰማርታችሁ የቀረውን በክርስትና ሽፋን ስለጫናችሁብን ሸሽተናል የሚል ነበር። ከጣሊያን ወረራ በኋላ ሕዝቡ ክርስትና እንዲነሣ በአዋጅ ስለተነገረ አንድም ሰው ሳይቀር በአዋጅ ታዘው ሕዝቡ ወንዝ ወርደው ተጠምቀዋል።*[137] *የጣሊያን ወረራ እንዳበቃም የኢትዮጵያ መንግሥት ከስደት ወደ መንበረ ዙፋኑ ከተመለሰ በኋላ ኢትዮጵያውያን በአንድ ሃይማኖት መተዳደር አለባቸው ብሎ ፓትሪያርኩ መመሪያ በማውጣት ፀጉራቸውን በመላጨት ክርስትና እንዲነሡ በማስገደዱ ከአላታና ከሐዋላ የተወሰኑ ለአበቱታ ወደ ንጉሡ እንደሄዱ በመጽሐፉ ተዘክሮአል።*[138]

[135] የሲዳማ ብሔር ታሪክና ባህል፣ 2003 ዓ.ም ገጽ 233
[136] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 233
[137] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 233
[138] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 234

በወቅቱ ስለነበረ ሁኔታ ሕዝቡ ስሜቱን በሥነ ግጥም እንዲህ ገልጸ ነበር፡-

ሲዳማኛ

Nugusaho Hayile Sillaase,

Hayile Sillaase qaalinni manna Kiritiiinna kayise.

Anera dunno gambayichi eino Hawasa daade:

Cimeeyye umma meendeenna bade labbanno mataate:

Meyaa labbaaha qodho tirreena lawanno Qulbate qaaqe.

ትርጉም በአማርኛ

ኃይለ ስላሴ ንጉሥ ናቸው

ሁሉ ሰው ተጠምቆ በትእዛዛቸው፤

በጥምቀቱ ሰበብ ውሃ እየፈሰሰ፤

እስከ ሐዋሳ ደረሰ።

ያዛውንቶቹ ራስ ሲመለጥባቸው

የማሰሮ አንገት ገል አስመሰላቸው፤

ሴቱም ወንዱም ባዶ እራቁቱን ሆነ

አዲስ የበቀለም እንጉዳይ መሰለ።[139]

መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ድርጊት አያውቀውም። ኢየሱስ ወደ እኔ ነ ብሎ ሰዎች በፈቃዳቸው ወደ እርሱ እንዲመጡ እንጂ በኃይልና በአዋጅ እንዲቀበሉት አላደረገም፤ ቅዱሳንም ክርስትናን በኃይልና የሰዎችን ፈቃድ በመጨፍለቅ እንዲያስፋፉ አላዘዛቸውም። ክርስትና በወንጌል ስብከትና በሰዎች በጎ ፈቃድ ላይ ተመሥርቶ የተሰራጨና የግለሰብን፣ የአገርንና የዓለም ታሪክ በአምንታዊ መልኩ የለወጠ መለኮታዊ እውነት ነው። ከላይ በካፋና በሲዳማ ክርስትናን በኃይልና በአዋጅ የማስፋፋት መከራ ምንጩ የእግዚአብሔርን ቃል በቅጡ ካለመረዳት የመጣ እንጂ ከመጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና ጋር ምንም ዓይነት የአስተምህሮና ታሪካዊ ቁርኝት እንደሌለው መታወቅ አለበት። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ጥንት፣ ዛሬና ለወደፊቱም የሰዎችን ነፃ ፈቃድ የሚያከብር የሕይወት፣ የለውጥ፣ የዕድገት መንገድና ብቸኛ የአዳም ዘር ሁሉ የመዳኛ መንገድ ነው።

[139] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 234

ይሏል። መያዝም ይገባዋል። ከላይ የተመለከትነው የኃይል አካሄድ ግን በስሚ የተካሄደ ትልቅ ስህተት ነው።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን አስተምራ ደቀመዝሙር ባለማድረጓ በቤተ ክርስቲያን በአባልነት ስም ሥርዓት እየፈፀሙ ለዘመናት የኖሩ በዘመናችን ባዶነት የተሰማቸው ሰዎች ወደ ሌላ እምነት፣ ወደ ባሕላዊ የሃይማኖት ሥርዓቶቻቸው በመመለስ ላይ ይገኛሉ። ይህ አርቶዶክስን ብቻ ሳይሆን አንዳንድ የፕሮቴስታንት አባላትንም ይመለከታል። ሰዎችን ያለ ወንጌል ትምህርት በአባልነት ስም ብቻ ይዛ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ወደ እግዚአብሔር ቃል ለራሷ ተመልሳ በመታደስ በእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ እንደገና ካልተነሳች ትተዋት እየሄዱ ያሉትን መመለስ ቀርቶ በእጇ ያሉትንም መከልከል በፍጹም አቅም አይኖራትም። ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ ነገሯ ውስጥ ጠፍታ ወደ ራሳቸው ነገር እየተመለሱ ያሉትን መታደግም ሆነ መመለስ በፍጹም አትችልም። ተሐድሶ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደሚያስፈልግ የእግዚአብሔር መንፈስ እየተናገረ ያለው ለዚህ ነው። ቤተ ክርስቲያን ትሰማ ይሆን?

ለአንድ ማኅበረሰብ ባሕላዊ እሴቱ የማንነቱ መለያና መገለጫ አልፎም የዕድገቱ መሠረት ነው። ወንጌል በዓለም ላይ ያለው የትኛውም ባሕል ሊመልስ ያልቻለውን የአዳም ልጆችን መንፈሳዊ ጥያቄ የመለሰ መለኮታዊ መልዕክት ነው። ባሕል ከሰው ለሰው ሲሆን ወንጌል ከእግዚአብሔር ለሰው ነው። ባሕል ጊዜያዊና ምድራዊ ሲሆን ወንጌል ሰማያዊና ዘላለማዊ ነው። ባሕል ከሕዝብ ሕዝብ ይለያያል ወንጌል ግን ለሕዝብ ሁሉ አንድ ነው። ባሕል በጊዜ ብዛት ተወልዶ፣ አድጎ በሌላ እሴት እየተለወጠና በአዲስ ባሕል እየተተካ የአንድ ማኅበረሰብ የመለያ ምልክት እየሆነ የመጣ ሲሆን ወንጌል ለዘላለም የማይለወጥ የድነት መንገድ ነው። የባሕል ትኩረት በአለባበስ፣ በአመጋገብ፣ በቋንቋና በመሳሰሉት ላይ ሲሆን የወንጌል ትኩረት በሰው ልብና መንፈስ ላይ ነው። ባለፉት ሁለት ሺ ዓመታት ብዙ ባሕሎች ከጊዜ ብዛት ተወልደው አድገው ሞተዋል በሌላ ባሕል ተተክተዋል፤ ወንጌል ግን አልተለወጠም፤ አይለወጥምም። ወንጌል እንደ ፋሽን አይለወጥም። የትኛውም ባሕል ከዘላለም ከኑሄና ሞት አያድንም፤ ወንጌል በተለያየ ባሕላዊ እሴት ሆነው የክርስቶስን አዳኝነትና የኃጢአታቸውን ይቅርታ በእምነት የተቀበሉትን ሰዎች ሁሉ ያድናቸዋል። ክርስትና ለምዕራቡ ዓለም የኢንዱስትሪ አብዮት መገኛ፣ የሰዎች የፈጠራ አቅማቸው ሙሉ በሙሉ እንዲለቀቅ ያደረገ፣ የሕዝቡን አኗኗር፣ አመለካከትና አገራቸው በዕድገት ጉዳና እንድትመራ አድርጓል። የኢትዮጵያ ክርስትና በዕድሜ ከሁሉ የቀደመና ታሪካዊ ቢሆንም የሕዝቡን አመለካከት በአምንታዊ መልኩ ለውጦ በአገር ዕድገት ላይ የገዘፈ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ ያለመቻሉ የአስተምህሮ ችግር እንዳለው ለማንም ግልጽ ነው። ክርስትናችን በቃሉ መፈተሽ፣ መታደስ፣ መመዘን፣ መጥራትና መታየት፣ አለበት የምንለው ከዚህ የተነሣ ነው። በአገሬ ጠያቂ አዕምሮ ውግዝ ቢሆንም ግንባራቸው እንደ ነሐስ የጠነከረ፣ በስሜትና በአባቶች ወግ ብቻ የሚነዱ ሳይሆን፣ ገለባን ከፍሬ የሚለዩ፣ የቃሉ ዕውቀት ያላቸው፣ ዋጋ ለመክፈል የተዘጋጁ፣ የጠራውን ወንጌል የሚሰብኩ፣ የመንፈሱን ኃይል የታጠቁ፣ የተሐድሶ አርበኞችና ጠያቂዎች በቤተ ክርስቲያን ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ተያይዘው

ዶናልድ ዶንሃምና ዊንዲ ጀምስ የኦርቶዶክስ ክርስትና በኦሮሞና በደቡብ ሕዝቦች የአበሻው ነገሥታቶች ሁሉን አበሻ የማድረግ ፖሊሲ ይዘው እንደነበር ሲናገሩ፦

> *ሁሉንም አበሻ የማድረግ (Abyssinianization) ሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች ያካተተ ነው፤ እነዚህም የጉልተ ርስት የመሬት ሥሪት መስፋፋት፣ አማርኛ ቋንቋ እንደ ራስ ቋንቋ መናገር፣ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መስፋፋት ናቸው*[140] ብለዋል።

ይህ ድርጊት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በደቡብ ሕዝቦች ዘንድ የሰፋ ተቀባይነት እንዳይኖራት እንዳደረገ ወንዲዬ ዓሊ ሲናገሩ፦ "*የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝብ የኦርቶዶክስ ክርስትናን እንደገባር ሃይማኖት ሰለሚቆጥር ለስሜቱ ሩቅ ለባሕሉ እንግዳ ሆኖበት እንዳሰለፈ በርካታ የአገርና የውጭ ተመራማሪዎች የመዘገቡት እውነት ነው*"[141] ፖሊ ኢ.ባሊሰካይ የተባሉ ጸሐፊም "*በሰሜነኞቹ ቅኝ ገዢዎች እጅ ከደረሰባቸው ብዝበዛና ጭቆና የተነሣ በወላይታዎች መካከል የኦርቶዶክስ እምነትን ለማስፋፋት የተደረገው መከራ ብዙ ውጤት አልባ ነበር*"[142] በማለት አንድ ታሪክ ጽፈዋል።

እንደ ጸሐፊዎቹ ከሆነ የኦርቶዶክስ ክርስትና በአካባቢያቸው በወንጌል ከኃጢአትና ከሰይጣን አገዛዝ ሰዎችን ነፃ የማውጣትና ክርስቶስን ለመከተል በፈቃዳቸው ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ሕዝቦች ለገቢውና ለአሸናፊው ክፍል ታዛዦች እንዲሆኑ በመሣሪያነት ያገለገለና በግዴታ እየተነዱ እንዲጠመቁ የተደረጉበትና በወንጌል ስብከት ሳይሆን በቤተ መንግሥት አዋጅና በኃይል የተስፋፋ ሃይማኖት እንደሆነ ያሳያል። ይህም ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድርጊት

ይነሣሉ። የአገራችን ክርስትና እንደሚገባው ለራሳችን አልጠቀመንም ለአገርም ጠቃሚዎች አላደረገንም። ስብዙዎች ክርስትና ከአባትና ከእናት የሚወረስ ሃይማኖት እንጂ የእግዚአብሔርን ቃል በግል በመረዳት፣ ለቃሉም በመታዘዝና የክርስቶስን እውነተኛ ወንጌል ለሌሎች በመመስከር፣ ለአገር ዕድገት፣ ለኢኮኖሚ ምጥቀትና ለዲሞክራሲ ማበብ የሚገባውን ሚና እንዲጫወቱ አላደረጋቸውም። ከዚህም የተነሣ ቀድመን "ክርስትና" ተቀብለን በብዙ የኋለኞች ኋለኛ ሆነናል።

ሐዋርያት ወንጌልን ያስፋፉት በጡንቻ ይሆን?

ኢየሱስን የሰቀሉ፣ ለሃይማኖታቸው ቀናኢ የነበሩና በዚህ ጉዳይ ከማንም ጋር የማይደራደሩ አይሁዶች የጴጥሮስን ስብከት በበዓለ ሃምሳ ዕለት *"በሰሙ ጊዜ ጴጥሮስንና ሌሎችን ሐዋርያት ወንድሞች ሆይ ምን እናድርግ?"* (የሐዋ.2፡ 28) ሲሉአቸው ንስሐ እንዲገቡ በመርዳት በአንድ ስብከት 3000 በላይ አክራሪ አይሁዶችን በወንጌል የማረኩት በሰይፍ ሳይሆን በወንጌል ስብከት ነበር። በሰማርያ ከተማ ሲሞን የተባለ ጠንቋይ አገርን እያስደመመ፣ የሕዝብን አዕምሮ በመግዛት ሀብታቸውን እየበዘበዘ እንደ ከተማ አምላክ ተፈርቶ ይኖር ነበር። ፊልጶስ ወንጌልን በዚያ ከተማ ያሰራጨው በወንጌል ስብከት እንጂ የጠንቋዩን ቤት በማፍረስ አልነበረም።

ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበክላቸው። ሕዝቡም የፊልጶስን ቃል በሰሙ ጊዜ የተናገረውን በአንድ ድምጽ አደመጡ። እርኩሳን መናፍስት በታላቅ ድምፅ እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ይወጡ ነበርና ብዙም ሽባዎችና አንካሶች ተፈወሱ በዚያችም ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ። ...ሲሞንም ደግሞ ራሱ አምኖ ተጠምቆም ከፊልጶስ ጋር ይተባበር ነበር (የሐዋ. 8፡ 4-8፡ 13) ይላል። መጽሐፍ ቅዱሳዊና አዲስ ኪዳናዊ የወንጌል ስርጭት ምሳሌ በአጭሩ ይህን ይመስላል። ሐዋርያው ጳውሎስም ወንጌል የመለኮት ኃይል እንደሆነ ሲገልጽ፡- *"በወንጌል አላፍርምና አስቀድም ለአይሁድ ደግሞም ለግሪክ ሰው ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና"* (ሮሜ.1:16) ብለዋል።

ወንጌል የመለኮት ኃይል ሆኖ የሰውን የአፍ ምስክርነት እንጂ ጡንቻ አይፈልግም። ከላይ እንደተመለከትነው በኢትዮጵያ የተሠራጨው የክርስትና ሃይማኖት ስም የተሰጠው ሥርዓት እንጂ የተቀበሉትን ሰዎች ሕይወት ለውጦ የለውጥ መሣሪያ የማድረግ ኃይል ያለው የወንጌል ቃል አልነበረም። ክርስትና ዓለማትን የገዛው ጌታና ንጉሥ የሆነ የናዝሬቱ ኢየሱስ በገሃድ የሚሰበክበት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት እንጂ ገዢዎች ተገዢዎችን የሚጫኑበት የፖለቲካ መሣሪያ አልነበረም። ገዢዎች ራሳቸው ክርስትና በትክክል ቢገባቸው ኖሮ ለክርስቶስ ተገዝተው ክርስትናን እንደ መሣሪያ በመጠቀም ዜጐችን ለመግዛት ባልተነሡ ነበር። የኢትዮጵያ ክርስትና ከመጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና ጋር የተፋታበት አንዱ ነጥብ ይህ ነው።

ዐፄዎችና ክርስትና

ምሳሌ፡-ዐፄ ዮሐንስ

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ *"ዐፄ ዮሐንስ እና የኢትዮጵያ አንድነት"* በሚለው መጽሐፋቸው፡- ***<u>ዐፄዎች በክርስትና ስም ሰዎችን ሲያሳድዱ፣ ሲያሠሩና ሲገድሉ እግዚአብሔርን ያገለገሉ ነው አንጂ ግፍ የሠሩ መስሎ አልታያቸውም ነበር</u>***[143] *(መስመሩ በኔ)* ብለዋል። ድርጊቱ አሐፊው እንዳሉት ከሆነ ቤተ ክርስቲያን ወንጌል ከጡንቻና ከሰይፍ ጋር በፍጹም ተያያዥነት እንደሌለው የእግዚአብሔርን ቃል እንዳላስተማሪችና ዐፄዎች ክርስቲያን ተባሉ እንጂ የክርስትና መሠረት የሆነ የክርስቶስ የወንጌል ቃል ዕውቀት እንደሌላቸው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ድርጊታቸው ያሳብቅባቸዋል። በአገራችን በክርስትና ስም የተፈጸሙ ግድያና ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ደርጊቶችን ሁሉ እንደ ጽድቅ ሥራ መቁጠር ዋናው ምክንያት ክርስትናችን ሥጋዊ ልምድ እንጂ የቃሉ መሠረት እንዳልነበረው አንዱ ማስረጃ ነው። የኢትዮጵያ ነገሥታት "ክርስቲያን" እንደነበሩ የታወቀ ነው። የክርስትና ስም ቢኖራቸውም አብዛኛው ድርጊታቸው ክርስቲያን እንደነበሩ አያመለክትም። ክርስቲያን የክርስቶስ ብርሃን በሕይወቱ የበራና የእግዚአብሔር ቃል በውስጡ ስለሚኖር በንግግሩ፣ በአስተሳሰቡ፣ በእርምጃውና በሥራው ክርስቶስን የሚያሳይ ሰው ነው።

በኢትዮጵያ ታሪክ ገናናና መንፈሳዊ እንደነበሩ ከሚነገርላቸው ነገሥታት መካከል አንዱ ዐፄ ዮሐንስ ናቸው። በሕይወታቸው በሙሉ ለአገራቸው አንድነት በብርቱ የደከሙና ወገናቸውን ከጥቃት ለመታደግ ሲሉ ሕይወታቸውን የሠዉ ታላቅ መሪ ስለሆኑ አንጸባራቂ ታሪካቸው በዘመን ሁሉ ይወሳል። አሁን እየኖርንባት ላለችው ኢትዮጵያ የነፍስ ዋጋን ከከፈሉ የአገራችን ብርቅዬና ታላቅ መሪዎች አንዱ በመሆናቸው እንኮራባቸዋለን። ዐፄ ዮሐንስ ለሃይማኖታቸው ቀናኢ እንደነበሩ፤ ከዚህም የተነሣ በኢትዮጵያ ታሪክ *"ዮሐንስ መነኩሴውና ወታደሩ"*[144] እየተባሉ እንደሚጠሩ ተጽፎዋል። ለኚህ ታላቅ ሰው አድናቆት ይገባቸዋል። በክርስትና ስም ያደረጉት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ድርጊቶች ግን ከተነገረላቸው የመንፈሳዊነት ምስክርነት ጋር በብዙ ይጋጫል። ዐፄ ዮሐንስም እንደ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በክርስትና ስም ኃይልን እንደተጠቀሙ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ዶክተር ላጵሶ ጌድሌዎ *"የኢትዮጵያ የመከራ ሥርዓትና የሌርትራ ጥያቄ"* በሚለው መጽሐፋቸው፡-

በአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት በዘመናዊ ጦር መሣሪያ በታጠቁ የኢትዮጵያ ነገሥታት በተለይም በዐፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት በአንድ በኩል የመንግሥቱን የክርስትና ሃይማኖት በኃይል የፖሊሲ ተግባር ለማስፋፋት ያደረጉት... እስከ ዛሬ ድረስ በመካሄድ ላይ ላሉት ውስብስብ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የሃይማኖት፣ የብሔረሰብ፣ የቋንቋ፣ የባህል ችግሮች ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደአደረጉ ግልጽ ነው[145] *ብለዋል።*

[143] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ(1982 ዓ.ም)፣ ዐፄ ዮሐንስ እና የኢትዮጵያ አንድነት፣ ኩራዝ አሳታሚድርጅት፣ 76
[144] ሐሪ አትክንስ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ገጽ 26
[145] ላጵሶ ጌ.ድሌቦ (ዶ/ር) (1985 ዓ.ም) የኢትዮጵያ የመከራ ሥርዓትና የኤርትራ ጥያቄ ገጽ 150

ክብሮም ብስራት የተባለው ጸሐፊም ስለ ዐፄ ዮሐንስ ሲናገሩ *"ኢትዮጵያውያን በኦርቶዶክስ ውስጥ ለማድረግ መሞከራቸው ድካማቸውን ያሳብቅባቸው"*[146] ሲሉ እንደ ገብረሥላሴ የታሪክ መጽሐፍ በዐፄ ዮሐንስ ዘመን የመንግሥት ክርስትና የነበረው በሰሜን ደጋማ ክፍል ብቻ ተወስኖ የነበረውን በቦሩ ሜዳ በተደረገው ጉባኤ (1870ዓ.ም) ከወሰኗቸው ውሳኔዎች፡-

- *በአገሪቱ ክርስቲያን ያልሆኑት ሁሉ እንዲጠመቁ፣*
- *በየአካባቢው ያሉ የመንግሥትና የሃይማኖት ኃላፊዎች ቤተ ክርስቲያን እንዲሠሩ።*
- *ወደ አገሩም ሚስዮናውያን እንዳይገቡ ጽኑ የፖሊሲ አዋጅ እንዳወጁ መረጃዎች ይጠቁማሉ።*[147]

ዐፄ ዮሐንስ ኢሰብዓዊ ድርጊቶች

ዐፄ ዮሐንስ ለቤተ ክርስቲያንና ለእግዚአብሔር ቃል እውነት በመቅናት *"2 ልደት ሃይማኖት በጣም ይወዱ ስለነበር 3 ልደት የሚሉትን ተቆጥተው የጥቂት ሰዎችን ምላስ እስከ መቁረጥ እንደ ደረሱ ታሪክ ያወሳል።"*[148] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ *"ዐፄ ዮሐንስ እና የኢትዮጵያ አንድነት"* በሚለው መጽሐፋቸው፡-

> *የዐፄ ዮሐንስ መሠረታዊ አሳብ፡ በክርስቲያኑ ሕዝባቸው መካከል "የጸጋ ልጅ፡ የቅባት ተከታይ" የሚባል ሁሉ ተደምሰሶ ሁሉም ክርስቲያን በተዋሕዶ እንዲያምን ነበር።*[149]

ዐፄ ዮሐንስ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት መፈለጋቸው ትልቅ ነገር ሲሆን መንፈሳዊ አንድነትን በሥጋ ለማምጣት መታገላቸውን የእግዚአብሔር ቃል አይደግፋቸውም። የታሪክ ጸሐፊ አለቃ አጥሜ ጊዮርጊስ በስፋትና በዝርዝር የንጉሡን በኃይል ሃይማኖትን የማስፋፋት ዘመቻ በ1878 ዓ.ም በወሎ ስለተደረገው ሲናገር፡-

> *ከዚያ ወዲህ ሕዝቡን በግድ ያጠምቁትና ያቆርቡት ጀመሩ። ጉልበት ያለውና በሃይማኖቱ የቆመ ወደ መተማ ከድርቡሽ ጋር ሲሆን ሄደ። እኩሉ ወደ ቀበናና ወደ ጅማ ወደ ሐረርጌም ተሰደደ። የሄዱበት አገር ሁሉ የሸፍታ አገር ሆነ። የሀባሻ አውራጃዎች ሁሉ የጦርነት ሥፍራዎች ሆኑ። ጅረቱ ሁሉ የሰው ደም ሆነ።*[150] *... ከዚያ በኋላ ዐፄ ዮሐንስ ወሎ ላይ ከረመ። <u>ሲያቆርቡ ያልቆረበውን ሲፈጁ በቦሩ ሜዳ ቤተ ክርስቲያን አየሠሩ።(መስመሩ በኔ)</u>*

[146] ማሪኪ፣ *ቅፅ 1 ቁጥር 43፣ ሴፕ 2005 ዓ.ም ገጽ 34*
[147] *ገብረሥላሴ፣ዳግማዊ ምኒልክ፣ገጽ 92*
[148] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ገጽ 75
[149] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ(1982 ዓ.ም)፣ ዐፄ ዮሐንስ እና የኢትዮጵያ አንድነት፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ ገጽ፣ 200
[150] ላጲሶ ጌ.ድስበ(ዶ/ር)፣ ገጽ 144

ክርስትናን በኃይል የማስፋፋት ዘመቻ ግራ ያጋባቸው ንጉሥ ሚኒልክ ወደ ዐፄ ዮሐንስ ቀርበው እንዲህ ብለው ጠየቁት፡-

> *ጃንሆይ እግዚአብሔር ይወድልናልን? በግድ ቁረቡ እያልን ሕዝባችንን ብንፈጀው ብለው ጠየቁ። ጃንሆይም ሲመልሱ የኢትዮጵያን ደም አበቀልላታለሁ። ግራኝ ኢትዮጵያን ሲያሰልማት በግድ በአሳትና በሰይፍ ነው። እኛስ የማርቆስን ሃይማኖት ካላቀናነው ካልመሠረትነው ማን ያቀናዋል።*[151]

የዮሐንስን ምክር የተቀበሉ ዐፄ ሚኒልክ በተራቸው *"ሌሊት እየገሰገሡ ቀን እየወረሩ... ቀጥቅጠው ቤተ ክርስቲያን እየተከሉ"*[152] እዚህ ላይ ዐፄዎች ይህን ሲያደርጉ ለወንጌልና ለቤተ ክርስቲያን በመቅናት አልነበረም። ዶክተር ላጲሶ ዋና ምክንያታቸው ምን እንደነበረ ሲናገሩ፡- *ዐፄ ነገሥታት ቴዎድሮስ፣ ዮሐንስ፣ ምኒልክና ኃይለ ሥላሴ የክርስትና ሃይማኖት ለአገር አንድነትና ግንባታ መሠረት ነው*[153] በማለት በስብከት የመጣውን ክርስትና በአዋጅና በኃይል አስፋፍተዋል። የኢትዮጵያ ክርስትና የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ የሚሰበክበት፣ ሰዎች ንስሐ ገብተው አዲስ ፍጥረት የሚሆኑበትና ወደው የነፍሳቸውን ጌታ የሚከተሉበት ሳይሆን ለቤተ መንግሥት የፖለቲካ ፍጆታ ብቻ እንደዋለ እንመለከታለን። *በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ሦስቱ መለኮታዊ አሀዳዊ <u>የክርስትና፣ የኦሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች የኖሩና የተስፋፉት በንብረተሰቡ ዘንድ የመንግሥት የፖለቲካ መሣሪያዎችና አገልጋዮች ሆነው ነው</u>*[154] ብለዋል። ኢትዮጵያውያንን በኃይል "ክርስቲያን" የማድረግ የዐፄዎችና *"የአሕመድ ግራኝ"*[155] ኢትዮጵያን "እስላም" ለማድረግ የ14

[151] ላጲሶ ጌ. ድሌበ *(1983 ዓ.ም)፣የኢትዮጵያ የመሀራ ሥርዓትና የኤርትራ ጥያቄ፣ ሦስተኛ መጽሐፍ፣ ገጽ 144*
[152] *የኢትዮጵያ ገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም 1900-1966 ገጽ 91*
[153] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 90*
[154] *የኢትዮጵያ ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች 1999 ዓ.ም ገጽ 44*
[155] ዓብደላ መሐመድ ዓሊ (ተርጓም) (2001 ዓ.ም) ፣ *የሐበሾችና የዘላሪ ሙስሊሞች የመካከለኛው ዘመን መንግሥታት ፖለቲካዊ ግንኙነት ታሪክ፣ድሬ ማቱሚያ፣ ገጽ 97* "በሐረሬዎች ዘንድ ካጉራኒ፣ በተባለ ስም የታወቀው ታላቁ የእስላሞች ጦር መሪ አውነተኛ ስሙ ካሕሕመድ ቢን ኢብራሂም ኤል.ጋዚ፣ በተለምዶ አሕመድ ግራኝ በሚለው ስም የሚጠራው በሐረርና በአጋዴን መካከል በሚትገኘው ሆባት በምትባል ቶላማ መንደር በ1498 ዓ.ም ተወልደ። እንደ ይልማ ዴሬሳ የኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፍ፡- አሕመድ ግራኝ ጦርነትን የጀመረው በሐረር የእስላም ሡልጣኖች ላይ ነበር። ይህም የአሕመድ ግራኝ ዓላማ እስልምናን የማስፋፋት ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ የበላይነት ፈላጎም እንደነበር ያመለክታል። እንደ ዶክተር ረጅብ ካግራኝ አሕመድ ዓላማ በሙሲልሞች ላይ በወቅቱ የሚፈፀመውን ወሰን የለሽ ግፍ ለመቋቋም*"*[155] ከተነሣ እስላሞች የነበሩ የሐረር ሡልጣኖችን በመዋጋት አሜር አቡበክርን በመግደል ኢትዮጵያን መውረርን የጀመረ ሰው በሙስሊሞች ላይ ይደርስ የነበረውን ገደብ የለሽ ግፍ ለማቋቋም ተነሣ ማለት እንዴት እንችላለን?

አማረ አፈሰ ቢሻው (1999 ዓ.ም)፣ *የሁለት ሺ ዓመታት ውጣ ውረድ በኢትዮጵያ፣* ሲያትል ዋሽንግተን አሜሪካ፣ ገጽ 128. ካአሜር አቡበክር ሆኑ ወጣቱ ይማም አሕመድ ሁለቱም በሃይማኖት አንድ ናቸው። ታዲያ እነዚህ ግለሰቦች ለሥልጣናቸው ሲሉ ራሳቸው መዋጋታቸው እንኳን ሊገቡ አልቻሉም። የሐረር አሚሮች በኃይል በወጣቱ ይማም አሕመድ ስልጣናቸውን ተነጠቁ፣[155] ይልማ ዴሬሳ (1999 ዓ.ም) ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን፣* ፋር ኢስት ትሬዲግ (ሁለተኛ እትም) 56 ካአንደ ይልማ ደሬሳ መጽሐፍ አሕመድ ግራኝ በሐረር አካባቢ በጦርነት የበላይነቱ ካጠናከረ በኋላ ኢትዮጵያን በመውረር በሰይፍና አገርን የማስለም ዓላማ አንግቦ እንደተነሣ ዘግቧል፡- ግራኝም ራሱ ይህንኑ የአስላምን ሃይማኖት በገዢዉ ማስቀበል የተባለውን ዘዴ ከሼኮች ሲማር ቆየ።፣[155] አሕመድ ኢብራሂም ኢትዮጵያን የመግዛትና የማስለም ዓላማውን*[155]*(ገዛኔ ከማሁ፣ ገጽ 86) ከግቡ ለማድረስ የሱማሌ፣ የየመን፣ የአሩሮች፣ ከሐረር ልዩ ልዩ ፕሮሳዎች ሌላም (አለዊ ሁሴንይን) የተሰኙ አረቦችም በጦር ሠራዊቱ ውስጥ ተካተው ነበር። እንዲሁም ነፍጥ (ጠመንጃ) ያነገቡ የቱርክ ወታደሮችንና ሠወደ አስልምና የገቡ ተዋጊዎችን አንድ ላይ አጣምሮ ነበር። አሕመድ ግራኝ ወረራውን ሲያካሄድ፡- የርሱ ሠራዊት ጠንክሮ እንዲዋጋለት በጦር

ዓመታት ትልቅ ጥፋት ያስከተለው ወረራ እንዳልተሳካ ሁሉ በዚህም ዘመን ምናልባት ሃይማኖታዊ አሃዳዊነት በኢትዮጵያ ለማስፈን ሕቡዕ አጀንዳ የፀነሱ ቢኖሩ በፍጹም እንደማይሳካለቸው ከታሪክ መማር አለባቸው። በኢትዮጵያ ያሉ አስላም፣ ክርስቲያኑ፣ የአይሁድ ሃይማኖት ተከታዮች፣ ባሕላዊ እምነት ተከታዮችና ሃይማኖት የለሽ ዜጐች በዚህች ታላቅ ታሪካዊት አገር በአንድነት ለመኖር የዜግነት እንጂ የሃይማኖት አንድነት አያስፈልጋቸውም። ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች ያሏቸው ሕዝቦች መኖሪያ እንጂ እንደ አገር ሃይማኖት የላትም። ክርስትና በክርስቶስ የተለወጠ ሕይወት እንጂ ሃይማኖት አይደለም።

ዛሬ አብዛኛው ሕዝበ ክርስቲያኑ የተሰጣቸውን ክርስትና ስምና በአጃቸው የገነቡት የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ እንጂ የክርስቶስን ቃል የማያውቁ ብቻ ሳይሆን ያለ ልብ ክርስቲያን መሆናቸው ነው። አገርን መውደድ መልካም ሆኖ እያለ በክርስትና ስም ሕዝብን መፍጀት፣ ሃይማኖት ማቅናት፣ አሕመድ ግራኝ እንዳደረገብን እኛም እናደርጋለን፤ ማለትና በሰይፍ የማርቆስን ሃይማኖት መመሥረት የኢትዮጵያ ክርስትና በወንጌል ስብከት ብቻ ሳይሆን በኃይልም እንደተስፋፋ ምስክር ነው። ይህ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ድርጊት ነው። ዛሬ ላለንበት ብዙ ግራ መጋባትም ዳርጎናል። ይህ ክርስትና ያመጣቸው ችግሮች ሳይሆን ክርስትናን በተሳሳተ መንገድ የተረዱት ሰዎች ክርስትናን ለተሳሳተ ዓላማ የተጠቀሙት አካሄድ እንደሆነ መዘንጋት የለበትም። ክርስትና የሰላም መንገድ ነው። ሃይማኖትና ፖለቲካን አንድ ላይ ቀይጠው በአገራችን ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ፣ አህመድ ግራኝ፣ ዐፄ ዮሐንስም ሆነ ሌሎች ያፈሰሱት ደም በእግዚአብሔር ቃል የተወገዘ ነው።

ዐፄ ዮሐንስ በኃይል ክርስትናን የማስፋፋት ዘመቻ ወሬ በዓለም ስለወጣ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር የነበራቸውን ግንኙነት እንዳያበላሽባቸው በመሥጋት በጎንደር 11. 1872 ዓ.ም ከአሥመራ ከተማ ለንግሥት ቪክቶሪያ ደብዳቤ ሲጽፉ፡- *"ባወንጌልም ጌታ ሰጽፍ በኃይል አድርጉ አላለም፣ አላዘዘም። በኃይል የተደረገም የለም"*[156] በማለት እንደ ካዱ ታሪክ ይናገራል። በአጠቃላይ ከላይ በተዘረዘሩት አሳቦች መሠረት ዐፄ ዮሐንስ በአዋጅ ሰዎችን በግድ እንዲጠመቁ፣ እንቢ ያሉትን እየፈጁ፣ ሌሎች አገር ጥለው እየተሰደዱ፣ የመንግሥትና የሃይማኖት ኃላፊዎች ቤተ ክርስቲያን እንዲሠሩ አድርገዋል።

ማዳ ላይ የወደቃችሁ እንደሆን መንግሥተ ሰማያት በርዋን ከፍታ ልትቀበላችሁ ትጠብቃለች፣ ስተሸሹ የሞታችሁ እንደሆን ግን ወደ ገሃነም ትወርዳላችሁ እያሉ ቃዲዎች ሰፊር ውስጥ ተዘዋውረው እንዲሰብኩ አደረጉ።[155] (ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 64) የዐፄዎች የቤተ ክርስቲያንን ሕንፃ በመገንባት መንግሥተ ሰማያት መግባት እንደሚቻል ሲያውጁ፣ አሕመድ ግራኝ ደግሞ ኢትዮጵያን በሰይፍ በማስለም የፖለቲካ የበላይነትን ለመቆናጠጥ በሚያካሂደው አገር የማውደም ጦርነት የሞቱ ሰዎች መንግሥተ ሰማያት በርዋን ዘፍታ ልትቀበላችሁ ትጠብቃለች፣ በማለት እንደነበር ታሪክ ምስክር ነው። መንግሥተ ሰማያት ሕንፃን በመገንባትና ለሃይማኖታችን በመቅናት ሌላውን በመግደል ሳይሆን ለኃጢአታችን የሞተልንን ጌታ በማመን ብቻ እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል።

[156] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ *ዐፄ ዮሐንስ*፣ ገጽ፣ 201

አልፎም እርሳቸው የሚያምኑትን ሃይማኖት ያልተቀበሉትን ሰዎች ምላሳቸውን ቆርጠዋል። ይህን ጌታና ወንጌልም እንደማይደግፉት ለንግሥት ቪክቶሪያ በጻፉት ደብደቤ ላይ እንደገለጹት የድርጊታቸው መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ እንዳልሆነ በራሳቸው ላይ መስክረዋል።

ታዲያ ዐፄ ዮሐንስ በሃይማኖት ስም ያካሄዱትን ኢሰብዓዊና የኃይል እርምጃ መንፈሳዊ ሽፋን ከሰጠነው የእግዚአብሔር ቃል አይደግፈንም። በአብዛኛው የኢትዮጵያ *"ክርስትና"* የተስፋፋው የጠራውን ወንጌል በመስበክ እንዳልሆነ ከላይ የተመለከትናቸው መረጃዎች ያመለክታሉ። የክርስቲያን ደሴት በተባለች አገራችን ክርስትና የተስፋፋው በእውነተኛው የወንጌል ስብከት ብቻ ሳይሆን የኃይል አጠቃቀም የገነነበት ለመሆኑ ይህ ተጨባጭ ማስረጃ ነው። በአጠቃላይ ረዥም ዕደሜን ያስቆጠረው የክርስትና ታሪካችን ሲጠና በወንጌልና በክርስትና ስም የሰውን ሰብዓዊ መብት ያለገደብ በመጣስ፣ በማለቃየትና በኃይል ጭምር እንደተስፋፋ ለመናገር ካሆናቸው መረጃዎች የተሻለ ሌላ ምስክር አያስፈልግም። ዐፄዎች በሃይማኖት ወጥነት ገመድ አንድ ላይ ሕዝቡን አሥረው ለመግዛት እንዲያመቻቸው የመጽሐፍ ቅዱስን ዕውቀት መሠረት ባላደረገው ባዶ ቅንዓት ይመሩ እንደነበር ሥራቸው ያመለክታል። የአገሪቷን ታሪክ በዘላቂነት ለማቆየት የነበራቸው ብርቱ ፍላጐት እጅግ የሚደነቅ ቢሆንም ባማያውቁት የነገረ መለኮት ክርክር ሁሉ በመግባት የተለየ አቋም በያዙት ላይ መዓት ሲያዘንቡ *"ቤተ ክርስቲያን"* ለምን ዝም አለች? *"ሰው የበላውን ይመስላል"* እንደሚባለው ዐፄዎች በክርስትና ስም በዚህ ምድር ያካሄዱት አሳፋሪና ዘግናኝ የኃይል እርምጃዎች የወንጌል ቃል በትክክል እንዳልገባቸው ያሳብቅባቸዋል። ዐፄ ዮሐንስን ያሳሳቱት በጊዜው በአጠገባቸው የነበሩ አንዳንድ ያልተማሩ ካህናት እንደነበሩ ጎሩይ ወልደ ሥላሴ፣ "ዋዜማ" በሚል መጽሐፋቸው ጠቅሰዋል፡-

> *ነገር ግን እውነተኛውን ትምህርት ያልተማሩ አንዳንድ ካህናትን ባጠገባቸው ከማኖራቸው የተነሣ የዝያን ምክር እየተከታተሉ አስላሞችን ሌሎችንም በሃይማኖት ያልመሰሏቸውን ሰዎች ትምባሆም የሚጠጡትን ሰዎች በአካላቸው በርስታቸው በገንዘባቸውም ስለቀጧቸው የውጭ አገር ጸሐፊዎች ታሪካቸውን አበላሽተው ጽፈውባቸዋል።*[157]

በአገራችን በክርስትና ስም የተፈጸሙ ግድያዎችና ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ደርጊቶች ሁሉ እንደ ጽድቅ ሥራ የተቆጠሩ ይመስላሉ። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮና አካሄድ በፍጹም እንዳልሆነ መታወቅ አለበት። ለመሆኑ ዐፄዎቹ ምን ዓይነት ወንጌል ተሰብኮላቸው ይሆን ቃሉን አስቀምጠው በሰይፍ በአማኞችና በክርስትና ስም በማያምኑት ላይ የዘመቱት? የተሳሳተ ድርጊት የተሳሳተ አስተምህሮና መረዳት ውጤት እንደሆነ የታወቀ ነው። ክርስትና ወደ ትክክለኛ ድርጊት የሚመራ ትክክለኛ የእምነት መንገድ ነው። ጥንትም ሆነ ዛሬ በሃይማኖት ስም የሚደረግ ማንኛውም የተሳሳተ የኃይል እርምጃ የተሳሳተ እምነት ውጤት እንደሆነ መታወቅ አለበት። ዛሬ ዓለምን በትልቅ ድንጋጤ፣ ፍርሃትና የሞት ድባብ ውስጥ የከተታት የእስልምና አክራሪዎች አጥፍቶ የመጥፋት ትልቅ ሜራ ምንጩ የተሳሳተ የሃይማኖት አስተምህሮና መረዳት እንደሆነ አንዘንጋ።

[157] ጎሩይ ወልደ ሥላሴ *(2001 ዓ.ም)* ፣ *ዋዜማ*፣ (ሁለተኛ እትም)፣ ገጽ 73

በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትንና ትክክለኛነትን አያጎናጽፋቸውም። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መዳን ሲናገር፦ *"መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና"(የሐዋ.4:12)። "ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም"(1ዮሐ.5:12)።* በማለት በግልጽ አስቀምጦታል። የሰው ልጅ ትምክህት በእግዚአብሔር ቃል በተገለጸው በክርስቶስ ኢየሱስ በወንጌል እውነት ላይ መመሥረትና በተዘጋጀለት የምህረት መንገድ በጸጋ መዳን ነው። ከዚህ ውጪ ሞት ነው።

በአጠቃላይ የክርስቶስ ቤዛነት የማይሰበክበት፣ ጸጋው በእምነት እንዳዳነን በግልጽ የማይታወጅበት፣ ሰዎች ድነታቸውን በሥራ ለማግኘት ደፋ ቀና እንዲሉ በሚደረግበት፣ ከቃሉ ይልቅ በቆየው አገራዊ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ያለቅጥ የሚሞገስበት *"የአገራችን ክርስትና"* የትም አላደረሰንም፤ የትም አያደርሰንምም። እግዚአብሔርን በቃሉ መንገድ እንጂ ከቃሉ ባፈነገጡ ልምዶቻችን አናገኘውም። ወደ ቃሉ መመለስ አለብን። ተሐድሶ! ተሐድሶ! ተሐድሶ! ያስፈልገናል። እሥራኤላውያን በኃጢአታቸው ከእግዚአብሔር እጅግ ርቀው፣ የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ሆኖና ራእይ ጠፍቶ ቤተ መቅደስ ነውር የሚፈጸምባት ዋሻ ሆና ነበር። በዚያ ዘመን እስራኤላውያን ከፍልስጥኤማውያን ጋር ለመዋጋት በወጡ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል በውስጣቸው ሳይኖርና ከእርሱ ጋር ያላቸው ግኑኝነት ፈርሶ የኪዳኑን ታቦት ይዘው ቢዘምቱም ከሽንፈትና ከሞት አልታደጋቸውም።

"ፍልስጥኤማውያንም የእግዚአብሔርን ታቦት ወስደው ወደ ዳጎን ቤት አስገቡት በዳጎንም አጠገብ አኖሩት"(1ሳሙ.5:2)።

ልባችን ለእግዚአብሔር ካልተሸነፈ ለእርሱ በምናደርገው ሥርዓት ብዛት እርሱ ዘንበል አይልልንም፤ በጠላቶቻችንም ላይ ድል አይሰጠንም። ረሃብ፣ እርዛት፣ ጦርነት፣ ድህነት፣ ኃላ ቀርነት፣ በሽታ፣ ጥላቻና ያለመቀባበል፣ የታሪካችን አካል ሆነው በምድራችን የገነኑት ከዚህ የተነሣ ይሆን? የእግዚአብሔር ቃል የበላይነትን ባልያዘበት የንስሐ ልብና የተሐድሶ ፍላጎት በሌለው የረኸም ዘመን ክርስትናችን ብቻ እየተኩራራን መጓዝ ከቀጠልን ዕድሜን ከመቁጠር ያለፈ ክርስትናችን እንደ ሌሎቹ አይጠቅመንም፤ ጠቃሚዎችም አያደርገንም። ከድግግሞሽ፣ ከሰዋዊ ወግ ዘበኝነትና ከባዶ ሃይማኖተኝነት ያለፈ እግዚአብሔር ወዳዘጋጀልን በረከት ቤተ ክርስቲያንንና አገርንም ለመምራት እንደ ሌላ አገር ክርስቲያኖች ዐቢይ ሚና መጫወት አንችልም። መፍትሔው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶ ነው። ያለፈውን የምናነሳው የመጣንበትን መንገድ ዞር ብለን ለማየት፣ ያለንበትን ለማወቅ፣ መጭውን በተሻለ ራእይ ለመተለም፣ ከስህተታችን ለመማር፣ የባሰ ታሪካዊ ስህተት እንዳንፈጽም፣ ስለ ራሳችንና ስለአባቶቻችን በደል በእግዚአብሔር ፊት በተሰበረ ልብና መንፈስ ለይቅርታ ለመውደቅ፣ ኢትዮጵያ ተባርካ ኢትዮጵያውያን ለዓለም በረከት በወንጌል ምክንያት እንድንሆን ነው።

የጎበጠው የክርስትና አስተምህሮ የሚቃናው በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ እንጂ በኃይል እርምጃና በማክረር አይደለም። ሰይፍ ሰይፍን እንጂ የጸጋን ወንጌል አይወልድም። ወደ እግዚአብሔር ቃል መመለስ አለብን።

የእግዚአብሔር ቃል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት ከተያዘችበት ቀለበት የመውጫ ብቸኛ መንገድ ነው። በአገራችን በኃይልም ቢሆን ክርስትናን ማቆየታችንና ኢትዮጵያን *የ"ክርስቲያን ደሴት"* ማለታችን በአንዳንዶች ዘንድ እንደ ትልቅ ጀብዱ ይቆጠራል። አሳዛኝ ጎኑ ግን ከቃሉ ውጭ በኃይል፣ በግድያና ሌሎችን እያሳደድን ባስጠበቅነው ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ "ክርስትና"ና የእግዚአብሔር ቃልና አብሮነት መታጣቱ ነው። ብዙ ክትባቶች በሽታ መሆን ከማይችለው ሕዋስ ተቀሚመው ለሰዎች ሲሰጡ ያ በሽታ ሰውነታቸውን ለማጥቃት ሲመጣ ቀድሞውኑ በክትባት መልክ ሰውነት ውስጥ የነበረው የበሽታው ሕዋስ በሽታን ይከላከላል። እንዲሁም የወንጌልን እውነት ያልተረዳ፣ የክርስቶስን ቤዛነት አምኖ ኃጢአቱን ተናዝዞ የልጅነትን ሥልጣን ያልተቀበለ፣ ከዓለም ክፋትና እርኩሰት ያልተለየና ደቀመዝሙር ያልሆነ ከክርስቲያን ቤተሰብ በመወለዱ /"ክርስቲያን" በመባሉ/፣ በ40/በ80 ቀኑ በመጠመቁና የክርስቲያን ስም ስለተሰጠው ክርስቲያን የሆነ መስሎት መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሕይወት ለዋጭ ክርስትና ሲነገረው በፍጹም የማይታገስ "አማኝ" ብዙ ነው። በሌላውም ሃይማኖት ቢሆን እጅግ ብርቱ ተከራካሪና ኃይልን ስለ ሃይማኖታቸው ከመጠቀም የማይመለሱ ሰዎች ስለ ሃይማኖታቸው በቂና የጠለቀ ዕውቀትና ግንዛቤ የሌላቸው ሰዎች ናቸው።

የክርስትና መታወቂያችን ፍሬያችን እንጂ ዕድሜያችን አይደለም። ጌታችን ይህን ሲናገር *"ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ ...መልካም ዛፍ ክፉ ማፍራት ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም። መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል ወደ እሳትም ይጣላል። ስለዚህም ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ"* (ማቴ.7:16-19)። የዕድሜያችንና የቁጥር ብዛታችን ብቻቸውን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የመሆን ማረጋገጫ ሊሆኑን በፍጹም አይችሉም። አይሁዶች ለአራት ሺ ዓመታት የመሲህ የኪዳን ቃል ይዘው መቆየታቸው ከኪዳኑ ጋር እንዳይተላለፉ አላደረጋቸውም። የእግዚአብሔርን ቃል በግልጽ እየተቃወሙ ረዥም ዕድሜ ያስቆጠሩና በአስደማሚ ፍጥነት በማደግ ላይ ያሉ ሃይማኖቶች በዓለማችን ብዙ ናቸውና። ለምሳሌ፦ በዋርዊክ ዩኒቨርሲቲ መምህር ፕሮፌሰር ሮበርት ጃክሰን ሲናገሩ፦ ማን እንደመሠረተው የማይታወቅ ሀንዱይዝም ሃይማኖት ዕድሜው 5,000 ዓመታት ሲሆን ከ700 ሚሊዮን በላይ ተከታዮች አሉት። የጃፓኖች ቀዳሚ ሃይማኖት የሆነው ሽንቶይዝም የተጀመረው ከክርስቶስ ልደት በፊት ሲሆን በብዙ ሚሊዮን የሚገመቱ ጃፓናውያን በዚህ ሃይማኖት ይኖራሉ።

ከላይ የተጠቀሱ እነዚህ ዕድሜ ጠገብና በአጠቃላይ ከአንድ ቢሊዮን በላይ ተከታዮች ያሏቸው ሃይማኖቶች ዕድሜያቸውና የሰው ቁጥር ብዛት ብቻውን

የቤተ ክርስቲያን ዝምታ ለምን?

በወቅቱ ቤተ ክርስቲያን የሥርዓቱ ደጋፊ ሳትሆን ራስዋ የሥርዓቱ መሪዎችን የምትቀባ፣ ምክር የምትሰጥና ድምፅዋ በቤተ መቅደስና በቤተ መንግሥት እኩል የሚሰማላት ሆና ሳለች በወንጌል ስም ዘግናኝ ድርጊቶችን ዐዒዎች ሲፈጸሙ ለምን ዝም አለች? ቤተ ክርስቲያን በጊዜው ከዐዒዎቹ ጋር ጣትና ቀለበት ብትሆንም ሰይፍና ወንጌል አብሮ እንደማይሄዱ ያስተማረች አይመስልም። ይህ በኢየሱስ፣ በሐዋርያትና፣ በጥንት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የማይታወቅና በቃሉም የተወገዘ ድርጊት ቢሆንም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዝምታ ለምን እንዳለፈች አይታወቅም። ቤተ ክርስቲያን በጊዜው ለመቃወም ቢያስፈራትም በኋላ በወንጌል ስም የተደረጉ ኢሰብዓዊ ድርጊቶችን ለምን አላወገዘችም? ዛሬም እንኳ ያን ድርጊት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደነበር ሲነገር አይሰማም፣ ሲጸፍም አይታይም። ይህን ጥያቄ ማንሣትና መጻፍ በራሱ በዚህ ዘመን ባይሆን ኖሮ እንደሚያስወግር የታወቀ ነው። እንዲያውም ያን ዘግናኝ ድርጊት በክርስትና ስም የፈጸሙ ሰዎች አሉታዊ ድርጊታቸው በአንዳንዶች ዘንድ እንደ ልዩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገድል ተደርጉ መወሰዱ ያሳዝናል።

በክርስትና ስም ዛሬ ገሃድ የወጣ በሰይፍ የመዝመት አዋጅ ባይኖርም በአንዳንዶች አንደበት አልፎ አልፎ የሚሰማው አደገኛና የኃይል መፈክር መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆነ ካለፈው ታሪካችን ስላለመሆኑ መካድ ይቻል ይሆን? የመጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና ዓለምን ያንበረከከው በነገሥታትና "በክርስቲያኖች" ሰይፍ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተሰበከው ሰማያዊ ወንጌል ነው። ቤተ ክርስቲያን ለወንጌል ትሞታለች እንጂ ስለ ወንጌል አትገድልም። ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ሰይፍ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል እንጂ የሥጋ ሰይፍ አልነበራትም፤ ዛሬም የላትም፤ ወደ ፊትም አይኖራትም። የወንጌል ስብከት ከሌለ እውነተኛ ክርስትናም ሆነ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ልትኖር በፍጹም አትችልም። ሰው ልቡ በወንጌል ካልተለወጠ በሃይማኖት ስም ሌላውን ከመግደል እንደማይመለስ ታሪክ አሳይቶናል። ለውጥ ደግሞ ከድርጊት ሳይሆን ከአመለካከት እንደሚጀምር መዘንጋት የለበትም። ስለ ጠንካራ የእምነት አቋሟቸውና የኮሚኒዝም የክሂደት መንፈስ በገሃድ በመግጠማቸው በደርግ የተገደሉ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ዋና ጸሐፊ የነበሩ ቄስ ገዲና ቱምሳ ሲናገሩ፣

> *እኛ ክርስቲያኖች የማመን መብታችንና እምነት እንዲሰፋፋ ያለን ምኞት እንዲከበር ከፈለግን፣ የማያምኑ ሰዎችና ሊያምኑ የማይችሉ ሰዎችንም መብት ማክበር አለብን።*[158] ብለዋል።

የመንፈስ ሰይፍ የሆነውን ቃሉን ጥሎ የሥጋን ሰይፍ ለማንሣት የሚቋምጥ *"ክርስትና"* መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። በዚህ ዓይነት አመለካከት ዛሬም የሚሰቃዩ ካሉ ይህ የተሸናፊነት፣ የፍርሃትና ወንጌልን በፍጹም ያለማወቅ ምልክት ነው። እነዚህ ሰዎች ወደ መስቀሉ ፍቅር፣ ለሰዎች ልጆች ድነት ወደ

[158] ገዲና ቱምሳ፣ *ምስክርነት ደቀመዝሙርነት*፣ ገጽ 31

ተሰጠው የክርስቶስ ጸጋ፣ በንስሐ በር በመዝለቅ በወንጌል ዓለምን ለመለወጥ እንደ ገና በቃሉና በመንፈሱ መወለድ አለባቸው። ለዚህም ለኢትዮጵያ ክርስትና ተሐድሶ ያስፈልገናል። ኢትዮጵያ የሰላም ወንጌል እንጂ የሥጋ ሰይፍ ይበቃታል። መገዳደላችን ከእግዚአብሔር ጋር ከመጣላት፣ በቀልን በውስጣችን አርግዘን እያቃሰትን ከመኖር፣ ኋላ ከመቅረት፣ ምድሪቷ ከእርግማን በታች እንድትወድቅ ከማድረግ፣ በፈረንጅ በጥቁሩ አገር ለእንጀራ ልመና ከመሰደድ በቀር ለምንም አልረባንም። ወንጌል ለዚህ ሁሉ ብቸኛ ፈውስ ነው። ቃሉም እንዲህ ይላል:-

> *"መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁ ለእናንተ ሰላምን የምሥራች ብሎ ሰበከ፤ በእርሱ ሥራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና"* (ኤፌ.2:17)። *"በሩቅም በቅርብም ላለው ሰላም ሰላም ይሁን እፈውሰዋለሁ ይላል እግዚአብሔር። ክፉዎች ግን እንደሚንቀሳቀስ ባሕር ናቸው ጸጥ ይል ዘንድ ሊይችልምና ...ለክፉዎች ሰላም የላቸውም ይላል አምላኬ"* (ኢሳ.57፡ 21)።

ከክርስቶስ ምን እንማራለን?

ክርስትናን ከክርስቶስ እንማር። የክርስቶስ ቃል ያልገነነበት ክርስትና ከዘላለም ሞትና ኩነኔ የማይታደግ ባዶ ሃይማኖት ነው። ክርስቶስ የክርስትና መንገድ ነው። ከእርሱ ምን እንማራለን? መጽሐፍ ምን ይላል?

> *"እርሱ ኃጢአት አላደረገም ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም፡ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ፡"* (1ጴጥ.1:22-23)።

ሐዋርያው ጳውሎስ በስደትና በትልቅ ፈተና ተከበው ለነበሩ ለሮም ክርስቲያኖች እነርሱን ለሚያሳድዱና ለሚጠሉ አጻፋቸው ምን መሆን እንደሚገባ እንዲህ ብሎ መክሮ ነበር:-

> *"የሚያሳድዱአችሁን መርቁ፤ መርቁ እንጂ አትርገሙ። ...ልባሞች የሆናችሁ አይምሰሳችሁ። ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ። ...ተወዳጆች ሆይ ራሳችሁ አትበቀሉ ...ጠላትህ ግን ቢራብ አብላው ቢጠማ አጠጣው ይህን በማድረግህ በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከምራለህና። ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ"* (ሮሜ.12:12-21)።

ሌሎችን መውደዳችንና የወንጌል ተከታዮች መሆናችን የሚገለጸው ግን የዳንበትን ወንጌል ለማይወዱንና ለሚቃወሙን ሰዎች በፍቅር ለማድረስ ስንጨክን ብቻ ነው። ክርስቶስ ጠላቱ ወደ ሆነው ሰው ልጅ የመጣው በሰይፍ ሳይሆን በወንጌል ነው። ወግ አጥባቂና የሃይማኖት አክራሪ ለሆኑ አይሁዶች ወንጌልን ሰበከላቸው እንጂ ሰይፍ አልመዘዘባቸውም። ኢየሱስ ሰዎችን ያዳነው ለሰዎች ራሱን አሳልፎ በመስጠት እንጂ ለሃይማኖቱ በሰይፍ በመዋጋት አልነበረም። የክርስቶስ መንገድ የመስቀል መንገድ እንጂ የሰይፍ መንገድ አይደለም። መስቀል ተሸክመን እርሱን እንድንከተል እንጂ በእርሱ ስም ሌላውን ሰው መስቀል እንድናሸክም አልተጠራንም።

ኢየሱስ የሰጠን ሃይማኖትን ሳይሆን ሕይወቱን ነው። እርሱ ራሱ ሲናገር፦ "እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ" (ዮሐ.10:10) በማለት ሃይማኖት ሳይሆን ሕይወቱን እንደሰጠን ተናግሯል። በኢትዮጵያ "ክርስትናን" በኃይል ለማስፋፋትና ለዎችንም በግድ በማጥመቅ እንዲቆርቡ በማድረጋችን ብዙዎች ክርስቲያን መባልን እንጂ በእውነት ክርስቲያን ለመሆን ደንታ ቢስ እንዲሆኑ ምክንያት ሆነናል። ክርስቶስ የማይታወቅበት ክርስትና በአገራችን እንዲንሰራፋ ምክንያት ሆነናል። ብዙዎች ክርስቲያን ስለመሆናቸው እንጂ ስለ ጽድቅና ስለ ቅድስና ኑሮ፣ ያልዳነውን ዓለም በወንጌል ስለመድረሷ፣ የማያምኑትን ሰዎች ስለመውደድ፣ ስለመዳናችንና ስላዳነን ጌታ ስለመመስከር፣ ለዓለም እውነተኛ ብርሃንና ጨው ስለመሆን መናገር አልለመዱም። የክርስትና ሃይማኖት እንዳለን እንጂ የክርስቶስ ተከታዮች እንደሆንን አንደበታችንም ሆነ ሕይወታችን አይናገርም።

በክርስትና ሃይማኖት ስም መቁጠር የማይቻል በዓላትን እያከበርን ስለኖርን ለሥራ ባለን አጅግ የወረደ አመለካከት አገራችንን የድሆች ዋሻ አድርገናታል። ዛሬ ያን የተዛባ የሥራ ባሕላችንን ለመለወጥ መንግሥት፣ ቤተ ክርስቲያንንና ዜጐችን ብዙ ዋጋ እየከፈልን ነው። ከሁሉ በጣም አሳዛኙ በኢትዮጵያ ክርስትና ለድርሳናት፣ ለገድላት፣ ለስማዕታት፣ ለቅዱሳን አበው ትልቅ ቦታ መሰጠቱ ባይከፋም ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ያ ቦታ መነፈጉ ነው። ክርስቶስ ለአገራችን ክርስትና ባዕድ ይመስላል። በአጠቃላይ የኢየሱስ ወንጌል በኢትዮጵያ በትክክልና እንደሚገባ በእውነት አልተሰበከም። ለዚህም በሁለት ሺ ዓመት ያፈራነውን ፍሬ ብቻ ማየቱ ከበቂ በላይ ነው። ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም በአዲስ ታይምስ መጽሔት፦

> *የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አሁንም እውነቱን አላወጣችም፣ ለንድም ለሽመት ያክበከብ ጳጳስ የክርስቶስን ጸሐየ ጽድቅነት አምኖና ተቀብሎ እውነቱን ለመናገር የደፈረ አልተሰማም።*[159]

በማለት የክርስቶስ እውነት በዚህች ምድር እንደሚገባው እንዳልተሰበከ ለመግለጽ ጥረዋል። ለወንጌል ያልተሰጠና ወንጌልን ለሌሎች ያልሰጠ ሰው ወንጌልን በትክክል አልተቀበለም። የወንጌል እውነት ሲገባን በወንጌል ከመኖር አኩል ወንጌልን ለሌሎች በማድረስ ሂደት ሞት እንኳን ቢመጣ ራሳችንን በደስታ ስለሌሎች መዳን አሳልፈን እንሰጣለን እንጂ ማንንም ለመግደል አናደባም። ቃሉም፦ *"እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅር ለውቀናል፣ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳትንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል"* (1ዮሐ.3:16) ይላል።

[159] አዲስ ታይምስ፣ ቅፅ1፣ ቁጥ ሀዳር 2005 ዓ.ም ገጽ 30

ከሰይፍ የተወለደ ሰይፍ

ዐፄ ዮሐንስ በግድና በኃይል... እምቢተኛ የሆነው አፍንጫው እየተፍነከነ ምላሱ እየተቆረጠ የጭካኔ ቅጣት ተቀበለ። የፈራው ክርስትና ተነሣ። የቀረው አገሩን ጥሎ የዐፄ ዮሐንስ ሥልጣን ወደ ማይደርስበት የጠረፍ ግዛቶችና የጎረቤት አገሮች ተሰደደ።[160] *በስደት ሄደው ከሃይማኖት ወንኖቻቸው ጋር ተደባልቀው በዐፄ ዮሐንስ ላይ ሲያሴሩ የቆዩትና በመጨረሻም በ1881 ዓ.ም በመተማ ጦርነት ሊበቀሏቸው የቻሉት።*[161]

የመንግሥት አሐዳዊነት ለመንግሥቱ ጥንካሬ መደላደል የመሆኑን ያህል ያለ አግባብና በግድ በሕዝብ ጎሊናዊ ነጻነት ላይ ሲጫን ግን ለሕዝብና ለአገር መበታተን ዋነኛ መነሾም መሆኑን እንደገና ለማጤን እንገደዳለን።[162] ዶክተር ላጵሶ በግምት ከ1270-1577 በሰሎሞናዊ መንግሥትና በእስላሙ የዋለሰማ ሱልጣኖች መካከል የመሬት፣ የንግድ፣ የሃይማኖት፣ የሥልጣንና የጐሳ ጦርነቶች ለረጅም ጊዜ እንደተካሄዱ፣ ሰሎሞናውያን ወታደራዊ የኃይል ሚዛን በማግኘት እስላሞችን በጭቆና ሥርዓት ሲገዙ ቆይተው በመጨረሻም ምዕራፍ በ16ኛው ምዕተ ዓመት እስላሞች በኢማም አህመድ ግራኝ መሪነት ባካሄዱት የበቀል ጦርነት በክርስቲያን መንግሥትና ኅብረተሰብ ላይ በሕይወትና በንብረት ከፍተኛ ጥፋት እንዳደረሱ[163] ጽፈዋል። ከዚህም የተነሣ የአንድ አገር ሕዝቦች በሃይማኖትና በፖለቲካ ተከፋፍለው ባደረጉት የእርስ በርስ ጦርነት በሺዎች የሚገመቱ ዜጐች ተሰውተዋል፣ የአገር ሀብት ወድሞአል፣ ምትክ የሌላቸው ቅርሶች ዶጋ አመድ ሆነዋል፣ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ተቃጥለዋል፣ እንዲሁም እጅግ ብዙ ካህናት ተገድለዋል። ይልማ ደሬሳ በኢትዮጵያ ሽምብራ ኩሬ *(የዛሬ ምጆ አካባቢ)* በሚባል ቦታ በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል የተካሄደውን የእርስ በርስ ጦርነት ዘግናኝ አልቂት እንዲህ አስፈረዋል።

> *በዚያች ቀን ሽምብራ ኩሬ ላይ የሞቱት የኢትዮጵያ ሰዎች ከክርስቲያኑ ሠራዊት 12000፣ ከእስላሞች 6000 የሚበልጡ ወታደሮችና መኮንኖች ሲል ታሪክ መዝግቧል። ...ሽምብራ ኩሬ የኢትዮጵያ ታሪክ መንገድ የተለወጠችበት ቀንና ቦታ ነች።*[164] ብለዋል።

አስደናጋጩ ነገር ዛሬም የሃይማኖት እኩልነትን የሚገልጽ ሕግ ልንም ባያበጅላቸው ኖሮ ሰይፍ ለማንሣት የማይመለሱትን መቁጠር ይቻል ይሆን? ከላይ እንደተመለከትነው በኢትዮጵያ የሃይማኖትን አህዳዊነት በማስፈን ለሕዝብ አንድነት የማይበጅ ርካሽና ስውር የፖለቲካ ርዕዮተዓለም ለማስፋፋት ታቅደው የተካሄዱ ግጭቶችና ጦርነቶች የንጹሃንን ደም በከንቱ ከማፍሰስ፣ የአገርን ሀብት ከማውደም፣ በድህነትና በተስፋ መቁረጥ ሸለቆ ከመውደቅ፣ የአገርን ታሪክ ከማበላሸት፣ አብሮ የመኖርን መንፈስ

[160] ወንድዬ አሰ፣ ገጽ 63
[161] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ (1982 ዓ.ም) ገጽ 200
[162] ወንድዬ አሰ፣ ገጽ 63
[163] ላጵሶ ጌድሌዎ (ዶ/ር) (1999 ዓ.ም) ፣ የኢትዮጵያ የመከራ ሥርዓትና የሌርትራ ጥያቄ፣ ገጽ 143
[164] ይልማ ደሬሳ *(1999 ዓ.ም)* ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን፣ ሁለተኛ እትም፣ አዲስ አበባ ገጽ 66

ከማደፍረስ፣ የፈረሰችና የወደመች አገር ለቀጣዩ ትውልድ ከማውረስ፣ የቂምና የበቀል መንፈስ ከማስፋፋትና ምድርቷን ከእርግማን በታች ከማድረግ ያለፈ ሌላ ትርፍ አላመጡም። ይህን ርካሽና ኋላ ቀሪ አጀንዳ ይዘው ዛሬም የሚነሡ ካሉ እነርሱም ከታሪክ የማይማሩና ይህች በብዙ የተጐዳችን አገር ለማፈራረስ የቆረጡ የጥፋት መልዕክተኞች መሆን አለባቸው። ይህ ህቡዕ አጀንዳ ድሮም አልተሳከም አሁንም አይሳካም። ከዚህም በኋላ አይሳካም። ኢትዮጵያ እስላም፣ ክርስቲያኑ እንዲሁም ሃይማኖት የለሽና ባሕላዊ ሃይማኖት ተከታይ ሕዝቦች በአንድነት የሚኖሩባት አገር ነበረች፣ አሁንም ናት። ክርስትና ለሰዎች ልጆች የሞተው ጌታ የሚሰበክበት ሕይወት እንጂ በክርስትና ስም ሰዎች የሚገዳደለብት ሥጋዊ ግንባር በፍጹም አይደለም። የሰውን ነፍስ የፈጠረ እግዚአብሔር ሰውን መግደል አቅቶት ሰው በሃይማኖት ስም ሌላውን ሰው እንዲገድል አይልክም። ለወንጌል እውነት ከገደሉን እንድንሞት እንጂ ሰዎች ወንጌልን ስላልተቀበሉ ወይም ለጽድቅ ቀናዒ በመሆን ሌሎችን እንድንገድል መጽሐፍ ቅዱስ አያስተምረንም። እንዲያውም *"ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ" (1ዩሐ 4፡ 15)* ያለው ቃሉ ነው።

ኢየሱስም ሲናገር፡- *"ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ"(ዮሐ.10፡10)*። በማለት የራሱንና የሰይጣንን ተልዕኮ በግልጽ አስረድቶአል።

የእኛ ድርሻ ወንጌልን መስበክ ሲሆን የተሰበከውን ቃል በመጠቀም የሰውን ልብ የሚለውጠው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ትልቁ ችግር ሰው የቃሉም ሰባኪና የሰው ልብ ለዋጭ ለመሆን ከተነሣ ነው። ሰው ያሰበው አልሳካለት ሲል ከተስፋ መቁረጥ የተነሣ፣ በሥጋዊና አጋንንታዊ ሀሳብ ተጽዕኖ ሥር ወድቆ በሰይፍ ክቡር የሆነውን የሰው ነፍስ በእግዚአብሔር ስም ለማጥፋት ይነሣል። በሰይፍ የሚያምን ሃይማኖት በታሪክ ሌላ እንጂ በፍጹም ክርስትና አይደለም።

ነጻነትን የተራበ ነጻ ሕዝብ

ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ሲናገር፡- *"የእርሱ ወደ ሆነው መጣ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም" (ዮሐ.1፡14)*። እርሱ ፈጣሪ፣ መልዕክትና መልዕክተኛም ሆኖ የገዛ ሕዝቡ እንኪ ሲሉት እንደ እኛ ዐዒዎች በሰይፍ ሳይሆን በቃሉ ብቻ የማጥፋት አቅም እያለው ያለመጠቀሙ በሰው ውስጥ የፈጠረውን ነፃ ፈቃድ ማክበሩን ያመለክታል። እግዚአብሔር ለሰው የሰጠውን አሳቡን የመግለጥ ነፃነት ራሱም ለመጣስ አይፈልግም፤ ሰውም የሌላወን ሰው ነፃነት እንዲጥስ አይፈቅድም። የምድራችን የጥንት ሆነ የዛሬ ዐቢይ ችግራችን የራሳችን አሳብ እንጂ የሌላውን አሳብ ማስተናገድ አለመቻላችን ነው። የራሱ የአሳብ ነፃነት እንዲከበርለት የሚፈልግ ሰው የሌላ ሰውን ነፃ አሳብ መገደብ የለበትም። በእኛ ላይ እንዲደረግ የማንፈልገውን ነገር በሌሎች ላይ መፈጸም የለብንም።

ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ዘመኑን ቀንበቦ የያዘውን የሃይማኖት መንፈስ እንደ ሚከተለው ሕያው አድርጎ አስቀርቶታል፡-

> *አንድ ልብ ብሩህ ያበሻ ሰው መሬት ትዘራለች ብሎ ቢያስተምር አሁን በቅርቡ በሐረርጌ በዳኛ ተይዞ አልነበረምን፤ አሁን በ1900 ዓመታት ክክርስቶስ ልደት በኋላ አልፈው ሀያኛውን መቶ ዓመታት ስንጀምር አንድ ሰው የተዋሕዶን ሃይማኖት ቢነቅፍ ካዲስ አበባ ገበያ ላይ በደንጊያ አልተቀጠቀጠምን?*[165] በማለት ለልምዳችን ያለንን ቆራጥነት፣ እርምጃ፣ ለለውጥና ለአዲስ ሐሳብ ያለን አሉታዊ አቋም ምን እንደሚመስል በተግባር ያስረዳል።

በየትኛውም መልክ አዲስ አሳብ በኢትዮጵያ እንደ ጦር ይፈራል። አሳብን በአሳብ ከማሸነፍ ይልቅ የተለየ አሳብ የሚያነሡ ሰዎችን ማሳደድ፣ የገቡበት ጉድጓድ ገብቶ ካልገደልን ማለት፣ ለመግደል ባይቻል ደግሞ አሳቡን ትቶ ግለሰቡን ማጣጣልና በየመድረኩ ስሙን ማንኳሰስ እንደ ትልቅ ጀብዱ ይቆጠራል። ይህ የኋላ ቀሪነታችንና የድህነታችን ዐቢይ ምክንያትና ምልክት ነው። በአገራችን ጓደኛህ አንድን አሳብ ከተቃወመ አንተም የግድ መቃወም እንዳለብህ ያስባል። እርሱ የሚቃወመውን አንድን አሳብ ከደገፍክ እንደ ቀንደኛ ጠላቱ አድርጎ አንተን ለመቁጠር ጊዜ አይፈጅበትም። አስተማሪውን የሚበልጥ ተማሪ በአስተማሪው ይገፋል። በኢትዮጵያ አዲስ አሳብ፣ አማራጭ መንገድና ልዩ አቀራረብ በየትኛውም መልኩ ተቀባይነት የለውም። ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ እንጂ ጠቃሚ እንኳን ቢሆን አዲስ ነገር እንደ ብርቱ ጠላት ይታያል።

አንብበን ከምንረዳው እውነት ይልቅ ላልነበረ የአፈታሪክ ትልቅ ቦታ እንሰጣለን። በቋንቋችን አንብበን ከተረዳነው እውነት ይልቅ በማንሰማው ቋንቋ ለተነገረን ውሸት ጥብቅና እንቆማለን። ሰውን እስከ አንገት እንጂ እስከ ቁመታችን ማሳደግ አልለመድንም። በመረጃ የተደገፈና በእጅ ካለው እውነት ይልቅ በንግርት እየተላለፈ የመጣ ውሸት በብዙዎች ዘንድ ነቁጥ አልባ እውነት ተደርጋ ትታመናለች። ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ ድርሳናትና ገድላት በብዙ ይታመናሉ፤ ይጠቀሳሉ። እውነትም ይህን ውሸት እየተሻገረ የመጣ የቆየ አሳብ እንጂ የተሻሉና የጊዜው ብዙ አማራጭ ሐሳቦች ፍጹም አይፈለጉም። መስለህ እንድትኖር እንጂ ራስህን ፈልገህ እንድታገኝ አይፈለግም። በኢትዮጵያ በየትኛውም መልኩ የተለየ ሐሳብ እንዳታመነጭ በሕግ የተከለከለ ይመስላል። ውጤቱም ያለንበት ባዶነትና ኋላ ቀርነት እንደሆነ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ሲናገሩ፡-

> *የኢትዮጵያ ሊቃውንት "ሲወርድ ሲዋረድ" በሚል በማያስብና በማያሳስብ የቁልቁለት አስተሳሰብ ለብዙ ምእተ ዓመታት ተጓዙ፤ ውጤቱ ዛሬ ያለንበት ደረጃ ነው።*[166]

[165] ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ *ሥራዎቹ (2004 ዓ.ም)*፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡ ፕሬስ፣ ገጽ 14
[166] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 13*

የወንጌል አማኝ ያለ ሲሆን ሕፃናት አንዳንዱ "መናፍቅ፣ መናፍቅ" እያሉ ሲከተሉት፣ ትልልቆች ደግሞ ሲያዩት ሲያማትቡ አውቃለሁ። አንድ ቀን ከአዲስ አበባ ለእንግድነት የመጣ አንድ ዘመዳችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት፣ ከቃሉ አስረግጦ ለመጀመሪያ ጊዜ ነገረኝ። በጽድቅና በእውነት አርሱን በመከተል ለክብሩ እንዲኖር ነገረኝ። ይህ በፍጹም ለእኔ ባዕድ ልምምድ ነበር። ወዲያው ልቤ ተነካ፣ ኃጢአቴን ተናዝዤ የሕይወቴን ጌታና አዳኝ ወደ ልቤ አስገባሁ፣ በሕይወቴ ላይቼና ሰምቼ የማላውቀው ሰላምና ደስታ ከልቤ መፍሰቅ ጀመረ። ከዚያች ቀን አንሥቶ ለግሌ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብና መፀለይ ልምዴ ሆነ። ድሮ የማደርጋቸውን አንዳንድ መጥፎ ነገሮች ሁሉ ለማድረግ አቅም አጣሁ። ቤተሰቤም "ጴንጤ" እንደሆንኩ በወሬ ሰለሰሙና ባሕሪዬ ስለተለወጠ በዓይን ቁራኛ ይከታተሉኝ ጀመር። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ፈተና ተቀብዬ ስላለፍኩ በ2003 ዓ.ም ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ስመጣ በግልጽ ክወንጌላውያን ተማሪዎች ጋር ጌታን ማምለክ ጀመርኩ። ወዲያው ለቤተሰቦቼ ተነገራቸው። አባቴ ደውሎ "ጴንጤ ሆንሽ አይደል?" ብሎ ጠየቀኝ፣ እኔም ፈርቼ "አልሆንኩም" አልኩ። ለአረፍት ስሄድ አባቴ በሌሎች ተማሪዎች በኩል ይከታተለኝ እንደ ነበረና "ጴንጤ" እንደሆንኩ አርግጠኛ ሆኖ ነገረኝ። እኔም ፈርቼ እንደገና ካድኩ። ምንም ዓይነት ዕቃ ነክቼ እንዳላረከስ ተነገረኝ። የቁም እስረኛ ሆንኩ። ተወልጄ ባደከብት በአባቴ ቤት ባይተዋርነት ተሰማኝ። ሁሉም አገለሉኝ፣ እናቴ ተፀየፈችኝ፣ አባቴ ለዓይን ጠላኝ፣ እህት ወንድሞቼ እንደ አርኩስ ቆጥረው ራቁኝ።

በመጨረሻው ቤተዘመድና ቁስ ተጠርተው፡- "ጴንጤ ሆነሻል ወይ?" ብለው ሲጠይቁኝ አስካሁን በመዋሸቴ መንፈስ ቅዱስ ወቀሰኝ፣ ተረጋግቼም፡- "የሕይወቴ ቤዛ የሆነውን ክርስቶስን እንደ ግል አዳኜ አድርጌ አምኛለሁ፣ ከኃጢአት እሥራት ተፈትቻለሁ፣ ትልቅ ሰላምና እረፍት አለኝ፣ ብዘውዎች ይህን እውነት እናገራለሁ" ስል ሁሉም ተነሡብኝ፣ "ካሣሬ ጀምሮ የእኛ አይደለሽም፣ ለእኛ እንደ ሞተ ሰው ነሽ" ብለው ልብሴን በአንድ ፈሰታል ውስጥ አድርገው በውድቅት ሌሊት በ6:00 ሰዓት ከቤት አባረሩኝ። ይህን ሁሉ ቢያደርጉብኝም ልቤ ስለ እነርሱ ያዝናል፣ ዓይኔን ያበራው ጌታ ዓይናቸውን እንዲያበራ ስማቸውን እየጠራሁ ሳልፀልይላቸው ውዬ አድሬ አላውቅም። አንተም ከእኔ ጋር እንድትፀልይላቸው ነው፣ አለችኝ።

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ሃይማኖታዊ መብቶችን የሚመለከተው አንቀጽ 27 (1) *"ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የኅሊና እና የሃይማኖት ነፃነት አለው። ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻው ወይም ሌሎች የመግለጽ መብትን ያካትታል"* የሚለውንም አንርሣ። በአገራችን ወንድ ልጅ እንዳባቱ፣ ሴት ልጅ እንደ እናቷ የግድ መሆን እንዳለባቸው እንደ ድሮም ባይሆን አሁንም ይታመናል። የሥነ ቃል ዘይቤ፡- *"ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንዳባቱ አመልማሉ ስጡት ይፍተል እንደ እናቱ"* የሚለውን መጥቀስ በቂ ይመስለኛል። በአብዛኛው በአገራችን ልጅ የወላጅ ሐሳብ ባሪያ ነው። ልጆች የወላጆቹ ቅጂ እንጂ ራሳቸውን እንዲሆኑ አይፈቀድላቸውም። ልጅ የወላጅን መልካም ምላሌ መከተሉ ባይከፋም ራሱን ትቶ የግድ እነርሱን ለመሆን መታገል ግን የለበትም። ልጆች ደርሰው የራሳቸውን ውሳኔ ሲወስኑ መምከር፣ መነጋገር፣ ለእነርሱ መፀለይና በልበ ሰፊነት መንገድ ከማሳየት ያለፈ ማግለልና ማሳደድ የኢሰብዓውያን ድርጊት ነው።

ያሉት ሊቃውንት ሳይቀሩ የአሳብ ልዩነትን በዚህ ምድር የማስተናገድ ችግር እንደነበረባቸው ያመለክታል። ዳር ድንበራችን ሲነካ ሆ ብለን በነቂስ እናት አገር ወይም ሞት ብለን እንደምንወጣ በፈጠጡ ውስጣዊ ችግሮቻችን ላይ ተነጋግረን አዲስ አሳብ በማመንጨትና በመሞረድ ወደ አዲስ አቅጣጫ ተያይዘን መራመድን ብዙ አልለመድንም። አንዳንዶቻችን ብዙ ጊዜ በጠመንጃ እንጂ አሳብን በተሻለ አሳብ ከጠላትነት መንፈስ በፀዳ ሁኔታ ማሸነፍ የሚቻል አይመስለንም።

በምድራችን ጀግና ተብሎ የሚፎከርለት በጦርና በጎራዴ ታንክ የማረከና ሺ የገደለ ብቻ እንጂ በመጠቀ አዲሶ አሳብ አገርን ወደ ብልጽግና ያሻገረ ሰው አይደለም። ከዕውቀት ይልቅ በጉልበት እናምናለንና። የተባለውን ሁሉ እሺ የሚል እንጂ ይበልጥ ለማወቅ ጥያቄን የሚያነሣ እንደ ባላንጣ ይታያል። አንድ ወጥ አሳብ እንጂ ተመሣሣይ አሳብ ራሱ አይፈለግም። አማራጭ አስተሳሰብ ስላልለመድን በአማራጭ ሐሳብ ከተለመደው የድህነት ወህኒ መውጣት አልቻልንም። ከቃሉ በአብዛኛው ያፈነገጠ ስመ ክርስትና እና በዓለም የሌለ ትውፊት ተሸክመን ያለ እኛ ዓለም ሁሉ በስህተት ውስጥ እንዳለ ለመናገር ቅንጣት ያህል እፍረት አይሰማንም። በአገራችን በተለይ አዲስ አሳብ ይዞ መገለጥ ላልተጠበቀ አደጋ ራስን እንደ ማጋለጥ ነው። ስለዚህ አዲስ አሳብ ላመነጨ ሰው ውሎ ሳያድር መገለል፣ መወገዝ ወይም መወገድ ይደገስለታል። ስለዚህ የአገሬ ዓይናማ (ባለራእይ) ሁላ እዚህ እኖራለሁ ካለ ዓይኑን ስለምናጠፋ አገር ለቆ መጥፋትን ዕጣ ፈንታው ያደርጋል። ይህ ተለውጦ በኢትዮጵያ የአሳብ ልዕልና መከበር አለበት።

የአባቱን ሃይማኖት ለውጦ የተገኘ ልጅ በልጅነቱ በአባቱ ቤት ለመኖር ቀርቶ ዓይንህን ላፊር ተብሎ በደረሰበት እንደ ክፉ አውሬ ይታደናል። ዘመድ አዝማድ እህል ውሃ ቀርቶ ሰላምታ እንዳይሰጡት እግድ ይጣልበታል። አባቱ *"በከበርከብት አገር ሰሜን ታጠፋለህ?"* በማለት "በጠፋው" ስሙ ምትክ የልጁን ነፍስ ለማጥፋት በልጁ ላይ ሰይፍ ከማንሣት አይመለስም። አባት ሃይማኖቱን ለምን እንደለወጠ የልጁን አሳብ ልብ ሰጥቶ ማጤንን እንደ ትልቅ ሽንፈት ይቆጥራል። የልጅ ነገር! ተብሎ ሁሌም ከልጅ ቁም ነገር እንዳንጠብቅ ባሕላችን ከልክሎናልና። በየትኛውም መልኩ በአሳብ ላለመሸነፍ በአንባሩ ግን በጉልበት ለማሸነፍ ተዘጋጅተን የምንኖር እንመስላለን። ቤተሰብ ልጅ የእነርሱ ግልባጭ እንዲሆንላቸው እንጂ እግዚአብሔር የወሰነለትን አሳብ በማንሣት የራሱን ስብዕና ተሳብሶ በዘመኑ አዲስ ታሪክ እንዲሠራ ፈቃድ አይሰጡትም። ለምሳሌ፡- ሐምሌ 2 ቀን 2005 ዓ.ም በአዋሳ ያገኘኋት አንዲት እህት ከአገልግሎት በኋላ እንዲህ አለችኝ፡-

ስሜ ሚሚ ገ/ሚካኤል (ሰሜ ለዚህ ጽሑፍ ሲባል የተቀየረ) እባላለሁ፣ ከአዋሳ ዩኒቨርሲቲ ዘንድሮ በኢኮኖሚክስ በዲግሪ ተመርቂያለሁ፣ ቤተሰቦቼ የኦርቶዶክስ አማኞች ናቸው። እኔም ከልጅነቴ ጀምሮ እዚያው አከታተል ነበር። በአካባቢያችን የፐሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን በፍጹም የለም፣ አይታወቅምም። በስተማችን በብዙሃኑ የሚታወቅ በሥራ ምክንያት ወደ ከተማችን የመጣ አንድ

ይናገራል።[167] ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም ኃጢአት ሞቶ በትንሣኤ ኃይል የተነሣው በኢየሩሳሌም ነበር። መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ ወርዶ የመጀመሪያው የዓለማችን ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በኢየሩሳሌም ነበር (ሐዋ.2:1-4)። ሐዋርያት ወንጌልን በኃይልና በሥልጣን ከመስበክ አልፈው ኢየሩሳሌምን በትምህርታቸው ሞልታችኋል ተብሎ ተነገሮላቸዋል። በአንደኛው ክፍለ ዘመን ኢየሩሳሌም የወንጌል ማዕከል ነበረች። 335 ዓ.ም ቆስጠንጢኖስ ኢየሩሳሌምን የክርስቲያን ማዕከል ብሎ በመሰየም ቤተ ክርስቲያን ገንብቶ ነበር።

የአረብ የሙስሊም ካልፋዎች ኢየሩሳሌምን በ638 ዓ.ም ወረው ተቆጣጥረዋል። የክርስትና ማዕከል ተደርጋ ትቆጠር የነበረችው ኢየሩሳሌም የሙሲሊም ማዕከል ተደርጋ መቆጠር ጀመረች።[168] የኢየሩሳሌም ስም 830 ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰ ሲሆን እስላሞች ቅዱስ መጽሐፍ በሚሉት ቁርዓን አንዱም እንዳልተጠቀሰች ይነገራል። ዶክተር ዳንኤል ፒፔስ የሚሉት ባለሀብት እ.ኤ.አ 2006 በቁርዓን "ኢየሩሳሌም" የሚለውን አንድ ስም ላገኘ ሰው አንድ ሚሊዮን ዶላር ሽልማት እንደሚሰጥ ይፋ አድርጓል።[169] *በ11ኛው ክፍለ ዘመን የግብፁ ፋትመድ ካልፋ አሊሐኪም ቢአሚር ለላህ በኢየሩሳሌም የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት እንዲወድሙ አዝዞ እንደ ነበር ታሪክ ይናገራል።*[170] የአረብ ወራሪዎች፣ በቅዱሳን ላይ ያካሀዱ የነበረው ግፍና ጭቆና፣ ሃይማኖታቸውን በኃይል የማስፋፋት አካሄድ፣ እንዲሁም አብያተ ክርስቲያናትን ማውደማቸውና ወደ ኢየሩሳሌም የሃይማኖት ተጓዥ አውሮፓውያን ላይ ያካሂዱ የነበረው ዝርፊያና እንግልት የአውሮፓ *"ክርስቲያኖች"* የበቀል ዘመቻ *"ቢመስቀል"* ስም በኢየሩሳሌም ላይ እንዲያውጁ ምክንያት ከሆኑት መካከል ይጠቀሳል።[171] የመስቀል ጦርነት የአረብ ሙስሊም ወራሪዎች ኢሰብዓዊ ድርጊት የወለደው የአውሮፓ ክርስቲያን ነን ባዮች ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የበቀል እርምጃ ነው። በጁላይ 1099 ዓ.ም ፋትመድ ኢየሩሳሌምን የተነጠቀው በመስቀል ጦረኞች ነበር፦

> *በ1099 ዓ.ም ደግሞ የመስቀል ተዋጊዎቹ በመስቀል ምልክቱ ሥር በመሰብሰብ ኢየሩሳሌም ከተማን በወረራ ከያዟት በኋላ በዚያ ይኖሩ የነበሩትን ቁጥራቸው 40,000 የሚሆኑትን ሕዝብ እያረዱ በመግደል የከተማዋን አውራ ጎዳናዎች በደም ጎርፍ ያጥለቀለቁ ሲሆን ከዚህም ሌላ በከተማዋ የነበሩ የአይሁድ ምኩራቦችን በእሳት አጋይተዋል። በየምኩራቦቻቸው ተሰብስበው የምሕረትና የይቅርታ ጩኸታቸውን ያሰሙ የነበሩትን አይሁዳውያንንም እያሰቃዩ በመግደል ለእግዚአብሔር የምስጋና መዝሙራቸውን ይዘምሩ ነበር።*[172]

[167] "Do We Divide the Holiest Holy City?". Moment Magazine. Archived from the original on June 3, 2008. According to Eric H. Cline's tally in Jerusalem Besieged.

[168] http://www.gojerusalem.com/article_530/Islamic-Conquest-of-Jerusalem

[169] http://www.danielpipes.org/blog/570

[170] a'oz, Moshe and Nusseibeh, Sari (2000). *Jerusalem: Points of Friction, and Beyond* BRILL. pp.136–138

[171] Richard C. Csaplar, Jr., is a member of the Board of Trustees of Regent University' http://www.cbn.com/spirituallife/onlinediscipleship/understandingislam/IslamHistory0212.aspx

[172] ሰሎሞን አሰፋ (ተርጓሚ) *(2002 ቁም)፤ በኢየሩሳሌም ላይ የምትጠልቀው የመጨረሻዋ ጀምበር*፡ ፋ.ኢስ ትራዲንግ ኃላ. የተ.የግ. ማህ. ገጽ 124

በሰው ዘንድ ያስተቸናል፣ በምድር ሕግና በእግዚአብሔር ዘንድ ያስጠይቀናል። ልጆች ታላቅ መለኮታዊ ራእይ ተይዘላቸው ለዓላማ ከእግዚአብሔር ለወላጆች፣ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለአገርና ለዓለም የተሰጡ ስጦታዎች ናቸው። ወላጆች ልጆቻቸው እግዚአብሔር እነርሱን የፈጠረበትን የከበረ ዓላማ አግኝተው ለዚያ እንዲኖሩ አጋዥ እንጂ የልጆቻቸው የመኖር ዓላማ ቀያሽ መሐኒሶች አይደሉም። በአገራችን ከቤት፣ እስከ ቤተ ክርስቲያን፣ የነፃ ሐሳብ ምሀዳር እጅግ ጠባብ ነው። ይህ የኋላ መቅረታችንና የድህነታችን ዐቢይ ምክንያት ነው። ሕዳሴን በአንደበት እየሰበክን በአመለካከት የምንዋጋ ምስኪኖችም አድርጎናል። የሕዳሴ መሠረቱ የቴክኖሎጂ ምጥቀት፣ የምጣኔ ሀብት ብልጽግ እና የመሠረተ ልማት ዕድገት ብቻ ሳይሆን ከነፃ አሳብ ይጀምራል። የነፃ ሐሳብ ልዕልና ባልሰፈነበት ምድር እውነተኛ ዕድገት አይታሰብም። የሐሳብ ነፃነት ከወላጆች፣ ከቤተ ክርስቲያንና ከመንግሥት የሚሰፈርልን ቀለብ ሳይሆን ከፈጣሪያችን የተቸረን ጸጋ እንደሆነም መዘንጋት የለበትም። በቤተ ክርስቲያንም አንድ ሰው እግዚአብሔር የሰጠውን ጸጋ በአዲስ ራእይና ሐሳብ ለመፈጸም ከተነሣ በቀድሞ ወዳጆቹ ዕውቅና ተነፍጎት ወዲያው ማንም እንዳይቀበለው የውግዘት ደብዳቤ ይበተንበታል። የስህተት ትምህርት አስተማሪ የሚል ለሌዳም በጀርባው ለመለጠፍ እጅግ ፈጣኖች ነን። ባጠቃላይ በአገራችን የጥንቱና ጊዜ ያለፈበት ሐሳብ እንጂ አዲስ ሐሳብ፣ አዲስ አካሄድ፣ ለቆየው ችግራችን አዲስ መፍትሔና ራእይ በተለይ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ዛሬም ተቀባይነቱ እጅግ የወረደ ነው። ከዚህም የተነሣ በወረደ የሕይወት ዘይቤ ውስጥ ለብዙ ዘመናት ለመኪተን ተገደናል።

ይህ አመለካከት ከቤተ ክርስቲያን በሕዝቡ ላይ ተዛምቶ እያሰቃየን ይሆን? የሐሳብ ነፃነት በማይከበርበት አገር የሚኖሩ ሰዎች ከሞቱት እንደ መሻል ከተቆጠረ በመንቀሳቀሳቸው፣ በመብላታቸውና በመናገራቸው ብቻ ነው። የአሳብ ነፃነት ስንፈጠር የተሰጠን ሰው የመሆንና የማንነታችን ክፍል ስለሆነ ማንም አይሰጠንም ማንም አይወስድብንም። *"በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ቁሙ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ" (ገላ 5:1)*። እግዚአብሔር ይህን እርግማን በዚህ ዘመን ከእኛ ላይ በኃይል ይሰብራል። መፍትሔው በተሰበረ ልብና መንፈስ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነው።

የመስቀል ጦረኞችና ኢየሩሳሌም

ኢየሩሳሌም ዕድሜ ጠገብ የዓለማችን ጥንታዊ ከተማ ናት። ጁድዝምና ክርስትና እንደ ልዩና ታሪካዊ ከተማቸው ሲመለከቷት ሙሲሊሞችም ከመካና ከመድና ቀጥሎ ሦስተኛ ሃይማኖታዊ ከተማቸው እንደሆነች ይናገራሉ። ከዚህ የተነሣ ብዙዎች ኢየሩሳሌምን ለመቆጣጠር ደም ተቃብተዋል። ኢየሩሳሌም በረዥም ዘመን ታሪኳ በጦርነት ሙሉ በሙሉ ሁለቴ እንደወደመች፣ 23 ጊዜ በጠላት እንደ ተከበበች፣ 52 ጊዜ እንደ ተወረረች፣ 44 ጊዜ በተለያየ ኃይላት ተማርካ እንደ ተገዛች ታሪክ

ድነት በእምነት እንጂ ሰውን በመግደል አይገኝም። በመጽሐፍ ቅዱስ አንድ የሮም ወታደር ከዛሬ 2000 ዓመታት በፊት ሐዋርያ ጳውሎስን፦

"እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?" በማለት ያቀረበው ጥያቄ ዛሬም የብዙሃን ጥያቄ ነው። ሐዋርያ ጳውሎስ ግልጽና አጭር በሆነ መልስ፦ *"በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አመን አንተና ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ"(ሐዋ.16:31)* ብሎታል። ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያንም በጻፈው መልዕክቱ ድነት የሥራ ሳይሆን በእምነት ከእግዚአብሔር የምንቀበለው ስጦታ እንደሆነ ገልጾዋል፦ *"ጸጋው በእምነት አድናአችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም"(ኤፌ.2:8)*።

የክርስትና ዋና መሠረትና አስተማሪ ኢየሱስ፦ *"ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ሰፍራው መልስ" (ማቴ 26: 52)* በማለት የጴጥሮስን ሥጋዊ እርምጃ ኮንኖታል። በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠው አምላክ የሚዋጋልን ብርቱ እንጂ በሰው ሰይፍ ተዋግተንለት ዙፋኑን እንደ ምድራዊ መንግሥት የምናስጠብቅለት ደካማ አይደለም። ማንም ሳያስገድደው ፍጹም የጠፋንና ጠላቶች የነበረነውን ሞቶልን በጸጋው ካዳነን በኋላ እኛም በተራችን የፍቅር መልዕክተኞች እንዲንሆን ወደ ዓለም ልኮናል። በእውነት ከእርሱ ጋር ከታረቅን ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር *"እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ሰለ ክርስቶስ መልዕክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለክርስቶስ እንለምናለን" (2ቆሮ.5:21)* ለማለት እንችላለን። ይህ ማለት አንዋጋም ማለት ግን አይደለም። የዳነው በጦርነት ለጦርነት ነው። ጥያቄው ምን ዓይነት ጦርነት? የሚል ይሆናል። በእውነት የዳነ፣ የክርስቶስ ደቀመዝሙር የሆነና ቃሉ በውስጡ ያደረ ሰው መንፈሳዊ ጦረኛ ነው። የምንዋጋው ግን ከሰው ጋር ሳይሆን ከአጋንንት ኃይላት፣ በዓለም ካለው ክፋ አሠራር፣ በውስጣችን ካለው ጥላቻ፣ ቂም፣ በቀል፣ ከንቱ ውዳሴ፣ ትዕቢት፣ ካለመታዘዝ መንፈስና ከውሸት ጋር ነው።

"ባሰው ልማድ ምንም እንኳ የምንመላለስ ብንሆን እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም፤ የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና ምሽግን ለመሰበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤ የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን" (2ቆሮ.10:3-5)።

በአገራችንም ቢሆን በክርስትና ስም የተካሄዱ ስም የማጥፋት፣ የስደት፣ የእስራትና ግድያ ድርጊቶች በእግዚአብሔር ቃል የተወገዙና ተቀባይነት የሌላቸው ብቻ ሳይሆን በክርስትና ስም ክፋት ፈጻሚዎቹ ልበ ክርስቲያን ያለመሆናቸው ከመስቀል ጦረኞች ጋር አንድ ያደርጋቸዋል። የክርስትና ጉልበት የእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ብቻ ነው። ኢየሱስ በጡንቻ መጥቶ ካልተዋጋ በጡንቻ እንድንዋጋለት በፍጹም አይልከንም።

የመስቀል ጦረኞች በአንደበት እግዚአብሔርን እያመሰገኑና የምስጋና መዝሙሩ እየዘመሩ በእጃቸው ሰውን እያስቃዩ የፈጁ የባዶ ሃይማኖት እስረኞች እንጂ የወንጌል አማኞች አልነበሩም። የኢየሱስ ወንጌል ይህን በፍጹም አያስተምርም። ይህ በእግዚአብሔር ቃል ፍጹም የተወገዘ ድርጊት ነው። የልብና የአመለካከት ለውጥ በአማኞች ላይ የማያመጣ ክርስትና ከኢ-አማኒነት አይለይም። የመስቀል ጦርነት "ክርስቲያን" ጦረኞች ከ1095-1270 ዓ.ም ከልጅ እስከ አዋቂ የሆኑ የአውሮፓ ምዕመናን በኢየሩሳሌም ላይ ያወጁት የጥፋት ጦርነት ነበር። የመስቀል ጦርነት ተዋጊዎች የእስልምናን ወረራ ለመቀልበስና ኢየሩሳሌምን ለመቆጣጠር ከ200 ዓመታት በላይ 8 የመስቀል ጦርነቶች አካሂደዋል። እ.ኤ.አ ጁላይ1099 የመስቀል ጦረኞች የኢየሩሳሌምን ከተማ ሰብረው ሲገቡ ጌታችንን የገደሉ በማለት አይሁዶችን ጨፍጭፈዋል፣ ዘርፈዋል፣ ከተማዋንና ታሪካዊ ቦታዎችን ወደ አመድነት ቀይረዋል።[173] የመስቀል ጦረኞች በጥቅል ክርስቲያኖች የተባሉ እንጂ የአዲስ ኪዳን እውነት የገባቸውና የክርስቶስ ደቀ መዝሙር የሆኑ ልቤ ክርስቲያኖች አልነበሩም። የመስቀሉ ሥራ ያልገባቸው የመስቀሉ ወታደሮች፤ ጌታን በሕይወታቸው የማያውቁ ነገር ግን በጌታ ስም የሚዋደቁ፤ ባዶ ሃይማኖት እንጂ ሕይወታቸውንና አመለካከታቸውን የለወጠውን እውነት በልባቸው ያላሳደሩ አማኞች የተባሉ ኢ-አማኒያን ነበሩ።

ለዚህም ዋቢ ካስፈለገ የጦርነቱን አንዱን ዓላማ ማየት ከበቂ በላይ ነው። የመስቀል ጦርነት ብርቱ ሰባኪና ጦሬኞቹን በፀሎት ባርከው የሸኙት የካቶሊክ ፖፕ ኡርባን ዳግማዊ ነበሩ። ሕዝቡን ለመስቀል ጦርነት ሲያነሣሱ፦ *ለመስቀል ጦርነት ለሚሄዱ ሁሉ የኃጢአት ሥርየትንና የዘላለም ሕይወትን ለመስቀል ጦረኞች ብቻ ሳይሆን ለቤተሰቦቻቸውና ለወላጆቻቸው ጭምር ተሰፋ ሰጥተው ነበር።* ለኃጢአት ሥርየት ስለ ሰው ልጆች በፈሰሰው የኢየሱስ ደም መታጠብ ወይስ የሌላውን ሰው ደም በማፍሰስ? ሰው በወንጌል ልቡ ካልተለወጠ በስተቀር ቤተ ክርስቲያን በመሄዱ፣ በመቁረቡ፣ በጸም ፀሎት ብርቱ በመሆኑ፣ ስለ ክርስቶስ ቀንቶ ሌላው ላይ ዘምቶ በመግደሉና ክርስቲያን የሚባል ስም በመሸከሙ አይድንም። የወንጌል ሰባኪው ጳጳስ የሰላም ወንጌል ጠፍቶበት ሰይፍ በማንሣት ጦርነትን እንደ ጽድቅ ቆጥሮ ከሰበከ የጽድቅ ቃል በውስጡ ያላደረውና ልበ ክርስቲያን ያልሆነው ሕዝብ ምን ይሆን? ክርስቲያን ክርስቶስን የሕይወቱ ቤዛ አድርጎ የተቀበለ፣ በእግዚአብሔር ቃል የሚመራ፣ የዕድሜ ዘመን ደቀ መዝሙር ሆኖ ክርስቶስን የሚከተል፣ በመልካም ሥራው በዙሪያው ላሉት ሰዎች የክርስቶስን መልካም መዓዛ የሚገልጥ፣ ለራሱ ፈቃድ ሞቶ ለሞተለት ጌታ የሚኖር እንጂ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን የሰውን ልጅ ለመግደል የሚያደባ አውሬ መሆን በፍጹም የለበትም። ድነት የሚገኘው በመታገል ሳይሆን በጌታ በማመን ነው።

[173] Riley-Smith, Jonathan.*(1990). The Atlas of the Crusades New York: Facts on File, "High ideals were besmirched by cruelty and greed ... the Holy War was nothing more than a long act of intolerance in the name of God".* http://en.wikipedia.org/wiki/Crusades

ሐዋርያት ስለ ክርስትና ገደሉ ወይስ ተገደሉ?

የክርስትና መሠረት ክርስቶስ ነው። ክርስቶስ የተገለጠው በቃሉ ነው። የእግዚአብሔር ቃል የሆነው ደግሞ በሁለት ኪዳናት የተከፈለ በውስጡ 66 መጻሕፍት የያዘ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በዚህ መጽሐፍ የክርስትና ዋና መሥራች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ለማዳን ሞተ። እርሱም በቀጥታ ወደ ዓለም የላካቸው አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ሲሆኑ እንደ ጌታቸው ላመኑበት የወንጌል እውነትና ለወንጌል አገልግሎት ለማዕት ሆነዋል፦

1. *ጴጥሮስ - ራሱን ወደ ታች ተዘቅዝቆ በሮም ተሰቀለ በ64 ዓ.ም አካባቢ*
2. *የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ - በድንጋይ ከወገሩት በኋላ አንገቱ ተቀላ*
3. *ማቲያስ - በመጥረቢያ ተቆረጠ በ60 ዓ.ም አካባቢ*
4. *የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ - በሰላም ሞተ*
5. *የአልፍዩስ ልጅ ያዕቆብ - በ90 ዓመቱ በድንጋይ ተወግሮ ሞተ*
6. *ፊልጶስ - በስቅላት ተገደለ በ54 ዓ.ም አካባቢ*
7. *ቀነናዊው ስምዖን - በስቅላት ተገደለ*
8. *ታዴዎስ - በቀስት ተገደለ*
9. *ቶማስ - በጦር ተወግቶ በህንድ ተገደለ በ72 ዓ.ም አካባቢ*
10. *ቤርተሎሜዎስ - በሕይወት እያለ ቆዳውን ገፈው አንገቱን ቀርጠዋል።*
11. *የዘብድዮስ ልጅ ያዕቆብ - በሰይፍ አንገቱ ተቀላ በ44 ዓ.ም አካባቢ*
12. *የአስቆሮቱ ይሁዳን የተካ ማቲያስ - በድንጋይ ኩተወገረ በኋላ አንገቱ ተቀላ*

ሐዋርያት ለጌታ ብለው ወንጌልን ለሌሎች እየሰበኩ እንደሞቱ እንጂ ለወንጌልና ለቤተ ክርስቲያን ብለው አንዳች ሰው እንዳስገደሉም ሆነ እንደገደሉ ቀርቶ ሰውን እንደሰደቡ እንኳ ቃሉም ሆነ ታሪክ አይናገርም።

ቦብ ጊሊያም *"ታላቁን ተልዕኮ ለመፈፀም ቤተ ክርስቲያን ተካቦች ማሰልጠኛ መመሪያ"* በሚል ርዕስ ባዘጋጁት መጽሐፍ *"Jesus Freaks"* ከሚል መጽሐፍ ያገኙትን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የአንድ ቤተሰብ አስደናቂ ተጋድሎ ያነበብኩትን ይጠቅመናልና እንመልከት፦

ታሪኩ የተፈፀመው ኢ.ኤ.አ 1970ዎቹ በካምቦዲያ ነው። በ"ግድያ ሜዳዎች" ዘመን የሆነ። የህይም ቤተሰቦች ሌሊቱን በመሉ አንድ ላይ ታሰረው እርስ በርሳቸው እየተያዩ መሬት ላይ ተኝተው እንዲያድሩ ተደረገ። ክርስቲያኖች ስለሆኑና የታላቁ አብሮት ጠላቶች ተብለው በኮሚኒስቶች ስለተቆጠሩ በዚያው ዕለት ማለዳ ለመግደል ምልክት ተደረገባቸው። በማለዳም የህይም ቤተሰቦች እያንዳንዳቸው የየራሳቸውን መቃብር እንዲቆፍሩ ተደረገ። ገዳዮቻቸውም ለእነርሱ ቸርነትን በማድረግ ተንበርክከው ቢጋራ ፀልየው ለምታቸው

እንዲዘጋጁ ዕድል ሰጧቸው። የህይም ቤተሰብ ወላጅና ልጆች እጅ ለእጅ ተያይዘው ለራሳቸው በቆፈሩት ጉድጓድ አጠገብ ተንበረከኩ። ከዕሎት በኋላ ህይም እነርሱን ለመግደል የተዘጋጁ ፖሊሶች፣ ኮሚኒስቶቹንና ተመልካቾችን ንስሐ በመግባት ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው እንዲቀበሉ በትልቅ ድፍረት ወንጌልን ሰበኩላቸው፤ በዚህ ጊዜ ምት ያስፈራው ህይም ታናናሽ ልጆች መኳከል አንዱ ኩተንበረከከበት ተነሥቶ በቅርብ ወዳለው ጫካ ሮጦ ገባ። ህይም ልጁን ለክርስቶስ በክብር ወደ መሞት ዕድል ለመጥራት እንዲፈቅዱለት እጅግ ተረጋግቶ ወታደሮቹን አጥብቆ ተማፀናቸው። ተንበርክከም ልጁ ተመልሶ ለክርስቶስ ኢየሱስ ከእርሱ ጋር ተመልሶ እንዲሞት ይለምን ነበር። ድምፁንም ከፍ አድርጎ "ልጄ አስብ" ብሎ ጮኸ! "ጥቂት ተጨማሪ የሕይወት ቀናትን በዚህ ጫካ ውስጥ ኮብላይ ኩምትሆን ከቤተሰብህ ጋር ለጌታ ብለህ ሞተህ ወዲያውኑ ለዘላለም በመንግሥተ ሰማይ በነጻነት ከመኖር ጋር ይወዳደራልን?" ሲል ልጁም እያለቀሰ ለክርስቶስ ከቤተሰቡ ጋር ለመሞት ተመለሰ። ህይምም በታላቅ ደስታ ለገዳዮቹ "አሁን ለመሄድ ዝግጁ ነን" አለ። ነገር ግን ይህን ለማመን የሚያስቸግር ትዕንት ያዩ ከነበሩ ወታደሮችመኳከል አንዳቸውም ሊገድላቸው አልቻለም። በቦታው ያልነበረ ወታደር መጣና የህይምን ቤተሰብ በአንድነት ገደላቸው። ለማዕትም ሆኑ።

በድልና በታላቅ ደስታ ወደ ቀጣዩ ሕይወት በክብር በአንድነት ተሻገሩ። ይህም በሐዋርያት ዘመን ብቻ ሳይሆን ለክርስቶስ ራሳቸውን የሰጡ ቤተሰቦች ከልጅ እስከ አዋቂ ላዳናቸው ጌታ በፍቅር ሲሞቱ በዘመናችን ማየት የእውነተኛ ክርስትና መንገድ ዛሬም እንዳልደበዘዘ ያመለክተናል። ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያን አባቶችና በየዘመናቱ የኖሩ እውነተኛ ክርስቲያኖች ለወንጌል ሲሞቱ እንጂ ለወንጌል ሰውን ሲገድሉ ቃሉና ታሪክም አይናገርም። ታዲያ የኢትዮጵያው በተሰይ የጥንትና የመካከለኛ ዘመን "ክርስትና" ሀገር በቀል ካልሆነ በስተቀር ሰውን በግድ ክርስቲያን ማድረግ፣ እንቢ ያለውን መግደልና ማሳደድ፣ ወደ ቃሉ እንመለስ ብለው ሀሳባቸውን የገለጹትን አፍንጫቸውን መፎነን፣ ምላሳቸውን መቁረጥና በድንጋይ መውገር ከየት አመጣው? የዚህ ክርስትና መሠረቱ መጠናት የለበትም ወይ? አሁን ካልሆነ መቼ ይጠናል? እኛ ካላጠናን ማን ያጠናዋል? ይህ ክርስትና ተብሎ ተመሳሳይ ስያሜ የተሰጠው ሌላ ሃይማኖት ይሆን? ያልተጠየቀና ለአንዳንዶች የሞኝ ጥያቄ ሊመስል እንደሚችል እያወኩ ጥያቄዬን ልድገም የኃይል አጠቃቀምና በግድ ሰውን ክርስቲያን የማስባል አካሄድን ተደግፎ የተሰራጨው የኢትዮጵያ ክርስትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው? ካልሆነ ንስሐ መግባት አለብን።

በአዋጅ "ቤተ ክርስቲያንን" ማሠራት

እንደ ጸሐፊ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ ዘገባ በ1900 ዓ.ም በአዲስ አበባ የሚኒልክ ቤተ ክርስቲያን ግንባታ አዋጅ፦

የሃይማኖት መሠረቱ የቤተ ክርስቲያን ምልክቱ ቤተ ክርስቲያን መሥራት ነው። ለጉልበትህና ለገንዘብህ ሳስተህ ቤተ ክርስቲያን አልሠራም ብለህ የወሰለትህ ሰው በሰማይ ይፈረድብሃል። በምድርም ሹመትህን ገንዘብህን ታጣለህ። የሚል ቃል በየሀገሩ አዋጅ ተነገረ

እውነተኛ የክርስትና እምነት መሠረቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ወይስ "ቤተ ክርስቲያን" መሥራት? ሰው የሚፈረድበት የክርስቶስን ቤዛነት ስላልተቀበለ ወይስ "የቤተ ክርስቲያን" ሕንጻ ስላልሠራ? እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ቤተ ክርስቲያን የሚለው የአማርኛ ቃል የመጣው ኤክለሽያ /ekklesia/ ከሚለው የግሪክ ሁለት ቃል በውስጡ ከያዘው አንድ ቃል ሲሆን ትርጉሙም "ተጠርቶ የወጣ ጉባኤ" ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያን አራት ቁልፍ ነገሮችን በውስጧ አቅፋለች። እነርሱም፦ አንድነት፣ ቅድስና፣ ዓለም አቀፋዊትና ሐዋርያዊት መሆኗ ነው። እነዚህን ቁልፍ ነገሮች ማቀፍ የሚችለው ሕያው የቅዱሳን ጉባኤ እንጂ የብረት፣ የድንጋይ፣ የሲሚንቶ፣ የአፈር ወዘተ... ቁልል አይደለም። ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ "ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱና ትምህርቱ" በሚል ርዕስ በጻፈው መጽሐፍ መቅድም፦

> *ቤተ ክርስቲያን ስንል በክርስቶስ በተፈጸመው ድነት አምነው ለቃሉ እየታዘዙ ኖረው አገልግሎታቸውን ፈጽመው ያለፉ እና አሁንም በዚህ ዓለም ገና በጉዞ ላይ ያሉ ክርስቲያኖች እያንዳንዳቸውና በማኅበር ያላቸው አድነትና ኅብረት ነው*[174] ያሉት እውነት መጽሐፍ ቅዱሳዊና የቤተ ክርስቲያን ትርጉም አማኞች እንጂ ሕንፃን እንደማያመለክት በግልጽ አስቀምጧል።

ሐዋርያው ጳውሎስም የቤተ ክርስቲያንን ምንነት ሲገልጽ፦ *"እናንተ የክርስቶስ አካል ናችሁ እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ" (1ቆሮ.12:27)* ይላል። በክርስቶስ አምነን ወደ ቅዱሳን ጉበረት ስንቀላቀል ቤተ ክርስቲያን እንሆናለን እንጂ ወደ ቤተ ክርስቲያን አንሄድም። ቤተ ክርስቲያን ሰው ሠራሽ ሕንፃ ሳትሆን ከዓለም ክፋት በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ተጠርተው የወጡ የቅዱሳን አንድነት ናት። ቃሉም ስለዚህ ሲናገር፦ *"የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?...የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እናንተ ናችሁ"*(1ቆሮ.3:16-17)። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ከሆነ ዛሬ መስቀልን ጉልላታቸው ላይ አድርገን በሲሚንቶና በድንጋይ የገነባናቸው ውብ ሕንፃዎችና በየመንደሩ የሠራናቸው የላስቲክና የሸራ መሰብሰቢያዎች ከፀሐይ፣ ከብርድና ከዝናብ የምንጠለልባቸው ጸሎት ቤቶች እንጂ ቤተ ክርስቲያን አይደሉም። የፀሎት ቤት ሕንፃ በስፋት በዓለም ላይ መገንባት የተጀመረው በ4ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደሆነ ታሪክ ይናገራል። ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ቃል፣ መንፈስ፣ ጸጋና ምህረት እንጂ በሰው እጅ አትሠራም። በወንጌል ያልተሠራ ማንነት የንጉሥ አዋጅ በመፍራት ብቻ ሕንጻ ገንብቶና በግድ ክርስቲያን መባል እንጂ የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ተከታዮች መሆን ግን አይችሉም። ምክንያቱም የኢየሱስ ለመሆን በእርሱ ማመን እንጂ ለእርሱ ሕንጻ በመገንባት እንደምንጀመር ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሁሉ የተሰጠ ብቸኛ ቃሉ ይህን አይናገርም። መዳን መልካምን በማድረግ ሳይሆን የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ የሆነውን ክርስቶስን በማመን ይጀምራል። መልካም የምናደርገው ለመዳን ሳይሆን ስለዳንን ነው።

[174] ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ(2003 ዓ.ም)፣ ዮሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱና ትምህርቱ፣ አዲስ አበባ፣ ገጽ 7

ለኢትዮጵያ ሉአላዊነት፣ አንድነትና ለሕዝቧ ነፃነት ቀደምት አባቶች ለከፈሉት ታላቅ መሥዋዕትነት አድናቆት ይገባቸዋል። *"አባቶችን የማያከብር ኩተዋረ የዱር አውሬ በላይ የከፋ ነው"* የቻይናውያን ብሂል እንደሚለው አባትን የማያከብር ልጅ በእግዚአብሔር ቃልና በባሕላችንም ውግዝ እንደሆነ ይታወቃል። አባቶችን ማክበር ማለት ግን በጠንካራ ነገራቸው ላይ መገንባትና ስህተታቸውን ያለመድገም እንደሆነ መታወቅ አለበት። የአገርን አንድነት በማስጠበቅ፣ የውጪ ወራሪ ኃይላትን በመቀልበስ፣ ቀለመ ብዙ ባሕል ባለቤቶች ስላደረጉንና ለዚህች አገር ለከፈሉት ታላቅ ዋጋ አድናቆትና ክብር ይገባቸዋል። ሁሌም እንኮራባቸዋለን። በሌላ መልኩ አንዳንዶች በክርስትና ስም ስላካሄዱት መጠነ ሰፊ ወረራ፣ በጦርነት ክርስትናን በማስፋፋትና ቤተ ክርስቲያንን በዘመቻ የመገንባት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮና አካሄድ በእነርሱ ምትክ እኛ ንስሐ ልንገባ ይገባናል። በኢትዮጵያ የተሰበከው ክርስትና በአብዛኛው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ሥር የሰደደ፣ የነቢያትንና የሐዋርያትን ዱካ የተከተለና በሰዎች የሕይወት ለውጥ ላይ ትኩረት ያደረገ ሳይሆን በባዶ ትውፊት፣ በተረት፣ በኃይል፣ በኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥርዓት ላይ የተመሠረተ ነው የሚባለው ከዚህ የተነሣ ነው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ያስፈልጋታል። የቀደሙ አንዳንድ አባቶቻችን የኖሩበት ክርስትና እና የመሩት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሕይወት ዘይቤዎች በዘመናችንም እጅግ ገዝፎ የሚታይ የባሰ ጥራዝ ነጠቅነት ዐቢይ ምልክት ነው። ይህም ዕድሜ ጠገብ የኢትዮጵያን ክርስትና እንደ ሌሎች አገራት ባለ ብዙ አምንታዊ ተጽዕኖ ባለቤት እንዳይሆን አግዶታል። እግዚአብሔር ልባችንን ወደ ራሱ ያቅና።

የአገራችን ክርስትና የእግዚአብሔርን ቃልና መንፈስ ማዕከል ስላላደረገ የሚጠበቅበትን ግላዊ፣ ቤተ ክርስቲያናዊ፣ አገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ለውጥና ዕድገት እንደሚገባው የማምጣት አውራ ሚና መጫወት አልቻለም። በዚሁ ከቀጠለም ተጽዕኖ መፍጠር ቀርቶ ባለበት ሁኔታ መሰንበት አይችልም። ብዙዎች በምድራችን በዕድሜ ጠገቡ ክርስትና ሃይማኖት ያለቅጥ ለመኩራራት እንጂ እንደ ዕደሜው የሚጠበቅበትን ምን አምንታዊ ለውጥ በዚህች አገር ላይ አመጣ? የሚል ጥያቄ መጠየቅን እንደ አመጽ ይቆጥራሉ። የዳነው ለዓለም የክርስቶስን ወንጌል በማቀበል የበረከት ምክንያት እንድንሆን መሆኑ የወንጌል እውነት ለገባው አማኝ ግልጽ ነው። እንደ ዕድሜያችን ወንጌልን ለሌሎች ቀርቶ ለራሳችን በወጉ ያለማሰራጨታችን በክርስትናችን ላይ ጥያቄ አያስነሣም ወይ? ክርስትናችን በሥራ ባሕላችን፣ በአመላካከታችን፣ በኅብረተሰባችን የሕይወት ለውጥና በአገር ግንባታ የተሻለ ሚና እንዲኖረን ለምን አላደረገንም? የሚሉ ጥያቄዎችን ማስነሣቱ አይቀሬ ነው። በአምንታዊ መልኩ መለወጥን እንቢ ካልን ለውጡ በአሉታዊ መልኩ እንዳይለውጠን እንቢ ማለት አንችልም። የተባለውንና የሰጡትን ሁሉ ሳይጠይቅ ተሸክሞ የሚጓዝ ትውልድ እያለፈ ሲሆን ጠያቂ፣ አንባቢ፣ ለውጥ ፈላጊና ለውጥ አራማጅ ትውልድ በኃይል እየተነሣ መሆኑ ነገሮች እንደዱሮ እንዳይቀጥሉ ያደርጋል።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራስዋን በማየት በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ብትመለስ፣ በወንጌል ለዓለም የበረከት ምክንያት ትሆናለች፤ ዕድሜዋን የሚመስል ዓለም አቀፋዊ የጽድቅ ፍሬዎች ባለቤት ትሆናለች፤ ሰው ሰው ሳይሆን ኢየሱስ፣ ኢየሱስን ትሸታለች፤ ኢትዮጵያ በእውነት ትባረካለች፤ የዚህች ምድር ሕዳሴ ሁለንተናዊ ይሆናል። የልብ ጥንካሬና ትዕቢት ካለ የባሰ ጥፋት፣ ስብራትና ውርደት መምጣቱ አይቀሬ ነው። ወደ እግዚአብሔር እንመለስ።

ዛሬን በቅጡ ለማወቅ ትናንትን የመረዳት ግዴታ

ድንጋይ፣ አሎሎም ሆነ ጦር አርቀን ወደ ፊት ለመወርወር ወደ ኋላ መንደርደር አማራጭ እንደሌለው ሁሉ መጭውን አርቀን ለማየት ወደ ኋላ ሄደን ታሪክን መቃኘት የግድ ይላል። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንግሊዝን በድል የመሩ ጠቅላይ ሚኒስተር ዊንስተን ቸርችልም ስለዚህ ሲናገሩ፡- *"The farther back we look, the farther ahead we are able to see."* በግርድፉ ሲተረጎም *"ያለፈውን ወደኋላ ዞር ብለን ለማየት በቻልን መጠን የወደፊቱንም አርቀን ለመመልከት እንችላለን።"* ወደ ፊት አርቀን ለማየት ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ዕውቅና መስጠትና ያለፈ ታሪካችንን መቃኘት የግድ ነው። መለኮታዊ ራእይን አንግበን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ እንድንከፍት እግዚአብሔር ከእኛ ይፈልጋል።

እግዚአብሔር በዘመናችን ምን እንደሠራን የሚጠይቀን በሀገራችን ታሪክና በቤተ እምነታችን ስም ላይ ተንተርሶ ሳይሆን በሰጠን ቃሉ፣ ጸጋና ራእይ ላይ ተመሥርቶ ነው። የአባቶቻችን ድል እኛ የሚበልጥ ታሪክ እንድንሠራ ካላነሣሳን፣ ከአለታዊ ታሪካቸው ካልተማርን ታሪኩ ለእነርሱ እንጂ ለእኛ ዋጋ የለውም። ትልቁ ጥያቄ አባቶቻችን ዛሬ እኛ የምንመካባቸውንና የምንደገፍባቸውን ታላላቅ ሥራዎች ከሠሩ እኛ ለልጆቻችንና ለቀጣዩ ትውልድ ምን የላቀ ሥራ ሠርተን እንለፍ? ነው። በኢትዮጵያ ጥንታዊነት ያለቅጥ የሚኮራና የዛሬዪቷን ኢትዮጵያ ውርደትና ውድቀት ለመለወጥ ራእይ አልባ የሆነ ሰው፤ የኢትዮጵያውያንን ቁጥር ከመጨመር ውጭ ለኢትዮጵያ አንዳች አይፈይድላትም። የአደዋን ድል ብቻ እያነሣ ዘራፍ የሚል፣ የዛሬን ብርቱ ጠላት ድህነትና ድንቁርናን ለመግጠም ምክንያት የሚደረድር እርሱ ለራሱም አይጠቅምም። በሁለት ሺ ዓመታት ፍሬ አልባ የክርስትና ስም ያለቅጥ የሚመካና በጥፋት ላይ ያለውን ዓለም በወንጌል ለመድረስ ደንታ የሌለውና የሃይማኖቱ ገድል ሰባኪ እርሱ የክርስቶስ የመስቀል ምንነት አልገባውም። ስለ አክሱም ሐውልቶች ገናናነት ለመተረክ ጊዜ የማይበቃው ዛሬ ብዙ የፈረሰውን የአገርን ቅጥር ለመገንባት ልብ የከዳው እርሱ ወሬን ሥራው ያደረገ ሰው ነው።

በዘመን ጠገብ ሃይማኖታዊ ትውፊት ከልክ ያለፈ የሚኩራራና የጊዜውን መለኮታዊ አጀንዳና መገለጥ ለመስማት ጆሮ የሌለው እርሱ ሃይማኖተኛ እንጂ የክርስቶስ እውነት የበራለት ክርስቲያን አይደለም። ትናንት በተገነባው የታሪክ ጥላ ሥር ሆኖ ዛሬ ሕይወቱ የፈረሰበትና ግራ የተጋባ እርሱ ራሱ የአገር ዕዳና ሸክም ነው። አንድ ጸሐፊ "ቅኝ የተገዛው ማነው?" በሚል ርዕስ ኢትዮጵያውያን ያለንበትን አሳዛኝ ሁኔታ ሲገልጹ *"ዛሬ እየኖርን ላይደለም። ያለፈ ታሪክ እያወራን ጉንጫችንን ሰናሰፋ ዛሬ ጥሎን ሄዷል"*[175] ብለዋል።

የኢትዮጵያና የኤርትራ ጦርነት የልብ ጥንካሬ ያመጣብን ይሆን?

እ.ኤ.አ በ1997 የአፍሪካ አገራትና ከዓለም ዙርያ የተሰበሰቡ የፀሎት ሰዎች የሆኑ ተወካዮች የተካፈሉበት የመላ አፍሪካ የፀሎት ኮንፍራንስ በአዲስ አበባ በሚገኘው *"ባለአፍሪካ አንድነት ድርጅት"* የስብሰባ ማዕከል ተካሂዶ ነበር። በገባኤው ላይ ልዩ የእግዚአብሔር መገኘት ነበር፤ ለአፍሪካ አገሮች ሁሉ በየተራው የምልጃ ፀሎት ተደርጓል። ከዚህ ፕሮግራም አዘጋጆች መካከል አንዱ የሆኑ ሪቨረንድ ጆን ማልንድ የሚባሉ ዩጋንዳዊ የእግዚአብሔር ሰው ስለ ኢትዮጵያና ኤርትራ በንስሐ ጥሪ ዕድል ያለመጠቀማቸው *"Tranforming Our World"* በሚለው መጽሐፋቸው እንዲህ ዘግበዋል፡-

> *ለኢትዮጵያና ለኤርትራ የምልጃ ፀሎት የሚደረግበት ጊዜ ደረሰ። ከሁለቱም አገሮች የመጡ ተወካዮች ወደ መድረክ ተጋበዙ። በምድራቸው በእርስ በርስ ጦርነት ስለተጨፈጨፉ፣ ምድራቸውን በሰው ደም የሸፈነ እርግማን ስላለ ከልብ እርስ በርስ ይቅር በመባባል በንስሐ በእግዚአብሔር ፊት እንዲወድቁ ጥሪ ተላለፈላቸው። ጉባኤው ስለ ሁለቱ አገራት በእንባ የምልጃው ፀሎት ልዩ መቃተት ውስጥ ገባ። የእግዚአብሔር ሀልዎት በመካከላችን ስለነበረ የኢትዮጵያና የኤርትራ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በብርቱ እንባ ውስጥ ሆነው ይቅር እየተባባሉ ሳሉ ነበረውን ሁኔታ የሚጋፋ መንፈስ ሲመጣብኝ፤ በዚህ ሁኔታ መካከል እንገቱን አቀርቅሬ ሳለሁ እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፡-*
>
> *"እነዚህ (የኤርትራና የኢትዮጵያ ተወካዮች ሆነው በመድረኩ እያለቀሱ የምፀልዩ) በእኔ ላይ እየሳገጡ ነው። እየደረገት ያለው ነገር ሁሉ ከልባቸው አይደለም። ሁሉም ለሰዎች ታይታ ነው፤ በምድራቸው ላይ በከንቱ የፈሰሰው ደም ወደ እኔ እየጮኸ ስላለ ልቤ እጅግ አዝኗል። ጠላት ሌላ የጅምላ ጭፍጨፋ በምድራቸው ሊያካሂድ የፈሰሰውን ደም እየተጠቀመ ነው። አገልጋዮች እየሳገጡ ነው፤ አለኝ። ውስጤ ተሰበረ፤ እጅግም አዘንኩ ሳለሁ፤ ከኢየሩሳሌም የፀሎት አገልጋዮች አንዱ የሆነው ጓደኛዬ ቶሚ ሀሰሲ ወደ እኔ መጥቶ "ካእግዚአብሔር የሆነ ቃል እንዳለህ እርግጠኛ ነኝ" ስለኝ "ግራ ገብቶኝ እባክህን ሰብቻዬ ተወኝ" አልኩት። በመጨረሻም ከተቀበልኩት መልዕክት ጥቂት ነገር ነገርኩት። እርሱም፡- የተቀበልከውን መልዕክት መናገር አለብህ ብሎ ገፋፋኝ። እኔም*

[175] *አዲስ ጉዳይ ማያዝያ 27 ቀን 2004 ዓ.ም ገጽ 8*

እያመነታሁ ወደ ፊት ወጥቼ። ሁሉንም ሳይሆን ጥቂቱን ተናገርኩ። ከጌታ የተቀበልኩትን ቃል እንዲህ ብዬ ተናገርኩ፦-

እግዚአብሔር በእውነተኛ ልብ፣ በተሰበረ መንፈስ በንስሐ ካልተመለሳችሁ ጠላት በተከፈተው በር ተጨማሪ ደም በምድራችሁ ያፈሳል፤ እናንተ ከኤርትራና ከኢትዮጵያ የተወጣጣችሁ መሪዎች ለ21 ቀናት ተያይዛችሁ ወደ ተራራ በመውጣት በፊቱም ራሳችሁን በማዋረድ እግዚአብሔር ምድራችሁን ከእርግማን እንዲያጸዳ መጠየቅና ከዚያም ተያይዛችሁ በምድራች ሁሉ ላይ ይቅርታ ማወጅ አለባችሁ። ይህን ካደረጋችሁ ምድራችሁ ይጸዳል ካላደረጋችሁ ግን በሚቀጥሉት ስድስት ወራት ተጨማሪ እልቅትና የደም መፋሰስ ይሆናል።

በእራት ጊዜ ለቶም ጌታ የነገረኝ ሁሉን ነገርኩት። እርሱም *"ሁሉን ነገር ካልነገርካቸው ተጠያቂው አንተ ነህ፤"* አለኝ።

እኔም፦- ***"እግዚአብሔር ተናገር ያለኝን ሲናገር እነርሱ እየተቀበሉኝ እኮ አይደለም"*** ሲለው እርሱ፦- *"አንተ የተቀበልከውን ተናገር እነርሱ ባለ መታዘዛቸው በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂዎች ናቸው"* አለኝ። እኔም ወደ ኮንፍራንሱ ተመልሼ ጌታ የተናገረኝን ቆመ ሁሉንም ተናገርኩ፤ ወዲያውም ከአደራሹ ወጥቼ እንደሄድኩ፤ ከአዘጋጆቹ አንዱ ተነሥቶ እንዲህ አለ፦- *"እግዚአብሔር በእውነት ይህን የተናገረ ሓይመሰለኝም፤ በመንፈሱ በተከከል ንስሐ እንደገባንና ይቅር እንደተባባልን እረዳለሁ። ሁላችንም ቆመን በእግዚአብሔር ፊት እንደሰት"* አለ፤ እኔም ወደ ይጋንዳ በረርኩ።

የእግዚአብሔር ሰው ማልንድ ኢትዮጵያና ኤርትራን ወክለው በቦታው የተገኙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር የተናገረውን ቸል በማለታቸው ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር እንዲህ አላለም፤ ብለው ለእውነተኛ ንስሐ ልባቸውን በማደንደናቸው በምድራቸው ያመጣውን የመዘዝ ውጤት እንዲህ ጽፈዋል፦- አራትና አምስት ወራት እንደቆየን ለንደን ሳለሁ ቶም ከአስራኤል ደውሎልኝ *"ኤርትራና ኢትዮጵያ ወደ ጦርነት እንደ ተመለሱ ሰምተሃል ወይ"* አለኝ።[176]

የጦርነቱ አስደንጋጪ ውጤት?

እግዚአብሔር በባሪያው በኩል እንደተናገረ ከንስሐ ይልቅ በራስ ማስተዋል መደገፋችንና ወደ እግዚአብሔር የመመለስና ራስን የማዋረድ ጥሪ ባለመቀበላችን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኖብን ይሆን? የእግዚአብሔር ሰው እንደተናገሩት ኢ.ኤ.አ 1998-2000 በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል የተደረገውን ጦርነት አንዳንድ ጸሐፊዎች በሁለት የዓለማችን ድሆች መካከል ውድ ዋጋ ተከፍሎ የተደረገ ጦርነት ብለውታል።[177] *በዚህ ጦርነት*

[176] John Mulinde *(2005), TRANSFORMING YOUR WORLD,* Prograssive Vision Publising, p.25-26

[177] *http: en.wikipedia.org wiki Eritrean Ethiopian_War*

በአጠቃላይ ወደ 70,000 የሚደርሱ ወታደሮች ከሁለቱም ወገን እንደሞቱ ቢቢሲና ሮይተርስን ጨምሮ የዓለም አቀፍ ብዙኃን መገናኛዎች ግምታቸውን ይፋ አድርገዋል።[178] ቢቢሲ የ*Ethiopian Economic Policy Research Institute* መረጃን ዋቢ በማድረግ ያዘጋጀውን IRIN አገለት 8 2011 ይፋ እንዳደረገው በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል በተደረገው የሁለት ዓመት ተኩል ጦርነት 2.9 ቢሊዮን ዶላር ወይም ወደ 50,000,000,000 (*ሃምሳ ቢሊዮን የሚጠጋ ብር) ወጪ እንደሆነ ይጠቁማል።*[179] ይህ ገንዘብ የህዳሴውን ግድብ ለመገንባት ቢውል ኖሮ ከግማሽ በላይ መሸፈን እንደሚችል አንዘንጋ።[180]

ዛሬም የኤርትራ አብዛኛው ቤተ ክርስቲያናት ተዘግተዋል፤ ብዙ መሪዎች ለማዕት ሆነዋል፣ ሌሎች በግዞት ቤት በመማቀቅ ላይ ሲሆኑ ብዙ ቅዱሳን በስደት በዓለም ላይ ተበትነዋል። ምድራቸው በትልቅ ጭንቅ ውስጥ ወድቃለች። ዛሬ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደ ኤርትራ ቤተ ክርስቲያን የነፃነት ችግር የለባትም። በታሪክ የሃይማኖት ነፃነት በሕግ ተረጋግጦ ዜጐች ሃይማኖታቸውን በአደባባይ የሚያካሂዱበት እንደዚህ ዓይነት ዘመን በኢትዮጵያ አይታወቅም። ስለዚህም እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። የኢትዮጵያንም መንግሥት እግዚአብሔር ይባርክ። በተቃረኒው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከራሷ አለማስተዋልና ድካም የተነሣ በተገኘው አንጻራዊ ነፃነት እንደሚገባ እንዳልተጠቀመችና በትልቅ መንፈሳዊ ቀውስ ውስጥ እንዳለች ዓይነ ብሩህ የሆኑ ጥቂቶች ብቻ ይናገራሉ።

ዛሬ በምድራችን እየተዘራን ያለው እኩይ ዘር

የተገኘውን ነፃነት ራሳችንን ለማፈራረስ እየተጠቀምንበት ያለ ይመስላል። ትውልዱ የወንጌልን እውነት ይዞ ለአገርና ለዓለም ጠቃሚ እንዳይሆን በወንጌል ስም የምኞት ሻንጣ አሸክመን ግራ አጋብተነዋል። "በትንቢት"ና "መገለጥ" ስም የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን አደጋ ላይ ወድቋል። በብዙኃኑ ድህነት ጥቂቶች ከብረዋል፤ ቤተ ክርስቲያን የሐሰተኛ ነቢያቶችና በገንዘባቸው የሚያስቡ "ባለሀብቶች"ና የአመራር ክህሎት የሌላቸው "መሪዎች" መፈንጫ ሆናለች። ይህ እግዚአብሔርን የሚፈሩ እውነተኛ መሪዎችንና ባለሀብቶች አይመለከትም። ትልቅ የሞራል ውድቀት እንደ ቀላል ነገር ከመቆጠሩ የተነሣ ለመሪ አገልጋዮች ፊቶ ማግባት እንደ ወረርሽን ከመዛመቱ የተነሣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌላ የተለየ መገለጥ የመጣልን ይመስላል። በጣም የሚያሳዝነው ይህን የሚያደርጉ አገልጋዮችን የእግዚአብሔርን ቃል በመተላለፋቸውና መጥፎ ምሳሌ ለእግዚአብሔር ሕዝብ በመሆናቸው ቤተ ክርስቲያን ድርጊቱን በገሃድ ስትገስጽ አትታይም፤ እንዲሁም የዚህ ድርጊት ፈጻሚ የሆኑ አገልጋዮችም ልባዊ ንስሐ ሲገቡና

[178] *"most reports put the total war casualties from both sides as being around 70,000." http://en.wikipedia.org/wiki/Eritrean%E2%80%93Ethiopian_War#cite_note-67*

[179] http://www.irinnews.org/Report/24680/ETHIOPIA-War-cost-over-US-2-9-billion Thus the military expenditure became 49.8 percent of the country's total recurrent expenditure," the... Ethiopian Economic Policy Research Institute... the report said. The border war, which lasted two and a half years, cost Ethiopia more than US $2.9 billion, the report asserts.

[180] *ዓጋአብ በቀለ (2005 ዓ.ም) ፣ ባለራእይነት፣ ርኖቡት አታሚዎች፣ ገጽ 67*

ለጊዜው እንኳን አገልግሎት ሲያቆሙ ያለመታየታቸው በሕዝቡ ዘንድ ትልቅ ግራ መጋባትን ፈጥሯል። ይህን ሀሳብ በየትኛውም ቦታ በአሉታዊ መልኩ የሚናገር እርሱ መንፈሳዊ ኃላቀር፣ ያልዘመነ፣ ያልተቀባ፣ ገና ብዙ ነገር እንደሚቀረው ስለሚቆጠርና ለእግዚአብሔር ቃል ሳይሆን ለሰዎች ቲፎዞ በሆኑ "አገልጋዮች" እንዳይብጠለጠል ስለሚፈራ የሞት ዝምታ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰፍኗል።

ለእግዚአብሔር ክብርና ወንጌልን ለማስፋት ሳይሆን የንዋይ ፍቅርና በዓለም ያጡትን መሪ የመሆን ረሃባቸውን ለማስታገስ ቤተ ክርስቲያን "ተካዮች" ሳይሆን "ከፋቾች" እንደ አሸን ፈልተዋል። አዳዲስ ቤተ ክርስቲያናትን በብዛትና በጥራት በመተከል በጣም አምናለሁ። በቂም ባይሆን ጌታ በረዳኝ መጠን ወንጌልን ባልሰሙት ሕዝቦች መካከል ሚሲዮናውያንን በመላክ አዳዲስ ቤተ ክርስቲያን በመትከል ላይ እንገኛለን። ኮንፍራንሶቻችን፣ የጀማ ጉባኤዎቻችንና የማነቃቂያ ስብሰባዎቻችን ላይ ሁሉም ሰው እንዲገኝ በነፃነቱ ተጠቅመን በፖስተር፣ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ወንጌል ይሰበካል፣ እውር ይበራል፣ ድንቅና ተአምር ይሆናል በማለት አብዝተን ብንጣራም ብዙዎች ገደብ የለሽ ጭፈራና ገንዘብ የማሰባሰብ አደገኛ አካሄድ ስለሰለቻቸው መምጣት አቁመዋል። ነገሩ ያልገባቸው ጥቂት ምስኪኖች ሲመጡ ወንጌል መስበክና ፀሎት ሁሉ ረስተን ክሳቸውን ለማራቆት ግብግብ እንፈጥራለን። በአገራችን በየኮንፍራሱ "ነቢይ" እንደሆኑ በፖስተር ተገልጸ አንዱም የእግዚአብሔርን ቃል ሳይናገሩ ከስሜት ኮርኳሪ ስብከት በኋላ ተነሥተው ገንዘብ፣ ወርቅ፣ ሞባይልና በአጅና በክስ ያለውን ሰዎች እንዲሰጡ የሚያስገድዱ እየበረከቱ ነው። በዚህ የተዋጣላቸው አንዳንዶች ካሰባሰቡት ገንዘብ 40% እንደሚጠይቁ ይነገራል። ይህ በሉተር ዘመን ወንጌል ረግጠው የኃጢአት ስርየትንና መንግሥተ ሰማያትን በቲኬት ሽያጭ እንደለወጡት በዘመናችንም ወንጌልን በገንዘብ የለወጡ "ገበያና ሆድ መሮ" አገልጋይ ተብዬዎች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። ይህን ኢወንጌል፣ ቤተ ክርስቲያንንና አገርን ወደ አደጋ የሚመራ አካሄድ የእግዚአብሔር ቃል ያላት ቤተ ክርስቲያን በገሃድ ልታወግዝ ይገባል። አሳዛኙ ስለዚህ ነገር በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የፍርሃትና ግራ የመጋባት ዝምታ መስፈኑ ነው።

አብዛኛው ጉባኤዎቻችን አፈ ጮሌዎች፣ በወንጌል ስም "ሌላ ወንጌል" የሚያራምዱ አገልጋይ ተብየዎችና የድርጊቱ ተባባሪ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔርን ብሎ የመጣውን ሕዝብ የምመዘብሩበት ሜዳ ሆኗል። በዚህ መርዝ የተለከፉ አገልጋዮች ብዙ ክርስቲያኖች ወደ ሚኖሩበት ከተማና አካባቢ እንጂ ተቃውሞ ወዳለበት አካባቢ በስህተት እንኳን ጉራ አይሉም። "ወንጌልን" የሚያሰራጩት ወንጌልን ከሺ ጊዜ በላይ በሰሙት አማኞች መካከል ነው። ከዚህም የተነሣ የከሰረ ነጋዴ፣ ለመማር ያልታደለ አዕምሮ፣ ሞፈር የሰቀለ ገበሬ፣ ለቤተ ክርስቲያን የማይታዘዝ ሁሉ የዋህ ሕዝብ ለመበዝበዝ እንዲያመቸው ሐዋርያ፣ ነቢይ፣ ፓስተር፣ ወንጌላዊ፣ የእግዚአብሔር ሰው፣ ወዘተ...የሚሉ የአገልግሎት ቢሮ አመልካች

ስሞችን በራሳቸው ላይ በመለጠፍ ትልቅ ብዝበዛ ከማካሄዳቸውም አልፈው ለወንጌል እንቅፋት የሚሆን ዘር በምድራችን ከከተማ እስከ ገጠር በስፋት እየተዘራ ነው።

እ.ኤ.አ በ2013 ናይሮቢ ኬንያ ለአገልግሎት ሄጀ ኬ.ት.ኤን በሚባል ቴሌቪዥን አንዳንድ "አገልጋዮች" "የተቀደሰ ውሃ"ና "ልዩ ዘይት" ብለው ሕዝቡን በገሃድ እየዘረፉ እንዳሉ፤ መንፈሳዊ የቴሌቪዥን፣ የራዲዮ ፕሮግራሞችና ኮንፍራንሶች ሁሉም ወንጌልን መስበክ ሳይሆን ገንዘብ ተኮር መሆኑ ያሳሰባቸው ጋዜጠኞች ልዩ ፕሮግራም አዘጋጅተው ታዋቂ አገልጋዮችን በመጋበዝ ቃለ መጠይቅ ያደርጉ ነበር። ስለዚህ ጉዳይ አስተያየት እንዲሰጡ ከተጋበዙት መካከል "ሪድምድ ጎስፔል ቸርቺ" የተባለ ከ4 ሚሊዮን በላይ የሚገመት አባላት ያለው የፐንቴኮስታል ቤተ እምነት መሥራችና ከአሥር ሺ በላይ አባላት ያለው ቤተ ክርስቲያን መሪ የነበሩ ዶ/ር ጳጳስ አርተር ግቶንጋ አንዱ ነበር። ጋዜጠኛው "የዚህን ዘመን ገንዘብ ተኮር ወንጌል እንዴት ታየዋለህ?" ሰዎች "የተቀባ ውሃ" "ተአምረኛ ዘይት" እያሉ በዚህ ምስኪን ሕዝብ ላይ በ5,000 በ10,000 በ100,000... ሺልንግ እየሸጡ ሲሆን በመገናኛ ብዙሃን በቀን በሌሊት ይህን ብቻ ይሰብካሉ፤ ይህን እንዴት ያዩታል? ብለው ሲጠይቁ። መልሳቸው፡- ይህ የእግዚአብሔርን ስጦታ እንደ ስምያን ለመሸጥና ለመግዛት እንደ መከጅል ነው፤(የሐዋ.8:9-13)። ይህ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ራስ ተኮር አደገኛ እንቅስቃሴ ነው፤ ካሉ በኋላ የተጠቀሙበት ሌላ ምሳሌ ያስገርማል። እንዲህ አሉ፡-

> *ላለፉት 25 ዓመታት በኮንጐ በሚሊዮን የሚገመት ነፍሳት የቀጠፈና በብዙ ሚሊዮን የሚገመቱ ዜጐችን ሰደተኛ ያደረገ የእርስ በርስ ጦርነት በዚያ ምድር እየተካሄደ ሰላለ በዚያች አገር ዩኒቨርሲቲ መማር፣ አርሶ መብላት፣ ነግዶ ማትረፍ፣ ሠርቶ መለወጥ የማይታሰብ ሲሆን ለአብዛኛው ኮንጐሊሲት ቀላልና አማራጭ የሥራ ዕድል ተደረጎ የተወሰደው ዘፈን ነው። እንደዚሁም በዛሬይቷ ኬንያ መማር፣ መነገድ፣ መሥራት፣ ያልቻለ "የአገልጋይነት" (ነቢይ፣ ሐዋርያ፣ ፓስተር፣ ወንጌላዊ) ጭንብል በመልበስ በአቋራጭ ለመበልጸግ፣ በተራቀቀ መንገድ በእግዚአብሔር ስም ገንዘብን ከሰው እጅ የሚነጥቁ የበግ ለምድ የለበሱ ነጣቂዎች በምድርቷ ላይ ተለቀዋል። ካሉ በኋላ መፍተሔው ቤተ ክርስቲያን ወደ ቃሉ ተመልሳ ሕዝቧንና አገልጋዮቿን ወደ ቃሉ ካልመለሰች ትውልድና አገር የሚያጠፋ ዘር ማጨዳችን አይቀርም፤ ያሉትን ሁሉ አልረሳም። በአገራችንም እየተካሄደ ያለው ተመሳሳይ ነው።*

ከሁሉም ይልቅ የሚያሳዝነው በአገራችን የትግሩን ፍጥነትና አደገኝነት እያየች የቤተ ክርስቲያን ዝምታ ነው። ቤተ ክርስቲያን በዝምታዋ ከቀጠለች እግዚአብሔር ለዝምታዋ ሁሉ ተገቢ ዋጋ የሚያስከፍላት ሌላ አካል ማስነሳቱ አይቀሬ ነው። ወደ እግዚአብሔር ተመልሰን መንገዳችንን ካላስተካከልን እርሱ ራሱ ምድርቷን በክፋታችን እንዳናጠፋ ሌላ ክልካይ በመንገዳችን ላይ ሊያቆም ወስኗል። ክልካይ ሳይወጣ ዛሬ በቃሉ ተይዘን ብንቆም ምንኛ መልካም በሆነ ነበር።

የአብያተ ክርስቲያናት ሕብረትና የቤተ እምነት ቢሮዎች ትክክለኛውን አካሄድ በማጠንከር አደገኛውን በማውገዝ የሚጠቀስ አገራዊ ሥራ ሲሠሩ ብዙ አይታዩም። ከላይ ያሉት ዝምታን ሲመርጡ ከታች ያለው ሕዝብ በእውነት መሳይ ውሸት ግራ እየተጋባ ነው። በብዙሃን ዘንድ የስህተት አሠራር ከእውነት በላይ ተቀባይነት አግኝቷል። በዘመናችን ይህን ሸፍጥና ምዝበራ በገሃድ በቃሉ ጉልበት የሚገጥሙ የተሃድሶ መሪዎች ከያሉበት በዘመናችን እንደሚገለጡ ጌታ ተናገሮኛል። ይህን ወንጌል ለበስ ወንጀል ይገጥማሉ። ድሉም የእግዚአብሔር ነው። ሌላው አሳዛኝ ነገር ከድህነት ለመውጣት አቋራጭ መንገድ ፈላጊነታችንን የተረዱ ቡቦለይ ከናይጄሪያ የመጡ አንዳንድ ብልጦች ቢቴሌቪዥን የታወቁ ሰዎች ምስል በትልቁ አሠርተው በተከራዩት ዘመናዊ አደራሾች ፊት ለፊት በመለጠፍ ወንጌልን ሳይሆን ገንዘብን እንደ ወንጌል በመስበክ ሕዝቡን ግራ እያጋቡት ነው። ሕዝቡ በቴሌቪዥን በሚያወቀው የአገልጋይ ምስል ተጋብዞ አደራሹ ውስጥ ሲገቡ በማያውቁት ሰው እጅ እየወደቀ ነው። ወንጌል ብልጽግናን ይጠቀልላል እንጂ ብልጽግና ወንጌልን አይጠቀልልም። ብልጽግና የሚጀምረው ከኪስ ሳይሆን ከአመለካከት ነው። አመለካከትን ደግሞ የሚለውጥ ወንጌል እንጂ ብልጽግና አይደለም። የሕዝባችን ትልቁ ችግር ወደ ብልጽግና የሚያስገባ የትልቅ ራእይ እጦትና ተግቶ ያለ መሥራት ነው። አንዳንዶች እንደምዋሸት ድሀ የሆነው በተሳሳተ የዓለማችን ክፍል ስለተፈጠርን፣ እግዚአብሔር ሰለማይወደን፣ ስለተረገምንና ብልጽግና አዋጅ በራሳችን ላይ ሰላላወጅን አይደለም። አመለካከታችን በቃሉ እውነት ለውጦ በሁሉ ሀብታም የሆነች አገራችንን በሥራ ለውጠን እንድንበለጽግ የማያደርገን ስብዕትና አስተምህሮ ምንጩ እግዚአብሔር አይደለም።

ለቅድስና፣ ለጸሎት፣ ለመታዘዝ፣ ደቀመዝሙር ሆነው ጌታን ለመከተል፣ ትዳራቸውን እንደ እግዚአብሔር ቃል የመምራት ትጋቱም ሆነ መሻቱ የሌላቸው "የብልጽግና" ስብከትም ሆነ አስተምህሮ አቀንቃኞች የጌታ ስለመሆናቸው የሚናገር ፍሬ የላቸውም። የብልጽግና ነገረ መለኮት አባት እንደሆኑ የሚነገርላቸው ኬኒዮን ሲሆን ይህን ትምህርት የጀመሩት እ.ኤ.አ በ1890ዎቹ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ። የብልጽግና ወንጌል በገሃድ መስበክ ያልቻሉው ደግሞ አራል ሮቤርት ሲሆን ጊዜውም እ.ኤ.አ በ1940ዎቹ ነበር። ክዚያም ኤ.አሳን፣ ቲ ኤል አስበርን፣ ኬኔቲ ሀገን፣ ቤንኒ፣ ች፣ እንዲሁም ከአፍሪካ አብዛኛው ናይጄሪያ አገልጋዮች በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ተቀላቅለዋል። በብልጽግና ወንጌል ሰባኪዎች የሚመሩ ቤተ ክርስቲያን ተለምዶአዊ የቤተ ክርስቲያን አመራር የማይከተሉ ሲሆን የቤተ ክርስቲያኑ መጋቢ የቤተ ክርስቲያኒቷ የበላይ ሆኖ ከፍተኛ ደሞዝ ተከፋይ እንደሚሆን ጥናቶች ያመለክታሉ። በአመራራቸውም ፈላጭ ቆራጭ እንደሆኑ በአንዳንዶች ይተቻሉ። የብልጽግና ወንጌል ከምቃወሙት መካከል አንዱ መጋቢ ሪክ ዋረን ሲሆኑ "*የብልጽግና ወንጌል የስህተት ትምህርት*"[181] ነው ብለው እስከ መተቸት ደርሰዋል።

[181] (September 10, 2006). *"Does God Want You To Be Rich?". Time.* Retrieved December 4, 2011.

ከብልጽግና ወንጌል ሰባኪዎች ቀዳሚ እንደነበሩ የሚነገርላቸው፣ በመዝባሪነታቸው 45 ዓመት ተፈረዶባቸው በምህረት የተለቀቁት ጂም ባኬር ስለ ብልጽግና ወንጌል የስህተት ትምህርት ስለመሆኑ እንዲህ ብለው ነበር፦

> *ጊዜ ወስጀ በጥሞና መጽሐፍ ቅዱሴን ደጋግመ ባጠናሁ መጠን የብልጽግና ወንጌል ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ተረዳሁ፤ ብዙ ሰዎችን በዚህ የስህተት ትምህርት በመከሰስ ልቤ በሐዘን ደቀቀ፤ ተሳስቼ እንደነበር ለመናገር እግዚአብሔር በምሕረቱ ሌላ ዕድል ሰጠኝ፤ ሐሰተኛ ነቢይ ሆኜ እንዳልሞት የንስሐን ዕድል የሰጠኝን አምላኬን ለማመስገን ቃላት የለኝም፤ ብሏል።*[182]

ናይጄሪያውያንም ሆኑ ሌሎችም ወንጌልን ለሕዝባችን ለመስበክ ከመጡ በትልቅ ደስታና አክብሮት እንቀበላቸዋለን። እግዚአብሔር በናይጄሪያውያን በዓለም ዙርያ እያደረገ ስላለው ታላላቅ ነገሮች እግዚአብሔርን ሁሉ አመሰግናለሁ፤ በእምነታቸው፣ በትልቅ ራእይና ድፍረታቸው፣ በድንበር ተሻጋሪ አገልግሎታቸው በተለይ ለእኛ አገር አገልጋዮች ትልቅ ምሳሌ ሊሆኑን እንደምችሉ አምናለሁ። አንዳንዶች በተቃራኒው ከተሰለፉ ግን ለሕዝባችን እውነትን የማስተማር ግዴታ አለብን። እነዚህ ሰዎች ያልዳኑ ሰዎች፣ ወንጌል ባልደረሰበትና ተቃውሞ ወዳለበት አካባቢ በስህተት አይሄዱም። ትኩረታቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉት በተለይ ባለሀብቶች በተባሉት ላይ ነው። በገንዘብ የደለቡ ትልልቅ ዓሦችን ከመረብ (ከየአብያተ ክርስቲያናት) ማጥመድ። የቆዩ የቤተ ክርስቲያናት አገልጋዮች ይህን ለመግጠም በፍርሃት የተያዙ ይመስላሉ። ሕዝቡ መረን ሲሆን ኃላፊነት እንደሚሰማውና ተጠያቂነት እንዳለው ሰው በስሜታዊነት ሳይሆን በእውቀት ላይ የተመሠረተ የመታደግ ሥራ ሲሠሩ ብዙ አይታዩም። ቆየት ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ከመደንዘዝ መንቃት አለባቸው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ለንጥቂያና ለዝርፊያ ተጋልጧል። ስህተት በእንግሊዝኛ ሲነገራቸው ትክክል የሚመስላቸው አንዳንድ ምስኪኖች የነዚህ ነጣቂዎች መብል በመሆን ላይ ይገኛሉ። ትልቁ ችግራችን የልብ እንጂ የኪስ ባዶነት አይደለም። ለዚህ ነው ኢየሱስ ለውጥን ከኪሳችን ሳይሆን ከልባችን የጀመረው። ወንጌል፤ ወንጌል፤ ወንጌል ይሰበክ።

ይህ ዓይን ያወጣ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና ወንጌልን ሽፋን ያደረገ ጥፋት ቤተ ክርስቲያንን ወደ አደገኛ አቅጣጫ ሲነዳት እያዩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዝምታ መርጠዋል። ለመሆኑ ቤተ እምነት መሪዎች፣ የነገረ መለኮት አስተማሪዎች፣ ከወረዳ ጀምሮ እስከ አገር አቀፍ በመዋቅር የተሳሰረው የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት፣ እግዚአብሔር በእውነት ቃሉን ሰጥቶ እንደጠራቸው የሚያምኑና የሚናገሩ አገልጋዮች ምን እየሠሩ ይሆን? የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ወሳኝ ጊዜ መንቃት ካልቻለች መንፈሳዊነትን ተላብሶ ሊያጠፋት በጉያዋ እየተፈለፈሉ ያሉ ህቡዕ የጥፋት ዘሮችን በቃሉና በመንፈሱ ካልገጠመች ሕሊውናዋ በትልቅ አደጋ ላይ ነው።

[182] Jim Bakker (1996), *I Was Wrong*. Nashville, Tennessee: Thomas Nelson, , p. 535.

ለዚህ ሁሉ መፍትሔው ተሐድሶ ነው። ወደ እግዚአብሔር ቃል እንመለስ። ካልተመለስን የዘራነው መራራ ዘር በብዛት አፍርቶ የባሰ ነገር ማጨዳችን አይቀሬ ነው። እግዚአብሔር ሆይ! በምሕረትህ አስበን።

በንስሐ ያልተወገደ የትናንቱ የበደል ስንክፍ

የኢትዮጵያ ረሃብ፣ ስደት፣ ጦርነት፣ በሽታና ያለመባረክ ሌላው ምክንያት በክርስትና ስም በዚህ ምድር የተደረጉ ኢሰብአዊ ድርጊቶችን በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ፊት ያለማቅረባችን እንደሆነ አውቀን በምድራችን አገራዊ የንስሐ ጥሪ ልናውጅና ንስሐ ልንገባ ይገባል። ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ፣ ተክታዮቹና ደጋፊዎቹ የተሐድሶ አሳብ አንግበው የተነሡትን እስጢፋኖሳውያን በኢሰብዓዊ ሁኔታ በዘመኑ ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን ጋር በማበር እንደፈጁአቸው በሰፊው ተመልክተናል። ከዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ቀጥሎ የነገሡት ዐፄ በእደ ማርያም (1460-1470) ዐፄ እስክንድር (1470-1487) እስጢፋኖሳውያንን በማሳደድ እንደ ቀጠሉ ታሪክ ይናገራል። የአሕመድ ግራኝ ታላቅ ግድያ፣ በኃይል አገርን የማስለም ጦርነት፣ አብያተ ክርስቲያናትን የማፍረስና ካህናት በጅምላ መግደል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በእስጢፋኖሳውያን በኩል ከእግዚአብሔር የተላከላትን የንስሐ ጥሪ የመቃወሚ ብቻ ሳይሆን በመልዕክተኞቹ ላይ ያደረገችው ዘግናኝ ጭፍጨፋና የመለኮታዊ ምሕረት ዐዋጅ የመጋፋት ውጤት እንደሆነ አንዳንዶች ይናገራሉ።[183] ከዚያም በኋላ የፖርቱጋል ወታደሮችን ተከትለው የመጡት ኢየሱሳውያን መነኰሳት የካቶሊክን ሃይማኖት በመስበካቸው በካቶሊኮችና በኦርቶዶክሶች መካከል በተካሄደው ጦርነት ከኦርቶዶክሳውያንና ከካቶሊካውያን 9,000 እስከ 12,000 ሰዎች እንደሞቱ ይገመታል።[184] በሁለቱም ወገን የተገደሉት ኢትዮጵያውያን እንደ ነበሩ መዘንጋት የለበትም። ከዚያም በኋላ የቅብዓቶችና የተዋሕዶዎች (1657-1847ዓ.ም) በማለት ጎራ ፈጥረው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጦርነት ገጥመው ብዙዎች ተገድለዋል።

ነገሥታቱ በማያውቁት ጣልቃ እየገቡ በሚያከራክሩበት ጊዜ የወገኑለትን ወገን ረቺ ሌላውን ተረቺ በማድረጋቸውና በተረቺው ላይ ጦር በማዝመታቸው ለረዥም ጊዜ የእርስ በርስ መገዳደል ሰፊኖ ነበር። እንዲሁም የካሮች ጭፍጨፋ (1947-1909 ዓ.ም) በክርስትና ስም በዚህ ምድር ተካሄዷል። የተዋሕዶችን ትምህርት ያልተቀበለ ከፍ ብሎ አንገቱን ዝቅ ብሎ ባቱን ይቄረጣል! በሚለው አዋጅ ቅባቶችና የጥንቱ ተዋሕዶዎች እጅና እግራቸውን ምላሳቸውን ጭምር ተቈርጠዋል። ይህ አዋጁ እስከ ምኒሊክ ሞት የጸና ነበር ይባላል። የጉንዳጉንዶ (የአባ አስጢፋኖስ ገዳም) መምህር የነበሩ አንድ አባት በማለዳ ጸሎት ጊዜ ለጉባኤው አባላት እንዲህ አሉ ይባላል:-

በአገራችን አስጢፋኖሳና ደቀ መዛሙርቱ በግፍ ደማቸው ፈሷል፤ ሕይወታቸው ተሠውቷል፤ ለአብ ለወልድ እና ለመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ ለሌላ ለንሰግድም በማለታቸው ለመሲሊሞች መጠለያ የሆነች አገር

[183] ኖኅተ ብርሃን፣ መጋቢት 2002 ዓ.ም ገጽ 9
[184] ዝኒ ከማሁ ገጽ 10

በእነርሱ ላይ ግፍ ፈጽማለች። በዚህ ጉዳይ ቤተ ክርስቲያናችን ንስሐ ካልገባች እስካሁን የተፈራረቁባት መቅሠፍት ይቀጥላል እንጂ አይቋረጥም።[185] ብለዋል ይባላል።

ዛሬም እግዚአብሔር ለአገራችን ኢትዮጵያ እውነተኛ ንስሐና በፊቱ የመዋረድና የመመለስ ጥሪ ያቀርባል። ካልተመለስን እየሄድንበት ያለው መንገድ መጨረሻው አሁን ካለው የባሰ ስብራት ይሆናል። እየሞላ ያለ መራራ ጽዋ በታትኖን ሳያጠፋን፣ የክርስቶስን መስቀል የጋረዱብንና እጅግ ብርቱ እንደሆኑ የሚነግሩን የሃይማኖት ሥርዓቶቻችን፣ ያለ ቅጥ የሚንኮራበት ታሪካችን፣ ልምዶቻችንና የአገልግሎት ሩጫዎቻችን ተመልሰው የማስናከያ አለት ሳይሆኑብን ወደ እግዚአብሔር እንመለስ።

መፍትሔ

ልባዊና እውነተኛ አገራዊ ንስሐ መግባት ይገባናል

"ነ· ወደ እግዚአብሔር እንመለስ" (ሆሴ.6:1)።

እግዚአብሔር እንደ ሙሴ "እባክህ እንደ ምሕረትህ ብዛት የዚህን ሕዝብ ኃጢአት ይቅር በል" (ዘኁ.14:19) ብለው ስለ ኢትዮጵያ በፊቱ የሚወድቁትን፤ እንደ ነህምያም *"እኔና የአባቴ ቤት በድለናል። እኛም በአንተ ላይ እጅግ ክፉ ሠርተናል" (ነህ 1:6)* በማለት ስለ ሕዝብና ስለ አገር ምሕረትን የሚጠይቁና ለግንባታ የሚነሡትን እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይፈልጋል። *"ቅምጥሊቱ ግን በሕይወት ሳለች የሞተች ናት"* (1ጢሞ.5:6) ቃሉ እንደሚለው ጽድቃችንን እያወራን፣ ልዩ መሆናችንን እየሰበክንና ከሁሉ ኋላ ቀርተን ከሁሉ የቀደምን አድርገን እንደትናንቱ ማወጅ አይገባንም። ትዕቢት ሁልጊዜ ከሰይጣን ነው። ቃሉ *"ግልቡ የታበየ በአግዚአብሔር ዘንድ ርኩስ ነው፤ እጅ በእጅም ሳይቀጣ አይቀርም"* (ምሳ.16:5) ይላልና።

ከኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትውፊቶቻችንና ክርስትና ቀመስ አገር በቀል አስተምህሮዎቻችንን ወደ እግዚአብሔር ቃል መመለስ አለብን። የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክና ፕሮቴስታንቶች የሚል ልዩነት ሳይኖር ሁላችንም ወደ እውነተኛ ቃሉ እንመለስ፤ ተመልሰን ራሳችንን በመመዘን ለተሐድሶና ለለውጥ ብንነሣ ለዓለም የበረከት ምክንያቶች እንሆናለን። አብያተ ክርስቲያናቱ ይህን ወሳኝ ጊዜ ካልተጠቀሙ ለራሳቸው፣ ለአገራቸውና ለዓለምም በወንጌል የለውጥና የዕድገት ሚና ሊጫወቱ ቀርቶ ሕሊውናቸው ራሱ በአደጋ ላይ ነው። ሁሉ ቆሞ የማይጠበቀን የበረከትና የተሐድሶ ዕድል በደጃችን ቆሞ ይጠራናል። በወቅቱ በዚያ የፀሎት

[185] ዝኒ ከማሁ ገጽ 10

የኢትዮጵያ ጳጳሳት፣ ካህናት፣ ቄሳውስት፣ ወንጌላውያን፣ መጋቢያን፣ ሳይንቲስቶች፣ ፖለቲከኞች፣ ባለሃብቶች፣ ምሁራን፣ ገበሬዎች፣ አርብቶ አደሮች.. ወዘተ በወንጌል ለኢትዮጵያና ለዓለም በረከት ሲሆኑ ማየት ነው። እንዲሁም ፈርሀ እግዚአብሔር የሰፈነባት ያደገችና የተለወጠች ኢትዮጵያን የማየት ብርቱ መሻት። ያለፈውንና የአሁኑን ታሪካችንን መለስ ብሎ መቃኘት ያስፈለገበት ምክንያት መጪውን በትክክል ለመረዳት እንዲያግዘን፣ የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት በእውነት የክርስቶስን ብርሃን ለዓለም ሕዝብ እንዲያበሩ፣ አዲስ የወንጌል ሚሲዮናዊነትን ምዕራፍ የሚከፍቱ ዓለም አቀፍ አገልግሎት ያላቸው ኢትዮጵያውያን እንዲነሡና መድረሻችንን ለመተለም መነሻችንን ለይቶ ማወቅ የግድ ስለሆነ ብቻ ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስም ሆነ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲናት በአንዳንድ የውጭ ሀገሮች ውስጥ በማቆጥቆጥ ላይ እንደሚገኙ ይነገራል። ይህም ሊደነቅ የሚገባ ትልቅ ጅማሬ ነው። ይሁን እንጂ በደረሰብት ምድር የሀገር ቤቱን ስም የያዙ አብያተ ክርስቲያናትን ለኢትዮጵያ ዲያስፖራ ከመክፈት ያለፈ ለሌሎች ሕዝቦች ደራሽና ተደራሽ ያለመሆን ብቻ ሳይሆን የመሆን ዝንባሌና የወንጌል መልዕክተኛነት ራእይ በማጣታቸው በብዙዎች ዘንድ ይተቻሉ። በአጭር ቃል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራስዋን አባላት እያደነች በሄዱበት ሀገር በራሳቸው ቋንቋና ባሕል ሀገራዊ አብያተ ክርስቲያናትን ከመክፈት ያለፈ የሌሎች ሀገር ሕዝቦችን የመድረስ ዓለም አቀፋዊ ራእይ የሌላት ቤተ ክርስቲያን እንደሆነች አሁን ያለችበት ሁኔታና አካሄዷ ይመሰክራል። ይህን የዘመናት ጠባብነትና ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከትና አካሄድ የሚለውጡ ባለ ራእዮች ከኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት የሚነሡበት ዘመን ይህ ነው።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዓለምን በወንጌል ከመድረስ ይልቅ የራሳን አባላት በመንደር ውስጥ ፈልጋ የመድረስ ብርቱ "አገልግሎት" ላይ የተጠመደች ትመስላለች።

የውስጥ ትኩረታችን ገዝፎ ዓለምን በወንጌል ከመድረስ ይልቅ እርስ በርሳችን አንዱ የአንዱ የበላይና ታላቅ እንደሆነ መስበክ፣ እኛ ብቻ አዋቂና እኛ ብቻ በዓለም ላይ ትክክለኛ እንደሆንን በድፍረት መናገራችን መረን መውጣታችንን ለመልካች ነው። እውነተኛ የሆነ ሰው ከእንደዘቡ ይልቅ እውነቱኛ ሥራው ለሁሉ ይናገራል። እግዚአብሔር ታላላት ዓለ ራእዮችን ከመካከላችን በማስነሣት ይህን ጠባብነትንና ጨለምተኝነትን እንድንቋቋል ይረዳናል። ጌታ ከዚህ ድንቁርና ሊያወጣን ይፈልጋል። ይህ ትውልድ በወንጌል ራእይ ከዚህ ጠባብ አመለካከት የምድራችንን ቤተ ክርስቲያን ያወጣል ብዬ አምናለሁ። ቀድመን ተወልደን ለራሳችንም ሳንበቃ፣ በቅርቡ የተወለዱት ታላላቅ መለኮታዊ ራእይ ሰንቀው በመገለጥ ለዓለም በረከት በመሆን ላይ እንዳሉት ሀገሮች ለመሆን የረፈደብን ቢመስልም ይህች መልዕክት ለብዙዎቻች የማንቂያ ደወል ትሆናለች። አንድ ዕውቅ አንትሮፖሎጂስት ሲናገሩ "*ከታሪክ መሰዊያ ላይ ልትወሰድ የሚገባህ አሳቱን እንጂ አመዱን ላይደለም።*" እንዳሉት በባሕል፣ በሃይማኖትና በማኅበረሰባዊ ሕይወት የዳበረ ታሪክ ካላት አገራችን ፍሬውን ከገለባ በመለየትና በመልካመ ላይ ተመሥርተን የሚበልጥ ታሪክ እንድንሠራ ጌታ ይርዳን።

ፕሮግራም ላይ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በእግዚአብሔር ሰው መልዕክት ላይ አላገጡ እንደተባለው ይህን መልዕክት እያነበብን ያለነውም እንደ እነርሱ እናላግጥ ይሆን? በንስሐ ልብና በመመለስ መንፈስ በእግዚአብሔር ፊት የሚያምጡ እንጂ የሚያላግጡ አያመልጡም፤ ትውልድንም አያስመልጡም።

ወገኖቼ፡- ወደ ምድራዊና ድርጅታዊ ስሞች ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር ቃል ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና እንመለስ። ኢትዮጵያ ሆይ ወደ እግዚአብሔር ቃል ተመለሺ! የእግዚአብሔር ቃል የበላይነት ባልተረጋገጠበት ሥፍራ በሥርዓታችን ብዛት እግዚአብሔር አይገኝልንም። ኢየሱስ ለዚያ ዘመን የሃይማኖት መሪዎች ጻሐፍትና ፈሪሳውያን፡-"*ስለ ወጋችሁም የእግዚአብሔርን ቃል ሻራችሁ*" *(ማቴ.15:6)*። እንዳለው በራሳችን ነገር ቃሉን ለመሻር የታገልንበት ዘመን ያብቃ። ሁላችንም በእውነት ለዚህች ምድር ፈውስና ለሕዝባችን በረከት ከፈለግን ተያይዘን ስለ አባቶቻችንና ስለራሳችንም ኃጢአት ንስሐ ልንገባ ይገባል። በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛ ነታችንን ሳይሆን መተላለፋችንን ይዘን እንቅረብ "*ቃሉ ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በእኛ ውስጥ የለም*" *(1ዮሐ.1:8)* ይላል።

በራሳቸው ጽድቅ ለሚመኩ ባለብዙ ምክንያት ሃይማኖተኞችና ብዙ እንዳወቁ ለሚገምቱ የንስሐ ጥሪው እንደስደብና ትልቅ ድፍረት እንደሚቆጠርብኝ እያወኩ የሰማይና የምድር ጌታ የሆነው ታላቁ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያናት እያስተጋባ ያለውን የንስሐ ጥሪ ይህን መጽሐፍ ለሚያነብ ሁሉ በተሰበረ ልብና መንፈስ አቀርባለሁ። እግዚአብሔር አገራችንን በእውነት ይቅር እንዲላትና ወደ ተያዘልን በረከት ገብተን በወንጌል ለዓለም የበረከት ምክንያቶች እንድንሆን እርሱ በመንፈሱ ይርዳን። የኢትዮጵያ ፈውስ በእግዚአብሔር እጅ ሲሆን ተያይዘን በንስሐ በፊቱ በመውደቅ ምህረትና ፈውስ ለምድራችን እናመጣለን። ቃሉም እንዲህ ይላል፡-

ዝናብ እንዳይወርድ ሰማያቱን ብዘጋ ወይም ምድሪቱን ይባላ ዘንድ አንበጣን ባገዘው ወይም በሕዝብ ላይ ቸነፈር ብሰድድ በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ ፊቴንም ቢፈልጉ ከክፉ መንገዳቸው ቢመለሱ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ። (2ዜና 7:13-14)

በለውጥ ለለውጥ እንነሣ

የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ለዚህ ሁሉ ባዶነትና ኋላ መቅረት ማንንም ተጠያቂ የማድረግና ማንንም ለመሸምና ለመሻር ዓላማም ሆነ አቅም የለውም። የእግዚአብሔር ፈቃድና የልቡ ሸክም ግን ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ የወንጌል እውነት ስትጥለቀለቅ፣ በወንጌል ሕይወት የበዛላቸው

ታሪክን የሚያወሩ ሳይሆኑ ታሪክን ለመሥራት መለኮታዊ ራእይን የሰነቁ ልጆች ለኢትዮጵያ ዛሬ ያስፈልጓታል። ራእይ ማጣትን በራእይ ኃይል የሚበቀሉና የግራ መጋባትን ጽልመት ከምድሪቷ የሚገፉ ኃያላን ይነሣሉ። ዛሬ ይህን መጽሐፍ የምታነብ ወገኔ ከእነዚያ ባለ ራእዮች አንዱ አንተ እንደሆንክ ታውቃለህ? የእግዚአብሔር ቅናት ይህን በአንተ እውን ያደርጋል። በተሐድሶ፣ ለተሐድሶ እንነሣ! በ21ኛው ክፍለ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጀምሯል። ይህ የተሐድሶ አዋጅ ነው። ወደ እግዚአብሔር ቃል እንመለስ። ንስሐ እንግባ። ተባርክን ለበረከት እንሆናለንና። እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ።

በአገራችን የሃይማኖታቸውን የበላይነት የሚሰብኩና እውነትን የተቀሙ አንዳንድ ሰዎች *"ፕሮቴስታንት"* ማለት "ሰይጣን" ማለት ነው በማለት ያለማወቃቸውን እንደ ዕውቀት ሲገልጡ ተስተውለዋል። ነገሩ እነርሱ እንዳሉት ይሆን? ሌሎች ደግሞ ራሳቸውን እንደ አገር በቀል ቤተ እምነት በመቁጠር *የፕሮቴስታንት ለብያተ ክርስቲያናትን "መጤ"፣ "የምዕራባውያን ቅጥረኞች"፣* ስለአገራቸው ግድ የማይላቸውና *"ባንዳዎች"* አድርገው ከመቁጠር አልፈው የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ በዓለም ላይ የአሉታዊ ተጽዕኖ ብቻ እንዳመጣ ኢሚዛናዊ ምስክርነታቸውን በተለያየ መልኩ ስላናፈሱ ተደጋግሞ የተነገረው ውሸት በአንዳንዶች ዘንድ እንደ እውነት ሳይቆጠር አልቀረም።

በእውነት ፕሮቴስታንቶች ለአገር ግድ የማይላቸው፣ ባንዳዎች ናቸው እንዴ? የፕሮቴስታንት እንቅስቀሴ በዓለም አዎንታዊና አንፀባራቂ ለውጦችን ያመጣ አይደለም ወይ? በዓለማችን ለወንጌል ሚሲዮናዊነት እንቅስቃሴ፣ ለሥራ ፈጣሪነት፣ ለዲሞክራሲ፣ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ ለዩኒቨርሲቲዎችና የምርምር መስፋፋት፣ ለሰው ልጆች የኋኋር ለውጥ፣ ለቤተ ክርስቲያንና መንግሥት መለያየት አንዱ ምክንያት የፕሮቴስታንት እንቅስቀሴ በዓለማችን መከሰት አይደለም ወይ? ለሚሉ ወሳኝ ጥያቄዎች መልሶችን በሚከተለው ምዕራፎች እናገኛለን። እንዲሁም የፕሮቴስታንት አጀማመር፣ የፕሮቴስታንት ምሰሶያት፣ የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ ዓለም አቀፍ አዎንታዊ ተጽዕኖዎችና እግዚአብሔር ለስሙ ክብር ባለፉት 500 ዓመታት በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በኩል የሠራቸውን አበይት ድንቅ ሥራዎቹን በወፍ በረር በሚከተሉ ምዕራፎች በመቃኘት ለዘመናችን ትምህርት እንቀስማለን።

ዋናውና ትልቁ ትኩረቴ በፕሮቴስታንቶች በተጠቀመው ጌታና ፕሮቴስታንቶች የሰበኩት የጠራው የዘላለም ወንጌል ላይ እንጂ በሆነ ጊዜ ተነሥቶ በሆነ ጊዜ በሚጠፋው እንቅስቃሴ ላይ እንዳልሆነ አንባቢያን እንድረዱኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ። እኔ ክርስቶስን እንድሰብክ እንጂ ለፕሮቴስታንት ጥብቅና አልተጠራሁም። ለዓለም ጥያቄ መልስ ኢየሱስ እንጂ ፕሮቴስታንትዝም አይደለምና።

ክፍል ሁለት

ዓለምን የለወጠው የፕሮቴስታንት ተሐድሶ

ክፍል ሁለት

ዓለምን የለወጠው የፕሮቴስታንት ተሐድሶ

ታሪክን የሚያወሩ ሳይሆኑ ታሪክን ለመሥራት መለኮታዊ ራእይን የሰነቁ ልጆች ለኢትዮጵያ ዛሬ ያስፈልጓታል። ራእይ ማጣትን በራእይ ኃይል የሚበቀሉና የግራ መጋባትን ጽልመት ከምድሪቷ የሚገፉ ኃያላን ይነሣሉ። ዛሬ ይህን መጽሐፍ የምታነብ ወገኔ ከእነዚያ ባለ ራእዮች አንዱ አንተ እንደሆንክ ታውቃለህ? የእግዚአብሔር ቅናት ይህን በአንተ እውን ያደርጋል። በተሐድሶ፣ ለተሐድሶ እንነሣ! በ21ኛው ክፍለ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጀምሯል። ይህ የተሐድሶ አዋጅ ነው። ወደ እግዚአብሔር ቃል እንመለስ። ንስሐ እንግባ። ተባርከን ለበረከት እንሆናለንና። እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ።

በአገራችን የሃይማኖታቸውን የበላይነት የሚሰብኩና እውነትን የተቀሙ አንዳንድ ሰዎች *"ፕሮቴስታንት"* ማለት "ሰይጣን" ማለት ነው በማለት ያለማወቃቸውን እንደ ዕውቀት ሲገልጡ ተስተውለዋል። ነገሩ እነርሱ እንዳሉት ይሆን? ሌሎች ደግሞ ራሳቸውን እንደ አገር በቀል ቤተ እምነት በመቁጠር *የፕሮቴስታንት ለብያተ ክርስቲያናትን "መጤ"፣ "የምዕራባውያን ቅጥረኞች"፣* ስለአገራቸው ግድ የማይላቸውና *"ባንዳዎች"* አድርገው ከመቁጠር አልፈው የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ በዓለም ላይ የአሉታዊ ተጽዕኖ ብቻ እንዳመጣ ኢሚዛናዊ ምስክርነታቸውን በተለያየ መልኩ ስላናፈሱ ተደጋግሞ የተነገረው ውሸት በአንዳንዶች ዘንድ እንደ እውነት ላይቆጠር አልቀረም።

በእውነት ፕሮቴስታንቶች ለአገር ግድ የማይላቸው፣ ባንዳዎች ናቸው እንዴ? የፕሮቴስታንት እንቅስቀሴ በዓለም አዎንታዊና አንፀባራቂ ለውጦችን ያመጣ አይደለም ወይ? በዓለማችን ለወንጌል ሚሲዮናዊነት እንቅስቃሴ፣ ለሥራ ፈጣሪነት፣ ለዲሞክራሲ፣ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ ለዩኒቨርሲቲዎችና የምርምር መስፋፋት፣ ለሰው ልጆች የኋኗር ለውጥ፣ ለቤተ ክርስቲያንና መንግሥት መለያየት አንዱ ምክንያት የፕሮቴስታንት እንቅስቀሴ በዓለማችን መከሰት አይደለም ወይ? ለሚሉ ወሳኝ ጥያቄዎች መልሶችን በሚከተለው ምዕራፎች እናገኛለን። እንዲሁም የፕሮቴስታንት እጀማመር፣ የፕሮቴስታንት ምሶሶያት፣ የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ ዓለም አቀፍ አዎንታዊ ተጽዕኖዎችና እግዚአብሔር ለስሙ ክብር ባለፉት 500 ዓመታት በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በኩል የሠራቸውን አበይት ድንቅ ሥራዎቹን በወፍ በረር በሚከተሉ ምዕራፎች በመቃኘት ለዘመናችን ትምህርት እንቀስማለን።

ዋናውና ትልቁ ትኩረቴ በፕሮቴስታንቶች በተጠቀመው ጌታና ፕሮቴስታንቶች የሰበኩት የጠራው የዘላለም ወንጌል ላይ እንጂ በሆነ ጊዜ ተነሥቶ በሆነ ጊዜ በሚጠፋው እንቅስቃሴ ላይ እንዳልሆነ አንባቢያን እንድረዱኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ። እኔ ክርስቶስን እንድሰብክ እንጂ ለፕሮቴስታንት ጥብቅና አልተጠራሁም። ለዓለም ጥያቄ መልስ ኢየሱስ እንጂ ፕሮቴስታንትዝም አይደለምና።

፭

የፕሮቴስታንት ተሐድሶ

የታሪክ ሞተር ያለ ደም ሰይንቀሳቀስም::

ማርቲን ሉተር

የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ በዓለማችን ከተወለደ ከ500 *ዓመታት በላይ ሲሆን ዛሬ በዓለማችን ካሉ 2.5 ቢሊዮን ክርስቲያኖች ከ800,000,000 /ስምንት መቶ ሚሊዮን/ በላይ ፕሮተስታንቶች እንደሆኑ ጥናቶች ያሳያሉ::*[186] ፕሮቴስታንት *Protestant* የሚለው ቃል ከፈረንሳይና ከጀርመን ቃላት ተዳቅሎ የተገኘ ሲሆን በላቲን ፕሮተስታሪ /protestari/ የሚለውን የቃሉን ትርጉም ምሁራን ሲፈቱ አንድን ነገር መደገፍ ለእርሱም ምስክርነት መስጠት ነው፤ ይላሉ:: ፕሮቴስታንት የሚለው ስያሜ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠው እ.ኤ.አ በ1529 ሉተርን ይደግፉ ለነበሩ የጀርመን ልዑላን የተሰጠ ስም ነው::

[186] Jay Diamond, Larry. Plattner, Marc F. and Costopoulos, Philip J. (2005), *World Religions and Democracy*. page 119.(also in PDF file, p49), saying "*Not only do Protestants presently constitute 13 percent of the world's population—about 800 million people—but since 1900 Protestantism has spread rapidly in Africa, Asia, and Latin America.*"


የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ለምን አስፈለገ?

ብዙን ጊዜ ስለ ፕሮቴስታንት ተሐድሶ ሲነገርና ሲጻፍ አስቀድሞ ለሙ የሚነሣው ማርቲን ሉተር ነው:: ታሪክን በጥንቃቄ ስናጠና ግን ከማርቲን ሉተር በፊት የተሐድሶን ዘር በደማቸው የዘሩትን ባለራእይ የእምነት አርበኞች እናገኛለን:: በቤተ ክርስቲያን አንዳንድ የታሪክ ምሁራን ከ4ኛው እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን ያለው ዘመን የጨለማ ዘመን ተብሎ ይታወቃል:: ያ ዘመን ይህን ስያሜ ሊያገኝ የቻለው ከቤተ ክርስቲያን አበው በኋላ በስደትና መከራ ቤተ ክርስቲያንን ያልቻለው የዚህ ዓለም ገዢ የተባለው ሰይጣን የመንፈሳዊ ውጊያ ስልቱን በመቀየር ዓለማዊነትን በቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ በሙላት ለመግለጥ ዕድል በማግኘቱ ነበር:: የጨለማው ዘመን መገለጫዎች *(መካከለኛው ዘመን እ.ኤ.አ ከ590-1517)*

- በዘመኑ ተናጋሪ ባልነበረው በሞተ ቋንቋ በላቲን በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ይደረግ የነበረው ሃይማኖታዊ ሥርዓት ወግ ከማራመድ ያለፈ የሰዎችን ውስጣዊና መንፈሳዊ ጥያቄ መመለስ ያለመቻል::
- እርኩሰት፣ ሽፍጥ፣ ግብዝነትና ክፉት ሁሉ በቤተ መቅደስ ውስጥ በእግዚአብሔር ስም መሸፈኛነት በገሃድ መካሄድ::
- "የመስቀል ጦርነት" በሚል ስም ፍጹም ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ጦርነቶችን እ.ኤ.አ ከ1095 - 1270 በማካሄድ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች መጨፍጨፍ::
- በበዛንታይን ሊዮ ሦስተኛ እ.ኤ.አ በ726 የሥዕል አምልኮ እንዲጀመር ፖሊሲ በማውጣት ካስተዋወቀ በኋላ ሥርዓቱን ወደ ደቡብ ኢጣሊያ፣ ግሪክና ወደ ባልካን ሀገሮች መዛመት መጀመር::[187] በአገራችንም ተንሠራፍቶ ይገኛል:: ምሳሌ *"ከሥዕሏ እንባና ወዝ ይወጣ ነበር ከወዙም የተቀቡት ከሚያስጨንቅ ደዌያቸው ይፈወሱ ነበር... ይህች ሥዕል ወደ ጴዲንያ የገባችበት ቀን መስከረም 10 ቀን ስለ ነበር ይህችን ቀን ያከብሯት ዘንድ ሊቀ ጳጳሳት ገዝተው ሠሩ" (8ኛ ተአምር ቁጥር 62)*
- *ከአራተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የሞቱት ቅዱሳን ሰማዕታት ማማለድ፣ መፈወስና ከክፉ መጠበቅ እንደሚችሉ መነገሩና በቤተ ክርስቲያን በእነርሱ ስም ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት እየተጀመሩ መምጣት::*[188]

[187] *http://www.historyworld.net/wrldhis/PlainTextHistories.asp?ParagraphID=dmc*

[188] *"The feeling had arisen by the close of the Fourth Century that martyrs and saints could make special intercession with God if requested to do so. It was thought that they were able to protect, heal, and aid. They were made guardians of cities, patrons of trades, and curers of disease. In effect, then, the saints and martyrs were made to replace the old pagan gods and goddesses."* http://www.historyworld.net/wrldhis/PlainTextHistories.asp?ParagraphID=dmc



ጆን ዊክሊፍ[190]

190 በተጨማሪ የእንግሊዝኖውን መረጃ ይመልከቱ *Wycliffe had been born in the hinterlands, on a sheep farm 200 miles from London. He left for Oxford University in 1346, but because of periodic eruptions of the Black Death, he was not able to earn his doctorate until 1372. Nonetheless, by then he was already considered Oxford's leading philosopher and theologian. He deepened his study of Scripture and wrote more about his conflicts with official church teaching. He wrote against the doctrine of transubstantiation: "The bread while becoming by virtue of Christ's words the body of Christ does not cease to be bread." He challenged indulgences: "It is plain to me that our prelates in granting indulgences do commonly blaspheme the wisdom of God." He repudiated the confessional: "Private confession ... was not ordered by Christ and was not used by the apostles." He reiterated the biblical teaching on faith: "Trust wholly in Christ; rely captionogether on his sufferings; beware of seeking to be justified in any other way than byhisrighteousness."http://www.christianitytoday.com/ch/131christians/moversandshakers/wycliffe.html...*
የጆን ዊክለፍ መጨረሻ The Council of Constance declared Wycliffe (on 4 May 1415) a heretic and under the ban of the Church. It was decreed that his books be burned and his remains be exhumed. The exhumation was carried out in 1428 when, at the command of Pope Martin V, his remains were dug up, burned, and the ashes cast into the River Swift, which flows through Lutterworth.

- *ቤተ ክርስቲያን ከዘመኑ መንግሥትና ሥርዓት ጋር ጋብቻ ፈጽማ ለመንፈሳዊ ነገር ቦታ ያጣችበት ዘመንና ወንጌል ስለሌላት የመንግሥተ ሰማያት የመግቢያ ቲኬት በመድረክ ላይ እስከ መሸጥ የደረሰችበት አስደንጋጭ ወቅት እንደ ነበር ታሪክ ይናገራል::*

በጨለማው ዘመን የተፈለፈሉ አደገኛ የኑፋቄ ትምህርቶች

- *የፐርግቶሪ[189] ትምህርት እ.ኤ.ኤ 600*
- *በቅዱሳን፣ በማርያምና በመላዕክት ስም ጸሎት በማድረግ እ.ኤ.አ በ709::*
- *የሮማ ጳጳስን እግር መሳም እ.ኤ.አ 995*
- *የሙታን ቅዱሳን ታሪክ በቀኖና ውስጥ መጨመር እ.ኤ.አ በ1079*
- *ለቁስ ንስሐ የመግባት ትምህርት እ.ኤ.አ በ1439*
- *ቅዱስ ቁርባን (የጌታ እራት) በሚወሰድበት ጊዜ ኅብስቱና ወይኑ በቀጥታ ወደ ጌታ ሥጋና ደም ይቀየራል (ትራንስብስታንሺዬሽን Transsubstantiation) የሚሉ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎች ቤተ ክርስቲያንን በመውረር እስከ ዛሬም ትልቅ ግራ መጋባትን በመፍጠር ላይ ይገኛሉ::*


ከዚህም የተነሣ የቤተ ክርስቲያን የታሪክ ምሁራን ዘመኑን "የጨለማው ዘመን" በማለት ሰይመውታል:: ጨለማውን በቃሉ ብርሃን ለመግለጥ በየዘመኑ የተነሡ የእምነት አርበኞች ተሰደዋል፣ ተገርፈዋል፣ በእሳት ተቃጥለዋል፣ ታሥረዋል፣ በቤተ ክርስቲያን "መናፍቃን" ተብለው ተወግዘዋል፣ ተገድለዋል፣ አጥንታቸውን ከመቃብር አውጥተው በማቃጠል አመዱን በወንዝ ላይ በትነዋል፣ እንደ ሳቱ ተቆጥረዋል:: ከፐሮቴስታንት ተሐድሶ ቀድመው የተነሡ የሁለት አርበኛ ባለራእዮች ገድል ለዚህ ትልቅ ምሳሌ ነው::

የተሐድሶ ንጋት ኮከቦች

ሀ. ጆን ዊክሊፍ (1328 – 1384)

በፐሮተስታንት ተሐድሶ እንደ ንጋት ኮከብ ከሚታዩት የእምነት አርበኞች መካከል አንዱ እንግሊዛዊው ጆን ዊክለፍ ነው:: የተሐድሶ ንጋት ኮከብ የተባለበት ምክንያት ተሐድሶው ከመምጣቱ በፊት የተሐድሶውን መንገድ በደመ በመጥረጉ ነው::

189 *ፐርግቶሪ (Purgatory) በሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት መሠረት ለማኞች ከሞቱ በኋላ ሙሉ ይቅርታ ስላልተደረገላት በኃጢአታቸው የሚሰቃዩበትና መንግሥተ ሰማይ ለመግባት የሚጠብቁበት ቦታ ነው:: ብለው ማመን ጀመሩ::*



ጆን ዊክሊፍ[190]

ጆን ዊክለፍ በኦክስፎርድ በሚገኘው በባሊዮል ኮሌጅ ፕሬዚዳንት የነበረ ሲሆን ፕሮፌሰርነትን ያገኘው በመጽሐፍ ቅዱስ የትንታኔ ጥናት ነው። በመንፈስ ቅዱስ አስተማሪነት መጽሐፍ ቅዱስን ባጠና መጠን በዘመኑ "ቤተ ክርስቲያን" ተብላ የምትጠራው ከቃሉ ጋር የተጋጨች መሆኗ ይበልጥ እያሳዘነውና ልቡን እየሰበረ እንደ መጣ ታሪኩ ያወሳል። በተለይ በቤተ ክርስቲያን ስም በሮም ይታዩ የነበሩት ክርስቶስ አልባ ካቴድሪያሎች፣ የጳጳሳትን ገንዘነትና የምእመናንን ተገዥነት እንዲሁም የካህናት ሊቅ የአኗኗር ዘይቤ ሲመለከት ሃዘኑን መራር እንዳደረገበት ይናገራል።

ከዚህም የተነሣ አንድ ነገር ለማድረግ ቆርጦ ተነሣ። ለመጀመሪያ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ከላቲን ቋንቋ ብዙሃኑ ወደሚያነቡት የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተረጐመ። ይህ መጽሐፍ ወደ እንግሊዝ ቤተ መንግሥት ዘልቆ የሰዎችን ሕይወት ለወጠ። ይህ ምስክርነት የተሰጠው እ.ኤ.አ በሰኔ 1394 በዳግማዊ ሪቻርድ ባለቤት የንግሥት አና የቀብር ሥነ ሥርዓት የፈፀሙት ሊቀ ጳጳስ አሩንዴል ሲሆን ጳጳሱ ዊክልፍ ወደ እንግሊዝኛ የተረጐሙት መጽሐፍ ቅዱስ በንግሥቲቱ ላይ ስላመጣው አዎንታዊ ተጽዕኖ ሲናገሩ፦

> *ንግሥት አና ወደ እንግሊዝኛ ተተርጉመው የነበሩትን አራት ወንጌላት ስማንበቢ የተነሣ በመንፈሳዊ ሕይወታ እጅግ የተመሰገነች ነበረች። እነዚህ መጻሕፍት እውነተኛና ሁሉም ሊያነባቸው የተገቡ ናቸው።* በማለት ቀብሩን አስፈጸመ፤ ብለዋል።

ጳጳስ አሩንዴል በንግሥቲ አና ቀብር ላይ ወደ እንግሊዝኛ የተተረጐመውን መጽሐፍ ቅዱስ በማሞጋገስ እንዳልተናገሩ ከ14 ዓመት በኋላ በተተረጐመው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሕዝቡን ሰብስቦ "ውግዝ ከመአርዮስ" በማለት .. *ከዚህ በኋላ መጽሐፍ ቅዱስን ሆነ ሌሎች ክፍሎች ወደ እንግሊዝኛም ሆነ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጐም ለማንም ሊይፈቀድም፤ ለዚህ ሥልጣኑ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው፤ ከዚህም የተነሣ በዊክሊፍ ወደ እንግሊዝኛ የተተርጎመው መጽሐፍ ቅዱስ እንደ እግዚአብሔር ቃል አይቆጠርም፤* በማለት የውግዘት ቃላቸውን አሳወቁ። ቃሉን ያነበቡ ብዙዎች ወደ ብርሃን ተሻግረው ስለ ነበር በቃሉ የተለወጡትን ሰዎች ብዛት የተመለከተው ጳጳስ እጅግ ተበሳጨ። በመጨረሻም ውግዘቱ ብቻ በቂ ሆኖ ስላልታያቸው እ.ኤ.አ ዲሴምበር 28 ቀን 1384 ጆን ዊክሊፍ ከሞተ ከ44 ዓመት በኋላ በ1428 የሮማው ጳጳስ ማርቲን አምስተኛ የጆን ዊክሊፍ አጥንቱ ከተቀበረበት ወጥተው እንዲቃጠልና አመዱ በወንዝ ላይ እንዲበተን አዘዋል። ጆን ዊክሊፍ በሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ቢወገዝም በሕይወቱ ዘመን ለእንግሊዝ ሕዝብ ያበረከተው አገልግሎት ከፍተኛ ጥቅም ስላስገኘ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ የንጋት ኮከብ ብላ ሰይማዋለች።[191] በጣም የሚገርመው የዚህ ታላቅ የእምነት ሰው ገድል እስከ ዛሬ በሚሊዮኖች ይወሳል። ይህ የተሐድሶን መንገድ ለመጥረግ የተከፈለ ታላቅ ዋጋ ነው።

[191] ዮሐንስ ሳንድቪድ *(1974)*፣ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በመካከለኛው ዘመን ዋተባበሩት አታሚዎች፣ ገጽ 9

ለ. ጆን ሑስ /1369 – 1415/

> *"ጳጳሱና ክርስቲያን ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ይዳኛሉ፤ ለመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ለማይታዘዝ ጳጳስ የመታዘዝ ግዴታ የለብንም።"* ጆን ሑስ

ጆን ሑስም ከሉተር በፊት ለተሐድሶ ብሎ ለማዕት የሆነ ታላቅ የእምነት ጀግና ነበር። ጆን ሑስ የቼክ ካህን፣ የሥነ መለኮት ምሁር፣ ፈላስፋና በፕራግ ዩኒቨርሲቲ መምህር ነበር። ጆን ሑስ በዘመኑ በሮም የሚገኘውን የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን ካቴድራል ለመሥራት በሚል *"የመንግሥተ ሰማይ መግቢያ ትኬት"* በቤተ ክርስቲያን በግልጽ በመሸጥ ይደረግ የነበረውን ዓይን አውጣ ገንዘብ የማሰባሰብ ዘመቻ፣ ሰዋዊና ምድራዊ የወንጌል ተጻራሪ ትምህርቶችን፣ ወደ ቅዱሳን የሚደረገውን ጸሎት፣ ለሞተ ሰው የሚደረገውን ጸሎት በገሃድ ይቃወም ነበር።[192]



ጆን ሑስ /1369 – 1415/
ምንጭ፦ *(http://ocaminho.com.br/ocaminho/Imagens/JohnHuss.)*

[192] *http://www.bible.ca/history/eubanks/history-eubanks-25.htm*



ጆን ሑስ /1369 – 1415/

ምንጭ:- *(http://ocaminho.com.br/ocaminho/Imagens/JohnHuss.)*

በቃሉና በመንፈሱ የታደሰች ቤተ ክርስቲያን በከፍታ ላይ እንዲትቆምና ወንጌል በገሃድ እንዲሰበክ ምክንያት ሆኗል። የማርቲን ሉተርን የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መሣሪያ እግዚአብሔር አድርጎት እንዴት እንደተጠቀመበት ከዚህ በታች በአጭሩ ቀርቧል።

የተሐድሶ መሪ



ማርቲን ሉተር (1483 – 1546)

ምንጭ፦ *(www.talktalk.co.uk/reference/encyclopaedia/hutchinso)*

በጆን ዊክሊፍ፣ በጆን ሑስና በብዙሃን የተሐድሶ ቅድመ አበው ደም የተዘራው የተሐድሶ ራእይ ዘር በማርቲን ሉተር ልብ ውስጥ አልፎ በዓለም ላይ ፈነዳ። ማርቲን ሉተር[195] መዝሙረ ዳዊትን፣ ገላትያን ከሁሉ በላይ

[195] ስለ ማርቲን ሉተር ተጨማሪ መረጃ በእንግሊዝኛ ይመልከቱ። *Martin Luther was born on 10 November 1483 in Eisleben. His father was a copper miner. Luther studied at the University of Erfurt and in 1505 decided to join a monastic order, becoming an Augustinian friar. He was ordained in 1507, began teaching at the University of Wittenberg and in 1512 was made a doctor of Theology. In 1510 he visited Rome on behalf of a number of Augustinian monasteries, and was appalled by the corruption he found there. Luther became increasingly angry about the clergy selling 'indulgences' - promised remission from punishments for sin, either for someone still living or for one who had died and was believed to be in purgatory. On 31 October 1517, he published his '95 Theses', attacking papal abuses and the sale of indulgences. http://www.bbc.co.uk/history/historic_figures/luther_martin.shtml...* Unless I am convinced by the testimony of the Scriptures or by clear reason (for I do not trust either in the pope or in councils alone, since it is well known that they have often erred and contradicted themselves), I am bound by the

ጆን ሑስ[193] ለዓለም ሁሉ ኃጢአት ከሞተው ከናዝሬቱ ከኢየሱስ ክርስቶስ ደም በቀር ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚወስድ ሌላ መንገድ በፍጹም እንደሌለ አበክሮ ያስተምር ነበር። ለሰው ልጆች ድነት የኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀሉ ሥራ በቂ ነው፤ በማለትና በእግዚአብሔር ቃል ምትክ የገነነውን የሰዎችን ወግና ሥርዓት እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን በፖለቲካ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ እጅግ በመቃወም ያስተምር ነበር። በክሳሾቹ ፊት ቀርቦ በጉባኤው መሪዎች ብዙ ዛቻ አቋሙን እንዳልለወጠ በተረዱ ጊዜ በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት ፈረዱበት። አስቀድሞ ግን ወደ አንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን አስገብተው ልብሰ ተክህኖ አልብሰውት በእጁ የቅዱስ ቁርባን ጽዋ ሰጡት። ከዚያም በኋላ ሁለት ጳጳሳት ቀርበው፦

"አንተ ይሁዳ የድነት ጽዋ ወለድንብህ" አሉት። ሑስም በበኩሉ፦ ***"ያመንሁት በመድኃኒቴ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ በዚህች ዕለትም በመንግሥቱ አዲሱን የድነት ጽዋ ለመጠጣት እንደምችል እርግጠኛ ነኝ ሲል መለሰላቸው"***

ከዚያም ወደሚሞትበት ሥፍራ እየገፈተሩት ሲሄዱ፦

ነፍስህን ለሰይጣን አሳልፈን እንሰጣለን አሉት" እስረኛውም ረጋ ባለ መንፈስ ወደ ሰማይ እያሻቀበ፦ *ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፦ ያዳንሽኝ አንተ ነህ በእጆችህ ነፍሴን አሳልፌ ሰጥቼአለሁ፤* ሲል ተናገረ[194]

ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ቀደምት አበው ግልጽ ጥያቄዎችን በቃሉ ላይ ቆመው በማንሣታቸው በግርፋት፣ በእሥራት፣ በሞት፣ እንደ እባብ በመቀጥቀጥ፣ በማቃጠል፣ በማውገዝ፣ ከአገር በማሳደድና ስማቸውን በማብጠልጠል ኢሰብአዊ ድርጊት በልጆቿ ላይ በመፈጸሟ ተሐድሶውን ማዝግየት እንጂ ማስቀረት አልቻለችም። የክርስቶስን ወንጌል በገሃድ የሚሰብኩትን የምታሳድድ *"ቤተ ክርስቲያን"* በየትኛውም መመዘኛ የክርስቶስ አካል ልትሆን አትችልም። ዛሬም ቢሆን ብዙዎች ለጊዜው በእውነት ላይ መዋሸት፣ ማደምና ለእውነት በቆሙት ላይ ሤራ ሊያሤሩ ቢችሉም በእውነት ላይ ምንም ማድረግ አይችሉም።

ጆን ሑስ በእሳት እየተቃጠለ *"ባለንድ መቶ ዓመት ጊዜ ውስጥ ልታፈን የማይችል የተሐድሶ ጥያቄ ያነገበ አንድን ሰው እግዚአብሔር ያስነሣል"* ብሎ የመጨረሻ ቃል በመናገር እንዳንቀላፋ ይነገራል። ጆን ሑስ እንደተናገረው ከመቶ ዓመት በኋላ ማርቲን ሉተር በእግዚአብሔር ምሕረት፣ ጸጋና ቃል ተሞልቶ ተቃውሞን ሁሉ ሰብሮ በመውጣት

[193] [193] *ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገ ይመልከቱ። John Huss (Jan Hus) was born in Bohemia (now part of the Czech Republic) in about 1371. He received a master's degree from Charles University in Prague in 1396, became a professor of theology in 1398, was ordained to the priesthood in 1400, was made rector of the University in 1402, and in 1404 received a bachelor's degree in theology (presumably a more advanced degree than the term suggests today). ...The Council, having just narrowly succeeded in uniting Western Christendom under a single pope after years of chaos, was not about to have its work undone. It accordingly found him guilty of heresy, and he was burned at the stake on 6 July 1415.* Matthew Spinka, John Hus: a Biography, (Princeton Up, 1968)

[194] ዮሐንስ ሳንደቪድ፤ ገጽ 97



ማርቲን ሉተር (1483 – 1546)

ምንጭ :- (www.talktalk.co.uk/reference/encyclopaedia/hutchinso)

ሮሜን በጥልቀት እያጠና በመጣ ጊዜ ሁለት ምርጫዎች ከፈቱ ተደቀነ። የመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያን ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ከሁለት አንዱ ትክክል አይደለም፤ የሚል ጠንካራ ውሳኔ ላይ ደረሰ። በመጨረሻም ከእግዚአብሔር የቃሉ እውነት ጋር ፍጹም የተፋታ በኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥርዓት፣ ትውፊትና አስተምህሮ ታንቃ በዘመኑ ገናና የነበረች የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በብዙ ስህተት ውስጥ እንደተዘፈቀች በቃሉ ብርሃን ተገልጦለት አየ። ማርቲን ሉተርም ቤተ ክርስቲያን በነበረችበት ትልቅ መንፈሳዊ ቀውስ ልቡ ስለ ተሰበረ በቃሉ ላይ በመቆም ለተሐድሶ ይጠራት ጀመረ። ቤተ ክርስቲደንን ያጨናነቀው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የአስተምህሮ መሠረቱ ተናጋ።

ከጀርመን የተነሣው የለውጥና የተሐድሶ አውሎ ንፋስ ዓለምን እንደ ክረምት ጎርፍ በአንዴ በማጥለቅለቁ፣ የዘመኑ መንበረ "ክርስትና" የነበረች ታላቂቷ ሮም በአንድ ሰው ራእይ ወገቧ ተፈቶ በመጠጥ ኃይል ናላው እንደ ዞረ ሰው መንገዳገድ ጀመረች። በአውሮፓ የካቶሊክ ባሕታዊ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪና ካህን በነበረው በጀርመናዊው ማርቲን ሉተር መሪነት የፈነዳው ተሐድሶ ዋና ዓላማው ብዙ የፐሮቴስታንት ቤተ እምነቶችን የሚያቅፍ አንድ ትልቅ ጎራ ለመፍጠር አልነበረም። ነገር ግን በመካከለኛ ክፍለ ዘመን የነበረችውን የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ከሆኑ አስተምህሮዎቿ፣ ቃሉን ከጋረዱ ሰዋዊ ሥርዓቶቿና እንደ ቃሉ ከተቆጠሩ ሜዳዊ ልምዶቿ በቃሉ ለማደስ ነበር።

ማርቲ ሉተር ይዞት የተነሣው ቃል *"ጻድቅ በእምነት በሕይወት ይኖራል" (ሮሜ 1፡ 17)*። የሚል ሲሆን ለድነት ብዙ ቅድመ ሁኔታዎችንና ሥርዓትን ደንግጋ ከቃሉ ውጭ ታስተምር በነበረችው በሮማ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ቁጣን ቀስቅሶ ነበር። ከዚህም የተነሣ ሉተር በተገኘበት እንዲገደልና በእንግድነት የተቀበለው ሰው ሁሉ እንዲታሠር ትዕዛዝ ወጥቶ ነበር። የተሐድሶ ባለራእዩ ግን ሁሉንም አልፎ በመሄድ ታላቅ ሥራ ሠርቶአል።

ማርቲን ሉተር ዊተንበርግ ቤተ ክርስቲያን በር ላይ 95 የተቃውሞ ነጥቦችን ጽፎ ሲቸነክር ዓላማው ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መውጣት ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጅግ ገነው የእግዚአብሔርን ቃል የጋረዱ ስህተቶቹን ለማረም ነበር። በመጨረሻም የተሐድሶ ጥያቄው በቤተ ክርስቲያን ተቃዋሚነት ስላስፈረጀውና አሳዳጆቹም ያነሣቸውን ነጥቦች ከቃሉ ጋር በማስተያየት ከመነጋገር ይልቅ ማባረርን ስለመረጡ ማርቲን ሉተር ተወልዶ አድጎ፣ ተምሮ ለአገልግሎት ከበቃበት ቤተ ክርስቲያን ኢ.ኤ.አ ጃንዋሪ 3 1531 ተባረረ። በዚህም የፕሮቴስታንቶች ልደት ሆኗል። ፕሮቴስታንቶች

Scriptures I have quoted and my conscience is captive to the Word of God. I cannot and will not recant anything, since it is neither safe nor right to go against conscience. May God help me. Amen. Brecht, Martin. (tr. Wolfgang Katenz) *(1996),"Luther, Martin,"* in Hillerbrand, Hans J. (ed.) Oxford Encyclopedia of the Reformation. New York: Oxford University Press. 2:460.

የተቃወሙት ቤተ ክርስቲያንን ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰርገው የገቡ የነፋቂ ትምህርቶችን፣ የሮም ጳጳስ የበላይነትን፣ ከቃሉ ምንም መሠረት የማይገኝላቸው ልምምዶችንና ሥርዓቶችን ነው። ከተሐድሶ በፊት በነበረው ዘመን *"ቤተ ክርስቲያን እንዳለችው"* የሚል ሀሳብ የተለመደ ሲሆን ከተሐድሶ በኋላ "መጽሐፍ ቅዱስ እንዳለው" የሚለው ገዢና ትክክለኛው አሳብ እየተለመደ መጣ። ይህም የተሐድሶ ውጤት ነው።

ከተሐድሶ በፊት ሰዎች በቤተ ክርስቲያን የተነገራቸውን ሁሉ እንዳለ የማመን እንጂ የማሰብና የመጠየቅ ምንም ዓይነት መብት አልነበራቸውም። ሉተርና የመካከለኛ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ መሪዎች ይህን የዘመናት አሉታዊ የአመለካከት ሰንሰለት በመበጣጠስ ሰዎች ለተባለው ሁሉ *"አሜን"* ከማለታቸው በፊት በቃሉ ሁሉን የመመርመር ነጻነት እንዲኖራቸው አደረጉ። የቤሪያ ሰዎች ለሐዋርያው ጳውሎስ ስብከት አሜን ከማለታቸው በፊት፡- *"ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ" (ሐዋ.17:11)* እንደሚለው ማለት ነው። ጠያቂ አዕምሮን የፈጠረው እግዚአብሔር ሰዎች ያልተረዱትን ሲጠይቁ እንዳለመታዘዝ አይቆጥርም። ከዚያች ቀን ጀምሮ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን እንጂ ቤተ ክርስቲያን የምትሰውን ኢመጽሐፍ ቅዳሳዊ ትውፊት ማመን አቆሙ።

ሰዎች ያልገባቸውን የመጠየቅ በር ተከፈተላቸው። አማኞች የመንፈሱ ማደሪያዎች እንደ መሆናቸው መጠን ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በግላቸው መንፈስ ቅዱስ በቃሉ በኩል ለልባቸው ያረጋገጠውንና የተረዱትን ወስኖ በመቀበል ማመን ጀመሩ። የጅምላ እምነት ቀረ። አሳዛኙ ነገር ግን ዛሬ ያሉ ብዙ የፐሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ብዙ ተሐድሶ በሚያስፈልጋቸው አካሄዶችና ልምምዶች ተተብትበው ወደ ፊት መራመድ ያለመቻላቸው ነው። ለምሳሌ፡- በትንቢትና በመገለጥ ስም ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምምዶችና አስተምህሮዎች ከመለመዳቸው በላይ የቃሉን እውነት ወደ መጋረድ ደርሰዋል። ለእውነተኛ ቤተ ክርስቲያን መታዘዝ ለቃሉ መታዘዝ ሲሆን ቃሉን ጥላ ውሸት ላይ የቆመችውን *"ቤተ ክርስቲያን"* ቃሉ ላይ ቆሞ መሞገት በእውነት የዳነ ሰው ምልክት ነው።

እውነተኛ ክርስቲያንነት በመሆን እንጂ በመባል አይገኝም፤ አይገለጥም። ቤተ ክርስቲያን ከቃሉ እንጂ ቃሉ ከቤተ ክርስቲያን አልተገኘም። ቃሉ ፈጠራት እንጂ ቤተ ክርስቲያን ቃሉን አልፈጠረችም። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ይገዛታል እንጂ ቤተ ክርስቲያን ቃሉን አትገዛም። የእግዚአብሔር ቃል ቤተ ክርስቲያንን ይመራታል እንጂ ቤተ ክርስቲያን ቃሉን አትመራም፤ የመለኮታዊና የመጨረሻ የሥልጣን ምንጭ የእግዚአብሔር ቃል እንጂ ቤተ ክርስቲያን፣ ጳጳስ፣ አበ እምነቶች፣ ነቢያት፣ ሊቃውንትና ነገረ መለኮታውያን አይደሉም። ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የተሰጣት ቃል ትሰብካለች እንጂ የራሷን ልምድና ሥርዓት እንደ እግዚአብሔር ቃል ለመስበክ ሥልጣን የላትም። የእግዚአብሔር ቃል የበላይ ነው። ለቃሉ የማይገዛ ሥርዓት፣ ትውፊት፣ የቤተ ክርስቲያን ሹመት፣ ልምምድና ለቃሉ የማይገዙ ድርሳናትና ገድላት በክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ቦታ የላቸውም። የቤቱ ራስ ኢየሱስ ከሆነ ኢየሱስን የማይገልጡና

የሚያሳዩ በቤቱ ተቀባይነት የሌላቸው ብቻ ሳይሆኑ በቃሉ የተወገዙ ናቸው። የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ መሠረት ይህ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን በማንበቢ ብቻ የተቃጠለች ሴት

በተሐድሶ ዘመን አንዲት ጀይኒ ዊስት የተባለች ሴት ከነበረችበት የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ወደ ተሐድሶ እምነት መጣች። የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ ከገዛች በኋላ ማየት የተሳናት ስለሆነች ለአንዲት አሮጊት ገንዘብ እየከፈለች እንድታነብላት ታደርግ ነበር። ለቃሉ ካላት ከፍተኛ ፍቅርና ከፍተኛ የማስታወስ ችሎታ የተነሣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተጣበቀች። በመጨረሻም ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች በልቢ መዘገበች። ቤተ ክርስቲያንም ከቃሉ ጋር እንደተጋጨች አስተዋለች። ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥርዓቶችን እንቢ በማለት የእግዚአብሔርንም ቃል በገሃድ መናገር ጀመረች። ከዚህም የተነሣ ጀይን በዚያን ጊዜ ጳጳስ በነበሩት ዶክተር ራልፍ ባይኒ የሊትቹ ፊልድና ዶክተር ድራይኮቲ በሚባሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ፊት አቀረቧት። በመጨረሻም መጽሐፍ ቅዱስ ያለውን ቃል በማመኗ ብቻ የስህተት ትምህርት ውስጥ ገብታለች በማለት ድርባይ በሚባል እሥር ቤት እንድትታሰር ወሰኑባት። ጴጥሮስ ፍቼ በተባለ ሰው በተደጋጋሚ ምርመራ ቢደረግባትም በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ያገኘችውን መዳኗን መስክራ አቋሟን እንደማትለውጥ ደጋግማ ተናገረች።

በሁሉ ምክረው ከቀመጠበት እውነት ሊያነቃንቋት ስላልቻሉ በጳጳሳት፣ በመንግሥት ባለሥልጣናት፣ በንግሥት መልዕክተኞችና በሕዝብ ፊት አቀረቧት። ድሃዋ ሴት በጉባኤው ፊት ቆማ እውነትን በመካድ ምህረትን እንደማትጠይቅ ነገረቻቸው። በመጨረሻም ሞት ተበይኖባት ፍርዱን ለሚፈጽሙ ታልፋ ተሰጠች። በአገስት 1 1556 ከጭራሮ ጋር ሊያቃጥሏት አቀረቧት። ወደ ምትቃጠልበት ቦታ በቀረበች ጊዜ ተንበርክካ ጸለየች። መቃጠልዋን ለማየት የተሰበሰቡ እንዲጸልዩላት ተመኘች። ጸሎቷን ከጨረሸች በኋላ ከጭራሮው ጋር አሠሯት እንጨቱም በእሳት ተለኮሰ ወዲያውም እሳቱ ነበልባል ድምጻዋን አጠፋ ሥጋዋ ተቃጥሎ ወደ ክርስቶስ እቅፍ ገባች። የእግዚአብሔርን ቃል የጋረዱና በቤተ ክርስቲያን የነገሡ የሰው ትውፊትና አ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወግና ባደ ምድራዊ ሥርዓት እንቢ ብላ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት በማመንዋ ብቻ በቤተ ክርስቲያን ተፈርደባት ለእሳት ራስዋን በመስጠት ሰማዕት ሆናለች።[196]

ስለ ተሐድሶ ሳጠና ያገኘሁት አንድ ትልቅ ምስጢር ቤተ ክርስቲያን ከእውነት መንገድ ስትወጣ የእግዚአብሔርን ቃል ይዘው ጥፋቷን የሚሞግቱ ልጆቿን ያለ ርኅራኄ በኢሰብዓዊ ሁኔታ በጭካኔ መግደሏ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የሚያስፈራትና የመጽሐፍ ቅዱስ ሙሉዕ እውነት የማይሰበክባት ቤተ ክርስቲያን ወደ ቃሉ እውነት መምጣት ካልቻለች "ቤተ ክርስቲያን" የሚል ስም ብቻ ቤተ ክርስቲያን አያደርጋትም።

[196] John Foxe, *(MXXXIX) Foxe's Christian Martyrs of the World*, Barbour Publishing, Inc, USA., , p 181

አንድ አማኝ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበቡ ብቻ ከላይ የተመለከትነውን ዓይነት ዘግናኝ እርምጃ የምትወስድ "ቤተ ክርስቲያን" የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ናት ማለት እንችላለን ወይ? የክርስቶስ ካልሆነች የማን ናት? መልሱን ለአንባቢያን። እኛስ ዛሬ ለእውነት ዋጋ ለመክፈል ተዘጋጅተናል ወይ? ባለፉት ምዕራፎች እንደተመለከትነው በአገራችን የተሐድሶ/የለውጥ/ ሐሳብ ያነገቡ በአለቃቂ ሁኔታ እንደ ተገደሉ በአውሮፓም የተነሣው የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ጥንቃቄ በተመሳሳይ ሁኔታ በመሥዋዕትነት ግቡን እንደመታ እንመለከታለን። በአውሮፓም ይሁን በአፍሪካ አልፎም በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር ቃል ሁሉን ይገዛል። በኢትዮጵያ ምድር ሊሆን ባለው የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ፊት ማንም ምንም ቢቆም ፍጹም መቀልበስ በማይቻልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። መንፈሳዊ ጦርነቱ ቀላል ባይሆንም የተሐድሶ መሪ የቤቱ ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ የድሉ ባለቤት ነው። ከእንግዲህ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ታላቅ አብዮት በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ይነሣ ዘንድ ሰማይ ወስኗል። ወንጌል ያሸንፋል!

በሩማኒያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቃሉን ይዞ በተነሣው ታላቅ የተሐድሶ ሰው ቤተ ክርስቲያን ያደረገችበትን እንመልከት፦



አባ ቴድሮ ፖፒስኮ "የሩማኒያው ሉተር"[197]
(1887-1963)
ምንጭ፦ (From Darkness to light book -2003)

[197] *On 26 January 1924, in the magazine The Free Word (Cuvantul Liber)* D. Theodorescu Wrote, *"We have in recent days a Romanian Luther! His name is Teodor Popescu."*

ጥቂት ስለ ሩማኒያ

ሩማኒያ በደቡብ ምስራቅ አውሮፓ የምትገኝ አገር ናት። እንደ ወርልድ ባንክ 2004 ሪፖርት የሕዝብ ብዛቷ 21.35 ሚሊዮን ሲሆን ብሔራዊ ቋንቋ ሩማንየኛ ይባላል። የሩማኒያ ሕዝብ ከ90% በላይ ክርስቲያን ቢሆንም የጽድቅ ተጽዕኖ በአገራቸውና በሌላው ዓለም ላይ እንደ ዕድሜያቸውና እንደ ብዛታቸው አላመጡም፤ እንዲያውም በዓለማችን ክርስቲያኖች በከፍተኛ ሁኔታ ከታሰሩባቸው፣ ከተሰደዱባቸውና ከተገደሉባቸው አገራት አንዷ ናት። በኮምኒስት መራሹ የሩማኒያ መንግሥት ዘመን 5,000 የኦርቶዶክስ ካህናት ተይዘው 1,700 ታስረዋል።[198] እ.ኤ.አ 1945-1952 ከእምነታቸው የተነሣ 80,000 ክርስቲያኖች ተይዘው 30,000 አማኞች በወህኒ ታስረው ተገርፈዋል፣ ማቀዋል አንዳንዶቹም በኢሰብዓዊ ሁኔታ ተገድለዋል።[199]

የሩማኒያ ኮሚኒስት መንግሥት ስለ ሃይማኖታቸው የታሰሩ ክርስቲያን የሕግ አሥረኞችን በ1,900 ዶላር በገሃድ ይሸጥ ነበር። 14 ዓመት በሩማኒያ ኮሚኒስት መንግሥት ግዞት ቤት ክፉኛ የማቀቀ ብዙ ዘግናኝ መከራ የደረሰበትና በተአምራት የተረፈውን ሪቻርድ ውንብራድን ለማስፈታት ግን የኖርዌይ ክርስቲያኖች 10,000 ዶላር ስለተጠየቁ ለሩማኒያ መንግሥት ቤዛ ከፍለው አስለቅቀዋል። በሩማንያ ወህኒ ስለ እምነቱ የደረሰበትን ግርፋት፣ መከራና በአጠቃላይ በሩማኒያ ኮሚኒስት መንግሥት በክርስቲያኖች ላይ ያደርስ የነበረው ኢሰብዓዊ ድርጊት ምን ይመስል እንደነበር በገሃድ የገለጠ በዓለማችን በ80 ቋንቋዎች የተተረጎመውን *"ለክርስቶስ ተሰቃየሁ"* የሚለውን ድንቅ መጽሐፍ ማንበብ በቂ ነው።[200] የመጽሐፉ ጸሐፊ የሆነው ሪቻርድ ውንብራንድ ስለደረሰበት ሲናገር፦

> *በተለያዩ እስር ቤቶች ባሳለፍኩባቸው ዓመታት ውስጥ አራት የጀርባና ሌሎች አጥንቶቼን ሰብረዋል። ብዙ ቦታ ተልተለውኛል፤ ጉድጓድ እስኪሆን ድረስ አካሌ ላይ አሥራ ስምንት ቦታ ወግተውኛል። ...የቤዛ ክፍያ ተደርጐ እኔና ቤተሰቤ ከሩማንያን ወደ ኖርዌይ በመጣን ጊዜ በአስሎ ያሉ ዶክተሮች ይህን ሁሉ እና ከሳንባ በሽታ የተነሣ ሳንባዎቼ ላይ ያሉትን ጠባሳዎች ያዩ ሐኪሞች በሕይወት መኖሬ ራሱ ተአምር መሆኑን ተናገረዋል! እንደ እነርሱ የሕክምና ዕውቀት ከሆነ ከዓመታት በፊት መሞት ነበረብኝ። እኔ ራሴም ብሆን በሕይወት መኖሬ ተአምር መሆኑን አውቃለሁ።እግዚአብሔር የተአምር አምላክ ነውና[201] ብለዋል።*

[198] January 23, 1999, issue of the London Tablet by Jonathen Luxmoore, Published by Chesterton Review Feb/May 1999

[199] Lucian N. Leustean. (Mar., 2007), *Constructing Communism in the Romanian People's Republic. Orthodoxy and State*, 1948-49. Europe-Asia Studies, Vol. 59, No. 2, pp. 303-329

[200] http://www.persecution.com/public/ourfounders.aspx

[201] ለክርስቶስ ተሰቃየሁ፤ 2006 ገጽ 34

እ.ኤ.አ በ2011 በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ ከሩማኒያ ሕዝብ ከመቶ 81.04% የኦርቶዶክስ ተከታዮች እንደሆኑ ያመለክታል።[202] *ከዚህም ውስጥ ከመቶ 7% ብቻ በሰንበት ቤተ ክርስቲያን ደጅ ተሳልመው ይመለሳሉ*[203] ይህ መረጃ ክርስትናቸው የስም እንደሆነ ያመለክት ይሆን?

በአገራችን አንዳንድ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች በተለይ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን በደፈና *"መጡ"* ብለው እንደሚፈርጁና *"ድርጅት"* እንጂ ቤተ ክርስቲያን ብለው እንኳ ለመጥራት እንደማይፈልጉ ሁሉ በሩማኒያም በተለይ የኮሚኒዝም አገዛዝ ሳይመጣ በፊት አንዳንድ የሩማኒያ አጥባቂ ኦርቶዶክስ ተከታዮች ሌሎች አብያተ ክርስቲናትን በንቀት እንደ *"ሃድን"* ብቻ ይቆጥሩ ነበር። *የቀናች፣ የቀደመች፣ ትክክለኛ ሃይማኖት ከጥንት አበው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የእኛ ነው፤ በማለት ያለቅጥ በሃማኖታቸው ይኮራሉ። አንድ ሰው ሩማኒያዊ ሆኖ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ ካልሆነ እውነተኛ የሩማኒያ ዜጋ እንደሆነ አይቆጠርም፤ ከኦርቶዶክስ ሃይማኖት ውጭ መገኘት ከእውነተኛ ሃይማኖት መንገድ እንደመሳት ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ስሜቱ የሞተ ሰው*[204] እስከ ማለት የተዛባ አመለካከት ተጠቂዎች ሆነዋል። የሃይማኖት ትምክህተኝነት አደጋ እንዲህ ያስታብያል። ትሁት አምላክ ትዕቢተኛ ሕዝብ የለውም። የአንድ ሃይማይኖት የበላይነት፣ የአንድ ብሔር የበላይነት፣ የአንድ አመለካከት የበላይነትና ፍልስፍና በገነነበት አገር ሰላም፣ ዕድገትና አንድነት በፍጹም ሊኖር አይችልም። በአገራችንም ቢሆን በዚህ መንፈስ የተበከሉ ነበሩ ዛሬም አይታጡም፤ ይህም የዕድገት እንቅፋት ሆኖብናል።

አባ ቴድሮ የተባለ በሩማኒያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህን የነበረ በሃይማኖቱ እጅግ ስለሚመጻደቀው የሩማንያ ሕዝብ ሲናገር፦ *ዛሬ በሩማኒያ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጌታ ሲሰሰ ክርስቶስ አይታወቅም። ሰወግ በሥርዓት መካከል የሚጠራ ስሙ እንጂ ማንነቱና በመስቀል ላይ የሠራው የቤዛነት ሥራው በሰዎች ሕይወት ቦታ የለውም። ይህም አደገኛና አሰደንጋጭ ጨለማ ነው*[205] ብሏል። እንግዲህ ይህም ሆኖ በሃይማኖታቸው ያለ ቅጥ ይኮራሉ። የሃይማኖት አንዱ አደገኛ ገጽታው ሰዎችን በባዶ ዋስትና መንፈሳቸውን በማደንዘዝ ምንም ሳይሆኑ ከሁሉ በላይ እንደሆኑ ራሳቸውን አዛብተው እንዲረዱና በድፍረት እንዲናገሩ ማድረጉ ነው። ይህ ከእውነተኛ ክርስትናና የክርስቶስ መንፈስ ጋር ይቃረናል። እግዚአብሔር ሲናገር፦ *"...ወደ ትሑት መንፈሱም ወደ ተሰበረ ሰው እመለከታለሁ" (ኢሳ.66:2)*። በእውነት የእርሱ ከሆንን እግዚአብሔር ከራሱ ውጭ ምንም ዓይነት ትምክህት እንድኖረን አይፈቅድም። የነገረ መለኮት ፕሮፌሰር የሆነው ኤግን ኤች. ፔትርሰን ሲናገር፦ *"ብዙ ሃይማኖት ፀረ ወንጌል ነው፤ ብዙ ሰዎች የራሳቸውን ትክክለኝነትና ትውፊት ከአምላክ በላይ ወደ ላይ በመስቀል ልዩ*

[202] 2011 Census Religion Statistics (final results)

[203] Center for Urban and Regional Sociology (CURS) 2011

[204] Horia Azimoara, (2003), *From Darkness To Light*, Brockhausdruck-Dillenburg, Germany, p.117

[205] Ibid, 35

እንደ ሆኑ ራሳቸውን አዛብተው እንዲረዱና እንዲናገሩ ሃይማኖታቸው ምክንያትና ጣዖት ሆኖባቸዋል" [206] ብሏል።

በአገራችንም ነጋድረስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ እንዳሉት *"ያገራችን ሰው ተዋህዶ ሃይማኖት ከሁሉ ሃይማኖት ይበልጣል ብሎ ያምናል... የክርስቲያን ሃይማኖትን አውራ መሠረት የወንጌልን ቃል አያውቅም።... ...ደግሞ በአገራችን አንድ ድንቁርና ነገር አለ። ሃይማኖቱ ተዋህዶ ያልሆነ ሰው ሁሉ እንደ አርከስ ይቆጠራል። ይህም እጅግ ያሰቃል፣ አእምሮ የሌለው ሕዝብ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ሳያውቅ የእግዚአብሔር ጠበቃ ሊሆን ይወዳል። ሃይማኖት የልብ ነገር ነው"*[207] ያሉት ከሩማንያውያን መንፈስ ጋር ይመሳሰል ይሆን?

እውነተኛ ክርስትና ከሌላው ሃይማኖት የሚበልጠው በመድረክ ስብከት ሳይሆን ከሁሉ በላይ የሆነውን ጌታ ዝቅ ብሎን ለዓለም የሚንሰብክበት የአገልግሎት ሕይወት በመሆኑ ነው። በክርስቲያኖች መካከል የሚደረግ የ"እኔ እበልጣለሁ" እሰጥ አገባ ወንጌልንና ጌታን በትክክል ያለማወቅ ዐቢይ ምልክት ነው። ትልቅ የሆነ ትልቅ ለመሆን አይታገልም። ትንሽነት የሚሰማው ደግሞ ትልቅ ለመባል የማይፈነቅሰው ድንጋይ የለም። እግዚአብሔር ትልቅ ነው፤ ትልቅነቱን ከማወጅ ውጪ አንዳች የምናደርግለት ነገር የለም። የእግዚአብሔርን ትልቅነት ስለተቃወምን እርሱ ትንሽ አይሆንም፤ ትልቅነቱ መገለጫውና ማንነቱ ነውና። ስለዚህ በዚህ ትልቅ አምላክ ልንደገፍና ልንኮራ ይገባል። የአንድ እውነተኛ ክርስቲያን ትምክህትና መመኪያው ሃይማኖቱ፣ የቤተ እምነቱ ስም፣ ብሔርና መንደሩ፣ የሚነገርለት ታሪኩና አገልግሎቱ ሳይሆን እግዚአብሔር ነው። *"የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ እግዚአብሔር ያመሰግነው እንጂ ራሱን የሚያመሰግን እርሱ ተፈትኖ የሚወጣ አይደለምና"* *(2ቆሮ.10:17-18)*። *"...ማንም እንዲይመካ ከሥራው አይደለም"(ኤፌ.2:9)*።

የክርስቶስ ኢየሱስ ማንነት በእውነት የገባው ሐዋርያ ጳውሎስ በራሱ አንዳች የሚመካበት ነገር እንደሌለው ሲናገር *"...ራሴ ግን ከድካሜ በቀር አልመካም"(2ቆሮ.12:5)*። ብሎ ትምክህቱ ምን እንደሆነ ሲናገር፦ *"ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልኩበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ"(ገላ.6:14)*። *"...በእርሱ እገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጉድፍ እቈጥራለሁ፤"(ፊል.3:9)* በማለት የትምክህቱ መሠረት የኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀሉ ሥራ እንደሆነ አውጇል። የምነገርልን ዝና፣ የምጻፍልን ታሪክ፣ የሚወራልን ገድልና በብዙዎች የሚሞገስ ሃይማኖትና ባሕል ቢኖረን እንኳ ሁሉም አንድ ላይ ቢጨፈለቁ

[206] Eugene H. Peterson,(1992), *Under the Unpredictable Plant,* William B.Eerdmans Publishing Company Grand Rapids, Michigan, p.34

[207] አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ *(2003 ዓ.ም)* ፣ የነጋደራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ሥራዎች፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡ ፕሬስ፣ ገጽ 27-28

የጌታ ያህል የሁልጊዜና የሁሉ ቦታ ምርኩዝ አይሆኑልንም። ስለዚህ ለዘላለመ የአዳም ልጅ ትምክህት በሆነው በክርስቶስ እንደገፍ፣ እንኩራ፣ እንታመን፣ ተስፋ እናድርግ። *"በእርሱ የሚያምን አያፍርም"(1ጴጥ.2:6)*።

በዓለማችን ላይ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ወደ ቃሉ ለመመለስ ሉተርን ያስነሣው በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበር። አባ እስጢፋኖስንና ተከታዮቹን ያስነሣው ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ነበር። *በዚህ ክፍል "የሩማኒያው ሉተር"* ተብሎ ቅጽል ስም እንደወጣለት፣ በሩማኒያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር አስነሥቶ ታላቅ ሥራ የሠራበትን አንድ ካህን በውስጡ የተፈጠረው ጥያቄ ሥርዓትና ወግ ሊሞላ እንዳልቻለ፣ ክርስቶስን ሳያውቅ ብዙ ዘመን የሞራል ሰባኪ ሆኖ እንደቆየ፣ በውስጡ ለተፈጠረው ጥያቄ መልሱን ከቃሉ አግኝቶ በእምነትና በድፍረት የወንጌልን ቃል በገሃድ መስበክ ሲጀምር ከቤተ ክርስቲያን የደረሰበትን ተቃውሞ፣ ጽናቱንና ጌታ የሰጠውን ድል እንመለከታለን። ይህ ሰው ቴድሮ ፖፒስኮ ይባላል። የተወለደው በጃንዋሪ 12 ቀን 1887 ዱንባረቫ በምትባለው በሩማኒያ በምትገኝ አንዲት መንደር ነበር። አባ ቴድሮ ቀድሞ በቡካረስት ሩማኒያ ሲሮክስ ነስቲ በሚትባል የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንደ አባቱ ካህን ነበር።

ለቴድሮ የነገረ መለኮት ትምህርት ቤት - "የጥያቄ ቦታ"

ቴድሮ ተወልዶ ያደገው በሩማኒያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህን ሆኖ በሚያገለግል አባቱ ቤት ሲሆን የቤተ ክርስቲያኒቷን ሥርዓት ከልጅነቱ ጠንቅቆ እንደተማረ ለማንም ግልጽ ነው። የመጀመሪያ ደረጃ የነገረ መለኮት ትምህርቱን በኩርታ ዲ አርግስ በሚባል ገዳም የተከታተለ ሲሆን በዚያ ቦታ ስለነበረው ቆይታ ሲናገር፦

> *የሩማኒያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና ወግ፣ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ሥርዓት እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አንዱም ሲነበብ አልሰማሁም፤ ከዚህም የተነሣ ትልቅ መንፈሳዊ ቀውስ የሰፈነበት ቦታ ሲሆን ብዙዎች ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና በመረን በወጣው ድርጊታቸው ይመጻደቁ ነበር። ለዚህ እኩይና ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ወግ ምስጋና እንደሚገባቸው ያስቡ ነበር። አንድም ለእግዚአብሔር ነገር የተራብ ሰው በዚህ ገዳም አላገኘ ሁም።*[208]

አንድ ሰው ከዚህ ገዳም ተመርቆ ሲወጣ የቤተ ክርስቲያኒቷን ሥርዓትና ወግ ይወቅ እንጂ በእግዚአብሔር እንኳ ባያምንም የቤተ ክርስቲያን ካህን ይሆን ነበር። የአባ ቴድሮን ሕይወት የመለወጥ ፊር የቀደደለት ከገዳም ትምህርት ቤት ወደ አባቱ ቤት መጥቶ በላቲን ቋንቋ የተጻፈና በቆሻሻ ቦታ ተጥሎ ያገኘውን በጣም የተቀደደና የቆሸሸ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ማንበብ ሲጀምር ነበር። በወንጌል ቃል ልቡ ተነካ። የሚማረው ሥርዓትና ወግ ያልናደው የኃጢአት ተራራ በልቡ እንደቆመ ተገነዘበ። ትልቅ የእግዚአብሔር ቃል ፍቅር ከዚያ ቀን ጀምሮ በሕይወቱ ላይ ወደቀ።

ቴድሮ የተሰማውን ስሜትና በልቡ የተፈጠረውን ጥያቄ እንዲህ ይገልጻል፦ *"የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በልቤ ላይ አስቀመጥኩ፣ እንደዚህ ዓይነት*

[208] *From Darkness To Light,*(2003), Brockhausdruck-Dillenburg, Germany p 12

መጽሐፍ በቀሻሻ ቦታ ተጥሎ መገኘቱ እጅግ ገረመኝ፤ መጽሐፉን ብወደውም አንዳንድ አስቸጋሪ ክፍሎችን የሚያስረዳኝ ሰው ብፈልግም አላገኘሁም›[209] ይላል።

ቴድሮ ወደ ገዳም ሲመለስ አዲስ ኪዳንን በከፍተኛ ሁኔታ ለማጥናት ቢወስንም ጥሩ አስተማሪ ማግኘት እንዳልቻለ ይናገራል። የቤተ ክርስቲያን ወግና ሥርዓትን በጥንቃቄ አጥንቶ ካጠናቀቀ በኋላ እ.ኤ.አ በ1907 ከገዳም ተመረቀ። ምንም እንኳ የገዳም ትምህርት ብቻውን በሩማኒያ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህን ሆኖ ለማገልገል በቂ ቢሆንም ከፍተኛ የነገረ መለኮት ትምህርት ለማጥናት ብርቱ ፍላጎት ስላደረበት በቡክሬስት ዩኒቨርሲቲ የነገረ መለኮት ትምህርቱን ቀጠለ። ከዚያም በኋላ በነገረ መለኮት የፒ.ኤች.ዲ ትምህርቱን በቡኮቪኒያ ዩኒቨርሲቲ የተከታተለ ሲሆን የጀርመንኛና የፈረንሳይኛን ቋንቋዎች ሊቅ ለመሆንም በቅቷል። በዚህ ሁሉ ለመንፈሳዊ ጥያቄው መልስ የሚሆነውን አላገኘም። መንገድ የሚያሳየውን ሰው በብርቱ ቢፈልግም ሊያገኝ አልቻለም። የዩኒቨርሲቲ የነገረ መለኮት ፕሮፌሰሮችንም መንገድ እንዲያሳዩት ቢመኝም ቀመራዊና ሥርዓታዊ የሆነ ነገር ከመናገርና ከማስተማር ያለፈ ከሕይወታቸው አልፎ ሕይወቱን የነካ አንዳች ነገር ማግኘት እንዳልቻለ ይናገራል።[210]

ከዚህ የምንረዳው ኢየሱስ ያልነገሠበትና የሌለበት የነገረ መለኮት የመተንተን አቅምና ነገሮችን ከተለያየ አቅጣጫ የመመልከት ክህሎት ብቻውን ለነፍስ ጥያቄ መልስ መሆን ያለመቻሉን ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነትና በመስቀል ላይ የከፈለውን ዋጋ በቅጡ የማይገልጥና እውነትን ከውሸት አበጥሮ አሳይቶ ለነፍስ ጥያቄ ከቃሉ መልስ ለመስጠት አቅም የለሽ የነገረ መለኮት ቀመራዊ የአዕምሮ ፍጭትና ፍጅት ቤተ ክርስቲያንን ከችግር ማውጣት አይችልም። የክርስቶስ እውነት ያልበራለት የነገረ መለኮት ምሁር ክርስቶስን በእምነትና በድፍረት የሚሰብክ አገልጋዮችን ማፍራት አይችልም። የምናፈራው እንደየወገናችን ነውና (ዘፍ.1:12)።

ለቴድሮ በቤተ ክርስቲያን ካህንነት - የወግ ሰባኪ

አባ ቴድሮ የውስጥ ጥያቄው መልስ ባያገኝም ትምህርቱን አጠናቆ እ.ኤ.አ በ1912 ገና በወጣትነቱ የትሮክስ ነስት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህን ሆኖ ተሾመ። አባ ቶድሮ ሲናገር፦ ኢየሱስ ክርስቶስን በሕይወቱ ሳላውቀውና በእውነት ሳልከተለውም የተዋጣልኝ ሰባኪ ነበርኩ። የሚሰብከው ወንጌል ሳይሆን ሕግ፣ የቤተ ክርስቲያን ወግና ሥርዓት፣ ሞራል፣ ሰዎች ሌሎችን መውደድ እንዳለባቸው ነበር። ሰዎችም ስብከቴ ትክክል እንደሆነ ይነግሩኝ ነበር።[211] ዛሬ ላይ ሆኜ ስመለከት ክስበከቴ የጎደለው የስብከት ልብ የሆነው ክርስቶስ ነበር። አንድም ቀን ድነት በመስቀል ላይ ክርስቶስ በከፈለው ዋጋ እንደሆነ ሰብኬ አላውቅም። ለሰላሳ ዓመታት በክርስቶስ ለተገለጠው ጸጋ ባይተዋር ሆኜ ኖሪያለሁ። መንፈሳዊ ዓይናቹ ማየት

[209] Ibid. 12
[210] Ibid, 17
[211] T. Popescu, (1949) unpublished sermon,

የተሳነው ሰው ሆኜ የሃይማኖት አስተማሪና አዋቂ አድርጌ ራሴን እቆጥር ነበር። ዘጎልጎታ አቻና ወደር ያልተገኘለት የአግዚአብሔር ፍቅር ያልገባው የናቅር ሰባኪ ነበርኩ።[212] ሰዎችን፣ ማጥመቅ፣ የጋብቻ ሥርዓት መፈጸምና ሥርዓትን ማስተማርና ካህን መባሌ የነፍሴን ጥያቄ መመለስ አልቻለም።[213] በአጠቃላይ ሩማኒያ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ክርስትና እንደ ብሔራዊ መለያና የዜግነት ኩራት ተደርጎ ከመቆጠር ያለፈ በካህናቱና ክርስቲያን በተባሉ ምዕመናን ዘንድ በቃሉ የተለወጠ ሕይወት የለም።[214] እንደ አባ ቴድሮ ከሆነ፦ የሩማኒያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የድነት አስተምህሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ከተገለጠው እውነት ጋር እጅግ ይቃረናል፤ ሰዎች መልካም ነገር ቢያደርጉ፣ ቢመፀውቱ፣ በሥርዓቱ መሠረት ጸመው ቢፀልዩም ስለ ድነታቸው እርግጠኞች ሆነው ሲናገሩ አይታዩም። በኦሮቶዶክስ ሃይማኖት አንድም ሰው ስለ ድነቱ እርግጠኛ አይደለም[215] ብለዋል።

አባ ቴድሮ በመንፈሱ ሕመምተኛና የጥያቄ ሰው ሆኖ ሳለ ሦስት ልጆች የወለዱችለት አቲና የተባለች ሚስቱ ብዙም ሳትታመም ስትሞትበት ሚስቱ ወደ ዘላለም እረፍት ወይም ሞት ስለመሄዷ እርግጠኛ ባለመሆኑ ሐዘኑን መራር እንዳደረገበት ይናገራል። ዱመትሮ ኮርኖሊስኮ የተባለው ከእርሱ ጋር በአገልግሎት የተጠመደ ዲያቆን ድነት በኢየሱስ ክርስቶስ የቤዛነት ሥራ በማመን ብቻ እንደሆነ የተረዳው መጽሐፍ ቅዱስን ለመተርጎም ለአራት ዓመታት ባደረገው ጥናት ነበር። በዚህ ሥራ መጽሐፍ ቅዱስን ያለ አንዳች የመጻፊያ መሣሪያ ከሌላ ቋንቋ ወደ ራሱ በእጁ ብቻ አራት ጊዜ ገልብጧል። በመጨረሻም ማንም ስለ ድነት መንገድ ሳይሰብከውና ሳያስረዳው ኢየሱስ ክርስቶስን አግኝቶ ዳነ። ጓደኛውና የአገልግሎት አጋሩ የሆነ አባ ቴድሮ በሚሰቱ ሞትና በመንፈሳዊ ጥያቄ ግራ ተጋብቶ እያለ ዱመትሮ አዲስ ኪዳን መጽሐፍ ሰጠው።

የካህኑ ኢየሱስ ክርስቶስን መቀበል

አባ ቴድሮ አዲስ ኪዳንን ደጋግሞ ባነበበ ቁጥር "ድነት" እና "ወደ አግዚአብሔር መመለስ" የሚሉ አሳቦች በፍጹም መረዳት እንዳልቻለ ይገልጻል። በመጨረሻም ቃሉን በትጋት እያጠና ለኃጢአቱ ዋጋ የሆነው የክርስቶስ የመስቀል ሞት መሆኑንና ያን ጸጋ በእምነት መቀበል ብቻ የድነት በር እንደሆነ ተረዳ። አባ ቴድሮ ሲናገር፦

> ለሥርዓቱ ታማኝ የሆነ የሃይማኖት ሰው መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ ማንበብ ሲጀምር እጅግ ይገረማል። ሥርዓቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሚያገኝ ተስፋ ቢያደርግም በፍጹም አያገኝም። የሚያገኘው ከጠበቀው የተለየ ነው። እኔ እንደ አንድ የኦርቶዶክስ ካህን የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓቶች ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት እንዲደረጉ አስተምር ነበር። የአግዚአብሔርን ቃል ሳጠና እውነቱ ከማምቴ የተለየ

[212] *From Darkness To Light* 2003, p10
[213] Ibid, p.22
[214] Ibid,p 32
[215] Ibid, p.76

ሆኖ አኘሁት። በመጨረሻም የደረስኩበት ድምዳሜ ሥርዓትና ልምድ ሌላ የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ ሌላ ነው[216] ብሏል።

ኃጢአቱን ለጌታ በመናዘዝ፣ ልቡን ለክርስቶስ አዳኝነት በከፈተ ጊዜ ታላቅ እረፍት፣ ታላቅ ሰላም፣ ታላቅ እርካታ፣ በልቡ ከከበረው ጌታ መፍሰቅ ጀመረ። ለድነቱም እርግጠኝነት ተሰማው ከቃሉም ማረጋገጫ ሊያገኝ ደስታው ወደር አጣ። ሕይወቱና አገልግሎቱ ሙሉ በሙሉ ተለወጠ። እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ያለውን ፍርዱን ሙሉ በሙሉ የመለሰው የክርስቶስ የመስቀል ሥራ እንደሆነ ተረዳ። አባ ተድሮ ስለዚህ ሲናገር፡-

ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአቴ እንደሞተልኝ ማመኔ በልቤ ጠንካራ መሠረት መሠረተ። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የኃጢአቴን ዋጋ ከፍሎልኛል፣ ያም በቂ ነው። ብዬ በእምነት መኖር ስጀምር ታሪክ ተለወጠ።[217]

በአዲስ ሕይወት አዲስ አገልግሎት

አባ ቴድሮ በግሉ ቃሉን በማጥናት ወደ ጌታ ከተመለሰ በኋላ፣ ስብከቱ ሐዋርያቶችና የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሲሰብኩ የተሰውለት የክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል ሆነ። በወንጌል እሳት የተለኮሰ ሕይወቱ በዙሪያው የነበሩና እንደ እርሱ የቀድሞ ሕይወት ባዶ የሃይማኖት ሥርዓት ግራ ያጋባቸውን ወደ ወንጌል ብርሃን መጥራት ጀመረ። እርሱ የሚያገለግልበት ቤተ ክርስቲያን በነፍሳት ከመጨናነቅ አልፋ ወደ ተለያዩ ከተማዎች ለወንጌል ስብከት ተጠርቶ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰዎች ድነት ዋናና ብቸኛው እንደሆነ በስፋት መስበክ ቀጠለ። አባ ቴድሮ የተባ ብዕረኛም እንደነበረ ይነገለታል።

እ.ኤ.አ በ1921 እና በ1922 *"ኢየሱስ ይጠራሃል"* *"ወደ ኢየሱስ ና"* የሚሉ ሁለት መጻሕፍት አሳትሞ በከፍተኛ ሁኔታ አሰራጭቷል። መጽሐፉን ያነበቡ ሰዎች ወደ ከተማቸው መጥተው ወንጌልን እንዲሰብክ ከየአቅጣጫው ጥሪያቸውን ያቀርቡለት ነበር። አባ ተድሮ በሩማኒያ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ መንፈሳዊ መነቃቃት አመጣ። ብዙ ምዕመናን ለመጀመሪያ ጊዜ በእርሱ ስብከት ወንጌልን ሰምተው በኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል በተሠራው የቤዛነት ሥራ ብቻ በማመን ለነፍሳቸው ዕረፍት ማግኘታቸውን በሄዱበት ሁሉ ይመሰክሩ ነበር። በአገሩ ካሉት ካህናት ሁሉ በተለየ ሁኔታ ቃሉ ላይ ብቻ በማተኮር በማንም እንደበት ያልተነገረውን የጸጋ ቃል እርሱ ሲሰብክ ለመስማት ብዙዎች ይፈልጉ ነበር። የወንጌል ብርሃን ሲበራ የዘመናት የጨለማ ጽልመት ተገፈፈ፤ ነፍሳት ወደ ክብሩ ወንጌል መፍለስ ጀመሩ። ወንጌል በትክክል የገባው ሰው እንደድሮ የመሆንና የመኖር አቅም ይክዳዋል። ንግግሩ፣ ኑሮው፣ እርምጃው፣ አመለካከቱና ሁለመናው የክርስቶስ ወንጌል ወንጌል ይሸታል። ክርስቶስ ብርሃን የሆነለት ሰው ለሌሎች

[216] Ibid, p.46
[217] Ibid, p.33

ብርሃን ይሆናል። በአባ ቴድሮ በወንጌል ቃል መለወጥና አገልግሎት የታየው እውነት ይህ ነው።

የአባ ተድሮ - የቤተ ክርስቲያን ዒላማ መሆን

ባለፉት ሁለት ሺ ዓመታት ለወንጌል አንዲ ብርቱ እንቅፋት የሆነችው በስም የጌታ በምግባር የራሷ የሆነች *"ቤተ ክርስቲያን"* ናት። የክርስቶስ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ ወንጌል ትኖራለች። የክርስቶስ ያልሆነች ቤተ ክርስቲያን ግን ለክርስቶስ ወንጌል ቦታ የላትም። ለክርስቶስ ወንጌል ቦታ የሌላት ቤተ ክርስቲያን ወንጌ፣ ሥርዓቷንና ትውፊቷን እንደ ወንጌል ትሰብካለች፤ ወንጌል ላልሰማው ዓለም ደንታ ቢስ ናት፤ ሥርዓትና ወግ ከተነካባት በአስደንጋጭ ቁጣ በሥጋዊ ጡንቻ ከመዋጋት አትመለስም።

ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶ የመንግሥቱን ወንጌል ሲሰብክ በንግግሩ ሊያጠምዱት በብርቱ ይከራከሩት የነበሩ፤ በመጨረሻም ጠንካራ ከሳሽ ሆነው በመስቀል እንዲቀጣ መስክረውበት ያስገደሉት በዘመኑ መጻሕፍትን ጠንቅቀው የሚያውቁ የቤተ መቅደስ መሪዎችና የሃይማኖት ሰዎች ነበሩ። ከእርሱም በኋላ ሐዋርያትን ያሳደዱ *"እኛ የእግዚአብሔር ሰዎች ነን"* የሚሉ አይሁዶች ጥንትም ሆነ ዛሬ በሃይማኖተኝነታቸው በዓለማችን አንደኞች ናቸው። በመካከለኛ ዘመን ከመንግሥት ጋር ጋብቻ ፈጽማ ወንጌልን ቀብራ የመንግሥተ ሰማይ የመግቢያ ትኬት ሽያጭ በገሃድ በማካሄድ ክርስቶስን የካደችና በምግባር ያሳደደች *"ቤተ ክርስቲያን"* ነበረች። በአገራችንስ ቢሆን ወንጌልን በእውነት ከመስበክ ይልቅ የቤተ ክርስቲያን ስም ከብዙ አሉታዊ ነገር ጋር መነሣቱ ይህ ሁሉ ለወንጌል እንቅፋት መሆን ነው። ወንጌል የጠፋባት ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ሰባኪ ሲወለድላት እግዚአብሔርን አመስግና ከመቀበልና ከመስማት ይልቅ ለማሳደድ፣ ለማሰር፣ ስሙን ለማጥፋትና ለመግደል በሙሉ ኃይል እንደምትነሣ በታሪክ የተረጋገጠ እውነት ነው።

ለወንጌል ቃል ባዕድ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ለወንጌል ሳይሆን ለገዛ ባዶ ሥርዓቷ ጥብቅና በመቆም ወንጌልን ለማፈን የማትፈነቅለው ድንጋይ የለም። በአባ ቴድሮ ሕይወትና አገልግሎት የምንመለከተው እውነት ይህ ነው። ሕይወቱ የተለወጠ ካህን የጠራና የጠለለ የወንጌል ስብከቱ ያልተማረውን፣ የተማረውን፣ የሃብታምና ድሃውን፣ የሃይማኖተኞችንና የአገሩን ሕዝብ እይታ መሳብ ሲጀምር የሩማንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ደነገጠች። በዓይነ ቁራኛ የዚህን ካህን አገልግሎት መከታተልና በተለያየ መንገድ ማጥናት ሥራዬ ብላ ተያያዘች። በአባ ቴድር የወንጌል ስብከት እንቅልፍ የራቃት ቤተ ክርስቲያን በስብከቱ የስህተት አስተምህሮ ስለመኖሩ እንዲገመግሙ የነገረ መለኮት ምሁራንን እርሱ ወደሚያገለግልበት ስትሮክስ ነስት ኦሮቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ጊዜ ልካለች። ከተላኩት መካከል የአባ ቴድሮ የቀድሞ የነገረ መለኮት አስተማሪ ፕሮፌሰሮች ነበሩ። እነርሱም የግምገማቸውን ውጤት ሲገልጹ፡-

በስብከቱ አጅግ መርካታቸውን፤ አንዳች የስህተት ትምህርት አለማግኘ ታቸውንና በሞራል ለወደቀችና ግራ ለተጋባች ቤተ ክርስቲያናቸው ተሐድሶ በዚህ በኩል ይመጣል ብለው ከማመናቸውም አልፈው አንዳንዶች ለእውነተኛ ወንጌል ልባቸውን ክፍተው ድነት በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ እንደሚገኝ ለማመን ቃሉ እንዳስገደዳቸው ተናግረዋል::[218] ይህ ሪፖርት ቤተ ክርስቲያንን አላስደሰታትም:: በቡካረስ ዩኒቨርሲቲ የኦርቶዶክስ ነገረ መለኮት ፕሮፌሰር የሆኑት ጆዮርጅ ተአስካ በአንድ መጽሔት ላይ ምስክርነታቸውን ሲሰጡ:- *የተሐድሶ ጨረርና የመንቃቃት ተሰፋ በአባ ቴድሮ በኩል አይተን ነበር:: ስብከታቸው ልባችንን ሰንጥቆ ይገባ ነበር:: ከዚህ የተነሣ ጠላሪያቸው ተሰብስበን ነበር[219]* ብለዋል::

ለቤተ ክርስቲያንና ለአገር ሁለንተናዊ ተሐድሶ ምክንያት ይሆናል ተብሎ በብዙሃኑ የታመነበት የተሐድሶ እሳት በቤተ ክርስቲያን ያለመታዘዝ ተዳፈነ:: ወንጌልን ይዞ የተነሣውን የገዛ ልጇን የሩማኒያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በግልጽ በማውገዝ ማሳደዷን ቀጠለችበት:: ዛሬ በአገራችንም እየተካደ ካለው የተሐድሶ እንቅስቃሴ ተቃውሞ ጋር እጅግ ይመሳሰላልና በጥንቃቄ እንመልከት::

የአባ ቴድሮ ከቤተ ክርስቲያን መባረር

ከሰፊር አልፎ የብዙኃን መገናኛው ዐቢይ ወሬ የቴድሮ የወንጌል ስብከትና የሩማኒያ ኦርቶዶክስ የቤተ ክርስቲያን የእርሱን አገልግሎት ባለመቀበል የተፈጠረውን ውጥረት ማራገብ ሆነ:: በሩማኒያ አነጋጋሪ ነገር ተፈጠረ:: በዚህም ጉዳይ ካህናት በሁለት ተከፈሉ:: አባዛኛዎቹ ካህናት የወንጌል ስብከቱን ሲቃወሙ እንደ እርሱ የክርስቶስ የመስቀል ሥራ ብቻውን ለነፍስ ድነት በቂ ነው፤ ከሚሉት ካህናት መካከል አላክሳድሮ ቴድስኮ፤ አለክሳድሩ ፓንትስኮና ቫሲል አቱ የተባሉ ደግሞ አቋሙንና አስተምህሮውን ይደግፉ ነበር::[220] እንዲሁም በቡካረስ ዩኒቨርሲቲ ከኦርቶዶክስ የነገረ መለኮት ሊቆች መካከልም ብዙዎች "የተመሰገነ/የከበረ ካህን" "*meritorious priest*"[221] ብለው ያደንቁት ነበር:: የቴድሮ አባት አባ ጊዮርጊህ ኢዮንስኮ የልጁን ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ጋር መጋጨት ወሬው እርሱ በሚኖርበት ከተማ ዱምብራቫ ሲሰማ በጣም ደነገጠ:: ወዲያውም ከልጁ አንደበት ሊያረጋግጥ ፊልጎ ረኸርም መንገድ ተገዘ ቴድሮ ወደሚኖርበት የሩማኒያ ዋና ከተማ ቡካረስት ደረሰ:: ለልጁ ለቴድሮም እንዲህ በማለት ጥያቄውን አቀረበለት:-

ምንድነው እየሰማን ያለው? ልጄ አንተ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በመቃወም፤ የሞቱ ቅዱሳንና ማርያም እንዳይመለኩ አስተምረሃል ወይ? ለምን እኛ ቤተሰብህን ታዋርደናለህ? አንተን ከቤተ ክርስቲያን ካስወገዱ በኋላ እኔን በእርጅናዬ እንደሚገድሉኝ አታውቅም? በእኛ ላይ ለሚደርሰው አደጋ ሁሉ ተጠያቂ እንደሆንክ አትርሳ::[222]

[218] Ibid,p. 43
[219] Ibid, p. 60
[220] Ibid 44
[221] Ibid,p.43
[222] From Darkest to Light, 2003, p.52

ልጁ ቴድሮም ሲመልስ:-

አይደለም፤ አባቴ እንደዚያ በፍጹም አታስብ:: እኔን አውግዘው ውጪ ሲጥሉኝ በዚያን ጊዜ እንዲህ በል:- "ልጄ ሙሉ ሰው ስለሆነ እኔ የለሁበትም፤ ለውሳኔውና ለእርምጃው እራሱን ጠይቁት በላቸው::"[223]

አባቱም መልሶ ልጁ ቴድሮ የኦርቶዶክስን ሥርዓትና ወግ ሁሉ ተቀብሎ እንዲያስተምር ከተደገሰለት ውግዘት እንዲያመልጥ ሊያግባባው በብርቱ ጣረ በመጨረሻም እንዲህ ብሎ መከረው:- *"ልጄ የፈለከውን በልብህ ማመን ትችላለህ፤ በእነርሱ ፊት ግን እባክህን እነርሱ ለመስማት የሚፈልጉትን ብቻ ተናገር"*[224] ሲለው:: ቴድሮም ለአባቱ ጽኑዕ የእምነት አቋሙን ያለ ማመቻመች እንዲህ ብሎ አሳወቀው:- *"አባቴ እንደዚያ በፍጹም አላደርግም! ወንጌል ግልጽ ስለሆነ ያለ ውሸት በገሃድ መታወጅ አለበት"*[225] አባቱ እንደመከረው በግብዝነት የሚያምነውን ላይሆን ካህናት ሊሰሙ የሚወዱትን ተናግሮ ዕድሜውን ማስረዘምና እንጀራውን በውሸት ማስጠበቅ አልፈለገም:: *"እውነትን ተናግሮ በመሸበት ማደር"* ይል የለ የእኛም ብሂል? ውሸትን እየሰበኩ ያለ ጌታ ረኸርም ዓመት በምድር ከመኖር እውነትን ሰብኩ ስለእውነት ሰማዕት መሆን ጥቂቶች ብቻ የሚያገኙት የክብር ሕይወት ነው:: በልጁ ጠንካራ አቋም እጅግ ያዘነውና የተበሳጨው አባት በመጨረሻም እንዲህ አለው:-

አንተ ድሃ ነህ ከዚህ ሥራ ብትባረር ለራስህ ምን ትበላለህ? ልጆችህን ምን ታበላለህ?[226]

ቴድሮም ለአባቱ እንዲህ ብሎ መለሰለት:-

አባቴ ስለዚያ ምንም አትጨነቅ፤ እኛ እግዚአብሔር አለን፤ እርሱ ስለ እኛ ያስባል::[227]

አባ ቴድሮ ስብከቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆነ የሕይወት ፍሬው፤ በአገልግሎቱ ወንጌልን አምነው በዳኑ ሕዝቦች ላይ የታየው የባሕሪይ ለውጥና በቤተ ክርስቲያን ላይ የተፈጠረው አዎንታዊ መነቃቃት ምስክር ነው:: በተጨማሪም የሩማኒያ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የነገረ መለኮት መምህራንና ተማሪዎች ባደረጉት የጥናት ሪፖርት ምንም ከእግዚአብሔር ቃል ያልሆነ አስተምህሮ እንዳላገኙበት መስክረዋል:: የስትሮክስ ነስት ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በእርሱ ላይ አንዳንድ ካህናቶችና የቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ባለሥልጣናት እንደተነሡበት ሰምተው በቁጣ ሊመልሱ በተነሡ ጊዜ አባ ቴድሮ ነገሮችን ከቁጣ በራቀ ሁኔታ እንዲመለከቱ አጥብቆ ያሳስብ ነበር:: በወቅቱ የመንግሥት የሃይማኖት ጉዳይ ሚንስቴር የነበሩ አክቶቪያን ጎጋ

[223] Ibid, p 52
[224] Ibid, P.52
[225] Ibid, p.52
[226] Ibid,p.52
[227] Ibid, 53

ጉዳዩን ለማየት አባ ቴድሮ ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ነበር። የስትሮክስ ነስትስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን የሩማኒያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአባ ቴድሮ ላይ የያዘችውን አቋም እንደሚቃወሙ ገልጸው እነርሱ የተናገሩትን ሚንስቴሩ በአንድ መጽሔት ላይ አውጥተው ነበር፡-

ዛሬ ቤተ ክርስቲያን የተለመደ ሥርዓታን ከማካሄድና መመሪያዋን ከመፈጸም ያለፈ ለነፍሳችን ምን እያደረገች ነው? ተከደናል፤ አላዋቂ የሆኑ ካህናት ሥርዓታቸውን ከማካሄድ ውጪ ምንም ሊያመጡ አይችሉም፤ ቤተ ክርስቲያኒቷ የራስዋን ውሳኔ ትወስን እኛን ግን ስለ ክርስቶስ ሊየሱስ ማን ያስተምረናል?[228] በማለት የህዘን ጥያቄያቸውን እንዳቀረቡ ዘግበዋል።

አባ ቴድሮ በዲሰምበር 26 ቀን 1923 ለሩማንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያሪክ በጻፈው ደብዳቤ የስብከቱን ይዘት እንዲህ አስቀምጦ ነበር፡-

የነፍሱ ጥማትና እኔም በብርቱ ለመሥራት የተጋሁት ነፍሳትን ለክርስቶስ ለመማረክ ነው። ላገኘሁት ለእያንዳንዱ ሰው በነፍስ ወከፍ ቀርቤ፡- አንተ ሰው የጠፋህ ኃጢአተኛ ነህ፤ ሊየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአትህ ሊያድንህ ሞተ፤ በእርሱ ብታምን አሁን ትድናለህ፤ ባታምን ግን ለዘላለም ትሞታለህ። የሚል ነው። ...ይህን በመስበኬ የቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ አመራር ተቃውመው እየገፉኝ ነው፤ እኔም ከቤተ ክርስቲያኔ ፍጹም የመውጣት ዓላማ የለኝም።[229]

ፓትርያሪኩ በሰየሙት ገባኤም ፊት ቆሞ አባ ቴድሮ ሲናገር፡-

እኔ የሩማኒያን ቤተ ክርስቲያን የማደስ ዓላማ የለኝም። ነገር ግን የግለሰቦችንና የሰዎችን ሕይወት በወንጌል ኃይል ለውጦ ለወንጌል ማስታጠቅ ነው። ...አንድ ከልብ የተረዳሁት እውነት ቢኖር ኢየሱስ ክርስቶስ ተራና የማያድን ሃይማኖታዊ ሥርዓት ብቻ እንዲፈጽም አልላክኝም፤ ወንጌልን እንድሰብክ እንጂ፤ ታዘልኝ የተሰጠውን ፀሎት እንድደግም ብቻ አልጠራኝም፤ ቃሉን እንዳስተምር እንጂ። የእኔ ቀዳሚውና የመጨረሻ ኃላፊነቴ እስክሞት ወንጌልን መስበክ ነው። ወንጌልን መስበክ ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ማፈንገጥ ተደረጎ ከተቆጠረ አምን ወንጌልን ይዤ አፈንግጫለሁ። ለእኔ ያፈነገጡና የሳቱ ወንጌልን የማይሰብኩና የማይኖሩ ናቸው[230] ብለዋል።

ቤተ ክርስቲያን ግን በጉያዋ የሰበሰበቻቸውን ሊወርድ ሲዋረድ የመጣ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምምዶቿና ሥርዓቶቿ በቃሉ ጉልበት መፈራረስ ስለጀመረ፣ እሳትና ጭድ አንድ ላይ ይዞ መንዝ በፍጹም ስለማይታሰብ፤ ከወንጌል ይልቅ ኢወንጌል የሆነ ነገሯን መርጣ እ.ኤ.አ በ1924 አባ ቴድሮን በማውገዝ አባረረች። የጌታ የሆነውን ሰው "ቤተ ክርስቲያን" ከመዋቅራዊና ከራስዋ ድርጅታዊ የአዝ ሰንሰለት ልታወጣው እንጂ ከአግዚአብሔር መንግሥት ማንንም ማውጣት ብቻ ሳይሆን ማስገባትም አትችልም።

[228] Octavian Goga, January 13, 1924, Magazine Our Country, editorial *"The Revolt from the Strok's Nest"*
[229] From Darkest to Light, 2003, p.59
[230] Ibid, 64

ታሪክ ራሱን ይደግማል፤ እንደሚባለው ዛሬም በተለያዩ የዓለማችን ክፍል ባሉት ቤተ ክርስቲያናት የሩማኒያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በተለያየ መልኩ እየተደገመ ነው። ወንጌል ግን ሁሌ አሸናፊ ነው።

የአባ ተድሮ ስደትና ስኬት

ከቤተ ክርስቲያን ያለፈቃዱ ከተባረረ በኋላ በአንድ ጋዜጣ ላይ አባ ቴድሮ አቋሙንና ለስደት ዝግጁ መሆኑን እንዲህ ብሎ ገልጾ ነበር፡-

እኔን በማውገዝና ከቤተ ክርስቲያን በማባረር የወንጌልን እውነት ማዳፈን አይቻልም። ከቤተ ክርስቲያን ቢያባርሩኝም እንኳ ውድ ጊዜዬን ከቤተ ክርስቲያን ጋር በመዋጋት አላጠፋም። የእኔ ጦርነት ከድንቁርና፣ ከሰይጣንና ከኃጢአት ጋር ሲሆን ብርቱ ረሃቤ ደግሞ ለራሴ ሳይሆን ነፍሳትን ለክርስቶስ መማረክ ነው። ስደት በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የታዘዘልን ስለሆነ ስደት እኛን የማስፈራትም ሆነ የማስደነቅ አቅም የለውም። ስደትና መከራ ጌታን ይበልጥ እንድንታመን ዕድል ይሰጠናል።[231]

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል እንዲህ ብሎአል፡-

ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ። ዋጋችሁ በሰማይ ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ ሐሤትም አድርጉ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳድደዋቸዋልና (ማቴ. 5፡ 11-12)።

አባ ተድሮን በሥነጽሑፍ፣ አብሮ በመጸለይና ወንጌልን ይሰብክ የነበረ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ሲተረጉም የኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ተገልጦለት በኢየሱስ ክርስቶስ የቤዛነት ሥራ ብቻ በማመን መዳኑን ይመሰክር የነበረው ዲያቆን ዱመትሮ በእርሱ ላይ ከተጠነሰሰበት የሞት ድግስ ወደ ስውዘርላንድ በመኮብለል አምልጧል። አባ ተድሮ ከሩማኒያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሲባረር ብዙ ሰዎች አገር ለቆ እንዲሰደድ ቢመክሩትም እንቢ አለ። እርሱ የተባረረው ብቻውን ሲሆን ማንንም ሳይጠራ ብዙ ሕዝብ እርሱን ተከትሎ ወጣ። የስትሮክስ ነስትስ ቤተ ክርስቲያንም ተዘጋ። ከእንግዲህ አበቃለት ብለው የአባ ቴድሮን ጥፋት ሲጠብቁ ከቀድሞ ይልቅ የወንጌል አገልግሎቱን በስፋት ቀጠለ። ቤተ ክርስቲያን ደጇን ብትዘጋባቸውም ሕዝቡ ቤቱን ቤተ ክርስቲያን አደረገ። ታላቅ የአገልግሎት በሮች ተከፈቱ፤ አባ ቴድሮ ከቤተ ክርስቲያን ሲባረር *"ካእንግዲህ የማያድን የሃይማኖት ባዶ ሥርዓት ባለመፈፀሜ የምከሰሰበት ዘመን አበቃ። አሁን ያለ አንዳች ተጽዕኖ በሁለቱ ክንፎቿ ለወንጌል የምበርበት ዘመን መጥቶልኛል"*[232] በማለት ከቤተ ክርስቲያን መባረሩን እንደ ትልቅ የወንጌል አገልግሎት በር ቆጥሯል። መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ተመሳጥረው በማሳደድ፤ በማሰር፤ በማስፋራራትና ስሙን በማጥፋት ከወንጌል አገልግሎት ሊያስቆሙት በብርቱ ቢታገሉም በእግዚአብሔር ጸጋ ሁሉንም አሸንፎ በማለፍ ሩማኒያን በወንጌል አርሷል።

በአገልግሎት ዘመኑ በሩማኒያ ከ200 በላይ ቤተ ክርስቲያናትን ተክሏል። በብዙ ሺ የሚገመቱ ሰዎችን ለክርስቶስ ማርኮ ደቀ መዝሙር

[231] T.Popescu, article published in *"The Morning"* newspaper, 1924
[232] Ibid, 67

አድርጓል። እግዚአብሔር በእርሱ አገልግሎት ክብሯል ሩማኒያም ተባርካለች። በሕይወቱ መጨረሻ ከእርሱ ጋር የነበሩትን ሲመክር፦

> *ወንጌልን ስበኩ ከማለት ያለፈ ትልቅ ምክር የለኝም። ባልተወሳሰበና ግልጽ የወንጌል እውነት ላይ ኑሩ፣ እኔ ሁልጊዜ ቀለል ባለና ግልጽ የሕይወት ዘይቤ በመካከላችሁ እንደኖርኩ ለትዘንጉ።*[233]

አባ ቴድሮ በወዳጆቹና በቅዱሳን ተከቦ ብዙም ሳይታመም እ.ኤ.አ በ1962 በታማኝነት ወዳገለገለው ጌታ ሄዷል። እ.ኤ.አ በፈቤርዋሪ ወቅቱ የቅዝቃዜና ምቹ ጊዜ ባይሆንም አምስት ሺ ሕዝብ የቡካረስን አውራ ጐዳና አጨናንቆ አስከረኑን በማጀብ ጋንካ በሚባል ሥፍራ በክብር ቀብሩ ተከናውኗል።

ተሐድሶ ከላይ ወደ ታች ወይስ ከታች ወደ ላይ?

ተሐድሶ ከላይ ወደ ታች ወይስ ከታች ወደ ላይ? በቤተ ክርስቲያን ትክክለኛ የተሐድሶ ጥያቄን ከትክክለኛ መልስ ጋር ይዘን ስለተነሣን ብቻ ከግቡ እናደርሳለን ማለት ዘበት ነው። እንደዚያ ቢሆን ኖሮ እነ አባ አስጢፋኖስና ተከታዮቹ፣ አለቃ ታዬ፣ ጆን ዊክልፍ፣ ጆን ሑስ አንግበው የተነሡትን ትክክለኛ የተሐድሶ ጥያቄ ፍሬውን ሳያዩ ሰማዕት ባልሆኑ ነበር። የተሐድሶ ጥያቄ ይዞ መነሣት ብቻውን በቂም አይደለም ውጤታማ እንዲኾንም አያደርገንም። በተለይ ተሐድሶን ከታች ወደ ላይ መሞከር ብዙ ጊዜ አስቸጋሪ ብቻ ሳይሆን ብዙ ዋጋን የማስከፈል፣ በቶሎ ውጤቱንም ለማየት ያለመቻል፣ ተስፋም የማስቆረጥ ባሕሪይም እንዳለው ምሁራን ይናገራሉ። በዓለማችን የተካሄዱ የተሳኩና ያልተሳኩ የተሐድሶ እንቅስቃሴዎች፦

ኢየሱስ ክርስቶስ

ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳም ዘር ጥያቄ መልስ ሆኖ ሲመጣ በተለይ የቤተ መንግሥትና የቤተ መቅደስ ቁንጮ ሆነው ሕዝቡን ይመሩ የነበሩ ታላቅ ተሐድሶ በዓለም ላይ ሊያመጣ የተገለጠውን ጌታ ለመቀበል ዝግጁ አልነበሩም። *"የእርሱ ወደ ሆነው መጣ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም"* *(ዮሐ.1:11)*። ወገኖቹ ቀርቶ፦ *"ወንድሞቹ ስንኳ አላመነበትም ነበርና"* *(ዮሐ.7:4)* ይላል። ሁልጊዜ እርሱ ሲያስተምር ለመስማት ከሚመጡት አብዛኛዎቹ በቃሉ ሊያጠምዱት፣ ነገር ለመፈለግ፣ እርሱን ለመወንጀልና ከተቻለም ለማጥፋት ነበር። ወደ ቀድሞ ክብርና ከፍታ የሰውን ልጅ ለመመለስ የመጣ ታላቁ ቤዛ በቤተመቅደሳቸው፣ በምኩራቦቻቸውና በቤተመንግሥታቸው አንዴም በአክብሮት እንደጋበዙት መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም።

[233] Ibid 134

ቤተ መንግሥት፣ ቤተ መቅደስ፣ የሃይማኖት መሪዎችና ተመሪዎችም በባሕላቸውና በፖለቲካዊ ርዕዮተዓለም መስኮቶቻቸው በኩል አጮልቀው ዕለት ዕለት ንግግሩን፣ አስተምህሮውን፣ ውሎ አዳሩንና የሕዝቡን ምላሽ በትኩረት ይከታተሉ ነበር። ኢየሱስ ከቤተ መንግሥት ተሐድሶውን እንዳይጀምር የአገሩ ንጉሥ አልነበርም፤ ተሐድሶውን ከቤተ መቅደስ ከላይ ወደ ታች እንዳይጀምር ሊቀ ጳጳስ አልነበረም፤ ራእዩውን እውን ለማድረግ የራሱ አካል የሆነችውንና የለውጥና የተሐድሶ ማዕከል የምትሆን ቤተ ክርስቲያንን መሠረተ። ኢየሱስ ክርስቶስ የዚህ አዲስ ሕያው አካል(ቤተ ክርስቲያን) ራስ በመሆን የታሰበውን ታላቅ ተሐድሶ አምጥቷል። በነባሩና ባረጀው መንገድ ላይ በመሄድ ሳይሆን አዲሱን የለውጥ ራእይ፣ እርምጃ፣ እምነት፣ ተነሳሽነት፣ መሸከም አቅም ያላትን ቤተ ክርስቲያንን በመትከል የለውጥ መሠረት ጣለ ሐዋርያት በዚያ ላይ ገነቡ።

አባ እስጢፋኖስ

ከማርቲን ሉተር የተሐድሶ ጥያቄ የቀደመው የአባ እስጢፋኖስና የተከታዮቹ እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት በሰፊው ተገልጿል። ታዲያ የጠራ ነገረ መለኮታዊ አቋም የነበረው፣ የተሳሳተና ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ ልምምዶችና የዘርዓ ያዕቆብን የ*"ሰገዱልኝ"* ጥያቄ በእንቢታ የሞገቱ፣ የእግዚአብሔርን ቃል የተንተራሱና ራሳቸውን ለዚህ እውነት እስከ ሞት ድረስ ሰጥተው እያሉ ተሐድሶው ለምን አልተሳካላቸውም? ለሚለው መልሱ ብዙ ቢሆንም ቀዳሚው ተሐድሶውን ከታች ወደ ላይ መጀመራቸው ነው። በጊዜው ቤተክህነትና ቤተመንግሥት በጥምረት እነርሱ ከሚሉት አሳብ የወጣ የማንኛውንም ቡድን ሆነ ግለሰብ ከላይ ወደታች ከመጫን አልፈው ለማጥፋት የማይፈነቅሉት ድንጋይ ስላልነበረ ከታች የተነሣው የእነ አባ እስጢፋኖስ ጥያቄ ውጤታማ ሊሆን አልቻለም። መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን በጥምረት የተሐድሶን ጥያቄ ይዘው በተነሡት ቅዳሳን ላይ የወሰዱት ኢሰብዓዊ እርምጃ በሕዝቡ ላይ ትልቅ ደንጋጤን ስለፈጠረ የተሐድሶ ጥያቄ በሰፊው እንዳይነሣ ምክንያት ሆኗል።

መምህር ጌታቸው በአገራችን የተነሣውን ተሐድሶ ያደናቀፈው የተሐድሶን ጥያቄ ይዘው የተነሡት ጥያቄውን አገራዊ ያለማድረጋቸው እንደሆነ ይገልጻሉ፦ ሌላው ዘርዓ ያዕቆብ ተአምረ ማርያም በየገዳማቱ እንዲነበብ ሲያዝ አባ እስጢፋኖስ ለራሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት እንዲቀበሉ ከማድረግ ያለፈ በዚህ አሳብ ላይ ሌሎች ገዳማትን የማስተማርና የማንቃት ሥራ አልተሠራም። አገራዊ ንቅናቄ አልፈጠሩም። ለዚህ ነው የእርሱ ገዳም ጉንዳጉንዲ የማርያም አማላጅነት ለብዙ መቶ ዓመታት ሳይታወቅ የቆየው። የሊቃውንት ተሐድሶን ስመለከት እነ አለቃ ታዬ፣ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ ከንቲባ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ እነዚህ ታላላቅ ሰዎች የሊቃውንት ተሐድሶን ያመጡ ናቸው። በሊቃውንት ደረጃ ሕዝቡን ያማከለ ስላልነበር ሊቃውንቱ ሊሞቱ እዚያው ተዳፍኖ ቀረ[234] *ብለዋል።*

[234] ከሣቴ ብርሃን፣ ቁ 3፣ 2004 ዓ.ም ገጽ 25

የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ አሳብ ከጌታ ዘንድ በአንድ ግለሰብ ወይም በቡድን በክል ለቤተ ክርስቲያን ይመጣል። የተሐድሶን አሳብ ይዞ የሚነሣው አካል በትክክል ለሌሎች የማስተላለፍና አገራዊ ንቅናቄ የመፍጠር ኃላፊነት እንዳለው መዘንጋት የለበትም። አገራዊ የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ለማምጣት አገራዊ ንቅናቄ መፍጠር የግድ ነው። የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶን ለመምራት፣ በቃሉና በመንፈሱ የታደሰ ማንነት፣ ከብርቱ ፀሎት የተወለደ ግልጽ ራእይ፣ የቤተ ክርስቲያንን ያለፈውንና የአሁኗን ታሪክ በጥልቀት በመረዳት መጪዋን ማሳየት፣ ትኩረት በችግሮች ላይ እንጂ በሰዎች ላይ አለማድረግ፣ መታደስ ያለበትን በቃሉ ለይቶ ማውጣት፣ የእግዚአብሔርን ቃል በሰፊው መስበክና ማስተማር፣ ኀስሜት ላይ ሳይሆን በእውቀት ላይ የተመሠረተ ስልታዊ አገራዊ እንቅስቃሴዎችን መንደፍና በፍጥነት በሥራ መተርጎም፣ እጅ ለእጅ መያያዝ፣ መረጃዎችን መለዋወጥ፣ ለእውነት ለመኖር ብቻ ሳይሆን ቢያስፈልግ ለእውነት ራስን አሳልፎ ለመስጠት ተዘጋጅቶ መኖርን ይጠይቃል።

ማርቲን ሉተር

ጀርመናዊው ማርቲን ሉተር ለዘመናት ለነፍሱ ድነት ባሕታዊ ሆኖ ከሰው ተለይቶ ራሱን በመጉዳት ያላገኘውን ሰላም በክርስቶስ ኢየሱስ የቤዛነት ሥራ በማመን ዕረፍት አገኘ። አንድ ባሕታዊ መላውን አውሮፓ ከመንግሥታት ጋር ተጣምራ ትገዛ የነበረችውን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከታች ወደ ላይ ያቀረበው የተሐድሶ ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቢሆንም ከላይ ያሉት ታች ያለውን ሉተር ከእነ እውነተኛ ጥያቄው ሊያጠፋት ተነሣ። ይህም የተሐድሶ ከታች ወደ ላይ አደገኝነትን ያመለክታል። ሉተርም እውነትን እንደያዘ የሮም ጳጳስ የጥፋት አዋጅ ሰለባ ለመሆን ጫፍ ደረሰ። የሮም ጳጳስ ክስ፣ ስደት፣ ውግዘትና ባሕሪይ ገደላ አዋጆች፣ በጥፋት የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ሕልውናው አደጋ ላይ ወደቀ፤ መላ አውሮፓ በዚህ ወሬ ተሸፈነች። ሉተርም ነፍሱን ለማስመለጥ ከከተማ ገጠር ምስኪን ኮብላይ ሆኖ ነበር። ሉተረ የነገረ መለኮት ጥያቄ እውነተኝነት ከለላ ሳይሆንለት ሲቀር እግዚአብሔር በሉዓላዊ ዕቅዱ በፖለቲከኞች በኩል ጣልቃ ገባ። በወቅቱ በካቶሊክ አሠራርና ጫና እጅግ የተማረሩ የጀርመን ቤተ መሳፍንት፣ የእንግሊዝ ነገሥታትና የዩኒቨርሲቲ ምሁራን ከሉተር ጋር ቆሙ።

በወቅቱ የነበሩት የጀርመን መሳፍንትና የእንግሊዝ ነገሥታት በርግም ጳጳስ አገዳና ውግዘት ማስፈራሪያ ተሰላችተው ነበር። ስለዚህም ቤተ ክርስቲያንን ከላይ ወደ ታች እንዲየዋቅር ሥልጣን ሰጡት። ይህም አዲስ መዋቅር የሉተር ትምህርት እንዲቀጥልና ስኬታማ እንዲሆን አስቻለ።[235]

በተለይ እ.ኤ.አ በ1519 ንጉሥ ሆኖ የተመረጠው ቻርሊስ 5ኛ ለተሐድሶ ከነበረው ቀና ልብ የተነሣ ለሉተር የተሐደሶ ጥያቄ ስኬት ትልቅ ሚና

[235] ተኑት ኢንቴርናሽናል ኮርስ 1 2013 ገጽ 64

እንደተጫወተ ታሪክ ይናገራል።[236] ከሉተር በፊት የተሐድሶ ጥያቄ ያነሡት አባ እስጢፋኖስና ተከተዮቹ እንደዚሁም ጆን ሑስ ሰማዕት ሆነው ከእነርሱ በኋላ ተመሳሳይ ጥያቄ ያነሣው ሉተር ለምን ተሳካለት? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ብዙ ሊሆን ቢችልም ሉተርም ቢሆን በነባሩ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆኖ ተሐድሶ ማምጣት ከታች ወደ ላይ መሄድ አስቸጋሪ ስለሆነበት አልቻለም። የተሳካለት በቃሉ እውነት ላይ ቆሞ አዲስ መዋቅር ከላይ ወደ ታች ማዋቀር ስለቻለ ነው።

አባ እስጢፋኖስና ጆን ሑስ ተሐድሶን ያልቻሉበት አንዱ ምክንያት ከታች ወደ ላይ ተሐድሶን ማድረግ እጅግ አደገኛ ስለሆነ ነው። በፍፁም አይቻልም ማለት ግን አይደለም። ቤተ ክርስቲያን በመዋቅራዊና ድርጅታዊ ሰንሰለት ከታሰረች ከቃሉ በላይ ራሷን ትሰማለች፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ በቁሳቁስ ትታመናለች፣ ከእግዚአብሔር ፊቃድ ይልቅ በእጅ ብልጫና በሕዝብ ብዛት ያለ ቅጥ ትደገፋለች፣ ዕድገትን የጨረሰች ስለሚመስላት ስለዕድገት እንድነገራት ብዙ አትፈቅድም። ባትማርም ለማስተማር ብቁ እንደሆነች ታስባለች፣ ከሁሉ ኋላ ቀርታ ከሁሉ እንደቀደመች ለመስበክ ቅንጣት ያህል አትፈራም። እንዲህ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ብዙን ጊዜ ከላይ ወደ ታች እንጂ ከታች ወደ ላይ ሥር ነቀል ለውጥ ማምጣት አስቸጋሪ ቢሆንም ለጌታ ግን ሁሉ ይቻላል። የለውጥ ጠላት የሆነ መዋቅር አንድ ትልቅ ጠቃሚና የጊዜው አሳብ ከታች ሲነሣ በአሉታዊና በትልቅ ጥርጣሬ መከታተል እንጂ መፍትሔ የሚሆን ነገር በዚህ ይመጣል ብሎ በፍጹም አያስብም።

ሌሎች የተሐድሶ ምሳሌዎች

1. **ፊልፕ ያዕቆብ ስፔንስር *(1635-1702)*** የቅድስና እንቅስቃሴ አባት በመባል የሚታወቀው ስፔንስር ከተራው የቤተ ክርስቲያን አባል አነስተኛ ቡድኖች በመመሥረትና ንቅናቄዎችን በመጠቀም ቤተ ክርስቲያንን ለመለወጥ በከፍተኛ ሁኔታ ሞክሮ ነበር። ይሁን እንጂ ከላይ ወደ ታች እንቅስቃሴውን ለመምራት ሥልጣን በማጣቱ አልተሳካለትም።

2. **ካውንት ኒኮላ ቮን ዚንዘንዶርፍ *(1700-1760)*** የሉተራን ቤተ ክርስቲያን አባላትን ከታች በተራ አባላት "grass root model" የመለወጥ በብርቱ ቢታገልም አልቻለም። በነባሩ ሲያቅተው የሞራቫውያን ወንድሞች የሚል አዲስ መዋቅር መሥርቶ ከላይ ወደታች በፈጠረው ተጽዕኖ የተለወጡና በአውሮፓና በአሜሪካ ትልቅ ተጽዕኖ ያመጡ አነስተኛ ቡድኖችን አፍርቶ ነበር።

3. **ጆን ዌስሊ *(1703-1791)*** ጆን ዌስሊ የተነሣው ከአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ራእዩ በዚያችው ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶን የማምጣት እንጂ ፍጹም ሌላ ቤተ እምነት የመመሥረት ዓላማ አልነበረውም። ዌስሊ ከታች ወደ ላይ ተሐድሶን ለማምጣት

[236] Henary Bettenson (1963), *Documents of the Christian Church*, London Oxdord University Press, p.269

ያደረገው ብርቱ ጥረት እንደ ሌሎቹ ወደ ስኬት አላመጣውም። ከእንግሊዝ ወደ አሜሪካ ተሻግሮ ያሰበውን ተሐድሶ ሊያመጡ የሚችሉ አዲስ መዋቅሮችን ከላይ ወደ ታች በማውጣት ታላቅ ተጽዕኖ አምጥቷል።

4. አባ ቴድሮ *ፖፒስኮ (1887-1963)* በሩማኒያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህን ሆኖ ያገለግል የነበረው አባ ቴድሮ ፖፒስኮ በቤተ ክርስቲያኒቷ የጠራ፣ የጠለለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶን ለማምጣት ከታች ወደ ላይ ብርቱ ትጋት ቢያደርግም ውጤቱ ውግዘትና መባረር እንደሆነበት ተመልክተናል። ቤተ ክርስቲያን ስታረጅና እውነት ሲጠፋባት ወደ እግዚአብሔር ቃል እንድትመለስ እግዚአብሔር ከአብራኳ የወጡ ልጆቿን የመመለስ መልዕክት ሰጥቶ ወደ እርሷ ሲልካቸው በማሳደድ፣ በማውገዝ፣ በማባረርና በመግደል የተሐድሶን እሳት ለማዳፈን እንደምትጥር በሰፊው አይተናል። በአባ ቴድሮ ፖፒስኮም ላይ የደረሰው ይኸው ነበር። በነባሩና በቆየው የሩማኒያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ለማምጣት የነበረው ራእይ ለጊዜው የከሰመ ቢመስልም ተስፋ ግን አልቆረጠም። በመጨረሻም ከላይ ወደ ታች አዲስ የተሐድሶ መዋቅር በመዘርጋት ከታደሰ ልብ የታደሰች አብያተ ክርስቲያናትን በዘመኑ ተክሎ፣ ብዙ ደቀ መዛሙርት አፍርቶ፣ በወንጌል እውነት ሺዎችን ማርኮ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት በመላት ገልጦ ወደ ቀጣዩ ሕይወት በድል ተሻግሯል።

በቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ለማምጣት ከላይ ወደ ታች ያለ ብዙ ትግል፣ ያለ አላስፈላጊ መሥዋዕትነት በአጭር ጊዜ እውን ማድረግ እንደሚቻል ምሁራን ይናገራሉ። ነገር ግን ተሐድሶ ከታች ወደ ላይ ሲሆን ብዙ መሥዋዕትነት፣ ረዥም ጊዜ፣ ሰፊ ጥናትና ዝግጅት፣ አካባቢያዊ፣ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ እንቅስቃሴ መፍጠርን ይጠይቃል። የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ጥያቄም ብዙ ምዕተ ዓመታት ያስቆጠረበት ምክንያት ጥያቄውን ያነሡት ከመሪዎች ሳይሆን ከተከታዮች፣ ሥልጣንና የውሳኔ አቅም ካላቸው ሳይሆን ውሳኔና ሥልጣናቸው በበላይ አካላት ላይ ምንም ተጽዕኖ መፍጠር ከማይችሉ በታች ካሉት አካል መነሣቱ ነው። ለምሳሌ፦ ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ ከመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ጋር በግልጽ የሚጋጭ "ተአምረ ማርያም" በአንዳንዶች "ፀረ ወንጌል" አሳብ የያዘ መጽሐፍ ተብሎ እየተከለሰና አንዳንድ ካህናት በግልጽ እየተቃወሙት በገዳማቱና በአብያተ ክርስቲያናት እንድነበብ ያደረገው ከላይ ወደ ታች የነበረውን ሥልጣን በመጠቀም ነው። ተሐድሶ ከላይ ወደ ታች እንጂ ከታች ወደ ላይ በጣም ከባድ ነውና። እግዚአብሔር ግን ከታች ወደ ላይም ማድረግ ይችላል። በላይም ሆነ በታች ያሉትን ለክብሩ የሚጠቀም እግዚአብሔር እስከሆነ ድረስ ራሳችንን ለእርሱ በመስጠት ለአገራችን የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ እንነሣ!

የተሐድሶ ባለራእዮች በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይፈለጋሉ፦

ይህ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በባዶ የአንደበት ፉክራ የምትገለጥበት ዘመን ሳይሆን ታላላቅ የተሐድሶ ባለራእዮች ከቤተ ክርስቲያን ተነሥተው ምድሪቷን ወደ እግዚአብሔር ዕውቀትና በረከት የሚመሩበትና ኢትዮጵያ በአራቱም አቅጣጫ ለዓለም ሕዝብ በረከት የምትሆንበት ወሳኝ ወቅት ላይ ደርሰናል። ሊነጋ ሲል እንደሚጨልም የታወቀ ሲሆን እንደዚሁም ወደዚህ ታላቅ በረከት አገራችን በእግዚአብሔር ቃል ታድሳ ለመገለጥ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ብርቱ መንፈሳዊ ጦርነት መኖሩ የተረጋገጠ ቢሆንም ድሉ የጌታና የልጆቹ ነው። አሜን!

ከአንግዲህ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ በፐሮቴስታንቶችና ካቶሊካዊት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ታላቅ የተሐድሶና የመንፈስ ቅዱስ እሳት በዘመናችን ይቀጣጠላል። ለዘመናት በዓለም ይጠበቁ የነበሩ ታላላቅ የቃሉ ሰባኪ ባለራእዮች ከምድራችን በእኛ ዘመን ይነሣሉ።

በሚቀጥለው ምዕራፍ የፐሮቴስታንት እምነት ከእግዚአብሔር ቃል በተወጣጡ አምስት ምሶሶያት እንደቆመ እንመለከታለን።



የፕሮቴስታንት ተሐድሶ አምስቱ ምሶሶያት

የፕሮቴስታንት ተሐድሶ መሪዎች ማርቲን ሉተር፣ ጆን ካልቪን፣ አልሪች ዝዊንግሊ፣ ጆን ኖክስ በዘመኑ ከነበረችው ከሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ልዩ የሚያደርጋቸውን አምስት ነገረ መለኮታዊ ቁልፍ የአስተምህሮ ምሶሶያት አስቀምጠዋል። እነዚህ አምስቱ የተሐድሶ ምሶሶያት "አምስቱ ሶላዎች" /Five Solas/ ተብለው ይታወቃሉ። ሶላ/Sola/ ማለት የላቲን ቃል ሲሆን ትርጉሙም "ብቻ" ማለት ነው። "አምስቱ ብቻዎች" የተባሉት፦

1. ለድነት መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ

"Sola Scriptura," or "Scripture Alone".

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ***"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል"*** *የሚልና ተመሳሳይ ዐረፍተ ነገር በብሉይ ኪዳን 3,808 ጊዜ ተጠቅሷል። በፔንታቱክ 700 ጊዜ፣ በታሪክ መጻሕፍት 400 በኢሳያስ ብቻ 150 ጊዜ፣ በሕዝቅኤል 350 የተጻፈ ሲሆን ይህም የቃሉ ምንጭና ባለቤት እግዚአብሔር እንደሆነ ያመለክታል"*[237] በቤተ ክርስቲያን ያለው ልምምድ፣ አስተምህሮና ማንኛውም ሥርዓት በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ይዳኛል፣ ይመራል፣ ይገመገማል፣ ይታረማል፤ የሚል ሲሆን ማርቲን ሉተር በአንድ ወቅት ፍርድ ቤት ቀርቦ አቋሙን እንዲለውጥ ሲጠየቅ፦ *መጽሐፍ ቅዱስና ሕሊናዬ መሳሳቴን ካልገለጠልኝ በስተቀር የሮም ጳጳስና አማካሪዎቹን ትምህርት አልቀበልም፤ አርስ በርሳቸው ይጣረሳሉና። አዕምሮዬና ልቤ ለእግዚብሔር ቃል እሥረኞች ናቸው። የሕሊናዬ ተቃዋሚ ሆኜ መሰለፍ አይሆንልኝም። ከዚህች አቋሜ ፍንክች አልልም። እግዚአብሔር ይርዳኝ። አሜን*

በማለት ለቃሉ ያለውን ታማኝነት ገልጾ ነበር። የፕሮቴስታንት ተሐድሶ *"መጽሐፍ ቅዱስ"* ብቻ ብሎ ሲነሣ 66ቱን መጽሐፍ የያዘ አንዱን መጽሐፍ ቅዱስ ለማለት ነው። ዶክተር ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ በአሜሪካ ባሉት ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ላይ ባደረጉት ጥናት ትልቁ ትኩረታቸው መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ሲገልጹ፦ *የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ክህነት ያላቸው ሳይሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የላቁ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የሰለጠኑ፣ የወንጌል ትምህርትን የሚጠብቁ አስተማሪዎች ናቸው። ክህነታቸው እምነታቸውና ታማኝነታቸው ነው። የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ትምህርት አጠቃላይ ፍልስፍና የወንጌል ትምህርት ከሕዝቡ ሕይወት ጋር በማያያዝ፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ምንባብ ከሕዝቡ የዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር ማጣመር፣ መጽሐፍ ቅዱስን የኑሮ መመሪያ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ያሳያሉ። የአውሮፓም ሆነ በአሜሪካ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት አዲሱ አመለካከት ይህ ነው*[238] ብለዋል።

የአዋልድ መጻሕፍት የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት አይደሉም!

በጥንት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የአዋልድ መጻሕፍት የመጽሐፍ ቅዱስ አካል ይሁኑ ወይስ አይሁኑ በሚለው አሳብ የተከፋፈለ አመለካከት ነበር። ያም ሆኖ ከጥንት የተሳለፈልን አብዛኛው መረጃ የአዋልድ መጻሕፍት ለንባብ

[237] Evans, Williams *(1949)*, *The Great Doctrine of the Bible, Moody*, Chicago.p203
[238] ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ (2001 ዓ.ም) ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ ገጽ 249

እንጂ እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት መታየት የለባቸውም የሚል ነው። ሌላው የአዋልድ መጻሕፍት በዕብራይስጥ የብሉይ ኪዳን ቅጅ ያለመኖራቸው በብዙዎች ዘንድ ጥሪጣሬያቸውን አጉልቷል። ዛሬ በእጃችን ያለው የጥንታዊ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር በ170 ዓ.ም በሰርዶሱ ጳጳስ ሜሊቶ የተጻፈ ነው።[239] እርሱም እንዲህ ብሎ ነበር፦

> *ወደ ምሥራቅ መጥቼ እነዚህ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በሚሰበኩበትና በሥራ ላይ በሚውሉበት ቦታ ስደርስ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን በትክክል አወቅኋቸው፤ እኔም እውነቱን ገልጬ በማስፈር መጻሕፍቱን ላክሁላችሁ። መጻሕፍቱም እነዚህ ናቸው፦ እምስቱ የሙሴ መጻሕፍት፤ ዘፍጥረት፣ ዘፀአት፣ ዘኍልቁ፣ ዘሌዋውያን፣ ዘዳግም፣ ኢያሱ፣ መሳፍንት፣ ሩት፣ አራቱ የነገሥታት መጻሕፍት፣ ሁለቱ ዜና መዋዕል መጻሕፍት፣ የዳዊት መዝሙር፣ የሰሎሞን ምሳሌዎችና ጥበብ፣ መክብብ፣ መኃልየ መኃልይ፣ ኢዮብ፣ ትንቢተ ኢሳያስ፣ ኤርምያስ፣ አሥራ ሁለቱ ደቂቅ ነቢያት፣ በአንድ መጽሐፍ፣ ዳንኤል፣ሕዝቅኤል፣ ዕዝራ (መጽሐፈ ዕዝራ -ነህምያን አካትቷል) ናቸው።*[240]

ሜሊቶ አሁን በእጃችን ከሚገኙት የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት መካከል መጽሐፈ አስቴርን[241] ከማስቀረቱ በስተቀር ከአዋልድ መጻሕፍት የአንዱንም ስም ያለመጥቀሱ በትኩረት ማስተዋል ያለብን ጉዳይ ነው። የአዲስ ኪዳን "ካኖን"[242] ተቀባይነት ማግኘትን ስንመለከት ደግሞ ለአዲስ ኪዳን ካኖን መጀመሪያ ዕውቅና በተሰጠበት ወቅት የጳውሎስ መልዕክቶች በየአብያተ

[239] Eusebiuys (1975), *Ecclesiastical History*, two vol. 5. London, Heinemann: and Cambridge, Mass: Harvard,

[240] ዌይን ግሩደም *(2003 ዓ.ም)* ፣ ስልታዊ ሥነ መለኮት፣ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ መግቢያ፣ ኤስ ኤይ ኤም ማተሚያ ቤት፣ ገጽ *54-55*

[241] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 55 (ሕዳግ) በጥንታ ቤተ ክርስቲያን ምሥራቁ ክፍልና አንዳንድ ሪቢዎች በራሳቸው ምክንያት የአስቴርን መጽሐፍ ቀኖናዊነት የልብ ማመንታት ቢኖርም በመጨረሻ ተቀባይነት አግኝቷል፤

[242] *«ካኖን» የሚለው ቃል የሚያመለክተው የጥንት አብያተ ክርስቲያን የእምነታቸው መመሪያ አንዲሆኗቸው የተቀበሏቸው የመጻሕፍት ስብስብ ነው። ቃሉ ተመሳሳይ ከሆነ ከግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን፣ ትርጉሙም «የሚለካ» ወይም «መለኪያ» ማለት ሊሆን ይችላል። በሃይማኖት አካባቢዎች «ካኖን» በአስተንፋሰ እግዚአብሔር ተጽፈዋል ሚባሉትና በዚህም ምክንያት በመንፈሳዊነት ረገድ በጣም ዋጋ ያላቸውን መጻሕፍት ያመለክታል። ስለዚህም ነው ከሌሎች በርካታ የክርስቲያናዊ ጽሑፎች የተለዩት። የካኖን ሂደት የተጀመረው በ95 ዓ.ም ገደማ ከመጨረሻ ደቀ መዝሙር (ዮሐንስ) ሞት በኋላ ነበር። የአዲስ ኪዳን ካኖን ውሳኔ በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ላይሆን የክርስቲያኖች የጋራ ስምምነት ውጤት ነው። በጣም የቆየው የካኖን ዝርዝር የአስክንድርያው ጳጳስ የሆነው አትናቴሶስ በ378 በጻፈው ደብዳቤ ይገኛል። በደብደቤው በአሁኑ አዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙትን 27 መጻሕፍት ዘርዝሯል። የክርታጎው ጉባኤ በ397 በጉዳዩ ላይ ሳይንጋገር የአትናቴሶስ ዝርዝር አጽድቋል። በአሁኑ «ቅዱስ መጻሕፍት» ብለን የሚንጠራውን ካኖን የተጀመረው በአይሁዳውያን ሲሆን አሁን «ብሉይ ኪዳን» ብለን የምንጠራውን 39 መጻሕፍት ያቀፈ ነው። ዛሬ የካቶሊክ ካኖን 80 መጻሕፍት (ንሂሩ በትሬንት ጉባኤ የታከሉትን 14 መጻሕፍት ጨምሮ) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካኖን 81 መጻሕፍት የፐሮተስታንትና የግሪክ ኦርቶዶክስ ካኖን 66 መጻሕፍትን ያጠቃልላል። (ታሪካዊ ሥነ መለኮት፣ 1991 ዓ.ም ገጽ 13 ከግርጌ ሕዳግ የተወሰደ።)*

ክርስቲያኑ የመነበብ ሥልጣን አግኝተው ነበር። ኤፌሜስ ማርቅያንንና ናስትሳውያንን በመቃወም አራቱን ወንጌላት ተቀበለ። በኢ.ኤ.አ 175 አካባቢ መራቶሪያን ካኖን ውስጥ ዕብራውያንን፣ 1ኛ እና 2ኛ ጴጥሮስ፣ 1ኛ ዮሐንስ እና ያዕቆብ መልዕክት ሲቀሩ ሌሎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተመዘገቡ። እንዲሁም ታላቁ አትናትዮስ ሊቀ ጳጳስ ዘእስክንድርያ *(የቤተ ክርስቲያን ምሰሶ፤ ሐኪም)* በማለት አበው የሚጠሯቸውንና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም በእርሳቸው ፓትሪያርክ አባትነት እንደተመሠረተች የሚነገርላቸው ኢ.ኤ.አ 367 የተጻፉት 39ኛው የፋሲካ ደብዳቤ ዛሬ በእጃችን የሚገኙትን 27 የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር በትክክል ይዟል። ከዚያም ሃያ ሰባቱ መጻሕፍት በስፋት ተቀባይነት አገኙ።[243]

> *በምሥራቅ የሚዲትራኒያን ዓለም ውስጥ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው የእነዚህ መጻሕፍት ዝርዝር ነው። ከሦሳኅ ዓመት በኋላ በ397 ዓ.ም የካርተጅ ጉባኤ ከሚዲትራኒያን በስተ ምዕራብ የነበሩት አብያተ ክርስቲያናትን በመወከል ከሚዲትራኒያን በስተ ምሥራቅ ከነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ጋር በእነዚያው የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ላይ ተስማምቷል። ዛሬ በእጃችን የሚገኘው የመጨረሻ ቀኖና እነዚህ የመጀመሪያዎቹ መጻሕፍት ዝርዝር የያዘ ነው።*[244]

አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በ66ቱ መጻሕፍት ላይ ከአፖክሪፋ (የአዋልድ) መጻሕፍት በመጨመር *"የመጽሐፍ ቅዱሳቸውን"* መጻሕፍት ቁጥር ከፍ አድርገዋል። በእስትንፋሰ እግዚአብሔር ያልተጻፉ መጻሕፍት */Apocryphal or Deuterocanonical books/* አፖክሪፋ የሚለው ቃል *a-pok'-ri-fal apokrupto* ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም፦ *ድብቅ የተሸፈነ ለደንዳ ያለው እንደ ማለት ነው።* ዲዮካትሮኖኒካል ማለትም ተጨማሪ ማለት ነው።[245] በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስመጥር የታሪክ ጸሐፊና ከቀዳሚ አባቶች አንዱ አቡነ ጎርጎርዮስ በመጽሐፋቸው ስለ አፖክሪፋ እንዲህ ጽፈዋል፦

> *ናስቲኮች ከራሳቸው አሳብ ጋር በመቀላቀል የሐዋርያት ትምህርት ይህ ነው እያሉ ቤተ ክርስቲያናትን ሲያወናብዱ እያሉ ዘመን ቆይተዋል። እነዚህም መጻሕፍት ድብቅ (አፖክሪፓ) በመባል የሚታወቁ ናቸው። በውስጣቸው አንዳንድ እውነት እንዳለ ይታወቃል። ነገር ግን ብዙውን የግኖስቲኮች ሃሳብ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን አትጠቀምባቸውም።*[246] *ብለዋል።*

የጥንት የቤተ ክርስቲያን አበው ከፕሮቴስታንት ተሐድሶ በፊት 66ቱን የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ብቸኝነትና ቅዱስነት እንዲህ መስክረዋል።

[243] ምኒሊክ አስፋውና ሰሎሞን ጥላሁን *(ትርጉም) (1991 ዓ.ም)* ፣ ታሪካዊ ሥነ መለኮት አመጣጡና ትንተናው፣ ገጽ 29-30

[244] ዌይን ግሩደም *(2011) (ትርጉም)*፣ ስልታዊ ነገረ መለኮት፣ ገጽ 62

[245] *Apocryphal a-pok'-ri-fal apokrupto = "hidden" or "secret" ISBE Encyclopedia, 607*

[246] አቡነ ጎርጎርዮስ ፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፣ አዲስ አበባ፣ ገጽ 69

> ቅዱሳት መጻሕፍት /66ቱ/ በመንፈስ ቅዱስ የተጣሩና የነጠሩ አንድ መንፈስ ያላቸው ናቸው::[247]
>
> ቅዱስ ቴዎፍሎስ

> ቅዱሳት መጻሕፍት /66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ/ ከእግዚአብሔር አፍ የወጡ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ለሰው የተነገሩ የልዑል ቃላት ናቸው[248]
> ቅዱስ ቀለምንጦስ

> ቅዱሳት መጻሕፍት /66ቱ/ ፍጹማንና የነጠሩ /inspired/ ናቸው፤ ቃላታቸው በመንፈስ ቅዱስ የተቃኙና የተፈተሹ ናቸው::[249]
>
> ቅዱስ ሲረንዩስ

> (የአዋልድ) መጻሕፍት መለኮታዊ ሥረ መሠረት እንዳላቸው የሚገልጽ ምንም ምልክት የላቸውም::
>
> የነገረ መለኮት ምዘር ሊ.ጂ. ያንግ

ታላቁ አትናትዮስ ሊቀ ጳጳስ ዘእስክንድርያ *(የቤተ ክርስቲያን ምሰሶ፤ ሐሊያ)* ስለ 66 መጽሐፍ ሲናገሩ:- *አምላካውያን መጻሕፍት 66ቱ ናቸው:: ለሕይወት ይነበቡ:: ለሌሎች ደግሞ ለንባብ ይሁኑ ሲል ተናገሮአል::[250] እንዲሁም አርጌን አንድም የአዋልድ መጽሐፍ ቀኖናዊ መሆኑን አላረጋገጠም እንዲያውም የመቃቢያን መጻሕፍት ከቀኖና መጻሕፍት ውጭ ስለመሆናቸው በግልጽ ተናግሯል::[251]* የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ከላይ በተመለከትናቸው አባቶች ዕውቅና ባገኘው 66ቱ መጻሕፍት ላይ የተመሠረቱ፤ እርሱን ብቻ እንደሚቀበሉና እንደሚሰብኩ ይናገራሉ::

ለፕሮቴስታንት ተሐድሶ ምላሽ ለመስጠት እ.ኤ.አ 1546 በትሬንስ ጉባኤ ተካሂዶ ነበር:: በዚህም ጉባኤ ላይ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሥነ ጽሑፍ ውጤቶችን ቅዱስ መጽሐፍ የሚድረግ ሥልጣን እንዳላት አቋም ያዘች:-

> *ፕሮቴስታንቶቹ ግን ቤተ ክርስቲያን አንድን ጽሑፍ መጽሐፍ ቅዱስ የማድረግ ሥልጣን የላትም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲጻፍ ላደረገው ለራሱ ቃል ዕውቅና ተሰጣለች ብለዋል:: በአንድ አገር ያሉ ፖሊሶች እውነተኛና ውሸተኛ የብር ኖቶችን የመለየት እንጂ የመሥራት ስልጣን የላቸውም:: መሉ ሥልጣን ያለው ሕጋዊ የሆነው ብሔራዊ ባንክ ብቻ*

[247] *St. Theopilos, Autolic,3,12 migne P.G.vol.col137*
[248] *st. Clement of Rome 1st letterto Corinthians 45, 2, 3 Migne p.. G.I, col.300)*
[249] st Iranies Against Heresies 2, 28,2 migne P.G.Vii col 804
[250] St Savkkou VHLq eortadtikh. Evpidtolh. Tou/ MVAqanadi.ou 1973-1974 page 9 *Qullensammlung zur Geschichte des Neutestamentlichen Kanons bis ouf Hieronymus (Zurich: Meyer and Zeller, 1844), pp. 7-9. A select Library of the Nicene and poast – Nicene Fathers of the christan church, vol. 4 (New York 1892). pp. 550-5*
[251] [251] *ዊይን ግሩደም፤ ገጽ 55*

> *እንደሆነ ሁሉ እውነተኛ ቃሎች በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ መጨመር ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው::[252]*

የአዋልድ መጻሕፍት ለምን ተቀባይነት አጡ?

ዲያቆን ዳንኤል ክብረት *"አርቶዶክስ መልስ አላት" /ከፕሮቴስታንቶ ለሚነሡ አንዳንድ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች/* በሚለው መጽሐፍ *"ብዙ ፕሮቴስታንት ክፍሎች አዋልድ መጻሕፍትን አይቀበሉም:: መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት እንዳላቸውም አይቀበሉም"[253]* ያሉት አንኳር ጽንሰ አሳብ እውነትነት ያለው ሲሆን ለምን እንዳልተቀበሉ ግን አላስቀመጡም:: *የአዋልድ መጻሕፍትን ለንባብና ለአንዳንድ ታሪክ ማጣቀሻነት ማንበብ እንሚቻል እንጂ ለክርስትና መመሪያም ሆነ ለደግማ መጠቀም እንደሌለብን የነገረ መለኮት ምሁራን ይናገራሉ::[254]* ፕሮቴስታንት ብቻ ሳይሆኑ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በፊት የነበሩ ብዙ አባቶች የአዋልድ መጻሕፍትን እንደ እግዚአብሔር ቃል እንዳልተቀበሉት በሰፊው ተመልክተናል፤ ለምን አልተቀበሉትም? ተጨማሪ መልስ ካስፈለገ ለምሳሌ:- ከአዋልድ መጻሕፍት ሄርመስ *"እረኛ"* የተባለ መጽሐፍ *"ንስሐ የመግባት አስፈላጊነት"* እና ቢያንስ አንድ ጊዜ ከጥምቀት በኋላ የኃጢአት ይቅርታ ማግኘት እንደሚቻል... ያስተምራል:: ጸሐፊው ከክርስቶስ ተሠግሞ በፊት መንፈስ ቅዱስን እና የእግዚአብሔርን ልጅ አንድ የሚያደርግ እንዲሁም ሥላሴ የተከሰተው የክርስቶስ ስብእና ወደ ሰማይ ከተወሰደ በኋላ ነው፤ የሚል ይመስላል*(Oxford Dictionary of the Christian Church. p.641)*፤ ሌላው በአንዳንዶች ዘንድ ለጊዜው እንደ ቀኖና ሲታይ የቆየው የቶማስ ወንጌል የሚደመድመው በሚከተሉት አሳፋሪ ዐረፍተ ነገር ነው *(JC.114)*

> *ስምዖን ጴጥሮስ እንዲህ አላቸው፤ "ሴቶች ለሕይወት የተገቡ ስላልሆኑ ማርያም ከእኛ ትለይ" ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ "እኔ እመራታለሁ፤ እናንተን ወንዶችን የምትመስል ሕያው መንፈስ እንድትሆን ወንድ አደርጋታለሁ:: ራሷን ወንድ የምታደርግ ሴት ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማይ ትገባለች::"[255]*

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ለመናድ የሚታገል የተገለጠ ሕፀፅ የተሸከመውን መጽሐፍ በቀኖና ውስጥ እንዴት ቦታ ሊያገኝ ይችላል? ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት በፍጹም የሌለው ሐሳብ ነው:: ከዚህም የተነሣ የቀደሙት የእምነት አበው የጠራውን የ66ቱን የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ቀኖና የሚቀበሉ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉም አዋልድ መጻሕፍትን የሚነበቡ መንፈሳዊ መጻሕፍት እንጂ እንደ እግዚአብሔር ቃል አይቀበሉም::

[252] *ዝኒ ዘማሁ፤ ገጽ 56*
[253] *ዳንኤል ክብረት (ዲ/ን) (2004 ዓ.ም) ፤አርቶዶክስ መልስ አላት፤ ገጽ 123*
[254] Philip Schaff, (1977) *Creeds of Christendom*, Baker Book House Vol. III pp.489-491
[255] ይህ ሰንድ የተጻፈው በሐዋርያው ቶማስ አይደለም:: በአሁኑ ጊዜ የሚሰጠው ምሁራዊ አስተያየት እንደሚያመለክተው ሰነዱን የጻፈው በሁለተኛው ክፍለ ዘመን የነበረ ቡቶማስ ስም የተጠቀመ ያልታወቀ ጸሐፊ ነው::

ዲዳኬ "Didache" በቃሉ ሲመዘን

"ዲዳኬ" በግሪክ ቋንቋ ትምህርት ማለት ሲሆን በዚህ ስያሜ የሚታወቀው ጥንታዊ ሰነድ "ትምህርተ ሐዋርያት" በመባልም ይጠራል። ዲዳኬ ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን መሠረት እምነቷን የምታስተምርበት የአስተምህሮ መጽሐፍ ሲሆን የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ በምታካሂድበት ጊዜ ሁሉ ይነበብ የነበረ መጽሐፍ ነው። ቀለሜንጦስ ዘአስክንድርያም ሆነ አርጌንስ ዲዳኬን የቅዳሳት መጻሕፍት አካል ነው ይበሉ እንጂ ቀኖናዊ መጽሐፍ ነው የሚለው ጉዳይ ዓለም አቀፋዊ ዕውቅና ስላላገኘ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ መካተት አልቻለም። ነገር ግን እንደ አትናቴዎስ ያሉ ስመ ጥሪ የቤተ ክርስቲያን አበው ዲዳኬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቢነበብ ሰዎችን ያንጻል የሚል አቋም ነበራቸው።[256]

ዲዳኬ በ1875 ዓ.ም በኮንስታንቲኖፖል ቤተ መጻሕፍት የተገኘ ሰነድ ነው። በቀኖና ውስጥ እንዲካተት ባይታሰብም ብዙ ምሁራን በጽሑፉ ላይ ሰፊ ጥናት ካካሄዱ በኋላ ከሁሉም በፊት የተጻፈ ሰነድ እንደሆነ ከስምምነት ላይ ደርሰዋል።[257] አንዳንዶች ግን ዛሬም ከጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት አንጻር ከአዲስ ኪዳን ጽሑፎች ጋር እኩል ሥልጣን እንዳለው አድርገው ይጠቅሳሉ። ችግሩ ዲዳኬ በአዲስ ኪዳን ሐሳብ ላይ መጨመርና መቀነሱ ነው። ለምሳሌ፦

- *ክርስቲያኖች መባቸውን (ምጽዋታቸውን) በእጃቸው ጨብጠው እንዲያቄዩ ተናግሯቸዋል (1:6)*
- *ሰዎች ከመጠመቃቸው በፊት እንዲጸሙ ይጠበቅባቸዋል እንዲሁም ጥምቀት መፈጸም ያለበት በወራጅ ውኃ መሆን እንዳለበት ተናግሯቸዋል (7:1-4)።*
- *ጾም በረቡዕ እና በዓርብ ቀናት እንጂ በሰኞ እና በሐሙስ ቀናት መጾም ተክልክሏል (8:1)።*
- *ክርስቲያኖች የጌታን ጸሎት በቀን ሦስት ጊዜ እንዲጸልዩ ታዘዋል (8:3)።*
- *ሐዋርያት ከሁለት ቀን በላይ በአንድ ከተማ ውስጥ እንዳይቈዩ ይከለክላል (11:5)። ነገር ግን ጳውሎስ አንድ ዓመት ተኩል በቆሮንቶስ እና ሦስት ዓመት በኤፌሶን መቈየቱን ልብ ይበል፤*
- *በመንፈስ የሚናገሩ ነቢያት ሊፈተኑ ወይም ሊመረመሩ አይችሉም 11:7 ፤ (ይህ ከ1ቆሮ 14:29 እና 1ተሰ 5: 20-21 አሳብ ጋር ይጋጫል)*
- *ድነት በመጨረሻው ጊዜ ፍጽምነትን ይፈልጋል (16:2)።*[258]

ከዚህ የምንረዳው ነገር ዲዳኬ ቀደምት ሰነድ መሆኑ በብዙዎች ታምኖ አንዳንዶች ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር እኩል ደረጃ ሰጥተው ለማስረዳት ቢታገሉም በውስጡ ከአዲስ ኪዳን መልዕክት ጋር በግልጽ የሚላተሙ ሐሳቦችን እንደያዘ እንመለከታለን። ለእግዚአብሔር ቃል የተለየ ቦታ ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ከማንበብ ባለፈ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ

[256] ተስፋዬ ሮበሌ *(1999 ዓ.ም)* ፣ ውኃውና ስሙ፣ ራእይ አሳታሚ አዲስ አበባ ገጽ 89

[257] Didache, (1975 7)1-4 ed. *Cyril C. Richardson, Early Christian Father* (New York: Macmillan, 174

[258] ዊይን ሣሩደም፣ ገጽ 66 (የግርጌ ማስታወሻውን ይመልከቱ)

ቃል የማይወሰዱት ከዚህ የተነሣ እንደሆነ ይናገራሉ። ቃሉም መጨመርና መቀነስን ይቃወማል።

> *"የዚህን መጽሐፍ የትንቢት ቃል የሚሰማውን ሁሉ አስጠነቅቃለሁ፤ ማንም በዚህ ቃል ላይ አንዳች ቢጨምር፣ እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሠፍቶች ይጨምርበታል፤ ማንም በዚህ የትንቢት መጽሐፍ ከተጻፈው ቃል አንዳች ቢያሥወድል እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ ዕድሉን ያሥወድልበታል" (ራእ. 22: 18-19 አ.መ.ት.)።*

ፕሮቴስታንቶች የአዋልድ መጻሕፍትና ዲዳኬን እንደ እግዚአብሔር ቃል ያለመቀበላቸው የሐዋርያት አስተምህሮ፣ የቤተ ክርስቲያን አበው ውሳኔ፣ ዘመን ዘለቅ የቤተ ክርስቲያን ታሪክና ስለ እግዚአብሔር ቃል የተረዱት እውነት ስለማይፈቅድልን ነው ይላሉ። ዕውቁ የነገረ መለኮት ምሁር ኢ.ጄ.ያንግ ስለ አዋልድ መጻሕፍት ያሉትን ልጥቀስ፦

> *እነዚህ መጻሕፍት መለኮታዊ ሥረ መሠረት እንዳላቸው የሚገልጽ ምንም ምልክት የላቸውም። ዮዲት እና ጦቢት የተባሉት ሁለቱም መጻሕፍት በርካታ ታሪካዊ እና መልክአ ምድራዊ ስሕተቶች የሚገኙባቸው ሲሆን፣ ቅደም ተከተል ያለ መጠበቅ ችግርም ይታይባቸዋል። እነዚህ መጻሕፍት ሐሰትና ማታለል ትክክል እንደሆኑ ለማመልከት አሳማኝ ምክንያት ለመስጠት ይሞክራሉ፤ ድነትን ለማግኘት በመልካም ሥራ ላይ መመርኮዝ እንደሚገባም ያስተምራሉ። መጽሐፈ ሲራክ እና የሰሎሞን ጥበብ ግብረገባዊነትን እንደ ቀላል ነገር ይመለከቱታል። ጥበብ የተሰኘው መጽሐፍ ዓለም የተፈጠረው ከፍጥረት በፊት በነበሩ ቁሶች እንደ ሆነ ይገልጻል (11:17)። መጽሐፈ ሲራክ ምጽዋትን መስጠት የኃጢአት ስርየትን እንደሚያስገኝ ያስተምራል (3:30)። መጽሐፈ ባሮክ እግዚአብሔር የሙታንን ጸሎት እንደሚሰማ ይናገራል (3:4) በመቃቢያን መጽሐፍም ውስጥ ታሪካዊ እና መልክአ ምድራዊ ስሕተቶች ይስተዋላሉ፤[259] ብለዋል።*

የአዋልድ መጻሕፍት ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ጋር መጋጨት

መጽሐፈ ሲራክ 20: 25 *"ሀሰት ከመናገር መስረቅ ይሻላል ሀሰተኛ ሰው ይጐሳቈላል ፈጽሞም ያፍራል"* ይላል። በ ዘፀ. 20:4-17፤እና በ ዘዳ 5: 6-21)። አሥርቱ ትዕዛዛት የተጠቀሱ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 8ኛው ትዕዛዝ አትስረቅ ይላል። ከሁለት ኃጢአት አንዱ ይሻላል የሚል ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። ታዲያ ሲራክ እግዚአብሔር በቃሉ ያወገዘውን ስርቆትን ይሻላል ማለት እንዴት ቻለ?

መጽሐፈ ሲራክ 24:3፤10 እንዲህ ይላል፦ *"እኔ እግዚአብሔር አብ ተወለድኩ ...በእርሱ ፈቃድ በከበረ ማርያም ማኅፀን ሥጋን ተዋሐድኩ በምኩራብ አስተማርኩ ..."*ይላል። የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ተብሎ

[259] E.J.Young, *The Canon of the Old Testament, In Revelation and the Bible* p.167-168

በተለጣፍነት የገባው የሲራክ መጽሐፍ ስለ ማርያምና ስለ ክርስቶስ የምኩራብ አገልግሎት ከየት አምጥቶ ነው የሚናገረው?

መቃብያን 23: 1-2 *"ቃየል በየዋህነት የተከተለውን ወንድሙን በሴት ቀንቶ ገደለው"* ይላል:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህን በፍጹም አይናገርም:: ዘፍ 4: 3-8 ይመልከቱ::

ሲራክ:- 5:1 *"ገንዘብ በቃኝ አትበል"* ይላል:: ለመሆኑ የሲራክ 1ጢሞ. 6:6፤11 *"ያለኝ ይበቃኛል"* የሚለውንና *"ገንዘብን መውደድ የኃጢአት ሁሉ ሥር ነው"* የተባለውስ?

ኩፋሌ 4: 8-9 *"አዳም በመጀመሪያዪቱ ሰባዔ ተፈጠረ፤ ሄዋን ደግሞ በ2ኛ ሰባዔ ተፈጠረች፤ አዳም በ40ኛው ቀን ወደ ገነት ይገዛትም ይጠብቃትም ዘንድ አስገባነው ሚስቱንም በ80 ቀን አስገባናት"* ይላል:: ይህ የመጽሐፍ ቅዱስን ሐሳብ ሙሉ በሙሉ ይቃወማል::

ኩፋሌ 15: 16 *"መልዓክ ውቃቤ ለበሮ ነገር ይጠብቅሃልና ከሞትና ከክፉ ነገርም ያድንህ ዘንድ መማለጃና እጅ መንሻ አትቀበል"* ይላል:: ሰውን የሚጠብቅ ውቃቤ ነው እንዴ?

በዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ የተጻፈ *"ሥግሣጽና ምክር"* በሚለው መጽሐፋቸው የአዋልድ መጽሐፍ አውራ ስለተባለው መጽሐፈ ሄኖክ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አሳብ እንዲህ ዘግበዋል:- *"የአዋልድ አውራቸው መጽሐፈ ሄኖክ የሚባለው መላዕክት ወደ ምድር ወርደው ሴቶችን እየመረጡ አግብተው እርስ በርሳቸው የሚባልገ ሦስት ሺህ ክንድ የሆነ ቁመታቸው ከነፋስ ጋር የሚሯሯጡ ማለትም ቁመታቸው (አንድ ሺህ አምስት መቶ ሜትር መሆኑን ነው) አንድ ዝሆን በአንደ እጃቸው አንስተው ከፀሐይ አቅርበው ጠብሰው የሚውጡ ወንዶች ልጆችን ወለዱ፤ የተወለዱትም እናት አባቶቻቸውን በሉ፤ እርስ በርሳቸውም ተባሉ፤ ስመ ነገዳቸው አዛኤልና አዛዝኤል ይባሉ ነበር"* ይላል:: (ሄኖክ 2:1-16):: ሄኖክ ግን ከአዳም ፻ኛው ትውልድ ሲሆን ሄኖክ ማቱሳላን፤ ማቱሳላ ላሜህን፤ ላሜህ ኖህን ወለደ:: ከኖህ ዘመን በኋላ ከጥፋት ውሃ የዳኑት የኖህና የልጆቹ ስምንት ቤተሰብ እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጸልናል (ዘፍ. 6: 13-22፤ 7: 1-24፤ 8: 15-22 ይመልከቱ)::

የእነ አዛኤልና ኤዛዝኤል ዘር ግን በዓለም ላይ ስለሌለ የባልቴቶች ተረት የመሰለ ፍጹም ውሸትና የፈጠራ ጽሑፍ ሲሆን ለመጽሐፈ ሄኖክ ጓደኞቸውና ምስክሩ ቁርዓን ወይም ማህዱስ ከሚባለው ዋናው የመሐመዳውያን መጻሕፍት ማላዕክት ወርደው ሚስቶችን አግብተው ሂሩትና ማሩት (አዛኤልና አዛዝኤል) የሚባሉ ረጃጀሞች ሰዎች ወለዱ፤ ይላል::

ስለዚህ የመጽሐፈ ሄኖክም ጽሑፍ ከላይ እንደ ተጠቀሰው የፈጠራ ድርሰት ነው::[260]

ታዲያ የኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ቤዛዊነትን ሥራ የሚጋርዱ እውነት መሳይ ተረት የሚያወሩ፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ ዐቢይ አስተምህሮ ጋር ፊት ለፊት የምላተሙ፤ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በቀደምት የቤተ ክርስቲያን አበው ያልተቆጠሩና ቅቡልነት ያላገኙትን የአዋልድ መጻሕፍትን እንደ እግዚአብሔር ቃል ዛሬ እንዴት እንቀባለን ብለው ፕሮቴስታንቶች ይጠይቃሉ? በአጠቃላይ የብሉይ ኪዳን አዋልድ መጻሕፍት ፕሮቴስታንቶች ያልተቀበሉበትን ምክንያት ሲዘረዝሩ:-

1) *መጻሕፍቱ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጋር በሚመሳሰል መንገድ ሥልጣን ያላቸው ስለመሆናቸው አይናገሩም::*

2) *እነዚህን መጻሕፍት በጻፉት አይሁዳውያን ዘንድ እንደ እግዚአብሔር ቃሎች አይቆጠሩም ነበር፤*

3) *ኢየሱስ ወይም የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች እነዚህን መጻሕፍት እንደ እግዚአብሔር ቃል አልቆጠሯቸውም፡*

4) *ከመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ትምህርተቶች ጋር የሚጣረሱ ትምህርቶችን ስላካተቱ::*[261]

አበው ከዛሬ 500 ዓመት በፊት ስለ መጽሐፍ ቅዱስና ስለ አዋልድ መጻሕፍት ያወጡትን የሃይማኖት መግለጫ ማወቅ ለዛሬ መረዳታችን ትልቅ መሠረት ነው:: በ1643 ዓ.ም በሌንደን ኢንግላንድ በዌስት ሚንስተር ጉባኤ ***"የዌስት ሚንስተር የእምነት መግለጫ"*** *(Westminster Confession of Faith)* አውጥተው ነበር:: ይህን የሃይማኖት መግለጫ የኦርቶዶክስ ፕረስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን እንደ ሃይማኖት መመሪያዋ ትጠቀማለች:: በዚህ የሃይማኖት መግለጫ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ በዚያ ዘመን የነበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ሊቃውንት ሲናገሩ:-

ልናምነውና ልንታዘዘው የሚገባን የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን የተመረኮዘው በማንም ሰው ወይም በቤተ ክርስቲያን ምስክርነት ላይ አይደለም፤ ነገር ግን እውነት በሆነውና በደራሲው በእግዚአብሔር ላይ ነው:: ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ በመሆኑ ሊታመን ይገባዋል(2ጢሞ. 3: 15-16፤ ዮሐ.5:46-47)::[262] *አዲስ የመንፈስ ቅዱስ መገለጥም ሆነ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣ የሰዎች ትምህርት አንዳችም ነገር በቃሉ መጨመር አይቻልም (2ጢሞ.3:15-17፤ ገላ.1: 8-9፤ 2ተሰ.2:2)::*[263] *መጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት ስለተጸፈና በእግዚአብሔር ጥበቃና እንክብካቤ ከስህተት ስለተጠበቀ እውነተኛነቱ የማይጠረጠር ነው (ማቴ. 5: 18፤መዝ 119:89)::* *በሃይማኖተኖም ክርክር ሁሉ ቤተ ክርስቲያን የመጨረሻ*

[260] ግርማ ዘውዴ (1992 ዓ.ም) ፤ ኢ.ትዮጲስ፤ ሁለተኛ መጽሐፍ፤ገጽ 162
[261] ዊይን ግሩደም፤ገጽ 57
[262] ጎይሉ መኮንን(ቄስ፤ተርጓም)(1983 ዓ.ም) እምነታችን (ዌስት ሚነስተር የሃይማኖት መግለጫ)፤ምዕራፍ አንድ ቁ 4 ዋሽንግተን ዲ.ሲ.፤
[263] እምነታችን፤ ምዕራፍ አንድ ቁጥር 6

አቤቱታዋ ማሰሪያ ታደርገዋለች(ኢሳ. 8:20፤ ማቴ. 15.3-6፤ የሐዋ.15:15፤ ሉቃ 16:31)[264] ይላል።

ስለ አዋልድ መጻሕፍት የዌስት ሚንስተር የሃይማኖት መግለጫ፡-

የአዋልድ መጻሕፍት በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፉ ስላይደሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ውስጥ አይገቡም። ስለዚህ በእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምንም ሥልጣን የላቸውም። ተራ የሰዎች ጽሑፎች ከሚኖሯቸው ሥልጣን የተለየ ሥልጣን ተሰጥቷቸውም በሥራ ላይ ሊውሉ አይገባውም (ራእ.22:18-19፤2ጴጥ.1:21)[265] ይላል።

የአበው የቀኖና መለኪያ

የጥንት አባቶች አንድ መጽሐፍ ቀኖናዊ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በሚከተሉት መለኪያዎች እንደተጠቀሙ ይታመናል፡-

1. የመጽሐፉ ቃል ሥልጣን ያለውና ጌታ እንዲህ ይላል የሚል አባባል አቅፎአል ወይ?
2. ትንቢት ነው? ወይስ በእግዚአብሔር ሰው የተጻፈ ነው?
3. የመጽሐፉ ይዘት አስተማማኝና ሐቀኛ ነው ወይ? (አጠራጣሪ ሲሆን ገሸሽ ማለት የአበዎች ስልት ነበር)።
4. ጽሑፉ ልብ የሚነካና መንፈስን የሚቀሰቅስ ነው ወይ? (ሕይወት የመቀየር ኃይል አዝሎአል ወይ?)
5. የቀደሙ የእግዚአብሔር ሰዎች ሲጠቀሙበት ቆይተዋል ወይ?
6. ይዘቱ የእግዚአብሔር ቃልነታቸው ከተረጋገጠላቸው ሌሎች መጻሕፍት ጋር የማይቃረንና የሚስማማ ነው ወይ? የሚሉ ጥያቄዎችን ያልመለሰና መመዘኛውን ያላሟላ መጻሕፍት በመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት መካከል እንደ አንዱ መቆጠር አልቻሉም።

የአዋልድ መጻሕፍት በዚህ መመዘኛ ማለፍ ስላልቻሉ በአበው ተቀባይነት አላገኙም። *የአዋልድ መጻሕፍት በባሕልና በታሪክ ጥናት በኩል የሚረዱ፣ እንዲሁም መንፈሳዊ ምክሮች ቢኖሩበትም፣ በጥንት አይሁድ ዘንድ ሆነ በሐዋርያትም ተቀባይነት ስላልነበራቸው ቀኖናዊ አይደሉም።* ቀኖናዊ ያልሆኑ የአዋልድ መጻሕፍት ለታሪክ ማጣቀሻነትና አንዳንድ መረጃዎችን

[264]እምነታችን፣ ምዕራፍ አንድ ቁጥር 8
[265] እምነታችን፣ ምዕራፍ አንድ ቁ 3

በትክክል ለመረዳት ካልሆነ በስተቀር እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንድንመራበት ሐዋርያት፣ የጥንት የቤተ ክርስቲያን አበውና ታሪክም አይደግፈንም።

በቀኖና ላይ የተካሄዱ ጉባኤዎችና ውሳኔዎቻቸው

በየጊዜውና በየቦታው የተነሡ የክርስትና ሃይማኖት አበዎች ቀኖናዊ የሆኑትን ለይተው ለመወሰን ጉባኤዎች ጠርተው የሚከተሉ ውሳኔዎችን አስተላልፈዋል።

- በ363 ዓ.ም የሎዶቂያ ሲኖዶስ ቀኖናዊነት የሌላቸው መጻሕፍት እንዳይነበቡ አግዶ ነበር።
- የሂፖል ጉባኤ ተብሎ የሚታወቀው በ393 ዓ.ም በአፍሪካ ምድር ተካሄዶ በአሁኑ ጊዜ በእጃችን ያሉ ቀኖናዊነት አላቸው የተባሉ መጻሕፍት ዝርዝር ትቶልናል።
- በ397 ዓ.ም የተሰበሰበው የካርቴጁ ጉባኤም ቀኖናዊነት አላቸው ከተባሉት መጻሕፍት ውጪ ሌላ መጽሐፍ በቤተ ክርስቲያን እንዳይነበብ ከልክሏል።
- ይኸው ጉባኤ እንደገና በ419 ዓ.ም በካርቴጅ ተሰብስቦ ቀኖናዊነት ያላቸውን መጻሕፍት ዝርዝር ለይቶ አረጋግጦአል።

እንግዲህ የአዋልድን መጻሕፍት ላለመቀበል የወሰኑ አብያተ ክርስቲያናት ከላይ የተጠቀሱ የጥንት የእምነት የአበው ትልቅ ውሳኔ በማክበርና የ66 የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ቀኖናዊነት በመረዳት እንደሆነ ይናገራሉ።

2. ድነት በጸጋ ብቻ

"Sola Gratia,"- Salvation by Grace Alone.

"ጸጋው በእምነት አድናአችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም" (ኤፌ 2:8)።

"ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና" (ቲቶ2: 11)።

"ጸጋ" የሚለው ቃል በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ወሳኝ ጥልቅና ሰፊ ጽንሰ አሳብ ያዘለ ቃል ነው። ብዙ ሰዎችም በተሳሳተ መንገድ የሚረዱት ቃል ነው። ጸጋን ከአንደበት ይልቅ ተቀብለን ስንኖርበት እናውቀዋለን። ጸጋን ከኢየሱስ ክርስቶስ ነጥለን ማየት አንችልም። የሚያድን ጸጋ የተገለጠው በኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ሐዋርያው ዮሐንስ በአራተኛው

ወንጌል መግቢያ ላይ ጠቅሶታል *"ሕግ በሙሴ ተሰጥቶን ነበርና ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ"* (ዮሐ.1:17)። ሐዋርያው ጳውሎስ ከዮሐንስ በላይ በጸጋ አስትምህሮ ላይ ልዩ ትኩረት መስጠቱን ስንመለከት የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናትም በጸጋ ላይ የተለየ ትኩረት ቢሰጡ አያስደንቅም። ለጳውሎስ የወንጌል ልብ፦ *"በክርስቶስ ኢየሱስ ስላመናችሁ በተሰጣችሁ የእግዚአብሔር ጸጋ ምክንያት"(1ቆሮ.1:4)።*

እንዲሁም የቆሮንቆስ ቅዱሳንን ሲባርክ ለእያንዳንዳቸው የኢየሱስ ክርስቶስን ጸጋ በመመኘትና በቂ እንደሆነ በማመልከት ነው፦ *የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን። አሜን (2ቆሮ.13:14)።* በኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠው ጸጋና እውነት የኃጢአትን ጉልበት የሰበረ፣ ሞትን የገደለ፣ ሰማይን ከምድር ያስታረቀ፣ ኃጢአተኛውን ያፀደቀ፣ የዘመናትን መልስ የመለሰ ድንቅ ስጦታ ነው። ያለ እግዚአብሔር ፍቅር ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ በፍጹም ማውራትም ሆነ መረዳት እንደማይቻል መታወቅ አለበት። ይህ ፍቅር መወደድ የማይገባ ሰው የተወደደበት ፍቅር(አጋፔ) ያ ሚስጢር ስገባን ኃጢአተኞችን ሁሉ ሊያድን በኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠው ጸጋ ሙሉ በሙሉ ባንረዳውም የጽንሰ ሐሳቡን ፍንጭ በጥቂቱም ቢሆን እንገነዘባለን።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ቅዱሳን በጻፈው መልዕክቱ ከሰው አንደበትና አዕምሮ በላይ የሆነ አቻ የለሽ የአጋፔ ፍቅር ለምን ዓይነት ሰው እንደተገለጠ ሲናገር፦ *ሰለ ጻድቅ ሰው የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና ስለ ቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል (ሮሜ.5:7)።* ለቸርና ለጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ተፈልጎ መገኘቱን ገልጾ ሐዋርያ እጅግ የተደነቀው "ነገር ግን" በማለት ከለየ በኋላ ቀጥሎ ምን እንዳስደነቀው ሲናገር፦ *"ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶልናል እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል"(ሮሜ.5:8)* ብሏል። ይህ ታላቅ የፍቅር ሥራ የተሠራው የእኛ ጾም፣ ፀሎት፣ መልካም ምግባር ፣ ባሕታዊነታችንና ለጽድቅ ያለን ረሃባችን ጫፍ ነክቶ ባለበት ሁኔታ ውስጥ ሳይሆን *"ገና ኃጢአተኞች ሳለን"* ክርስቶስ በፍጹም ለማይገባን ሰዎች ሞተ። እርሱም የዳንንበት የእውነትና ጸጋ ምንጭ ሆኖልናል። ለዚህ ታላቅ የድነት ስጦታ የተገባ እስኪሆን ድረስ አልጠበቀንም ነገር ግን የእኛን ሞት ሞቶ ሙሉ የደም ዋጋ በመክፈል ለዚህ ታላቅ ጸጋ የተገባን አድርጎናል። ስሙ ከዘላለም እስከ ለዘለዓለም የተባረከ ይሁን።

ሐዋርያው እርሱ የጸጋ ምንጭ ሊሆንልን ምን እንዳደረገ ሲገልጽ፦ *"የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቸር ስጦታ አውቃችኋልና ሀብታም ሲሆን እናንተ በእርሱ ደህነት ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሃ ሆነ"* (1ቆሮ.8:9) ብሏል።

ጸጋ ቁሳቁስ ሳይሆን በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ሕያው የፍቅር ግንኙነትን ያመለክታል። ጸጋ ማለት ገና ኃጢአተኞች ሆነን ጥፋት ስገባን የተገላብጦሽ የዘላለም ድነትና ብፅዕና በነፃ መቀበላችንን ያመለክታል። አንድ ፖፒዮ የተባለ የካቶሊክ ጸሐፊ የጸጋን አስደናቂነትና ከሰው አዕምሮ በላይ መሆን እንዲህ በማለት ገልጿል፦ *"በቀኝ ይመጣል ብላችሁ ሲትጠብቁ በግራ ያገኛችኋል፤ በግራ ይመጣል ብላችሁ ሲትጠብቁ በቀኝ ታገኙታላችሁ።"* ጸጋ ከጠላነው፣ ካመጽንበት፣ ከጎዳነው፣ ከበደልነውና ከራቅነው አምላክ የተሰጠን የማይገባን ከዘላለም ሞትና ኩነኔ ያዳነን ኃይል ነው። ጸጋ በክርስቶስ ሥራ የተሰጠን የማይገባን ስጦታ ስለሆነ ትህትና፣ አክብሮት፣ ፍቅር፣ ምስጋናና ልባዊ አምልኮ እንዲሁም በተሰበረ ልብ ማገልገል እንጂ ከራሳችን የሆነ አንዳች እንደሌለን ማወቅ አለብን። ፕሮቴስታንቶች ከዚህ የተነሣ ነገረ ጸጋ የተሐድሶና የፕሮቴስታንትዝም እንቅስቃሴ መሠረት ነው፤ ብለው ያምናሉ፤ ያስተምራሉ።

በክርስቶስ ኢየሱስ የተቀበልነው ጸጋ በዚህች ምድር ላይ ስንኖር በሥጋችን ማድረግ የማንችላቸውንና ከአቅማችን በላይ የሆኑ ነገሮችን የማከናወን ብቃትና ኃይል እንደሚሰጠን ጳውሎስ "ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም"(2ቆሮ.15:10) በማለት ተናግሯል። የክርስቶስ ጸጋ ከእግዚአብሔር የዘላለም ቁጣና የዘላለም ሞት አንዱ መዳኛ ሳይሆን ብቸኛ መዳኛ ነው። የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በአማኝ ሕይወት በመሥራት ከኃጢአት እሥራት ነፃ ያደርገናል፤ ከመንፈሳዊ ሞት ወደ ሕይወት ያሻግረናል።

3. ድነት በእምነት ብቻ

"Sola Fide," Salvation by Faith Alone

ለጸጋ ያለን ምላሽ እምነት ነው። እምነት እጅግ ቀላል የሚመስል ከባድ ነገር ነው። እምነትን ከባድ ያደረገው ለማመን አስቸጋሪ የሆነውን ነገር እንድናምን እኛን መጠየቁ ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ 150 ጊዜ ኃጢአተኛ ድነት የሚያገኘው በእምነት ብቻ እንደ ሆነ ተገልጾአል። የሰውን ነፍስ ማዳን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ሲሆን ይህን እውን የሚያደርገው ሰዎች በልጁ የመስቀል ሥራ ሲያምኑ ብቻ ነው። እምነት ሥራ ሳይሆን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ሙሉ በሙሉ መደገፍ ማለት ነው።

በሮማን ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ድነት ሂዴት ነው። ድነት በኢየሱስ ክርስቶስ ባለን እምነት፣ በሥራና ቅዱስ ሚስጢራትን በመፈጸም እንደሚገኝ ያምናሉ።[266] እምነትና ሥራም ለድነት አስፈላጊነታቸው ላይ ያሰምራሉ። ማርቲን ሉተር ሲናገር፦ *እምነትና ሥራ እንደ እሳትና ሙቀት የማይለያዩ ቢሆኑም ለነፍስ ድነት በክርስቶስ እናምናለን እንጂ ለመዳን መልካም ሥራ*

[266] J.D. Christian, *Christian Celebration: The Sacraments* p65

አንሠራም። እምነትና ሥራ አንድ ባይሆኑም በፍጹም ማለያየት አይቻልም፤ መልካም ሥራ እምነታችንን የማይከተል ከሆነ የሚያድን እምነት እንደሌለን ያመለክታል። የዳንነው በእምነት ብቻ ነው፤ ነገር ግን ብቻውን በሆነ እምነት ግን አይደለም። ያለ ሥራ እምነት ሙት ነውና (ያዕ.2:17-20)። እንደዚሁም ሥራ የእምነት ውጤት እንጂ እምነት የሥራ ውጤት አይደለም። መልካም ሥራ የመዳናችን መሠረት ሳይሆን ማስረጃ ነው(ኤፌ.2:10)። መልካም ሥራ የመዳናችን ምልክት እንጂ ምክንያት አይደለም። ስለዚህ ለመዳን እናምናለን እንጂ አንሠራም፤ ብሏል።

ድነት ነፃ ስጦታ ነው። ድነት በጸምና ፀሎት፣ ለነዳያን በመመጽወት፣ በባሕታዊነት፣ ራስን በማጉሳቆል፣ በመገርጣትና በመራብ፣ በተዝካር ድግስ፣ አማላጆችና ቅዱሳን በተባሉ ልዩ ሰዎች መካከለኛነት፣ በቤተ ክርስቲያን አባልነት ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ሥራ በማመን ብቻ ይገኛል። ከኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ውጭ ሌላ የድነት መንገድ እንዳለ በሊቀ ጳጳስ፣ በጳጳስ፣ በካህን፣ በሐዋርያ፣ በነቢይ፣ በመጋቢ በወንጌላዊ ወይም በሊቀ መላዕክት እንኳ ቢሰበክ ለእርግማን የሚዳርግ *"ሌላ ወንጌል"* (ገላ.1:8-9) ነው። የሐሰት ወንጌል ስብከት ውግዝና ለእርግማን(*Anathema* አናቴማ)[267] የሚዳርግ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም ጥንትም ሆነ ዛሬ ብዙ ሰባኪዎች ይህን የዘላለም ጥፋት መንገድ መምረጣቸው እጅግ ያሳዝናል። በተለይ በዘመናችን። በዓለማችን ያሉት አብዛኛው ሃይማኖቶች የመጨረሻ ፍርድ እንዳለ አምነው ከዚያ ፍርድ ለማምለጥ ዛሬ እርግጠኛ መሆን እንዳማይቻል ያስተምራሉ። አንዳንድ በቃሉ እናምናለን የሚሉት አብያተ ክርስቲያናትም ሳይቀሩ ስለድነታቸው እርግጠኞች አይደሉም። ፕሮቴስታንቶች ግን በተገለጠው ቃሉ ላይ ቆመው፣ በኢየሱስ ክርስቶስ የቤዛነት ሥራ ለኃጢአት ሥርየት በቂ መሆኑን በእምነት በመቀበል ስለመዳን በእምነት እርግጠኛ መሆን ይቻላል ብለው በቃሉ ያምናሉ፣ የቃሉንም እውነት በእምነት ይሰብካሉ። በክርስቶስ ሥራ ያለን እምነታችን ለድነታችን መያዣ ነው። ድነትን በእምነት መቀበል የክርስትና ጉዞ የመጀመሪያ እርምጃ ነው። የምንኖረው በእምነት፣ ሕይወትን ከእግዚአብሔር የተቀበልነው በእምነት፣ የእግዚአብሔር ልጆች የሆነው በእምነት፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚንወርሰው በእምነት፣ እንዲሁም ዓለምን የምናሸንፈው በእምነት ነው።

እምነት ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ ቃሉ መልስ አለው፡- *"እምነት ተስፋ ስለሚናደርገው ነገር የሚያስረግጠን የማናየውንም ነገር የሚያስረዳን ነው"* (ዕብ.11:1)።

[267] *"ዎተረገመ ይሁን"* የሚለው ሐረግ በግሪክ *"አናቴማ"* የሚል ሲሆን ቀደሚ ሲል ቃሉ በቤተ ጣዖት ስለትን ለመፈጸም የሚሰጠውን ክፉያ ለማመልከት ነበር። በኋላ ግን ቃሉ ርግማንን ለማሳየት በግሪኩ ዓለም ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው። (1ቆሮ.12:3፤ 16:22፤ ሮሜ. 9:3)። የዚህ ቃል ጠንካራ ትርጉም በሐዋርያ 23: 14 ላይ ተገልጾአል። John F.Walvoord, Ray B Zuck (1984), *The Bible Knowledge Commentary Vactoor*, Books Division of Sp Publications Inc p590

በዚህ ክፍል ስለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት የሚያስረዱን ሁለት ቁልፍ ቃሎች *"ማስረገጥ"*ና *"ማስረዳት"* የሚሉት ናቸው። ማስረገጥ ማለት፡- *"ምርኩዝ መሆን"* *"መደገፍ"* ማለት ነው። እምነት ለድነታችን እንደ ጠንካራ ምርኩዝ በክርስቶስ እንድንደገፍ ይረዳናል። ስለ እርግጠኛ እንድንሆን ያደርገናል። ሁለተኛው ቃል *"ማስረዳት"* የሚል ሲሆን ይህም እምነት አንድ ግልጽ ያልሆነውን ነገር የመረዳት አቅም እንደሚሰጠን ያመለክታል። አንድ ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ የቤዛነት ሥራ ሲያምን ለድነቱ እርግጠኛ ይሆን ዘንድ እምነት ውስጣዊ መረዳትን ያጎናጽፈዋል። የሌለ ሰው መኖር እንደማይጀምር ሁሉ ክርስቶስን በእምነት ተቀብሎ በመንፈሳዊ ሕይወት አዲስ ሆኖ ያልተወለደ ሰው የክርስትናን ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በመመላለስና ክርስቲያን በመባል መኖር አይጀምርም። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ሲናገር፡- *"በተስፋ ድነናልና"* (ሮሜ.8:24) ይላል።

የድነት እምነት ምንጩ በልባችን በተዘራው የቃሉን እውነት በማመን እግዚአብሔር በልጁ በኩል የሰጠንን የዘላለምን ሕይወት (ዮሐ.17:3) የምንቀበልበት ሂደት ያመለክታል። ክርስቶስ በቃሉ ሲናገር በእኔ የሚያምን ቢኖር ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል (ዮሐ.11:26) ብሎ እንደተናገረው እርሱ በሠራልን የቤዛነት ሥራ አምነን ከተቀበልን እርሱ እንደ ተናገረው ብንሞት እንኳ ሕያዋን ነን። ኃጢአት ያላወቀ ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ባለን እምነት እኛን በመቀበል የራሱን ጽድቅ አልብሶን የእግዚአብሔር መንግሥት ተካፋዮች እንዳደረገን ያወቅነው በእምነት ነው። አንድ ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል በተገኘው ጸጋ በማመን ብቻ ይድናል።

"በእርሱ <u>የሚያምን</u> ሁሉ የዘላለም <u>ሕይወት አንዲኖረው እንጂ አንዳይጠፋ</u> እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲህ ወዶአልና" (ዮሐ.3:16)። *"በጌታ* በኢየሱስ ክርስቶስ <u>እመን</u> አንተና ቤተሰቦችህ <u>ትድናላቸሁ</u>"* (ሐዋ. 16: 31)። ለመዳን ከማመን ውጭ ምንም የምንሠራው ሥራ የለም፤ ስለዳንን ግን መልካም ሥራን ሁሉ እንሠራለን። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ጥሩ ሥራ መሥራት ሳይሆን በልጁ የመስቀል ሥራ አምነን ኃጢአታችን በደሙ በእምነት መታጠብ የግድ ይላል። ጥሩ ሥራ የድነት ውጤት እንጂ የድነት መግባ አይደለም። ድነትን በእምነት እንቀበላለን እንጂ ድነታችንን አንሠራውም፤ በእምነት መዳን ማለት ስለ እኛ ኃጢአትና መተላለፍ በመስቀል ላይ ክርስቶስ ኢየሱስ የከፈለው ዋጋ በቂ እንደሆነ በእምነት መቀበል ማለት ነው። ከዚህ የተነሣ የፐሮቴስታንት አበው ድነት በመልካም ምግባር፣ በሌሎች ፀሎት፣ በመመጽወት፣ በመመነን፣ በገንዘብ፣ ከልዩ ዘር በመወለድና በሃይማኖት ሳይሆን ድነት የኢየሱስ ክርስቶስን የቤዛነት ሥራን በእምነት ብቻ በመቀበል እንደ ሆነ በቃሉ እውነት ላይ ቆመው ያውጃሉ።

4. ድነት በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ

"Solus Christus," In Christ Alone:

ሊቀ ጉባኤ አባ አበራ በቀለ ስለ ኢየሱስ ብቸኛ አዳኝነት ሲናገሩ፡-

> *"እውነተኛዋና ትክክለኛዋ የዘላለም ሕይወትን የምታሰጥዋ ሃይማኖት የትኛዋ ናት? በማለት እንደገና እንጠይቃለን:: መልሱም በ(ዮሐ.3:16) መሠረት ለእኛ ድኅንነት ከእግዚአብሔር ዘንድ በመጣው በባሕርይ ልጁ ላይ ያለን ሃይማኖትና አምነት ብቻ ነው:: ምናልባት መስሎንም ሳይመስለንም ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት አምነታችንንና ትውክልታችንን(መታመናችንን)፣ ፍቅራችንንና አምልኮአችንን ከእርሱ ውጭ በሌላ ነገር ላይ አድርገነው እንደሆነ የመዳን ተስፋ የለንም:: ምክንያቱም ማዳን የእግዚአብሔርና የበጉ ነው ተብሎ ተጽፏልና(ራእ.7:10):: ሕዝብንም አሕዛብንም በደሙ የዋጀ የእግዚአብሔር በግ ነውና(ራእ.5:8-10)::"*[268] ብለዋል::

"በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም" (ሮሜ 8:1):: ኃጢአት የሌለበት ፍጹም ጻድቅና ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰው ልጆች ሁሉ ምትክ መሞቱና መነሣቱ ከአብ ጋር መታረቅ ሆኖልናል:: ስለ ክርስቶስ ሞት ቃሉ ሲገልጽ "አንታይ" የሚል የግሪክኛ መስተዋድድ "ምትክ" "ፈንታ" የሚል ቃል ይወክላል:: ምትክ ለሚለው ቃል ጥሩ ምሳሌ የሚሆን ቃል የሚገኘው ደግሞ በፊልሞና 13 ላይ ነው:: (ማቴ. 20:28 ማር 10:45) ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱ ለብዙሃች ቤዛ እንደ ሆነ ተናግሯል:: ስለዚህ ድነት በእርሱ ብቻ ነው::

ከኃጢአታችን በደሙ ስለዋጀን(ራእ.5:9) እርሱ ብቸኛ አዳኝ ነው፤ በደሙም ስለዋጀን (ስለተገዛን) በሥጋችን እርሱን ማክበር እንዳለብን ቃሉ ይነግረናል (1ቆሮ.6: 19-20):: እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ የመዳናችንን ምክንያት ሲያስረዳ:- *"እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ ለሕግም በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ"* (ገላ.4:5)::

በሞቱ ዓለምን ከአብ ጋር ስላስታረቀን ኢየሱስ ብቸኛ አዳኝ ነው (2ቆሮ.5:19):: ማስታረቅ ማለት መለወጥ፣ ማገናኘት፣ የተበላሸውን ግንኙነት ማደስና ተራርቀው የነበሩትን ማቀራረብ ማለት ነው:: ክርስቶስ ብቸኛ አዳኛችን ስንል ይህን በሰማይና በምድር በብቸኝነት በደሙ የሠራው እርሱ ብቻ ስለሆነ ነው:: በበደላችን ከአብ ጋር ተጣልተን የሞትና የቁጣ ልጆች የነበርነውን በሞቱ ወደ ልጅነት ክብር መልሶን የፍቅር ልጆች ያደረገን ኢየሱስ ነው:: ክርስቶስ ከአባቱ ጋር ያስታረቀው ዓለምን ሲሆን በእምነት ስለተቀበልነው ለእኛ አድኖን የልጅነት ሥልጣን ደግሞ ሰጥቶናል (ሮሜ.5:11)::

[268] አበራ በቀለ(ሊቀ ጉባኤ አባ) (1996 ዓ.ም) *ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ምግባር*፣ አዲስ አበባ ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ ገጽ 293

ኢየሱስ ክርስቶስ ማስተሰሪያ ስለሰጠን ብቸኛ አዳኝ ነው:: ማስተሰሪያ /propitiation/ ፕሮፒሺኤሽን/ ማለት አምላክን ማርካት ወይም ቁጣን ማብረድ ማለት ሲሆን ቅዱስና ጻድቅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ የኃጢአት ቅጣት በራሱ ላይ በመውሰድ የአባቱን ልብ በማርካት በእኛ ላይ የነበረውን የዘላለም ቁጣ በሞቱ አብርዷል::

ስለዚህ እርሱ ብቸኛ የዓለም አዳኝ ነው (ማር.3:29፣ 14:21):: ይህም በእኛ ጉዳይ ብቸኛ ጣልቃ ገብነቱን ያሳያል (ሮሜ.1:18፤ ኤፌ 5:6):: እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ የቤዛነት ሥራው ስለረካ በእርሱ የሚመጡትን ሁሉ ለማዳን ፈቃዱ ሆኗል:: ስለዚህ ለድነት ወደ የትም፣ ወደ ማንም መሄድ እንደሌለብን እርሱ ራሱ ሲናገር "በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም" (ዮሐ.14:6) ብሎ አቻ የለሽ መሆኑን አስረግጦ የዘጋ ሲሆን ሐዋርያ ጴጥሮስም *"መዳን በማንም በሌላ የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና"(የሐዋ.4:12)* በማለት ኢየሱስ ብቸኛ አዳኝነቱን ገልጦ ከሰማይ በታችን አንዳች የሚያድን ከእርሱ በቀር እንደሌለ በመንፈሱ የተገለጠለትን እውነት በገሃድ መስክሯል:: **ክርስቶስ ብቸኛ የድነት ራስ ስለሆነ በእርሱ በማመናችን**

- መንፈሳዊ ልደት (ዮሐ. 3:5)
- ልጅነት (ገላ. 4:5)
- የሰማይ ዘግነት (ፊልጵ. 3:20
- በንጉሣዊው ክህነትና (1ጴጥ.2:5) የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባልነት (ኤፌ.2:19)
- በበጉ ሠርግ መታደም (ራእይ 19:7) ሆኖልናል::

ክርስቶስ ለሰው ልጆች ኃጢአት እንደ ሞተና እንደተነሣ፣ በእርሱ የኃጢአት ዋጋ ሙሉ በሙሉ እንደተከፈለና በእርሱ ሥራ ብቻ በማመን ድነት እንደተቀበልን በገሃድ የማይሰበክባቸው መድረኮች የሌላ እንጂ የወንጌል መድረኮች አይደሉም:: ሰውን ከአምላክ ጋር፣ ሰውን ከሰው ጋር፣ ሰውን ከራሱ ጋር እንዲሁም ፍጥረተ ዓለሙን ከአብ ጋር በሞቱ ያስታረቀውና የሰዎች ልጆች ቤዛ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: *"ልጁ ያለው ሕይወት አለው የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም"* (1ዮሐ.5:12):: በዩኒን ቲኦሎጂካል ሴሚኔሪ የስልታዊ ነገረ መለኮት ፕሮፌሰር የሆኑት ሮበርት ማካፍ *"የፖፖቴስታኒቲዝም መንፈስ"* በሚለው መጽሐፋቸው:-

> *መጻሕፍት የክርስቶስ የመገኛ ቤት እንጂ ክርስቶስ አይደሉም:: የመጻሕፍት ትልቁ ሥራ ስለ ክርስቶስ መመስከር ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ የመጻሕፍት ንጉሥና ጌታ ነው:: ስለዚህ እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጽ ኢየሱስን የመግለጥ ግዴታ አለባቸው::*[269] ብለዋል:: ፕሮፌሰሩ ማርቲን ሉተርን ዋቢ በመጥቀስ ሲቀጥሉ:- *መጻሕፍት ሁሉ ስለ ክርስቶስ ያውጃሉ፤ ሐዋርያው ጳውሎስም ከክርስቶስ በስተቀር ሌላ ዕውቀት እንደሌለው ተናግሯል፤ ኢየሱስን የማይገልጥ የትኛውም ትምህርት ጴጥሮስም ሆነ ጳውሎስ እንኳ*

[269] Robert McAfee Brown (*1961*), *The Sprit of Protestantism*, New York Oxford University Press, p.74

፱

የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ትሩፋቶች

የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ያልተጠበቀና ያልተገመተ ሁለንተናዊ ለውጥና ዕድገት በዓለም የመምጣት ምክንያት ሆኗል። ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ካሉት አገሮች አንዷ እንደመሆኗ መጠን የለውጡ ተቋዳሽ ናት። ብዙዎች ደማቸውን ያፈሰሱለት፣ አጥንታቸው ከመቃብር ወጥቶ ተቃጥሎ አመዱ በወራጅ ውሃ ላይ የተበተነበት፣ ብዙዎች በጸሎት ያስቀሱለት፣ ብዙዎች መቼ ይሆናል ብለው ለማየት ጓጉተው በዘመናቸው ለማየት ያልቻሉት የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ዓለም አቀፋዊ ለውጥ አስከትሎ መጣ። የፕሮቴስታንት ተሐድሶ በእግዚአብሔር ጊዜ፣ ማርቲን ሉተር በተባለው የጀርመን ዜጋ በሆነው አንድ የካቶሊክ ባሕታዊ እውን መሆኑ ለዓለም ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ፣ ለሳይንስና ለምርምር፣ ለእንዱስትሪው አብዮት ሕዳሴ በር ከፋች እንደሆነ የታሪክ ምሁራን ይጠቅሳሉ። የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ትሩፋቶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

ቢሰብኩት ሐዋርያዊ አይደለም። ደግሞም ይሁዳ፣ ጲላጦስም ሆነ ሄሮድስ ኢየሱስን ከሰበኩት መልዕክታቸው ሐዋርያዊ ነው[270] ብለዋል።

በማለት የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረትና ምሰሶ የሆነ መልዕክት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነና እርሱን የማይሰብክና የማይገልጥ የትኛውም ሃይማኖት ሆነ ሥርዓት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንዳልሆነ ይናገራሉ። ድነት በኢየሱስ ብቻ ነው። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛ መልዕክት ሲሆን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንም ይህን እውነት ብቻ እንድትሰብክ በእርሱ ተመሥርታለች። ከዚህ የተለየ በምንም የትም ይሰበክ ኑፋቄ ነው።

5. ለእግዚአብሔር ክብር ብቻ

"Soli Deo Gloria," For the Glory of God Alone

የዳንነው በእግዚአብሔር ኃይል ለእግዚአብሔር ክብር ብቻ እንደሆነ በማወቅ በእርሱ ፊት በእውነተኛ ቅድስናና አምልኮ መኖር ይገባናል። በእግዚብሔር ፊት፣ በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር ለእግዚአብሔር ክብር ብቻ መኖር አለብን። አሜን። ከላይ የተዘረዘሩ "አምስቱ ብቻዎች" የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ቁልፍ አስተምህሮዎች */Fundamental Doctrines/* የመመዘኛ ነጥቦች ሲሆኑ ዛሬም እውነተኛ ወንጌል ለምትሰብከውና ለተሐድሶ ለምትነሣው የአገራችን ቤተ ክርስቲያን አማራጭ ሐሳቦች ሳይሆኑ ብቸኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ናቸው።

[270] Robert McAfee Brown, . *Works of Martin Luther.* Vol. VI.p. 478

ተሐድሶ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ቃሉ ብርሃን መልሷታል

ከተሐድሶ በፊት የነበረችው ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ የሌለባት ነበረች። መጽሐፍ ቅዱስ የሌለባት ቤተ ክርስቲያን ማለት ሞተር እንደሌለው መኪና፣ ዘይት እንደሌለው ቀንዲል፣ መሠረት እንደሌለው ቤት ማለት ነው። በዘመኑ የነበሩ ካህናት መሥዋዕት ከማቅረብ፣ የተወሰነ ቃላትና ሥርዓት ከመደጋገም፣ በሌሎች በማይታወቅ በላቲን ቋንቋ ከመጸለይና አንዳንድ መዝሙሮችን፤ በዚያው ቋንቋ ከመዘመር፣ የሞቱ ሰዎችን ከማቆያ ቦታ /purgatory/ ወደ ገነት ለማሻገር ገንዘብ ከመሰብሰብ ያለፈ ነፍስን ከአምላክ ጋር የሚያገናኝ የወንጌል ስብከት በፍጹም አልነበራቸውም ማለት ይቻላል። በቃሉ እውነት ላይ በመቆሙ በ1551 ዓ.ም በንግሥት ሜሪ ትዕዛዝ ከሌሎች ቅዱሳን ጋር በእሳት እንዲቃጠል የተፈረደበት ጳጳስ ሁፐር ሲናገሩ፡- በ331 ካህናት ላይ ባደረጉት ጥናት 168ቱ ብቻ አሥርቱን ትዕዛዛት መድገም ችለዋል፤ 40 ካህናት አሥርቱን ትዕዛዛት በመጽሐፍ ቅዱስ በየትኛው መጽሐፍ እንደሚገኝ አያውቁም፤ ከ40 ካህናት 31 የጌታችን ጸሎት ደራሲ ማን እንደሆነ አያውቁም ነበር። በማለት የመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃል የሌላቸው ሰባኪዎች የበዙባት እንደነበረች አመልክተዋል።

ቃል ከካህን ከጠፋ ሕዝቡ ቃል ከየት ያምጣ? በአጠቃላይ ከተሐድሶ በፊት ሃይማኖት ያለ እውቀት፣ ሃይማኖት ያለ እምነት፣ ሃይማኖት ያለ ሕያው ተስፋ፣ ሃይማኖት ያለ ክርስቶስና መንፈስ፣ ድነትን የማያስገኝ ባዶ የትውፊት ስብከት፣ የክርስቶስ ቃል ጠፍቶ የሮማው ጳጳስ ቃል የገነነበት፣ ለሥዕል የሚደረግ ስግደትና ወደ ቅዱሳን የሚደረግ ጸሎት የደራበት፣ ሰዎች ለካህናት በሰጡት ገንዘብ መጠን ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት እርግጠኛ የሆነበት የጨለማ ዘመን ነበር። ከላይ የተመለከትናቸው የጨለማ ዘሮች የእግዚአብሔር ቃል ከቤተ ክርስቲያን የመታጣቱ ውጤቶች ሲሆኑ በቤተ ክርስቲያን የመጣው ተሐድሶ የቃሉ ብርሃን በጨለማው ላይ እንዲያበራ በር ከፍቷል።

> *ከተሐድሶ ውጤቶች ጥቂቶቹ የቤተ ክርስቲያን እውነተኛ በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ላይ መመሥረትና እያንዳንዱ አማኝ ከቃሉ ጋር በቀጥታ ተገናኝቶ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅና ሕሊውናውን በእግዚአብሔር ቃል መግዛት መቻሉ ናቸው።*[86] ሔገል ጀርጅ

እ.ኤ.አ ማርች 6 ቀን 1519 ቤተሰቦች በአውሮፓ ልጆቻቸውን አሥርቱን ትዕዛዛት፣ የጌታን ፀሎት፣ የሐዋርያት የእምነት መግለጫ በእንግሊዘኛ በማስተማራቸው ብቻ በእሳት ተቃጥለዋል። ይህም ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን በራሳቸው ቋንቋ ማንበብና ማስተማር መጀመራቸው ምን ያህል በዘመኑ

[86] Hegel, GeorgWilhelm Friedrich (1944), The Philosophy of History, New York: Willey,. p.417

የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን እንዳስቆጣት ያሳየናል። እግዚአብሔር ልጁን የላከው ለአዳም ዘር ቋንቋና ብሔር ሳይለይ ለሁሉም ሰው ነው። በአገራችንም በ1880 ዓ.ም አካባቢ በአጼ ዮሐንስ ዘመን፡-

> *የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ካለበት ቦታ ተሰብስቦ በመንግሥት ባለሥልጣኖች ትዕዛዝ እንደተቃጠለና*[87] *በቤተ ክርስቲያንም አካባቢ በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንዲሰጥ ይፈልጉ የነበሩ አስተማሪዎችና ምዕመናን "ፀረ ማርያሞች" በሚል ክስ ንብረታቸውን እንደተዘረፉ በእሥራት፣በግርፋትና በስደት እንደተቀጡ ታሪክ ይናገራል።*[88]

በዚያን ዘመን የነበረውን ስደት በማስመልከት አንድ ጸሐፊ ልጃቸው የአማርኛውን ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ሲያነብ ያዩት አንድ የአቢሲንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቄስ ከእጁ ነጥቀው ጭቃ ውስጥ ቢጥሉበት ልጁ "ይህ እኮ የእግዚአብሔር ቃል ነው" ባለው ጊዜ፡-

> *ስዳዊት (በግዕዝ ትርጓሜ የነበረ የዳዊት መዝሙራት መጽሐፍ) በቀር የእግዚአብሔር ቃል የለም ብለው መጽሐፉን ረግጠው ከጭቃ ቀላቀሉት... ይህ ታሪክ ብዙ ኦርቶዶክሳውያን የታተመ ቅዱሳት መጻሕፍት ከአባቶቻቸው ለወረሱት የክርስትና ቅርስ ባዕድ ሆነው ስለታዩአቸው ሊቀበሉአቸው እንዳልቻሉ ያመልክታል። የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ብራና ላይ በእጅ የተጻፉ ብቻ ነበሩ። ስለዚህ በወረቀት ላይ የታተመ መጽሐፍ ሁሉ የመናፍቅ ሥራ እንደሆነ ይቆጠር ነበር*[89] ብሎ አትቶአል።

ዛሬ ደግሞ *"የእናንተ መጽሐፍ ቅዱስ ሌላ ነው"* በማለት የመጽሐፍ ቅዱስ ስም ገና ሲጠራ የሚፈረጥጡ ክርስቲያን ተብዬዎች በአገራችን ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስን ከፍቶ የቃሉን እንጀራ ራስን ችሎ ለመመገብ፣ እውነቱን ለማወቅና የተረዳውን በቃሉ እውነት ላይ ከሌሎች ጋር መነጋገርን እንደ ድፍረት የሚቆጥሩ፣ በቤታቸው ያለውን መጽሐፍ ቅዱስ በእጅ የማይነኩና ሌላውን መጽሐፍ ግን ጠዋት ማታ የሚደጋግሙ "ክርስቲያኖችን" ቁጥር መገመት አይቻልም። በክርስቶስ ያለን እምነት እንጂ ስመ ክርስትና አያድነንም። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የትኛውንም መጻሕፍት ማነብነብ ምናልባት ክርስቲያን ቢያስብለን እንጂ እውነተኛ ክርስቲያን ሊያደርገን በፍጹም አይችልም። የእግዚአብሔር ቃል በእውነት የማይሰበክባት "ቤተ ክርስቲያንም" የክርስቶስ አካል መባል እንጂ መሆን በፍጹም አትችልም። ክርስትና ሕይወት እንጂ ስም አይደለም። ያን መለኮታዊ ሕይወት የምንረዳው ከቃሉ ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ቃል በማይታወቅበት ሚዳ የአባቶች፣ ተረት፣ ከቃሉ ጋር የሚጋጭ ትውፊቶች፣ ድርሳናትና ገድላት ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል ይመስሉናል።

[87] *R.Pankhurst (1962), "The Foundation of Education, Printing Newspapare, book production, Libraries and Literacy in Ethiopia", Ethiopia observer, vol. 6, No.3 p.248*

[88] *Aren, Evanglical Pioneers,pp. 177-180*

[89] *ከራሚ ዶናልድ 1972 ገጽ 31*

አ.ሔ.አ በ1905 ስናሲሞስ ነሲብ /ስባ ገመቺስ/ በኦሮምኛ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስን ተርጉሞ ሕዝቡን በቋንቋው በማስተማሩ በነቀምት የነበረ ካህናት አድማ በመቃወም በአርጆ አውራጃ ገዢ ለነበረው ገብረ እግዚአብሔር በደብዳቤ ያቀረቡት ክስ "መጽሐፍ ቅዱስን ስተራ ሕዝብ መስጠት ትልቅ ጥፋት ሲያመጣ ይችላል።" [90] የሚል እንደነበር ታሪክ ይናገራል።

አንድ ሊታወቅ የሚገባ ነገር ዘመን ዘለቅ ለሆነው እውነት የእግዚአብሔር ቋንቋ የተባለ ልዩ ቋንቋ በዓለም ላይ አለመኖሩ ሲሆን በሌላ ጽንፍ ደግሞ አንዳንድ ሰዎች ቋንቋቸውን የእግዚአበሔር ቋንቋ እንደሆነ መረጃ በሌለው እውነት ለማስረዳት መታገላቸው ያስደንቃል። መንፈሳዊ ነገር በዚህ ቋንቋ ብቻ ይገለጣል ከዚህ ቋንቋ ውጪ ያለው ቋንቋና ጽሑፍ ሁሉ እርኩስ ነው። ከዚህ ቋንቋ ውጭ የእግዚአብሔርን አሳብ ለመግለጥ የትኛውም ቋንቋ ብቁ አይደለም የሚለው "መንፈስ" በ21ኛው ክፍለ ዘመን በአንዳንዶች ዘንድ ቢኖርም ምንጩ በመካከለኛው ዘመን የነበረችው የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነ መዘንጋት የለበትም።

ዊልያም ቴንድል የተባለው እንግሊዛዊ ምሁርና ታላቅ የእምነት ሰው ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ እንግሊዘኛ በመተርጎሙ ብቻ እንደ ትልቅ የስህተት አስተማሪና ወንጀለኛ ተቆጥሮ አንድ ዓመት ከታሠረ በኋላ እ.ኤ.አ በ1536 በእንጨት አሥረው አቃጥለውታል። ዊሊያም በእንጨት ላይ ታስሮ ሲቃጠል ለመጨረሻ ጊዜ ድምፁን ከፍ አድርጎ *"እግዚአብሔር ሆይ የእንግሊዝን ንጉሥ ዓይን ክፈት"* [91] ብሎ ነፍሱን እንደሰጠ ተጽፎአል። ዊሊያም ከተቃጠለ ከ75 ዓመት በኋላ ማለትም በ1611 በእንግሊዝ ንጉሥ ጀምስ ትዕዛዝ በሃምሳ አራት ምሁራን የተተረጎመውና እስከ ዛሬ ተወዳጅ የሆነው ኪንግ ጀምስ/King James Version/ የሚባለው የእንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም መሠረት ያደረገው በዊሊያም ተንድል ትርጉም ላይ ነው።[92] እግዚአብሔር የዊልያም ቴንድልን ጸሎት ሰምቶ መልሶአል።

ዛሬ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ /ስልሳ ስድስቱ መጽሐፍ/ በዓለም ላይ በ450 ቋንቋዎች አዲስ ኪዳን ብቻውን ደግሞ ከ2000 በላይ ቋንቋዎች ተተርጉሟል። እንደ ጎርደን ኮርንዌል ሴሚናሪ ጥናት በየዓመቱ 83,000,000 /ሰማንያ ሦስት ሚሊዮን/ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮፒ ታትሞ በዓለም ላይ ይሠራጫል። መጽሐፍ ቅዱስ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች መተርጎሙ መጽሐፍ ቅዱስ የጳጳሳትና የካህናት መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን የሕዝቦች መጽሐፍ እንዲሆን አድርጎታል። ይህ የተሐድሶ ሕያው ውጤት ነው። ያለ ተሐድሶ ወደ አማርኛ፣ ወደ ኦሮምኛ፣ ወደ ትግሪኛ፣ ወደ ቡርጂኛ፣ ወደ ኮንሰኛ፣ ወደ ሱማልኛ...ወዘተ የተተረጎመ መጽሐፍ ቅዱስ ዛሬ ለማንበብ ዕድል

[90] Ibid, Gustav Aren, pioneers,p.425

[91] *John Foxe(1570) , Actes and Monuments , VIII.1229*

[92] *http: en.wikipedia.org wiki William_Tyndale*

አይኖረንም ነበር። ያለ ፕሮቴስታንት ተሐድሶ መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ቋንቋ አይተርጎምም፤ መጽሐፍ ቅዱስ ካልተተረጎመ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የድነት ዕውቀት ለዓለም ባዕድ በሆነ ነበር። በቋንቋችን መጽሐፍ ቅዱስ ተተርጉሞ እንኳ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የድነት ዕውቀት የተገለጠ ስውር ከሆነብን መጽሐፍ ቅዱስ በቋንቋችን ባይተርጎም ኖሮ ሙሉ በሙሉ የጨለማ ምርኮኞች በሆንን ነበር።

እስከ ዛሬ ድረስ አንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ በተመሰኑ የሃይማኖት ሰዎችና በቤተ መቅደስ አካባቢ ባሉት ሰዎች እጅ ብቻ መያዝና በእነርሱ አንደበት ብቻ መነገር አንዳለበት ያስባሉ። ይህ ሰይጣን በሰዎች ላይ ያለውን የአገዛዝ የሥልጣን ዕድሜውን እንዲያራዝም አጋዥ አመለካከት ነው። እግዚአብሔር የረዳው ብቻ ከዚህ ዕድሜ ጠገብ ቀንበር በጸጋው ያመልጣል።

ዛሬም ያለ ካህን መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ብቻ ሳይሆን መንካትን እንኳ እንደ ትልቅ ስህተት አድርገው የሚቆጥሩና ለማያውቁት መጽሐፍ ጥብቅና የሚቆሙ ሰዎች ብዙዎች ናቸው። ዛሬም ብዙ የአገሬ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ ለመታዘዝ ሳይሆን ማታ ሲተኛ መጥፎ ሕልምና ቅዠት እንዳያስቸግረው ጥራሱ ሥር በመቅበር ተአምር ይጠብቃል። ሰይጣን መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነቡ፣ የሚያምኑና የሚታዘዙትን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ የማያነቡና የሚፈሩ ሰዎችን አይፈራቸውም። ያለማወቅ ጨለማ የሰይጣን ምሽግ ነው። የተሐድሶ አርበኞች ምሽጉን ያፈራረሱት በእግዚአብሔር ቃል ጉልበት ነው። ዛሬ ለእኛም ብርቱ መሣሪያችን ቃሉ ነው።

ተሐድሶ የጸጋ መንገድ ከፍቷል

ከተሐድሶ ቀደም ብሎ ድነትን የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች በካህናት፣ በሰማዕታት፣ በጳጳሳት፣ በቅዱሳን ስም፣ ምስሎችን በመለመንና በመማጠን ጫካ ውስጥ ተቅበዝብዘው እንኳ ድነትን እንዳገኙ አርግጠኞች አልነበሩም። ሰው ባህታዊ ካልሆነ፣ ካልጸመ፣ ገንዘብ ካልከፈለ፣ የተለያዩ ሥርዓቶችን ካልፈጸመ እግዚአብሔርን ማግኘት እንደማይችል ቢነገርም ተራው ሕዝብ ቀርቶ የድርጊቱ መሪዎች የሆኑ ካህናት እንኳ መንገዱ የጠፋባቸውና ልባዊ እረፍት የራቀቸው ምስኪኖች ነበሩ። ከተሐድሶ በኋላ የእውነተኛ አማኞች ዓይን ስለ በራ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት ለመቅረብ ቻሉ። ቃሉም ከክርስቶስ ኢየሱስ ውጭ ሌላ ሰው በእኛ ምትክ እንዲቀርብልን ሳይሆን ዕርዳታ ፈላጊው በቀጥታ ወደ ጸጋው ዙፋን መቅረብ እንደሚችል ይናገራል። *"እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ"(ዕብ 4:16)።* በጌታ ባለን እምነት ወደ እርሱ የመግባት በር እንደተከፈተልን ቃሉ ሲናገር እንዲህ ይላል *"ባእርሱም ዘንድ ባለ እምነታችን በኩል በመታመን ድፍረትና መግባት በእርሱ አለን" (ኤፌ.3:12)።*

ተሐድሶ መጽሐፍ ቅዱስ በሁሉም እጅ እንዲሆን ትልቅ ሚና ተጫውቷል። በአዲስ ኪዳን አማኝ ሁሉ ካህን እንደሆነና ያለ ሌላ አማላጅና ዕርዳታ በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ በኩል ወደ ጸጋው ዙፋን መዝለቅ እንደሚችል ለሁሉም ግልጽ የሆነው ከተሐድሶ በኋላ ነው። የበደልና የኃጢአት ሸክም ያንከራተተው ሰው ኃጢአቱን በመናዘዝ በክርስቶስ ደም የኃጢአትን ይቅርታ በመቀበል፣ ክርስቶስን በእምነት በልቡ በማንገሥ የእግዚአብሔርን የልጅነት ሥልጣን ተጎናጽፎ በደስታና በድል መኖር እንደሚችል የታወቀው በተሐድሶ ማግሥት መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት በገሃድ በመሰበኩና ተራ ያተባለት አማኞች እጅ ገብቶ መነበብ በጀመረበት ጊዜ ነበር።

ተሐድሶ ለዳኑት ሁሉ የአገልግሎት በር ከፍቶላቸዋል

በክርስቶስ አገልግሎት የዳነ ሰው ሁሉ አገልጋይ ነው። እውነተኛ የወንጌል አገልጋይ ሁሉ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የዳነ ሰው ነው። ክርስቶስ ያዳነን አገልጋዮች ሊያደርገን እንጂ የቤተ ክርስቲያን አባል ብቻ እንድንባል አይደለም። በእውነት በክርስቶስ የመስቀል ሥራ የዳነ ሰው ዓለምን በወንጌል የማዳን ሥራን ከክርስቶስ ጋር አብሮ የሚሠራ ብርቱ ሠራተኛ እንጂ የሥርዓትና የወግ ዘበኛ የሆነ ሃይማኖተኛ አይደለም።

በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ አምኖ የዳነ ሰው ያልዳነውን ዓለም ለማዳን ይተጋል እንጂ የሃይማኖትን ፕሮቶኮል ለመጠበቅና ለማስጠበቅ አይጋደልም።

የክርስቶስ የሆነ ሁሉ በክርስቶስ ለክርስቶስ እንጂ ለሃይማኖት በሃይማኖት እንዳልዳነ ያውቃል። ከተሐድሶ በፊት በነበረው የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ጳጳሳትና ካህናት እንጂ ሌላው ሰው ምንም ዓይነት የአገልግሎት ዕድልና ቦታ አልነበረውም። መንፈሳዊውን ነገር በሞኖፖልነት የያዙት በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች ብቻ ሲሆኑ ብዙኃኑ ከተመልካችነትና አድርጉ የተባሉትን ከማድረግ ውጭ ያልገባቸውን መጠየቅ እንኳ እንደ ትልቅ መተላለፍ ይቆጠርባቸው ነበር። ሰው ሁሉ በልቡ እየጮኸ አፉ ተሸብቦ ይመላለስ ነበር። ተሐድሶ ይህን የዘመናት ዐጥቃ ሰብሯል። የሐዋርያት መሪ የነበረው ጴጥሮስ በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ስለዳኑት ቅዱሳን ምንነት ሲናገር፦ *"እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ የንጉሥ ካህናት ቅዱስ ሕዝብ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ" (1ጴጥ2:9)* ብሎአል።

ተሐድሶ መንግሥትን ከቤተ ክርስቲያን ጋር አፋቷል

የሮማው ቆስጠንጢኖስ ክርስትናን የሮም መንግሥት ሃይማኖት አድርጎ ካወጀበት ጊዜ አንሥቶ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ጋር ጋብቻ ፈጸመች።

ለሦስት ምዕተ ዓመት በጓዳ የተገደበች ቤተ ክርስቲያን የሮም አደባባይና አውራ ጎዳናዎችን ተቆጣጠረች። የዋሻ ዘመኗ አብቅቶ ቤተ መንግሥትን ወረሰች። ክርስቲያን መሆን እንደ ተረገመ ፍጡር እንዳልተቆጠረ ሁሉ በሮም ግዛት ያለ ሕዝብ ክርስቶስን ሳያውቅ ክርስቲያን ለመባል ተለለፈ። የነበረው ልዩነት ከመደብዘዙም አልፎ ቤተ ክርስቲያን ከመንፈሳዊነቷ ይልቅ የፖለቲካ ሚናዋ ጎልቶ መታየት ጀምሮ ነበር። በመሆኑም በመካከለኛው ዘመን የቤተ ክርስቲያንንና የቤተ መንግሥትን ድምፅ ለይቶ ለመረዳት በፍጹም አይቻልም ነበር። ከተሐድሶ በፊት ቤተ ክርስቲያን የመንግሥትን ፖለቲካ፣ የነገሥታትን ውሳኔና የአገርን ሕግ በበላይነት የመጫንና አቅጣጫ የማስቀየር አቅም የነበራት ሲሆን መንፈሳዊ ነገሯ ግን ሙሉ በሙሉ ከስሞ ነበር። በመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያን የመንግሥት ሥርዓት ደጋፊ ሳትሆን እራስዋ የመንግሥት ሥርዓት ሆና ነበር። ጆን ሃልዊል የተባሉት ጸሐፊ ስለዚያ ዘመን ሲገልጹ፦ *"በዓለም ታሪክ ቁሳርን ማምለክ የዓለም ሃይማኖት የሆነበት ዘመን ነበር። በዚያን ዘመን ማክስዮስ የብሔራዊ ሃይማኖት ካህን ሆኖ ነበር። እራሱም መንግሥትና ቤተ ክርስቲያንን ይመራ ነበር፡ በአጭር ቃል እርሱ ራሱ ቤተ ክርስቲያንም መንግሥትም ሆኖ ነበር"*[93] ብለዋል።

ቤተ ክርስቲያን በዓለም የራስዋ የቤት ሥራ የሆነውን ወንጌልን የመሰበክ ሥራ እንድትሠራ እንጂ ከምድራዊ መንግሥት ጋር ተወዳጅታ ሴሳ «ወንጌል» እንድትሰብክ የጌታ ፈቃድ አይደለም።

የቤተ ክርስቲያን ሥራ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ በኃይል መመስከር፣ የዳኑትን ደቀ መዛሙርት ማድረግና በምድር ላይ መንግሥቱን ማስፋት ነው። የመንግሥት ተግባር ደግሞ ዜጐችን በእኩልነት ማስተዳደር፣ የአገርን ሉአላዊነት ማስጠበቅ፣ ለሕግና ለሥርዓት መገዛትና ዜጎችን ማስገዛት፣ ወንጀለኞችን መቅጣት፣ አገራዊ የዕድገት ራእይ አንግቦ ለተፈጸሚነቱ ከዜጎች ጋር አብሮ መሥራት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌላት፣ ሐዋርያትም በመልዕክቶቻቸው ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት በራሳቸው መርህ እየተመሩ ተልዕኮቸውን እንደሚፈጽሙ እንጂ በዚህ ዓለም አንዱ ሌላውን እንደሚተካ አላስተማሩም። ተሐድሶው የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ሚና ወይም የፖለቲካንና የሃይማኖትን ሚዳ በመለየት አሁን በዓለማችን ላለው የፖለቲካ ተሐድሶና ኢኮኖሚ ዕድገት አንጸባራቂ ሚና ተጫውቶአል። በአራተኛው ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያንንና መንግሥትን በሕግ ያጋባው የሮማው ዐፄ ቆስጠንጢኖስ ሲሆን የቤተ ክርስቲያንንና የመንግሥትን ጋብቻን ያፋተው ደግሞ የፐሮቴስታንት ተሐድሶ ነው።

[93] see John H. Hallowell, (1950), Main Currents in Modern Political Thought (New York:Holt, Rinehart & Winston),pp.23, 27, 28

ተሐድሶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅድስናን ገልጧዋል

"ወደ ዓለም እንደ ላክኸኝ እንዲሁ እኔ ወደ ዓለም ላክኋቸው አነርሱም ደግሞ በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ እኔ ራሴን ስለ አነርሱ እቀድሳለሁ"
(ዮሐ.17: 18 - 19)

ከተሐድሶ በፊት አንድ ሰው ለመቀደስ፣ ከኃጢአት ለማምለጥና እግዚአብሔርን ለማስደሰት የግድ ከሰው ተለይቶ ባሕታዊ መሆን አለበት ተብሎ ይታመን ነበር። ከዚህም የተነሣ በአፋቸው ዓለም በቃኝ ያሉ በልባቸው ግን የዓለምን ፍቅር የተሸከሙ ሰዎች ገዳማትን አጨናንቀው እንደነበር ይነገራል። ከተሐድሶ በኋላ ግን ዓለም፣ ሥጋንና ሰይጣንን ወደ ጫካ በመሸሽ ሳይሆን በክርስቶስ በተገኘው የልጅነት ሥልጣን፣ በቃሉና በመንፈሱ በመታጠቅና ዕለት ዕለት አጥብቆ በመቃወም በቅድስና መኖር እንደሚቻል ብዙዎች እያመኑ መጡ። ቅድስና በረከሰች ዓለም በቃሉና በመንፈሱ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በመኖር እንጂ ኃጢአት የለም ተብሎ ወደሚታሰብበት ዋሻ በመሄድ ተደብቆ መኖር አይደለም። የሰው የዓለማዊነት ፈተናው ከልቡ የሚመነጭ እንጂ ከሚሰማውና ከሚታየው ነገር ብቻ እንዳልሆነ ቃሉ በግልጽ ይናገራል። በዓይን ከሚታየው፣ በጆሮ ከሚሰማውና በእጅ ከሚዳሰሰው ዓለም ወደ ገዳም ከሸሸን በልባችን ካለው ውሸት፣ ትዕቢት፣ የዚህ ዓለም አሳብና የሥጋ ምኞት መሸሽ አይቻልም። እስኪንሞት በቃሉና በመንፈሱ እየታገልን በጸጋው ብርታት እያሸነፍን ወንጌልን ለፍጥረት እየሰበክን ወደ ቀጣዩ ሕይወት በድል እንሻገራለን እንጂ ከቃሉ የተሻለ የማምለጫ ዋሻ በዓለም ላይ የለም። ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ጠርቶ ወንጌል አሸክሞአቸው ከዓለም ወደ ዓለም እንጂ ወደ ልዩ ገዳም አልላካቸውም።

ሰው ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ እንዳመነ ወደ ጫካ ከገባ ለቀረው ዓለም ወንጌልን ማን ይስበክ? የእውነተኛ አማኝ ቅድስና ክርስቶስን በመልበስ የሚገኝ አዲስ ማንነት እንጂ ከሰው ተለይቶ ወይም ከቅዱስ ጋብቻ ርቆ በመኖር የሚገኝ አይደለም። አንዳንድ ጃንደረቦች መኖራቸው ባይካድም። የተሐድሶ መሪ የነበረው ማርቲን ሉተር ለረዥም ዘመን ባህታዊ ሆኖ የኖረ ቢሆንም ሕይወቱ እረፍት አልነበረውም፣ ባሕታዊነቱ ከጌታ ጋር ሊያገናኘው ውም አልቻለም ነበር። ትልቅ መፈታት የሆነለት በክርስቶስ ኢየሱስ ሥራ አምኖ በዚያ መኖር በጀመረ ጊዜ ነው።

ተሐድሶ የሳይንስና የምርምር በር ከፍቷል

> *ክርስትና ባዶ ሃይማኖት ሳይሆን በተጨባጭ ሊታይ የሚችል ሳይንስ ነው።*[94] ቲኢ ፕለር የማቲማቲካል ፊዝክስ ፕሮፌሰር

[94] Tipler, F.J *(Professor of Mathematical Physics)*(2007). *The Physics Of Christianity*. New York, Doubleday

> *በሳይንሱ ዘርፍ ከተሰማሩ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች አንዱ እንደ መሆኔ መጠን የእግዚአብሔርን አለመኖር ያረጋገጠ የሳይንስ ዘርፍ እንደሌለ ተረድቻለሁ።*[95] ኢትዮጵያዊ ሳይቲስት ዶክተር ጥላዬ ታፈሰ

አብዛኛዎቹ የዘመናዊው ዓለም የታሪክ ምሁራን ያለ ፕሮቴስታንት ተሐድሶ አሁን ያለው የሳይንስና ምርምር ውጤት በዓለማችን ላይ እንደማይታሰብ ይናገራሉ። ከተሐድሶው በፊት በነበረው ዘመን ቤተ ክርስቲያን እያንዳንዱን የሳይንስና የምርምር እንቅስቃሴ ሁሉ በዓይነ ቁራኛ በመከታተል አንዳንዱን የምርምር ፕሮጀክት ገና ከጅማሬው ታስጨነግፍ እንደነበርና ከእርሷ መረዳት ውጭ አንዳች ግኝት ይፋ ለመድረግ የሚቃጡትን በገዛድ ታወግዝ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ።

የፕሮቴስታንት ተሐድሶ አሁን ባለው የሳይንስና የዲጂታል ተክኖሎጂ ምጥቀትና የምርምር ነፃነት ትልቅ ሚና ተጫውቶአል ።

ለምሳሌ በዘመኑ ካገኛቸው ትልልቅ ግኝቶችና ፋና ወጊ ምርምሮች የተነሣ "የዘመናዊ ፊዚክስ አባት"[96]ና "የዘመናዊ ሳይንስ አባት"[97] ተብሎ የተሰየመው ጋሊሊዮ ጋሊሊ *(1564– 1642)* ከሳይንሳዊ ግኝቶቹና ከፊጠራ ሥራዎቹ የተነሣ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተወግዞ ነበር። በዚያን ዘመን በጋሊሊዮ ጋሊሊ ላይ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ባለማወቅ ስለወሰደችው እርምጃ ፖፕ ጆን ፖል ሁለተኛ ከ350 ዓመታት በኋላ በኦክቶበር 31 1992 ግልጽ ይቅርታ ጠይቀዋል።[98] እንደ ፖፕ ጆን ፖል ሁለተኛ በአገራችንም ከዛሬ 500 ዓመት በፊት በአባ እስጢፋኖስና በተከታዮቹ ላይ ስለ ተደረገው ዘግናኝ ጭፍጨፋ ግልጽ ይቅርታ ጠያቂ አካል ቢገኝ እንዴት መልካምና ታላቅ ፈውስ በምድራችን በሆነ ነበር።

አንዳንድ ታሪክን አዛብተው የሚረዱ ሰዎች የፕሮተስታንትን እንቅስቃሴና የወንጌል አማኞችን እምነት የሳይንስ ተቃዋሚ አድርገው መቁጠራቸው ትልቅ ስህተት ነው። የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ለሰው ልጆች የምድር ሕይወት ዕድገትና ለውጥ አዎንታዊ ሚና የሚጫወቱ የሳይንስ ግኝቶችና ምርምሮችን ከመደገፍም አልፈው የብዙ ሳይንቲስቶች መፍለቂያና የዓለማችን ቀዳሚ ዩኒቨርሲቲዎች መሥራቾች እንደሆኑ መዘንጋት የለብንም። ለምሳሌ፦ ማክስ ፕላንክ የኳንተም ሜካኒክስ *"Quantum mechanics"* ግኝት ባለቤት የሆኑት ስመጥር ሳይንቲስት እ.ኤ.አ በ1918

[95] ነሀሩ 2004 ዓ.ም ገጽ 21

[96] *Weidhorn, Manfred (2005). The Person of the Millennium: The Unique Impact of Galileo on World History. iUniverse. pp. 155.*

[97] *Finocchiaro (2007).*

[98] *"On 31 October 1992, Pope John Paul II expressed regret for how the Galileo affair was handled, and issued a declaration acknowledging the errors committed by the Catholic Church tribunal that judged the scientific positions of Galileo Galilei, as the result of a study conducted by the Pontifical Council for Culture"* " Vatican admits Galileo was right". *New Scientist* (1846). 1992-11-07. Retrieved 2007-08-09..

በፊዝክስ የኖቤል ሽልማት አሸናፊ ሲሆኑ ከ1920 እስከ ዕለተ ሞታቸው በአሜሪካ የአንዲት ሉተራዊት ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ሆነው ያገለግሉ እንደነበረ ታሪካቸው ይናገራል። አሳቸውም፡- *"የተፈጥሮ ሳይንስና ክርስትና በእግዚአብሔር እንድናምን ይጠይቁናል"* ብለዋል።

አርተር ኮምፕተን በ"Compton effect" በፊዝክስ የኖቤል ሽልማት አሸናፊ በአንዲት የመጥመቃዊያን ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን ሆኖ ያገለግል ነበር። ከዓለማችን ዕውቅ ሳይንትስቲስቶች• አንዱ ሮበርት ቦያሉ (1627-1691) *"የሳይንስ ጥናትና ምርምር እግዚአብሔርን ይበልጥ እንድናከብር ያደርገናል"* በማለት ሳይንስና ክርስትና ጥል እንደሌላቸው በገሃድ ተናግሮአል። በአገራችንም በአኛ ዘመን በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች፣ በማስተማርና በተለያየ ምርምር ላይ የተሰማሩ እውነተኛ የክርስቶስ ተከታዮች የሆኑ ሳይንቲስቶች እንዳሉ መዘንጋት የለበትም። ከእነርሱ መካከል የሰማያዊ ወንጌል አገልጋይ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቪርሲቲ በፊዚክስ ትምህርት ክፍል የሚያስተምሩ የአስተሮፊዚክስት ባለሙያ ዶክተር ለገሠ ወትሮ ሲናገሩ፡- *"እግዚአብሔር የሳይንስ ውጤት አይደለም፣ የሳይንሱ ባለቤት እንጂ። ሳይንስ ደግሞ የእግዚአብሔርን እውነት የሚገልጥ ታማኝ አገልጋይ ነው"*[99] በማለት እግዚአብሔር የሳይንስ ባለቤት እንደሆነ መስክረዋል። በአጠቃላይ ተሐድሶ ለሳይንስ ግኝቶችና ምርምሮች የአዲስ ዘመን በር ከፍቶላቸዋል ቢባል የተጋነነ አይደለም። የሳይንስ ምርምር ነፃ ባይሆን ኖሮ ዓለማችን አሁን የደረሰችበት የሕዋ ምርምርና የዲጅታል ቴክኖሎጂ አብዮት ዘመን ላይ ትደርስ ይሆን? የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የጭፍን ሃይማኖተኝነትን ድንበር በሳይንስና በምርምር ጥሰው ያለፉት በወንጌል ልቦናቸው በርቶ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን እምቅ አቅም ለሰው ልጆች በረከት ለእግዚአብሔር ክብር ለመጠቀም የወሰኑ ምሁራን ነበሩ።

ተሐድሶ ለዓለም የለውጥ ምክንያት ሆኗል

ጆቢ ማርከት የተባለ ምሁር፡-

> *እ.ኤ.አ በ2009 የፕሮቴስታንት ተሐድሶ በሳይንስና በኢንዱስትሪው አብዮት ወቅትና በኋላ ለኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ ሚና እንደ ተጫወተ ለሀርቨርድ ዩኒቨርሲቲ ባቀረበው ጥናቱ አመልክቷል።*[100]

ጆቢ ማርከት ለጥናቱ የተጠቀመባቸውን ምንጮች ሲገልጽ ማርቶን እ.ኤ.አ በ1938 *"የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ በእንግሊዝና በጀርመን የዘመናዊ ሳይንስ ማበብ ምክንያት ነው"* ያሉትን፣ ሕሊ የተባሉ ምሁር እ.ኤ.አ በ1961

[99] *ማቴቴስ፣ ቁጥር 21 ሐምሌ፣ 2004 ዓ.ም፣ ገጽ 28*

[100] *JOB MARKET' (2009), The Economic Effects of the Protestant Reformation, Davide Cantoni_ Harvard University, 10 November,p.6*

"የፕሮቴስታንትን የማድረግ ምስጢር ሲገልጹ በሰው ነፃነትና ለእግዚአብሔር ተጠያቂ በመሆኑ ላይ ማተኮራቸውና ለአዲስ አስተሳሰብ ያላቸው የተከፈተ ልብ ነው" ያሉትንና በተለይ በጀርመን ላይ ያደረገው ስፊ ጥናት ወደዚህ ውጤት እንዳደረሰው ገልጸአል። ጆቢ ማርከት በተለይ በጀርመን ላይ ባደረገው ጥናት ማርቲን ሉተር የተሐድሶ እንቅስቃሴን ሲመራ ትልቅ ሁለንተናዊ አብዮትና የአመለካከት ለውጥ በዓለም ላይ ያመጣል ብሎ የጠበቀ አይመስልም። ትልቁ የእርሱ ትኩረት ሰዋዊና ምድራዊ ልምምዶችና አስተምህሮዎች ከቤተ ክርስቲያን እንዲወገዱና ቤተ ክርስቲያን እንደ ቃሉ የዓለም ብርሃንና ጨው እንድትሆን ነበር።

> *ከብዙ የሕይወት ዋጋ፣ እልህ አስጨራሽ የሞት ሽረት መንፈሳዊ ውጊያ፣ ከብዙ ዛቻ፣ የፍርድ ቤት ውሎና ማስጠንቀቂያ፣ ከብዙ መከራ፣ ብርቱ ጸምና ጸሎት፣ ስደት፣ እንግልትና ፍርሃት በኋላ ተሐድሶው እውን ሊሆን በዓለም ላይ ያልተጠበቀና ሁለንተናዊ ለውጥ እንዲመጣ ይነገራል።*[101]

ተሐድሶው ያመጣው የመጽሐፍ ቅዱስና የአዲስ ኪዳን ነገረ መለኮት መነቃቃት ብቻ ሳይሆን በሃይማኖቱ፣ በፖለቲካው፣ በሳይንሱ፣ በግለሰብ፣ በማኅበራዊ ሕይወት፣ በአገር፣ በአህጉርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተሐድሶ በፊት በዓለም ላይ የነበሩ ነገሮች እንደተለመደው በፍጹም እንዳይቀጥሉ ማድረጉ ነው። በኢትዮጵያም ለፖለቲካው፣ ለኢኮኖሚው፣ ለትምህርትና ለማኅበራዊ ዘርፍ፣ ለፋብሪካውና ለንግዱ እንዲሁም ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ምጥቀት የዜጐችን እምቅ አቅም ሥራ ላይ እንዲውል የሚያደርግ ከዘመናት በፊት የተጫረው የተሐድሶ እሳት ተቀጣጥሎ ዓለምን ማዳረስ አለበት። ተሐድሶ አሁን! የአሜሪካ ስመጥር የታሪክ ምሁር ፔጅ ስሚዝ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ በአሜሪካና በዓለም ላይ ያመጣውን አዎንታዊ ተጽዕኖ ሲገልጹ፡ *"የፕሮቴስታንት ተሐድሶ አዲስ አመለካከትና አዲስ ዓይነት ሰው በዓለም ላይ ፈጥሮአል"*[102] ብለዋል። በዓለም የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶና የአገር ሕዳሴ አንድ ላይ ይሄዱ ይሆን? ካለፈው ታሪክ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምን ትማር ይሆን? ተሐድሶን ማዘግየት እንጂ ማስቀረት በፍጹም እንደማይቻል የትናንቱ ታሪክ ዋቢ ከሆነ በምድራችን እየነፈሰ ያለውን የተሐድሶ ንፋስ በአዎንታዊ መንገድ መጠቀመ ብልህነት ነው። ጌታ ማስተዋሉን ይስጠን።

[101] የነገረ መለኮት ምሁር ፊልፒ ስለ ተሐድሶ ዓለም አተፋዊ ተጽዕኖ ያሉትን በእንግሊዘኛ እንዳለ አቅርብያለሁ፡- "The Reformation of the sixteenth century is, next to the introduction of Christianity, the greatest event in history. It marks the end of the Middle Ages and the beginning of modern times. Starting from religion, it gave, directly or indirectly, a mighty impulse to every forward move-ment, and made Protestantism the chief propelling force in the history of modern civilization" *(Philip Schaff, History of the Christian Church).*

[102] *Page Smith,(1976), Religious Origins of the American Revolution (Missoula, MT: Scholars Press,), I.*

ተሐድሶ ሃይማኖትና እምነትን ለያይቷል

ከተሐድሶ በፊት የነበረው ጊዜ የጨለማ ዘመን ተብሎ በዓለምና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይታወቃል። የጨለማ ዘመን የተባለበት አንዱ ምክንያት ከሮም መንግሥታት ጋር የተጋባች የመሳከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያን ቃሉን ዘንግታ፣ ሰዎችን በሚዳዊ ሥርዓትና ወግ ጠፍራ ክርስትና የልብ ጉዳይ መሆኑ ቀርቶ እንደ ሸቀጥ በገንዘብ የሚሸመት ተራ ነገር ወደ መሆን ወርዶ ስለ ነበረ ነው። በዘመኑ ከሮም እስከ አሌክሳንደርያ፣ ከጀርመን እስከ አርሜንያ፣ ከኢትዮጵያ እስከ እንግሊዝ ያለው አብዛኛው ሰው ክርስቲያን መሆኑ ይታወቅ እንጂ ለክርስቶስ ቃል ባይተዋር ነበር፤ የክርስቶስ ፈቃድ ለሕይወቱ ምን እንደሆነም አያውቅም ነበር። ቃል የሌላቸው ካህናት አንዳንዱ እነርሱ በማያውቁት የላቲን ቋንቋ ከሚነግሩአቸው ውጪ ለራሳቸው የእግዚአብሔርን ቃል አውቀው የሚተገብሩበት ዕድል አልነበራቸውም። ብዙ ሰው ሃይማኖት አለኝ ይበል እንጂ በዚህ አምናለሁ የሚል ነገር አልነበረውም።

ጃክስ ኤሉል የተባሉ የፈረንሣይ የነገረ- መለኮትና የማኅበራዊ ጥናት ምሁር *"ሃይማኖት ከፍ ሲል መገለጥ ዝቅ እያለ ይሄዳል"* እንዳሉት ከተሐድሶ በፊት ሃይማኖት ስለገነነ መለኮታዊ መገለጥ አልነበረም። ክርስትና ሃይማኖት አይደለም፤ ሃይማኖትም ክርስትና አይደለም። ዊልያም ስትሪንግ ፌሎው የተባሉ የነገረ መለኮት ምሁር በመጥቀስ የሃይማኖትን ምንነት እንዲህ ይገልጡታል፦

> *በአጭሩ ሃይማኖት እግዚአብሔር አሁንም ያልተደረሰበት እንደሆነ ያስባል፤ ክርስትና ግን እግዚአብሔር ቀደም ብሎ ወደ እኛ መምጣቱን ይናገራል ...ለሃይማኖት እግዚአብሔር ምስጢር ሲሆን በሃይማኖታዊ ዲሲፕሊኖችና ድርጊቶች እንደሚገለጥ ይናገራል። እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የመገለጡ መልካም ዜና እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ በግልጽና በክፍተኛ ተሳትፎ እንደሚታይ ያሳያል። ቤተ ክርስቲያን ለዚህ መልካም ዜና ታማኝ በሆነችበት ሥፍራ ሰዎች እግዚአብሔርን ለማግኘት የሚመጡበት ቦታ እንደሆነች ሳይሆን እግዚአብሔር ሰዎችን ለማግኘት የመጀመሪያ ተግባራዊ እርምጃ መውሰዱን ለማወጅ የሚሰበሰቡበት ሥፍራ ነው።*[103]

ሃይማኖት ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ለራሳቸው ያዘጋጁት መንገድ ሲሆን የክርስትና እምነት ግን ወደ ሰው የመጣውን የእግዚአብሔርን ልጅ በመቀበል የዳንንበት ሕያው መንገድ ነው። ይህን ለዘመናት ተደብቆ የቆየውን እውነት ገሃድ ያወጣው የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ነው።

[103] *William Stringfellow(1962), A private and Public Faith (Grand Rapids: Eerdman, p.17*

ተሐድሶ በዓለማችን የሥራን ባሕል ለውጧል

አውሮፓውያን ለሥራ የነበራቸውን የተዛባና የተሣሣተ አመለካከት የገለበጠውና ወደ ኢንዱስትሪ አብዮት እንዲገቡ ዐቢይ ምክንያት ከሆኑት ነገሮች መካከል አንዱና ዋነኛው የፕሮቴስታንት ተሐድሶ የሥራ ሥነ ምግባር እንደሆነ በሰፊው ይነገራል። በዚህ አሳብ ላይ ሰፊ ጥናት ያደረጉት የማኅበረሰብ ትምህርት መሐንዲስ የተባሉና የኢኮኖሚክስ ምሁር የነበሩት ጀርመናዊው ማክስ ዌቤር እ.ኤ.አ በ1905 *"The Protestant Ethic and the Spirit of Capitalism"* በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጽሐፋቸው፤

> *ከፕሮቴስታንት ተሐድሶ በኋላ ሃንዱን ክፍል በመሪነትና በሀብት ባለቤትነት የያዙት፣ የሰለጠኑ ሠራተኞችና የዘመናዊ ኢንቴርፕራይዝ ዋና አንቀሳቃሾች ፕሮቴስታንቶች ሆነዋል፣ ይህም ለሥራ ካላቸው የተሰየ አስተምህሮና ልዩ ሥነ ምግባር የተነሣ ነው።*[104] ብለዋል።

ከተሐድሶ በፊት የነበረችው የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ትኩረቱ ዓለምን በሥራ የመለወጥ ሳይሆን ዓለም በቃኝ ብሎ የገዳም ሕይወትን መምረጥ እንደ ቅዱስና ልዩ ጀግንነት የሚታይበት ዘመን ነበር። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነው የገዳም ሕይወትና አስተምህሮ ሰዎች በሥራ ዓለምን እንዲለውጡ ሳይሆን በዓለም ላይ ያለው ሁሉ ክፉ ስለሆነ ዓለም በቃኝ ብለው ሁሉንም እርግፍ አድርገው ወደ ገዳም እንዲገቡ የሚያደርግ ትምህርት ነበር። ከዚህም የተነሣ ስለ ሥራ የነበረው መረዳት እጅግ የወረደና ብዙዎችን ከሥራ ያገለለ ብቻ ሳይሆን ሥራ እንደ እርግማን እንዲቆጠር ያደረገ ነበር። እግዚአብሔር ጆን ካልቪንንና ማርቲን ሉተርን እንዲቆጠር ያደረገ ነበር። እግዚአብሔር ጆን ካልቪንንና ማርቲን ሉተርን ለቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ብቻ ሳይሆን ስለ ሥራ በዓለም የነበረውን የተንሸራፈፈ አመለካከት ያቀናበት መሣሪያዎቹና የምዕራቡ ዓለም የብልጽግና ፋና ወጊዎች እንደሆኑ እንደላካቸው ድርሳናት ያወሳሉ።

> *በዚህ ምድር የምንሠራው ማንኛውም ሥራ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። ሥራችን በቤተ ክርስቲያን ይሁን በቤት፣ በማዕድ ቤት ይሁን በአርሻ ሁላችንም እግዚአብሔርን እየገለገልን ነው።* ማርቲን ሉተር

ክርስቶስ የሌለበት ክርስትና

ፕሮቴስታንቶች ወይም የወንጌል አማኞች ዐቢይ መለያቸው መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ፤ ድነት በእምነት ብቻ፤ ድነት በጸጋ ብቻ፤ ድነት በኢየሱስ ብቻ፤ ብለው መነሣታቸው ነው። ከባዶና ሃይማኖታዊ ልዩ ልዩ ሥርዓቶች በክርስቶስ ባለው እምነት ተለውጠ፣ እንደ ቃሉ ብርሃንና ጨው በመሆን ለእግዚአብሔር ክብርና ለሰዎች በረከት ሆኖ መገኘት የፕሮቴስታንቶች ተሐድሶ መለያ ነው። ከዚህም የተነሣ ዓለማችን አሁን ላለችበት መንፈሳዊ፤

[104] Max Weber,(*1905), The Protestant Ethic and the Spirit of Capitalism. p1*

ፖለቲካዊ፣ ማኅበረሰባዊና ሳይንሳዊ ምጥቀትና ዕድገት የበኩላቸውን አንጸባራቂ ሚና እንደተጫወቱ በዓለም ታሪክ የታወቀውን እውነት በጥቂቱ ተመልክተናል።

የፐሮቴስታንት እንቅስቃሴ መሠረትና ምሶሶ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ለአፍታም መዘንጋት የለበትም። ኢየሱስ ክርስቶስ የሌለበት፣ መንፈሱና ቃሉ ቦታ ባላገኙበትና ሕይወት በቃሉ ባልተገራበት ክርስትና አመጽ፣ ኃጢአትና እርኩሰት በክርስትና ስም መንገሡ አይቀሬ ነው። ዋናው ስም ሳይሆን ሕይወት ነው። የሕይወት ምንጭ ደግሞ የስም ክርስትና ሳይሆን "እኔ ሕይወት ነኝ" ያለው ክርስቶስ ነው። የትኛውም ሃይማኖት እንደ ኢየሱስ የሰውን ሕይወት፣ አመለካከት፣ ባሕሪይና የአኗኗር ዘይቤ ብቻ ሳይሆን የሰውን የዘላለም ዕጣ ፈንታ መለወጥ አይችልም። ኢየሱስ ያልገነነበት ፕሮቴስታንትዝም እንደ ሌሎች ባዶ የሃይማኖት ሥርዓቶች ለድነት የማይጠቅም ባዶ ነው። ዋናው በፐሮቴስታንትዝም የተገለጠው የሰዎች ልጆች ቤዛ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ለዚህም በዓለማችን ከሕዝባቸው 80% በላይ የፐሮቴስታንት ስም ተሸክመው ውርጃንና ግብረሰዶማዊነትን በማስፋፋት የአንበሳውን ድርሻ የያዙ የስካንዲንቪያን አገሮችን በምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ራልፍ ዊንቴር ሚሽን ፎርጉቴርስ መጽሐት /2008 እ.ኤ.አ/ ክርስቲያኖች ተብለው አሉታዊ ተምሳሌት ስለሆኑ አገሮች እንዲህ ብሎ ገልጾ ነበር፦

> *መካከለኛ አፍሪካ በአንዳንዶች ዘንድ በዓለማችን ኣደገኛና በሙስና ከታወቁት አገሮች አንዱዋ ስትሆን 59 ቤተ እምነትቶችን የያዘች፣ ከሕዝቡ 70% የወንጌል ኣማኞች ሲሆኑ ይህም በአፍሪካ ቀዳሚ ያደርጋቸዋል። ናሚቢያ በተባለው የሀንድ ክፍለ አገር አንድ ጎሳ 90% የፐሮቴስታንት ክርስቲያኖች የሚኖሩበት ብቸኛው ክፍለ አገር ስትሆን በተለይ ወጣቱ ክፍል በሱሰኝነትና በቁማር ተለክፏል። ሩዋንዳ በዓለማችን ከ90% በላይ ክርስቲያኖችን በመያዝ ቀዳሚ ከሆኑ አገሮች አንዷና የምሥራቅ አፍሪካ የመንፈሳዊ አንቅስቃሴ የትውልድ አገር ተብላ ስም የወጣላት በአንጻሩ ግን ዘር የማጥፋት ዘግናኝ ወንጀል በእርስ በርሳቸው ላይ ፈጽመዋል።*[105]

ከዚህ የምንረዳው እውነት፦ ሰዎች በአንድ አገር ክርስትና ስለተቀበሉና ክርስቲያን ስለተባሉ ብቻ ፍትሕ፣ ፍቅርና እኩልነት ያሰፍናሉ ማለት እንዳልሆነ ነው። ቢሆን ኖሮ ለዝንተ ዓመታት "የክርስቲያን ደሴት" የተባለቸው እናት አገሬ ኢትዮጵያ በአሉታዊ ታሪክና ኢክርስቲያናዊ ድርጊትና ቀውስ ሁሉ ስሟ ባልተጠቀሰ ነበር። ዛሬ የተወለደ ጨቅላ ነገ አደጎ ብዙ መሥራት እንደሚችል እሙን ቢሆንም ሳያድግ ግን መሥራት አይችልም። ለማደግ ብርቱ ጥንቃቄ፣ ጊዜ፣ ምግብ፣ መልካም ጤንነትና ምቹ አካባቢ ውሳኝነት አለው። አንድ ሰው በመንፈሳዊ ዓለምም ሲወለድ መንፈሳዊ ሕይወቱን የሚያሳድግ ተንከል የሌለበት የእግዚአብሔር ቃል ምግብ፣ በቃሉ ያደጉ አሳዳጊዎች፣ ጊዜና ትክክለኛ ቦታ ማግኘት የግድ ነው።

[105] *Christopher J.H.Wright,(2006), The Mission of God, Inter-Varsity Press, p.321*

በወንጌል ስርጭት በጌታ አምነው ወደ ጌታ የመጡ መንፈሳዊ ሕፃናት የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ተምረው ደቀ መዝሙር ካልሆኑ ስለተጠመቁ ብቻ ክርስቶስን የሚገልጥ አሸናፊ ሕይወት መኖር አይችሉም። ለዚህ ነበር የክርስትና መሠረት የሆነው የናዝሬቱ ኢየሱስ አሥራ ሁለት ሐዋርያትን ሦስት ዓመት ሙሉ ቀንና ሌሊት መንፈሳዊ ምግብ ሲመግባቸው፣ ባሕሪያቸውን ሲሞርድ፣ አመለካከታቸውን ሲለውጥ፣ ጠባብ አይታቸውን ሲያሰፋና በሕይወታቸው አስቀድሞ በእነርሱ ሲሠራ አስቀድሞ ሕይወታቸውን በመሥራት የቆየው። አንድ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወቱ ካላደገ ለእግዚአብሔር መንግሥት መስፋት፣ ለአገር ዕድገት፣ ሰላም፣ ብልጽግና፣ ለዜጐች አንድነትና ፍቅር ተምሳሌታዊ ሕይወት ሊኖረው አይችልም። ስለዚህ ቃሉን አውቀውና ጎልምሰው በዚያ ላይ በተግባር ለመገለጥ በእምነት ካልወጡ በስተቀር የካቶሊክ፣ የኦርቶዶክስና የፐሮቴስታንት ክርስቲያን መባሉ ብቻውን ከክፋት ሰውን አያርቅም። የድነት መንገድም አይሆንም። የግለሰብን ሕይወት ሆነ አገርን አይለውጥም። የለውጥ መሠረቱ ኢየሱስ ነው።

ማጠቃለያ

የፐሮቴስታንት ተሐድሶና እግዚአብሔር ለተሐድሶ የተጠቀመባቸው ሰዎች ምንም ስህተት አልነበራቸውም የሚል ሰው እራሱ የተሳሳተ ነው። ከፐሮቴስታንት ተሐድሶ ጋር ብዙ ስህተቶች ተፈጥረዋል። አንዳንዶችን ለመጥቀስ ካስፈለገ በፐሮቴስታንትና በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መካከል የተካሄዱ ስም የማጥፋት ዘመቻዎች፣ የጥላቻ ፕሮፖጋንዳዎች፣ አመጾች፣ የተገደሉ ሰዎች፣ ጦርነቶችና መለያየቶች ከተሐድሶ ጋር ከተያያዙ አሉታዊ ድርጊቶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። እንዲሁም መቆሚያ ያልተገኘለት መበጣጠስ። ይህ እስከ አሁን ድረስ የዘለቀ ችግር ነው። ፕሮቴስታንቶች በካቶሊኮች ሲሰደዱ እነርሱም በተራቸው አናባፕቲስቶችን (ዳግም አጥማቂዎችን) ያሳድዱ እንደነበር ታሪክ ይናገራል። ከላይ የተመለከትናቸው አሉታዊ ተጽዕኖዎች እንዳሉ ሆነው ተሐድሶ የእግዚአብሔርን ቃል ብርሃን ወደ ገሃድ አውጥቷል። የተሐድሶ መሪዎች በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የተወለዱ፣ ያደጉ፣ የተማሩና ብዙዎች ካህናት የነበሩ ሲሆን በእነርሱ የተጀመረው ተሐድሶ የዓለም የበረከትና የለውጥ ምክንያት ሆኖአል።

ተሐድሶ አንዱ ብቻ የሚደረግ ድርጊት ሳይሆን በግል ሕይወታችንና በቤተ ክርስቲያን በቃሉና በመንፈሱ አማካይነት ሁሉ የሚካሄድ *"the on going reformation"* ለውጥና በረከት አመንጪ ሂደት ነው። ተሐድሶን እንደ አጥፊና እንደ ተዋጊ አውሬ የምንመለከት ከሆነ በተሐድሶው ተጠቂዎች እንጂ ተጠቃሚዎች አንሆንም። በ21ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን፣ በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንና በኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በሚካሄደው መለኮታዊ ተሐድሶ ተጠቃሚዎች እንጂ ተጠቂዎች እንዳንሆን ጌታ ሁላችንንም

ይርዳን። የኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ተሐድሶን መንፈሳዊ ተሐድሶ መቅደም አለበት። የኢትዮጵያን ሕዳሴ በቃሉ የታደሰች ቤተ ክርስቲያን መምራት ይኖርባታል። ኢትዮጵያ ለዘመናት ከታሠረችበት የድህነት፣ የረሃብና የጦርነት ታሪክ ለመላቀቅ በብርቱ ትግል ላይ በምትገኝበት በዚህ ወሳኝና ታሪካዊ ዘመን ላይ መገኘት በራሱ ትልቅ ዕድል ነው። ከዚህ ታላቅ መነቃቃት ጀርባ የታላቁ ጌታ እጅ እንዳለ አምናለሁ። የኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ሕዳሴ የግድ መሆኑ ከታመነበት የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት የሕዳሴው ፋና ወጊዎች እንዲሆኑ ይጠበቃሉ። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው በወንጌል የተለወጠ አዕምሮ የአምንታዊ ለውጥ እርሾ እንደሆነ የዓለም አቀፍ የፓሮቴስታንት ተሐድሶ ትሩፋቶች አንፀባራቂ ምስክሮች ናቸው።

የአሁኗ ቤተ ክርስቲያን የአባቶች ታሪክ ጠባቂ ብቻ ሳትሆን በራሷም ዘመን አዲስ ታሪክ ሠሪ መሆን ይገባታል።

እውነተኛ ተሐድሶ የሚጀምረው ከራስ መሆኑን በመረዳት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለአገራዊ ለውጥ ከመነሣትዋ በፊት ራስዋን መመልከት ግድ ነው። ከአገራዊ ሕዳሴ ግላዊ ሕዳሴ ይቀድማልና። ቤተ ክርስቲያን በዚህ አገራዊ ተሐድሶ ዐቢይ ሚና ለመጫወት በቃሉና በመንፈሱ አስቀድማ መታደስ ይገባታል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በቃሉ መስተዋት ራስዋን ተመልክታ ካፈጀውና ካረጀው አካሄድ መላቀቅ፣ ስላለፈው ገድል ብቻ ከመተረክ መንፈሳዊ ተጋድሎ መጀመር፣ ከትናንት ድልና ሽንፈት ተላቃ ለሚበልጥ ውጤት ግልጽ ራእይ ይዛ መነሣት፣ ያለፈውን ትውልድ ምንነትና ማንነት ብቻ ከማስረዳት ትውልዱ በጌታ ማን እንደ ሆነና በጌታ ምን መሥራት እንደሚችል ማስተማር ይጠበቅባታል። አገራዊ ሕዳሴ ከመምራቷ በፊት ራስዋ በቃሉ ስለመመራቷ እርግጠኛ ልትሆን ይገባታል። እግዚአብሔር የኢትዮጵያን አብያተ ክርስቲያናት ይባርክ።

የታደሰው ክርስትና ለምዕራቡ ዓለም፣ ለደቡብ ኮሪያና ለቻይና የኢኮኖሚ ምጥቀት፣ ለዲሞክራሲ ማበብ፣ ለማኅበረሰብ ግንባታ፣ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ምጥቀት፣ ለሥራ ፈጠራ በር ከፋች እንደሆነ ቀጣዩ ምዕራፍ በአስደናቂ መረጃ የዳበረ እውነት ይዟል። በሁለት ሺ ዓመታት በኢትዮጵያ የተሰበከው ክርስትና በእነዚያ አገራት ከተሰበከው እጅግ የቀደመና አንድ ከሆነ አንድ ዓይነትም ባይሆን ትንሽ እንኳ ተቀራራቢ ለውጥ ለምን አላመጣም? የሚል ጥያቄን በማንሣት ክርስትናችን በእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ መፈተሽ እንዳለበት ይሞግታል።

I

ክርስትና
የዓለም ሕዳሴና ዕድገት መሠረት

በደቡብ ኮሪያ

የኢትዮጵያ አርበኞች የደም ዋጋ ለኮሪያ ነፃነት

ከዛሬ 70 ዓመታት በፊት ኢትዮጵያ ከኮሪያ በኢኮኖሚ፣ በመከላከያ ኃይል፣ በዓለም በነበራት እውቅና፣ በታሪክና በነፃነት ቀዳሚ እንደነበረች ታሪክ ያወሳል። እ.ኤ.አ 1960-1968 ደቡብ ኮሪያውያን በጦርነትና በድርቅ ከመድቀቃቸው የተነሣ ድሮ የማይበሉትን ቅጠላ ቅጠልና የባሕር ዛፍ ቅርፊት ለመብላት የተገደዱበት ጊዜ እንደ ነበር ታሪካቸው ይናገራል። በወቅቱ ከነበረችበት አሳዛኝ ሁኔታ የተነሣ *"ሳሰፋ የሌላት"*፣ *"በቅገፖት ውስጥ የነበረች"*፣ *"የአይጥ ጉድጓድ"* የሚል ቅጽል ስም የተሰጣት ሀገር ነበረች። ከዛሬ ስልሳ ዓመት በፊት 6000 ኢትዮጵያውያንን ያቀፈ *"ቃኘው ሻለቃ"* የሚል ስያሜ የተሰጠው ጦር ደቡብ ኮሪያ በሰሜን ኮሪያ በተወረረች ጊዜ ዘምቶ ነበር። ዓለማውም ደቡብ ኮሪያን ከባዕድ ወረራና ጭቆና ነፃ ለማውጣት ሲሆን የቃኘው ሻለቃ ዘማቾች የዘመቱት በተባበሩት መንግሥታት በኩል ነበር።

በላይ አባላት አላቸው።[109] በማለት የኮሪያን አስደናቂውን ለውጥ ያመለክታል። የኮሪያ ቤተ ክርስቲያን ፈጣን ዕድገት ያስመዘገበችበት ዘመን እ.ኤ.አ ከ1970ዎቹ እስከ 1980ዎቹ ሲሆን የኮሪያ የዓለም አቀፍ የሚሲዮናዊነት ራእይም የተወለደው በዚያው ወቅት ነበር። የቤተ ክርስቲያን ዕድገት ውጤት ሁልጊዜ ሚሲዮናዊነት ባይሆንም የኮሪያውያን ቤተ ክርስቲያን የዕድገቷ ውጤት ታላቅ የሚሲዮናዊነት እንቅስቃሴ አብሮ መወለዱ ቤተ ክርስቲያኒቷን በዓለማችን ላይ እጅግ ጠንካራ አድርጓታል።[110] ኮሪያውያን በራሳቸው የዕድገት መነቃቃት ጥላ ሥር ጊዜያቸውን፣ አትማቸውን፣ የተሰጣቸውን ጸጋና ዕድሜ በከንቱ አላባከኑም፤ ነገር ግን ሉልአቀፋዊ ራእይ ይዘው ለዓለም በወንጌል በረከት ሆነዋል።

ኢግ ጂን ኪም በደቡብ ኮሪያ የወንጌውያንን እድገት እንዲህ አስፍረዋል፦

> *ባለፉት 100 ዓመታት የክርስትና ዕድሜ 40% ከሆነሩ ሕዝብ የወንጌል አማኝ ሲሆን፣ 170 ወንጌላውያን ቤተ እምነቶች ያሉባት፣ 47,810 አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት፣ 430 ሀገር በቀል ክርስቲያናዊ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ 210 ባሕር ዘለል ሚሲዮናውያንን የሚልኩ መንፈሳዊ ድርጅቶች፣ 180 የነገረ-መለኮት ሴሚናሪዎች፣ ኮሌጆችና ዩንቨርሲቲዎች፣ 521 ትልልቅና ብሔራዊ ልዩ የጸሎት ማዕከላት፣ 15,000 ባሕር ዘለል ሚስዮናውያን ወደ 170 የዓለም ሀገሮች የተላኩ ሲሆን፣ በዚሁ አገልግሎቷ ከአሜሪካ ቀጥላ ሁለተኛዋ ደቡብ ኮሪያ እንደሆነችና በቅርብም ከአሜሪካ የቀዳሚነቷን ሥፍራ እንደምትረከብ[111] ጽፈዋል።*

የኮሪያ ወርልድ ሚሽን አሶሴሽን (KWMA) መሥራችና ዳይሬክተር ካንግ፦

> *ከጀን 2010 ጀምሮ ደቡብ ኮሪያ 22,000 ሚሲዮናውያንን ወደ 170 ሀገሮች እንደ ላኮች፣ እስከ እ.ኤ.አ 2030 ድረስ 100,000 ኮሪያውያን የወንጌል ሚሲዮናውያንን ወደ ዓለም ሁሉ የመላክና ከ300 የኮሪያ ክርስቲያኖች አንዱ ሚሲዮናዊ እንዲሆን ዕቅድ ይዘው በትጋት እየሠሩበት እንዳሉ ይናገራሉ።[112] አሜሪካ ሰላሳ ሦስት ሺ ሚስዮናውያንን በዓለም ላይ በመላክ አሁንም ቀዳሚ ሚሲዮናዊ አገር እንደሆነች ቢነገርም ሃያ ሁለት ሺ ሚሲዮናውያንን በመላክ ተከታይ የሆነች ኮሪያ ከሕዝብ ብዛት አንጻር ከታየ ቀዳሚ ልትሆን ትችላለች። በአሜሪካ ከ7000 ክርስቲያኖች 1ዱ ሚሲዮናዊ ሲሆን ኮሪያ ከ900 ክርስቲያኖች 1ዱ ሚሲዮናዊ ነው።[113]*

አስደናቂው ነገር ምዕራባውያን ሚሲዮናውያን ላኪ አገሮች በጣም እየቀነሱ ሲሆን ከኤስያ፣ ከህንድ፣ ከብራዚል፣ ከአፍሪካና ከቻይና ሚሲዮን

[109] http://www.prayerfoundation.org/world_christian_growth_statistics.ht

[110] Johnson and Chung, Christianity of Gravity, AD 33-2100 p. 53

[111] Ig-Jin Kim,(2003), History and theology of Korean Pentecostalism, Uitgeverij Boekencentrum, Zoetermeer, The Netherlands, p.5

[112] Christian today, March 2006, Vol. 50, No. 3

[113] BEYOND CHRISTENDOM 2008, p384

ለደቡብ ኮሪያ ነፃነት አባቶቻችን 253 ውጊያዎችን አድርገው፣ 120 ኢትዮጵያውያን ሕይወታቸውን ለደቡብ ኮሪያ ነፃነት እንደከፈሉላትና 536 በጦርነቱ እንደ ቆሰሉ መረጃዎች ይጠቁማሉ።[106]

በደቡብ ኮሪያ ስለተዋጉት የኢትዮጵያውያን ወታደሮች ጀግንነት ሜጀር ጀኔራል አርተር ጂ.ትሩዲ የአሜሪካ ጦር ኃይል ሪዳት ኤታማዦር ሹም የነበሩ ሲናገሩ፦ "*በደቡብ ኮሪያ ዐውደ ግንባር ማንም እንደ ኢትዮጵያውያን አልተዋጋም*"[107] ብለዋል። በጦርነቱ 2,000,000 /ሁለት ሚሊዮን/ ኮሪያውያን እንደሞቱ ታሪክ ያወሳል። ኢትዮጵያውያን ለኮሪያ ነፃነት ስለከፈሉት የደም ዋጋ ውለታና አድናቆታቸውን ለመግለጥ የኮሪያ ፕሪስቢታሪያን ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ "ሚዩንግሳንግ ክርስቲያን ሜዲካል ሴንተር" (MCM) ትልቅ ሆስፒታል ገንብታለች። የዚህ ልዩ ሆስፒታል ዋና ዓላማ፦

> *የኢትዮጵያ ወታደሮች በዚያች አገር ላፈሰሱት ደምና ለከፈሉት መሥዋዕትነት እንደ ውለታ መመለሻ ይሆን ዘንድ በእግዚአብሔር ፍቅር ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የሚሠራ ሆስፒታል (Hospital Working With The People of Ethiopia In Love of God) በሚል መርህ ይንቀሳቀሳል። የዚህ ሕክምና ማዕከል ዋነኛ መርህ "ኢትዮጵያ እናመሰግናለን" (Thank you Ethiopia) የሚል ነው፤ ይህም የመሆኑ ምክንያት ይኸው አባቶቻችን ለኮሪያ ነፃነት የከፈሉት መስዋዕትነት ነው።[108]*

ለበለፀገችና በወንጌል ለዓለም በረከት እየሆነች ላለችው ለዛሬዪቷ ደቡብ ኮሪያ የኢትዮጵያውያን ድርሻ በደም የታተመ እንደሆነ ታሪክ ይዘክራል። ለኮሪያ ዕድገት ዐቢይ ሚናን የተጫወትን ሕዝቦች ለራሳችን ዕድገት ምንም ማድረግ ለምን አቃተን?

የክርስትና ሚና ለደቡብ ኮሪያ ዕድገት

ከዛሬ 100 ዓመታት በፊት ኮሪያ ለወንጌል ድንግል ሀገር ስትሆን በዲሀዝምና የተለያዩ የጣዖታት አምልኮ የተቆጣጠሯትና በጨለማ ሥር የወደቀች ሀገር ነበረች። ወንጌል ኮሪያ ከመግባቱ ከ1900 ዓመታት በፊት ኢትዮጵያ ወንጌል እንደደረሳትና ብዙ አማኞች እንደ ነበሩባት ድርሳናት ይናገራሉ። በአጠቃላይ ከዛሬ 100 ዓመት በፊት ደቡብ ኮሪያ በቡዲሀዝም፣ በአጋንንት አሠራር፣ በድህነት፣ በጦርነትና በኋላ ቀርነት የደቀቀች አገር እንደ ነበረች ታሪክ ያወሳል። ወርልድ ክርስቲያን ስታትስቲክስ ድረ ገጽ፦ *በ1900 በኮሪያ አንድም የፐሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ያልነበረ ሲሆን ለመግባትም በፍጹም የማይሞክር ነበር። ዛሬ በኮሪያ ዋና ከተማ በሴኦል ብቻ ከ7000 በላይ ቤተ ክርስቲያናት ሲኖሩ እያንዳንዳቸው በአማካይ ከ10,000*

[106] Kimon Skordiles, KAGNEW the history of the Ethiopian fighters in Korea, p.,xi

[107] Ibid., p.xiv

[108] አዲስ ጉዳይ፣ ቅፅ ቁጥር 120 ሐምሌ 2004 ዓ.ም ገጽ 38

ላኪ አብያተ ክርስቲያናት በከፍተኛ ፍጥነት እየበዙ መሆናቸው ነው። ይህ 21ኛው ክፍለ ዘመን የክርስትና ማዕከል ከሰሜን ወደ ደቡብ የዓለማችን ክፍል ስለመሻገሩ ተጨባጭ ማስረጃ ነው። ይህ ዘመን የእኛ ዘመን ነው። ሌላው አስገራሚ ነገር ደቡብ ኮሪያ 1,000,000 /አንድ ሚሊዮን/ አባላት ያላት አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኝባት የዓለማችን ብቸኛ ሀገር መሆኗ ነው። በዓለማችን ከአምስት ትልልቅ ቤተ ክርስቲያኖች መካከል አንዱ በደቡብ ኮሪያ እንደሚገኝ መረጃዎች ያመለክታሉ።[114] አንድ የደቡብ ኮሪያ ሚስዮናዊ በ1940ዎቹ (እ.ኤ.አ) *ኮሪያውያን ዛሬ አዲስ ቦታ ቢደርሱ በነጋታው አዲስ ቤተ ክርስቲያን ይተክላሉ፣ ቻይናውያን ምግብ ቤት ጃፓኖች ደግሞ ፋብሪካን ይከፍታሉ።* በማለት ኮሪያውያን ምን ያህል ለወንጌል ሥራ እንደተሰጡ የተናገሩት በብዙዎች የሚጠቀስ አባባል ሆኗል።

የኮሪያ ዲያስፖራና የሚሲዮናዊነት ራእይ

እ.ኤ.አ በ2005 6.6 ሚሊዮን የኮሪያ ዲያስፖራ በ160 አገሮች እንደሚኖሩ ታውቋል።[115] ከዚህ ውስጥ 3 ሚሊዮን የክርስቶስ ተከታዮች የሆኑ ኮሪያውያን በ10,000 አብያተ ክርስቲያናት ተሰብስበው በውጭ አገር ጌታን ያመልካሉ።[116] እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት አብረው ከማምለክ ያለፈ ዓለምን በወንጌል የመድረስ ታላቅ ራእይ ይዘው በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኙ ጥናቶች ያመለክታሉ። የኮሪያ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቲያን ቤተሰብ ልጆች ከሕፃናት መዋያ እስከ ዩኒቨርሲቲ ላሉት ተማሪዎች ደረጃውን የጠበቀና ወጥ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት በኮሪያውያን የነገረ መለኮት ሊቃውንት ተቀርጾ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ላሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የተዘጋጀ ትምህርት ይሰራጫል። አንድ ኮሪያዊ ልጅ የትም ቢያድግ የሚማረው መንፈሳዊ ትምህርት ደረጃውን የጠበቀና ተመሳሳይ ነው።

እ.ኤ.አ በ1961 *"የዩኒቨርሲቲ የመጽሐፍ ቅዱስ ሕብረት"*[117] የሚባል በኮሪያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ የተለየ ትኩረት ሰጥቶ የሚሠራ አገልግሎት ተቋቁሟል። የዚህ አገልግሎት ዋና ዓላማ የኮሪያ ከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ትምህርታቸውን በከፍተኛ ልሂቀት እንዲከታተሉ ማገዝ፤ ሚሲዮናዊ እንደሆኑ አውቀው ዋጋን በመክፈል በሚማሩበት የትኛውም የዩንቨርሲቲ ማኅበረሰብ በክርስቶስ ወንጌል መድረስ፤ ከተመረቁም በኋላ በሰለጠኑበት መስያ አገርንና ሕዝብን በማልማት ከማንም ደሞዝ ሳይከፈላቸው ሚሲዮናዊ ሆነው በዓለም ሁሉ እንዲያገለግሉ የሚያደረግ ነው።

[114] *mega church, the free encyclopedia*
[115] Statistics by the Ministry of Foreign Affairs and Trade, Korea 2005
[116] Korean Diaspora and Christian Mission, (2011) p.262 Regnum Books International,
[117] "The University Bible Fellowship is a non-denominational, evangelistic campus mission organization focused on raising disciples of Jesus Christ who live sacrificial lives for the gospel and contribute to society and their nation by preaching the gospel of Jesus Christ to collage students and young people." Pter Chang (ed) preach the good News to All Creation (Bonn: Europe UBF Press, 2008 p.146-147

እ.ኤ.አ ከ1990 እስከ 1999ዎቹ እየተማሩና በሙያቸው እየሠሩ የሚሲዮን አገልግሎታቸውን የመኖር ዋና ዓላማቸው ያደረጉ 250 ሚሲዮናውያን የኮሪያ ተማሪዎች ወደ ጀርመንና አውሮፓ ዩንቨርሲቲዎች ተልከዋል።[118] እጅግ ብዙ ቤተ ክርስቲያናትም መሥርተዋል። በአጠቃላይ ከኮሪያ ወደ አውሮፓ ሚሲዮናዊ ሆነው የተሻገሩ ተማሪዎች በትምህርታቸውም እጅግ የላቁ ስለሆኑ ከእነርሱ መካከል እስካሁን 300 ተማሪዎች ሚሲዮናውያን በተለያየ የትምህርት ዓይነት ሦስተኛ ዲግሪያቸውን *(ዖ.ሌ.ዲ)* ተቀብለዋል።[119] በአሜሪካ ዛሬ ከ700 የተማሪ ሚሲዮናውያን በአገልግሎት ላይ ይገኛሉ።[120] እግዚአብሔር ታላቅ ነገር በኮሪያውያን እየሠራ ነው።

ክርስትና ለደቡብ ኮሪያ ማኅበረሰብ ለውጥ

አብዛኛዎቹ የደቡብ ኮሪያ ክርስቲያኖች፣ ክርስትና በኮሪያ ማኅበረሰብ ጎጂ ባሕሎችና ኋላ ቀር አመለካከቶች ላይ ሥር ነቀል ተሐድሶ እንዳመጣና የዛሬ የመልካም እሴቶች ባለቤት እንዳደረጋቸው አፋቸውን ሞልተው ይመሰክራሉ። ለምሳሌ፡- በኮሪያ ባሕል ሴቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ ምንም መብት አልነበራቸውም፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆች በሩቅ ምሥራቅ ባሕል እኩል ዋጋ አይሰጣቸውም ነበር፣ ባል የሞተባቸው ባልቴቶች እንደገና የማግባት መብት አልነበራቸውም፣ ልጆች እንደ እግዚአብሔር ስጦታዎች ሳይሆኑ ለወላጆቻቸው ለሎሌነት እንደተፈጠሩ ይቆጠሩ ነበር። ከዚህም የተነሣ ማኅበረሰባዊ እንጂ ግላዊ መብት አልነበራቸውም። ይህን አሉታዊ ባሕላዊ እሥራት በኮሪያ የበጣጠሰው ክርስትና እንደሆነ ኮሪያውያን ይመሰክራሉ።

ኮሪያውያን ወንጌልን ከተቀበሉ መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር እንደተፈጠረና እኩል ዋጋም እንዳለው በሚያስተምረው ትምህርት እንዲሁም በሥራ ባሕላቸው ላይ ታላቅ አምንታዊ ተጽዕኖ እንዳመጣ ይናገራሉ።[121]

ክርስትና የኮሪያውያንን የሥራ ባሕል በከፍተኛ ሁኔታ እንዳነቃቃና ሁለንተናዊ የለውጥና የዕድገት ራእይ አንግቦ እንዲነሡ እንዳስቻላቸው ዛሬ የደረሱበት ሁለንተናዊ ፈጣንና አስደናቂ ዕድገት ምስክር ነው።

ክርስትና ለደቡብ ኮሪያ ኢኮኖሚ ዕድገት

እ.ኤ.አ ከ1962 ወዲህ የደቡብ ኮሪያ ኢኮኖሚ በአማካይ አርባ ሺህ /40,000%/ እንዳደገ መረጃዎች ይጠቁማሉ።[122] ለዚህ አንጸባራቂና "ምትሃታዊ"

[118] S.Hun Kim and Wonsuk Ma (Eds) , (2011), Korean Diaspora and Christian Mission, Regnum Books International,Uk p 228
[119] Ibid, p 228
[120] Ibid, p 230
[121] *http://en.wikipedia.org/wiki/Christianity_in_Korea*
[122] *"Since 1962 the nation's GDP has gone up about 40,000%, making it the world's 13th largest economy." http://www.time.com/time/magazine/article/0,9171,2094427-2,00.html ተጨማሪ ኢ.ትሺ፣ ሚዲያ ዳሰሳ (The Times) መጽሔትን ጠቅሶ አሐድ ማለዳ ጥቅምት 5 ቀን 2005 ዓ.ም ሰፊ ዘገባ በዚህ ላይ አቅርቦ ነበር።*

የኢኮኖሚ ፍንዳታ የእግዚአብሔር እጅ እንዳለበት ኮሪያውያን ብቻ ሳይሆኑ ልዩ ጥናት ያደረጉ የዓለማችን ዕውቅ ኢኮኖሚስቶች ሳይቀሩ መስክረዋል። ኢ.ኤ.አ በ2003 ሮበርት ባሮ እና ራሄል ማክክሊሪ የተባሉ የታወቁ የሀርቨርድ ዩንቨርሲቲ የኢኮኖሚ ጠበብት፦ *"ክርስትና በደቡብ ኮሪያ የኢኮኖሚ ዕድገት ቀዳሚ ሚና ተጫውቷል"*[123] በማለት በአንዳንድ ኢኮኖሚስቶች ዘንድ ያስተቻቸውን አስተያየት ለመስጠት ተገደዋል።

ክርስትና አላዋቂዎች እንደሚያስቡት፣ እንደሚገምቱትና እንደ ሚናገሩት ሜዳዊ ሥርዓትና ልበወለድ ሃይማኖታዊ ወግ አይደለም። ዓይናቸው ያልበራ ሰዎችና በራሳቸው የማይተማመኑ ሰዎች የመደቂበያ ዋሻም አይደለም። የሥራ ፈቶች፣ የስነፎችና የማሰብ ችግር ያለባቸው ምስኪኖች የተሰበሰቡበት ካምፕም አይደለም። የኮሪያ ኢኮኖሚ አስገራሚ ምጥቀት በዩንቨርሲቲዎች ከሚሰጠው የኢኮኖሚክስ የቀመር ዕድገት ውጭ እንደሆነ ምሁራን እንደ ተነጋገሩበት እሙን ነው። ከዚህም የተነሣ ምሁራኑ በቀመራቸው ውስጥ የሌለ የኢኮኖሚ ዕድገት ሲገጥማቸው የእግዚአብሔርን ስም ለመጥራት አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ገብተዋል። አንዳንድ ሃይማኖተኞች እንደሚሉት የክርስትና ፋይዳ ከሞት ወዲያ ላለው ሕይወት ብቻ አይደለም። በእውነተኛ ክርስትና ሕይወታቸው የተለወጡ ሰዎች በአገራቸው ሁለንተናዊ ሕዳሴና ዕድገት ዐቢይ ሚና እንደሚጫወቱ ዕድሜ ጠገቡ ሕያው መጽሐፍና የደቡብ ኮሪያ የዕድገት ታሪክ ምስክሮች ናቸው።

"ኮሪያውያን ለወንጌል ለመሞት ይፈልጋሉ"

ኢ.ኤ.አ በ2006 ኪም ሱን የተባለ የ30 ዓመት ወጣት የደቡብ ኮሪያ ዜጋ የሆነ ሚሽነሪ የጦር አውድማ ወደሆነችው የኢራቅ ዋና ከተማ ባግዳድ የሰላም ወንጌል ይዞ እንደገባ በሃይማኖት ጽንፈኞች እጅ ወድቆ ስለወንጌል ወዲያው አንገቱን በስይፍ እንደ ተሰየፈ የዓለም መገናኛ ብዙኃን በሰፊው የዘገቡት ጉዳይ ነው።

> ***የኮሪያ ሚሲዮናውያን ለወንጌል ለመሞት በብርቱ ይፈልጋሉ።***
> *ሚስተር ሙኒ የኮሪያ ጥናት ኢንስቲትዩት መሪ*

ከዚህ እንደምንረዳው ለኮሪያውያን ክርስቲያኖች ክርስትና ለእነርሱ የመባረኪያ መንገድ ብቻ ሳይሆን በትልቅ ደስታ ሕይወታቸውን አሳልፈው የሚሰጡበት መንገድ እንደሆነ እንመለከታለን። እዚህ ጋ ልናስተውለው የሚገባው ጉዳይ ለወንጌል ብለው ለመሞት እንጂ ለወንጌል ብለው እንደ አንዳንዶች ሰውን ለመግደል የሚፈልጉ እንዳልሆነ ነው።

[123] *http://www.economics.harvard.edu/faculty/barro*

ደቡብ ኮሪያውያን በዓለም በምን ይታወቃሉ?

1. *ደቡብ ኮሪያ በዓለማችን ብዙ የወንጌል ሚሲዮናውያንን ወደ ተለያዩ አገሮች በመላክ ከአሜሪካ ቀጥላ ሁለተኛ አገር ናት።*[124]
2. *ደቡብ ኮሪያ የዓለማችን ግዙፍ ኢኮኖሚ ባለቤት ሆና በ8ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ይህ ዕድገት ላለፉት 40 ዓመታት ዕድገት ብቻ እንደሆነ አንዘንጋ።*
3. *ደቡብ ኮሪያ በዓለማችን ፈጣን የኢንተርኔት ዳውንሎድ ስፒድ 32.45 Mbit/s. በመጠቀም ሁለተኛ አገር ናት።*[125] *የ5G ኔትወርክ ብቸኛ ተጠቃሚ ለመሆን 1.5 ቢሊዮን ዶላር ፕሮጀክት ለመጀመር ወስናለች። ይህም አሁን በጣም ፈጣን ተብሎ ከሚወሰድ 4G LTE ኔትወርክ ከ1000 እጥፍ በላይ ፍጥነት እንደሚኖረው ታምኖበታል። ደቡብ ኮሪያ የዚህ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ከሆነች በዚያች አገር ዳውንሎድ የማድረግ ፍጥነት በሰከንድ 1000 ሜጋ ባይትስ ሊደርስ ይችላል።*
4. *የደቡብ ኮሪያ ሳምሳንግና ኤልጂ የሞባይል አምራች ካምፓኒዎች በዓለማችን ምባይልን ከሚያመርቱ ቀዳሚ ካምፓኒዎች ዋነኞቹ ሲሆኑ ኢ.ኤ.አ በ2010 በዓለም የሁለተኝነት ደረጃን አግኝተዋል።*[126] *ኢ.ኤ.አ 2013 ሳምሳንግ ጋላክሲ 4 የተሰኘው ስማርት ስልክ በዓለማችን አንደኛ ስልክ ሆኗል።*[127]
5. *ደቡብ ኮሪያ ከ100,000 ለሚበልጡ የውጭ አገር ተማሪዎች ነፃ የትምህርት ዕድል በመስጠት በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎቿ ታስተምራለች።*[128]
6. *የደቡብ ኮሪያ ተማሪዎች በዓለም ላይ "Problems Solving" አንደኛ በሒሳብ ሦስተኛ በሳይንስ ሰባተኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ።*[129]
7. *ደቡብ ኮሪያ ከመዋዕለ ሕፃናት እስከ ዩንቨርሲቲ የመማር ማስተማሩን ሂደት ሙሉ በሙሉ ኮምፒዩተራይዝድ በማድረግ የብዕር፣ የደብተር እንዲሁም የመጽሐፍ አገልግሎት ከትምህርት ቤት እንዲሰናበት በማድረግ የዓለማችን ቀዳሚ አገር ናት።*
8. *ደቡብ ኮሪያ በዓለማችን አምስተኛ ከኤስያ ሁለተኛ የኒውክለር ኃይል አምራች አገር ናት።*[130]
9. *የደቡብ ኮሪያ ኢኮኖሚ የተመሠረተው በዓለም አቀፍ ንግድ ላይ ሲሆን ኢ.ኤ.አ በ2010 በዓለማችን ብዙ የፋብሪካ ውጤቶችን ወደ ውጭ በመላክ በዓለም ስድስተኛ ስትሆን ዕቃዎችን በማስገባት አሥረኛ አገር ናት።*
10. *የደቡብ ኮሪያ ኢኮኖሚ የኤስያ ነብሮች የሚል ቅጽል ስም ከተሰጣቸውና በአስደማሚ ዕድገት ላይ ከሚገኙ አገሮች ቀዳሚውን ሥፍራ ይይዛል።*

[124] *Christianity Today.* (2009) Christianity Today International..
[125] Retrieved February 12, 2012.
[126] *International Data Corporation, January 29, 2010.*
[127] *http://www.ibtimes.com/samsung-galaxy-s4-release-date-approaches-phone-ranks-no-1-antutu-quadrant-benchmarks-photos-1157903*
[128] *Education-blog.net. August 28, 2008. http://www.education-blog.net/2008/08/28/south-korea-now-open-for-foreign-students/*
[129] *Pisa.oecd.org. http://www.pisa.oecd.org/. Retrieved February 18, 2010.*
[130] *The Diplomat. July 19, 2010. http://the-diplomat.com/2010/07/19/another-korean-nuclear-issue/*

11. አ.አ.አ ማርች 2011 ደቡብ ኮሪያ "ቲ - 50 ወርቃማው ንስር" በሚል ስያሜ ጀት አምርታ ለኢንዶኔሽያ ለማቅረብ የተፈራረመች ሲሆን ይህም በኤስያ የመጀመሪያዋ ሱፐርሶኒክ ጀት ላኪ አገር ያደርጋታል::[131]

12. የደቡብ ኮሪያ ፋብሪካዎች አውቶሞቢሎችን፣ ከባድ ማሽነሪዎችን፣ መርከቦችን፣ ሮቦቶችንና የኤለክትሪክ ዕቃዎችን በማምረት ከዓለም ስመጥር ፋብሪካዎች ተርታ ይሰለፋሉ::

13. ደቡብ ኮሪያ የዓለማችንን የመጀመሪያ በኤልክትሪክ የሚሠራ ባስ ለአገልግሎት አብቅታለች:: ይህ ድንቅ የተባለ የኮሪያ የኤሌክትሪክ ባስ ኔትወርክ በተወሰነ ሥፍራ በትቀመጡ የኤሌክትሪክ ቻርጅ ማድረጊያዎች የሚጠቀም አይደለም:: ሲስተሙን ድንቅና አስገራሚ ያስባለው ባሶቹ እንዲንቀሳቀሱ በተመረጠባቸው መንገዶች ላይ ሲያልፉ በገመድ አልባ ቴክኖሎጂ (Wi-fi) ኤሌክትሪክ የሚያቀብሉ የኤሌክትሪክ ክብሎች በመተከላቸው ነው::[132]

14. ደቡብ ኮሪያ በኢኮኖሚ በልጽገው ዓለምን እየመሩ ካሉና G-20 የሚል መጠሪያ ከተሰጣቸው አገሮች አንዷ ናት::

የአገራችን መንግሥት የኮሪያን ዕድገት በምሳሌነት በመውሰድ እንደ ኮሪያ በአጭር ጊዜ ማደግ ይቻላል! ብሎ እንደ ተነሣ የታወቀ ነው:: ይህም ትልቅ እይታ ነው:: የዕድገታቸው መሠረት ካደረጉት አንዱ ፈሪሃ እግዚአብሔር እንደሆነ መዘንጋት የለበትም::

ለደቡብ ኮሪያ የጠቀመው ክርስትና ለኢትዮጵያ ለምን?

መንግሥታችን ኮሪያን በምሳሌነት ከወሰዳት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በ100 ዓመት የወንጌል ዕድሜዋ ዓለምን በወንጌል በማጥለቅለቅ ላይ ካለችው የኮሪያ ቤተ ክርስቲያን ለመማር ትፈቅድ ይሆን? ክርስትናን በዓለም ላይ ካለው ከየትኛውም ፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለምና ሥርዓት ጋር ማያያዝ ትልቅ ስህተት ነው:: ምክንያቱም የተለያየ የፖሊቲካ ትንታኔዎችና ሥርዓቶች ጊዜያዊ ሲሆኑ ክርስትና ግን በተለያየ የፖሊቲካዊ ትንታኔዎችና ሥርዓቶች በሚኖሩት ሰዎች ሕይወት የሚሠራ ዘመን ዘለቅ መለኮታዊ መልዕክት ነው:: ክርስትና ስለጠቀማቸው አንዳንድ አገሮች ስናነሣ በተለያዩ ሥርዓቶችና የፖሊቲካ ርዮተዓለም አሳቢዎች መካከል በወንጌል እውነት ላይ የቆሙት ቤተ ክርስቲያን በሰዎች አጠቃላይ አመለካከት ላይ ያመጣችውን አዎንታዊ ተጽዕኖና ውጤት ለማመልከት እንጂ የፖለቲካዊ ፍልስፍናቸውን ትክክለኝነት ለማመልከት እንዳልሆነ መታወቅ አለበት:: ለኮሪያ የኢኮኖሚ

131 http://www.thejakartaglobe.com/home/korea-aerospace-signs-deal-to-sell-trainer-jets-to-indonesia/443285

132 አዲስ ጉዳይ፣ ቅጽ 7፣ ቁጥር 178 ነሐሴ 2005 ዓ.ም. ገጽ 32

ምጥቀት ባለፉት መቶ ዓመታት የተሰበከባት ክርስትና እንደጠቀማት ገሃድ የወጣ እውነት ነው::

በክርስቶስ የማያምኑ ምሁራን ሳይቀሩ በኮሪያ ኢኮኖሚ ክርስትና ያደረገውን ታላቅ አዎንታዊ ተጽዕኖ ያለፍርሃት ለዓለም ለመመስከር ተገደዋል:: ለ2000 ዓመታት በኢትዮጵያ የተሰበከ "ክርስትና" ለምን ተመሳሳይም ባይሆን እንኳ ተቀራራቢ ለውጥ እንድናመጣ አላገዘንም? በኮሪያ ላለፉት መቶ ዓመታት የተሰበከው ወንጌልና በኢትዮጵያ ለሁለት ሺ ዓመታት ከተነገረን ሃይማኖት ጋር አንድ ይሆን? ኮሪያውያን በ70 ዓመታት በዓለም በሁሉም ቀዳሚ እንዲሆኑ ወንጌል ዐቢይ ሚና ከተጫወተ ለ2000 ዓመታት ለኢትዮጵያውያን ከተነገረን ሃይማኖት የተለየ ይሆን? ዛሬም አንዳንዶች ይህን እያዩ እንደተለመደው የቀደሙና ከሁሉ የተሻሉ እንደሆኑ ይሰብኩን ይሆን? የኢትዮጵያ ክርስትና ተሐድሶ ያስፈልገዋል የተባለው አንዱ ከዚህ የተነሣ ነው:: ልብን ያልለወጠ ክርስትና ለለውጥና ለዕድገት ሰው እንዳይነሣ ወደ ታች የሚጫን ባዶ ሃይማኖታዊ ሸክም ነው:: ባዶ ሃይማኖት ለምድርም ሆነ ለሰማይ ሕይወት አይጠቅምም::

የኮሪያ ቤተ ክርስቲያን በመቶ ዓመት ዕድሜዋ ሃያ ሁለት ሺ ድንበር ዘለል ሚሲዮናውያንን ወደ አንድ መቶ ሰባ አገሮች ልካ፤ ከአስራ አምስት ዓመታት በኋላ ደግሞ መቶ ሺ የወንጌል ሚሲዮናውያንን ለመላክ በብርቱ ጥረትና ዝግጅት ላይ ትገኛለች፤ የሁለት ሺ ዓመታት ዕድሜ ያስቆጠረች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ዲያስፖራን እንደ ከብት ጭራ እየተከተለች ለእነርሱ ብቻ የምትሆን ባሕላዊና በአገር ቤት አውድና ስም ቤተ ክርስቲያን በመክፈት ላይ የተጋች ትመስላለች:: እነርሱም ቢሆኑ ሌላውን በወንጌል መድረስ ቀርቶ ለራሳቸውም በመንደርተኝነት መንፈስ ተለክፈው በመበጣጠስና በመታመስ ላይ እንደሚገኙ ይነገራል:: ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በአንድ መጣጥፉ በአውስትራሊያ የኢትዮጵያውያንን ቤተ ክርስቲያን አሳዛኝ ሁኔታ እንዲህ አስነብቦን ነበር:-

> አንዳንዱን አበሻ ተባበር ከምትለው ተሰቀል ብትለው ይሻለዋል:: ሁሉም በየጎጡና በየሠፈሩ ነው:: አብዛኞቹ ቤተ ክርስቲያኖች እንኳን ዘርን መሠረት ያደረጉ ናቸው:: የአማራውን፣ የትግሬውን፣ የኦሮሞውን፣ ቤተ ክርስቲያን ትለየዋለህ:: ትግሬውም አንድ መሆን እያቃተው አድዋ፣ ሽሬ ሲል ታገኝዋለህ:: አማራው ወልቃይት፣ ጎንደር እየተባለ ሰብቻው ቸርች ይከፍትልሃል:: ...በውጭ ያለው ዳያስፖራ ስለ ኤርትራ መገንጠል ሁልጊዜ እየተንገበገበ ያወራል:: እርሱ ግን ራሱ በፈቃዱ ያለ ሪፈረንደም ተገንጣጥሏል::[133]

ኤፍሬም እሸቱም በአሜሪካ የኢትዮጵያውን ቤተ ክርስቲያንን ሁኔታ ሲገልጽ:-

> በዲሲ አካባቢ 20 የሚደርሱ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ቢኖሩም አንድነት እንደሌላቸውና የኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብ እንደ ግሪኮች፣ ቪየትናሞች፣ ግብጾች፣ ሕንዶችና የደቡብ እስያ ሕዝቦች የመቻቻል ባሕል ያለማዳበራቸው እንደሚገባ ተሰሚነት እንዳላጣቸው ይገልጻሉ:: "ቤተ

133 አዲስ ጉዳይ፣ ቅጽ 7፣ ቁጥር 180 ቅዳሜ 2005 ዓ.ም ገጽ 32

ክርስቲያን የልዩነት ቦታና ምልክት መሆኗ 'በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኗል"[134] ብለዋል።

የሁለት ሺ ዓመት መንፈሳዊነታችን ወንጌልን ለሌሎች ማቀበል ቀርቶ ክልብ ተቀባብለን በአንድነት እንድንኖር እንኳ አላስቻለንም። ከእርስ በርሱ ያልታረቀ ሕዝብ ዓለምን ከጌታ ጋር ማስታረቅ በፍጹም አይችልም። አብረንም ሆነ ተለያይተን መኖር የማንችል እንደሆን የሚነገርብንን ክፉ እርግማን በቃሉ እውነት ላይ ቆመን መስበር አለብን። ለዚህ መፍትሔው ተሐድሶ ነው። በሌላው ዓለም አዉድ ተገልጠው ቤተ ክርስቲያን የሚተክሉ የወንጌል ድንበር ዘለል ሚሲዮናውያንን በጥራትና በብዛት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የምትልከው መቼ ይሆን? ታዲያ ይህን ለመሥራት ከሁሉ ቀድማ ከሁሉ ኋላ የቀረችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ አያስፈልጋትም ማለት እንዴት እንችላለን?

ክርስትና ለቻይና የኢኮኖሚ ምጥቀት

እ.ኤ.አ በ1970ዎቹ መጀመሪያ ማኦ ከቻይና የአብዮት መሪነት ወደ ሕጋዊና ብቸኛ የቻይና ሃይማኖት የተሻገረበት ዘመን ነበር። የቻይና ባሕላዊ ሃይማኖቶች ዳዮይዝም፣ ኮንፈሽኒዝም፣ ቡድሂዝም ከክርስትናና ከእስልምና ጋር በፍጹም ታገዱ። የተለያዩ መቅደሶች ተዘጉ፣ ፈረሱ፤ ቤተ ክርስቲያናት ወደ ፋብሪካነትና ወደ ትምህርት ቤትነት ተቀየሩ፤ መነኮሳትና ካህናት ወደ ጉልበት ሥራ ማዕከልና ወደ ወህኒ ተላኩ። በማኦ የሕይወት ዘመን የኮሚኒስት ፓርቲ ብቸኛና ሕጋዊ ማዕቀፍ የተበጀለት ኃይለኛ ሃይማኖታዊ ድርጅት ሆኖ ነበር። *የኮሚኒስት ፓርቲው በመንገዱ ላይ የቆሙትን ሁሉ የማጥፋት ዓላማ አንግቦ ይጓዝ ነበር።*[135] ከማኦ ሞት በኋላ በዓለም አቀፍ ደረጃ በኮሚኒዝም ርዕዩተዓለም ላይ የመጣው ነውጥ የቻይናን ኮሚኒዝም ፓርቲ ሙሉ በሙሉ ባይለውጥም በብዙ ነገሮች ላይ ጥገናዊ ለውጥ ለማድረግ ተገደዋል። ከዚህም የተነሣ ታላቅ የሃይማኖት መነቃቃት በቻይና በመካሄድ ላይ ይገኛል። በዚህ ታላቅ የእምነት መነቃቃት ዘመን ላይ የቻይና ክርስቲያኖች ወንጌልን በማስራጨት ብቻ ሳይሆን በሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት ዐቢይ ሚና በመጫወት ላይ እንደሚገኙ የአደባባይ ምስጢር እየሆነ ነው። ክርስቶፊር ላንደው የቢቢሲ ዜና ዘጋቢ በቻይና ዊንዞአ ግዛት ስለሚገኘው *Wenzhou's Christian entrepreneurs* እንዲህ ዘግበዋል። በቻይና ኢኮኖሚ ዕድገት ቁልፍ ሚና እየተጫወቱ ካሉት ፋብሪካዎች አንዱ በዊንዞአ ግዛት የሚገኝ በአንድ ክርስቲያን ባለሀብት ተመሥርቶ ክርስቲያን ሠራተኞች በብዛት ያሉበት ፋብሪካ ነው። የፋብሪካው ዋና ሥራ አስኪያጅ ውንግጅን ዋኡ */Weng-Jen Wau/* ይባላል። ስለ ፋብሪካው ሲናገሩ፦

[134] አዲስ ንዳይ፣ ቅጽ 6፣ ቁጥር 134፣ ጥቅምት፣ 2005 ዓ.ም፣ ገጽ 33
[135] *INDEX, vol 33. No 4. 2004. Issue 213. p.201*

ፋብሪካችን በየወሩ 5 ሚሊዮን ዶላር የሚገመት ምርት ለገበያ ሲያቀርብ ከዚህም ውስጥ 40% ለውጭ ገበያ ነው። ሠራተኞቻችን አብረው መጽሐፍ ቅዱስ ያነባሉ ይጸልያሉ። በክርስቲያን ሠራተኞች ላይ ከሌሎች የላቀ የሥራ ፍላጎት፣ ብርታትና ውጤታማነት ይታይባቸዋል። በተሰየ የሥራ ሥነ ምግባር የታነጹና ኃላፊነት የሚሰማቸው ስለሆኑ በፋብሪካችን እንዲሠሩ ለክርስቲያኖች ቅድሚያ እንሰጣለን፣ ብለዋል።

የቻይና ወርልድ ሪሊጅን ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር ፕሮፌሰር ዜሆ ዚንፒንግ ሲናገሩ፦

በቻይና ኢኮኖሚ ላይ ክርስቲያኖች እያመጡ ስላለው አዎንታዊ ጫና መካድ በፍጹም አይቻልም በማለት ክርስቲያኖች ለቻይና ኢኮኖሚ ዕድገት እየተጫወቱ ስላለው አዎንታዊ ሚና መስክረዋል። እንዲሁም ጎበረተሰቡ ከእነርሱ ልዩ የሥራ ባሕል እንደ ወረሰና ክርስትና ለምዕራባውያን ዕድገት ምክንያት እንደሆነ ለማረጋገጥ እንደቻሉም ይናገራሉ።[136]

የቻይና ከሚኒስት መንግሥት የምዕራባውያን የወንጌል ሚሲዮናውያንን ከአገር በማባረር፣ ቤተ ክርስቲያንን በመዝጋትና ቅዱሳንን በማሰር ላለፉት ስልሳ ዓመታት በዓለማችን ተወዳዳሪ ያልተገኘለት መንግሥት ነው። በአሁኑ ጊዜ በቻይና ሕጋዊ እውቅና ተሰጥቶአቸው በእንቅስቃሴ ላይ የሚገኙ የቫቲካንን የበላይነት የማትቀበልና 12 ሚሊዮን አባላት እንዳሳት የተገመተው የቻይና ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፣[137] እና ለርዕዮተዓለሙ እውቅና የሰጡ አንዳንድ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ሲሆኑ አብዛኛው ወንጌላውያንና በመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ላይ የሚያተኩሩ አብያተ ክርስቲያናት ለኮሚኒስት ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያና ሕጎች እውቅና መስጠት እንቢ ስላሉ የቤት-ቤተክርስቲያን ሆነው በከፍተኛ ሁኔታ በመብዛት ላይ እንደሚገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ሕጋዊና ገዛዳዊ የመሰብሰብ መብት የሌላት የቻይና ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት ላይ እያመጣች ካለው አዎንታዊ ተጽዕኖ የተነሣ የቻይና መንግሥት በክርስትና ላይ ያለውን አሉታዊ አቋም በመለወጥ ላይ ይገኛል። የቻይና መንግሥት የቻይና ክርስቲያኖች በብዛት በሚገኙበት አካባቢ ባሉት የክርስቲያን ኢንዱስትሪዎች የስኩቱ ምስጢር ምን እንደሆነ ለማወቅ ጥናት አድርጓል። ውጤቱም በአንድ ክፍለ አገር በ19ኛዎቹ የምዕራቡ ዓለም ሚሲዮናውያን በዚያ አካባቢ እንደኖሩ፣ ወንጌልን እንደሰበኩና በሕዝቡም የሥራ ባሕል ላይ ከፍተኛ አዎንታዊ ተጽዕኖ እንደፈጠሩ ያመለክታል።

በተጨማሪም ብዙ የቻይና የኮሚኒስት ፓርቲ አባላት፣ ዕውቅ የአገሪቷ ምሁራንና ባለሀብቶች ሳይቀሩ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች እንደሆኑ በገሃድ በመመስከር ላይ እንደሚገኙ ይነገራል። በ21ኛው ክፍለ ዘመን ቻይናውያን በኢኮኖሚ ዕድገትና ዲጂታል ቴክኖሎጂ ምጥቀት ብቻ ሳይሆን ወንጌልን ለዓለም ሕዝብ በኃይልና በሥልጣን በመስበክ ቀዳሚ ይሆናሉ

[136] Christopher Landau *(26 August 2010) BBC News, Christian faith plus Chinese productivity.*
[137] TIME, MAY 2006 p.25

ተብለው ይጠበቃሉ። የቻይኒዝ ቋንቋ ማወቅ ወሳኝ የሚሆንበት ጊዜ ላይ እየደረስን ነው። ብዙ የአሜሪካና የአውሮፓ ሕፃናት ቻይንኛ በማጥናት ላይ እንደሚገኙም ይነገራል።

ይህ ማለት የኢኮኖሚ ዕድገት ብቻውን ዋናና ብቸኛ ነገር እንዳልሆነ መታወቅ አለበት፤ ቻይና የግለሰቦችን የእምነትን ነፃነት በማፈን በዓለም ላይ የታወቀች ስትሆን የትኛውም አገር ይህን መጥፎ ምሳሌነት መከረጅ የለበትም። እንደ ስትራትስፎር ያተባለ ተቋም ከሆነ የቻይና ኢኮኖሚ የተገነባበት መሠረት ጠንካራ ባለመሆኑ ውድቀቱ እይቀሬ እንደሆነ ይናገራሉ።

የቻይናውያን ዓለምን በወንጌል የመድረስ ራእይ

ከ40 ዓመት በላይ ስለጌታ የታሰረና ከ20 ሚሊዮን አባላት በላይ ያላት ቤተ ክርስቲያን መሪ የሆነ ፒተር ዙ ዮንግዝ ሲናገር:- *"የራሳችን የምንላቸውን ትናንሽ አስተምህሮዎች በመከተል ለመጽናት አንፈልግም። አንዳችን ከሌሎቻችን ብርታት ለመማር፣ ብርቱዎችና ለኢየሱስ የቀረብን እንሆን ዘንድ እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ ለመለወጥ ፈቃደኞች ነን" ብሏል።* የቻይና የቤት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን በመከራ እቶን መካከል ቆማ ያበበች ናት። በክርስቶስ ቤዛነት ድነው የተለወጡ ክርስቲያኖችም ለአገራቸው ኢኮኖሚ ዕድገት የበኩላቸውን ወሳኝ ሚና በመጫወት ላይ ያሉ ባለ ራእዮች ናቸው።

ፒተር ዙ ዮንግዝ ከላይ በጥቅሱ እንደገለጸው የቻይና ቤተ ክርስቲያን ዕድገት ሚስጢር ለአዎንታዊ ለውጥ ዝግጁ መሆኗ፣ በጠባብነት ከመታጠር ይልቅ ከሌላው ለመማር ፈቃደኛ መሆኗና ለክርስቶስ ወንጌል የትኛውንም ዋጋ ለመክፈል መዘጋጀቷ ነው። በብዙ መከራ፣ ድህነት፣ መገፋትና አደገኛ ስደት መካከል ያበበች የቻይና ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የ21ኛውን ክፍለ ዘመን ዓለም በወንጌል የሚለውጥባት መሣሪያ እንደምትሆን ብዙዎች ያምናሉ። ለዚህም ዋቢ የሚሆነን የቻይና ቤተ ክርስቲያን አንግባ የተነሣችውን ትልቅ ራእይ ማየቱ ብቻ በቂ ይመስለኛል። እስከ ዛሬ ድረስ ሕጋዊ ዕውቅናና ከለላ የሌላት ከመቶ ሚሊዮን በላይ አባላት ያላት የቻይና የቤት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ከተለመደውና ከጥቃቅን የሰፈር ራእይ ተፋታ *"ወንጌልን ወደ ኢየሩሳሌም እንመልስ"* በሚል ታላቅ ራእይ 100,000 /መቶ ሺህ/ በመከራ ትምህርት ቤት የተሠሩ ሚስዮናውያንን ለወንጌል ሥራ በዓለም ሁሉ መላክ ጀምራለች። ከዚህም የተነሣ ብዙ ቻይናውያን ዐረብኛና እንግሊዝኛን በከፍተኛ ሁኔታ በማጥናት ላይ እንደሚገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ።[138] የዕድሜና የቀኖና ባለጠጋ የሆነችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከቻይና የቤት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ራእይ ምን ትማር ይሆን?

[138] *ፓውል ሀታዊይ (ተርጓሚ ላበቁቸው ፋንታሁን) (1997 ዓ.ም) ፤ ወንጌል ዳግም ወደ ኢየሩሳሌም፣ ራእይ አሳታሚ፣ አዲስ አበባ ገጽ 119*

እንደ ፕሮፌሰር ፒተር ዋግነር እ.ኤ.አ በ2025 የቻይና ቤተ ክርስቲያን በዓለም ላይ ብዙ ሚስዮናውያንን በመላክ ቀዳሚና የቀጣዩ ዓለም የክርስቲያን ማዕከል እንደምትሆን በእርግጠኝነት ይናገራሉ።

ቻክ ፕራይስ የተባሉ አሜሪካዊ ነቢይ "*God's Unfolding Battle Plan*" በሚለው መጽሐፋቸው:-

> *እ.ኤ.አ በ2016 የዓለም ኢኮኖሚ የበላይነት ለመቆናጠጥ ተራው ይደርሳቸዋል፤ በ2026 ቻይናውያን በዓለማችን ላይ ቀዳሚ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሕዝቦችና ታላቁን መንፈሳዊ መከር ለእግዚአብሔር ከብር የሚሰበስቡ መሣሪያዎች ይሆናሉ፤ በማለት ተንብየዋል።*[139]

በርቲ አረንድስ የተባለ የቄሊ ስትሪት ጆርናል የዓለም ገበያ አጥኚ ጋዜጠኛ እ.ኤ.አ አፕርል 25 2011:- *የአይ.ኤም.ኤፍ ዋሽ የሆነች የአሜሪካ የኢኮኖሚ የበላይነት ማብቂያ ዘመን ላይ ደርሰናል። የቻይና ኢኮኖሚ የአሜሪካን ኢኮኖሚ የበላይነት እ.ኤ.አ በ2016 ሳይረከብ አይቀርም።*[140] በማለት በቻክ የተነገረውን ትንቢት አጠናክሮታል።

የቻይና ሁለንተናዊ ለውጥ በመስቀል

ፕሮፌሰር ፒተር ዋግነር አንድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል አምኖ የዳነ የቻይና ኢኮኖሚስትን በዚህ ጉዳይ ላይ አነጋግሮ የቻይና ኢኮኖሚ እ.ኤ.አ 2016 ሳይሆን በ2020 በዓለም አንደኛ ለማድረግ በብርቱ ሥራ ላይ እንዳሉ እንደተነገራቸው በድረ ገጻቸው ላይ አስታውቀዋል። በ2016 ሆነ በ2020 ቻይና በኢኮኖሚ የዓለማችን አንደኛ የምትሆንበት ዘመን በደጃችን እንዳለ አመልካች ነው። ከዚህም አስደናቂ ዕድገት ጀርባ ትልቅ መለኮታዊ አጀንዳ አለ። ፕሮፌሰር ፒተር ዋግነር በማርች 2012 ለአገልግሎት ወደ ቻይና በሄዱ ጊዜ የቤጅንግ ዩኒቨርሲቲ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ፕሮፌሰርና የሳይፐርስ ሊደርሽፕ ኢንስቲትዩት ፕሬዝዳንት *Peter (Xiao) Zhao (pronounced "Chow")* ጠንካራ ክርስቲያን፣ የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ አባል እንደሆነ ገልጸው ምስክርነቱን እንዲህ አስፍረዋል:-

> *ብዙ የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ አባላት ወደ ጌታ እየመጡ ነው። እምነታቸውም ለሁሉም እየታወቀ ነው። አሁን ያለውን 7% የቻይና ክርስቲያኖች ቁጥር "2030 ቪዥን" የሚል ራእይ ይዘን በመነሣት እ.ኤ.አ በ2030 30% ቻይናውያን ክርስቲያን እንዲሆኑ በትልቅ ትጋት እየሠራን ሲሆን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ በአዋጅ የክርስቲያን ስደት በቻይና ሙሉ በሙሉ ይቆማል ብዬ አምናለሁ። በ2030 ቻይና በዓለም ላይ በክርስቲያን ሕዝብነት በዓለም ላይ ትታወቃለች። "China of Tomorrow will experience*

[139] Chuck D. Pierce, (2007) *God's Unfolding Battle Plan: A Field Manual for Advancing the Kingdom of God* (Ventura CA: Regal books), pp. 211-216.

[140] *"The International Monetary Fund has just dropped a bombshell, and nobody noticed. For the first time, the international organization has set a date for the moment when the 'Age of America' will end and the U.S. economy will be overtaken by that of China. And it's a lot closer than you may think. According to the latest IMF official forecasts, China's economy will surpass that of America in real terms in 2016-just five years from now." **Brett Arends (2011): MarketWatch of the Wall Street Journal dated April 25,***

"transformation with the Cross!" የቻይና የነገ ለውጥ በክርስቶስ ሊየሱስ የመሰቀል ሥራ አውን ይሆናል፣ ብለዋል።

እ.ኤ.አ 2000 የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ በአገሩ ለኢኮኖሚክስ ፕሮፌሰር ዙሀ ቹአ (Zhao Xiao) "የአሜሪካን ኢኮኖሚ ስኬት ምስጢር" ጥናት እንዲያደርግ የቤት ሥራ ሰጠ። በጊዜው ምሁሩ አማኝ አልነበረም። ምሁሩም "እግዚአብሔር የቦርዱ ሊቀ መንበር ነው" የሚል አነጋጋሪ ጽሑፍ አቀረበ። ከዚያም *"ቤተ ክርስቲያን ያለችበት የገበያ ኢኮኖሚና ቤተ ክርስቲያን አልባ የገበያ ኢኮኖሚ"*[141] በሚል ርዕስ የመጨረሻ ጽሑፍ ይፋ አደረገ።

በጥናቱም የአሜሪካ የኢኮኖሚ ምጥቀት ምስጢር በእግዚአብሔር አውነተኛ ቃል ላይ በመቆማቸው፣ ከሙስና የፀዱ በመሆናቸው፣ ለእርስ በርሳቸው ያላቸው ቤተሰባዊ ፍቅርና በወንጌል ሥነ ምግባር በታነጹ ክርስቲያን ባለ ራእይ አባቶች በመመራታቸው መሆኑን በዝርዝር አመለከተ። ዶክተር ዙሀ ቹአ ለመንግሥት ጥናቱን ይፋ ካደረገ በኋላ እ.ኤ.አ 2002 በገሃድ ክርስቶስ ኢየሱስን ተቀብሎ ተጠመቀ።[142]

ኮሚኒስቱ የቻይና መንግሥት ለሃይማኖት ያለው አሉታዊ ሕግና የተቀነባበረ ሜራ የቻይናን ቤተ ክርስቲያን እንዳትበዛና ዓለም አቀፋዊ ባለ ራእይ ሆና እንዳትነሣ ሊያግዳት አልቻለም። ራእይ ካለ መንገድ አለ። የቻይና ቤተ ክርስቲያን የጨለማና የስደት ዘመን መደምደሚያና በኃይል የመገለጥ ዘመን መግቢያ ላይ ትገኛለች። የቻይና አማኞች ዓለምን በክርስቶስ ወንጌል ለመድረስ ያላቸው የራእይ ትልቅነት፣ እምነትና እርምጃ እጅግ በጣም ያስደንቃል። በመንገድ ሥራ፣ በንግድና በኢንዱስትሪ፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በዩኒቨርሲቲዎች ለማስተማር ብዙ ቻይናውያን ወደ አገራችን በመጉረፍ ላይ ይገኛሉ። እንዲሁም በቅርብ ጊዜ የቻይና የወንጌል ሚሲዮናውያን በአገራችንና በመላው ዓለም ሁሉ በልዩ የአገልግሎት ራእይ ይገለጣሉ ተብለው ይጠበቃሉ።

ከቻይና ክርስትና ምን እንማራለን?

ለሁለት ሺ ዓመታት በኢትዮጵያ የቆየው "ክርስትና" ሰዋዊ ሥርዓትና ወግ ከማስፋፋት ያለፈ ለምን ሁለንተናዊ ተሐድሶን አላመጣም? በስደት ላይ የምትገኝ የቻይና ቤተ ክርስቲያን ከመቶ ሺ የሚበልጡ የወንጌል ሚስዮናውያንን ወደ ዓለም ሁሉ ለመላክ ከተዘጋጀች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከኢትጵያውያን ባሕልና ቋንቋ ያለፈ ዓለምን በወንጌል ለመድረስ የተጨበጠና ዓለም ያወቀው ራእይዋ ምን ይሆን? በዚህ አንጻራዊ ሰላምና ነፃነት ላልተጠቀመችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መከራ ያልበገራት የቻይና ቤተ ክርስቲያን ምን ታስተምራት ይሆን? በአጠቃላይ ቀደምት የዓለማችን የክርስትና ማዕከል የነበሩ ኢየሩሳሌም፣ አንጾኪያ፣ እስክንድርያ-

[141] *FRONTLINE World,Jesus in China, Interview, http: www.pbs.org frontlineworld*

[142] *Beyond Economy China's Transformation with the Cross Dr.Peter Zhao Xiao _ TimSchraeder.com.htm*

ግብፅ፣ ራሺያ፣ ግሪክና ኢትዮጵያ የጥንት ትውፊትና ያለፈውን ክርስትና ታሪክ የሚናጠናባቸው እንደ ሙዚዬም ከመታየት ያለፈ፣ የአሁኗን ዓለም በወንጌል መድረስና ሁለንተናዊ ለውጥን በአገራቸው እንደ ኮሪያና እንደ ቻይና ቤተ ክርስቲያን ለመምራት ፋና ወጊ መሆን እንዳልቻሉ ጥናቶች ያመለክታሉ። ያለፈ መልካም ታሪክ እስረኞች የሆኑም ይመስላሉ።

ኩርሴ ሽፈኖ ከኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል አንዱ ሲሆኑ "ባተሐድሶ የሚዘረጋ ትውልድ" በሚል ርዕስ ባዘጋጁት መጽሐፍ የታሪክ እስረኝነት አደጋ እንዳለው ሲገልጹ፦

ታሪክ በአግባቡ በተጠበቀ ሚዛን ካልተያዘ በስተቀር አዲስ የተሐድሶ ራእይን እንዳናይ ይጋርዳል። ታሪክን ብቻ ስናጠና ወደ ኋላ ማተኮር ብቻ እንጂ በአዲስ ራእይና አቋም ወደፊት መዘርጋት ያቅተናል። ምንጊዜም ዕድገት ሀብትና ዕውቀት ካልተጠነቀቅበት ያስመካል እኔ ነኝ ያሰኛል። የዓለማ መዘናጋትን ያስከትላል። እንዲያውም እግዚአብሔር ለትውልዱ ሊገልጽ የሚወደውን አዳዲስ የተሐድሶ ምንጮችን ባለማስተዋል መድፈን ይከተላል። እኛ የማናውቀው ምን አዲስ ነገር አለ? ያሰኛል። እግዚአብሔር ሁልጊዜ የአዲስ ሥራና የተሐድሶ አምላክ መሆኑን ፈጽሞ መዘንጋት አይገባም። እግዚአብሔር ትናንትና፣ ዛሬም፣ ነገም አዲስ ሥራ የሚሠራ ዘላለማዊ አምላክ መሆኑን ሁልጊዜ ማስታወስ ይኖርብናል። ስለዚህም አመለካከታችን ሚዛናዊ እንዲሆን 20% ያህሉን የቀደመውን ታሪክ እናስብ፣ 50% ያህሉን የዛሬን እንሥራበት፣ 30% ያህሉን ደግሞ ለወደፊቱ ለአዲስና ቀጣይ የተሐድሶ ራእይ ብናቅድና ብንጸልይ ጥሩ ነው።[143]

በማለት ቤተ ክርስቲያን የትናንት ታሪካዊ እሴቶቿን በመጠበቅ ዛሬ በብርቱ ሥራ ላይ በመጠመድ መጪውን በሚበልጠው ራእይና በተሐድሶ መንፈስ ማየት እንዳለባት ይመክራሉ። በአፍሪካ ደረጃ እንኳ ስንመለከት በ21ኛ ክፍለ ዘመን በአፍሪካ እያበቡ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ከቆዩት የግብፅ ኮፕትክ ቤተ ክርስቲያን፣ በኢትጵያና በኤርትራ የራሳቸውን ባሕላዊ መንገድ ከሚከተሉ አብያተ ክርስቲያናት ለየት እንደሚሉ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይገልጻሉ። ልዩ መሆን ክፋት ባይኖረውም በልዩነታችን በሌሎች ላይ አውንታዊ ተጽዕኖ የማንፈጥር፣ ወንጌልን ለዓለም በማድረስ ረገድ ፋና ወጊ መሆን ካልቻልን፣ የወንጌል ሚሲዮናውያንን ከራሳችን ቋንቋና ባሕል አልፈን ለዓለም ካልላክን፣ በስም ሳይሆን በሕይወት ለውጥ ላይ ትኩረት የማናደርግ ከሆነ፣ ከነገው ትልቅ ራእይ ይልቅ በዱሮ ታሪክና ስኬት ያለቅጥ የምንደገፍ ከሆነ፣ ራሳችንን ለመመዘን የማንፈቅድና እኛ ብቻ ዛሬም አንደኛና ትክክለኞች ነን ብለን እየፎከርን ሌላውን "መናፍቅ" "ዐረ ማርያም" ብለን እንደ ዱሮ የምናሳድድ ከሆንንና ያለፈውን ብቻ እያወራን ዛሬ ወንጌልን ካልሰበክን *"ክርስትናችን"* ዒላማውን እንደሳተ ቀስት ነው። በዚህ ከቀጠልን ከሁሉም ይልቅ ሊታዘንልን ይገባል። ተሐድሶ! ተሐድሶ! ተሐድሶ!....የሚል ጩኸት ከዘጠኝ ምዕተ ዓመት በላይ በምድራችን የሚሰማው ከዚህ የተነሣ ነው።

[143] *ኩርሴ ሽፈኖ (2003 ዓ.ም) ፣ ባተሐድሶ የሚዘረጋ ትውልድ፣ ገጽ 41*

የተወሰዱትን አናሲሞስ ነስቢ(አባ ጋማቺስ) ከባሪያ መሸጫ ገበያ ገዝተው አስተምረው መጽሐፍ ቅዱስን በአፋን ኦሮሞ እንዲተረጉሙ ያደረጉት የስዊድን የወንጌል መልዕክተኞች ነበሩ። ሌሎችን ነፃ ለማውጣት ራሳቸውን ለባርነት የሸጡ ክርስቲያኖች እንደነበሩ ታሪክ ያወሳል።

- ጥንት በሮማውያንና በግሪካውያን ባሕል አዋቂን መግደል ወንጀል ሲሆን የራስን ሕፃን መግደል አያስጠይቅም ነበር። ይህን አደገኛ የሞት ባሕል የገታው ወንጌል ነው።

- እጅግ ኋላ ቀር በሆኑ የዓላማችን አካባቢዎች ሰው የሰውን ሥጋ የመብላትን *"cannibalism"* ባሕል ራሳቸውን አላልፈው ሰጥተው በማስተማር የለወጡት የወንጌል ሚስዮናውያን ናቸው።

- ቻይናውያን *"የማይታወቅ ሰው እንባ ውሃ ነው"* እንደሚሉ ሳይሆን በታሪክና በዓይናችንም ደጋግመን እንዳየን ምዕራባውያን አማኞች የማያውቁት ሰው ሲራብ፣ ሲታረዝና ሲቸገር እጃቸውን ለመዘርጋት ፈጣኖች ናቸው። ይህ ባሕል ከሮማውያንና ከግሪካውያን የወረሱት ሳይሆን ከክርስቶስ ወርሰው ባሕላቸው ያደረጉት ነው። ይህም ወንጌል ሕይወታቸውን እንደ ሠራ እንመለከታለን። ወንጌልን ከእነርሱ በፊት የተቀበልን ቢሆንም እነርሱን ረጂ ያደረገው ወንጌል እኛን ከተረጂነት ለምን አላወጣንም? የሚል ጥያቄ አለብን።

- የዓለም የትምህርት መሠረት የፕሮቴስታንት ተሐድሶ እንደሆነ በብዙዎች ይታመናል። በአፍሪካ፣ በቻይና፣ በኤስያ፣ በላቲን አሜሪካ በገዛ ቋንቋቸው ዜጎችን ማስተማር የጀመሩ የወንጌል ሚሲዮናውያን ናቸው። ዛሬ የዓለማችን ገናና የትምህርት ተቋማት ለምሳሌ ሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ[145] ዬል ዩኒቨርሲቲ፣ የኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ ...ወዘተ እና የአሜሪካ የመጀመሪያ 126 ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች የተመሠረቱት በቤተ ክርስቲያንና በወንጌል ሰባኪዎች ራእይ እንደነበር ይነገራል። በዓለማችን በረኸቦም ዕድሜው፣ ለሰው ልጆች ነፃነት ትልቅ ቦታ በመስጠት፣ ለብዙ አገሮች በምሳሌነት የሚጠቀሰውን የአሜሪካን ሕገ መንግሥት ካረቀቁ ከ55 አባቶች 52ቱ የወንጌል አማኝ ክርስቲያኖች እንደሆኑና በቃሉ መርህ ላይ ቆመው መሠረቷን እንዳነጹ የታሪክ መዛግብት ያወሳሉ። የመጀመሪያ የአሜሪካ ሕግ በወንጌል አማኝ አባቶች ከረቀቀ በኋላ የፀደቀው በ3,000,000 ፕሮቴስታንት፣ በ300,000 ካቶሊክ እና በ5,000 የአይሁድ እምነት ይከተሉ በነበሩ ዜጎች እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ፕሬዝዳንት ጆርጅ ዋሺንግተን ሕጉን በፊርማቸው ሲያፀድቁት "በጌታችን ዓመት በ1787" በማለት ነበር።[146]

[145] Harvard, for example, was founded on this statement: *Let every student be plainly instructed, and earnestly pressed to consider well, the maine end of his life and studies is, to know God and Jesus which is eternal life, John 17:3*

[146] Pat Robertson (1990),The New Millennium,p. 165

ክርስትና ለምዕራቡ ዓለም ዕድገት

የታሪክ ምሁር ፕሮፌሰር ጎንዘሊዝ በብዙኃን በተደነቁ በሁለት ክፍል በተከፈሉ የታሪክ መጻሕፍት ስለ ምዕራባውያን ዕድገት ምስጢር ሲናገሩ፡-

> *ክርስትና ለምዕራባውያን ስልጣኔ መሠረት ነው፤ ትምህርት፣ የሰብዓዊ መብት ነፃነት፣ ዲሞክራሲ፣ እኩልነትና የኢኮኖሚ ምጥቀት ሁሉም የተወለዱት ከክርስትና ማሕፀን ነው*[144] በማለት በጥናት የተረጋገጠውን እማኝነታቸውን ይፋ አድርገዋል።

የእኛ የተገላቢጦሽ ነው። በክርስትና ከዓለም ሕዝብ በኩር እንደሆንን አፋችንን ሞልተን ብንናገርም ዓለም የሚያውቀን በረሃብ፣ በድርቅ፣ በስደትና፣ በእርስ በርስ ጦርነትና በኋላ ቀሪነታችን ነው። ምዕራባውያንን የጠቀመው ክርስትና ለእኛ ለምን አልጠቀመንም? ለእነርሱ የተሰበከው ወንጌል ከእኛ የተለየ ይሆን? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ልባችንን አስፍተን በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ ቆመን ክርስትናችንን የግድ መፈተሽ አለብን። ከንቱ ውዳሴና ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምምዶች ባጠላበት ዕድሜ ጠገብ ክርስትናችን መኮፈሳችንን ከቀጠልን ከማጡ ወደ ድጡ እንደሚባለው ወደ ቁልቁል በፍጥነት መውረዳችን ይቀጥላል። የአገራችን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የማኅበራዊ ቀውሶችና ኋላ መቅረት የመንፈሳዊ ቀውስ ነፀብራቅ ነው። እውነተኛ ለውጥና ዕድገት በታላቂቷ አገራችን እንዲመጣ ከተፈለገ የመንፈሳዊ ነገር መሠረት ከሆነችው ከቤተ ክርስቲያን የግድ መጀመር አለበት። ለውጪ መሠረት ደግሞ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትውፊትና አገራዊ ድርሳናት ሳይሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቀና የተቸረው፣ የጠራና የጠለለው ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ሊሆን ይገባል። ለምዕራባውያን ፈርጀ ብዙ ዕድገትና ለውጥ ክርስትና ትልቅ ሚና እንደተጫወተ ምሁራኖቻቸው፣ ጸሐፊዎቻቸውና ሕያው ታሪካቸው ይመሰክራሉ። ለትምህርታችን አንዳንዱን ብቻ እንመልከት፡-"የምዕራባውያን ድል" በሚለው መጽሐፉ የታሪክ ምሁሩ ጆ.ኤም.ሮበርስ

> *ማኅበረሰባችን እያጣጣመ ላለው ብልጽግናና ጠንካራ ማኅበራዊ መሠረት ላለው ሥርዓት ምክንያቱ የክርስትና እምነት ነው። በሕጋችን፣ በኢኮኖሚያችን፣ በፖለቲካችን፣ በቀን ለቀጣጠራችን፣ በበዓላችን፣ በአስተሳሰባችን፣ በሞራላችንና በባሕላችን የክርስትና አንጸባራቂ አሻራ አለበት፣ ብሏል።*

- በዓለማችን የባርያ ፍንገላ እንዲያከትም ካደረጉት ታላላቅ የእምነት ሰዎች መካከል የእንግሊዝ ፓርላማ አባል፣ የክርስቶስ ተከታይና ደቀ መዝሙር እንደሆነ በገሃድ ይነገርለት የነበረው ዊሊያም ዊልበረትፎርስ ተጠቃሽ ነው። ለምሳሌ በአገራችን ባሪያዎችን ከገበያ እየገዙ ነፃ ያወጡ የነበሩ የወንጌል ሚስዮናውያን ነበሩ። ከኤሰባበር አካባቢ ተሸጠው ወደ ምጽዋ

[144] *In his two volumes of The Story of Christianity [Rev. and Updated. New York: HarperOne, 2010) Justo L. Gonzalez has extensively written about the role of Christianity in transforming the cultural, political, and socioeconomic life of Europe and North America.*

አሜሪካ የተመሠረተችው እግዚአብሔርን የማምለጫ ለሰታቸው አድርገው በሚያምኑ ሕዝቦች ነው።

የአሜሪካ 40ኛ ፕሬዝዳንት ሮናልድ ሬገን (1981 - 89)

ለአንድ ሀገርና ሕዝብ ከእግዚአብሔር ቃል በላይ ጠንካራ መሠረት ይኖር ይሆን? እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዕድገት ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ፖለቲካና ፖሊሲ አውጪዎች ሁሉ ያስፈልጋቸዋል። የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የበረከት መሠረት እግዚአብሔርና ሕዝቧ ናቸው።

ሳይንስ የተመሠረተው ሁሉን እግዚአብሔር ውብ አድርጎ እንደፈጠረ በሚያምንና በሚያስተምር ክርስትና እንጂ ሁሉን ቅዠት፣ ክፉና ዋጋ ቢስ አድርገው በሚያስቡ ሌሎች ሃይማኖቶችና አስተምህሮዎች ላይ ላይደለም። ጆን ኤፍ ኬኔዲ

- ክርስትና የዓለማችንም መዚቃ አሁን ለደረሰበት ደረጃ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ኢየሱስ ባይወለድ ኖሮ አሁን የምንሰማውን ድንቅ የመዚቃ ቅንብሮችና ጣዕመ ዜማዎችን መስማት አይታሰብም ነበር። ዓለምን ካነጋገሩና እያነጋገሩ ካሉ መዚቀኞች መካከል የቤተ ክርስቲያንን መድረክና ደጅ ያልረገጡትን ማግኘት አስቸጋሪ ሲሆን በዓለማችን የታወቁ ጸሐፊዎች እንደ ሼክስፒር፣ ዶስቶቭስኪይ፣ ዲክንስ፣ ሚልተን፣ ገጣሚ ለምን ሲሣይ... ወዘተ ያሉ መጽሐፍ ቅዱስ ተጽዕኖ ፈጥሮባቸው እንደ ነበር ከሥራቸው ማወቅ ይቻላል።

ቀጣዩ ምዕራፍ ትናንት ከተሐድሶ ማኅፀን የተወለዱ ፕሮቴስታንቶች ዛሬ እንዳረጁና በመንፈሳዊ ሞት መንፈስ እንደተወረሩ በማመልከት ግልጽ የተሐድሶ ጥሪ ያቀርባል።

፲፩

የተሐድሶ ጥሪ

ለኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያናት

ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ቦታ ሳትሆን የሚጸልይ ሰው፣ ቤተ ክርስቲያን የበድን ድንጋዮች ቁልል ሳትሆን ክርስቶስ በሞተላቸው ሰዎች የተገነባች የቅዱሳን ሕያው ጎብረት ናት። ቤተ ክርስቲያን ቦታ ሳትሆን በቦታ ላይ የሚኖሩ የክርስቶስ ልጆች አንድነት፣ ቤተ ክርስቲያን የሚሰገድላት ግሉዝ አካል ሳትሆን በእውነትና በመንፈስ ለእግዚአብሔር የሚሰግዱ ቅዱሳን አንድነት ነፀብራቅ ናት። ቤተ ክርስቲያን በድንጋይ፣ በስሚንቶ፣ በእንጨት፣ በብረት ሳይሆን በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተገነባች መለኮታዊ አካል ናት። ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ የዳነ ቅዱስ ሕዝብ እንጂ በሰዎች እጅ በድንጋይም፣ በጭቃ፣ በእንጨት፣ በሣርም ሆነ በብረት የተገነባች ሕንፃ አይደለችም።

ቤተ ክርስቲያን አንድ ናት!

ክርስቶስ አንድ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን ሦስትና ሁለት መሆን አትችልም። ቤተ ክርስቲያን አንድና "ካቶሊካዊት" *(ማለት የዛሬይቷን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ማለት ሳይሆን ዩኒቨርሳል ወይም ዓለም አቀፋዊነት ለማለት ነው)* ናት።